


Scanned with CamScanner

# አላቲኖስ

"ኢትዮጵያዊያንን ኢትዮጵያ ውስጥ መውለድ ሳይሆን፤ ኢትዮጵያን ኢትዮጵያውያን ውስጥ መውለድ ይኖርብናል!"

ቃልኪዳን ኃይሉ ገብሬ

አዲስ አበባ–ኢትዮጵያ

Scanned with CamScanner

©ቃልኪዳን ኃይሉ ገብሬ፡፡ልብ ወለድ፡፳፻፲፡ዓመተ፡ምሕረት፡፡አዲስ አበባ

የደራሲው፡መብት፡በሕግ፡የተጠበቀ፡ነው፡፡

የመጀመሪያ፡ዕትም፡መስከረም፡2010

ሁለተኛ ዕትም፡ኅዳር፡2010

ሦስተኛ ዕትም፡ መጋቢት፡ 2014

## የደራሲው ስራዎች

-የነጎድጓድ ልጆች (2006 ዓ.ም.)

-ለምን አትቆጣም እና ሌሎችም (ያ ትውልድ Vs ይህ ትውልድ) (2007 ዓ.ም.)

-ክብር (2013 ዓ.ም.)

## ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ

ዳና (ምዕራፍ አራት) (አምስት ክፍል)

ወላፈን (ከምዕራፍ ሦስት እስከ ፍጻሜው) (ሃምሳ አራት ክፍል)

## ለአስተያየትዎ

ኢ-ሜይል kaldanhailu@gmail.com

ስልክ 0947 15 41 95

Like us on facebook Kalkidan Hailu

## ሽፋን

መነሻ ሐሳብ-ንቁ መጽሔት

ዲዛይን-ፀጋልደት ተፈራ



Scanned with CamScanner

## ከሁሉ በፊት

### እንግሊዝ-1507 ዓ.ም.

የእንግሊዙ ንጉሥ የሄነሪ ስምንተኛ አማካሪ፣ የሕግ ባለሙያው፣ ደራሲና በአንድ ወቅት የካቶሊክ መነኩሴ የነበረው ቶማስ ሞር አዕምሮ ውስጥ ገላ ላይ እንዳረፈ ቅንጣት አሲድ ልብ-ልብ እያደረገው ነው። እንቅልፍ ቢወስደኝ ብሎ ለመተኛት ሞክሮ ነበር። ወዲህ ቢገለበጥ፣ ወዲያ ቢተኛ እንቅልፍ ከወዴት አባቱ? ከተኛበት ብድግ ብሎ ሊያልቅ የተቃረበውን መጽሐፉን አነሳ። ጥቁሩን ባለላባ ብዕሩን ቀለም ነከረና ምንም ሳይጽፍበት ቀድሞ የጻፈውን ማንበብ ጀመረ። አዲሱን መጽሐፉን ሊጨርሰው ነው። ምን እንዳስገደደው ባያውቅም የመጽሐፉን ርዕስ 'ዩቶጵያ' ለማለት ወስኗል።

እንደ ጎራዴ የተሳለውን፣ ደመ ቀዝቃዛና ጺም የለሽ ፊቱን፣ አሁንም አሁንም አሸት አሸት እያደረገ በአንዱ እጁ ቀለም ያዠ ብዕሩን ጋለል አድርጎ ይዞ የራሱን መጽሐፍ ያነባል። የመስቀል ወፍ መንቆር የመሰለው አፍንጫው ላይ ላብ ችፍ ችፍ ብሏል። ከብብቱ ሥር ላቡ እንደ ውኃ ሲንቆረቆር ይሰማዋል። እንደ ጎረምሳ የሚያፏጭ ብርድ ባለበት ውድቅት ሌሊት ካባውን ከላዩ ላይ አውርዶ አንገተ ረዥም ሸሚዙ ላይ ያሉትን ቁንጠኛ አዝራሮች ፈታትቶ ማንበቡን ቀጠለ።

ብዙ ጊዜ ቶማስ ሞር ለነገሮች ትኩረት ሲሰጥ እንቅልፍ እምቢ ይለዋል። የዛሬው የቶማስ ሞር የሀሳብ ምልሰት ከኢትዮጵያ ብሪታንያ፣ ከብሪታኒያ ኢትዮጵያ እያለ ልክ እንደ ጥጥ ማደወሪያ ከወዲያ ወዲህ በአዕምሮው ውስጥ ይሾራል፣ መወርወሪያ ውስጥ እንዳለ ድውር ግራ ቀኝ ይቅበዘበዛል።

የኢትዮጵያውያን አኗኗር ለቶማስ ሞር እጅግ አስደንቆታል። ቶማስ ሞርን ይበልጥ ያስገረመው መሪዎቻቸው ብዙዎቹ ሃይማኖተኛ መሆናቸው፣ እንዲያውም ከነገሥታቱ ጥቂት የማይባሉት መመንኮሳቸው። ኢትዮጵያውያን 'ምን እንበላ ይሆን፣ ምንስ እንጠጣ ይሆን' ብለው አይጨነቁም። ሁሌም የጋራ ሌማታቸው ሙሉ ነው። ከእንስራው እንደልባቸው ቢጠልቁት አይነጥፍም። ነገር ግን ጠንብን ብለው ወይም ጥማችንን ቆረጥን ብለው አልሰነፉም። ይልቁንስ ብርቱ ሰራተኞች ሆነው አገኛቸው እንጂ። ከአጠቃላይ ሕዝቡ ውስጥ ጥቂቶቹ ብቻ እያረሱ ሁሉም የሚጠግቡባት አገር፣ በግል ሳይሆን በጋራ የሚደሰቱባት ኢትዮጵያ አስቀንታዋለች። ለዚያም ነው በዓለም ላይ ያለውን መልካሙን ነገር ሁሉ 'ዮቶጵያ' ሲል የሰየመው። ለላቲን ቋንቋ አዲስ ቃል ሊያበረክት ነው። 'ዮቶጵያ'። ትርጉሙም 'መልካም ያማረ' ማለት ነው።

"ኢትኤል ጣና ደሴት ላይ ተቀምጦ የመሠረታት፣ ይቺ ሦስት መቶ ዓመት ከሮም ቀድማ ክርስትናን የተቀበለች፣ የሙሴ ሚስትን ያፈራች፣ ከአብርሃም በላይ ሊቀ

Scanned with CamScanner

ዮቶጵያ ያቺ አፍሪካ ውስጥ ያለችው ጥቁር አገር እንደሆነች ማንም እንዲያውቅ አልፈለገም። ቶማስ ሞር ከኢትዮጵያውያን ማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሐብታዊ እና ሃይማኖታዊ አስተሳሰባቸውን ወስዶ በእንግሊዝ ላይ መተግበር ብቻ ነው የሚፈልገው።

"መደረግ ያለበት ኢትዮጵያን አስረስቶና አጥፍቶ ዩቶጵያ መሰሏን እናት ብሪታኒያን በሕዝቡ ውስጥ ማስረፅ ነው።" አለ ቶማስ ሞር በህሊናው ዩቶጵያ መሰሏን እንግሊዝ በደስታ ተሞልቶ እየተመለከተ።

በትጋትና በጥንቃቄ ያቺ የመልካም ኑሮ ምሳሌ የሆነችውን የኢትዮጵያ መገለጫ የሆኑትን ቃላት ለይቶ አወጣ። ከዚያም በምትኩ ኢትዮጵያ ከሚገልጿት ቃል በተቃራኒ ማስገባት ጀመረ። በተለይ ደግሞ የኢትዮጵያውያን እምነት የሆነውን ተዋሕዶን በጣኦት አምልኮ ቀየረው። 'ሚትራስ' የተባለ የኢራን አምላክን የዩቶጵያውያን አምላክ እንደሆነ አስመስሎ መጽሐፉ ውስጥ ከተተው።

'ሚትራስ' የሮም ወታደሮች የሚያምኑት አምላክ ሲሆን አስተምህሮው ደግሞ ልክ (ግ)ኖስቲኮች ሁሉ 'ምድራዊ ነገሮች ሁሉ የተፈጠሩት በደጉ አምላክ ሳይሆን በክፉው አምላክ ነው' ብለው ነው። ይህ አስተሳሰብ ግን የኢትዮጵያውያንን እምነት የሆነውን የተዋሕዶን ሳይሆን በብዙ ካቶሊኮች ላይ ተፅእኖ ያሳደረው የአውግስጢኖስ 'የጥንተ አብሶ' አስተሳሰብን ይመሳሰላል።

ኢትዮጵያውያን አገራቸውን በጣም የሚወዱና በአገራቸው የሚኮሩ ቢሆንም ቶማስ ሞር በተቃራኒው 'አኮሪያኖች' የሚለውን የላቲን ቃል በመጠቀም 'አገር የሌላቸው ሕዝቦች' የሚል ትርጉም የሚሰጥ ቃል ሰጠው። ኢትዮጵያ የደጉ ንጉስ መቀመጫ ብሎ ቀድሞ አማራ ነው ቢልም አሁን ግን በተመሳሳይ ቃል 'አማውሮት' ብሎ አማራ የሚለውን ቃል ለወጠው። 'አማውሮት' ማለት በላቲን 'የጨለማው አህጉር' ማለት ነው።

ኢትዮጵያ በውኃ የተከበበች አገር መሆኗን እያወቀ ከእሱ ተቃራኒ የሆነ የላቲን ቃል ፈልጎ 'ውኃ አልባ' የሚል ትርጉም ያለውን 'አናይደርን' የሚለውን ቃል ተጠቀመ። እንዲህ እንዲህ እያለ የኢትዮጵያውያንን ሥነ ምግባር እና አመለካከት የማይወክለውን ቃል በተደጋጋሚ ማስገባት ጀመረ። 'አኔሞላውያን' እና 'ባርዜን' የሚለውን የግሪክ ቃል ሆን ብሎ አስገባው። 'አኔሞላውያን' ሲል 'በአየር የተነፋ ባዶ' ማለት ሲሆን 'ባርዜን' ደግሞ መሪዎችንም ተመሪዎችንም አንድ ላይ ጨፍልቆ ሲተች የተጠቀመበት ቃል ነው። ትርጉሙም 'የከብቶች መሪ' ማለት ነው።

እንደዚህ እያደረገ የድርሰቱን ረቂቅ ከቀያየረው በኋላ ለንጉሥ ሄነሪ ስምንተኛ ደብዳቤ መጻፈ ጀመረ። ረዥም ምስጋናና አክብሮት የመግቢያ ሐረግ ከተጠቀመ በኋላ ፍሬ ሃሳቡን እንዲህ ማስፈር ጀመረ።



Scanned with CamScanner

“ክቡርነትዎ! የዚህ ድርሰት ዋና ዓላማ ሁለት ነው፡፡ እሱም እንግሊዛውያንና ከነገሥታት እስከ ተራው ሕዝብ ቁጭት ውስጥ ከቶ ለተሻለ ኑሮ ማንቃትና ማነሳሳት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ዮቶጵያን በእንግሊዝ መመሥረት ነው፡፡ ብሪታንያ ለሕዝቦቿ ሳይሆን ለሌሎችም መመኪያና መከታ እንድትሆን፤ ሕዝቧ በደስታ በፍቅር እንዲኖሩ፤ ሕዝቡ ተዋዶና ተፋቅሮ እንዲኖር፤ በዓለም ላይ በልጣና ልቃ እንድትታይ ነው፡፡ ለዚህ አላማ መሳካት አንደኛዋና የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያ የምትባል አገር በዚህ አቋምና ልክ መቀጠል አይኖርባትም ምክንያቱም አንድ ደማቅ አገር በዓለም ላይ ካለ ሌላው ሊደምቅ አይችልም፡፡

“ክቡርነትዎ! ተዋህዶ ሃይማኖት ለኢትዮጵያውያን ለመልካም አኗኗራቸው ዋና ምክንያት ነው፡፡ ስለዚህም ከተዋሕዶ አስተሳሰባቸው ውስጥ ከቀኖና እና ዶግማ ውጪ መልካሙን ሁሉ ወስደን፤ ኢትዮጵያውያንን ካቶሊክ ልናደርጋቸውና በሮም ሥር ሊተዳደሩ ይገባል፡፡ ለዚህም ተፈጻሚነት እኔ እንዲሁም ሌሎች ፖርቹጋላውያን እና ስፔናውያን ወዳጆች ሆነን ማኅበር ልንመሰረት አስበናል፡፡ ዓላማውም ኢትዮጵያውያንን ካቶሊክ ማድረግ ሲሆን፤ በረዥም ጊዜው ግን የኢትዮጵያውያንን አኗኗር ለአውሮፓውያን አድርገን በተቃራኒው የእኛን የተመሰቃቀለ አኗኗር ለእነርሱ ማድረግ ነው፡፡

“የማኅበሩ ዓላማ ይህ ቢሆንም በግሌ ግን እንዲህ ይሰማኛል፡፡ ከእንግሊዝ ሕልውና በላይ የኢትዮጵያውያን ሕልውና ስለማይበልጥብን፤ ከኢትጵያውያን ውስጥ የተዋሕዶን አስተሳሰብ ልናጠፋው ግድ ነው፡፡ ክቡርነትዎ! ደፈርከኝ አይበሉኝና የእንግሊዝ ሕዝብ በጣም እየተማረረ ነው፡፡ ይህ ምሬቱ በተለይ ለሱፍ ምርት ተብሎ የምናረባቸው የበጎች ጉዳይ ነው፡፡ በእርስዎ በክቡርነትዎ አገር ከሰው በላይ በግ እየበለጠ ነው፡፡ ስለዚህ ሌላ አማራጭ ያስፈልገናል፡፡ ከላይ በዮቶጵያ ልብ ወለድ ላይ እንደገለጽኩት፤ ኢትዮጵያውያን ሕዝባቸውን ሳይጎዱ የሚፈልጉትን ነገር በሰው አገርና መሬት ላይ እንደሚያደርጉት ሁሉ እኛም የበግ ምርታችንንም ሆነ ሌሎች የሚያስፈልጉንን ነገሮች በሌሎች አገር ላይ በሌሎች ጉልበት ማስፈጸም እንችላለን፡፡



Scanned with CamScanner

# ቅድመ ታሪክ

## አሜሪካ-ኒውዮርክ

## 1960 ዓ.ም.

ከጠቆረው ሰማይ ስር ችፍ ችፍ የሚለው ካፊያ፤ ካፊያውን ከወዲያ ወዲህ እያለ የሚበትነው ንፋስ ተደማምሮ ብርዱ እንኳን ከቤት ወጥቶ ስብሰባ ለማድረግ አይደለም ለመተኛት እንኳ ሞቅ ሞቅ ያለ ብርድ ልብስ መደራረብ ይጠይቃል። ነጎድጓድ እና መብረቁ ግራ ቀኝ እያለ ሰማዩን ያርሰዋል።

ቄስ ካርሎ ከቅዝቃዜው የተነሳ ትንባሆ እንደማገ ሰው በተነፈሰ ቁጥር ከአፉ አሁንም አሁንም ጭስ ይወጣል። እንደ በረዶ የቀዘቀዘውን መዳፉን ሙቀት ለመፍጠር እርስ በእርሱ እያፋተገ፤ አንዳንዴም ጥርሱን እያፋጨ ከዜሮ በታች ለሆነው የሙቀት መጠን ሳይበገር ስብሰባውን ለመካፈልና ለመምራት ጣደፍ ጣደፍ እያለ ወደ ስብሰባ አዳራሹ ደረሰ።

ይህ ስብሰባ ድብቅ ነው። ከጥቂት የአውሮፓ አገር ተወካዮችና ከአሜሪካ በስተቀር ሌላው የዓለም አገር ይህን ጉዳይ አያውቅም። ስብሰባውን ያመቻቹት ደግሞ የቫቲካኑ ሊቀ ጳጳስ ሲሆኑ የነገሮቹ ሁሉ ጠንሳሽ ግን ቀጭንና ረጅሙ፣ ድምጸ ቃጭሉ፣ ኮስታራውና ፊቱ ላይ አንድም ጺም የሌላው ጎልማሳው ቄስ ካርሎ ነው።

ቄስ ካርሎ አባቱን ያጣው በኢትዮጵያና በጣልያን ውጊያ ማይጨው ላይ ነበር። በዚህ ጦርነት አባቱ የሙሶሎኒ ቀንደኛ ደጋፊ ስለ ነበሩ ለሙሶሎኒ ኢትዮጵያን ሊያስገብሩ፤ ለእናት አገራቸው ጣልያን ደግሞ ተጨማሪ ርስት ሊመሰርቱ ከሮሙ ጳጳስ ቡራኬ ተቀብለው ከመጡ ሳተና የጣልያን ወታደሮች አንዱ ናቸው። ቢሆንም እንደታሰበው ሳይሆን የካርሎ አባት ልጃቸውን እና ሚስታቸውን ሮም ላይ በትነው ማይጨው ላይ ተሰዉ።

የካርሎ አባት የሚደግፉት ሙሶሎኒም ከበትረ ሥልጣኑ ተነስቶ ተገደለ። የካርሎ አባት ሞት የቤተሰቡን የገቢ ምንጭ አደረቀው። ሌማቱ ውስጥ የሚላስ የሚቀመስ ጠፋ። በቦሃ ላይ ቆረቆር ተጨመረበትና የካርሎ እናት በጠና ታመሙ። እንኳን ታመው እንዲሁም ቤታቸው በችጋር ተመትቶ ነበርና ለካርሎ እናት ለሕመማቸው መታከሚያ ጠፋ። የካርሎ እናት በሽታውና ርሃቡ ጠንተውባቸው በስቃይ ሞቱ።

ይህን የቤተሰቦቹን መከራና ስቃይ ያየው ካርሎ ዓለም በቃኝ ብሎ ሊመነኩስ ወሰነ። መነከሰና ገዳም ገባ። ቢመለኩስም በልጅነቱ ያሳለፈው መከራና ስቃይ ተደራርበው ለካርሎ የተለየ ባህርይ አላበሱት። ካርሎ ጥሞናን አብዝቶ የሚወድ፤ በኢትዮጵያ ላይ



Scanned with CamScanner

ልዩ ጥላቻ ያለው፤ ለአባቱም ሆነ ለእናቱ መሞት ኢትዮጲያን እንደ ዋነኛ ምክንያት ከሚቆጥር ኢትዮጲያና ኢትዮጲያውያን ላይ ክፉኛ አቄመ።

ካርሎ በሂደቱ ሁሉን እሺ እሺ ባይ፤ ዝምተኛ እና የተረጋጋ ሆነ። ስራው ቀጥሎ ብሎ መንፈሳዊ መጻሕፍትን ማንበብ ሆነ። በባህሪውም በመንፈሳዊ እውቀቱም ከፍ ከፍ ብሎ የፓትርያርኩ የቅርብ ረዳት መሆን ቻለ። ቅርበቱን ተጠቅሞ ለፓትርያርኩ ኢትዮጲያ ላይ ያለውን ጥላቻ በግልፅ ነገራቸው። ለጣልያን ብሎም በዓለም ላይ ላለ ነጭ ሁሉ የሃፍረት ማቅ ያከናነበችው ኢትዮጲያ ማፈር እንደሚገባት ፓትርያርኩን አሳመነ።

ካርሎ ሀሳቡን ሲያቀርብ "ኢትዮጲያ ያሸነፈችው ጣልያንን አይደለም፤ ያሸነፈችው መላ አውሮፓዊነትንና ነጭ ቀለም ያለን ሁላችንን ነው። ይህ ሽንፈት አሜን ብለን መቀበል የለብንም። ኢትዮጲያውያን ለአድዋ ጦርነት ማሸነፋቸው ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ አስተዋፅኦ አላት። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያኗን አንድ ነገር ልናደርግ ይገባል።"

ይህ ንግግሩ የካቶሊኩ ፓትርያርክ አዕምሮ ውስጥ ቀስ ቀስ እያለ ትልቅ ቦታ አገኘ። ስለዚህም የካርሎን ሀሳብ የራሳቸው እያስመሰሉ ለሚያገኟቸው የአውሮፓ መሪዎች በጥሞና ማስረዳታቸውን ቀጠሉ። ለዚህ ነበር ፓትርያርኩ የአውሮፓ መሪዎችን አስጋብዘው መደበኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስብሰባ ከመደረጉ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ከአሥራ አንድ የአውሮፓ አገራት የመጡ ተወካዮች ጋር የካቶሊኩን ካርሎን ጨምሮ ስብሰባ እንዲቀመጡ በድብቅ ያስወሰኑት።

------//------

ካርሎ ለተሰብሳቢዎቹ ሀሳቡን ባጭር ባጭሩ እየገለጸ ነው። የመጨረሻውን ነጥብ እንዲህ በማለት በስሜት ተውጦ ነው ያስቀመጠው።

"ኢትዮጲያ በቅኝ ላለመገዛቷ ዋናዋ እንቅፋት ቤተ ክርስቲያኗ ናት። የኦርቶዶክስ እምነት የመንግሥት ሃይማኖት ስለሆነች ቤተ ክርስቲያኗ በፖለቲካው ላይ ትልቅ ተፅእኖ ማሳረፍ ችላለች።

"ከቫቲካን ጥናትና ምርምር ክፍል እንዳገኘሁት ምሥራቃውያን በአጠቃላይ እኛ ምዕራባውያንን ካቶሊክም ሆነ ፕሮቴስታንቶችን እንደ እውነተኛ አማኝ አያዩንም፤ ለእኛ እምነት ምንም ቦታ አይሰጡንም። ከዚያ ይልቅ የእኛ አባቶች ለፖለቲካና ለሥልጣን ብለው እምነታቸውን የሸጡ እንደሆኑ አድርገው ነው የሚቆጥሯቸው። እኛንም አዲሱን ትውልድ ከሃዲ የከሃዲ ልጅ አድርገው ነው የሚያዩን። መሰሪውያን ነው የሚሉን።



Scanned with CamScanner

"የኢትዮጵያም ኦርቶዶክስ ተዋህዶም እኛን እንደ እህት ቤተክርስቲያን ሳይሆን እንደ ባላንጣ ነው የምታየን። ከምንም በላይ ደግሞ አፍሪካዊ አገር ስለሆነች እንዲሁም በየትኛውም ጊዜ ማንም የአውሮፓ አገር ቀኝ ገዝቷት ስለማያውቅ ለእኛ ለምዕራባውያን ምንም ዓይነት በጎ የሆነ ሥነ ልቦናዊ አመለካከት የላቸውም። ይህ አመለካከታቸውን ለመላው አፍሪካ እንደሚያጋቡ ደግሞ ሳይታለም የተፈታ ነው።

"በተለይ ከአንዱም ሁለቱ ተሞክረው ቅኝ መገዛትን እንዲጠየፉ ያደረጋቸው ቀድመው ምንም ዓይነት የምዕራባውያን እውቀትና አመለካከት ስለሌላቸው ነው። ከምንም በላይ እኛን ከመጤፍ ስለማይቆጥሩንና ቤተ ክርስቲያናቸው ደግሞ መላው አውሮፓን እንደ ከሀዲ ስለምታይ ነው።"

ይህ የካርሎ ሃሳብ በይበልጥ የሳበው የእንግሊዙን ተወካይ ነው። እንግሊዝ ኢትዮጵያን ከጣልያ አስጥላ እሷ ቅኝ ለመግዛት ጥረት ብታደርግም ኢትዮጵያውያን ለቅኝ ግዛት የሚሆኑ አልነበሩም። ይበልጥ ተቃውሞና ተግዳሮቱ የሚበረታው የቤተ ክርስቲያኗን ትምህርትና ዘመናዊ እውቀት የቀሰሙ ሰዎች ሆነው ተገኝተዋል።

ከዚህም ከፍ ባለ ሁኔታ ቶማስ ሞር ለንጉሥ ሄነሪ ስምንተኛ የጻፈውን ደብዳቤ ያነበበውን እንግሊዛዊው ከፍተኛ ባለሥልጣን ያስደሰተ ሀሳብ ነው የተነሳው። ነገር ግን ቅኝቱ በቫቲካን ሳይሆን በእንግሊካን እንዲሆን ይፈልጋል።

ስለዚህ የመጀመሪያውን ንግግር ያደረገው ሙሉ ጥቁር ሱፍ በነጭ ሸሚዝና በሰማያዊ ከረቫት ያደረገው ጂማሙ የእንግሊዙ ተወካይ ነበር። ይህ ሰው የእንግሊዝን ፖለቲካ የመዳፉ ያህል ያውቀዋል የሚባል ነው "የተነሳው ሀሳብ መልካም ነው። በአሁኑ ሰዓት ብዙ የአፍሪካ አገሮች ነጻነታቸውን ተቀዳጅተዋል። ስለዚህም ብዙ ነገሮቻቸውን ከኢትዮጵያ መገልበጥ ይፈልጋሉ። የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነታቸውን ሳይቀር። ምክንያቱም ለሌሎች የአፍሪካ አገሮች ለነጻነታቸው ጥያቄ ዋነኛ መነሻ የሆነቻቸው ይህች አገር ነች። ለነጻነታቸውም የተዋሕዶ ሃይማኖታቸው ትልቅ ድርሻ አለው።" ጂሙን እንደ መዳበስ እያደረገ ለሰከንዶች ጸጥ አለና ንግግሩን እንደ አዲስ ኮስተር ባለ የድምጽ ቃና ጀመረ።

"በተለይ ከአድዋ በኋላ አፍሪካውያን በአጠቃላይ 'ለካ ነጭ ይሸነፋል!' የሚል አስተሳሰብ አድሮባቸዋል። ሌላው ደግሞ ካቶሊክም ሆነ ፕሮቴስታንት የቅኝ ገዢዎቻችን እምነት ነው ብለው ያምናሉ። ስለዚህ የነጻይቱን አገር የኢትዮጵያን ሃይማኖት እና አስተሳሰብ ለመቀበል ፍላጎት አላቸው።

"ኢትዮጵያውያን 'በጦርነት ያሸነፍነው እግዚአብሔር ፈቅዶ ነው' ይላሉ። በዚያ ላይ ቀሳውስቱ ሕዝቡን ለባዕድ እንዳይገዛ እየገዘቱ፤ ለጦርነት ሲወጡም ታቦት ተሸክመው ነበር። ይህ ደግሞ ሕዝቡ ውስጥ አንድም ታቦቱን ላለማስደፈር አንድም ታቦቱ ላይ



Scanned with CamScanner

የእግዚአብሔር መንፈስ አድሮ ይረዳናል በሚል አስተሳሰብና ወኔ ሽንፈትን እንደ ጣልያን ሳይሆን እንደ አውሮፓ እንድንጎነጭ አድርገውናል።

"በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ በአፍሪካ ተሰሚነቷ ከመቼውም ጊዜ በላይ ጨምሯል። ስለዚህ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነትን ከግብፅ ይልቅ ኢትዮጵያ ለሌሎች የአፍሪካ አገራት ልታስተዋውቀው እንደምትችል ተገንዝበናል። ስለዚህም ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የኦርቶዶክስን እምነት እና ኢትዮጵያዊ ብሔርተኛ ስሜታቸውን ለማክሰም መሥራት እንዳለብን ቃልኪዳን ልንገባ ግድ ነው።"

የእንግሊዙ ተወካይ ንግግሩን እንደ ጨረሰ የዓይን መነጽር ያደረገውና የሚያምር ቡናማ ቀለም ያለውንና ሞቃታማውን ካፖርት የደረበው ፈረንሳዊ ንግግሩን ጀመረ "በአሁን ሰዓት በቅርቡ ነጻ ለወጡት የአፍሪካ አገራት አዲስ መንገድ ቀይሰንላቸዋል። በተለይም ደግሞ ከእምነት አንጻር መንግሥት እና ሃይማኖት ሊለያዩ ይገባል የሚል የ'ሰክዩላሪዝም' ጽንሰ ሀሳብ ልንዘረጋ ነው። ይህም በቅድሚያ በአዲሶቹ የአፍሪካ አገራት ላይ ልንሞክረው ነው ያሰብነው። ስለዚህ ብዙዎቹ ይህን ሀሳብ እንደሚቀበሉት እርግጠኞች ነን።

"ይህ የ'ሰክላዩሪዝም' ጽንሰ ሀሳብ በደንብ አፍሪካ ላይ ከተተገበረ አፍሪካን ነገም ቢሆን እንደልባችን ለመዘወር አያቅተንም። ምክንያቱም አፍሪካውያን ብዙም ትምህርት ስላልቀሰሙ በዚያ ላይ ከሃይማኖት ርቀው አገራቸውን ለመምራት ስለማይችሉ የእኛን እርዳታ ይፈልጋሉ። በዚያ ላይ ሃይማኖታቸውን በገዛ እጃቸው እንዲያጠፉ ሃይማኖት እና ፖለቲካ የተለያዩ ናቸው ብለን ካስተማርናቸው ራሳቸው ቀደምት ሃይማኖቶቻቸውን ይፈልጋሉ። ካልሆነም እንዳላችሁት እምነታቸውን ከኢትዮጵያ +ከወሰዱ አደጋ ይኖረዋል።"

ፈረንሳዊው ንግግሩን እንደጨረሰ የተረዳው የስዊድኑ ተወካይ ቀበል አድርጎ "ቢሆንም አፍሪካውያን አንድነታቸውን የመሠረቱት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ብዙ የአፍሪካ ሀገር መሪዎች ለኢትዮጵያው ንጉሥ አክብሮት አላቸው። ስለዚህም ብዙ ነገራቸውን በቀላሉ ከኢትዮጵያ ሊቀበሉ ይችላሉ።

"እንኳን አፍሪካውያን ጃማይካውያን ሳይቀሩ ንጉሡን ያመልኳቸዋል። ሌሎች አፍሪካውያንም 'ኢትዮጵያኒዝም' የሚል የነጻነት መንፈስ ማስተጋባት ጀምረዋል። ኢትዮጵያውያን ምን እንደሚያመልኩ በቅጡ እንኳ ሳያውቁ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ኢትዮጵያንና እምነቷን እየተቀበሉ ነው።

"ይህ ለእኛ ትልቅ አደጋ ነው። አንድ አፍሪካዊ መሪ በግድ ሳይሆን ተወደና ተለምኖ የራሱ ባልሆኑ ሰዎች እስከመመለክ ሲደርስ አስደንጋጭ ነው። ለሌሎች አፍሪካውያንም ትልቅ መነቃቃትን ይፈጥራል። በዚያ ላይ እንደ ዱሮው



Scanned with CamScanner

ፓትርያርክም ሆነ ጳጳስ ከግብፅ አይቀበሉም። አሁን የራሳቸው ሲኖዶስ አቋቁመዋል። ይህ ትልቅ አደጋ ነው።"

በዚህ ጉዳይ ላይ በቂ እውቀት ያለው ስፔናዊው ረዥሙና መልከ መልካሙ ወጣት ንግግሩን ቀጠለ "ጀማይካውያን ሥር መሠረታቸው ኢትዮጵያውያን ናቸው።" ንግግሩን ፈገግታና ሳቅ ሞላው። በጣም እንዲህ እንዲገረም ያደረገው። የጀማይካውያን በደመ ነፍስ ወገኖቻቸውን ማወቅና የመፈለጋቸው ነገር አስገርሞታል።

"ጀማይካውያን ከኢትዮጵያ በመርከብ ተጭነው ደቡብ አሜሪካ እንዲያርሩ ያደረግነው እኛ ነበርን። ለዚህ ነው ጀማይካውያን ሳያውቁት ኢትዮጵያውያን ጋር ያለው የደም ትስስራቸው እንዲህ የሚስባቸው" አለ ስፔናዊው በንባብ የሚያውቀውን ቀደምት አባቶቹ የጻፉትን ታሪክ እንደ ማስታወስ ብሉ።

የኔዘርላንዱ ተወካይ የሀገሩ ምሁራን ስለ ኢትዮጵያውያን የነገሩትን ሀሳብ መጨመር ስለፈለገ እጁን አነሳና እድሉ ሲሰጠው መናገር ጀመረ። "ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ሃይማኖቶች በጦርነት አልተስፋፉም ይሁዲነት በሠላማዊ መንገድ ነው የገባው። ክርስትናም ሆነ እስልምና ያለምንም ጦርነት ነው ወደ ኢትዮጵያ የገባው።

"የሚገርማችሁ ኢትዮጵያውያን አገራቸው የሚገባውን ነገር ሁሉ ኢትዮጵያዊ የማድረግ አባዜ ይሁን ብቃት አላቸው። መጀመሪያ የንጉስ ሰሎሞን ምኒሊክ ቀዳማዊ አይሁድንና አይሁዳውያንን ይዞ ሄዶ በሠላም አይሁድነትን ብቻ ሳይሆን የሰለሞንን ሥርወ መንግሥት መሠረተ። የመጀመሪያዎቹ ሙስሊሞች የነብዩ መሐመድን ልጅ ጨምሮ ኢትዮጵያ ሄደው የተመሰረተው እስልምና ሃይማኖት ኢትዮጵያዊ ሆኖ አረፈው። አሁን ሙስሊሞች ከኦርቶዶክሶች ጋር በሰላምና በፍቅር ነው የሚኖሩት። ይህ የሚያናድድና የሚገርም ነው።"

ወፍራሙና ቦርጫሙ የጀርመኑ ተወካይ ለመስማት በሚያስቸግር እንግሊዝኛ ማውራት ጀመረ። እንደው ስለስብሰባው አስፈላጊነት ስላመነበት ነው እንጂ እንግሊዘኛ ማውራቱን ውስጡ አልፈቀደመውም "ኦርቶዶክስ እምነት ውስጥ መንፈሳዊ ጉዳይ ብቻ አይደለም ያለው። ብዙ ለዓለም የሚጠቅሙ እውቀት ያላቸው መጻሕፍት አላቸው። የእኛ ሊቃውንት እንደገለፁልን ከሆነ ስለ ሥነ ሕይወት፣ ስለሕክምና ፣ ስለ ዘመን አቆጣጠር፣ ስለ ሥነ ከዋክብት፣ ስለ ፕላኔት… ብዙ ብዙ ዓለማዊ እውቀት የያዙ መጽሐፍት አሏቸው።"

ፈረንሳዊው ልዑክ አንድ በማትረባ አፍሪካዊት መሪ እንዲህ ተጨንቀው ማሰቡ በራሱ ንዴትና ቁጭት ውስጥ የከተተው ይመስላል። በቁጣና ንዴት ከአፉ የቁጣ ቃል አመለጠው "…እና ምን እናድርጋቸው ትላላችሁ?" አለ።



Scanned with CamScanner

ጀርመናዊው ሰውዬ ንግግር በማድረግ ላይ እያለ በስሜታዊው ፈረንሳዊ ሰውዬ ሳያስበው ስላቋረጠው መልሶ የጀርመንኛ ቅላጼ በተጫነው እንግሊዘኛ መናገር ጀመረ "ከእኛ ሊቃውንት እንደ መፍትሔ የተነገረኝ እነዚህ ሰዎች የራሳቸውን የባህል ትምህርት እንዳያዳብሩ አውሮፓ ቀመስ ትምህርት ልንሰጣቸው ይገባል።

"እውቀት ማለት አውሮፓዊ ትምህርት ብቻ እንደሆነ ማመን ይገባቸዋል። ሌላው እነሱ አለን የሚሉት በግዕዝ የተጻፉ መጽሐፍቶቻቸውን ተረት ተረት እንደሆነ በራሳቸው ሰዎች ማስወራት ይኖርብናል። ስለዚህም ለኢትዮጵያውያን የትምህርት እድል ልንሰጥ ይገባል። ከዚያም የራሳቸው ልጆች ከእኛ ዘንድ ተምረው ሲመለሱ የእኛን ነገር ብቻ ትልቅ እና እውነት እንደሆነ የሚያንቆለጳጵሱ መሆን ይኖርባቸዋል" አለና ጀርመናዊው ሰውዬ ወደ ተቀመጠበት ጀርባውን በኃይል ውርውር አድርጎ ሲደገፍ ቦርጩ እንደ በሬ ሻኛ ተርገፈገፈ።

ፖርቱጋላዊው መልከ መልካሙ ሰውዬ እስከ አሁን ሲያሻሽው የነበረውን ወርቃማ የአገጩን ጺም ጎተት ጎተት አደረገና ንግግሩን ጀመረ "በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት እኛም እንደ ጃፓን ልንሰለጥን ይገባል እያሉ ንጉሳቸውን እየወተወቱ ነው። በጃፓን መንገድ ከሄዱ ሊሳካላቸው ይችላል። ይህ ከሆነ የአውሮፓ ህልውና በአፍሪካ ላይ የመቀጠሉ ነገር አስተማማኝ ላይሆን ይችላል።

"አሁን የተነሳው የትምህርት ጉዳይ ጥሩ ነው። በትምህርቱ ውስጥ አውሮፓዊ ባህልና አውሮፓዊ ትምህርት ለኢትዮጵያውያን ወጣቶች ልንሰጣቸው ይገባል። ብዙዎች ከዚህ ቀደም አውሮፓና አሜሪካ መጥተው የተማሩ ኢትዮጵያውያን የቤተክርስቲያን ትምህርት የቀሰሙ ነበሩ። አሁን ግን በዚህ መንገድ የትምህርት እድሉን ልንሰጥ አይገባም። ቀጥታ ምንም አይነት የቤተ ክርስቲያኗን ባህላዊ ትምህርት ያልቀሰሙ ልጆችን በኤንባሲዎቻችን በኩል እየለየን ነው የትምህርት እድሉን መስጠት ያለብን።

"እነዚህ አውሮፓ የተማሩ ወጣቶች ወደ አገራቸው ሲመለሱ እውቀትና ሥልጣኔ ማለት እንደ አውሮፓ መሆኑን አምነው አገሬውን ሊያሳምኑ ይገባል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ኢትዮጵያ በራሷ እውቀትና መንገድ እንደ ጃፓን ሁሉ ጥሩ ምጣኔ ሐብት ላይ ከደረሰች የተቀሩት አፍሪካውያን ልክ እንደ ኢትዮጵያ ብለው መነሳታቸው አይቀርም።

የአሜሪካኑ ተወካይ ፈገግ ብሎ ንግግሩን ቀጠለ "መልካም! ...አሁን ያነሳችሁት ሀሳብ ጥሩ ጥሩ ነው። ባልሳሳት የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች በይበልጥ ከአገሪቱ የሰሜን ክፍል ይመስሉኛል። የአገሪቱንም ፖለቲካ የሚዘውሩትም እነዚሁ ሰዎች ናቸው። እኔ እንዳለኝ መረጃ ከደቡብ አካባቢ የኦርቶዶክስ እምነት ክፍተት አለ። ክፍተቱት እንደ ጥሩ አጋጣሚ አይተን ልንጠቀምበት ይገባል።



Scanned with CamScanner

"ሌላው ኢትዮጵያውያን በተለይ መንፈሳዊ ሰዎቻቸው ብዙም ስነጭ እድናቆትም ሆነ የተለየ አቋም የላቸውም። እንዲያውም ነጭ ጠልነት አለባቸው። ስለዚህም መጀመሪያ መስራት ያለብን በዚህ አመለካከታቸው ላይ ነው።"

ሽቅርቅሩ የእንግሊዝ ተወካይ ኮቱን እየቆለፈ ንግግሩን በድጋሚ ቀጠለ "በአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ቀደም የተሄደበት መንገድ አለ።"

እንግሊዛዊው የቶማስ ሞር እቅድ እውን የሚሆንበት ሰዓት እንደ ደረሰ እርግጠኛ ሆኗል። "የአንግሊካን ፕሮቴስታንት አስተሳሰብ በኢትዮጵያ ውስጥ ልዕልና ሲይዝ ነው ታላቋ ብሪታንያ በሙሉ ልቧ እርፍ የምትለው። ለዚህም ነው እነ ጀነራል ዊንጌት ኢትዮጵያ ድረስ ሄደው ጣልያንን አስወጥተው እንግሊዝ ውስጥ የዩቶጵያን አስተሳሰብ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ ኢትዮጵያዊነት መንፈስን አጥፍቶ የጎሳ አገር ለመመሥረት መደላድል ፈጥረው የወጡት። ስለዚህ የዛሬውን ውይይት ተልእኮ እና ዋና ሚና እንግሊዝ ልትወስድ ግድ ነው" እያለ በውስጡ ለስከንድ እሰብ አደረገ።

እንግሊዛዊው ተወካይ ስብሰባ ውስጥ መሆኑን ተረዳና ከግል ሀሳቡ ወጣ ብሎ ወሳኙንና አስፈላጊውን ንግግሩን ቀጠለ "ኢትዮጵያዊነት ብሔርተኝነት ማጥፋት ካለብን ሁለት ነገሮች ልናደርግ ይገባል። አንደኛው እንደ ሀገር ኢትዮጵያዊነትን በጎሰኝነት መተካት፣ እንደ ቤተክርስቲያን ተዋህዶን በተሐድሶ ልንተካ ግድ ነው።" ብዙዎቹ የስብሰባው ታዳሚዎች በመስማማት አንገታቸውን ነቀነቁ።

የስዊድኑ ተወካይ ቀበል አድርገው "በዚህ ጉዳይ እኛ ቀደም ብለን ብዙ ሔደንበታል። ስለዚህ ከእንግሊዙ አንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ጋር ተቀናጅተን ይህን ጉዳይ አጠናክረን መቀጠል አለብን።"

ካርሎ የሚንሸራሸረውን ሃሳብ ወድዶታል። ትንሽ ቅር ያለው ነገር ስዊድንና እንግሊዝ አጀንዳውን ከቫቲካን ወደ አንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ሊወስዱት መሆኑ ነው። በልቡ "ደህና ይሞክሩና ቀጣዩን እናየዋለን" ብሎ ዝም አለ።

አሜሪካዊው ተጨማሪ ሀሳብ መናገር ስለፈለገ ጉሮሮውን እንደመጠራረግ አድርጎ መናገር ጀመረ "ስለዚህ አካሄዳችን መሆን ያለበት እንዲህ ሊሆን ይገባል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስህተት እንደሆነች ለኅብረተሰቡ ማስተማር። የቤተ ክርስቲያኗ አስተምህሮ በተረት ተረት! በእንቶ ፈንቶ ላይ የተመሠረተ! ከእውነተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታ እንደራቀ ማሳየት። ኦርቶዶክሶች ታሪክ እና ትውፊታቸውን ከእምነት ጋር እየቀላቀሉ ስለሚያስተምሩ ከዚህ ታሪካቸው እና ትውፊታቸው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ በሚል አስተምህሮ ከማንነታቸው ልናፋታቸው ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስንም በእነሱ የቀድሞ ትርጉም ሳይሆን በእኛ አስተምህሮ ልንቃኘው ይገባል። ለዚህም ትልቅ እንቅፋት የሆነውን የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንም



Scanned with CamScanner

የሰሜኖች ታሪክና ባህል እንጂ መንፈሳዊ ጉዳይ እንዳልሆነ ለሌሎች ልናስረዳቸው ይገባል፡፡" አለና ወደ ወንበሩ ላይ ለጠጥ እንደ ማለት ብሎ ንግግሩን ቀጠለ፡፡

"ሌላው ቅድም ስለ እስልምና የተነሳው ጉዳይ እኔም ይገርመኛል፡፡ ኢትዮጵያውያን እስልምናን እንኳ ኢትዮጵያዊ አድርገውታል። ስለዚህ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች አረባዊ እንጂ ኢትዮጵያዊ እንዳይመስል ልናነቃቸው ይገባል። ይህን *ሥራ መሥራት* ያለብን ወጣቶቹና ታዳጊዎቹ ላይ እንጂ ያረጁ ሽማግሌዎች አይደለም። ስለዚህም ውጤቱ ለእኛ ሳይሆን በልጅ ልጆቻችን የሚታይ ነው፡፡" ሁሉም በጭብጨባ ድጋፋቸውን ገለጡ፡፡ ቂስ ካርሎ ግን ቅር አለው፡፡



Scanned with CamScanner

## አመክንዮ

## እንግሊዝ-ለንደን

## 1964 ዓ.ም.

የቴንደሉ የነገረ መለኮት ምሁር ዶክተር ጂም ፓከር ኢትዮጵያ ውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ለማደስ በጥረት ላይ የሚገኘው በአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ቅርንጫፍ የሆነው የሠራዊተ ክርስቶስ ማኅበር መሪ ዳዊት ስቶክስ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ መንፈሳዊ አገልግሎት በጥሩ ሁኔታ ሲሠጡ የቆዩት ቄስ ማንስል እንዲሁም በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ ልትበር የተዘጋጀችው ሚስዮናዊቷ እመቤት ሄዘል ኮሊንዝ ለስብሰባ ተቀምጠዋል።

ይህ ስብሰባ ከስውሩ ቡድን ሰብሳቢ ከሆነው ከቄስ ካርሎ እንዲሁም ከጸሐፊው ከእንግሊዙ ተወካይ በተሰጠ ምሥጢራዊና ጥብቅ ትእዛዝ የሚከናወን ነው። ዶክተር ጂም ፓከር ኢትዮጵያ ላይ እየተካሄደ ያለውን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ፍጹም አንግሊካን የማድረግ እንቅስቃሴ የሚሠማሩ ሰዎችን በጥሩ ሁኔታ የሚያስለጥን የነገረ መለኮት ምሁር ነው። ተጠሪነቱ የእንግሊዝ ፓርላማ አፈ ጉባኤ ሰብሳቢነት ለተቋቋመ ቡድን ነው። ምንም አይነት የተሐድሶ እንቅስቃሴ በገንዘብ፣ በእውቀትና የተለያዩ ቁሳዊ አቅርቦቶችን ከተለያዩ የአውሮፓ አገራት እንዲመጡ የሚያሳልጥና የሚያመቻች ነው። ዶክተር ጂም።

የዚህ ስብሰባ ዓላማ ባለፉት ዓመታት እየሄዱበት ያለውን የተሐድሶ እንቅስቃሴ ለመገምገምና የአካሄድ ለውጥ ለማድረግ ነው። ካስፈለገም ለውጡን አካሂዶ በፍጥነት ወደ ተሻለ እንቅስቃሴና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ሙሉ ለሙሉ ለማደስና በአንግሊካን ሥር ለማድረግ ነው።

ይህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን የማደስ ዓላማ ከዶክተር ጂም በስተቀር ሌሎች ከመንፈሳዊ ቅናትና የእምነታቸው ትክክለኛነት ለዓለም ለመስበክ ካላቸው ቅንነት የተነሳ የሚንቀሳቀሱት እንጂ ከጀርባ መላ አውሮፓ የተባበሩበትና ሌላ ዓላማ እንዳለው አያውቁም።

ስብሰባው "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን እንዴት እናድሳት?" በሚል አጀንዳ ላይ ነው። በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ ጉዞዋን ልታደርግ የተዘጋጀችው ሚስዮናዊዋ እመቤት ሄዘል ኮንሲል ከመሄዷ በፊት መጠነኛ ጥናት አዘጋጅታ ስለነበር ያንን ጥናት እያቀረበች ነው።

"ከአውሮፓ ብዙ መንፈሳውያን ሚሲዮናውያን መላክ የጀመሩት በአጼ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት ነበር። ዓላማውም ኢትዮጵያን የሮም ግዛት ማድረግና ከኦርቶዶክስ ወደ



Scanned with CamScanner

ካቶሊክ ሙሉ ለሙሉ በፍጥነት መቀየር ነበር። ለዚህም ፖርቱጋልና ስፔን ትልቅ ሥራ ለመሥራት ሞክረዋል። በዚህ ላይ በተለይ በአልፎንሱ ሜንዴዝ የተሰበከው አስተምህሮ እስከ አሁን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ላይ ትልቅ አሻራ መጣሉ እውነት ነው። በዚህ ሰዓት በኦርቶዶክስ ላይ ቀባል የማይባል ተጽእኖ አሳድሯል። እስከ አሁንም ጸጋ፣ ቅባት እና ተዋህዶ የሚል ክፍፍል አምጥቷል።" አለች ደርባባዋ እምቤት ሄዘል። እምቤት ሄዘል ስትናገር ፈጠን ፈጠን እያለች ቢሆንም የምትናገረው ግን በደንብ ይሰማል።

"ከ'ካቶሊክ ሚሽነሪ' በኋላ 'ቸርች ሚሽነሪ ሶሳይቲ' የተባለ የአንግሊካን ፕሮቴስታንት ሚሽነሪ በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘመን በ1837 ዓ.ም አይዘንበርግና ክራፕፍ የተባሉ ግለሰቦችን ወደ ኢትዮጵያ ላከ። እንደውም ክራፕፍ ኦርቶዶክስን 'የአቢሲኒያ እምነት' እያለ ነበር የሚጠራው። በተቃራኒው ከኢትዮጵያ ውስጥ ኦሮሚኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ያሉበትን አካባቢ ቋንቋቸውን በደንብ አጥንቶ በጥሩ ሁኔታ አካባቢውን በወንጌል ተቆጣጥሮት ነበር። ቢሆንም ለቸርች ሚሽነሪ ሶሳይቲ በግልጽ የመሥራት እና የመንቀሳቀስ ፈቃድ የሰጡት ዳግማዊ ምኒልክ ነበሩ።

"ዳግማዊ ምኒሊክ ፈቃድ የሰጡት ለስዊድን ወንጌላዊ ሚስዮን ድርጅት ነው። ይህ ድርጅት የአቅሙን ያህል ህብረተሰቡን በማስተማር እንዲሁም በምፅዋ መደበኛ ትምህርት ቤት ከፍቶ ነበር። በዚህ ትምህርት ቤትም ሁለት ተጽእኖ ፈጣሪ ሰዎችን አፍርቷል።"

እመቤት ሄዘል ቀና ብላ ወደ ዳንኤል እና ቄስ ማንሰል ውብ ባለ ሰማያዊ ቀለም ዓይኖቿን ከወዲያ ወዲህ ብለል ከብለል በማድረግ በጥሞና ማተረች። እንዳሰበችው ነው። ሁሉም በጥሞና እየተከታተሏት ነው። ግራጫ መልክ ያለውን ኮቷን ሳብ ሳብ እንደ ማድረግ ብላ ንግግሯን በድጋሚ ቀጠለች።

"አንደኛው የኦሮምኛ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚውን አናሲሞስ ነሲቡን ሲሆን ሌላኛው ጸሐፊውንና ምሁሩን አለቃ ታዬን አፍርቷል" ቀና ብላ በድጋሚ ታዳሚዎቿ በትህትና ገርመም አደረገች።

"ሌላ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለማደስ ጥሩ እንቅስቃሴ ያደረገው የኛው ድርጅት 'ባይብል ቸርች ሚሽነሪ ማኅበር' ነው። ይህ ማኅበር በኢትዮጵያ ትምህርት ቤት ከፍቶ ጥሩ ጥሩ ወንጌላውያንን አስልጥኖ 'ሠራዊተ ክርስቶስ ማኅበርን' ኢትዮጵያ ውስጥ መሥርቷል። ይህ ማኅበር በጣም ብዙ ሊቃውንትን እያሰባሰብን ሲሆን በዚህ በሠራዊተ ክርስቶስ የተገኘው ሊቅ አለቃ መሠረተ ስብሐት ለአብ ነው።

"አለቃ መሠረተ ስብሐት ለአብ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ተሐድሶን አጥብቆ የሚመኝ። 'ሰምዐ-ፅድቅ ብሔራዊ' የሚል የተሐድሶ መሠረታዊ ሀሳቦችን የያዘ መጽሐፍ የጻፈ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ነው። ይህ ሊቅ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን

አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን የመጀመሪያውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ናቸው፡፡

"ፓትርያርኩ የሰበኩት ክርስትናና አሁን ያለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ክርስትና ይለያያል የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ በተለይ 'ከአጼ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የተጨመሩት የማርያምና የመላእክት አማላጅነት ጉዳይ ኦርቶዶክስን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ አድርጓታል' ብሎ የሚያምን ሳተና የወንጌል አርበኛ ነው፡፡

"አለቃ መሠረት 'ማኅበረ በኩር' የተባለ መንፈሳዊ ድርጅት አላማውን ከሚደግፉ ወዳጆቹ ጋር ሆኖ በማቋቋም ላይ ነው..." አለችና እመቤት ሄዘል ወደ ዳዊት ስቶክስ ቀና ብላ እየተመለከተች እጇን በአክብሮት ወደ ዳዊት ጠቆም እያደረገች

"ለዚህ ምስክራችን ዳዊት ነው በቅርበትም ያውቀዋል..." ሄዘል ይህን ስትል ዳዊት በፈገግታ ራሱን ነቀነቀ፡፡

እመቤት ሄዘል ጉሮሮዋን እንደመጠራረግ ብላ ንግግሯን ቀጠለች "ሌላው 'ሀይማኖተ አበው' የተባለው የተማሪዎች ማኅበር ለእንቅስቃሴያችን ጥሩ ድጋፍ የሚሰጥና ንቁና ተሐድሶን አጥብቀው በሚፈልጉ ሊቃውንት የተሞላ ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ትምህርት ቤት ይዘን ወደ ተሐድሶ መንገድ መጓዝ አያቅተንም፡፡" ብላ ንግግሯን ከደመደመች በኋላ እመቤት ሄዘል 'ህምምምም...' ብላ ተነፈሰች መጨረሷን ለማሳወቅ ያህል፡፡

'የሠራዊተ ክርስቶስ' ማኅበር መሪ ዳዊት ስቶክስ ረጋና ቀስ ብሎ የሚናገር ዓይነት ሰው ነው፡፡ ዳዊት የሚናገረው የነገረ መለኮት ምሁሩን ዶክተር ጂም ፓከርን እየተመለከተ ነው፡፡ ፀጉሩ ለስላሳና አብረቅራቂ ሲሆን ጭንቅላቱን መሀል ላይ ከፍሎ በግራና ቀኝ አስተኝቶ አበጥሮታል፡፡ ፊቱ ላይ ተለቅ ያለ መነጽር ያደረገ ሲሆን፤ የፊት ጺሙን ተላጭቶ ከአፍንጫው ሥር ያለው ጺሙን ብቻ በስሱ ትቶታል፡፡ ሰፋፊ የፊት አጥንቶቹ ደልደልና ሰፋ ያለው ደረቱ፤ ጠንከርና ፈርጠም ያለው የእጅና የእግሩ ጡንቻ ከመንፈሳዊነቱ ይልቅ ስፖርተኛ ያስመስለዋል፡፡

"የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ለማደስ..." ዳዊት ረጋ ብሎ መናገር ጀመረ "...አሁን እየሄድን ያለውን መንገድ አጠናክሮና አደራጅቶ መቀጠል ነው፡፡ ወንጌል በአገሪቱ በምልአት አልተሰበከም፤ ህብረተሰቡ ፈጣሪን የሚያመልከው በውርስ በተቀበለው እምነት እንጂ ጌታን አውቆና አምኖ አይደለም፡፡ ቤተ ክርስቲያናቸውን ሳያውቋት በነሲብ ነው የሚወዷት" ዶክተር ጂምና ቁስ ማንስል አንገታቸውን በመስማማት እየነቀነቁ በጥሞና እያዳመጡ ነው፡፡

ዳዊት ስቶክስ ግራ እጁን ጨብጦ አድርጎ ወደ አፉ በማስጠጋት ጉሮሮውን "እህምም... እህምም" ብሎ አጸዳና ንግግሩን ቀጠለ "በተለይ ደግሞ ደቡብ ኢትዮጵያ



Scanned with CamScanner

ወይ ወንጌልም የለ፤ ወይ የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባሕላዊ ትምህርት የለ። የሚያሳዝኑ ሕዝቦች ናቸው።

"በአሁኑ ሰዓት ወንጌልን እንድንሰብክ ከንጉሡ ፈቃድ አግኝተን አዲስ አበባ ካለው ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቤተ ክርስቲያን ለማስተማር በዝግጅት ላይ ነን። እንዲሁም መነኮሳቶቻቸውን አስተዳደራዊም ሆነ መንፈሳዊ ትምህርቶች እንድንሰጥ ፈቃድ አግኝተናል። ይህ ደግሞ ለዓላማችን መሳካት መልካም አጋጣሚ ነው። ምክንያቱም እነዚህ መነኮሳት ነገ ፓትርያርክ እና የሲኖዶስ አባላት መሆናቸው አይቀሬ ነው።"

ልክ ዳዊት ንግግሩን እንደ ጨረሰ ቄስ ማንስል የመናገር እድሉን ለመውሰድ በፍጥነት እጃቸውን አወጡ። ቄስ ማንሰል ቀጭን ረዥም መልከ መልካም ሸንቃጣ ሰው ናቸው። እንደ ዳዊት ሁሉ ዓይናቸው ላይ ሰፊ መነፅር አድርገዋል። ዶክተር ጂም ዓይን ዓይኑን ለጥቂት ሰከንድ እየተ አደረጉትና አንገታቸውን በለሆሳስ ወደ ላይ ከፍ ሲያደርጉ ዶክተር ጂም ገባውና "እሺ ቄስ ማንስል ይቀጥሉ" አለ።

ቄስ ማንስል ለመናገር ወንበሩ ላይ ተደላደሉና መናገር "አሁን ዳዊት በተናገረው ላይ ትንሽ ማስተካካያ ብናደርግበት ብዬ ነው።" በእርግጥ ቄስ ማንስል ያሰቡት ማስተካከያ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ የዳዊትን ሀሳብ የሚሽር ነው። ነገር ግን ለትህትናው ብቻ ነው 'ትንሽ ማስተካከያ' ያሉት።

"እርግጥ ነው ንጉሡ ካህናትንም ሆነ መማር የፈቀዱትን ሁሉ እንድናስተምር መልካም ፈቃዳቸውን ሰጥተውናል፤ ቢሆንም ይህን መልካም ፈቃድ ዘወትር እናገኘዋለን ብዬ አላምንም። በመጀመሪያ የእኛን እንቅስቃሴና ትምህርት ያልወደዱት ብዙ የኦርቶዶክስ ሊቃውንት አሉ። ስለዚህ ይህ ፈቃድ ይሰንብት ይጠር የምናውቀው ነገር የለም።

"ሌላው ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየው ነገር አስጊ ነው። በቅርቡ ከባድ ፖለቲካዊ ቀውስ ሊቀሰቀስ ይችላል። ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ አለመረጋጋት ከተከሰተ የእኛ ተቀባይነትና መልካም ፈቃድ ጥላ ሊያጠላበት ይችላል።"

ዶክተር ጂም ፓከር በአድናቆትና በተመስጦ ቄስ ማንሰልን ተመለከተ። በውስጡ እንዲህ ብሎ ያብሰለስል ጀመር 'ምርጥ እንግሊዛዊ ማለት ጥሩውንም መጥፎውንም ነገር አስቀድሞ የሚያስብ ነው፤ እንግሊዛዊነት ነገን ብቻ ማሰብ አይደለም ቀጣይ ዓመታትን አስቀድሞ መገመትና ችግርን ከነመፍትሔው አቅራቢ መሆንም ጭምር እንጂ። ልክ እንደ ቶማስ ሞር!' እያለ ስለ እንግሊዛዊነቱና ስለ ቄስ ማንስል አስተሳሰብ በአድናቆት ለራሱ ደሰኮረ።



Scanned with CamScanner

“ስለዚህ…” አሉ ቄስ ማንስል፡፡ ዶክተር ጂም እንደጠበቀው ቀድሞ ችግርን መገመት ሳይሆን ቄስ ማንስል መልካም መፍትሄ እንደሚያመጣ ተሰማው፡፡ “ስለዚህ እንዲሁ ሕዝቡን ከማስተማር ይልቅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን ባህላዊ አስተምህሮ በደንብ ጠንቅቀው ያወቁና ብሩህ አእምሮ ያላቸውን ሕጻናትና ወጣቶች መልምለን የአስኳላ ትምህርታቸውን አስጨርሰን ከዚያም የነገረ መለኮት ኮሌጅ እንዲቀላቀሉ እናድርጋቸው፡፡ ያኔ እኛ ሳንሔድ በራሷ ልጆች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትታደሳለች፡፡ ወንጌል በምልአት ይሰበካል ‘ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ኢየሱስ ምስክር’ የሚለው ራዕይ ይፈጸማል፡፡”



Scanned with CamScanner

## ምዕራፍ ፩

## አዲስ አበባ-አራት ኪሎ

## ጥር-1964 ዓ.ም.

ሰናይ የአለቃ ምሕረቱ ልጅ ነው። አለቃ ምሕረቱ ልጃቸው መጽሀፍን እንዲያውቅ ብርቱ ፍላጎትና ምኞት ነበራቸው። ለዚህም ነው በአገራቱ አሉ ከሚባሉ ማስመስከሪያ ቤቶች በዐቃ ለማርያም ደብር ከፊደል አንስቶ እስከ ጾመ ድጓ ድረስ እንዲማር ብርቱ ግፊት ያደረጉበት። ሰናይም አባቱን ሳያሳፍር ጾመ ድጓ ቀፅሏል።

የኔታ መንበሩ በሰናይ ቀለም አያያዝ እጅግ በጣም ደስተኛ ናቸው። በእርግጠኝነት ይህ ልጅ እሳቸውን ተከቶ ወንበራቸውን እንደሚይዝ ይሰማቸዋል። መቅደስ ገብቶ የቀደሰ እንደሆን በተመስጦ ሳዳመጠው ምዕመን ድምጹ በተመስጦ ወስጥ አንሳፍፎ አርያም አድርሶ ወደ ምድር ይመልሳል።

የኔታ መንበሩ ስለሚያደንቁት ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መወድስ ቅኔ እንዲያቀርብ አድርገውት ነበር። ኃይለ ሥላሴም በድምጹ በጣም ተመስጠው "ይህ ልጅ ድምጹ አስድስቶናልና ከፍ ያለ የውጪ ትምህርት እድል እንዲያገኝ..." ብለው ለአልፍኝ አሽከራቸው ሹክ ብለው ነበር። በንጉሡ ትእዛዝ መሠረት ሠናይ ከአለቃ መሠረት ጋር መዋል ጀመረ።

የኔታ መንበሩን ለቁጭት የዳረጋቸውም ይህ ነው። ምንም እንኳ በቤተ ክርስቲያኗ የዜማ ትምህርት የተማረ ቢሆንም አለቃ መሠረትን ሊያምኑት አይችሉም። አለቃ መሠረት 'ሠራዊተ ክርስቶስ' ከተባለው የመንፈሳዊ ድርጅት አባላት ጋር ውሉና አዳሩን ካደረገ ቆይቷል። እንደውም መስራች ነው ሲባል ሰምተዋል። አሁን ደግሞ እንደ ዓይናቸው ብሌን የሚያዩትን፣ ተተክዬ ብለው ተስፋ የጣሉበትን፣ የአለቃ ምሕረቱን ልጅ፣ የየኔታ መንበሩን ጥይት ተማሪ አሜሪካ የሚገኘው ዱክ ዲቪኒቲ ኮሌጅ የነገረ መለኮት ትምህርት እንዲያጠና ሊሰድደው ነው።

ወጣቱ ዲያቆን ሰናይ ውጪ አገር ትምህርት ማግኘቱ ጮቤ አስረግጦታል። የሚሄድበትን አገር ገና ሳይሄድ በሀሳብ እያለመው ነው። እሱ ብቻ ሳይሆን አባቱ አለቃ ምሕረቱም በደስታ ነበር የልጃቸው ውጪ አገር ሄዶ መማር የፈቀዱት።

--------//--------



Scanned with CamScanner

## ኢትዮጵያ-ጎንደር

## ታሕሳስ-1965

አለቃ መሠረት 'የኢትዮጵያውያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት መፍለቂያ ዋሻ' እየተባለ ከሚሞካሸው ደብረ አባይ አቡነ ሳሙኤል ከተባለ ገዳም ማልዶ ነበር የደረሰው። በዚህ ገዳም ድንቅ ድንቅ ልጆችን እንደሚያገኝ በልበ ሙሉነት ተማምኖ ነው የመጣው። ይህ ደብር ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የእውነትም ሊቃውንትነታቸው የሚመሰከሩት ከዚህ ገዳም መጥተው የተጠየቁትን ከመለሱ፤ የሚቀኙትን ተቀኝተው 'ይበል' ከተባሉ ነው። ቅዳሴ ቀድሰው በሊቃውንቱ አንደበት 'ድምጸ መረዋ' ካልተባሉ በስተቀር መቅደስ ገብቶ መቀደስ አይታሰብም።

ለዚህ ነው አለቃ መሠረት በልበ ሙሉነት ተማምኖ ሊቀ ሊቃውንቱን ሊመለምል የተነሳው። ያስደሰተው ደግሞ ከደብረ አባይ ባለ ብሩህ አዕምሮዎችን ማግኘት ብቻ ሳይሆን ወደ አሜሪካ እንደሚወስዳቸው እርግጠኛ ነው።

የቦስተኑ የነገረ መለኮት ኮሌጅ ለአራት ልጆች የትምህርት እድል ሰጥቷል። ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ደግሞ 'እምቢ ከእኛ ምን አነሰና ነው ውጪ ሄደው የሚማሩት' እንዳይሉት የአጼ ኃይለ ሥላሴን ትእዛዝ በያዘ ደብዳቤ ሊቃውንቱ ኀበዝ ኀበዝ ደቀመዛሙራንን መርጠው ለውጪ አገር የትምህርት እድል እንዲያመቻቹ ተጠይቀዋል። ሊቃውንቱ የጃንሆይን ቃል ለማክበር ሲሉ ነገ ሊቀ ጳጳስ ይሆናሉ ያሏቸውን የዓይናቸው ስስት የሆኑትን ባለ ብሩህ አእምሮ ታዳጊዎችን ነው ለአለቃ መሠረት ያስረከቡት።

---------//---------

## ኢትዮጵያ-ሐዋሳ

## ግንቦት 1984

የደብሩ አስተዳዳሪ አባ ኃይለማርያም አራቱን ዲያቆናት በፍቅርና በስስት ነው የሚያዩዋቸው። ለዚህም ነው ዋና መጠሪያ ስማቸውን ሽረው በቅጽል ስም የሚጠሯቸው። ለንብረትና ለፍፁም 'መረዋ' የሚል ቅጽል ስም የሰጧቸው። ምክንያቱም እነዚህ ልጆች መቅደስ ገብተው ሲቀድሱ ውስጥን እንዳች ደስታ ይሞላሉ።



Scanned with CamScanner

ሔራሞ ድምጹ አስገምጋሚ ነው። ሲናገር ቤቱ የሚናድ ይመስላል፤ የእግዚአብሔርን ስም ሲጠራ እውነት ይህ ድምጽ ከአንድ ሰው ያውም በዚህ እድሜ ከሚገኝ ነው የሚያስብል ነው። እጁን እያማተበ 'በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ' ሲል ሃሳብን ሁሉ አስረስቶ የሰዎችን ቀልብ የመሳብ አቅሙ ከፍተኛ ነው። ለዚህ ባለ አስገምጋሚ ድምጽ ለሆነው ታዳጊ ልጅ 'ነጎድጓድ' ብለው ቅጽል ስም አውጥተውለታል።

ዳግማዊ ገና በታዳጊነቱ ሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ ታናናሾቹን ሰብስቦ ወንጌል ሲሰብክ ፍዝዝ ያደርጋቸዋል። ታናናሾቹን ብቻ ሳይሆን ታላላቆቹን ጭምር እጃቸውን አፋቸው ላይ ጭነው እንዲያዳምጡት የሚያደርግ አንዳች መስህብ አለው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ያነበበውም ሆነ ከታላላቆቹ እግር ሥር ቁጭ ብሎ የተማረውን በድጋሚ ከእሱ አንደበት ሲወጣ አዲስ ይሆናል። ይጣፍጣል፣ ይገባል፣ ያሳምናል...። "ይህ መቼም ጸጋ ነው ሌላ ምን ይባላል" ይላሉ የደብሩ አስተዳዳሪ በአግራሞት አንገታቸውን እየነቀነቁ። ለዚህ ነበር ስሙን 'ርቱዕ' ያሉት።

እነዚህን እንደ ዐይናቸው ብሌን የሚያዩዋቸውን ልጆች መሪጌታ በላቸው ሲወስድባቸው ነው። አባ ኃይለማርያም በእነዚህ ልጆች ላይ ትልቅ ህልም ነበራቸው። ነገ ትልቅ መምሕር ሆነው ኦርቶዶክስን በደቡብ ኢትዮጵያ ያስፋፉሉ ብለው ጠብቀው ነበር። ነገ ዳግማዊ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፤ ዳግማዊ እጨጌ ተክለ ሃይማኖት ይሆናሉ ብለው አስበው ነበር።

ቢሆንም ቆርጠው መሪጌታ በላቸውን መከልከል አልፈለጉም ምክንያቱም እነዚህ ልጆች የተሻለ ትምህርት እንዲያገኙ ወደ አሜሪካ እንዲሄዱ እድል ተመቻችቷል። ይህንን ልጆቹም ቀድመው ሰምተው ተደስተዋል። እንኳን ልጆቹ ቤተሰቦቻቸው በኩራትና በደስታ ልባቸው ሞልቷል። ስለዚህ እንደምን የልጆቹን እና የቤተሰቦቻቸውን ደስታ 'እምቢ' ብለው ያደፈርሳሉ። አይቻላቸውም!



Scanned with CamScanner

## ምዕራፍ ፪

## አዲስ አበባ-አራት ኪሎ

ሮዳስ ነጭ 'ኤክስክዩቲቭ' መኪናውን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አቆሞ፤ የአያቱን ሙት ዓመት ለመዘከር፤ ለነድያን የቻለውን ያህል ገንዘብ "ነብስ ይማር!" እያለ ይሰጥ ጀመር። እጅግ በጣም ብዙ ቁጥር ያለው ነድያን እጃቸውን በመሻማት ሲዘረጉለት የተቻለውን ለመስጠት ቢሞክርም ወጣቶች፣ ሕፃናት፣ አሮጊቶች፣ ሽማግሌዎች... ለእርዳታ እጃቸውን ስፍ ስፍ ብለው ሲዘረጉ ሲያይ ሮዳስ ልቡ ይደማ ጀመር።

'ወጣቶች በተስፋ ማጣት ውስጥ ናቸው፤ ሕፃናት እለሁ ባይ ስለሌላቸው ለራሳቸው በመስላቸው መንገድ እየተንቀሳቀሱ ነው፤ አረጋውያን ጧሪ ወገን በማጣት በሀዘን በምሬት ተቆራምደው የሰው ፊት እያዩ ነው። እንዲህ ያለ ችግር በገዛ ወገን ላይ ማየት ልብን ይሰብራል፤ አንገት ያስደፋል።' እያለ እያብሰለሰለ ነው።

ሮዳስን ከምንም በላይ የረበሸው የእማማ ፍቅርተ ለማኝ መሆን ነው። እማማ ፍቅርተ አራት ኪሎ በቀበሌ ቤት የሚኖሩ መካን ሴት ናቸው። እኚህ ሴት የሰፈሩን ልጆች ያሳደጉ ናቸው። አቅም በነበራቸው ጊዜ ጠላና ዳቦ እየሸጡ የባላቸውን ሠላሳ ብር ጡረታ ከቀበሌ እየተቀበሉ ይኖሩ ነበር።

ሮዳስ እማማ ፍቅርተን የሚያውቃቸው ለቁርስ ከእሳቸው ቤት ሙል ሙል ዳቦ ለመግዛት ሲሄድ ነው። ያኔ እማማ ፍቅርተ አንድ ሽልጦ ሸጠው ሌላ የሽልጦ ግማሽ ደግሞ እንደ ምርቃት "እንካ አንተ ከላባ! ቀስ ብለህ ይህቺን ዳቦ እየገመጥክ ቤትህ ሂድና እሱን ደግሞ በሻሂ ብላ" ብለው ዳቦ ይሰጡታል። ይህ ቸርነታቸው ለሮዳስ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የሰፈሩ ልጆች ነው።

እኚህ ደግ እናት አሁን እድሜያቸው ሲገፋ፤ እጃቸው አሻሮ መቁላት ሲያቅተው፤ ጀርባቸው እህል መሸከም ሲከብደው፤ ጉልበታቸው ጌሾ መውቀጥ ሲሳነው፤ እግራቸው ወፍጮ ቤት ለመሄድ ሲለግም፤ ሠላሳ ብር ወር ሳይሆን አንድ ቀን ማዋል ሲያቅታት፤ ለችግር የሚደርሱ የነበሩ እናት ለችግራቸው ደራሽ ሲያጡ፤ ቀበሌ ቤታቸውን ነጥቆ ኮንዶሚኒየም ሲሠራበት ለእሳቸው አቅም የሚሆን ቤት ሊገነባ አልቻለም። ቅያሬው ቤትም ቢገኝም የድሮውን መንደራቸውን ደስታ፣ ፍቅር፣ ሠላምን ሊተካ አልቻለም። ስለዚህም ለነ ሮዳስ አንድ ሙልሙል ዳቦ ላይ ሌላ ግማሽ ዳቦ ያለ ስስት በምርቃት የተሰነዘረ እጃቸው፤ ዛሬ ግን ለልመና ተዘረጋ፤ ያ ፈገግታና ለጋስነት የተላበሰው ፊት በሃፍረት ድፍት ብሎ በሰው ፊት ግርፋት ተሸማቀቀ።



Scanned with CamScanner

'ይህ ህመም ነው' አለ ሮዳስ በቁጣ፡፡ 'ሰፈር በቁስ ብቻ አልተሰራም፡፡ ሠፈር ውስጥ ሕይወት፣ ማኅበር፣ አንድነት፣ ምንነት፣ እምነት፣ ምስጢር እና ጨዋታ አለ፡፡ ሠፈር ሲፈርስ ይህን ሁሉ ነገር ይታጣል፡፡ ሠፈር ሲፈርስ ለዘመናት የተገነባ መተማመን፣ መፋቀር፣ መዋደድ፣ መተሳሰብ፣ መተማመን... አንድ ላይ ይፈርሳል፡፡ ማኅበረሰብን የማፍረስ ተግባር ላፍራሹ ቀልድ ነው፡፡ ለፈረሰበት ግን ከፍተኛ ሕመም ያስከትላል፡፡' እያለ መፈላሰፍ ጀመረ፡፡

ሮዳስ በዚህ ጥልቅ ሕመም ውስጥ ሆኖ ወደ አራት ኪሎ በእግሩ እየሄደ መጎብኘት ጀመረ፡፡ አራት ኪሎ የዱሮ ባሏን ፊትታ አዲስ ልታገባ የምትሰናዳ እንስት ትመስላለች፡፡ የዱሮ ትዳሯን የሚያስታውስ ምንም ነገር ማየት የምትፈልግ አትመስልም፤ ከቀደምት አኗኗሪዎቿ ጋር እንኳ ዳግም መተያየት አትሻም፡፡

ሮዳስ የሕፃንነት ድክ ድኩን፣ የጎረምሳነት መጉረምረሙን፣ መፍጨርጨሩን፣ የወጣትነት ፍጥነቱን፣ አለሁ አለሁ ባይነቱን፣ ስኬትና ውድቀቱን፣ የዓይን ፍቅርን፣ የጎረቤት ልጅ መውደድን ያየው በዚህ ሰፈር ነው፡፡

ይህ ሰፈር ለሮዳስ ልጅነቱ ብቻ አይደለም ማንነቱም ጭምር ነው፡፡ ልጅነት ከነማስታወሻው፤ ፎቶው ከነ ማዕቀፉ፤ ማንነት ከነ ደስታና ሐዘኑ ከአራት ኪሎ ጋር ፈረሰ፡፡ የእሱነቱን ሙሉ ምስል ከአራት ኪሎ አፈር ውስጥ በዶዘር ተቆፍሮ፤ በዶዘር አፈር ለብሶ፤ ኮንዶሚኒየም የሚባል ሐውልት እየቆመለት ነው፡፡

ይህ የእሱ ብቻ ቁጭት አይደለም የእኩዮቹም፣ የታናናሾቹም ሆነ የታላላቆቹ 'ወይ አቅም ማጣት' እያሉ ስርክ የሚያዝኑበት ጉዳይ ነው፡፡ የአራት ኪሎ መፍረስ ጉዳይ በሮዳስ ፊት ከተነሳ እንዲህ ሲል ሰፈርን ከወንድ ልጅ ጋር እያገናኘ ይንተነትናል፡፡

"በኢትዮጵያውያንም ሆነ በብዙ የዓለም አገራት ከወንድ ልጅ ይልቅ ሴት ልጅ ነች አግብታ ከቤት የምትወጣው፡፡ በተቃራኒው ወንድ ልጅ ካለው በራሱ፤ ከሌለው ባባቱ ርስት ላይ ያገባል፤ የአባቱንም የራሱንም ርስት ይጠብቃል እንጂ እንዲህ አለ ምክንያት ጎጆውን ሆነ መንደሩን ማስረከብ ክብረ ነክ ነው፡፡ ለወንድ ልጅ ሰፈሩን ያለ በቂ ምክንያት ለሌሎች ለቆ እሱ ወደ ሌላ ቦታ መሄድ ውርደት ነው፡፡"

እንዲህ በስሜት ሲናገር ጓደኞቹ ቁጣውን ከፍ ለማድረግ "የሚፈርሰው እኮ ለልማት ነው" ይሉታል፡፡ ሮዳስም በቁጣ እንዲህ ሲል ይመልሳል "ልማት ልማት የሚሆነው የመሬቱን ባለቤት ተጠቃሚ ሲያደርግ ብቻ ነው፡፡ እኔ ተወልጄ ያደኩበትን ሰፈር ሳልፈቅድ እየተነሳሁ፤ ሌላ ሰው በምትኩ ከተቀመጠበት የግፍ ጥጉ ይሄ ነው፡፡ አያት ቅድመ አያቶቼ የሞቱልኝ በአገሬ መሬት እንደ ልብ እንድፈልል፤ እንደ ልብ ቦርቄ፤ እንደ ምኞቴ እንድኖር እንጂ በሌሎች መልካም ፈቃድ ከገዛ ሰፈሬ ወደ የትም እንደ እንስሳ እንድጋዝ አይደለም፡፡"



Scanned with CamScanner

ሮዳስ በስሜት ተውጦ፤ በሀሳብ ተሳክሮ አራት ኪሎን እየቃኛት ነው። የሰፈሩ ልጆች የፈረሰው ቤታቸውን ንቃይ መስኮት፣ በር፣ ቆርቆሮ፣ እንጨት፣ ብረታ ብረት… ከፈረሰ ሰፈራቸው ደጃፍ ላይ ደርድረው ለሽያጭ አቅረበዋቸዋል። ገቢ እስኪመጣ ብለው ነው መሰል ልጆቹ በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሰምጠው አንድ ሲጋራ ለአራት እየተቀባበሉ እያጨሱ ካርታ ይጫወታሉ።

ሰውነታቸው ያደፈ፤ ለእግራቸው ቆሻሻ ነጠላ ጫማ የተጫሙ፤ እላያቸው ላይ ንጽሕና የጎደለውን ቲሸርት የለበሱ ወጣቶችን ሲያይ ሮዳስ ዕምባው በዓይኑ ሞላ። ታግሎ ሊያቆመው ቢሞክርም ቁጭትና እልህ አንዘበዘበው። የገዛ ቤታቸውን በራሳቸው መደሻና ዶማ አፍርሰው ባራ፣ መስኮት እና በር የሚሸጡ ወጣቶች ሲያይ ሆዱን አባባው፤ አፈናቃዮቹም ላይ ቂም እንዲቋጥር፤ ጥርስ እንዲነክስ ገፋው።

በትክክል አዲስ አበባ ከቀደምት ነዋሪዎቿ ጋር እየተቆራረጠች ነው። ለሮዳስ አዲስ አበባ ሴተኛ አዳሪ ሆናችበት። 'ላለው ሁሉ አዲስ አበባ፤ ለገዛት ሁሉ ሰጥ ለጥ ብላ የምትገዛ፤ የራሷ የሆነ ቀለም የሌላት፤ የራሷ የሆነ አድራሻም ሆነ ድርሻ የሌላት፤ የኔ የምትለው ዘመዶችም የሌላት ነች። ቆርቋሪዎቿን ለባለጊዜ ለተደጋጋሚ የለወጠች ለከፋይ ያደረች ሁሌ የምትሸጥ ነች። አዲስ አበባ ዝብርቅርቅ፣ ድፍርስርስ፣ ጉራማይሌ… ነች።

'በእርግጥ ጉራማይሌ መሆኗ ባልከፋ ግን ቀደምቶቿን ሰውታ አዲሶቿን ካበቀለች ቅብብሎሾቹ ጤናማ አይደለም። አገርን ከነእሴቱ ከነማንነቱ በሰላምና በፍቅር ካልተቀባበልነው ቀጣይነቱ አጠያያቂ ነው። በዚያ ላይ ከአብዛኛው ነዋሪዎቿ ጋር የተጣላች ከተማ ለዘላቂነቷ ምን ዋስትና አላት?' እያለ በእልህ፣ በቁጣና በንዴት ውስጥ ሆኖ ሰራሱ ሲደሰኩር የእጅ ስልኩ ጠራ። ሮዳስ እጁን ኪሱ ውስጥ ከትቶ ዘመናዊውን ስልኩን አወጣና ደዋዩን ከስክሪኑ ላይ ተመለከተ። ፍቅረኛው ሰንቤር ነች።

ሮዳስ ስልኩን አነሳና በደከመ ድምፅ "ሄሎ" አለ።

ሰንቤር በደስታ ውስጥ ሆና ፍንክንክ እያለች "አንተ ቀጥረኸኝ የት ሄደህ ነው?"

ቀዝቀዝ ብሎ "እለሁ ኧረ" አለ

"የታለህ? ድምፅህ ምንድነው የቀዘቀዘው?"

"ይቅርታ ሰን እዚህ ድሮ ሰፈሬን አየት ላድርገው ብዬ ወጥቼ ነው። መጥተሻል?"

"አዎ መኪናህን እዚህ ገትረህ አንተ የለህም በል ቶሎ ና እየጠበኩህ ነው"

ሮዳስ ዞሮ ወደ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ወደሚወስደው መንገድ እያቀና "እሺ እሺ" መጣሁ አለ፡፡

-------------//---------

## ናይሮቢ-ኬንያ

ሳሮቫ ስታሊን ሆቴል እ.ኤ.አ በ1902 ዓ.ም በእንግሊዛዊዋ እመቤት ማየንስ ቤንት እንጨት በእንጨት ሆኖ እንደ ነገሩ ተገንብቶ አገልግሎት የጀመረ የኬንያ ቀደምት ሆቴል ነው፡፡ ይህ እድሜ ጠገብ ሆቴል በአሁኑ ሰዓት 'ሳሮቫ ስታንሊ' የሚለውን ስሙን ቀይሮ 'ኒውስታንሊ' በመባል በፎቅ ላይ ፎቅ በመደራረብ ሁለት መቶ አሥራ ሰባት ውብ፣ ዕጹና ምቹ ክፍሎቹን ይዟል፡፡ ኒውስታንሊ ሆቴል ሦስት ሬስቶራንትና አንድ ባር አካቶ በናይሮቢ መሃል ከተማ ላይ ይገኛል፡፡

ይህ ሆቴል ታሪካዊነቱ በዕድሜው ብቻ ሳይሆን ብዙ በዓለም ታሪክ ላይ ዋና ተዋንያን የነበሩ ሰዎችን አስተናግዷል፡፡ የቀድሞውን የእንግሊዙን ጠቅላይ ሚኒስተር ዊንስተን ቸርችል፤ 'የአውት ኦፍ አፍሪካን' ደራሲ ካረን ብሊክሰን፤ እንዲሁም እውቁ ደራሲ ኧርነስት ሔምንግዌይ ከአንጋፉም ሁለቱ መጥቶ 'ዘግሪን ሒል ኦፍ አፍሪካ'፣ 'ዘ ስኖው ኦፍ ክሊማንጃሮ' የሚለውን ጽሑፍ ረቂቅ ከዚህ ሆቴል ቁጭ ብሎ ከትቧል፡፡ 'ሳፋሪ' የተባለውን ቃልም ለእንግሊዘኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላት እንካችሁ ያለው ከዚሁ ከኒውስታንሊ ሆቴል ውስጥ ሆኖ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ መንፈሳዊ መምህራን ድብቁን ስብሰባ የሚያደርጉት ለደራሲው ኧርነስት ሔምንግዌይ ለክብሩ መገለጫ ሲባል በስሙ በተሰየመለት የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በቁንጥ የተሰፋውን ረዥሙንና ዘርፋፋውን ነጭ ወይም ጥቁር ቀሚስ ለብሰው፤ በእጃቸው መስቀል ይዘው፤ አንገታቸው ላይ የሚያብረቀርቅ ረዥም ሠንሰለት ላይ መስቀል በማሰር የሚታወቁት መንፈሳዊ ሰዎችን ዛሬ ላያቸው እነሱ ናቸው አይደሉም ብሎ ለሰዓታት መወዛገቡ አይቀሬ ነው፡፡

ገሚሱ ሙሉ ሱፍ ለብሷል፡፡ የተቀሩት ደግሞ ቀለል ያለ ሸሚዝና ጅንስ ሱሪዎችን አጥለቀዋል፡፡ ሱፍ የለበሱት በልካቸው በጥሩ ሰፊ ስለተሰፋ ሰውነታቸው ላይ ልክክ ብሎ ደስ የሚል ገፅታን አላብሷቸዋል፡፡ ሌሎችም አለባበሳቸው ጥሩና እነሱ ራሱ ብዙም ያልለመዱት ገፅታን አላብሷቸዋል፡፡ በዚያ ላይ ያሉበትን ቦታ የወደዱት ይመስላል ፊታቸው ላይ ብሩህ ገፅታና ደስታ ይታያል፡፡

ተሰብሳቢዎቹ ኢትዮጵያዊ ይሁኑ እንጂ የመጡት ከተለያዩ የዓለም ክፍል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ከሚያገለግሉበት ደብር ነው፡፡ አምስቱ ከዱባይ፣



Scanned with CamScanner

አራቱ ከአሜሪካ፣ አሥሩ ከኢትዮጵያ፣ ሌሎች ሁለት ሁለት ሰዎች ከእንግሊዝ እና ከደቡብ አፍሪካ ነው የመጡት፡፡

ሁሉም የስብሰባው ታዳሚዎች በአንክሮ ገለጻውን እያዳመጡ ነው፡፡ ገለጻውን የሚያደርገው ዶክተር መርሐዊ ሲሆን ከጎኑ ደግሞ ረዳቱ ዶክተር ሩቢዮ አለ፡፡ ሁለቱም የነገረ መለኮት ምሁራን ሲሆኑ ፊታቸውን ወደ ተሰብሳቢዎች አዙረው ቁጭ ብለዋል፡፡

ከፊት ለፊታቸው ባለ ጠረጴዛ ላይ ትልቅና እጅብ ያለ በሕብረ ቀለማት ያሸበረቀ የተፈጥሮ አበባ አለ፡፡ ከአበባው ትንሽ ፈቀቅ ብሎ የሩቢዩና የመርሐዊ አፕል ኮምፒውተር ተከፍቶ ከፊት ለፊታቸው ተቀምጧል፡፡ መርሐዊ ከላፕቶፑ ጎን በፕላስቲክ የታሸገውን ውኃ ከፈተና ተጎነጨለት፡፡

መርሐዊ ከኤልሲዲ ፕሮጀክተር ጋር ላፕቶፑን አገናኝቶ ገላጻውን እያደረገ ሲሆን ከኤል ሲዲው በሚወጣው የብርሃን ጨረሮች አማካኝነት ከአቡጀዴው አናት ላይ በቀይ ቀለም ከዮሐንስ ራዕይ ላይ ያለው ጥቅስ በጉልህ ይነበባል

“በዙፋን ያለው ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ (ራዕ 21፥5)”፡፡

ዶክተር አባ መርሐዊ ከፊት ለፊቱ ያስቀመጠውን አፕል ላፕቶፕ አየት አደረገና ንግግሩን ቀድሞ በነበረው ተመስጦ ቀጠለ “የእለቃ ኪዳነ ወልደ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ተሐድሶ የሚለውን የግዕዝ ቃል ‘ማደስ፣ መለወጥ፣ ሐዲስ ማድረግ፣ ማጥናት ማበረታታት፣ መሥራት፣ መጠገን፣ በተጨማሪ አዲስ ነገር ማውጣት መፍጠር ነው’ ብለው የፈቱ ሲሆን እንግሊዝኛው ደግሞ ተሐድሶን በሦስት አይነት ቃላት እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፡፡

“አንደኛው ‘ሪፎርሜሽን’ የሚለው ቃል ሲሆን ትርጉሙም የተበላሸውንና የተመሰቃቀለውን አስተካክሎ እንደገና መሥራት እንደገና መለወጥ የሚል አንድምታ ሲኖረው ቃሉ ከግሪኩ ‘ዳዮርቶሲስ’ ከሚል ቃል የመጣ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ‘ሪ-ኒዋል’ ሲሆን ቃሉ ‘አናካይኖ’ ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ነው፡፡ ትርጉሙም አዲስ ማድረግ ማለት ነው፡፡ ሦስተኛውና የመጨረሻው ቃል ‘ሪ-ስቶሬሽን’ ሲሆን ግሪኩ ‘አፖካስታቶስ’ ይለዋል ትርጉሙም ከስፍራው የለቀቀውን፣ የተሰረቀውን፣ የተወሰደውን ወደ ቀደመ ሥፍራው መመለስን ያመለክታል፡፡

“እንደ ማጠቃለያ ቦብ ግሊየም የተባሉት አሜሪካዊ የተናገሩትን ልንገራችሁ” አለና ከፊት ለፊቱ የተቀመጠውን የውኃ ኮዳ አንስቶ ጎንጨት አለ፡፡ በንግግር ብዛት የደረቀው ጉሮሮው ራስ ሲል መላ ሰውነቱ እንዳች ደስ የሚል ስሜት ተሰማው፡፡



Scanned with CamScanner

"ቦብ ግሊየም የቲ-ኔት ኢንተርናሽናል የፓስተራል ሊደርሺፕ ኮሌጅ ፕሬዝዳንት ሲሆኑ 'ታላቁ ተልእኮን መፈፀም' በሚለው መጽሐፋቸው ስለ ተሐድሶ እንዲህ ብለዋል 'ተሐድሶ ማለት የነገረ መለኮታዊ አስተሳሰብ፣ የድርጅታዊ እና የፕሮግራም አወቃቀሮችን ዳግም ማደስ ማለት ሲሆን ይህም ቤተ ክርስቲያን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንድትኖርና በመነቃቃት የተገኙትን ውጤቶች እንድታበዛ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለተከታታይና ረዘም ላለ ጊዜ በተሳካ ሁኔታ እንድትፈጽም የሚያስችላት ለውጥ ነው' ብለዋል።

"ከላይ እንደ ተመለከትነው ተሐድሶ ስንል አዲስ ወንጌል እንሰበክ ማለታችን ሳይሆን የቀደመውንና የጥንቱን የክርስቶስን ወንጌል የጋረዱና የተቀላቀሉ እንግዳ ትምህርቶችና ሰው ሰራሽ ቀኖናዎች በቃሉ አበጥሮ ሐዋርያት ወደ ሰበኩት የጠራና የጠለለ የወንጌል እውነት መመለስ ነው። በቃ ተሐድሶ ሌላ ነገር የለውም የክርስቶስ ያልሆነውን ነገር ማስወገድ ብቻ ነው።" መርሐዊ ስሜት ውስጥ ገብቷል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን በተሐድሶ ጎዳና የማየት ናፍቆቱ በቃላትም በስሜትም ከሚገለጸው በላይ ነው። 'ተሐድሶ ማለት የክርስቶስ ያልሆነውን ሁሉ ማስወገድ ነው' የሚለው አባባል ሁሉንም የስብሰባውን ታዳሚዎች ቀልብ ስቧል። በቃላቸው ለመያዝ ዓረፍተ ነገሩን በአዕምሯቸው ይደጋግሙት ጀመር።

--------//------



Scanned with CamScanner

## ምዕራፍ ፫

## አዲስ አበባ-አራት ኪሎ

ሮሚና ካፌና ሬስቶራንት እንደ ወትሮው በሰዎች ተጨናንቋል፤ የካፌው ትላልቅ ዛፎች እያዘቀዘቀች ካለችው ጀንበር ጋር አንዳች ደስ የሚል ሕብር ፈጥረው ንፋሱን ከአየር እየቀዘፉ በሥራቸው ለመዝናናት ለተቀመጡ ሰዎች ያለ ስስት ይለግሳሉ።

በካፌው ውስጥ ያሉት ሰዎች አንዳንዶቹ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በነጻነት የሚጫወቱ፤ ሌሎቹም ከባድ የሐገር ምሥጢር ያወሩ ይመስል የሚያንሾካሹኩ፤ አንዳንዶቹም ብቻቸውን ከፊት ለፊታቸው የሚጠጡትን አስቀምጠው ስልካቸውን እየጎረጎሩ ሰው የሚጠብቁ፤ ዝም ብለው ብቻቸውን የሚዝናኑ፤ አንዳንድ ብቻቸውን ያሉ ወጣት ወንዶች ደግሞ ምንም እንኳ ስልካቸውን እየጎረጎሩ ቢሆንም አንዲት እንስት ወደ ካፌው ስትገባ አንገታቸውን ቀና አድርገው በዓይናቸው ይመዝኑና ቆንጆ ከሆነች ከፊት ለፊት የምትታያቸው ከሆነ አንዴ ፊቷን፣ አንዴ ጡቷን፤ አንዴ እግሯን እያፈራረቁ በሰከንዶች ውስጥ ያያሉ። ከኋላ የምትታያቸው ከሆነ መቀመጫዋን በዓይናቸው ቸብ ቸብ እያደረጉ ይሸኟትና ወደ ስልክ ጉርጎራቸው ይመለሳሉ። አንዳንዶቹማ በዓይን የሚከተሏት እንስት ወንበር ይዛ ስትቀመጥ ዓይን ለዓይን ይጋጩና አፈር ብለው አንገታቸውን ይደፋሉ።

ሰንፔርና ሮዳስ ፊት ለፊት እየተያዩ ተቀምጠዋል። ከእነሱ ፊት ለፊት ባለው ጠረጴዛ ላይ ደግሞ የሚጠጣ ለስላሳ እንዲሁም በሰፌና ሞላላ ቄንጠኛ ነጭ ሰሀን ላይ ድንች ጥብስ፤ ተገምጦ ከጥርስ የተረፈ ክለብ ሳንዱች የተዘጋጀበት የዳቦ ጠርዝ ሲኖር፤ ከሳሀኑ ውጪ ደግሞ ጠረጴዛው ላይ ተዝረክርኮ ከአፍ የወደቀ ቲማቲም፣ ሥጋ፣ ሰላጣ፣ እንቁላል እና የተጠበሰ ድንች ይታያል።

ሰንፔር በግራ እጇ አፍ ማበሻ ይዛ በመጠኑ ተለቅ ብሎ ከፊት ለፊቱ ያሞጠሞጠውን ግመጡኝ ግመጡኝ የሚለውን ቀዩን ከንፈሯን ታብሳለች። ከእሷ ፊት ለፊት የተቀመጡ ወንዶች አንዳንዴ ሰረቅ እያደረጉ ያዩዋታል። አንዳንዴ ዐይናቸውን ከእሷ ላይ መንቀል ከብዷቸው ፍዝዝ ብለው ያዩዋታል። ይብስ ብሎ አንደኛው ልጅ ጠቀሳት። ሰንፔር ልጁ ላይ ፊቷን ቅጭም አድርጋ ወደ ሮዳስ ተመለሰች።

ልጁ ግን ሮዳስን ሳይፈራ ያዘዘውን በርገር በእጁ እንዳንከረፈፈ ለአፍታ ድርቅ ብሎ በሰንፔር ውበት ተደምሟል። ውበቷ አንዳች ምትሀት ያለው ይመስል የወንድም ይሁን የሴት ዐይን ፊቷ ላይ ሲያርፍ ለቅንጣት ደቂቃ እንዲቆይ የሚያስገድድ አንዳች መስህብ አለው። ፊቷ ሙሉ ለሙሉ ክብ ባይባልም እንደነገሩ ክብ ነገር ነው። ፊቷ በጣም ከመቅላቱ የተነሳ ወደ ቢጫነት ያደላ ሳይሆን ብስል ቀይ ነች፤ ጉዳዩ ቅላቷ ሳይሆን ፊቷ ላይ በጥበብ የተቀመጡት ትላልቅ ዐይኖቿና ዐይኗን



Scanned with CamScanner

ያለበሰው ቅንድብና ሽፋሽፍቷ ነው። ቀጥ ብሎ የወረደው የአፍንጫዋ ግርማ ሞገስ የጃንሆይን ቤተሰብ አስመስሏታል። ሰንፔርን አፍጥጦ የሚያያት ባለ በርገሩ ልጅ ብዙም ባይሆን ከአፉ ውስጥ ለሀጩ እንደመዝረክረክ አለ። ደንገጥ አለና አፉን በአንድ እጁ አፉን ጠረገና በርገሩን ለመግመጥ በስሱ ወደ በርገሩ ቀረብ ብሎ አፉን ከፈተ።

ሰንፔር ቁመቷ ልከኛ የሚባል ሲሆን የወገቧን ቅጥነት ላየ ሰው የዳሌዋ ስፋትና ትልቀት ሲያይ ይህ ነገር ተፈጥሯዊ ነው አይደለም ብሎ በጥቂቱም ቢሆን መወዛገቡ አይቀርም። በርገር እንደሚገምጠው ልጅ ያለ ደግሞ መቀመጫዋን እያየ ፓንቱ የሚጠበው፤ ዐይኑና ብልቱ ቅርብ የሆነበት ሰው ብዙ ነው።

ሰንፔር ላይ ቀልቡን ልጅ በርገር ለመግመጥ ብቻ መለስ ያደርግና መልሶ ያፈጥጣል። 'ከዚህች ውብ ላይ ዐይንን አለመንቀል እንደ ሴሰኝነት አይቆጠርም ምክንያቱም ተፈጥሮ ውብ መሆኗን ማድነቅ ሰሪውን ማድነቅ እንጂ ተሰሪውን ስላልሆነ።' የሚል ይመስላል።

ሮዳስ ሰንፔር ስትስቅ በብረት የተለበጠውን ጥርሷን አያየ የተለመደው የሹፈት ሳቁን ስቆ "እኔ እምለው ይህን የመሰለ ውበት ሰጥቶሽ እንዴት ጥርስ ነፈገሽ?" አለ ሊያናድዳት ፈልጎ። ጥርሷ ድርብ እያለ አትወደውም ነበር። አሁን ብሬስ ታስሮለት በውበቷ ላይ ሌላ ውበት ደፍቶባታል።

ሰንፔር በስሱ ኮስተር ብላ "ምነው ቅናት መሰለብህ አንተማ ጥርሴ ባይሠራልኝ ድርብ እንደሆነ ቢቀር ደስ ይልሀል? አየህ አይደለ this is medicine!"

"ኸረ እኔ..." አለ ሮዳስ እንደ መሳቅ ብሎ

"ያንቺ ውበት በየቀኑ እንደ ዘመኑ ኑሮ ቢንር ደስታዬ ነው? አለ አይደል..." ብሎ ነገሩን አንጠንጥሎት ዝም አለ

ሰንፔር ውብ ከንፈሮቿን ከተጋጠሙበት እያላቀቀች በመሳቅ "አንተ እኮ አትመስል ኑሮና ውበት ሃሃሃ..." እያሾፈች ሳቀችበት

"ምነው" አለ ዐይን ዐይኗን እያየ

እየሳቀች "አይ ምንም አለ አይደል ምን... ጨርሰዋ አለ አይደል... ስትል?"

"አይ ትንሽ እንክን ቢኖርሽ ጥሩ ነው? እንዲህ ማማር ምንድነው? ኮምፒትሽነል አይከብደኝም ብለሽ ነው?"



Scanned with CamScanner

"ውይ ወንዶች እርስ በርሳችሁ መወዳደር ትወዳላችሁ። እኛ እኮ የእናንተ ኮምፒትሽን አይደለም የሚገዛን። ከዚያ ይልቅ ስብእናና ወንድነታችሁ ነው። እናንተ ግን ለሴት ብላችሁ ብትገዳደሉ ሁሉ ደስ ይለኛችኋል። ስትገርሙ!"

"ቆንጆ መውደድ ተፈጥሯዊ ነው። እኛ ወንዶች ለቆንጆ ሴት ትልቅ ዋጋ መክፈል እንደ ተፈጥሮ ግዴታ እንቆጥራለን። በተለይ መውደዳችን የሚጨምረው ሴቶቻችን ላይ ሌሎች ወንዶች ሲቅበዘበዙ ነው። ይህኑ ቁጣና አልበለጥም የሚል ኃይል ውስጣችንን ያሞላዋል። ስለዚህም ምንም አይነት ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ ነን።"

በጎርር እንደ ማር ወለላ ላሱኝ ላሱኝ የሚለውን ከንፈሯን ለፈገግታ ከፈት አድርጋ "ይህን ነገር የተናገርከው አስበህበት ነው? አስቀኚኝ ማለትህ እኮ ነው?"

ሮዛስ ጠያም ራሱን አከላተረውና "ኖ! ኖ! እንደዛ ለማለት አይደለም። እንዲህ በመሰለች ቆንጆ መቅናትማ መች ያቀራል ችግሩ ነው እንጂ። በጣም ካስቀናሽኝ ግን አልችልም ከባድ ነው"

"ምነው ራሩህ እንዲህ ቆይ አንድ ቀን በጣም አስቀናሃለሁ"

ሮዛስ ሳቅ እያለ "እሬ ከባድ ነው እኔ ከቀናሁ መጥፎ ነው"

"ኪዳስ አዘኑን እንዳለ ላቃጥላት እችላለሁ። አታምኚም እኮ" አለ እየሳቀ

በጎርር በብሬስ ጥርሷን የተደረደረውን ጥርሷን ብልጭ አድርጋ እየሳቀች "የምር ተመቸኝ መሉ ጋኪም ጉራ ነው። እንጂ ኪዳስ አዘኑን እንደ ደሰሁ ወረቀት አታቃጥልም።

"ሀሀሀሀ..." ሮዛስ አፉን ከፍቶ ሳቀና "እንዴት እንደ ምክሬውና አላደሻለሁ"

"ቃልዳን ተሰውና እኔ እምልህ ሥላሴ ምን ልትሆኚ ሄደህ ነው?"

"አልነገርከችም እንዴ ባሬት አያቴ ከሞተች ከፊት አመት ነው ስለዚህ ስሟን አስታወሼ ነፍስ ይማር ልል መሄዴ ነው"

በጎርር ሳቅ ቢያስገርምም ሳቋን ተቆጣጥራ በሉሉ ሳቅ ብላ "ትገርሙኛላችሁ ሰው ከሞተ በኋላ ነፍስ ይማር ምንድነው ጥቅሙ? ፍትሃት፣ እርዳ፣ ሶሎላ፣ ሰማንያ... ምናምን አይገባኝም ግን ብሎ ተረት እኮ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ..." ሰጎርር ከተናገረች በኋላ እንደተሳሳተች ገባት።

ሮዛስ ነገር ከያዘ አይለቅም እንደሷ አባባል 'አቻቻ...' ነው። ምክንያቱም በአጠቃላይ ስለ ሞትና ፍትሐት ቀኖናም ስለ ሃይማኖት ጥቅምጥቅ ሊጀምር ነው። ሮዛስን

ታውቀዋለች በሃይማኖት ጉዳይ እስከ ጥግ ድረስ ሄዶ ማስረዳትና መረዳት ይወዳል። በይበልጥ ማሸነፍንና ማሳመንን ስለሚፈልግ እንደሚጨቃጨቁ አወቀች። ቢሆንም አንዴ አውጥታ ተናግራዋለች መልሳ አትውጠው ነገር።

ሮዳስ የተናደደ መሰለ "አንቺ ሳትሆኚ እዚህ ላይ እኔ ነኝ መሳቅ ያለብኝ? እንደኛው ለምን እንደምናደርግ አለማወቅሽ ነው፤ ሌላው ሳታውቂው መሳለቅሽ ነው።"

ሰንፔር ከገባሁበት አይቀር ልናገር ብላ ድጋሚ ፍርጥም ብላ መልስ መስጠት ጀመረች "አልተሳሳትኩም እውነቱን ነው! አንዴ ሰው ሞቶ ከተፈረደበት በኋላ በሞተ በሦስተኛው ቀን፣ በአርባ፣ በሰማንያ፣ በዓመት፣ በሰባት ዓመት ምናምን ነፍስ ይማር እየተባለ መድገስ ምን ማለት ነው? ሳይንስም መጽሐፍ ቅዱስም አይደግፍም። እግዚአብሔር ፍርድ ከሰጠ በኋላ ፍርድ ለማስገልበጥ ካልሆነ በስተቀር ይህ ደግሞ ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።"

"ሰን ለመናገር ብለሽ ነው የተናገርሽው ወይስ ከእኔ መልስ ፈልገሽ ነው የጠየቅሽኝ?"

"አዎ መልስ ካለህ ደስ ይለኛል ብትነግረኝ" ብላ ሳቅ አለች።

ሮዳስ በረዥሙ እንደ መተንፈስ ብሎ ደረቱን ወደ ላይ ነፋ አደረገና መልሶ ከነትንፋሹ ከደረቱም ዝቅ አለ "በመጀመሪያ ለሙታን መለመንም ሆነ በሙታን ስም ምጽዋት መስጠት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። ይህን ነገር የምናደርገው የእግዚአብሔርን ፍርድ ለማስቀየር አይደለም። ከዚያ ይልቅ በእግዚአብሔር ተስፋ ስላለን ነው። እምነት፣ ፍቅርና ተስፋ ደግሞ የክርስትና መሠረት ነው። ስለዚህ ለሙታን ጸሎት ስናደርግ በተስፋ ነው እንጂ ፍርድ ለማስቀልበስ አይደለም።

"መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው አይደለም ለሚለው ጥያቄ መልሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። ታስታውሺ እንደሆነ የያዕቆብ የበኩር ልጅ ሮቤል ይባላል። ሮቤል ግን የአባቱን እቁባት ባላንን ወደ አባቱ አልጋ ወጥቶ ተገናኛት በዚህ የተነሳም አባቱ ያዕቆብ ሮቤልን ረግሞት ነበር። ነገር ግን ዘመናት ካለፉ በኋላ ቢያንስ ከአንድ ከመቶ ዓመት በኋላ ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ከምድረ ግብፅ ነፃ ሲያወጣ የአባቶቻቸውንም አፅም ይዘው ይወጡ ነበር። ከእነዚህ አፅሞች በተለየ ሁኔታ የሮቤል አፅም ጠቁሮ ስለነበር ሙሴ እንዲህ ሲል ለሮቤል ጸለየለት 'ወዳጄ ሮቤል በሕይወት ይኑርልኝ፤ አይሙትብኝ' አለ። ተመልከች አንቺ አርባ ሰማንያ ሙት ዓመት ትያለሽ ሮቤል ከሞተ ከመቶ ዓመት በኋላም ተጸልይዋል። ይህን ታሪክ ዘፍጥረት እና ዘዳግም ላይ ልታይው ትችያለሽ። መጽሐፈ ሩት ምዕራፍ ሁለት ቁጥር ሃያ ላይም 'ቸርነቱን በሕያዋንና በሙታን ላይ አልተወምና' ይላል።"

ሰንፔር ብዙም አላሰመነኝም በሚል አስተያየት ፊቷን እያወዛወዘች እያየችው "ይህ እኮ ብሉይ ኪዳን ላይ ነው ሐዲስ ኪዳን ላይ አውራኝ እስኪ?" አለችው። ዛሬ ብቻ



Scanned with CamScanner

ሳይሆን ብዙ ጊዜ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሲያወሩ ለሰንፔር ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የብሉይ ኪዳን ማስረጃዎች ብዙም አይዋጡላትም።

ሮዳስ በደስታ በሚል ዓይነት ፈገግ ብሎ ወንበሩ ላይ ተደላድሎ እየተቀመጠ "እሺ. ቅዱስ ጳውሎስ በኤፈሶን ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ በጥሩ ሁኔታ ለረዳው ሄኔሲፎሩ ለተባለ ሰው ሲሞት እንዲህ ሲል ጸልዮለታል በመጀመሪያ ለቤተሰቦቹ መፅናናትን ከተመኘ በኋላ 'በዚያን ቀን ከጌታ ምህረትን እንዲያገኝ ጌታ ይስጠው' ብሏል። ቅዱስ ዮሐንስም በመጀመሪያ መልዕክቱ እንዲህ ብሏል 'ማንም ወንድሙን ሞት የማይገባውን ኃጢያት ቢያደርግና ቢያየው ይለምን' ይላል። ደግሞ እንዲህ ስንል ነው የምንጠይቀው 'አቤቱ አገልጋይህን በያዕቆብና በአብርሃም፣ በይስሐቅም እቅፍ አስቀምጥልን' ነው የምንለው።

"እኔ የማምነው የእምነት አስተምህሮ ውስጥ ለሙታን መጸለይ ትልቅ የእምነቱ መገለጫ ነው። እንደምታውቂው ሁለት ዓይነት ሞት አለ። ክርስቶስን አምኖ መሞትና ሳያምኑ መሞት። ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳለው 'ትንሳኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፤ ሕያው የሆነ የሚያምንብኝ ሁሉ ለዘላለም አይሞትም' ስለዚህ የምንጸልየው ለሙታን ሳይሆን ለሕያዋን ነው ማለት ነው።" ሰንፔር ፊት ላይ የመደበር ምልክት ይታያል። እንደ ፈራችው ክበቂ በላይ እኘኙ ቀጠለ።

"የሞቱትን ስናስታውስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን አንድነት የሚጠበቅበት ስለሆነ ነው።"

"ሃሃ... ደግሞ ይሄ ምን ማለት ነው?"

"ጥሩ... ቤተ ክርስቲያን ምድር ላይ ሳይሆን ሰማይ ላይም አለ። ምክንያቱም የክርስቲያን አገሩ በሰማይ ነው። ስለዚህም እላይ ካለው አገራችን ጋር አንድነት የምንፈፅመው በክርስቶስ አምነን ከሞትን ብንሞትም ሕያው ነን። በዚህ ሕያውነት ውስጥ ከምድር እስከ ሰማይ ድረስ በጸሎት ሰንሰለት ወደ አንድነት እንመጣለን።

"በዚህ ጊዜ ብሔር፣ ቋንቋ፣ ዘር፣ ቦታ መሰል ልዩነቶች ጠፍተው ወደ አንድነት ይመጣሉ። መቼም የታወቀ ነው እግዚአብሔር የሙታን አምላክ እንዳልሆነ። ክርስቶስም 'እኔ የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ አይደለሁም' ብሏል። ጨምሮ ካልሺኝ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ሲል ስለ አብርሃም ተናግሯል 'አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ተመኘ አየም ደስም አለው' ስለዚህ ሙታን ምንም አያውቁም ማለት አይደለም። እንኳን አብርሃም ቀርቶ ሲኦል ያሉትም ያውቃሉ ለዚህ ደግሞ 'ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞተ በኋላ ሲኦል ገብቶ ሠላም ሰበከላቸው' ይላል መጽሐፍ ቅዱስ።"



Scanned with CamScanner

ሰንፔር መሸነፉ አልተዋጠላትም ስለዚህ መናገር ጀመረች "መጽሐፍ ቅዱሱን እንደ ምኞትህ እያስኬድከው ነው። ለዛ ነው ጥቅሶችህ ሁሉ እውነት የመሰሉህ። ሌላው ግን ለሙታን ተጸልዮ ወደ ገነት ማስገባት ከተቻለ ምድር ላይ መልካም ሥራ መሥራት ምን አስፈለገ? በሕይወት እያሉ የልብን ሠርቶ ከዚያ ቤተ ዘመድ ጸልዮ ገነት ያስገባሀል እንደ ማለት ነው። ያርግላችሁ!" ሰንፔር ትንሽ እንደማላገጥ ብላ ሳቀች።



Scanned with CamScanner

## ምዕራፍ ፬

ሮደስና ሰንፔር የተዋወቁት በተሳሳተ የስልክ ጥሪ ነው። ይህ የተሳሳተ የስልክ ጥሪ የተደረገው በሮዳስ ጓደኛ ቤት ነው። ሮዳስ የመጀመሪያ ዓመት የሐዋሳ ዩንቨርቲ ትምህርቱ ጨርሶ ለእረፍት አዲስ አበባ መጥቶ ነበር። ሁሌም እንደሚያደርገው ጓደኛው ሰርጸ ቤት ሄዶ ስለ ዓመቱ የዩንቨርስቲ ቆይታ እየተጫወቱ ነበር።

ሮዳስ ስለ ሐዋሳ ሰርጸ ስለ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ሕይወት እየተጨዋወቱ ሳለ የነሰርጸ ቤት ስልክ መጮህ ጀመረ። ሰርጸ ስልኩን አነሳውና ሁሌ እንደሚያደርገው በትህትና እና በአክብሮት "ሄሎ?" አለ።

ከወዲያኛው ጫፍ ግን መልስ አልነበረም። ሰርጸ በድጋሚ "ሄሎ?" አለ። መልስ አልነበረም። ሰርጸ ቆጣ ብሎ "ሄሎ! ሄሎ! ሄሎ!" አለ። ከወዲያኛው የስልክ ጫፍ የሚሳሳቁ የእንስቶች ድምፅ ይሰማ ጀመር። ሰርጸ በንዴት ስልኩን ዘጋው። ድጋሚ ስልኩ ጠራ። ሰርጸ ስለ ተናደደ ስልኩን ማንሳት አልፈለገም። '...ጢርርር... ጢርር...' የሚለው የስልኩ ጩኸት በቤቱ ውስጥ ማስተጋባቱን አላቆመም።

ሰርጸ ስልኩን ላለማንሳት ሮዳስን እያየ "ምን ላይ ነበር ወሬያችንን ያቋረጥነው?" አለ።

ሮዳስ "ለምን ስልኩን አታነሳውም?" አለው።

ሰርጸ በስጨት ብሎ "እባክህ ተዋቸው የሆኑ ጨጩዎች እያሾፉ ነው። ሙድ ሲይዙ ነው" አለ ቆጣ ብሎ

ሮዳስ ከተቀመጠበት ሶፋ ተነሳና "ታዲያ እኛስ ብንደበርባቸው ምን ይለናል? አይቆጥርብን ይቆጥርባቸዋል እንጂ?" ብሎ ወደ ስልኩ ሲሄድ ድብልብሏ የቤት ሠራተኛዋ ከደጅ ወደ ሳሎን ስልኩን ለማንሳት ስትገባ ሮዳስ ቀድሞ ስልኩን አንስቶታል።

ሮዳስ ሳቅ እያለ "ሄሎ" አለ። ሰራተኛዋ ዞራ ወደ መጣችበት ተመለሰች።

ተስረቅራቂ የልጅ ድምጽ "ሄሎ" ሲል ተሰማ

"ሄሎ ማን ልበል?"

ድጋሚ ተስረቅራቂው የልጅ ድምፅ ሳቅ ባፈነው ቃና "ሄሎ" አለ

ሮዳስ የሳቅ ድምጹ ሲሰማው ስልኩን ሳያፍን ጮክ ብሎ "አንተ እውነትም ጨጩዎች ናቸው እያለመጡብን ነው" አለ።



Scanned with CamScanner

ሰርጸ "'ባክህ ተዋቸውና ና?"

ከስልኩ ውስጥ "ማሪቱ አለች?" የሚል ፍርሃትና ሳቅ ያፈነው ድምጽ ተሰማ

ሮዳስ ነገሩን እንደቀልድ ስላየው እንደመቀሰድ ብሎ "ማሪቱ የለችም ግን ማርይሁን ይኖራል" አለ፡፡

"በቃ ማር ይሁንን አቅርብልን?" አለች ያችው የልጅ ድምፅ ያላት እንስት

"ነኝ ማን ልበል?" አለ ሮዳስ ፈጠን ብሎ

"ሠላም ነው ማር ይሁን ምን እያደረክ ነው?" አለች ድምፀ ቀንጆዋ ልጅ

"ይሄው አንቺን እያወራሁ እገኛለሁ፤ አንቺስ?"

"እኔም አንተን እያወራሁ ነው" ብላ ድምጸ ቀንጆዋ ልጅ መለሰች፡፡ ሮዳስ ሊመልስላት ሲል ስልኩ ተዘጋ፡፡ ሮዳስ የደዋይዋን ድምፅ በተደጋጋሚ በአዝነ ልቦናው እያሰበ ማድነቅ ጀመረ፡፡ ውስጡ 'በደወለች፣ በደወለች፣ በደወለች' የሚል ስሜት መጣበት፡፡ ይህን እያሰበ ባለበት ቅጽበት ስልኩ በድጋሚ ጠራ፤ ሮዳስ ድንግጥ ብሎ ስልኩን አነሳው፡፡ ሰርጸ በአግራሞት ሮዳስን እያየ ሳቀበት፡፡

"ሄሎ!" አለ

ጎርነን ያለ የእንስት ድምፅ "ሄሎ" አለ

ሮዳስ ከወዲያኛው የተለየ ድምጽ ሲሰማ ፊቱን ቋጠር አደረገ፡፡ ሰርጸ ሌላ ሰው እንደደወለ ገባውና ስልኩን ሊቀበለው ተነሳ

"ሄሎ አቤት ማን ልበል" አለ ሮዳስ ድምፁን ትህትና አላብሶ

"ሄሎ ማሪቱን ፈልገን ነበር ማር ይሁን..." አለችና ሳቀች፡፡ ትንሽ ጎርነን ያለ ድምፅ ያላት ልጅ፡፡ የባለ ጎርናናዋን ሳቅ ተከትሎ ሮዳስን ቀድማ ያናገረችው ልጅም ሳቅ አኩል ተሰማ፡፡ ሮዳስ ደዋዮቹ ሁለት እንደሆኑ አወቀና "ማሪቱ እንኳ የለችም እኔ ግን አለሁ" አለ፡፡ ፊቱ በኩርፊያ ከመጠየም ወደ ደስታ ተቀይሮ እየበራ፡፡

ድመጸ ቀንጆዋ ልጅ ስልኩን ተቀብላ ማውራት ጀመረች "እንዴት ነህ ማር ይሁን? አሁን ያናገረችህ ጓደኛዬ ነች፡፡ ይቅርታ ስልክ ሰርቀን ስለምንደውል ሰው ስለመጣብን ነው የዘጋነው"



Scanned with CamScanner

ሮዳስ ከድምፇ ማማር ታማኝነቷ እንዲሁም በስልኩ ውስጥ የልጅ ድምጽ ቢሰማም እርጋታዋን ወደደው። ከዚያም ለረዥም ሰዓት ከስንፔር ጋር የባጥ የቆጡን ያወሩ ጀመር። ስንፔር በጊዜው የእጅ ስልክ ስላልነበራት ሮዳስ የራሱን የእጅ ስልክ ሰጣትና ተለያዩ።

-----//-----

## ኬንያ ናይሮቢ

ቀብጥባጣዋ ትርሲት ሽሚዝና ቀሚሱ የተያያዘ ቱንጠኛ ልብስ አድርጋለች። ተሰብሳቢዎቹ ሰረቅ እያደረጉ ያይዋታል። በሱሪና ጥብቅ ባለ ቀሚስ የሚንቀጠቀጠው መቀመጫዋ ዛሬ አደብ ገዝቶ በለበሰችው ቀሚስ ውስጥ ክትት ብሏል። በተመስጦ የመርሐዊን ገለጻ እያዳመጠች ነው። ከእሷ ጎን ዘላለም እና ዳንኤል ያሉ ሲሆን፣ ከትርሲት ፊት ለፊት ባለው ወንበር ላይ ግሩም እና ሄራሞ ተቀምጠዋል። ሁሉም በመርሐዊ ንግግር የተመሰጡ ይመስላል።

"ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን ክርስቶስን የማይገልጡ ስብከቶች፣ መዝሙሮች፣ ትንቢቶች፣ ልምምዶችና ሥርአቶች ቤተ ክርስቲያንን አጨናንቀው የሉም ወይ?" አለና መርሐዊ ታዳሚዎችን ቀና ብሎ አያቸው። ሁሉም በስሜት ተመስጠው እያዳመጡት ነው። መርሐዊ ጎንበስ አለና ኮምፒውተሩን እየተ አድርጎ ንግግሩን ቀጠለ።

"የክርስቶስን ብቸኛ ቤዛነት በገሀድ የሚቃወም፣ ወንጌልን የጋረዱና የምእመኑን ሥነ ልቦና ያደነዘዙ ባዕድ ትምህርቶች የተጫኑባቸው ድርሳናት እና ገድላት በክርስቶስ ቤት ምን ይሠራሉ? መልሱ ምንም ነው። ምንም! ስለዚህም እናንተ ልክ ማርቲን ሉተር እ.ኤ.አ ጥቅምት 31 በ1517 ዓ.ም በሳክሶኒ በሚገኘው የዊተንበርግ ቤተ ክርስቲያን በር ላይ በመዶሻ የጠረቀውን ዘጠና አምስት ነጥቦች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መቅደስ ላይ እንስታችሁ ልትጠርቁት ግድ ነው። ተሐድሶ የተጋረደውን ክርስቶስን በራሱ በቃሉ መግለጥ ነው እንጂ ሌላ አይደለም።

"ለክርስቶስ መነቀል ያለበት አዋልድ መጽሐፍት ካለ ይነቀላል፤ ለክርስቶስ የሚስተካከልና የሚታረም ቅዳሴ ካለ ይታረማል፤ ለክርስቶስ እሮጌውን ሁሉ አንስተን በእሱ በራሱ በቃሉ ብቻ እንደ አዲስ ፍጥረት አዲስ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እንሆናለን!" በዚህ ንግግር ሁሉም ስሜታዊ ሆኑና አንድ ላይ "አሜን!" ብለው አጨበጨቡ። ሩቢዮ ብዙም አማርኛ ስለማይሰማ ሰዎቹን እንዲህ ስሜት ውስጥ የከተታቸው ምን ቢላቸው ነው ብሎ በአድናቆት መርሐዊ ላይ አፈጠጠበት።

ስብሰባውን በዋናኝነት እየመራው ያለው ዶክተር ቀሞስ አባ መርሐዊ ነው። እለቃ መሠረት ከአሜሪካው ቦስተን ዩንቨርስቲ የትምህርት እድል እንዲያገኝ ከደብረ-አባይ

ቅዳሴ ቤት ነው የወሰደው፡፡ አብረውት አሜሪካ ቦስተን የነገረ መለኮት ኮሌጅ ከገቡት ኢትዮጵያውያን ይበልጥ በፍጥነት በተሐድሶ እንቅስቃሴ የተወሰደው መርሐዊ ነበር።

የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቱን በቦስተን ዩንቨርሲቲ ሲማር 'የተሐድሶ እንቅስቃሴና ውጤቱ በአውሮፓ' በሚል ርዕስ ላይ ነው የመመረቂያ ጥናቱን የሠራው፡፡ ቀጣይ የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያውን እንዲሁ በሐርቫርድ ዲቪኒቲ ትምህርት ቤት ሲማር 'የተሐድሶ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን' በሚል ርዕስ ላይ ነው የሰራው፡፡ በዚያ ላይ በተለየ ሁኔታ አፍቅሮተ-አርዮስ የተጠናወተው ነው፡፡ "አርዮስ ጠቢብ ነው ሊወገዝ አይገባውም" እያለ በመከራከር ይታወቃል፡፡

አርዮስ "ኢየሱስ (ወልድ) በእግዚአብሔር (በአብ) የተፈጠረ ፍጡር ነው" ብሎ የሚያምን በአራተኛው ክፍለ ዘመን የተነሳ ሰው ነው፡፡ ይህንን ሰው ነው መርሐዊ በፍቅር ነው የሚወደው፡፡ መርሐዊ አርዮስን እንዲህ ሲል ይገልጸዋል "ለእኔ አርዮስን የሚያክል የአቋም ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም፤ ለሀሳቡ መሳካት የሔደበት ርቀት፤ በጊዜው የነበሩትን ሊቃውንት የተፈታተነበት የእውቀት መራቀቅና ምጥቀት ነፍሴን ይገዛዋል" ይላል፡፡ እንደውም የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጽሑፉን "አርዮስ ትክክል ሊሆንባቸው የሚችልባቸው መንገዶች" ብሎ ሊሠራ ነበር፡፡ ግን አማካሪውና ወዳጁ ሩቢዮ "ተው!" ብሎት ነው የተወው፡፡

መርሐዊ ለአርዮስ ወግና መከራከሩን የሚያውቁት ወዳጆቹ "መርሐዊ አርዮስን የሚደግፈው ለየት ለማለት ፈልጎ ነው፡፡ በቃ የተጠላና የተወገዘን ሰው በማድነቅ እሱም አድናቆትን ለማግኘት ሲል የሚያስነሳው አቧራ ነው እንጂ በክርስቶስ አምናለሁ፤ ስለ ክርስቶስ ሁሉ ነገር እንደ አዲስ ይሁን እያለ የሚቆረቆር የሚጨነቅ ሰው መልሶ የአርዮስ አድናቂ መሆን ትንሽ እውነታን መጋፋት ነው" ይሉታል፡፡

በመንፈሳዊ እውቀቱና በችሎታው የማይታማው መርሐዊ ብዙዎቹ በተክለ ሰውነቱ ይገረማሉ፡፡ 'መንፈሳዊ ሰውም ሆነ የምሁር አቋም የለውም' ይላሉ 'ከዚያ ይልቅ በርገር ነጋዴ ካልሆነም ሀሳብ የማያበዛ ባለ ሀብት ነው የሚመስለው' ይሉታል፡፡

ምክንያታቸው ደግሞ ከበሮ የሚያክለው ቦርጩ ነው፡፡ ቁመቱ ሜትር ከሰባ ስድስት ቢሆንም ወፍራም ሰውነቱ ስለዋጠው ኩሩሩ አስመስሎታል፡፡ አንገቱ ብዙም ስለማይታይ ትከሻ ብሎ ጭንቅላት ይባል ይሆን እንደው እንጂ አንገት አለው ብሎ ደፍሮ ለመናገር የመርሐዊን አንገት እንደ እማኝ አይቶ ለማሳመን ስለሚከብድ 'የሰው ልጅ ሁሉ አንገት አለው' በሚለው አመክንዩ ብቻ መከራከር ነው የሚቀልው፡፡

መርሐዊ ሲናገር እንኳ ብዙ መተንፈስ ይጠበቅበታል፡፡ ከዚያ በተረፈ ጠይም ፊት ያለው፤ ሲያዩት ሰርሳሪና አንዳች ነገር የሚፈልግ ዐይን አለው፡፡ ቀጥ ያለ አፍንጫ ቢኖረውም ስልካካ እንዳይባል ፊቱ ላይ ግራና ቀኝ የተንዘላዘሉት ወፍራም ጉንጮቹ ሸፍነውታል፡፡ ቢሆንም ፈገግታ የተላበሰና ገራገር የሚመስል ፊት ነው ያለው፡፡



Scanned with CamScanner

ከአጠገቡ ደግሞ የቀድሞ አስተማሪው የአሁን ደግሞ የቅርብ ወዳጁን ዶክተር ሩቢዮ አለ። መርሐዊ ዋሽንግተን ዲሲ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሆኖ የሚያገለግል ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ በተጋባዥ መምህርነት ሌሎች ቦታዎችም ያገለግላል። ከዚያ በተረፈ የሩቢዮና የመርሐዊ ቅርበት ግን ለተመለከተው ሰው ከባልንጀርነት በላይ ይመስላል።

ሩቢዮ ቀጭንና ረዥም አሜሪካዊ ነው። ዓይኑ ሰማያዊ ሲሆን ጸጉሩ ቢጫ ሆኖ በአጭሩ ተቆርጦታል። ጥቁር ግማሽ ማዕቀፍ ያለው ማራኪ መነፅር ያደረገ ሲሆን፤ ከመነጽሩ መስታወት ጀርባ አሁንም አሁንም ክፍት ዘጋ እያለ ሲያርገበግበው ሽፋሽፍቱ ውስጥ የሚታዩት ዐይኖቹ ልክ እንደ ሽማኔ መወርወሪያ በፍጥነት ግራ ቀኝ የማለት አባዜ አለባቸው፤ ፈገግ ሲል ጥርሱ ቢጫ እና በልኩ ያልተደረደረ ነው። ቢሆንም ሩቢዮ ፈግግታውን ሳይሰስት ለሁሉም የሚለግስ ሰው ነው።

መርሐዊ በአሰቃ መሠረት ከደብረ አባይ ከተወሰደ በኋላ አራት ጊዜ ኢትዮጵያ እየተመላለሰ ቤተሰቦቹን ጠይቋል። አራተኛው አመጣጡ እንኳ ኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሄደ ያለውን የተሐድሶ እንቅስቃሴ እንዲመራ አውሮፓ ካለው የተሐድሶው ክንፍ ተልእኮ ከተሰጠው በኋላ ነው። የመጣው ደግሞ ከአራት ዓመት በፊት ደቂቀ እስጢፋኖስ ከተባለውን ሕቡዕ ድርጅት ጋር ለመገናኘት ነው።

በዚያውም የኢትዮጵያ ሚሊኒየም ስለ ነበር በአዲስ መንፈስ፣ ዕቅድ እና መመሪያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን የማደስ ሥራ ለማነቃቃት ነበር። ኢትዮጵያ በተገኘበት ሰዓት በተጋባዥ መምህርነት በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪዎችን የነገረ-ክርስቶስ (ክሪስቶሎጂ) ትምህርት ሰጥቷቸዋል።

ብዙዎች በትምህርቱ ተደምመው ነበር። በጣም ወፍራም ስለሆነ ይሁን ወይም ከእሱ ይወጣል ብለው ባልጠበቁት ቀጭንና ዜማዊ ድምፁ ያስደንቃቸው ብቻ ትምህርቱ መስጫቸው ነበር። ስለ ክርስቶስ የሚሠጠው ትንታኔ፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚያጎርፈው ጥቅስ ለዚያውም አንዱን ከአንዱ እያገናኛ ሲያቀርብ፣ ታሪክ ሲጠቅስ፣ በግዕዝ ሲናገር ተማሪዎቹ እንዲደነቁና እንዲያደንቁት አደረጋቸው።

ብዙ ተማሪዎችም በግል ሲያገኙት እንደሚፈልጉ ነግረውት ኢሜይሉን ተቀብለውታል እሱም ደስ እያለው ሰጥቷቸዋል። ከእነሱም ውስጥ አሁን ለኬንያው ስብሰባ ከመጡት ውስጥ ይገኛሉ።



Scanned with CamScanner

እንኳን ሴት እና ወንድ ሆነው ለሄዱ ፍቅረኛሞች ቀርቶ ብቻውን ለሄደ ሰውም ፍቅረኛህን አምጣና ተዝናና የሚል የሆነ ሆድ የሚያባባ አንዳች ነገር አለው፡፡

ቤቱ ድብዝዝ ባለ ቀይ ብርሃን ተንቆጠቆጧል፤ መቀመጫው ቀይ ሶፋ ሲሆን ከፊት ለፊቱ በቀይ ካርድ ውስጥ ያለ ሻማ በርቷል፤ ከሻማው ጎን ያልፈነዳ እንቡጥ ፅጌሬዳ አበባ በውብ ብርጭቆ ውስጥ ሆኖ ለቤቱ ተጨማሪ ድምቀት ሆኗል፤ ዲጄው ተጨንቆና ተጠቦ በዓለም ላይ አሉ የተባሉትን የፍቅር ዜማዎች እያጫወተ ነው፡፡

ሮዳስና ሰንፔር ይህን ቤት ይወዱታል፡፡ ብዙ ጊዜ ራታቸውን እየመጡ ያመሹበታል፡፡ ዛሬም ጣት የሚያስቆረጥመው ራት ከበሉ በኋላ ወይናቸውን እየተጎነጩ ልፊያና ቀልድ ጀምረዋል፡፡ ነገረ ሥራቸው ሁሉ እንደ ፍቅረኛ ቢሆንም ግን ፍቅረኞች የሚለውን ማዕረግ እርስ በእርስ አላፀደቁትም ነበር፡፡

ስለዚህም ሮዳስ አንድ መላ ዘየደ፡፡ ሮዳስ የሰንፔርን ውብ ከንፈር አፍጥጦ መመልከት ጀመረ፡፡ ሰንፔር የሮዳስን እይታ ችላ ብላ ጨዋታዋን ብትቀጥልም ሮዳስ ሆን ብሎ እንደ እንጆሪ በሊፒስቲክ ወዝቶ ግመጡኝ ግመጡኝ የሚለውን ከንፈሯን በዐይኑ መሳም ጀመረ፡፡ ሮዳስ የሰንፔርን ዐይንና ከንፈር እያፈራረቀ እየተመለከተ ምራቁን ሲውጥ የጉሮሮው እንቅስቃሴ የሚጮህ ድምጽ አወጣ፡፡

"ምንድነው?" አለች ሰንፔር ማፍጠጡና የጉሮሮው ጩኸት ሲበዛባት ሳቋ አፍን እያደረጋት

"አይ ምንም ማስቲካ አስተኛኝክሽ ደስ ይላል" አላት፡፡ ድምጹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ፡፡

"አቤት! አካበድክ ትናንት ከዚህ በተለየ ሁኔታ አኝክ ነበር?" አለች ሰንፔር ሳቅ እያለች

"እኔንጃ የዛሬው ማስቲካሽ ደግሞ ለየት ይላል ጠረኑ ራሱ ደስ ሲል" አለ ሮዳስ

"ኡው እንደውም አስታወስከኝ ማስቲካውን ሳንተም አምጥቼልሀለሁ፡፡ አክስቴ ከውጪ ስትመጣ ይዛልኝ መጥታ ነው" ብላ ቦርሳዋን መበርበር ጀመረች፡፡ ሰንፔር ቦርሳዋን እየበረበረች ፊቷ ቅይርይር አለ፡፡

"ምነው?" አለ ሮዳስ የፊቷን መቀያየር አይቶ

አሁንም አጎንብሳ ቦርሳዋን እየበረበረች "አይ ምንም ማስቲካውን እረስቼው መጥቻለሁ መሰለኝ፡፡ አጣሁት፡፡ ሲያናድድ በናትህ..." አለች በስጨትጨት እያለች፡፡

"ኧረ ችግር የለውም አሁንም ቢሆን ትሰጪኛለሽ" አላት ሳቅ እያለ



Scanned with CamScanner

"አልገባኝም ነገ እዎ እመጣልሀለሁ ለአሁኑ አለመያዜ ግን በጣም አናድዶኛል"

"ኧረ አትናደጂ አሁን ትሰጪኛለሽ እያልኩሽ"

"ማለት? እረሳሁት እያልኩህ.... እያሾፍክ ነው?"

"ኧረ አይደለም ከምታኘኪው ላይ ለምን አትሠጪኝም?"

"ያምሀል እንዴ የታኘከ ደግሞ ምን ያደርግልሀል?"

"እንደውም እሱ አይበልጥብኝም ብለሽ ነው።" አላት ሮዳስ እጁን እየዘረጋ

"አንተ የምርህን ነው?"

"እዎ የምሬን ነው ሰን"

"እኔ ምን አገባኝ እንካ" ብላ ማስቲካውን ከአፏ አውጥታ በእጇ ልትሰጠው ስትል

"አይ! አይ!" ሮዳስ በእጁ የአልፈልግም ምልክት እያሳየ "አይ! ከእጅሽማ አልቀበለም ከዚያው ካለበት ነው እንጂ" አለ

ሰንፔር እንደ መሽኮርመም እንደመሳቅ እያለች በእጆቿ ወደ ከንፈሯ እያመለከተች "ማለት ከዚህ ከከንፈሬ?" ብላ ሳቅ አለች።

"አይ እንደሱማ አይሆንም"

ሮዳስ በተራው እየተቆጣ "ነው? ተይው በቃ ተይው" ብሎ የውሸት አኮረፈ.

"አንተ የምርህን ነው?" አለች ሰንፔር ሳቋ እየመጣ። ሮዳስ እንደ አኮረፈ ሰው ዝም አለ። ለቀልድ ያህል ሮዳስ ኩርፊያውን እንዲተው ብላ ማስቲካውን ጥርሷ ላይ አንጠልጥላ "እንካ በቃ" አለችው። ሮዳስ ዞሮ ሲያይ ሰንፔር ማስቲካውን ጥርሷ ላይ ይዛ እየሳቀች ነው። የት እንዳመጣው ባልታወቀ ድፍረት በማስቲካ እወስዳለሁ ሰበብ የሰንፔርን ከንፈር ከነማስቲካው መጠጠው።

የሮዳስ የልብ ምት ጨመረ። እግሩ ንፋስ እንደሚያወዛውዘው ቄጤማ ብርክ ብርክ አለበት። ፊቱ ከመጠን በላይ ወዛ። እጆቹም ላብ ጥምቅ አደረጋቸው። ሰንፔርም በድንጋጤ ክው ብላ ዝም ብላ ከንፈሯን ተሳመች። ውስጧ ደስታና አዲስነት ተሰማት። ለሰከንዶች እራሷን እንደመሳት አደረጋት። የከንፈር ህጋን ለሮዳስ ሰጥታ እሷም የእሱን ከንፈር ከየትኛዋም እንስት ቀድማ ቀመሰች። ሮዳስ በተደጋጋሚ ምራቁን እየዋጠ ጭምቅ አድርጎ ሳማት።



Scanned with CamScanner

ከስሜት ማዕበል ስትወጣ ሮዳስን በስሱ ገፋ አድርጋው ከንፈሯን ጠረገችው። ሮዳስም እንደመደንገጥ ብሎ ከንፈሩን ከሰንፔር ከንፈር ነቀለና የሰንፔርን ዐይን ዐይኗን ያያት ጀመር። አልተቆጣችም ቢሆንም ደስታዋንም አላሳየችም። እራስዋን ተቆጣጥራ አቀረቀረች።



Scanned with CamScanner

# ምዕራፍ ፮

## ኬንያ ናይሮቢ

በስታንሊ ሆቴል የሚደረገው ስብሰባ ዛሬም ቀጥሏል። ዛሬ ሩቢዮ የለም። ጉባዔው በመርሐዊ ብቻ እየተካሄደ ነው። በፕሮጀክተሩ ላይ 'የተሐድሶ አካሄድ' ውጤቱ ይላል።

መርሐዊ ንግግሩን ጉሮሮውን ከጠራረገ በኋላ ንግግሩን ጀመረ "ተሐድሶ ከላይ ወደ ታች ወይስ ከታች ወደ ላይ የሚለውን ጥያቄ ማየት ግድ ይለናል። የትኛውንም አይነት ትክክለኛ ጥያቄ ብንይዝ፤ ምንም አይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመክንዮ ስላመጣን ከግብ እናደርሳለን ማለት አይደለም።

"ከሥላሴ ውጪ ለሌላ ለማንም አልሰግድም ያሉት አባ እስጢፋኖስ፤ የተሐድሶ የንጋት ኮከብ የተባለው ጆን ዊክሊፍ ከቃሉ የተጋጨችውን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ለማስታረቅ የጣረው፤ 'ሁሉ ነገር በመጽሐፍ ቅዱስና በቃሉ ይዳኝ' ያለው ጆን ሑስ ለምን እንዳልተሳካላቸው?" ቀና ብሎ ትምህርቱን የሚከታተሉትን ተመለከታቸው። ሁሉም መልሰው አፈጠጡበት። መልስ የሚሰጠው ማንም እንደሌለ ስለገባው ንግግሩን ቀጠለ።

"የተሐድሶ ጥያቄ ንድፍ፣ መርሕና አካሄድ ይጠይቃል። እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ሰዎች ተሐድሶ ያልተሳካላቸው ተሐድሶውን ከስር ስለጀመሩ ነው። አቅሙ፣ ጉልበቱ፣ ስልጣኑ ካላቸው ሳይሆን በተቃራኒው በአለቆች ትእዛዝና መልካም ፈቃድ ከሚኖረው ከምእመን ወይም ከተራ አገልጋይ ስለጀመሩ ነው።

"ስኬታማውን ማርቲን ሉተርን። የተሐድሶውን ጥያቄ ብቻውን ሆኖ ቢጠይቅም፤ እከሌ ያግዘኛል ብሎ ባያምንም ባልተጠበቀና ባልታሰበ መንገድ እግዚአብሔር በፖለቲከኞች በኩል ሆኖ የጀርመንና የእንግሊዝ ነገስታትን ረዳት ሰጠው። በተለይ ጀርመን ለሉተር የማስተማር ፈቃድ ስትሰጠው ታላቁ ተሐድሶ በዓለም ለዓለም እንደ ፀሐይ አበራ። እንደ መስከረም አደይ አበባ በዓለም መስክ ላይ ደመቀ።

"እንዲያ ባይሆን ኖሮ የሉተር እጣ ፋንታ እንደ አባ እስጢፋኖስ ተወግሮ መሞት፤እንደ ደቀመዝሙሮቻቸው አፍንጫን መፎነን፣ በጅራፍ መገረፍ ብሎም በድንጋይ መወገርን ያስከትላል። እንደ ጆን ዊክሊፍ ውግዘትና ሞት፤ ሞቶ አላረካ ሲል አጽማችሁ ከተቀበረበት ተነስቶ መቃጠልን፤ እንደ ጆን ሑስ በቁም መቃጠልን ብሎም ታሪክ እንደሌለው እንደ አልባሌ መሆን ነው ትርፉ።" ተሰብሳቢዎቹ ይህን ሲናገር በልባቸው የመዘግነን ስሜት ተሰማቸው።

"ይህ ዘግናኝ ድርጊት እልቂትና መከራ የደረሰው ስለ ወንጌል ቢሆንም በአካሄድ ስህተት ነው። ምክንያቱ ልክ ቢሆንም መንገዱ ግን ልክ አልነበረም።" መርሐዊ ቀና ብሎ አያቸው። ፊታቸው ላይ መጨነቅ አየ። እየሰሙት እንደሆነ ካረጋገጠ በኋላ ንግግሩን ቀጠለ።

"ስለዚህ ጅማሬያችሁ ከታች ወደ ላይ ሳይሆን ከላይ ወደ ታች ይሁን። በእርግጥ ከስንት አንዴ ከታች ወደ ላይ ይሳካል። በዚህም መንገድ የተሳካለት ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የድሮውን የብሉይ ኪዳን ወደ ክርስትና ሲያድሰው ከቤተ መንግሥት አልጀመረም። ከቤተ መቅደስም እንዳይጀምር ፈሪሳውያን እና ሰዱቃውያን የሚያስቀርቡ አልነበሩም። ስለዚህ የራሱን ቤተ ክርስቲያን መሠረተ። የራሱን ሰዎች መረጠና በዓለም ላይ ወደር የማይገኝለትን ተሐድሶ አመጣ። ይህ በጣም ከባድና እንደ ክርስቶስ መሆን ይጠይቃል። እሱ ደግሞ አይቻለንም።

"ከላይ ወደ ታች ስላችሁ ግዴታ ከሲኖዶስ ላይሆን ይችላል ነገር ግን እስኪ ዞር ብላችሁ ሌላ ነገር እዩ። አንድ ሰው ሲኖዶስ አባል ከመሆኑ በፊት ምን ማለፍ አለበት? አንድ ሰው ሐገረ ስብከት ከመግባቱ በፊት ከየት ይነሳል? ቄስ፣ ዲያቆን፣ መምህር፣ መሪጌታ፣ ቆሞስ መሆን አለበት። እንዚህ ሁሉ መነሻቸው የት ነው? ከትምህርት ቤት ነው።

"ስለዚህም ምንጨን መቆጣጠር። አዲስ አበባ ያሉትን ሁለቱን ቅድስት ሥላሴ እና ሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ኮሌጅን እንዲሁም መቀሌ የሚገኘውን ፍሬምናጦስ ኮሌጅን መቆጣጠር። ይህን በተቻለን መጠን አድርገነዋል ወደፊትም እናደርገዋለን። እነዚህ ኮሌጆች ውስጥ የሚማሩትን ደቀ መዝሙሮች ከተቆጣጠርን ነገ ሲኖዶስ፣ ቤተ ክህነት፣ ሐገረ ስብከት፣ አብነት ትምህርት ቤት... የመሳሰሉትን ስለሚረከቡ ተሐድሶው ስላማዊና ቀላል ያደርግልናል።

"ሌላው ተሐድሶውን እንድናውጅ የሚረዳን መንግሥት አለ። መንግሥት ድጋፍ እንዲሰጣችሁ ማድረግ መቻል አለባችሁ። በዚህ ዓለም ላይ ሥልጣን ቀላል ነገር እንዳይመስላችሁ። ሥልጣን ባታውቁም አዋቂ ያደርጋችኋል፤ ብታረጁም ልጅነትን ይሰጣችኋል፤ ሥልጣን ውበት፣ ህይወት፣ ፍቅር፣ ትዳር፣ ህልውና የሁሉ ነገር ፈቃድ ማግኛ ትልቅ መሳሪያ ነው። ስለዚህ ይህን ሥልጣን ለአላማችሁ እንዴት እንደምታውሉት እስኪ አውጠንጥኑት?

"አውሮፓና አሜሪካ ያለው አያሳስባችሁ ምክንያቱም ቀድሞ የተመቻቸ ሥልጣን አለን። እሱም የአሜሪካውን ስደተኛውን ሲኖዶስ መጠቀም እንችላለን። አሜሪካ ያለው የተሰደደው ሲኖዶስ ከአገር ቤቱ ሲኖዶስ ጋር ከፍተኛ ግጭት ስላለበት ለመንገዳችን ይመቸናል። ስለዚህ የውጪውን የኦርቶዶክስ ጉዳይ ለእኛ ተውት ቀላል ነው።" መርሐዊ ውስጣዊ ደስታ ተሰማው።



Scanned with CamScanner

---------//---------

“ልዩነት በፍቅር ውስጥ መቼ እንደሚበቅል የማይታወቅ ዘር ነው፡፡ በተለይ የሃይማኖት ልዩነት በፍቅር ውስጥ ለዚያውም እንደ ኢትዮጵያ ሳለች አገር ትዳር ማለት ዘመድ አዝማዱ ጥብቅ ጉድኝነት በሚፈጥሩባት አገር፤ በልዩነት ለመኖር መወሰን በየትኛውም ሰዓት ሊፈነዳ የሚችል ቦንብ ቀብሮ ከሞት ያልተናነሰ እንቅልፍ ለመተኛት እንደመሞከር ነው፡፡

“ፍቅር በልዩነት ውስጥ አብሮ መኖርን ያስችል ይሆናል እንጂ ልዩነትን አያጠፋውም፡፡ ልዩነት በፍቅር ውስጥ ሙሉ ለሙሉ በፍቅር ተተክቶ ወደ አንድነት ይመጣል ማለት ይከብዳል፡፡ ምንም እንኳ መዋደድ መፋቀር ቢኖርም ልዩነት ባ ባልታሰበና ባልተጠበቀ ሰዓት እንደ አረምም በፍቀር ዘር ላይ ያጎቆላል፡፡” እያለ የሃይማኖት ልዩነት በፍቅር ውስጥ ያለውን ተጽእኖ ሲገልፅ የነበረው ሮዳስ በፍቅር ተሸንፎ ከባዱን ውሳኔ ወሰነ፡፡ ልዩነትን፡፡

ሮዳስና ሰንፔር የፍቅር ግኑኙነት ሲጀምሩ ሮዳስ የሃይማኖት ጉዳይን ወደ ጎን ከፍቶ ብሎ ፍቅር አይሉበት ነበር፡፡ እሷን ከሚያጣ ምኑም ምንም ቢቀርበት ይሻለው በነበረ ሰሞን አንድ ቃል ገባ፡፡

ይኸውም “እምነትሽን እምነቴ ብዬ እቀበላለሁ ነገር ግን ሁሉንም ታስተምሪኛለሽ ብሎ፡፡ በቃላቸው መሠረት ሰንፔር ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ ስለ ሃይማኖቷ ምንነት፣ አስተምህሮና እውነት ታስረዳው ጀመር፡፡ ሰንፔር የፓስተር ልጅ በመሆኗ እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ታንጻ በማደጓ መንፈሳዊ እውቀቷ በጣም ጥሩ የሚባል ነው፡፡

ሮዳስም ከልጅነቱ ጀምሮ ሰንበት ትምህርት ቤት ዘማሪ ሆኖ ሲያገለግል ያደገ፣ ዩንቨርስቲ ሲገባም በግቢ ጉባኤ ውስጥ ነገረ መለኮት የተማረ የተማረ፤ መንፈሳዊ እውቀቱንም በማንበብ ያደበረ የሚያምነውን ያውቃል የሚባል አይነት ኦርቶዶክስ ነው፡፡

ቢሆንም የሰንፔር ፍቅርና የሃይማኖታዊ አስተምህሮዋ ወደ ራሷ ብቻና ብቻ እየወሰዱት መጡ፡፡ ሮዳስ ከራሱ ፍላጎትና ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቀረና ከሰንፔር እና ከፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን መገኘት ሆነ ስራው፡፡ የሰንፔር ፍቅር በሮዳስ ልብ ውስጥ እንደ ኅበዝ ገበሬ ሰብል በጥሩ ሁኔታ ሲያብብ፤ የፕሮቴስታንት አስተምህሮ ደግሞ በሰንፔር ገበሬነት፤ በሮዳስ ለምና ፈላጊ አእምሮ ውስጥ አዲስ ፍቅር እየጠጣ በፍቅር አበበ፡፡ ሰንፔርም በሮዳስ ፍቅር እንዲሁም እምነቷን እምነቱ አድርጎ በመቀበሉ ይበልጡኑ አፈቀረችው፡፡

ነገር ግን ከቀን ቀን ሮዳስ ውስጡ መጠየቅ ጀመረ፡፡ ሳይጠይቅ እንደ ህጻን ልጅ ሲማር የነበረው ሮዳስ ከአራት ወር በኂላ እየተቀየረ መጣ፡፡ አንዳንድ የፕሮቴስታንት

አስተምህሮዎች ከኦርቶዶክሳዊ እምነቱ ጋር እየተቃረኑ መጡበት። የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ቁጭ ብሎ የኦርቶዶክስን አስተምህሮ ማሰብ ማሰላሰል ጀመረ። ውስጡ ተረበሸ። ከራሱ ጋር 'የሰንፔር ፍቅር ወይስ እውነት ነው ያሳመነኝ?' ማለት ጀመረ።

እንዳለውም አልቀረ የልዩነት ዘሩ ባላሰበው ቀን በውስጡ አበበ። ያደገበት በልጅነትና በወጣትነት የያዛቸው ኦርቶዶክሳዊ የሃይማኖት አስተምህሮዎች ከአዲሱ አስተሳሰብ ጋር ልብ እና አዕምሮውን ሜዳቸው አድርገው ግብግብ ገጠሙ። ኦርቶዶክስነት ከተደበቀበት፣ ከተሸፈነበት መልሶ እየወጣ ይጠይቀው ጀመር።

ስለ እምነቱና ስላለበት የፍቅር ሕይወቱ ሲያስብ "አንዳንዴ ፍቅር ምንም አይነት አመክንዮ ለመስጠት እድል አይሰጥም" ማለት ጀመረ። "ስታፈቅር አመክንዮ ወይም ሕግ አይገዛህም። ከዚያ ይልቅ ያፈቀርከውን ለማግኘት ያለህ ጉጉት ነው ውሳኔህ። ተፈቃሪህን ያስደስተዋል የምትለው ምንም ነገር ትክክል ነው ብለህ ታምናለህ።"

ሮዳስ ፍቅር ከወሰደው ሩቅ መንገድ ቆም ብሎ ራሱን እየገዛ ስለ ሃይማኖት በድጋሚ መመርመር ጀመረ። ድሮ ሲማር የያዛቸውን ማስታወሻዎች ለራሱ ማጥናት እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ጀመረ። ሰንፔር እንደ ቀድሞው ስታስረዳው ፊት ለፊት ይጋፈጣት ጀመር።

ለወትሮ ዝም ብሎ "እሃ ለካ እንደዚህ ነው" እያለ ይቀበል የነበረው ሮዳስ "እይ እንደሱ አይደለም እኔ እንዲህ ነው የማምነው" እያለ መጣ። ሮዳስን በዚህ መንገድ የማታውቀው ሰንፔርን መናደድ ጀመረች።

"ሮዳስ ለምንድነው የምትከራከረኝ? ፍቅር እኮ የጀመርነው ቃል ገብተህልኝ ነው። ሃይማኖቴን ሃይማኖትህ አድርገህ ልትቀበል ነው። አንድ የጠየከኝ ነገር እንዳስረዳህና እንዳስተምርህ ብቻ ነው። ይህንም እያደረኩ ነው። አንተ ግን እየተከራከርከኝ ነው።" ትለዋለች በቁጣና በኃይል። ሮዳስም መልሶ በቁጣ ይመልስላታል "ያልመሰለኝን በግድ እንድቀበል ነው የምትፈልጊው? ካልገባኝ እጠይቃለሁ፤ ካልተዋጠልኝ አልውጥም፤ ካልመሰለኝ አልቀበልም ይሄ ቃል ከገባሁልሽ ጋር ምንም አይገናኝም" ይላል በቁጣ።

"ምን ማለት ነው? ሃይማኖትህን መቀየር ስትፈልግ እኔን ወደህ ሃይማኖቴንም በነጻ ተቀብለህ ነበር። የማስተምርህ አውቀህ እንድታምን እንጂ ተከራክረን ለመተማመን አይደለም። ዱሮ ያለ ክርክር ትቀበል ነበር። እኔ የሃይማኖት ክርክር ፈርቼ አይደለም ይህን የምልህ። መቀበልና ተከራክሮ መተማመን ለየቅል ናቸው።

"በተለይ ፍቅረኞች በሃይማኖት ጉዳይ ተከራክረው ለመተማመን ሲጥሩ ሁሉን ነገር በፍቅር ዐይን ስለሚያዩት ቅያሜና ቶሎ ቁጣ ውስጥ ይገባሉ። እኔና አንተም ወደ እዚያ እየሄድን ነው። መጀመሪያ ተከራክረኸኝ እንደምታምን ቃል አልገባህም። አሁን



Scanned with CamScanner

እየካድከኝ ነው። እምነት ደግሞ በማመን የሚገኝ እንጂ በክርክር የሚገለጥ ነገር አይደለም።" አለች ሰንፔር ቁጣና እልህ የሞሉበት ውብ ዐይኖቿ በእልህ ድፍርስርስ ብለው።

"ሰንፔር! እኔ አልካድኩሽም። ውስጤን በግድ ተቀበል አልለውም። እዕምሮዬ ጠየቀኝ። ለጠየቀኝ አእምሮዬ መልስ ካልሰጠሁ ደግሞ ያመኛል። ታውቂያለሽ ያደኩት በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ነው፤ ስለዚህም የማውቀው የምፈልገው አስተምህሮ፣ ትውፊትና ሥርአተ አምልኮ አለ። ስለዚህም አንቺ የምታስረጂኝን ሁሉ እሺ ብሎ መቀበል ውስጤ እሺ ላይለኝ ይችላል። አንቺም ራስሽ በእኔ ቦታ ብትሆኚ እሺ እንደማትይ አውቃለሁ።

"የምትለው ነገር ይገባኛል። ለዚህ እኮ ነው እንዲህ ባለ ሁኔታ ውሳኔ እንጂ ማስረጃና መረጃ ብዙም ቦታ የማይኖራቸው። በመጀመሪያ እንዲህ ያለ አቋም ቢኖርህ ኖሮ በእርግጠኝነት ልንገርህ ፍቅር አንጀምርም ነበር። ቃል ገብተህ ፍቅር ከጀመርን በኋላ 'ውስጤን ከበደኝ፤ አላሳመነኝም፤ ተሳስቼ ነው፤ ኦርቶዶክስን ሳላውቀው ቀርቼ ነው፤ የልጅነት ውሳኔዬ ነው' ምናምን እያልክ ብትከራከረኝ እንደሸወድከኝ ወይም እንደ ካድከኝ ከማመን ውጪ ሌላ ምንም አማራጭ የለኝም። ችግሩ የኔን ሕይወት ብቻ ሳይሆን የገዛ ራስህንም ሕይወት ነው ያበላሸኸው። በሃይማኖት ልዩነታችን ብንለያይ ከፍቅር ሕመሙ ሌላ ጸጸቱን አትችለውም። ምክንያቱም የተለያየነው ባንተ ባልጸናው አቋምህ ነው።

"ሮዳስ ከዚህ በኋላ ምንም አይነት የሃይማኖት ትምሕርት አይኖረንም፤ አንተም ወደ መሰለህ መንገድ ትሔዳለህ። ለጊዜው አንተም በምታምነው እኔም በማምነው መንገድ በልዩነት እንቀጥላለን። በዚህ ልዩነት ውስጥ ለጥቂት ጊዜ እንቆያለን እንጂ ዘለቄታ አይኖረውም" ሰንፔር ውብ ዐይንዋ እንባ አርግዞ ተናገረች። እንዲህ ስትሆን ውበቷ ይጨምራል። ጉንጯ ቲማቲም ይመስልና እንባዋ እንዳይወጣ ትታገለችው። ከንፈሯ አምጥሙጦ ይበልጥ ሳሙኝ ሳሙኝ ይላል። በስተመጨረሻ እንባዋ ከቀረጢቱ ሞልቶ በሕጻን ጉሮሮ እንደሚፈስ የእናት ጡት ለሰስ ብሎ በቀላው ጉንጯ ላይ ሸርተት እያለ መውረድ ጀመረ።

ሮዳስ ጥፋተኝነት ተሰማው። ከሰንፔር ጋር የሚለያይ ሲመስለው ሞት መስሎ ይታየዋል። አብሮ መኖርም የሃይማኖት ልዩነቱ ስለማይፈቅድ፤ እሱም ስለማያምንበት፤ አንዳቸው ወደ አንዳቸው ተጠቃለው አንድ እንዳይሆኑ ደግሞ ሁለቱም ቀድመው የሚያውቁትና የሚያምኑት እውነት ሲተናነቃቸው ለፀብ ይጋበዛሉ። "አንዳንዴ ፍቅር ችግር አለበት" ይላል ሮዳስ ብስጭት ብሎ። "በስልክ የተገናኘንበት ያ ቀን..." ብሎ ለመራገም ይልና መለስ ብሎ "አይደለም አይደለም..." ይላል "እኔ ልቤን የሰጠሁበት ቀን ነው እንጂ... አይ አይ ጥፋተኛውማ ልቤን የሰጠሁ እኔ ነኝ እንጂ መቼ ቀኑ ሆነና?" ይላል።



Scanned with CamScanner

# ምዕራፍ ፮

## አዲስ አበባ-ቦሌ

ቀኑ ኮምፓስ እንደሌላው መርከብ ተወዛግቧል። ወትሮ ተግ ብላ ስትሞቅ የነበረችው ፀሐይ በሂደት ደብዘዝ ብላ ትጠፋና ቅዝቃዜው ይመጣል። ትንሽ ቆየት ብሎ ሰማዩ ጠየምየም ብሎ ደመና ይሆናል። እርጥት ባዘለው ሰማይ ስር ነጎድጓድ ሰማዩን እያረሰው ዝናብ ጠብ ጠብ ይልና ዶፉን ይረግጠዋል። ይህ ነበር በዘልማድ የታወቀው የዝናብ አመጣጥ። አሁን ግን አዲስ አበባ ውስጥ እንዲህ ያለ ዑደት የቀረ ይመስላል። እልም ስልም እንደሚል የልጅአገረድ ዐይን ዝንብ ይልና በቅጽበት የሚያቃጥል ፀሐይ በሰማዩ ይነግሳል። ሰው ካፖርት ይልበስ ቲሸርት፣ ጃኬት ይልበስ ኮት፣ ጋቢ ይሁን ነጠላ ከፍት ጫማ ይጫማ ወይስ ለጭቃ የሚሆን ትልቅ ቦቲ... መምረጥ ከብዶታል።

ያልታሰበው ዝናብ ሲመጣ ሰዎች መጠለያ ፍለጋ በየካፌቴሪያው፣ በየሕንጻው፣ በየመድኃኒት ቤቱ፣ በየከተማ አውቶቢስ ፌርማታ፣ በተገኘው ታክሲ ውስጥ ለመግባት ግፊያ ነው። እንስቶች በቅርቡ የተሰሩት ጸጉራቸው እንዳይበላሽ ላስቲክ የሚገዙበት ሱቅ ፍለጋ መባከን፣ ወንድ ባለ መኪኖች ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው ለቆንጆ ሴት መኪናቸውን እንደ መጠለያ ለማጋራት ዐይናቸውን ልክ እንደ ዝናብ መጥረጊያቸው ግራ ቀኝ ሲያሯሩጡት፣ ሽቅርቅር ወንዶች ለዝናብ ሮጡ እንዳይባል አንገታቸውን ደፍተው ሱሪያቸውን ከታች በእጃቸው ሰብሰብ አድርገው ከሩጫ ባልተናነሰ እርምጃ ሲሄዱ፣ አዛውንቶች ትልቅ ዣንጥላቸውን በፍጥነት ዘርግተው ራሳቸውን ከዝናቡ ሊያድኑ ሲሯሯጡ ፍዝዝ ብሎ እያየ ነው።

ሮዳስ ይህን ሁሉ ትንግርት የሚያየው አራተኛ ፎቅ ላይ ከሚገኘው ቢሮው የመስኮቱን ነጭ መጋረጃ ወደ ጎን ገፋ ገፋ አድርጎ በመስታወት በኩል ነው። ከሮዳስ ጀርባ በዝግባ እንጨት የተሰራው ውብ ጠረጴዛ ፊት ለፊት ትይዩ ምቹ ባለ ሌዘር ጥቁር ሶፋ የተቀመጠ ሲሆን፣ ፈዛዛ ወይን ጠጅ ቀለም የተቀባው ግርግዳን ደገፍ ብሎ ትልቅ የመጽሐፍ መደርደሪያ አለ። ነጭ ቀለም በተቀባው ሌላኛው ግርግዳ በኩል ደግሞ የተለያዩ ፋይሎች የያዘ መደርደሪያ አለ። ሮዳስ በመስታወቱ ውስጥ ውጪውን የሚመለከተው ለረጅም ሰዓት ተቀምጦ አድካሚውን ድረገጽ ከሰራ በኋላ ነው። እንደ ተለመደው ሁሉ ድረገጹን ሲሰራ ለስላሳ ሙዚቃ ይከፈታል። በተለይ የማሕሙድን አሕመድን፣ የተሾመ ምትኩን፣ የበዛወርቅ አስፋውን፣ የዶን ዊልያምን እና የኤታ ጀምስን ዘፈን ይከፍታል። ካልሆነም ለስላሳውንና የረጋውን የያኒን በመሳሪያ ብቻ የተቀናበረውን ሙዚቃ ያዳምጣል። የእነዚህ ከያኒዎች ሥራ የሮዳስን አዕምሮ ከኮምፒውተሩ ጋር ያያይዙለታል። ከዚያም በተመስጦ ውስጥ ይገባና ሥራውን ይከውናል እንጂ እንዴትና ምን እንደ ሰራ ለማድነቅም ሆነ ለመንቀፍ



Scanned with CamScanner

የሚሞክረው ሥራውን ሲጨርስ ነው። በዚህ ተመስጦው መሀል ግን እንዲህ እንደ አሁኑ ወደ መስኮቱ ጠጋ እያለ አካባቢውን ይቃኛል።

ወጪ ወራጁን በአንክሮ እያየ እያለ ነው አበጋዝ ወደ ቢሮው የገባው። ረዥሙና ለግላጋው አበጋዝ በሩን በስሱ ኳኳ አደረገና ከፍቶ ወደ ውስጥ ገባ። ዕለቱ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ስለነበር ሮዳስን የሚያግዙት ወጣቶቹ የኮምፒውተር ባለሙያዎች የሉም። ሮዳስ ጀርባውን ሰጥቶ ከቆመበት መስኮት እግሩን ሳያንቀሳቅስ ዞር ብሎ ማን እንደመጣ ተመለከተ።

ሽቅርቅሩ ሁሌም ቢሆን ውብና የሚያምርበትን ሱፍ የሚለብሰው አበጋዝ ነው። ሮዳስ ሽቅርቅር ሰዎች ቁም ነገርና ብዙ እውቀት ያላቸው አይመስለውም። በእርግጥ ይህ አስተሳሰቡ ሁሌ ትክክል ላይሆን እንደሚችል ቢያውቅም "በጣም ሽቅርቅር የሚል ሰው በየትኛው ጊዜው ነው ቁም ነገር የሚሰራው" ይላል። ቢሆንም አበጋዝ ይህን አስተሳሰቡን አፍርሶበታል። "ብቃ እውቀት እንደ አበጋዝ" እንዲል አድርጎታል። በጣም አዋቂና አስተዋይ እንዲሁም ሽቅርቅር ሆኖበት ሮዳስን ሁሌ ያስደምመዋል። ሮዳስ ሁሌ በአድናቆት "ሲሳካልህ!" ይለዋል። ሮዳስ ከልብ በሆነ ፈገግታ "አው አበጋዝ እንኳን ደህና መጣህ ሰላም ነው?" እያለ በአክብሮት አበጋዝን ለማቀፍ እጁን ወደ ላይ ከርፈፍ አድርጎ ተጠጋ

አበጋዝም ለሮዳስ ሰላምታ አጸፋውን እየሰጠ "አለን ሰውየው በዚህ ሳልፍ ላግኝህ ብዬ ነው እንዴት ነህ?"

"ደህና ነኝ.... ስላየሁህ በጣም ደስ ብሎኛል፤ እንደውም ደክሞኝ ነበር አንድ የጀመርኳት ነገር አለች ትንሽ አስተካክያት መጣሁ አስር ደቂቃ ብቻ ጠብቀኝ"

"ችግር የለውም ወዳጄ ቴክ ዩር ታይም ባይሆን እዚህ ቢሮህ ቁጭ ብዬ ወጪ ወራጁን ልታዘብ"

"ትችላለህ" አለና ሮዳስ የእንግዳ መቀበያ ክፍሉን ለአበጋዝ ለቆ ስርክ ስራዎቹን ወደሚያከናውንበት ክፍል ገባ። ሮዳስ የመጀመሪያና ዲግሪውን በኮምፒውተር ሳይንስ፤ ሁለተኛውን በሶፍትዌር ምህንድስና ተቀብሏል። በአሁኑ ሰዓት በአዲስ አበባ ውስጥ አለ የሚባል የድረገጽ አዘጋጅ ነው። ቦሌ ደምበል ሕንጻ ላይ የራሱን ቢሮ የተለያዩ ድርጅቶችን ድረገጽ ያዘጋጃል።

ሮዳስ የራሱ የሆነ ድረ ገጽ ከፍቶ የተለያዩ ጽሑፎችን የሚያስነብብ ሲሆን በይበልጥ መንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ያተኩሩ ጽሑፎችን በመጻፍ ይታወቃል። ለዚህም ይመስላል ብዙ መንፈሳዊ ተቋማትም ድረገጽ እንዲያዘጋጅላቸው ወደ እርሱ የሚመጡት።

ሮዳስና አበጋዝ የተዋወቁት አበጋዝ ድሬ ገጽ ለማስራት ወደ ሮዳስ ቢሮ ሲመጣ ነው። አበጋዝ ሚሽናህ በተባለ ሆስፒታል ውስጥ የአእምሮ ሐኪም ነው። አበጋዝ ህሙማንን በአካል በማግኘት ብቻ ሳይሆን የሚያክመው፤ ሌሎች እሱን ማግኘት ላልቻሉ ሰዎችም ድረገጽ ከፍቶ ጤና ነክ እውቀት የያዙ ጽሁፎችን በመጻፍ ለሌሎች ሰዎች ያጋራል።

መጀመሪያ ድረገጹን የሰራለት ሮዳስ ስለነበር ተጨማሪ ምክርና እውቀት ስለ ድረገጹ ማወቅ ሲፈልግ ሮዳስን እየመጣ ያማክረዋል። አበጋዝ በሮዳስ ስራና ታማኝነቱ እንዲሁም ምንም ሳይሰስት የድረገጽ እውቀቱንና አጠቃቀሙን ስለሚያስረዳው ከአገልጋይና ተገልጋይነት ይልቅ ወዳጅነታቸው ይበልጥ የጸና ሆነ።

-------//------

## ኬንያ ናይሮቢ

ይህኛው ስብሰባ ደግሞ ለሌሎች ተሰብሳቢዎችም ድብቅና ምስጢራዊ ነው። ስታንሊ ሆቴል ሆኖ ነገር ግን ከዋናው ስብሰባ አዳራሽ በተለየ ሁኔታ በሩቢዮ ክፍል ነው የሚካሄደው። መጀመሪያ ያልነበረው ቶኒም አለ። ቶኒ የተሐድሶው ቡድን የደህንነትና ዘመቻ መምሪያው ክፍል ኃላፊና አማካሪ ነው። የመጣው ከእንግሊዙ የስለላ ድርጅት ከኤም አይ ሲክስ ወይም ኤስ አይ ኤስ ሲሆን ከሲአይኤ ጋር በአንድነት በዚህ ጉዳይ ይሰራል።

ከዋናው ስብሰባ ሰዎች በልዩ ሁኔታ ተመርጠው የሚታደሙበትን ስብሰባ የሚያካሂዱት በውቡና ጽዱው የሩቢዮ ክፍል ሳሎን ውስጥ ነው። ለዚህ አላማ የተመረጡ አንድ ከአዲስ አበባ፤ አንድ አንድ ከዱባይና ከአሜሪካ የመጡ ሰዎች ናቸው። ከአዲስ አበባ የመጣው ዘላለም በቴኳንዶ ካራቴ ሁለተኛ ዳን አለው። ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ደግሞ በነገረ መለኮት የመጀመሪያ ዲግሪ ሲኖረው፤ የመንፈሳዊ ኮሌጁ ኃላፊ የሕቡዕ ድርጅቱ የደቂቀ እስጢፋኖስ አባል ስለነበር ይህ ልጅ ከትውልድ መንደሩ ወልቃይት ወረዳ ካለው ቤተ ክርስቲያን ኦርቶዶክስ ለመሆኑ ማረጋገጫ ካስጻፈ በኋላ ያለምንም ማቅማማት ተቀብሎታል።ዘላለም ነገረ መለኮት የተማረው በአላማና በፍላጎት ነው። በትምህርት ላይ እያለ በየወሩ ሦስት መቶ ሃምሳ ዶላር ከደቂቀ እስጢፋኖስ ህቡዕ ቡድን ይከፈለው ነበር። ገንዘቡም ባይከፈለውም ዘላለም መንፈሳዊ ኮሌጅ ገብቶ መማሩ አይቀሬ ነበር። ምክንያቱም ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ላይ ትልቅ ቂም አለበት። ዘላለም አሁን አንድ ሺህ ዶላር በወር የሚከፈለው ሲሆን የግሉ ቤትና ቀንጠኛ መኪና ተሰጥቶል።



Scanned with CamScanner

ሌላኛው ተሰብሳቢ ከአሜሪካ የመጣው ለዓለም ነው። በ1993 ዓመተ ምህረት በአዲስ አበባ የሕዝብ አመፅ ላይ ተሳትፈሀል ተብሎ አዲስ አበባ ከሚገኘው ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የተባረረ ሲሆን ለዘመናት በስራ ማጣትና በችግር የተንገላታ ነበር። መንፈሳዊ ኮሌጅ ውስጥ ጥሩ የትምህርት አቀባበል እና መልካም ሥነ ምግባር የነበረው ቢሆንም ከኮሌጁ ከተባረረ በኋላ ግን ሥነ ምግባሩ ተበላሸ። ጫት ይቅማል፣ መጠጥ ጥምቢራው እስኪዞር ይጠጣል፣ ለከሮ ከሰው ጋር ይደባደባል፣ ከሴተኛ አዳሪ ጋር ይተኛል ...። በዚህ የሱስና የተስፋ መቁረጥ ዘመኑ ውስጥ ነው ዲቪ ደርሶት አሜሪካ የሄደው።

ዛሬ ስብሰባውን የሚመራው ቶኒ የግል ማህደሩን ካጠና በኋላ ለተሐድሶው እንቅስቃሴ አጭቶታል። ለዓለም የመጻሕፍ ቅዱስ እውቀቱ ደህና የሚባል ሲሆን አሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ የሚገኘው ደብረ ልዑል አማኑኤል ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን በሰባኪ ወንጌልነት እንዲያገለግል እድል ተመቻችቶለት። በዚያውም የተሐድሶ እንቅስቃሴውን በስደተኛው ሲኖዶስ ውስጥ ሆኖ እንዲያፋፍም ተመረጠ።

ከዱባይ የመጣው ዳንኤል የዱባይ ሹፌር ነበር። ተወልዶ ያደገው አዲስ አበባ ጉለሌ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ነው። ዳንኤል በሰፈሩ አመጸኛና ተደባዳቢ ሲሆን ድህነትን አምርሮ የሚጠላ ነው። በአንዲት ጠባብ ክፍል ውስጥ ለስድስት ሆኖ ያደገ፣ መጸዳጃ ቤት በማጣት ቤታቸው ውስጥ ጉድጓድ ቆፍረው እዚያው እዳሪ ከሚወጡ ቤተሰቦች ውስጥ የወጣ ነው።

አባቱ አቶ አለሙ ገርባ ጭቃ አቡኪ ሲሆኑ እናቱ ወይዘሮ ጥሩዓይነት ደግሞ አባታቸው ጭቃ አብኩተው፣ ጠጅ ጢምብራቸው እስኪዞር ጠትውና ሰክረው፣ ተደብድቦ ከመዘረፍ በተረፈው ገንዘብ የሚተዳደሩ ሰዎች ነበሩ። በዚህ የቤተሰብ ችግር ውስጥ ያደገው ዳንኤል እድሜው ከፍ ሲል ድህነትን አምርሮ ይጠላ ጀመር። ዳንኤል ድህነትን ለማሸነፍ ገንዘብ ከሰው ለምኖ የጫማ ቀለም፣ መቀቢያ ብሩሽ እና መያዣ ሳጥን ገዝቶ ሊስትሮ መስራት ጀመረ።

ዳንኤል ጫማ እየጠረገ በትንሹም ቢሆን ኑሯቸውን መደገፍ ቢጀምርም አባታቸው አቶ አለሙ በመጠጥ ብዛት ለከፍተኛ ጉበት በሽታ ተዳረጉ። የእሳቸው ከስካርና ከዝርፊያ የሚተርፈው ገንዘባቸው ከነጭራሹ ጠፋ። ዳንኤል በጫማ ጠረጋ የሚያገኘው ገቢ የአባቱን ሕክምናና የቤተሰቡን ሆድ መቻል ነበረበት። ቢሆንም በቀን አስራ አምስትና ሃያ ብር እያለ የሚሰበስባት ገንዘብ ለቤተሰቡ ጠብ የሚል ድትማ መሆን አልተቻላትም። አባቱም በህክምና እና በእንክብካቤ እጦት ተሰቃይተው በጉበት በሽታ ሞቱ። ዳንኤል አባቱን ማጣቱ ክፉኛ ጎዳው። ትንሽም ቢሆን ቤቱን የሚያግዙ ስለነበሩ፣ የእሳቸው ሞት እንደ አባትም እንደ አባወራም ቤተሰቡ ላይ ትልቅ ጉዳት እና ሐዘን አደረሰ። ዳንኤል እናቱን መጦር እና የሶስት ታናናሽ እህቶች አሳዳጊ መሆን ውዴታው ሳይሆን ግዴታው ሆነ። ይህን ችግር የተጋራችው የሁለት አመት



Scanned with CamScanner

ታናሽ እህቱ ነበረች። የዳንኤል እህት የወንድሟ መከራ! የቤተሰቡ ችግር አፍጥጦ ሊበላት ቢደርስ፤ ሴትነቷን ለወንዶች እየሸጠች ቤተሰቡን መደጎም ጀመረች።

እህቱ ገንዘብ እንዴት እንደምታገኝ ሲያውቅ ዳንኤል በጣም ነበር የውስጥ ሀዘኑ የበረታበት። ቢሆንም ምንም ማድረግ አልቻለም። ተይ እንዳይል ለእህቱ ምንም አማራጭ ሊሰጣት አይችልም። ስለዚህ እያወቀ እንዳላወቀ መሆን ግዴታው ነበር።

የዳንኤል እህት ገንዘብ አጠራቅማ ዱባይ ልትሄድ ዝግጅት ጀመረች። ነገር ግን ለጉዞ አስፈላጊ ከነበሩት የጤና ምርመራዎች ውስጥ አንዱ ምርመራ በጉበት ቫይረስ መጠቃቷን አሳየ። ስለዚህም ከዱባይ ጉዞዋ እንዳትሄድ ተከለከለች። ስለዚህም በእሷ ምትክ ወንድሟን እንዲሄድ ላከችው። ዳንኤል ዱባይ ውስጥ በሹፍርና እያገለገለ ቤተሰቦቹን ይረዳ ጀመር። ቢሆንም ገንዘብ መቼም በቃኝ ሊል እንደማይገባው ያለፈበት የኑሮ ውጣ ውረድ አስተማረው። አንዳንድ ጊዜ ዱባይ ውስጥ ከሌሎች ሹፌሮች ጋር ሰብሰብ ብለው ገንዘብ ይዘርፋሉ። ይህን የሚያደርጉት ግን እንዲህ በቀላሉ ሳይሆን በብርቱ ጥንቅቃቂና ከዱባይ ባንክ እስከ ታክሲ ሹፌር ድረስ መዋቅር ዘርግተውና ተመሳጥረው ነበር።

ዳንኤል በዚህ አደገኛና ወንጀል የበዛበት ሕይወት ውስጥ እያለ ዱባይ የሚገኘው ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን መሪጌታ እና የሕቡው ደቂቀ እስጢፋኖስ ክንፍ ኃላፊ ለነበረው እምሩ ለተባለ ሰው በመኪናው የማጓጓዝ አገልግሎት ይሰጠው ጀመረ። መሪጌታ እምሩ ለመጓጓዝ ከሚጠየቀው የአገልግሎት ክፍያው በላይ ከፍተኛ ጉርሻ ለዳንኤል ስለሚሰጠው ወዳጅነታቸው ጨመረ። መሪጌታ እምሩ ዳንኤልን እንደ ግል ጠባቂው ይቆጥረው ጀመር። ዳንኤልም እንደ ጠባቂ መቆጠሩ አልከፋውም።

ቀስ ቀስ እያለ መሪ ጌታ እምሩ ለዳንኤል አንድ ተልእኮ ሰጠው። ይህ ተልእኮውን ከፈጸመ ለዘመናት ይመኘው የነበረውን ከዱባይ መኪና የማስጫንና አዲስ አበባ የመሸጥ ሕልሙን እንደሚሳከለት ቃል ተገባለት። ስለዚህም የዱባይ አገረ ስብከት አስተዳዳሪ የነበሩትን ሊቀ ጳጳስ ለመግደል ተልእኮውን ተቀበለ። እንደታዘዘውም ሊቀ ጳጳሱን መኪናቸው ውስጥ ገድሏቸው ተሰወረ። ከዚያ በኋላ ለከፍተኛ ተልእኮ እና ሥራ ተፈላጊ ሰው ሆነ።

ዘላለም እና ዳንኤል በቂ ስልጠናና ትምህርት ከቶኒ ከወሰዱ በኋላ የመግደል፣ የማፈንና ማንኛውንም አይነት ጥቃት በታዘዙት መሠረት ይወስዳሉ። ለዓለም ሰው መግደል አይደለም ጠንከር ያለ ስድብ የማይችል ነው! በጭንቅላቱ እንጂ በጉልበቱ መጠቀም እንደማይፈል ስለተረዳው ቶኒ እውቀትና መንፈሳዊ ነክ ጉዳዮችን ብቻ እንዲያከናውን አድርጎታል። መንፈሳዊ ጥያቄና መልሶችን በበቂ ሁኔታ ይመልሳል። መንፈሳዊ ክርክሮችም ላይ እየተገኘ ምላሽ ይሰጣል።



Scanned with CamScanner

# ምዕራፍ ፰

## ኬንያ-ናይሮቢ

የሩቢዮ መኝታ ቤት ሳሎንም ጭምር አለው። ሳሎኑ ከቱርክ በመጣ ምንጣፍ የተንቆጠቆጠ ሲሆን፤ የራስጌ መብራቶቹ ጃፓን ሰራሾችና በራሳቸው በጃፓኖች በጥንቃቄ የተገጠሙ ናቸው። ግርግዳው ላይ የተሰቀሉት ስዕሎች በባለሙያዎች አጠራር 'ሪያልስቲክ' የሚባል ሲሆን የናይሮቢን የዱር ከተማዋን ገጽታ የሚያሳይ ትልቅ ሥዕል ግራጫ ቀለም ባለው ቁንጠኛ ፍሬም ውስጥ ሆኖ እነ ሩቢዮ ከተቀመጡበት ሶፋ ትይዩ ተሰቅሏል።

እነ ሩቢዮ የተቀመጡበት ሶፋ የተሰራው እዚያው ኬንያ ናይሮቢ ሲሆን የተሰፋበት ነጩ ጨርቅ የመስኮቱን መጋረጃ ጨምሮ ከጣልያን በውድ ዶላር የተገዛ ነው። የጨርቁ ጥራትና ንጣት ዐይን ያጥበረብራል። በግርግዳው ኮርነር ላይ የራስጌ መብራቶቹ የተቀመጡበት ኮመዲኖ በዝግባ እንጨት የተሰሩ ሲሆን የቤቱ ተጨማሪ ድምቀቶች ናቸው። ይህ ሁሉ ነገር ፍክት ብሎ እንዲታይ የቻይና ባለሙያዎች ቁንጠኛውን አምፖል በየግርግዳው ኮርነር ውብ አድርገው ገጥመውታል።

ቶኒና ሩቢዮ ትንሽ ትንሽ አማርኛ ይሰማሉ። አማርኛውንም እንግሊዘኛውንም ጠንቅቆ የሚያወራውና መልእክት እንዲያስተላልፍ የሚጠበቀው መርሐዊ ከውጪ ወደ ውስጥ ሲገባ ቤቱ ውስጥ የነበረው የዝምታ ድባብ ተሰበረ፡፡ ሩቢዩ መርሐዊ ከውጪ ወደ ውስጥ ሲገባ በጣም የሚያፈቅራት ፍቅረኛው ቀጥራው ለረዥም ሰዓት አስጠብቃው ብቅ ስትል የሚሰማው አይነት ደስታ ተሰማው።

"ወደ ጉዳይችን ስንገባ...እህምምም..." አለ መርሐዊ ለመስማት በማያስቸግር የእንግሊዘኛ ቅላጼ።

መርሐዊ ጉሮሮውን እንደመጠራረግ ብሎ የተቀመጠበትን ሶፋ በደንብ እያመቻቸ ንግግሩን በመቀጠል "ተሐድሶው አይቀሬ ከሆነ የትኛውንም መንገድ ልንጠቀም ግድ ነው። ቅድም ከሌሎች ጋር ሆነን እንደተነጋገርነው ተሐድሶውን ከግብ ለማድረስ ከላይ ወደ ታች እንጂ ከታች ወደ ላይ መጀመር የለብንም ስለዚህ የመንግሥት ድጋፍ ያስፈልገናል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ተቀናቃኞችን የሆነው ማኅበረ ቅዱሳን ሌላ ደጋፊ ከንፍ አግኝቷል።" አለና መርሐዊ ወደ ቶኒ እየተመለከተ

"እባክህ ቶኒ ስለ ሕቡዕ ቡድን ያለውን ነገር በጥቂቱ ብትለን?" ብሎ ትህትና በተሞላበት ንግግር ጥያቄ እያቀረበ።

ቶኒ ሳያስበው መርሐዊ እንዲናገር ስለጋበዘው በመጠኑ ፈገግ አለና ምራቁን ዋጥ አድርጎ ንግግሩን ጀመረ።



Scanned with CamScanner

"እሺ... የእንግሊዝ የስለላ ድርጅት እንዳረጋገጠው ከሆነ የተሐድሶን ጉዳይ በጥንቃቄ የሚያየው 'ፊስአልጎስ' የተባለ ሕቡዕ ቡድን ነው፡፡ ይህ ሕቡዕ ድርጅት ማንኛውም አይነት ጥንታዊቷ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አላት የሚሏትን ቀኖና እና ትውፊት የሚነካባቸውን ሰው ይቃወማሉ፡፡ ምንም አይነት የኦርቶዶክስን ስህተት የሚያሳዩ መጽሐፍት ቢጻፍ እንኳ በፍጥነት መልስ ምት በመጽሐፍ ይሰጣሉ፡፡ ለጊዜው ያለን እውቀት ይህ ነው፡፡ ግን ደግሞ በቅርቡ የበለጠ መረጃ እንዲኖረን ጥረት እናደርጋለን፡፡" ቶኒ ንግግሩን ስለጨረሰ ዝም አለ፡፡

መርሐዊ መልሶ መናገር ጀመረ "የኦርቶዶክስ ምእመናን የኢትዮጵያዊነት ብሔርተኝነት ስሜታቸው ከፍተኛ ነው፡፡ አንዱ የኦርቶዶክስ ድክመት ይሔ ነው፡፡ የትም አገር ሂዱ ኦርቶዶክሶች ያሉበት ቦታ ከወንጌል ይልቅ እምነታቸውን እንደ አገራቸው ይወዳሉ፡፡ የማያውቁትን ሃይማኖት በፍቅር ይወዱታል፡፡ የማያውቁትን ወንጌል በስማ በለውና በውርስ ይቀባበሉታል እንጂ ውስጡን አያዩትም፡፡ አብዛኛው ኦርቶዶክስ ለወንጌል ሳይሆን ለሃይማኖቱ እና ለአገሩ ከፍተኛ ፍቅር አለው፡፡ ምንድነው በአንድ ራስ ሁለት ምላስ መሆን? አንዴ አገራችን በሰማይ ነው ማለት ሌላ ጊዜ ደግሞ አገሬ ኢትዮጵያ ነው ማለት?

"የተሐድሶው አንዱና ዋነኛው አላማ ይህን አላስፈላጊ ብሔርተኝነት ማቀዝቀዝ ነው፡፡ ይህ አላማ የመንግሥት ትልቅ አጀንዳ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ከመንግሥት ጋር ለመስራት ቶኒ ነገሮችን ያመቻችልናል፡፡ በአሁን ሰዓት የኢትዮጵያ ብዙዎች ባለ ሥልጣናት ጌታን ተቀብለዋል፡፡ ይህ ነገር መንገዱን ለእኛ መልካም መደላድል ይፈጥራል፡፡"

መርሐዊ ንግግሩን ቆም ሲያደርግ እስከ አሁን ድምጹ ያልተሰማው ሩቢዮ ንግግሩን ጀመረ "ለምሳሌ መንግሥት ባንዲራ ልቀይር ቢል ትልቅ ተግዳሮት የሚገጥመው ከቤተ-ክህነት ነው፡፡ ባንዲራው ላይ ኮከብ ሳድርግ እንኳ ቢል እንዴት ነው የተቃወሙት፡፡ ስለዚህ በአሁኑ ሰዓት፤ ለዚህ ዘመን፤ ለዚህ ትውልድ፣ ለዚህ መንግሥት ኦርቶዶክስ ብዙም የምታስፈልግና የማትመጥን፣ ዘመን ያለፋበት፣ ፀረ-ዲሞክራሲ ተቋም ነች፡፡ ይህንን በኦርቶዶክስ እና በመንግሥት መካከል ያለውን አለመፈላለግ እኛ ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡ ኦርቶዶክስ እስከ ዛሬ ያለፉት ነገሥታትን ተጠቅማ ኦርቶዶክስን ኢትዮጵያ፤ ኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ አስመስላ ኖራለች አሁን ግን ይህ ጉዳይ በጌታና በቃሉ ይሰበራል፡፡ ኢትዮጵያ የጌታ እንጂ የተዋሕዶ አትሆንም፡፡" ሩቢዮ ለዘብተኛ ፕሮቴስታንት ነኝ ብሎ የሚያምን ሰው ነው፡፡ ዛሬ በተናገረው ነገር ግን አክራሪ የሆነ መስሎታል፡፡

ሩቢዮ ንግግሩን ማቆም አልቻለም "ከዚህም በላይ ጌታን የተቀበለ ባለሥልጣን ለዓላማችን ያስፈልገናል፡፡ ቅድም ሩቢዮ እንደ ነገራችሁ ሥልጣን ትልቅ አቅም ነው፡፡ ስለዚህ ይህን አቅማችንን ለማልጎበት 'ፊስአልጎስን' ማን እንደሚመራው፤ አላማው



Scanned with CamScanner

ምን እንደሆንና እንዲሁም በመንግሥት እንዲጠላና በሽብርተኝነት እንዲፈረጅ ማድረግ አለብን። እሱን ብቻ ሳይሆን ማኅበረ ቅዱሳንን ጭምር።"

ቶኒ ከሩቢዮ ቀበል አድርጎ "በእኔ እይታ ማኅበረ ቅዱሳን መንፈሳዊ ተግባሩን በሰላም ለማካሔድ ሲል ማንኛውንም አይነት የተሐድሶ እንቅስቃሴን እንደ ዱሮው ከመታገል ይልቅ በፊስአልጎስ ሊታገል ፈልጓል። ታዝባችሁ ከሆነ አሁን አሁን ማንኛውም የተሐድሶ እንቅስቃሴን በተመለከተ የጽሑፍም ሆነ የስብከት መልስ የሚሰጡት በግለሰብ ደረጃ ነው። ነገር ግን ከጀርባ የማኅበረ ቅዱሳን ጥናትና ምርምር ክፍል ይረዳቸዋል።" ለዓለም የቶኒ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያለው ጠለቅ ያለ መረዳትና እውቀት ስላስገረመው እጁን አፉ ላይ ጭኖ ነበር የሚያዳምጠው።

"ስለዚህ እናንተም ስትንቀሳቀሱ እንደ ግለሰብ እንጂ እንደ ተሐድሶ ወይም እንደ ደቂቀ እስጢፋኖስ እንዳይሆን። ምንም ነገር ቢፈጠር በግለሰባዊ አቋማችሁ እንጂ ከየትኛውም አይነት መንፈሳዊ ድርጅት ጋር እንድትፈረጁ አንፈልግም። እንደውም ከዚያ ይልቅ አሁን ባላችሁ አቋም እንደ ኦርቶዶክስ ቀጥሉ። ይህን ያልኳችሁ ድንገት ፊስአልጎስ ቢደርስባችሁ እኛ ኦርቶዶክስ ነን ነው የምትሉት። ሌላ መልስ የላችሁም። ዝርዝር የፊስአልጎስ መረጃውንና የምትሰሩትን ሥራ በቅርቡ በእያንዳንዳችሁ ኢሜይል ይደርሳችኋል።

መርሐዊ መናገር ጀመረ። የፊቱ ወዝ በደስታ እንደ ሰም እንደተቀባ ጣውላ እያበራ ነው። "በነገራችን ላይ አሁን እንደ ዱሮው የምንጠብቀውም የምንታገሰውም ነገር የለም። ውስጥ ያሉ ወዳጆቻችን ሰዓቱ ምቹ እንደሆነና እርምጃ እንድንወስድ እየጠየቁን ነው። ከአንዳንድ የመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር ያለንን ግንኙነትም አጠናክረናል። ሰዓቱ ሲደርስም ጥሩ ሽፋን እንደሚሰጡን ቃል ገብተውልናል።

"እንደምታውቁት እስከ 1950 ዓ.ም. ድረስ የሄድንበት ቀጥተኛ የራስን አስተምህሮ መግለጽ እንደማያዋጣ በግልጽ ተሞክሮ አይተነዋል። ከ1950 ዓ.ም. እስከ 1990 ዓ.ም. የሄድንበት የተዋሕዶ አስተምሕሮ ስሕተቶችን እየነቀሱ፣ ከወንጌል ይልቅ ተረታ ተረት የበዛበት መሆኗን እየገለጹ ወንጌል በተዋሕዶ መቅደስ በሞላ እንዲያበራ ሳይሆን ጥቂት ሰዎችን ገንጥሎ በመውሰድ አድነናል። ቢሆንም የተፈለገውን ያህል ውጤት አላስገኘልንም። ስለዚህ ከ1990 ዓ.ም. የሥልት ለውጥ ያደረግንበትና አሁን እየሔድንበት ያለው የጥንቷን በአራተኛው ክፍለ ዘመን በአቡነ ሰላማ የተሰበከውን እውነተኛውን ወንጌል ዳግም የማምጣት አካሄዳችን በጣም አመርቂ ውጤት አምጥቷል። በአሁኑ ሰዓት የቤተ ክርስቲያኒቱን ዋና ዋና መዋቅር ተቆጣጥረን ቤተ ክርስቲያኗ ባለችበት ምእመኑ የትም ሳይሄድ ጌታን እንድትቀበል ለማድረግ ከጫፍ ደርሰናል።

"አሁን እየጠበቅን ያለነው የራሳችንን ሰዎች ጳጳስነት ማስሾም ብቻ ነው፡፡ ሰዎቻችንም እጩ ሆነዋል ከሳምንታት በኋላ ይሾማሉ፡፡ ሹመቱን ከአገር ቤትም ከስደተኛው ሲኖዶስም እናገኛለን፡፡ አሜሪካ ካለው ሲኖዶስ ለሹመት ከተመረጡት ውስጥ አንዱ እኔ ነኝ፡፡" ለዓለም በተመስጦ ሲያዳምጥ ከነበረበት ውስጥ ድንግጥ አለ፡፡ መርሐዊ የተናገረው ነገር ያልጠበቀው ስለ ነበር አንዳች ደስ የማይል ስሜት ሲወርረው ተሰማው፡፡ ለዓለም የመርሐዊ ንግግር በጣም እየኮሰኮሰው ቢሆንም በጥሞና ማዳመጡን ቀጠለ፡፡ ዳንኤል እና ዘላለም የመርሐዊን ንግግር ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው ሁለቱም በአንድ አንገት እንደሚንቀሳቀስ ጭንቅላት ጣራ ጣራውን እኩል አንጋጠው ያያሉ፡፡

"ምዕመኑን ደግሞ በነጠላውና ባንጠለጠለው የአንገት ክሩ ላይ ጌታን እንዲቀበል አድርገነዋል፡፡ ብዙው ኦርቶዶክስ ነኝ የሚለው ማኅበረሰብ በተለይ አዲሱ ትውልድ የተዋሕዶ ስሙን እንጂ አስተምህሮው የእኛ ነው፡፡ በቃ የሚፈለገው ይህ ነው፡፡

"አዲሱ የተዋሕዶ ምእመን መዳን በእምነት ብቻ፤ አማላጅ ኢየሱስ ብቻ፤ ክብርና ምስጋና ለአንዱ ጌታ እንጂ የምን ማርያም፣ ቅዱሳን መላእክት ነው? አዋልድ መጽሐፍትን እንደተረትና ምሳሌ የሚያይ፤ እንኳን አዋልድ መጽሐፍ ሰማንያ አሐዱ መጽሐፍን እንኳ የማያውቅ ትውልድ እየተፈጠረ ነው፡፡ ይሄ በጣም መልካም ነገር ነው፡፡ ሰዓቱ ደርሶ ራሳችንን ስንገልጽ እነዚህ ናቸው የእኛ ደጀኖች፡፡ የቱ ነው ትክክለኛው ኦርቶዶክስ ሲባሉም የሚያውቁትን ነው የሚመሰክሩት፡፡"



Scanned with CamScanner

## ምዕራፍ ፱

## እንግሊዝ-ለንደን

ለንደን ከሁለት ሺህ ዓመት በላይ ታሪክ ያላት ከተማ ነች፡፡ ይህች ከተማ የእርስ በእርስ ጦርነት፣ የእሳት አደጋ፣ ሕዝባዊ አመፅ፣ የቦንብ ድብደባን፣ የአሸባሪዎች ጥቃትን አስተናግዳለች፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት የብሩተስ ጦር ጉግማንግ የተባሉትን ቀደምት የቦታውቹን ነዋሪዎችን አፈናቅሎ ነው ለንደንን ያቀናት፡፡ ቢሆንም ሮማውያን የራሳቸውን የሮም ከተማ መልክ እንድትይዝ በወንዝ አካባቢ ቀረቀሯት፡፡

ከሥልሳ ዓመት በፊት በአዶልፍ ሒትለር ቦንብ ጣይ ጀቶች እንዳልነበረች ሆና የፈረሰችው ለንደን ከተማ አሁን ውበቷን ላየ የቦንብ ድብድባውን ታሪክ ማመን ይሳነዋል፡፡ ድልድይዋ፣ ባቡሮቿ፣ የመንገድ እና የህንጻዎቿ ጥንታዊ መምሰል ድንቅ ይላል፡፡ ለንደን ዱሮዋን መርሳት የማትፈልግ መሆኗን ለማሳየት በፈረስ የሚጎተቱ ጋሪዎቿ በከተማዋ እንዲንቀሳቀሱ በፍቅር ፈቅዳለች፡፡ ያውም በስስት እያየች፡፡

የለንደን ነዋሪዎች እንደወትሯቸው ሁሉ ውክቢያ ላይ ናቸው፡፡ መኪናው ሰልፍ ይዞ ይተማል፡፡ የረፋዱ ፀሐይ ደግሞ ማቃጠል ጀምሯል፡፡ ፓስተር ናፍያድ ገመቹ ቢኤም ደብልዩ መኪና ውስጥ ከኒሳ ወንበር ቁጭ ብሎ ኢትዮጵያ ካለችው ልጁ ከሰንፔር ጋር በቫይበር እያወሩ ነው፡፡

ሮሌክስ የተባለውን የእጅ ሰዓቱን ተመለከተ ከረፋዱ ለአራት አስር ጉዳይ ይላል፡፡ ስብሰባው የሚጀመረው አራት ሰዓት ነው፡፡ ስለዚህ ሹፌሩ አነዳዱ ፈጣን ስለሆነ ለስብሰባው በሰዓቱ እንደሚደርስ እርግጠኛ ነው፡፡ ስለዚህም በመኪናው መስታወት አሻግሮ የለንደን ከተማን ውበት እያደነቀ ዘና ብሎ ስልኩን ማውራት ቀጠለ፡፡

ፓስተር ናፍያድ የፕሮቴስታንት እምነት ፓስተር፣ ጥሩ መንፈሳዊ እውቀት ያለው ሲሆን በብዙ ሰው ዘንድ የተከበረና የተመሰገነ ሰው ነው፡፡ በኤልሻዳይ ቴሌቪዥን ላይ የራሱ የሆነ መንፈሳዊ ዝግጅት አለው፡፡ በጋዜጠኝነት እና ኮሚዩኒኬሽን የማስተርስ ዲግሪ በተጨማሪም በነገረ መለኮት ፍሎሪዳ ከሚገኘው ኖክስ ቲዮሎጂካል ሴሚናሪ ከሌጅ ሁለተኛ ዲግሪ አለው፡፡ ፓስተር ናፍያድ የኤልሻዳይ ቴሌቪዥን የቦርዱ አባልም እንዲሁም የኤፌሶን መንፈሳዊ ቴሌቪዥን ጣቢያም አማካሪ ነው፡፡

ፓስተር ናፍያድ ጥሩ መንፈሳዊ አባት በመሆኑ በአማኙ ዘንድ ቢወደድም በአንዳንድ ፓስተሮች ዘንድ ግን ፊት ለፊት በመናገርና ፍትሐዊ ያልሆነን ነገር በመጋፈጥ ስለሚታወቅ አይወደድም፡፡ በተለይ 'የእኛ ሰው ስለሆነ' ተብሎ ምንም አይነት መጥፎ ነገር እንዲሸፋፈንም ሆነ የሥነ ምግባር ጥሰት ሲፈጸም ዝም ማለትን አይፈልግም፡፡

"ሰንፔር ምንድነው የሚያጣላችሁ? እኔ አዲስ አበባ እያለሁ ሰላም አልነበራችሁ?"



Scanned with CamScanner

"አባቢ ችግር አለበት። በሕይወቱ ውስጥ ጣልቃ መግባት ይፈልጋል። በማያገባው ነገር ልግባ ይላል። ልክ አንተ እግርህ ወጣ እንዳለ ቱጥጥር ጀመረ። በዚህ ሰዓት ለምን ትገቢያለሽ። ከሮዳስ ጋር ለምን አይሻለሁ እያለ ይጨቃጨቃል።"

"ያው ወንድምሽን ታውቂዋለሽ። በሰው ጉዳይ ጣልቃ መግባት ይወዳል። ነገር የማክረር ባህሪ አለው እስኪ ታገሽው። ስመጣ እንደሚሆን እንደሚሆን እናደርገዋለን"

"እረ አባቢ ብትታገሰውም እሱ የሚታገስ አይደለም። እኔ እኮ ትልቅ ልጅ ነኝ። የማደርገውንና የምወስነውን አውቃለሁ። እሱ የእኔ ህይወት ካፒቴን መሆን ያምረዋል። እኔ የሚገርመኝ የኔን ሕይወት የሚኖርልኝ ይመስል የሚያወርደው ትእዛዝ እና መመሪያ ብዛቱ..."

"ይገባኛል ሰንፔር ማዕረግ ትንሽ ችኩልና ሁሉን ትክክል ነኝ ባይ ነው። ከስብሰባው ስወጣ ሰውዬ አናግረዋለሁ። ሰንፔር አሁን ወደ ስብሰባው ቦታ እየደረስኩ ስለሆነ ስልኩን ልዘጋው ነው።"

"እሺ አባቢ፤ ይቅርታ በስብሰባህ መግቢያህ ሰዓት ስሞታ ስላበዛሁብህ"

"ምንም አይደል ሰንፔር እንደውም ስለነገርሽኝ ደስ ነው ያለኝ። ስብሰባውን እንደጨረስኩ ለእሱም እደውላለሁ ለአንቺም እወድልልሻለሁ።"

"እሺ አባቢ መልካም ስብሰባ" ስልኩ ተዘጋ።

------//----

## ኢትዮጵያ-አዲስ አበባ

አቢጋዝ ሮዳስ በድረገጹ ላይ የሚያወጣቸውን የተለያዩ ማሕበራዊ ጽሑፎቹ እንዲሁም መንፈሳዊ ሐሳቦች እጅግ በጣም ስለሚያስደስተው ሮዳስን ወደ ሕቡዕ ድርጅት ሊያስገባው ጥረት እያደረገ ነበር። በጥሩም ሁኔታ ተሳክቶለት አንድ ቀን ሮዳስ ራሱ ስለሚሰራበት ሆስፒታል ምንነትና ማንነት ይጠይቀው ጀመር።

"አቢጋዝ?" ሮዳስ መጀመሪያ አቢጋዝን ዶክተርነቱን ላለመርሳት 'ዶክ' ይለው ነበር አሁን ግን አቢጋዝ ራሱ በስሜ ጥራኝ ስላለው በስሙ ነው የሚጠራው። "... የምትሰራበት ሆስፒታል ስሙ አይገባኝም ምነኛ ነው? ምን ማለትስ ነው?" አለ ሮዳስ እንደ መሳቅ ብሎ

"ሮዳስ ሃላክሃ የሚባል ቃል ሰምተህ ታውቃለህ?" አለ አቢጋዝ የሮዳስን ስሜትና አመለካከት ለመረዳት



Scanned with CamScanner

ሮዳስ ድንግርግር እያለ "ምን ሃክላካ? ሌላ አደናጋሪ ቃል ጭራሽ" አበጋዝ በሮዳስ ፊደል በመግደፉ በሳቅ ፈረሰ።

አበጋዝ ሳቁን ጋብ እያደረገ "ልክ ነህ ሮዳስ ቃሉ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሰማ ትንሽ ያደናግራል፤ ለመጥራት እራሱ ግራ ያጋባል። ሃላክሃ ማለት የእብራይስጥ ቃል ሲሆን የአንድ የትምህርት ክፍል መጠሪያ ነው"

"ኧረ አበጋዝ አወሳሰብክብኝ እስኪ አፍታተህ ንገረኝ? ነገሩ ምንድነው? እኔ እኮ ስለ ሆስፒታላችሁ ነው የጠየኩህ ስሙን አላውቀውም እንዴ ተሳሳትቼ ይሆን?"

"ኖኖ ትክክል ነህ" አለ አበጋዝ የቀኝ እጁን ጠቋሚ ጣት እያወዛወዘ "ግን ከዚያ ጋር ስለተገናኘ ነገር ልነግርህ ፈልጌ ነው። ከመጀመሪያው ልንገርህ። በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ አይሁዶች የትውፊትና ብሉይ ኪዳን አስተምህሯቸው እንዳይበላሽ፣ እንዳይጠፋ እና እንዳይረሳ በረቢ ሂላል አማካኝነት አንድ የትምህርት ክፍል ተመሰረተ። ቀጠለና ሻማይ በተባለ ረቢ የሕግና ሥርአተ ትምህርት ቤት ተከፈተ።

"ይህ አስተምህሮ ወጥና አንድ ሆኖ ታልሙድ ተብሎ መጣ። ታልሙድ የአረማይክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ማስተማር እንደ ማለት ነው። ታልሙድ ሚሽናህ እና ገማራ የተባሉ ሁለት ክፍሎች ሲኖሩት ሚሽናህ ማለት የተደገመ ሕግ ወይም ዘዳግም እንደ ማለት ነው። ትምህርቱም የቀደምት የአይሁድ መምህራንን አመለካከትና ሐሳብ የያዘ ነው። ይህ ትምህርት እስከ ሁለተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በቃል ብቻ የሚሰጥ የነበረ ቢሆንም ከዚያ በረቢ ጻዳድ ሃ ናሲ አማካኝነት አንድ ወጥ መጻሕፍ ሆኗል።" ሮዳስ በአበጋዝ ንግግር እየተመሰጠ መጣ።

ሮዳስ ጥሎበት ምስጢር ይወዳል። የኮምፒውተር ሶፍትዌር ከመጫን ይልቅ የጠፋ የሚስጢር ቁልፍ መፈለግ፤ አንዳንድ አይደፈሩም የተባሉ ድርጅቶችን የምስጢር መግቢያ ቁልፎችን ሰብሮ እንደ መግባት የሚያስደስተው ነገር የለም። ከዚህም በተጨማሪ እንዲህ አበጋዝ እንደሚያወራለት አይነት ወሬ በጣም ይመስጠዋል።

አበጋዝ እየሸሸ ያለውን ጸጉሩን ወደፊት ለፊቱ በእጁ መዳፍ እንደ ማስተኛት ብሎ ሮዳስን ተመለከተው። ሮዳስ በተመሰጦ እያዳመጠው መሆኑን ሲረዳ ንግግሩን ቀጠለ "ገማራ መደምደሚያ ወይም ማጠናቀቂያ ማለት ሲሆን፤ የሚሽናህን አንድምታ ይዟል። ይህ መጽሐፍ ሁለት ጥራዞች አሉት። የመጀመሪያው በአራተኛው ክፍለ ዘመን በኢየሩሳሌም የተጠረዘ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በአምስተኛው ክፈለ ዘመን በባቢሎን ተጠርዟል።

"ሌሎች ደግሞ ቶሴፍታና ሚድራሺ የሚባሉ ናቸው። ቶሴፍት ተጨማሪ ማለት ሲሆን የአይሁድ መምህራን አመለካከትና አስተምህሮ የያዘ ነው። ሚድራሺ ደግሞ



Scanned with CamScanner

ሃይማኖታዊ መጽሐፍት የሚጠኑበት ክፍል ነው። ሚድራሺ ሁለት ክፍል አለው እሱም ሃላክሃ እና ሃጋዳህ ይባላሉ።

"ሃላክሃ ተማሪው በእምነቱ ቀናኢና ታማኝ እንዲሆን የሚማርበት ክፍል ሲሆን። ምንም አይነት መከራ፣ ስቃይና ችግር ቢደርስበት ይህን ስቃይና መከራ ተቋቁሞ እንዴት ለአምላኩና ላመነበት ነገር ቆርጦ እንደሚገኝ ትምህርት የሚሰጥበት ክፍል ነው።"

"አበጋዝ አፈጠንከው ሌክቸር እየመሰለኝ ነው። ረጋ ብለህ ንገረኝ የምታወራኝ የተያዘልኝ አይመስለኝም።"

"እሺ እረጋጋለሁ ከፈልክ እደግምልሀለሁ። ለማንኛውም ሃጋዳህ የሙሴ መጽሐፍት ትረካዊ ክፍሎች የሚታዩበት ሲሆን። የሙሴን አምስቱን መጽሐፍት በጥልቀትና በስፋት ይዳሰስበታል።"

"ስለዚህ ሆስፒታላችሁ የእስራኤሎች ነው ማለት ነው?"

"አይ አይደለም ሆስፒታሉ የኢትዮጵያውያን ነው። በእርግጥ የሚተዳደረው በቦርድ ነው። አርባ ፐርሰንት አክሲዮኑ የተሸጠ ቢሆንም ስልሳ ፐርሰንቱ ፊስአልጎስ የተባለ ድርጅት ነው። የዚያ ድርጅት መስራች ደግሞ አቡነ ፋኑኤል ይባላሉ።"

"ፊስአልጎስ ደግሞ ምንድነው?"

አበጋዝ በተቻለው መጠን ረጋ ብሎ መናገረ ጀመረ "ፊስአልጎስ ነገረ መለኮትንና ሥነ ሕይወትን አንድ ላይ በማቀናጀት በተለየ መልኩ ስለኢየሱስ ክርስቶስ አመስጥሮ የሚናገር መጽሐፍ ነው። ፊስአልጎስ ተጻፈ ተብሎ የሚታመነው 140 ዓ.ም. እስክንድርያ ውስጥ በግሪክ ቋንቋ ነው። የመጽሐፉ ርዕስና ማን እንደጻፈው አይታወቅም ግን 'ዘተናገረ ጠቢብ ፊስአልጎስ' (ጠቢብ ፊስአልጎስ እንደተናገረው) ስለሚል ፊስአልጎስ ተባለ።

"ይህ መጽሐፍ በአምስተኛው ክፍለ ዘመን ወደ ግዕዝ ቋንቋ በተስአቱ ቅዱሳን ተተርጉሟል። ይህ መጽሐፍ እንስሳትን፣ አእዋፋትንና የተከበሩ ማዕድናትን እንደ ምሳሌ እያደረገ ስለ ክርስቶስ የሚያስተምር ነው። ክርስቶስን ከአንበሳ፣ ከከራዲዮን፣ ከፀሐው፣ ከፊንክስ... ጋር እያገናኘና እያመሰጠረ የሚያስተምር ነው።

ሮዳስ ነገሩ ከቅድሙ በባሰ ሁኔታ እየተምታታበት ነው "እንዴት ማለት አልገባኝም?"

"ለምሳሌ ከራዲዮንን ብንወስድ፤ ከራዲዮን ሙሉ ለሙሉ ነጭ የሆነ ወፍ ነው። በጠና የታመመ ሰው እና ዐይኖቹ የታወረ ሰው ካለ ይህ ወፍ ወደ ታማሚው ፊቱን



Scanned with CamScanner

ያዞርና በሽታውን ተሸክሞ ወደ ፀሐይ ይበራል። ከዚያም ደዌውን ተሸክሞ በፀሐይ ይቃጠላል። ከራዲዮን በዚህ ፀሐይ የሰው በሽታ ተሸክሞ ይቃጠልና ሰውየውን ያሽለዋል። ከራዲዮን የተባለው ወፍ ግን ለቀናት ይጎዳል። ወደ ቀድሞው ማንነቱ ለመመለስም ጊዜ ይፈጅበታል። ይህን ስለ ሰው ሕመም ሲል በፀሐይ የሚቃጠለውን ከራዲዮን የተባለውን ወፍ ነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የሚያመሳስለው።"

"እንዴት እንዴት ተደርጎ ነው ኢየሱስና አሁን ያልከው ወፍ የሚገናኙት?"

"ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም አይነት ኃጢያት እና በደል ሳይኖርበት ስለ ሰው ልጅ ሲል የከፈለውን ዋጋ ነው ምሳሌ የሚያደርገው። ከራዲዮኑም ፀሐይ ላይ የሚቃጠለው ስለ ሰው ደዌ እንጂ ስለ ራሱ ሕመም አይደለም። ፊስአልጎስ መጽሐፍ ይህን አካሄድ የወሰደው ከዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ አምስት ቁጥር አምስት ላይ ቅዱስ ዮሐንስ ኢየሱስ ክርስቶስን ከአንበሳ ጋር አመሳስሎ 'ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ' የሚለውን ሐረግ ሁሉን ድል አድራጊ መሆኑን ከአንበሳ ጋር በማመሳሰል ለመግለፅ የተጠቀመበት ዘዬ ተከትሎ ፊስአልጎስ መጽሐፉን ጽፏል።"

ሮዳስ ከተወራው ውስጥ የሚያውቀው ቀድሞ የጠራለትን የጳጳሱን ስም ብቻ ነው። ከአመታት በፊት በእስራኤል አገረ ስብከት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ነበሩ። "ግን ጳጳሱ እንዴት ሆስፒታል ለመክፈት የሚያስችል አቅም ኖራቸው?" እያለ ራሱን እየጠየቀ ነው። አበጋዝ የተቀረውን ታሪክ ገና ምንንም ለማያውቀው ሰው መናገር አልፈለገም።

"ይገርማል እስራኤሎች እንደዚህ ጠንካራ የትምሕርት መሠረት ስላላቸው ነው በዚያ ሁሉ መከራ ውስጥ አሁንም ያልጠፉት። ኢትዮጵያ እንደ እስራኤል አይነት መከራና ስቃይ ቢደርስባት እውነት ለታሪክ ትቀያለች? እኔ አይመስለኝም።

"የእስራኤላውያን ዛሬን እዚህ መገኘት መሠረት ስለ ራሳቸው ያላቸው እውቀት ነው። ያን እውቀት ይዘው በመኖራቸው ነው ለታሪክም ለዓለምም የተረፉት። እስራኤሎች ማንነታቸውን፣ ክብርና ሞገሳቸው የማያጎላ ነገር ካለ ሌላውን ከነሱ ያልሆነውን ምንም ጠቃሚ ቢሆን እንኳ ለመተው አያቅማሙም። ከአገራቸው ከወንዛቸው የተገኘውን ክርስቶስን እንኳ እንደሚፈልጉት ሆኖ ስላላገኙት ተውት። እኛ ግን የራሳችን ያማረ የተዋበ የነጠረ ነገር እያለን የሌላ ያምረናል።"

አበጋዝ ዐይኑን ፈጠጥ አደረገና "ልክ ብለሀል፣ አሁን ግን ኢትዮጵያ እና ቤተ ክርስቲያን ሕማማት ውስጥ ናቸው። በራሳቸው ላይ የእሾህ አክሊል አድርገው፣ እርጥብ እንጨት ተሸክመው፣ በጅራፍ እየተገረፉ፣ ቀራኒዮ ላይ ለመቸንከር መራራ ሃሞት እየተጎነጩ ዳገቱን እየወጡ ነው።"



Scanned with CamScanner

"እውነትህን ነው የምንሰማው ነገር ሁሉ ሕመም" አለበት። ቢያንስ የቀራኒዮን ተራራን መውጣት ራሳችንን ባንታደግ መስቀሉ ላይ ከመቸንከር ቀድመን ልንደርስ ይገባል። አገር ክብሯ እየተዋረደ ነው። ከዚህች አገር ጋር ከአንድ ሺህ ስድስት መቶ አመታት በላይ የዘለቀች ቤተ ክርስቲያን መከራ እየተቀበለች ነው። ታዲያ ምን እናድርግ ትላለህ አበጋዝ?" አለ ሮዳስ አዝን ባለ ድምጽ።

"እኛስ እንደ ሃላክሃ ያለ ተቋም አያስፈልገንም ትላለህ? የነገ ኢትዮጵያን የሚያስቀጥልልን፤ ሕልውናችንን የሚያስጠብቅልን ትውልድ ልንፈጥር ይገባል። ካልሆነ ግን ነገ አገርም ሃይማኖትም አልባ መሆናችን አይቀሬ ነው።"



Scanned with CamScanner

## ምዕራፍ ፲

## እንግሊዝ-ለንደን

የኤፌሶን መንፈሳዊ የቴሌቪዥን ጣብያ የቦርድ አባላት፣ በጣብያው ላይ ዝግጅታቸውን የሚያቀርቡ እውቅ ፓስተሮች፣ ወንጌላውያን፣ ነብያት እንዲሁም እንደ ኤፌሶን ቴሌቪዥን ጣቢያ ሁሉ መቀመጫውን እንግሊዝ አገር ያደረገው የኤልሻዳይ ቴሌቪዥን ጣብያ ቋሚ አማካሪ የሆኑት ዶክተር ሰናይ እና ፓስተር ናፍያድ ለስብሰባው ልምዳቸውንና ተሞክሯቸውን እንዲያካፍሉ ተጋብዘዋል፡፡ በስብሰባው ላይ የኤም አይ ሲክስ ቶኒ የተገኘ ሲሆን ይህ ውይይት ኬንያ ከተደረገው ስብሰባ ቀጥሎ ከሁለት ሳምንት በኋላ የተደረገ ነው፡፡

የስብሰባው ዓላማ ተሐድሶ በገሃድ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ በይፋ ሲታወጅ ስለሆነ የኤፌሶን ቴሌቪዥን ጣቢያ ለተሐድሶው እንቅስቃሴ ሙሉ ሽፋንን እንዲሰጥ የግንዛቤ ማስጨበጫ ለመስጠት ነው፡፡

ስብሰባው ለቶኒ ሲባል በእንግሊዘኛ ቋንቋ የሚካሄድ ሲሆን፤ በስብሰባው ላይም ሁሉም ሰው ወጥና አንድ አይነት አቋም እንዲይዙ ይጠበቃል፡፡ ቀለሙ ይለያይ እንጂ ሁሉም ወንድ ተሰብሳቢዎች ሙሉ ሱፍ ከነ ከረቫቱ አድርገዋል፡፡ ስብሰባው ላይ ሁለት ሴቶች ሲኖሩ እነሱም ሸቅርቅር ብለው ዘንጠዋል፡፡

ፈዛዛ ሰማያዊ ቀለም የተቀባው የመሰብሰቢያ ክፍሉ ግርግዳ ላይ በትልቁ በማሆጋኒ እንጨት የተሰራ መስቀል አለ፡፡ ከመስቀሉ በላይ የሐዋርያት ስራ ምዕራፍ አራት፤ ቁጥር አስራ ሁለት ላይ "መዳን በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና" የሚለው ጥቅስ በነጭ ቀለም በጂፐሰም ተቀርፆ በትላልቅ ፊደላት ተጽፏል፡፡

መሰብሰቢያ ክፍሉ ሰፊ ቢሆንም ተሰብሳቢዎቹ መሀል ላይ ባለው ሞላላውና ረዥም ባለመስታወት ጠረጴዛ ዙሪያ ክብ ሰርተው ተቀምጠዋል፡፡ ከፊት ለፊት ስስ ዥንጉርጉር ሸሚዝ በጥቁር ሱሪ በታኮ ጫማ የተጫማችው መልከ መልካሟ ሰብለ እየተናገረች ነው፡፡ ከጎኗ ያለው ዶክተር ጌታቸው ጥቁር ሰማያዊ ሙሉ ጥቁር ሱፍ በነጭ ሸሚዝ አድርጓል፡፡

ወንጌላዊቷ ኤማንዳ በስተቀኝ ያለች ሲሆን ከእሷ ጎን ቶኒ ተቀምጧል፡፡ ከእነሱ ትይዩ ዶክተር ሰናይና ፓስተር ናፍያድ ጎን ለጎን አሉ፡፡ ከሰብለ ፊት ለፊት ሐዋርያው ሰለሞን ቁጭ ብሏል፡፡

የሁለት ልጆች እናትና በአርባዎቹ መጀመሪያ የምትገኘው ደርበብ ያለችው ሰብለ የመክፈቻ ንግግር ማድረግ ጀመረች "የኤፌሶን ቴሌቪዥን ጣብያ ለተሻለ ተልእኮ

የሚነሳበት ጊዜ ደርሷል። ከዚህ ቀደምም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በተለያየ አጋጣሚ ወጥተው ከእኛ ጋር ለመስራት የፈለጉትን ሰዎች ስናግዛቸው እንደነበር ይታወቃል።" በቀይ ሊፒስቲክ የወዛው ከንፈሯን እርስ በራሱ አጋጥማ ጭምቅ አደረገችውና ንግግሯን ቀጠለች።

"ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካላት ብዙ ቁጥር ያለው የእምነት ተከታይ፤ ለዘመናት በኢትዮጵያ ላይ ቀላል የማይባል ተጽእኖ አንጻር በቂ ወንጌል አልሰበከችም። ስለዚህም እነዚህን ሰዎች እየረዳን ውስጣቸውን እንጂ ሌላ ማንነታቸውን ሳይቀይሩ እዚያው ያሉትን ነፍሳት እንዲታደጉ ጥረት ስናደርግ የነበረው። አሁን ግን በተለየ ሁኔታ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የምትታደስበት፣ በቃሉ የምትታነጽበት፣ የሚያረጋጋው ወንጌልና ወንጌል ብቻ የሚሰበክበት ሰዓት ደርሷል።

"ዘመኑ ለዚህ የተመቸ ስለሆነ ተሐድሶ በድብቅና በጓሮ ሳይሆን በፊት ለፊት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ብርሃኑን ሊፈነጥቅ ግድ ነው። ከወንጌል የጸዳ፣ ገድል የበዛበት፣ ከነገረ ክርስቶስ ይልቅ ነገረ ማርያም የነገሰበት፤ ከትክክለኛው መጻሕፍ ቅዱስ ውጪ በተጨማሪ ሌሎች መጻሕፍት የተሞላችውን ኦርቶዶክስን ልናርማት ይገባል። ይህም እንዲሆን የኤፌሶን ቴሌቪዥን ጣብያ እገዛ ሊያደርግ ይገባል።" ፓስተር ናፍያድ ንግግሩ ያስደሰተው አይመስልም። ከእሱ በተቃራኒ ደግሞ ወንጌላዊቷ ኤማንዳና ዶክተር ጌታቸው በንግግሩ ተደስተው በመስማማት አንገታቸውን ወደ ላይ ወደ ታች እየነቀነቁ ነው።

መሰብሰቢያ ክፍሉ በጥግ በኩል የተተከለው ማቀዝቀዣው ንጹህ አየርን ለማምጣት ቢሽከረከርም መሞቁ አልቀረም። ሰብለ ንግግር እያደረገች እንኳ እንደ ወንዶች አልሞቃትም ምክንያቱም ስሱን የዶልቼ ጋባና ምርት የሆነውን ሸሚዝ ነው የለበሰችው። "የተሐድሶ ጥቅሙና እውነትነቱ" በሚል ርዕስ ያዘጋጀችውን ጽሁፍ ስታቀርብ የተሰማት ደስታና ፊቷ ላይ ያለው ፈገግታ ያሳብቃል።

"... አሜሪካ ካለው ሲኖዶስ ወንጌል የገባቸው ክርስቲኖች ጳጳስ ሆነው በቅርቡ ይሾማሉ። ስለዚህም አዲሱን የተሐድሶ አዋጅ በቅርቡ ያውጃሉ። እኛም ይህን የምስራች በምልአት ልንሰብክ ልናስተጋባ ይገባል። በውግዘትና በስደት ከእናት ቤተክርስቲያናቸው የተሰደዱት ወንድሞቻችንም የልፋታቸውን ውጤት የሚያዩበት ሰዓት ነው።" ሰብለ በፈገግታ ታጅባ ወደ ኋላ ለጠጥ አለችና 'እኔ ጨርሻለሁ እናንተ ሀሳብ ካላችሁ' በሚል ተሰብሳቢዎቹን ገረመመች።

ክፍሉ ሙቀቱ እንዲሁም ሁሉም የተቀቡት ባለ ጥኡመ መአዛ ያለው ሽቶና ቦዲ ስፕላሽ ተደበላልቆ ከውጪ ለመጣ ሰው እንዳች ጭንቅ የሚል ነገር አለው። ከሁሉም በላይ ፓስተር ናፍያድ ገመቹ እንደተጠበቀው ከባድ ተቃውሞውን ለማውረድ የመጀመሪያ ተናጋሪነት ረድፉን ያዘና ንግግሩን ጀመረ።



Scanned with CamScanner

"እኔ የምለው ምን እያደረግን ነው ያለው? ኦርቶዶክሶች ላይ ምን አይነት አዋጅ እያወጅንባቸው ያለው?" ፓስተር ናፍያድ ሬጋ ያለና ኮስታራ ሰው ነው። ዛሬ ግን በንግግሩ ውስጥ ቁጣና ስሜታዊነት ይነበባል።

"እነሱ ከእኛ መንገድ ጋር የሚቃረን አቋም አላቸው፤ የኛን የእምነትና አስተምህሮ አይቀበሉም ብለው ያወገዟቸውን ሰዎች እንቀበላለን..."

በቅርቡ ከእሷ እድሜ የሚያንሰውን ወጣቱን ዘማሪ ያገባችው ወንጌላዊት ኤማንዳ ብልጭ አለባት። የመናገር እድሉን ሳታገኝ ዝም ብላ መናገር ጀመረች "ፓስተር ምን ማለት ነው? ማንም ሲድን ቢፈልግ አንተ ከእኛ አይደለህም አትግባ እንለውም መቼም" አለች ቆጣ ብላ። ሌሎችም አንገታቸውን በአዎንታ ነቀነቁ። ዶክተር ሰናይ ግን ኮስተር ብሎ ፊቱን በስተቀኝ አዙሮ ፓስተር ናፍያድን በጥሞና እያዳመጠ ነው።

"ይቅርታ ኤማንዳ አልጨረስኩም ነበር። እኛ ሰዎችን መቀበላችን እነሱም እኛን መምረጣቸው ደስታ ይሰጠኛል። ግን ሲጀመር መጠለያ አረጉን እንጂ መርጠውን መጡ ለሚለው እርግጠኛ አይደለሁም። ካመኑበትና ፈልገውን ከመጡ በጣም ደስ ይለኛል። እኔን አልገባ ያለኝ ግን የኦርቶዶክስን ቀኖና እና ዶግማ በእነዚህ ሰዎች አማካኝነት እያነሱ መተቸት፤ ትችቱንም በእኛ ቴሌቪዥን ጣብያ ማስተላለፍ ምን ማለት ነው? የምናደርገው ነገር ይገባናል? በጣም የሚገርመው እነዚህ ሰዎች ሲወገዙ ማዕረግና ሥልጣናቸውንም ጭምር ነው። ምክንያቱም ይህን ማዕረግ የሰጠቻቸው ቤተ ክርስቲያኗ ስለሆነች የመንጠቅም መብትም አላት። ታዲያ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ይህን የተነጠቀ ማዕረግ በቴሌቪዥን ላይ ተጽፎ፤ አለባበሳቸው ኦርቶዶክሳዊ ሆኖ ነው የሚታዩት። የእኛ ቸርች ማዕረጋቸውን መልሳላቸው ነው ወይስ ኦርቶዶክሶችንን ለማብሸቅ ነው? ይህ እኮ በሕግም ሊያስጠይቅ ይችላል?" አለና ለጠየቀው ጥያቄ መልስ የሚሰጠኝ ካለ ብሎ ዝም አለ።

--------//----

## ኢትዮጵያ-አዲስ አበባ

ሮዳስና አበጋዝ በሚነፍሰው ምሽት በአግራቸው አስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያንን ሽቅብ ይዘው በውጪ ጉዳይ ወደ ቤተ መንግስት የሚወስደውን መንገድ ይዘዋል። ጨዋታቸው ደርቷል። አበጋዝ ይናገራል ሮዳስ ደግሞ በጥሞና ያዳምጣል። ወሬያቸው ባለፈው ጀምረውት ስለነበረው ስለ ሃላክሃ ነው።

ጥንድ ጥንድ የሆኑ ፍቅረኛሞች ተቃቅፈው ካልሆነም እጅ ለእጅ ተያይዘው ጸጥታ በሰፈነበት ውጪ ጉዳይ መስሪያ ቤት አካባቢ ይንሸራሸራሉ። አንዳንዳ ወጣትና አዛውንቶች በተናጠል እንዲህ እንደነ ሮዳስና አበጋዝ በቡድን እየተጫወቱ አቀበቱን የሚወጡ፤ ቁልቁለቱን የሚወርዱ አሉ።



Scanned with CamScanner

አበጋዝ በቀስታ እጁን እያንቀሳቀሰ ያወራል "የእስራኤሉን ሃላከሃን የመሰለ ኢትዮጵያ ውስጥ ፊስአልጎስ የተባለ ሕቡዕ ድርጅት አለ። ስራው ግን ገሀድ ነው።"

"ምን ማለት ነው ሕቡዕ ድርጅት ስራው ገሀድ?"

"ምን ማለት መሰለህ ሚሽናህ ሆስፒታል ሕጋዊና ሕዝቡን የሚያገለግል ነው። ሕቡዕ የሆነው የሆስፒታሉ ባለቤቶችና አላማ ነው።"

"እኬ አሁን ገባኝ"

"ይህን ድርጅት ያቋቋሙት በእስራኤል አገረ ስብከት አስተዳዳሪ የነበሩት አቡነ ፋኑኤል ናቸው። አላማውም በዓለም ያሉትን የኦርቶዶክስ ቤተ እምነቶችን በአጠቃላይ አፍርሶ የታደሰች ኦርቶዶክስ ለማድረግ ከአሜሪካ እና ከእንግሊዝ መሪዎች ወደ ሲአይኤና ኤም አይ ሲክስ የስለላ ድርጅቶቻቸው መመሪያ ከተላለፈ በኋላ ነው።

"አልገባኝም ምክንያቱ ምንድነው? እነዚህ ሐገሮች አንድም ኦርቶዶክስ አማኝ ዜጋ የላቸውም ማለት ነው?"

"ሀሳባቸው በነሲብ ኦርቶዶክስን ከመጥላት የተነሳ አይደለም። ከዚያ ይልቅ ያደጉ አገራት ግሎባላይዜሽን ለማስፋፋት፣ ሊበራሊዝምን እንደ ፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም፣ ነጻ ገበያን እንደ ኢኮኖሚ መርህ በማስፋፋት ዓለምን ለመቆጣጠር ይሰራሉ። ይህ የግሎባላይዜሽንን አካሔድ ኦርቶዶክስ፣ እስልምና፣ ኮንፊሽይዝም፣ ቡዲዝምን... የመሳሰሉ ጥንታዊ እምነቶች በገሀድ እየተቃወሙት ነው።

"አሜሪካ እና እንግሊዝ የግሎባላይዜሽን ዋና አቀንቃኝ እንዲሁም ተጠቃሚ ስለሆኑና በጋራ ስለሚሰሩ ለግሎባላይዜሽን እደጋ የሚባሉትን ሃይማኖቶች፣ አገራትና ባህሎችን እንደ ጠላት ፈርጀው የማጥፋትና የማዳከም ስራ ይሰራሉ።

"ስለዚህም ሌላውን እንደሚያደርጉት ሁሉ ኦርቶዶክስን ሰክዩላሪዝምና ሲንክሬሲትዝም በሚባል ፖሊሲያቸው ማጥፋትና መበረዝ ይፈልጋሉ። እነዚህ ሁለት ፖሊሲዎች ዓለምን ከሃይማኖት የጸዳችና የሰይጣን አምልኮን የሚያስፋፉበት ልዩ መንገድ ነው። የሰክዩላሪዝም ጽንሰ ሀሳብ ሃይማኖትና መንግስት አንዱ በአንዱ ጣልቃ እንዳይገባ ለመነጣጠል ነው ቢሉም ዋናና ድብቁ አጀንዳቸው ግን ዓለም ለሰይጣን አምልኮ የተመቸና ሃይማኖት የለሽ ማኅበረሰብ መፍጠር ነው።

"ሴንክሬሲቲዝም ደግሞ የሃይማኖትን አስተምህሮ ከሌላ የሃይማኖት አስተምህሮ በመቀላቀል ሰዎች የሃይማኖታቸው ድንበር እንዲጠፋባቸው ማድረግ ነው። የሃይማኖት ምንጮች አንድ ናቸው ብሎ ማሳመንና ብዙም ሕግና ሥርአት የሌለው



Scanned with CamScanner

ገደብ የለሽ ነጻነት ለግለሰብ መስጠት ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያን ለሚፈልጉት አላማ ለማዋል ኦርቶዶክስን አድሶ በአንግሊካን ፕሮቴስታንት ስር ማድረግ ይፈልጋሉ።"

ሮዳስ በአግራሞት ውስጥ ሆኖ አቢጋዝን እያዳመጠ ስለነበረ ሳያስበው ጥያቄ ሰነዘረ "እዚህጋ ያልገባኝ ነገር አለ። ኦርቶዶክስም ሆነ ፕሮቴስታንት አላማቸው አንድ ነው። የአስተምህሮ ልዩነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ አማኞቻቸውን ወደ ገነት ለማስገባት የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲወርሱ ማድረግ ነው። ስለዚህ ኦርቶዶክስን አድሰው ፕሮቴስታንት ቢያደርጓት አሁንስ ቢሆን ምን ይጠቀማሉ?" አለ ሮዳስ ግር ባለው መንፈስ አቢጋዝን እያየው።

"ይኸውልህ ሮዳስ አሜሪካም ሆነ እንግሊዝ እንደ አገርም ሆነ እንደ ፖሊስ ለየትኛውም አይነት ሃይማኖት ደንታ የላቸውም። ከእስልምና ጋር ሲጋጩ ለክርስቲያን አዝነው ወይም ለክርስትና ተቆርቁረው አይደለም። ከዚያ ይልቅ እስልምና ለአላማቸው ምቹ ስላልሆነ ነው።

"እነዚህ አገራት ግሎባላይዜሽንን ለማስቀጠል ነጻ ገበያ መር ሊበራሊዝም እንዲሁም የግለሰብ ነጻነትን እስከ ጥግ ድረስ መፍቀድ ይፈልጋሉ።" አቢጋዝ ፈገግ ብሎ ለሰከንዶች ደስ ከሚለው ነፋሻማ አካባቢ ላይ የሚበቃውን አየር ሳብ ሳብ ካደረገ በኋላ ንግግሩን ቀጠለ።

"ስለዚህም በተለይ አሜሪካ እነዚህን ፖሊሲዎቿን የሚያግዷትን ማጥፋት ግድ ይላታል። ለምሳሌ ኦርቶዶክስን ብታይ ማኅበራዊ ትስስሩ የበዛ፣ ከግለሰብ አምልኮ ይልቅ በቡድን ማምለክ፣ መንፈሳዊ ሥልጣኑም ተዋረዳዊ ወይም ኃርዮሻዊ ነው።

"ለምሳሌ ኦርቶዶክስ ድኅነት በክርስቶስ አማካኝነት ለዓለም ሁሉ መጣ ትላለች፣ ፕሮቴስታንት በተቃራኒ ጌታን እንደ ግል አዳኝ ተቀበል ትላለች። በኦርቶዶክስ ግለሰባዊ የሃይማኖት አረዳድና አተረጓጎም የለም። ይልቁንስ መጽሐፍ ቅዱስን የምንረዳው አበው፣ ከዚያ ቀደምት ሊቃውንት ከሐዋርያት በተቀበሉት እነርሱም በተረዱበት መንገድ እንጂ እያንዳንዳችን በመሰለንና ደስ ባለን መንገድ ተርጉመን አይደለም ብላ ታምናለች።

"ፕሮቴስታንትን የወሰድክ እንደሆነ ማንም ግለሰብ አምስቱን የማርቲን ሉተር 'ሶላዎች' እስካላፈረሰ ድረስ መጽሐፍ ቅዱስን እንደፈለገው መተርጎምና ተረጉሞም ከፈለገ የራሱን እምነት መያዝና እምነቱን እንደተረዳው መግለጥ ይችላል ይላል። ይህ ለግለሰቦች የተሰጠ ገደብ የለሽ ሥልጣን ለመንፈሳዊ ጉዳይ ለዘብተኛ ያደርጋል። ከዚህም በላይ ሐዋርያዊት ከሆነችው አንዲት ሃይማኖት ሊያወጣ ይችላል ብላ ኦርቶዶክስ ታምናለች። ከዚህ በተቃራኒ ላሉት የግሎባላይዜሽን አራማጆች ደግሞ እንዲህ ያለ ኦርቶዶክሳዊ አስተሳሰብ የሚዋጥ አይደለም።



Scanned with CamScanner

"እንደምታውቀው የአሜሪካም ሆኑ የእንግሊዝ ባለ ሥልጣናት ፕሮቴስታንትን እንደ ስቴት እምነት ያዩታል፡፡ ይህን የሚያደርጉት ክርስትያን ለመባል ወይም ክርስትና ገዷቸው አይደለም፡፡ ከዚያ ይልቅ እምነቱን እንደፈለጉት በልካቸው እየሰፉት ስለሆነና ለግሎባላይዜሽን ስለተመቻቸው ነው፡፡ ሌላው የየትኛውንም አገር መንፈሳዊም ሆነ ብሔርተኝነት ስሜትን በፕሮቴስታንትነት ማለዘብ እንደሚቻል ልምድም ተሞክሮም አስተምሯቸዋል፡፡"

አበጋዝ ሮዳስን ወደ ጎን ዞር ብሎ ተመለከተው፡፡ ሮዳስ በትክክል በነገሩ እንደተመሰጠ ያስታውቃል፡፡ አበጋዝ ንግግሩን ቀጠለ "ስለዚህ ኦርቶዶክስን ለአላማቸው ሊያውሏት ብቻ ሳይሆን ሊያጠፏት ነው፡፡ በይበልጥ ኢትዮጵያ ባለፉት ዘመናት ውስጥ ለነጮች የተመቸች አገር ስላልነበረች፣ እንዲሁም የአፍሪካ ሕብረት መቀመጫ ስለሆነች ከተሳካላትና ካደገች ለሌላው አፍሪካም ቢሆን ማስተማሪያ ስለምትሆን በኃይልና በአላማ እየሰሩባት ነው፡፡ ለነጮች እንዳትመች ያደረገው ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ናት ብለው ደምድመዋል፡፡"

Scanned with CamScanner

# ምዕራፍ ፲፩

## አሜሪካ-ዋሽንግተን

ሩቢዩ የናይክ ምርት የሆነውን ነጠላ ጫማ የተጫማ ሲሆን ቡኒ ቁምጣና ነጭ ቲሸርት ለብሶ ወደ መታጠቢያ ቤት ውስጥ ገባና በመስታወት ውስጥ ፊቱን ተመለከተ። ፊቱ በላብ ወርዝቷል። ጺሙም አድጓል። በእጁ ፊቱን አበስ አደረገና የጥርስ ብሩሹን ከተቀመጠበት አነሳና የመፋቂያ ሳሙናው ብሩሹ ላይ አደረገው።

ሩቢዮ ጥርሱን እየፋቀ ከመታጠቢያ ቤት ወደ መኝታ ቤቱ ተመለሰ። መርሐዊ አልጋው ላይ በጀርባው የተኛ ሲሆን ሩቢዮ ወደ ውስጥ ሲገባ አየውና በደስታ ፈገግ አለ። ሩቢዮን እንዲህ በቁምጣ ሲያየው ደስ ከሚለው ነገሩ ውስጥ አንዱ ቢጫውና ድፍት ያሉት የእግር ጸጉሮቹ ናቸው።

ሩቢዮ በአንድ ጉንጩ የጥርስ ሳሙናውን እንደመያዝ ብሎ "ማር አትነሳም?" አለ።

መርሐዊ ፈገግ አለና ለሩቢዩ ፈገግታ አጸፋውን ከልብ በመነጨ ፈገግታ እየመለሰለት "እሺ እነሳለሁ፤ ዛሬ እንደውም የመጨረሻ አገልግሎት አለኝ" አለ መርሐዊ ከተኛበት ተነስቶ ቀና ለማለት እየሞከረ። እውነቱን ነው አሁን የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን 'አቡነ ሰላማ' ተብሎ ተሰጥቶታል ስለዚህ ቀድሞ ዋሽንግተን ዲሲ ከሚገኘው ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በቆሞስነት የሚያገለግል የነበረ ቢሆንም አሁን ግን የካሊፎርንያ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ ስለ ተሾመ መሄድ ይኖርበታል። ስለዚህ የዲሲ ምዕመን "ይደልዎ" እያለ ሽኝት ሊያደርግለት ነው።

ሩቢዮና መርሐዊ ግብረ ሰዶማዊ እንደሆኑ ማንም አያውቅም። በተለይ መርሐዊ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ስለሆነ ይህ ነገር ቢሰማ ምድር ቀውጢ እንደሚሆን ለቅጽበት ያህል ውል ሲለው ይሰቀጥጠዋል። ስለዚህ ሩቢዮና መርሐዊ የፍቅር ግንኙነታቸው እንዳይታወቅ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። መርሐዊ በትዝታ ጎንደር ደብረ አባይ አቡነ ሳሙኤል ገዳም ቆሎ ተማሪ ቤት እያለ የሆነው ሁሉ በሃሳቡ መጣበት።

--------//---------

መርሐዊ የቆሎ ተማሪ ሳለ ለምሳና ለእራቱ የሚሆን ምግብ "በእንተ ስማ ለማርያም" ብሎ ለመቀፈፍ በአካባቢው ይዘዋወራል። መርሐዊ በዚህ አጋጣሚ አንድ ቤት ሁልጊዜ ከመሄዱ የተነሳ ከአንዲት ሴት ጋር ይግባባል።

ይህቺ ሴት ግን በአካባቢው ባለ ደብር ውስጥ ቀዳሽ ቄስ የነበሩት ሚስት ነበረች። መርሐዊ ቄሱ ወደ እርሻ ሲሄዱ እሱ ትምህርት ከሌለው እሷጋ እየሄደ ምግብ



Scanned with CamScanner

ይበላል፡፡ ለአራቱም በአኮፋዳው ቂጣውን፣ ፍትፍቱን፣ ቋንጣውን... ከትታ፣ በኮዳውም ጠላ ካለ ጠላ ካልሆነ ቅራሪ ትሞላለትና በደስታ ትሸኘዋለች፡፡

ይህ ቅርበታቸው ወደ ፍቅር ተቀይሮ ግንኙነት ይጀምራሉ፡፡ መርሐዊ ከፍቅር ግንኙነቱ በተጨማሪ ለአራት ለምሳ አለማሰቡ እረፍት ሰጥቶታል፡፡ ችግሩ ሕጋዊ ሚስት ከሌለው በስተቀር ከሴት ጋር ጾታዊ ግንኙነት ያለው ሰው ድቁናው እንደሚያፈርስ ያውቃል፡፡ የከፋው ነገር ከካህን ሚስት መሆኑ ነው፡፡ ይህም ቢሆን ማንም እንደማያውቅበት ስለሚያውቅ ብዙም አላስጨነቀውም፡፡

የፍቅር ግንኙነቱ በዚህ መንገድ ለወራት ዘለቀ፡፡ መላመድ፣ ከሴትየዋ የያዘው ከባድ ፍቅር፣ መነፋፈቁ ተጨምሮ ወትሮ የሚያደርገውን ጥንቃቄ ትቶ በሩቅ የሴትየዋ ባለቤት አለመኖራቸውን ካረጋገጠ በኋላ ሰርክ እየሄደ መዋል ጀመረ፡፡

አንድ ቀን መርሐዊ መልዕክት እንዲያደርስ ራቅ ወዳለ ሌላ ደብር ተልኮ ለሶስት ሳምንት ያህል ከቆየ በኋላ ወደ ደብሩ ሲመለስ ሴትየዋ በጣም ናፈቀችውና ወደ ሴትየዋ ቤት ሄደ፡፡ እንደተያዩ ናፍቆታቸውን መቆጣጠር ስላልቻሉ ቀጥታ መደብ ላይ ይወድቃሉ፡፡

የሴትየዋ ባል እርሻ ሲያርሱ ድንጋይ እግራቸውን ይቆርጣቸውና ማሰሻ ፍለጋ ወደ ቤት ይመጣሉ፡፡ መርሐዊና ሚስታቸው በወሲብ ስሜት ሰክረው መደቡ ላይ ከፍ ዝቅ ሲሉ ይደ፟ዟቸዋል፡፡ ባልየው በድንጋጤ የሚያደርጉት ይጠፋባቸዋል፡፡ ሚስታቸውና መርሐዊም በድንጋጤ ድርቅ ብለው ዓይናቸው በሀፍረት ቁልጭልጭ ማድረግ ጀመሩ፡፡

ሰውየው ከድንጋጤያቸው ይመለሱና አጠገባቸው ባገኙት ሽመል መርሐዊን ግንባሩን ይሉታል፣ መርሐዊ ራሱን ይስታል፡፡ ሚስታቸው እሪታዋን ትለቀዋለች፡፡ ሰውየው ሚስታቸውን ይተውና በዱላቸው ራሱን የሳተውን ልጅ ሲያዩ የሞተ መስሏቸው መልሰው በመደንገጥ ውሃ ያደርጉበታል፡፡

መርሐዊ ውሃ ሲደረግለት ራሱን ከሳተበት ይነቃል፡፡ ይህኔ ሰውየው ንዴታቸው ዳግም ይመለሳል፡፡ እጅና እግሩን ጥፍር አደርገው ያስሩትና በብልቱ ላይ በገዛ ራሱ ኮዳ ውስጥ ቅራሪ ከትተው ያንጠለጥሉበታል፡፡

የሰውየው ሚስት ደንግጣ ጥላቸው ትጠፋለች፡፡ መርሐዊን ብልቱ ላይ ኮዳውን እንዳንጠለጠሉበት መሽቶ ይነጋል፡፡ ከዚያም መርሐዊን ከታሰረበት ፈትተው ይለቀቁታል፡፡ መርሐዊ ከዚያን ቀን ጀምሮ ጾታዊ ግንኙነት ማድረግ ተሳነው፡፡ ስሜት ቢኖረው እንኳ ብቁና ዝግጁ አካል የለውም፡፡



Scanned with CamScanner

መርሐዊ ፈጣሪ እንደቀጣው በየቀኑ ያብሰለስል ጀመር። ከዚህ ማብሰልሰሉ ለመውጣት ትምርህቱን በጥሞና መከታተልና ኢጲስ ቆጶስ ለመሆን ቆረጠ። በትምህርት ጎበዝ ሲሆን ሲቀድስም ጥሩ ድምጽ ነበረው። እንዳሰበው ሆነለትና አለቃ መሠረት ስብሐት ለአብ ቦስተን ዩንቨርስቲ የትምህርት እድል እንዲያገኝ አደረገው።

መርሐዊ ግን ተስፋ በመቁረጥ ውስጥ ሆኖ አሜሪካ ገብቶ መማር የጀመረ ቢሆንም በልቡ ውስጥ ከፍተኛ ቂም በቤተ ክርስቲያኗ ላይ ቋጠረ። ምክንያቱም "ቅስናዬን እንዳሳጣኸኝ እኔም ወንድነትህን አሳጣሀለሁ" እያሉ ብልቱ ላይ የገዛ ኮዳውን ያንጠለጠሉበት ቄስ እና ቅስና የሚባል ማዕረግ ትዝ ይለዋል። ስለዚህም ማዕረጉንም፣ ቅስናውን የምትሰጠውን ቤተ ክርስቲያንንም ተጠየፋት።

ለዚህ ነው ለንዴቱ መበቀያና ቂም መወጫ ያለውን ኢጲስ ቆጶስነት ለመሆን የቆረጠው። በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሰረት የማይገባውን የጵጵስና ሥልጣን ለራሱ ወስዶ የቤተ ክርስቲያኗን ማዕረግ ምንምነቱን ማስመስከር ይፈልጋል። ይህን ሀሳቡን ከግብ እንዲያደርስ የረዳው ሩቢዮ ነው።

መርሐዊ ሁለተኛ ዲግሪውን በቦስተን ዩንቨርስቲ ሲሰራ ነው ከሩቢዮ ጋር የተዋወቁት። ሩቢዮ የመርሐዊን ጭንቀት፣ መረበሽ፣ ራስን ከመውቀስ አባዜ አወጣው። ከዚያም ብሶ የፈለገው አይነት ጾታዊ ግንኙነት እንዲኖረው በህክምናና በሥነ ልቦና እንዲረዳ አደረገው። ከዚያ በኋላ ሩቢዮ እና መርሐዊ የሰዶም ፍቅረኛሞች ሆኑ።



Scanned with CamScanner

## ምዕራፍ ፲፪

## እንግሊዝ-ለንደን

ሰብለ ቀጣዩን የመናገር እድሉን ለዶክተር ፓስተር ጌታቸው ሰጠች፡፡ በእድሜ ተለቅ ያሉት ዶክተር ጌታቸው በፓስተር ናፍያድ ገመቹ ንግግር ደስ ያላቸው አይመስልም "ፓስተር ሀሳብህን አከብራለሁ" ብለው ንግግራቸውን በእርጋታ ጀመሩ፡፡ ከሰውነታቸው ግዝፈት የተነሳ ጎላ ያለ ድምጽ ማውጣት ይከብዳቸዋል፡፡

"ፓስተር አንተም እንደሌላ ሰው እንዲህ ማሰብህ ቅር አሰብሎኛል፡፡ አንተ ኦርቶዶክስ ላይ ደባ የሰራን አስመሰልከው፡፡ እየሰራን ያለነው የእግዚአብሔርን እቅድ ነው፡፡ ትውልድን የማዳን ሥራ፡፡ ትውልዱ በውርስ የተቀበለውን እምነት በወንጌል ለመግለጥና ለመድረስ ነው፡፡ በቃ ከዚህ ውጪ ኦርቶዶክስን ለመረበሽ ወይም አማኞችን ለመበጥበጥ አይደለም፡፡" ብለው መጨረሳቸው እንዲታወቅ ወደ ሰብለ ፊታቸውን አዞሩ፡፡

ኤማንዳ ጥያቄ ማንሳት ስለፈለገች በዐይኗ ሰብለን 'እኔ ላውራ?' አለች፡፡ ሰብለም ገባትና "እሺ ኤማንዳ" አለች አንገቷን ወደ ሰብለ እየሰበቀች፡፡

"ቅድም ፓስተር ባለው ነገር ላይ ጥያቄ አለኝ፡፡ አለባበሱና ማዕረጉ ለኦርቶዶክሶች ብቻ ማነው የሰጣቸው? እኛም ኢትዮጵያዊ ነን፡፡ ስለዚህ ለእነዚህ ሰዎች እንደ ኢትዮጵያዊነታችንና እንደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንነታችን የመፍቀድ መብት ያለን ይመስለኛል፡፡"

ፓስተር ናፍያድ በኤማንዳ ሀሳብ እጅግ በጣም ደንግጧል፡፡ ሊስቅ ፈልጎ አልሳቀም፤ ሊቆጣ ፈልጎም ሊቆጣ አቃተው ብቻ ግራ ገባው ከማን ጋር እንደተሰበሰበ ሁሉ ተምታታበት፡፡ ለማንኛውም ይህን መልስ ዶክተር ሰናይ እንደሚመልስ ስለገባው ዝም አለ፡፡ ዶክተር ሰናይም ከፓስተር ናፍያድ በላይ ተናዷል፡፡ በዚህ ልክ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ይነሳል ብሎ አልጠበቀም፡፡ ሳያውቀው ውስጡን አመመው፡፡

ዶክተር ሰናይ አለቃ መሠረት ስብሐት ለአብ አራት ኪሎ ካለው ከባዕታ ማርያም ገዳም የወሰደው ልጅ ነው፡፡ ሰናይ አሜሪካ ካለው ዱክ ዩንቨርስቲ የነገረ መለኮት ትምህርት ቤት ገብቶ ትምህርቱን እስከ ፒኤች ዲ ተምሯል፡፡ ሰናይ የኦርቶዶክስን ትምህርቶች ጠንቅቆ ያውቃል በመንፈሳዊ ኮሌጅም ትምህርቱን በብቃት ነው የጨረሰው፡፡ በተሐድሶ ጉዳይ ያለው አቋም ከተሰበሰቡበት ሰዎች በጣም ይለያል፡፡

ሁሉም የጥያቄውን መልስ ከዶክተር ሰናይ በመጠበቅ ፊታቸውን ወደ እሱ አዞሩ "እሺ..." አለና ትንሽ ሰዓት ትንፋሹን ያዝ አደረገ፡፡ ዶክተር ሰናይ ስሜታዊ ሆኖ መናገሩን ስላልፈለገ ትንሽ የጥሞና ሰአት ለመውሰድ ብሎ ዝም አለ፡፡



Scanned with CamScanner

“ኤማንድ አንቺ ያነሳሽው ጥያቄ በቀጥታ ከመመለስ ይልቅ እንደሚዲያ ሥርአትም የቱ ያስጠይቃል የቱ አያስጠይቅም ብለን ልንመልሰው የሚገባን ይመስለኛል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እነዚህን የተወገዙትን ሰዎች ማዕረግና ስማቸውን ስትስርዝ እኛ ግን ከነ ማዕረጋቸው ከተቀበልናቸው ትልቅ ወንጀል ሰርተናል።

“ለምሳሌ ማንም ሰው ከመሬት ተነስቶ መቶ አለቃ፣ ኮሬኔል ወይም ጀነራል እንደማይሆንና የእነዚህንም ማዕረጋትና ልብስ እንደማይለብሰው ሁሉ የቤተ ክርስቲያንንም ማዕረግም ሆነ አልባሳት እንደዚሁ ነው። አንድ ጀነራል በተለያዩ የሥነ ምግባር ግድፈቶች ምክንያት ማዕረጉ በሕጋዊ መንገድ ቢነጠቅ አልባሳቱን ተነጥቋል ማለት ነው።

“ነገር ግን ይህን የተነጠቀውን ማዕረግ ወይም ልብሱን ተጠቅሞት ቢገኝ እንደሚያስቀጣ ሁሉ የእነዚህም ሰዎች ጉዳይ እንደዚያ ነው። እንደ ወታደራዊ ልብሱ ሁሉ የቤተ ክህነቱም ልብስ ሊከበር ይገባል። አይደለም ወታደር ቤት ቀርቶ አለማዊ ትምህርት ቤትም ዲግሪም ሆነ ዶክትሬትን የሚያሳምንና ሕጋዊ የሆነ የሚያስቀማ ምክንያት ካገኘ መቀማትና ማስረጃ የለሽ ማድረግ ይችላል።

“ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለምትሰጠው ስምና ማዕረግ ብሎም መንጠቅ ሉአላዊ ሥልጣን አላት። በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ የአለባበስ ሥርአቶች አሉ። እነዚህ አለባበሶች እንዲሁ በዘፈቀደ አይለበሱም። ለአንዳዶቻችን ካባ መልበስ ቅንጦት ሊመስለን ይችላል። እንዲሁም ነጠላ ማጣፋት ወይም ማደግደግ፣ ጥንግ ድርብ መልበስ፤ ጥለት በቁመቱ መልበስ እንዲሁ ዘልማድ ይመስለናል። ግን አይደለም። በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካባ የሚለበሰው ወንበር ዘርግቶ የሚያስተምር ሊቅ ብቻ ነው። በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ለምስጋና ሲቆም የድጓ፣ የአቋቋም መምህራን፤ የደብር አለቃ፣ የደብር አስተዳዳሪ፣ መሪጌቶች፣ ሊቀ ዲያቆን፣ ዲያቆን፣ መዘምራን... እያለ እንደየ ማዕረጋቸው ሆነው ያገለግላሉ። እነዚህ ሰዎች እንደየ ማዕረጋቸው ከሸማ የተሰሩ የተለያዩ አልባሳት ይለብሳሉ። ይህ የአለባበስ ሥርአት፣ ማዕረግና ሥልጣን የኦርቶዶክስ ብቻና ብቻ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ብንከሰስ ፍርድ ቤት ሊያቆመንና ሊያስፈርድብን ይችላል። የባለቤትነት ጥያቄ ነውና።

“አይደለም ቤተ ክርስቲያኗ ሥልጣናቸውን ገፋቸው ቀርቶ የሌላ እምነት ድርጅት እራሱ ለምስጋና የያሬድና ዜማ ለመጠቀም ከቤተ ክርቲያኗ ማስፈቀድ ይኖርበታል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀብት ነው ብለን በድፍረት መጠቀም ለዚያውም ኦርቶዶክስን ቅር በሚያስብል መልኩ ትንሽ የሚከብድ ይመስለኛል።” ሰናይ ደስታ ተሰማው። ማለት ያለበትን ተናግሯል። ባይናገር ኖሮ ዛሬ አልጋው ላይ ሲገላበጥ ነበር የሚያድረው። ቅር እንደሚላቸው ይገባዋል። ግን የሚያማክራቸው እንዳይሳሳቱ እንጂ እንዲሳሳቱ እስካልሆነ ድረስ እውነቱን መናገር አለበት።



Scanned with CamScanner

ሐዋርያው ሰለሞን መናገር የፈለገ ስለመሰላት ሰብለ እድሉን ሰጠችው "በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናት ተሐድሶ የጠራነው እኛ ነን እንዴ ፓስተር?" ሰለሞን ያስጨነቀው አለባበስ ወይም ማዕረግ አይደለም ከዚያ ይልቅ የተሐድሶ ጉዳይ ነው፡፡ ሰለሞን ወደ ፓስተር ናፍያድ እየተመለከተ ነው የሚናገረው፡፡ ፓስተር እየሆነ ያለው ያናደደው ይመስላል፡፡ ያው የተለመደውን ተሐድሶን የጠሩት አባ እስጢፋኖስ ናቸው ሊለው ነው፡፡

"ፓስተር በአስራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን አባ እስጢፋኖስ ናቸው ከማርቲን ሉተር ቀድመው ከክርስቶስ በቀር ለማንም አልሰግድም ያሉት…" ሐዋርያው ሰለሞን ፓስተር ናፍያድ እንደጠበቀው ተናገረ፡፡

ቅርብ ጊዜ ስለ ተሐድሶ ሲወራ ሁሉ ሰው አባ እስጢፋኖስን ስለሚጠቅስ ፓስተር ናፍያድ ስልችት እያለው ነው፡፡

"እኛስ ቢሆን ከየት ነው የመጣነው ቤተሰቦቻችን ኦርቶዶክስ አይደሉም እንዴ? በውርስ እምነታችንን ተቀበልን ያለ ወንጌል፤ ያለ ቃሉ፤ ስለዚህም ጌታን ፈልገን አገኘነውም፡፡ እዚህ ያለነው እያልን ያለው ጌታን በማጣት እየተቅበዘበዙ ላሉት ነፍሶች እንድረስላቸው ነው፡፡" ሐዋርያው ሰለሞን አባቱ ባለውቃቢ ናቸው፡፡ እናቱም የባላቸውን ውቃቢ የሚካድሙ ናቸው፡፡ ሐዋርያው ሰለሞን ለቤተሰቦቹ ውቃቢ አማኝ መሆን ዋና ምክንያቱ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ነው ብሎ ያምናል፡፡ ስለዚህ ኦርቶዶክስ ስትታደስ የቤተሰቦቹም ሆነ የሌሎች የእሱን ቤተሰብ መሰል ታሪክ ያላቸው ሰዎች ይድናሉ ብሎ ያምናል፡፡

ፓስተር ናፍያድ ከተሰብሳቢዎቹ ጋር በሀሳብ የተለያየ መሰለው፤ ሀሳብ መላ አካሉን ድክም ስላደረገው ሳይሰበው በረዥሙ "ኡፍፍፍፍፍ…" ብሎ ተነፈሰ፡፡

-------//-----

## እንግሊዝ-ለንደን

ስብሰባውን ከእረፍት መልስ የቀጠሉ ቢሆንም ውጥረቱ ግን በመሰብሰቢያው ክፍል ነግሷል፡፡ በየጠረጴዛቸው አዳዲስ የታሸገ ውኃ ተቀምጦላቸዋል፡፡ ዶክተር ሰናይ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ያስፈልጋታል ብሎ ቢያምንም ልክ ማርቲን ሉተር ካቶሊክ ላይ እንዳስነሳው አይነት ተሐድሶ እንዳልሆነ ያምናል፡፡ ሰናይ በኦርቶዶክስም ሆነ በፕሮቴስታንቱ ምእመን ዘንድ አይታወቅም፡፡ ለኤልሻዳይ ቴሌቪዥን ጣብያ የቦርድ አባልና የነገረ መለኮት አማካሪ ሆኖ ቢሰራም አንዳንዴ የኤፌሶን ቴሌቪዥንንም ያማክራል፡፡ የሙሉ ጊዜ ስራው ግን በዱክ ዩንቨርስቲ የነገረ መለኮት መምህር ነው፡፡ ዶክተር ሰናይ ትንሽ መወዛገብ ይታይበታል፡፡ መንፈሳዊ ሕይወቱም እንደ ዱሮው ጥብቅ አይደለም፡፡ ቢሆንም ውስጡ መምረጥ ያለበትን



Scanned with CamScanner

በትክክል እየነገረው ነው፡፡ ያንን የውስጡን ጥሪ ልቀበል አልቀበል እያለ እያታገለ ነው፡፡

ጥቁር ሱፍ በሰማያዊ ሸሚዝና ጥቁርና ነጭ ሸንተረር ያለው ከረቫት ያደረገው ሰናይ ከእረፍት መልስ መናገር ጀመረ "ከእረፍት በፊት ዶክተር ጌታቸው ያነሱት ሀሳብ ላይ ተቃውሞ አለኝ፡፡ ነገሮችን ማየት የፈለግነው ከእኛ አንጻር እንጂ ከኦርቶዶክስ አንጻር አልመሰለኝም፡፡ ፓስተር ናፍያድ ለምሳሌ ያየበት መንገድ በኦርቶዶክሶች ጫማ ውስጥ ቆሞ ነው፡፡ ስለዚህ ችግሮቹ በደንብ ታይተውታል፡፡

"የተሐድሶው አላማ ምንድነው ብለን ከጠየቅን ኦርቶዶክስ ክርስቶስን ስለማታምን ለማሳመን የሚደረግ ጥረት እንደማትሉኝ ተስፋ አለኝ፡፡ ይልቁንስ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የክርስትና አስኳል የሆነውን ክርስቶስን እየሰበኩ አይደለም ነው መልሱ፡፡

"በዚህም ራሱ እርግጠኛ አይደለንም፡፡ ብዙዎቻችሁ አማርኛ ተናጋሪ ስለሆናችሁ እንጂ ቅዳሴም ሆነ ማኅሌት፤ ኪዳንም ሆነ ሰዓታት ክርስቶስ ነው የሚመሰገነው፡፡ በእርግጥ ሕዝብ በሚሰማው ቋንቋ በአማርኛ ሳይሆን በግዕዝ ሆነና ብዙዎች ሳይሰሙት ቀሩ፡፡ እስማማለሁ አብዛኛው የተዋሕዶ አማኝ ከእውቀት ማነስ የተነሳ የዓለም ቤዛ በሆነው ኢየሱስ ሳይሆን መላእክት እና ማርያም ላይ በጣም የተደገፈ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይሄ የቤተ ክርስቲያኗ አቋም አይደለም፡፡"

ሰናይ አዲስ አበባ በዐታ ማርያም ሳለ የተማረውንና የሰማውን መካድ ውስጡ አልፈቅድ አለው፡፡ በዐይነ ሕሊናው ባለጥቁር ጥለቱን የእናቱን ነጠላ ለብሶ፤ ዳዊቱን ማንገቻ ባለው ማሕደሩ ውስጥ ከትቶ፤ ሰያፍ አንገቱ ላይ አንጠልጥሎ፤ በሌሊት ገስግሶ በዐታ ማርያም አባቱን አለቃ ምሕረቱን ተከትሎ ሲሄድ ታየው፡፡ መምሕሩን የኔታ መንበሩን ጭራቸውን ይዘው በርጩማቸው ላይ ቁጭ ብለው ፊደል ሲያስቆጥሩ ትዝ አለው፡፡

"በተለይ በአሁኑ ሰዓት ደግሞ እርግጠኛ የሆንን አይመስለኝም፡፡ ጥናት ይፈልጋል፡፡ በኦርቶዶክስ አዲስና ትኩስ ቤተ ክርስቲያን የወጣቶች ማዕበል ተነስቷል፡፡ የክርስቶስን ጉዳይ በምልአት እየሰራበት እንደሆነ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡ ስለዚህም ተሐድሶው አላማውን ልንከልሰው ይገባል፡፡ ካልሆነ እያደረግን ያለነው ነገር የሃይማኖት ቅሰጣ ወይም 'ሲንክሬቲዝም' ነው፡፡

"እውነት አላማችን ኦርቶዶክሶችን ወንጌል እንዲያውቁ፤ ወንጌል በስፋት እንዲገለጥ ከፈለግን 'ኢኩሜኒዝምን' ልንተገብር ይገባል፡፡ ኢኩሜኒዝም እንደምታውቁት አንድ ቤተ ክርስቲያን ምእመናኖቹን በሥነ ሥርአት ወንጌልን እንዲሰብክ፤ በአስተምህሮ እንዲዳረስ እኛ ክርስቲያኖች የምንረዳዳበት መንገድ ነው፡፡ ማንም ክርስቲያን ድርጅት ከሌላ ክርስቲያን ድርጅት አማኞችን ሲነጥቅ ወይም አዳዲስ አስተምሮዎችን ሲቀስጥ

አይገባም፡፡ ምእመን ከነጠቅን አልያም አዳዲስ አስተምህሮ እያንሸራተትን ካስገባን ጉዳዩ መንፈሳዊ አይሆንም፡፡"

ፓስተር ናፍያድ አጋዥ በማግኘቱ በደስታ ልቡ ቅቤ ጠጣ፡፡ ፓስተር ናፍያድ በፈገግታ በድጋሚ ለመናገር እድሉን ፈለገ፡፡

በፓስተር ናፍያድና በሰናይ አመለካከት ላይ ቶኒ ግራ ገባው "እነዚህ ሰዎች የምራቸውን ነው እንዴ?" አለ፡፡ "ዋና አላማችን ኦርቶዶክስ ታድሳ ክርስቶስን እንድትሰብክ እኮ አይደለም፡፡ ምስኪን" አለ በምጸት እየሳቀ፡፡ ለራሱ፡፡

ከመጀመሪያውኑ እንዲህ አይነት አመለካከት ያላቸው ሰዎች መጋበዝ እንዳልነበረባቸው የገባው ዘግይቶ ነው፡፡ ቢሆንም በቅርበት ሀሳባቸውን መስማቱ ደስታ ሰጠው፡፡ እንደውም እዚሁ ቁጭ ብሎ ሌላ ውጥን አሰበና አንገቱን ወዘወዘ፡፡ ተሰብሳቢዎቹ እያሳቁት ነው፡፡

"ዓላማው መንፈሳዊ ተግባር ይመስላቸዋል እንዴ?" አለ በልቡ፡፡

ፓስተር ናፍያድ ዳግም ንግግሩን ቀጠለ "ወንድሞች የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ተሐድሶ እንዲህ እንደምናስበው ቀላል አይመስለኝም" በውስጧ 'ቅድም ብሎት የለ' አለች ኤማንዳ በንዴት፡፡

"ተሐድሶው እኛ በምንፈልገው መንገድ ሔደ ብንል እንኳ ሁሉም ሙሉ ለሙሉ ይታደሳል ማለት አይደለም፡፡ ወይ ግማሹ ይታደስል ወይም ጥቂት ቦታዎች የታደሱ ኦርቶዶክሶች ይሆናሉ፡፡ ይህኔ የማያባራ፣ ትልቅና ግልፅ ጦርነት በላያችን ላይ እንደማወጅ ነው፡፡

"ልጆቻችን በወንጌል የተዋጀች አገር እናወርሳለን ብለን በተቃራኒው እርስ በእርሳቸው የጎሪጥ የሚተያዩ፣ ለመገዳደል የሚፈላለጉ፣ መንፈሳዊ ቅናት ያስቀጣቸው ወንድማማቾች፣ የመጠቃትና የመደፈር ስሜት የሚሰማቸው አባቶች እናፈራለን፡፡ ድርጊታችንን ሳናጠና በግብታዊነት ከወሰንን እዚህ እኛ ጋር ብቻ ሳይሆን እነሱም ጋር እሳት ሊለኮስብን ይችላል፡፡ ተሐድሶ ለእኛስ አያስፈልገንም ትላላችሁ?

"እኛ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ዱሮው ጾም እናውጃለን እንዴ? ወንጌልን ትተን ስለ ብልጽግና አይደል የምንሰብከው፣ የውሸት ራዕይ፣ የውሸት ትንቢት በእኛ አልበዛም? የማንቆጣቸው የማንገስጻቸው ወጣቶቻችን ዝማሪያቸው እውነተኛና መንፈሳዊ ነው ወይስ ካንትሪ፣ ሂፕ ሆፕ፣ ራፕና ሬጌ ቅጂ ነው? ይህን ችግራችንን እንዴት አላየነውም? የራሷ አሮባት የሰው ታማስልላች እንዳይሆንብን?"



CamScanner

## ምዕራፍ ፲፫

## ኢትዮጵያ-አዲስ አበባ

ጨረቃ ቦታዋን ከፀሐይ ልትረከብ ወጥታለች። ፀሐይ መምሸቱ ያስቆጣት ይመስላል ደም መስላ ማዘቅዘቅ ጀምራለች። ሰማዩ ጠያይሟል፤ አንዳንድ ቦታ ጠቆርቆር፤ አንዳንድ ቦታ ደግሞ በነጭ ጉም የተሸፈነ ሰማይ ይታያል። ሮዳስና አበጋዝ ይህን የተፈጥሮ ዑደት የሚያደንቁ አይመስሉም። እንደውም በከባድ ወሬ ተጠምደዋል።

"ስለዚህ በአሁኑ ሰዓት ተሐድሶ የሚባለው ቡድን..." አበጋዝ ንግግሩን በስሜት ውስጥ ሆኖ እየተናገረ ነው "ደቂቀ እስጢፋኖስ የሚባለው ሕዋስ ኃይለኛ ሥራ እየሰራ ነው። ይህን ችግር በቀላሉ ልንመክተውና እንደ ዱሮው ቀድሰንና ማኅሌት ቆመን፤ እግዚኦ እግዚኦ ብቻ ብለን ልናልፈው አንችልም። ከዚያ ይልቅ የተደራጀ ቡድንና በቂ የሰው ኃይል ይህንን ጥቃት ሊመክት ይገባል።"

"ለዚህ አላማ እንዲሆን ብለው ነው በእስራኤል አገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ፋኑኤል በእስራኤል ያሉትን የትውፊት ትምህርቶች አጥንተው አገራዊ ቀመር ቀምረው የሃላክሃን መንፈስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ለማምጣት የፈለጉት። ለእምነትህ፣ ለማንነትህ፣ ለትውፊትህ፣ ለአገርህ ዘብ መቆምን፤ ቆመንም ጽኑ የሚያደርግ ትምህርት ማምጣት የተፈለገው።"

ሮዳስ የደነገጠ ይመስላል። አበጋዝ ሳያስበው የሆነ ምስጢራዊ ነገር የነገረው ስለመሰለው "ቆይ ቆይ አበጋዝ እየነገርከኝ ያለኸው ምስጢር እንዳይሆን? እርግጠኛ ነህ ለእኔ ልትነግረኝ ይገባል?" አለ።

"አዎ እርግጠኛ ነኝ ላንተ ነው እየነገርኩህ ያለው። አንተ በድረገጽህ ቀንና ሌሊት ስለ ተሐድሶ ያሉህን መረጃዎች የምታወጣው፤ በቁጣና በንዴት የምትይዘው የምትጨብጠውን የምታጣው ቤተ ክርስቲያኗ በተሐድሶዎች እንዳትበረዝ ፈልገህ መስሉኝ?

"በገዛ አገርህና በገዛ ሃይማኖትህ እናውቅልሀለን ሲባል፤ 'እኛ ካላደስናችሁ በስተቀር ክርስቲያን አይደላችሁም' ስትባል ህመሙ ተሰምቶህ መስሎኝ ሌት ተቀን መረጃህን በፌስቡክና በየድረገጹ የምታወጣው። በቃ ይህን ነገር ከፍ እናድርገውና በአገርም በቤተ ክርስቲያን የመጣውን መከራ ፊት ለፊት እንጋፈጠው ነው የምልህ።"

ሮዳስ በዝምታ ቢያዳምጥም ውስጡን አመመው። "እውነትህን ነው እናውቅልሀለን መባል ከምንም በላይ ያማል" አለ ሞቅ ባለ ድምጸት። ሮዳስ ስሜታዊ የሆነ መሰለውና እራሱን ታዘበው፤ ቢሆንም ንግግሩን አላቋመም "በተለይ በእምነት እና

በፖለቲካ ከባለቤቱ ውጪ የማይመለከታቸው ሰዎች እናውቅልሀለን የሚሉ ከሆነ በትክክል አገር ታማለች።"

"እውነት ብለሀል ሮዳስ። ለዚያም ነው አቡነ ፋኑኤል ይህን ሕቡዕ ድርጅት ያቋቋሙት። ድርጅቱን ሲያቋቁሙት ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የእስራኤል ዜግነት ያላቸውንና በኢትዮጵያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ምሁራንን፣ ባለሃብቶችና ተጽእኖ ፈጣሪ ሰዎችን አንድ ላይ በማሰባሰብ ሚድራሺ የተባለ ትልቅ ሆስፒታል በማቋቋም ነው። እኔ የምሰራበት ሆስፒታል ማለት ነው።

"በነገራችን ላይ ሆስፒታላችሁ በጣም ዘመናዊ የሆኑ መሳሪያዎች፣ እውቅናና እውቀት የተካኑ ሐኪሞችን የያዘ እንደሆነ እሰማለሁ። በተለይ ለኩላሊት፣ ለልብና ለአእምሮ ቀዶ ጥገና ሰዎች ከአገር ወጥተው ሔደው መታከምን ቀንሳችኋል እየተባለ ነው።

"ልክ ነህ ሮዳስ ግን ዋናው ነገር በዚህ ሆስፒታል ውስጥ ቅድም ያልኩህ ፊስአልጎስ የተባለው ሕቡዕ መንፈሳዊ ድርጅት አለ። ሆስፒታሉም በበላይነት የሚተዳደረው በዚህ ሕቡዕ ድርጅት ነው።"

-----//------

## ለንደን-ሻፍተ በሪ ጎዳና

ቶኒ በአንድ ጆሮው የጆሮ ማዳመጫ ሰክቶ ስልክ እያወራ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን በአርክቴክት 'ጆርጅ ቪሊያሚና' በኢንጅነሩ 'ሰር ጆሴፍ ባዛልጌት' በተገነባችው የምሥራቅ ለንደን መንገድ ላይ እያሽከረከረ ነው። ሻፍት በሪ ጎዳና 'ሀሪ ፖተሪ' እና 'ዴዝሊ ሀሎውስ' እንድ የተባሉት ፊልሞች የተቀረጹበት ሲሆን 'በዋይልድ ዌስት ኢንድ' በሚለው 'በድሬ ስትሬይት' ዘፈን ሻፍት በሪ ጎዳና ስሙ በተደጋጋሚ ተጠርቷል።

ወትሮ ቢሆን ለቶኒ በሻፍት በሪ ጎዳና ማሽከርከር ደስታ ይሰጠው ነበር። አሁን ግን በጣም አስፈላጊ የስልክ ልውውጥ ውስጥ ሆኖ እየነዳ ስለሆነ ብዙም ለመንገዱ ትኩረት አልሰጠም።

"አሁን እኔ የምፈልገው የፓስተር ናፍያድን ሪኽም ስብከት እፈልጋለሁ። በተለይ ስብከቱ ሰዎች ስሜታዊ የሆኑበትን ከመድረክ ላይ የተቀረጸው ይዘጋጅ"

በወዲያኛው ስልክ ጫፍ "እስከ ነገ ልትታገሰኝ ትችላለህ?" አለ ረጋ ያለ የሴት ድምጽ።



CamScanner

ቶኒ ተቆጣ "አሁን! አሁን! ነው የምፈልገው በፍጥነት ኢሜይል አድርጊልኝ"

"እሺ ቶኒ ትንሽ ጠብቀኝ?" አለች ከወዲያኛው የስልክ ጫፍ ያለችው እንስት።

"እሺ አመሰግናለሁ" ብሎ ስልኩን በፍጥነት ዘጋውና ስለ ፓስተር ናፍያድ ማሰላሰል ጀመረ። ሰውየው በጣም አናድዶታል።

ቶኒ እንደተለመደው ሁሉ "በአንድ ድንጋይ ሁለትና ከዚያ በላይ ወፍ" የሚለውን የተልእኮውን መርህ ሊያዘጋጅ ነው። በእርግጥ ከሰናይ ይልቅ ፓስተር ናፍያድ የሚያመጣው አደጋ ከባድ ነው ምክንያቱም ፓስተር ናፍያድ የሚኖረው ኢትዮጵያ ነው፤ ብዙ ተከታይና ምእመናን የሚሰብክ ሰው ነው። በዚያ ላይ ከተሐድሶው አላማ ጀርባ ያለው ነገር ገብቶታልም አስግቶታልም። ሰናይ ግን ብዙም አደጋ አያመጣበትም። የሚኖረው አሜሪካ ነው በተጨማሪም በኦርቶዶክሱም በፕሮቴስታንቱም ዘንድ አይታወቅም።

## ምዕራፍ ፲፬

ጨለማው ሙሉ ለሙሉ በሰማዩ ላይ ነግሷል። እንደ ቅድሙ እግር ለማፍታታት የሚንሸራሽሩ ሰዎች እምብዛም አይታዩም። በእግራቸው እየተንሸራሸሩ ቤተ መንግሥትን እያለፉ ነው። ቀያይ ኮፊያ ያደረጉ መከላከያ አባላት የሆኑት የቤተ መንግሥቱ ጠባቂዎች ከቤተ መንግሥቱ አጥር ላይ ባለ ከፍ ያለ ቦታ ላይ ቆመው አላፊ አግዳሚውን፣ ወጪ ወራጁን አንዳንዱን በግልምጫ፣ አንዳንዱንም በመኮሳተር እየተመለከቱ ነው።

"ፊስአልጎስ ህቡዕ ድርጅት ከዚህ ቀደም እንደነገርኩህ ኢየሱስን ከአእዋፋትና ከዱር አራዊት ጋር እያገናኘ መልካም በሆነ መልክ ከሚገልጸው መጻሕፍ ነው ስሙን የወሰደው።"

"በነገራችን ላይ ስለ ነገርከኝ ወፍ ከዚህ ቀደም ምንም አላውቅም። መጽሐፉንም አግኝቼ ባነበው ደስ ይለኛል።"

"ጥሩ ከወደድከው አንድ ምሳሌ ልጨምርልህ። ፊንክስ የተባለው እስከ አምስት መቶ ዓመት እድሜ ያለው ወፍ ሲያረጅና ወደ መሞቻው ዘመን ሲቃረብ ወደ ደጋ ዛፍ ይሄድና ቅርንጫፎቻቸውን ሰብሮ በክንፎቹ ሸንጉጦ በሰማይ ላይ ይበራል። ከዚያም እንጨቶቹ ይነዱና ፊኒክሱም ተቃጥሎ ወደ ምድር ይወርዳል። ፊንክሱ ከተቃጠለበት መሬት አመዱ ውስጥ ትል ይገኛል። ትሉ በሦስተኛው ቀን ጫጩት ወፍ ይሆናል። በአራተኛው ቀን ሙሉ ፊኒክስ ወፍ ይሆንና መብረር ይጀምራል። ኢየሱስ 'ነፍሴን ከሥጋዩ አዋሕጄ ላነሳት ሥልጣን አለኝ፣ መልሼ እወስዳት ዘንድ እንደገናም አንስቼ ላኖራት ሥልጣን አለኝ' ላለው ቃል ምሳሌ ነው።

"ይህ ሃምሳ ሰባት ክፍሎች ያሉት ኢየሱስ ክርስቶን አርቆና አመስጥሮ የሚገልጽ ፊስአልጎስ መጽሐፍ ከአገራችን ከወጣ አመታት ተቆጥሯል። አይደለም ወንጌል ሌላ እንዲህ አይነት መጽሐፍ ባንጽፈው እንኳ ተርጉመን የምንጠቀም እኛ ነን። እንግዲህ ኢየሱስን በሚገባው ልክ አላወደሳችሁም፣ አላከበራችሁም፣ አላመለካችሁም... ተብለን እንድንታደስ የተፈለገው። ለዚህም ነው ፊስአልጎስ ብለን ማኅበራችንን የሰየምነው።

"ሌላኛው ግን ዩቶጵያ የተባለው አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤታችን ነው።" ዮቶጵያ ቶማስ ሞር የጻፈው የመጻሕፍ ስም ነው። ፊስአሎጎስም እንዲሁ የመጻሕፍ ስም ነው። የሁለቱም ሕቡዕ ድርጅቶች ስም የመጽሐፍ ርዕስ ነው። ሮዳስ ግጥምጥሞሹ ገርሞታል።

ሮዳስ ዩቶጵያ በከተማው ጥሩ የሚባል ትምህርት ቤት እንደሆነ ሲወራለት ሰምቷል። ነገር ግን ትምህርት ቤቱ ከእንደዚህ አይነት ነገር የተገናኘ አይመስለውም ነበር።



CamScanner

ሮዳስ የመጨረሻዋ የአበጋዝ ንግግር አዕምሮው ውስጥ እንደሚነጥር ኳስ ጠብ ጠብ ጠብ እያለች ቦታ ስትይዝ ታየችው 'ኢትዮጵያዊያንን ኢትዮጵያ ውስጥ መውሰድ ሳይሆን፤ ኢትዮጵያን ኢትዮጵያውያን ውስጥ መውሰድ ይኖርብናል።'

ሮዳስ የዚህ ቡድን አባል መሆን በጣም ነው የፈለገው "የፊስአልጎስ አባል ለመሆን የሚያስፈልገው ምንድነው?" ሲል በጉጉት አበጋዝን ጠየቀው

"ፊስአልጎስ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶን ከጥፋት ለማዳን የተቋቋመ ስለሆነ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶና አስተምህሮዋን መቀበል ይጠይቃል። ነገር ግን ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ክፍት የሆነው ዩቶጵያ የተባለው ሕቡዕ ድርጅት ለሁሉም ኢትዮጵያዊና የኢትዮጵያን ታላቅነት ለሚመኝ ሁሉ ክፍት ነው።

"አባል ለመሆን የሚያስፈልገው ጥልቅ የአገር ፍቅርና ኢትዮጵያዊ መሆን ነው እንጂ ምሁር ወይም በኑሮ ከፍ ያለ ደረጃ መሆንን አይጠይቅም። በእርግጥ በዓሁኑ ሰአት እንደ አጋጣሚ ሆኖ በኢትዮጵያና በተቀሩት የዓለም ክፍል ውስጥ በትላልቅ ቦታዎች ላይ በሥራና በትምህርት ላይ የሚገኙ ሰዎች በአባልነት ይበዛሉ። ነገር ግን አላማው በጠላት እንዳይጨናገፍ ሲባል ሰዎች ሲመለመሉ ጥንቃቄ ይደረጋል። ቅድም እንዳልኩህ ዩቶጵያ በስራ ገሀድ የወጣ በአላማ ግን ሕቡዕ ነው።

# ምዕራፍ ፲፫

## አዲስ አበባ-ሳሪስ

አየሩ እንኳን ከቤት ውጪ ላለ ሰው ቤት ውስጥም ላለ ሰው ተጨማሪ የሚሞቅ ነገር ካልደረቡበት በስተቀር ብርዱ ሰውነት ውስጥ ገብቶ እንስፍስፍ ያደርጋል፡፡ አየሩ ወይ አይዘንብ ወይ ፀሐይ አይሆን እንዲሁ ሰማዩ ላይ ዳምኗል፡፡

ሙሉ ለሙሉ ነጭ የተቀባው ግርግዳ ንጽህናው አንዳች ደስታ ይሰጣል፡፡ የቤቱ ወለሉ የቱርክ ምርት የሆነው ምንጣፍ የተነጠፈበት ሲሆን፤ ከግዙፉ ሶፋ ስር ያለችው ድንኪ ጠረጴዛ የሆነ መስህብ አላት፡፡ በሸክላ የተሰራው ውቡና ትልቁ የአበባ ማስቀመጫ ከነአበባው ከሳሎኑ በር በስተቀኝ ጥግ ላይ ይታያል፡፡

ሰንፔር ኅመኔ ቀለም ያለው ምቹው ሶፋ ላይ ጋደም ብላለች፡፡ ነጭ ፒጃማዋን ለብሳ ከላይዋ ላይ ስሱን ብርድ ልብስ አድርጋ 'ኤም ቢሲ ፎር ቻናል' ላይ 'ዘ ዶክተር' የተሰኘውን የቴሌቪዥን ቻናል በባለ አርባ ስምንቱ ኢንች ቴሌቪዥን እያየች ነው፡፡

የሰንፔር ወንድም ማዕረግ ከውጪ ወደ ውስጥ ገባ፡፡ ፊቱ ላይ ቁጣ የሚነበብት ማዕረግ ወፍራም ሲሆን ቁመቱ አጭር ነው፡፡ ቀይ ፊቱ ይብስ በንዴት ቀልቷል፡፡ ጎረድ ያለ አፍንጫውንና ክርዳዳ ጸጉሩን በተደጋጋሚ ያክከዋል፡፡

"አንቺ ለምንድነው ለአባዬ እንደዛ ብለሽ የተናገርሽው?" አለ መቀመጫው እንኳ ወንበር ሳይነካ

ሰንፔር የቴሌቪዥን ሪሞቱን እየነካካች ኮስተር ብላ "ምኑን?" አለች፡፡

"ምን ምኑን ትያለሽ? ታውቂዋለሽ ለአባዬ የነገርሽውን" አለ ማዕረግ እህቱን በንቀት ነው እያየ፡፡ የሰንፔር ፍቅረኛ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ በመሆኑ እንዲሁም እህቱ በጣም ቆንጆ ነች ብሎ ስለሚያስብ እንዴት ተደርጎ ነው ስለ ውበቷ ሲባል ሮዳስ እምነቱን የማይቀይረው ብሎ ይናደዳል፡፡ ለዚህ ሁሉ ችግር የእህቱ ልፍስፍስነት ነው ብሎ ያምናል፡፡

"ታዲያ እንደ ታላቅህ ልታከብረኝ አልቻልክም፡፡ በዚያ ላይ እኔ አውቅልሻለሁ ብለህ ብዙ ነገር ታወራለህ፡፡ እሱን ብትፈራው ብዬ ነገርኩት" አለች ሰንፔር አሁንም ሪሞቱን እየነካካች፡፡

"ሲመጣ አይደርስም ነበር እንዴ? ለንደን ድረስ የምትደውይው፡፡ ደግሞ አውቅልሻለሁ ማለት ይነሰኝ? የፓስተር ልጅ ሆነሽ ከማንም አህዛብ ጋር ትዳር ልትፈጽሚ ስትዪ ዝም እላለሁ እንዴ?"



CamScanner

ሰንፔር ተቆጣች "አንተ ችግር አለብህ፡፡ ጭንቀትህ ስለ ክብር ምናምን ነው፡፡ በመጀመሪያ ለአባቴ ክብርም ሆነ ማንነት የምታስበው አንተ ብቻ ሳትሆን እኔ ልጁም ጭምር ነኝ፡፡ ሲቀጥል ባሰኘ ነህ ቃልህን አስተካክል አህዛብ ማለት በእግዚአብሔር የማያምን ማለት ነው፡፡ እንዲህ በለመደ አፍህ ሌላ ቦታ ብትናገር ትዋረዳለህ፡፡ ይሄ ንግግርህ ያለመሰልጠንህ ያለማወቅህም ምልክት ነው፡፡"

ማዕረግ በቁሙ ሶፋው ላይ ዘፍ ብሎ ተቀመጠና ንግግሩን ቀጠለ "ተቆረቆርሽ ማለት ነው? አህዛብ በማለቴ ቅር ይልሻል እንዴ? እደግመዋለሁ ፍቅረኛሽ ጌታን የማያውቅ አይሁድ ሳይሆን አህዛብ ነው፡፡ አንቺም አህዛብ መሆን አማረሽ እንዴ?"

"አዎ አምሮኛል ንግግርህ በጣም ብስለትና ግብረ ገብ የጎደለው ነው፡፡ አንተ አሁን እንዴት አድርገህ ነው ስለ ወንጌል፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ስለ ቤተሰብ ተቆርቋሪ የምትሆነው? ለሰው የሌለ ስም እየሰጠህ አይደብርህም ትንሽ?"

ማዕረግ እንደማሾፍ እያለ "ለምን አፍራለሁ ውድ እህቴ? እውነት እኮ ነው የማወራው፡፡ አንድ ወቅት አንቺም የምታምኝበት ሃቅ ነበር፡፡ ዛሬ ምን ሀሳብ የሚያስቀይር ነገር ተገኘ? አንቺ እኛን መናፍቅ ሲሉን ትከራከሪልናለሽ?"

"አዎ እኔ ፊት እንዲህ የሚለኝ ካለ እከራከራለሁ፡፡ የድንቁርና ጨለማን መልሰህ በመሳደብ ወይም ለጸብ በመጋበዝ ልታበራው አትችልም፡፡ ይልቁንስ እውነታውን በማስረዳትና በመግባባት እፈታዋለሁ እንጂ በእነሱ የጠላሁትን ስም መለጠፍ መልሼ እኔም ስም በመለጠፍ ልዩነትና ችግርን አላባብስም፡፡

ሰንፔርና ማዕረግ እየተጨቃጨቁ የሰንፔር ስልክ ጮኸ፡፡ ሰንፔር ወንድሟን ማናገር ተወት አደረገችና ሙሉ ለሙሉ በእንጨት ከተሰራውና ከሶፋው መሀል ካለው ድንክ ጠረጴዛ ላይ ያለውን ስልኳን አንስታ ተመለከተችው፡፡ ቁጥሩን አታውቀውም፡፡ እንደውም የአገር ውስጥ ስልክ ቁጥር አይደለም፡፡

ቤት ውስጥ ለማናገር ኔትወርኩ ስለማይሰራ ሰንፔር ስልኳን ያዘችና ከተኛችበት ሶፋ ተነስታ ነጭ ካልሲ በለበሰው እግሯ ውስጥ ነጠላ ጫማዋን አደረገች፡፡ ማዕረግ ስልኩን የደወለው ሮዳስ ስለመሰለው ፊቱን አጠይሞ ዝም ብሎ በትዝብት ዐይኑን አፍጥጦ ያያታል፡፡

ሰንፔር ከቤት ወጣችና ስልኩን አንስታ "ሄሎ?" አለች

ከወዲያኛው ጫፍ ረጋ ያለና ሰንፔር ሁሌም ስትሰማው ደስታ የሚሰጣት ሰው ድምጽ ነው፡፡ የአባቷ፡፡ "ሄሎ ሰንፔር እንዴት ነሽ?"

"ሄሎ አባቢ እንዴት ነህ ሰላም ነው?"



CamScanner

“እዎ ሰንፔር ሰላም ነው እናንተ እንዴት ናችሁ?”

“እኛ ደህና ነን አባቢ እንዴት ነው ስብሰባህ አለቀ?”

“እዎ አልቋል...” አለ ፓስተር ናፍያድ በረዥሙ ተነፈሰ። ሲተነፍስ ስልኩ አስተጋባና ለሰንፔር ጆሮ የሚሰቀጥጥ ድምጽ ሰጣት።

“ምነው አባቢ ደክሞሀል እንዴ? በረዥሙ ተነፈስክ”

“አይ ምንም ፀሐዩ ትንሽ ሳያደካክመኝ አልቀረም፤ ኤኒ ዌይስ እሮብ አዲስ አበባ እገባለሁ”

“እረ አባቢ ፈጠንክ። ትንሽ እቆያለሁ ብለህ አልነበረም?” ሰንፔር የአባቷ በፍጥነት ለመምጣት መወሰን ገርሟታል።

“አይ በቃ ለመምጣት ወስኛለሁ”

“እሺ አባቢ ደስ እንዳለህ ልትመጣ ስለሆነ ደስ ብሎኛል።”

# ምዕራፍ ፲፯

ሮዳስ ከነጭራሹ አልተኛም፡፡ ያልጠበቀውን ቪዲዮ በዩትዩብ ደጋግሞ ሲያይ ነበር፡፡ ይበልጥ ያስደነገጠው ምስሉና ድምጹ የሰንቬር አባት መሆኑ ነው፡፡ በአይሆንም ስሜት ቪዲዮውን በተደጋጋሚ ተመልክቶታል ግን ሆኗል፡፡ ፓስተር ናፍያድን ያውቀዋል እንዲህ ያለ አቋም ይኖረዋል ብሎ አልጠበቀም፡፡ እንዲሁ ሲንጋለበጥ ከሌሊቱ አስራ አንድ ሰዓት ላይ ከፊስአሉጎስ ሕቡዕ ድርጅት ጠዋት ስብሰባ እንዳለ የሚነግር መልዕክት በስልኩ ደረሰው፡፡ ከዚያም ሲገላበጥ ትንሽ ቆየና ወደ ፊሰአልጎስ ቢሮ መንዳት ጀመረ፡፡

ሰዓቱ ለአዲስ አበባ ከድቅድቁ ጨለማ ወደ መንጋት ቢሆንም ጨለማውን የተቀበለው ፀሐይ ሳይሆን ያኮረፈ ሰማይ፤ ጉም ያጠላበት አየር ነው፡፡ ስለዚህም አዲስ አበባና ነዋሪዎቿ እንደ ወትሮዋቸው ገና በማለዳ ነቃ ነቃ አላሉም፡፡ ምክንያቱም የሰማዩ መጎሽ፤ የአየሩ መቀዝቀዝ ከቤትም ሆነ ከመኝታ አትውጡ አትውጡ ይላል፡፡

የፊስአልጎስ ሕቡዕ ድርጅት የመሰብሰቢያ አዳራሽ የአዲስ አበባን ብርድ፣ ጉምና ቁር ተቋቁመው በመጡ ሰዎች ተጣብቧል፡፡ ሰማያዊው ባለመደገፊያው የስፖንጅ ወንበር ላይ ከተቀመጡት ሰዎች በላይ በወንበር እጦት ምክንያት የቆሙ ሰዎች አሉ፡፡ ብዙዎች ወፍራም ሹራብ ወይም ጃኬት ደርበዋል፡፡

ፊስአልጎስ የሕቡዕ ድርጅት አባላት በፍጹም ቁጣ ውስጥ ናቸው፡፡ ተሐድሶውንና ስትራቴጂውን እንዲህ በገሀድ ለዚያውም በጣም ታዋቂ በሆነ የፕሮቴስታንት መምህር ይነገራል ብለው አልጠበቁም፡፡ ከዚያም በላይ 'በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በእያንዳንዱ ሰንበት ትምህርት ቤት ሰው አለን' ያለው ነገር አስደንግጧቸዋል፡፡ በዚህ ማለዳ ሁሉም ሲሰበሰቡ ብርዱ አልበገራቸውም፤ የቦታ ርቀትም አላስጨነቃቸውም፡፡ ከዚያ ይልቅ ቀጥሎ ስለሚያደርጉት ነገር ለመነጋገር ጓጉተዋል፡፡

ከፊስአልጎስ አባላት ውስጥ ቪዲዮውን ያልተመለከቱ ብዙ አሉ፡፡ በወሬ ግን ከሌሎች ስለሰሙ ካዩት ሰዎች እኩል ተናደዋል፡፡ ስለዚህም በድጋሚ አንድ አይነት አቋምና ስሜት ለመያዝ ቪዲዮውን በድጋሚ ለመክፈት አስፈላጊ መሆኑን የኮሚቴው መሪዎች ወስነዋል፡፡

የአዳራሹ መብራት ሲጠፋ የብዙ ሰዎች የጩኸት ድምፅ ተሰማ፡፡ ከዚያም በግርግዳው ላይ ካለው ፕሮጀክተር ላይ የኤልሲዲው ብርሃን አረፈና ሰማያዊ ቀለምና ከስር ላቲን ፊደላት ታዩና ቶሎ ድርግም ብሎ ጠፋ፡፡ መልሶ ከኤል ሲዲው ጋር በኬብል የተያያዘውን የኮምፒውተሩን የፊት ለፊት ገጽ አሳየ፡፡ በዴስክቶፑ ላይ የኮምፒውተሩ ክርሰር እንደ መፈለግ አለና በቪኤልሲ ሶፍት ዌር የተቀመጠውን 'ሪፎርም' የሚለውን ፋይል ተከፈተ፡፡

"ዛሬ የምንነጋገረው አርዕስት ተሐድሶ ነው። ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ያስፈልጋል። በይበልጥ ደግሞ ሳትታደስ ሳረጀችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጌታ ተናገር ያለኝን እናገራለሁ። እናንተ ኦርቶዶክስን እንደሌላ የምትመስከቱ የቸርች ሰዎች ብታቀሙ ይሻላችኋል።" የፓስተር ናፍያድ ንግግር ፌዝ ስላለበት ሳቅና ጭብጨባ በአዳራሹ ሞላ።

"ኦርቶዶክስ ለእኛ አሮጊቷ ሳራ ማለት ነች። ሳራ ደግሞ እኛን ወለደች። ብዙዎቻችን ወይ ከኦርቶዶክስ እማኝነት፤ ከኦርቶዶክስ ቤተሰብ ነው የተገኘነው ስለዚህ የዚህች ቤተ ክርስቲያን ልጆች ነን። እንደ ልጅነታችን የሌሎች ሰዎች መዳን ግድ ይለናል። ስለዚህም ኦርቶዶክስን ልናድሳት ግድ ነው። እግዚአብሔር በቅዱስ መጽሐፉ በኢሳያስ ምዕራፍ አርባ ቁጥር ሠላሳ አንድ ላይ እንዲህ ሲል ይናገረናል። 'እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ'" በአዳራሹ 'አሜን!' የሚል የደቦ ድምጽ ተሰማ። ፓስተር ናፍያድ ውኃ ለመጠጣት ወደ አትሮንሱ ተጠጋና የታሸገውን የውኃ ኮዳ አነሳና ሁለቴ ተጎነጨለት። ከዚያም ነጩን መሐረቡን አንስቶ ከንፈሩንና ፊቱን አበሰ አደረገ።

"ዛሬ ስለ ተሐድሶ ጥቅም አሳወራም ወንጌል 'በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ' ይላል" ከአዳራሹ 'አሜን! ሐሌ ሉያ!' የሚል ድምጽ ተሰማ። "... ስለዚህም በቃሉ መሠረት ለመታደስ አትስነፉ። ዛሬ የማወራችሁ በተለይ እናት ቤተ ክርስቲያን ኦርቶዶክስ እንዴት ትታደስ? እዚያ 'ተሐድሶ ተሐድሶ' እያሉ የሚጮሁ የወንድሞችን ድምፅ እንዴት እንመለስ በሚለው ነው።

"በነገራችን ላይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥሪ ከዘመኑ ጋር አብሮ የመጣ ከመሰላችሁ ተሳስታችኋል። ኦሮሮሮሮ...ቆየ በጣም ቆየ እኮ" እንደማሾፍ እያለ።

"ማርቲን ሉተር ካቶሊክ ትታደስ ብሎ መጽሐፍ ቅዱሱን ከማንሳቱ ቀደም ብሎ በአጼ ያግብዓ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ኦርቶዶክሳውያን መምህራን 'ለመስቀልና ለሥዕለ ማርያም እንሰግድም' ብለው ነበር። ይህ አስተሳሰብ አደገና በአጼ ዘርአ ያዕቆብ ጊዜ በኃይልና በጌታ ፍቅር ደቂቀ እስጢፋኖሳውያን 'ከአብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ በስተቀር ለማንም አልሰግድም' ብለው ተነሱ። በነገራችን ላይ ይህ ታሪክ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይታወቃል። በአጼ ያግብዓ ፅዮን ዘመነ መንግሥት በትግራይ ውስጥ 'ለሥዕልና ለመስቀል አንሰግድም ምክንያቱም ሥዕል ስሌዳ ነው፤ መስቀልም የጎለጎታ እንጨት ነው' የሚሉ አካላት ነበሩ።

"ይህንን በአንድ ወቅት ከዓለም በፊት ተጠይቆና ተሞክሮ የተቋረጠውን የተሐድሶ ጥያቄ ዛሬ ሶላ ብለን እንጀምረዋለን። ሶላ ታውቃላችሁ?" አለና ፓስተር ናፍያድ ምእመኑን ተመለከተ። ግማሹ ምእመን ሳቀ ግማሹም ዓይኑን ፍጥጥ አደረገ።

ፓስተር ናፍያድ እንደ መሳቅ አለና "ሶላ ማለት የተሐድሶ አርበኛው የማርቲን ሉተር የአሸናፊነት ቃል ነው። የሶላ የአማርኛ አቻ ትርጉም 'ብቻ' ማለት ነው። አምስቱ ብቻዎች ናቸው የተሐድሶ ምሰሶዎች። እደግመዋለሁ አምስቱ ብቻዎች፤ አምስቱ ምሰሶዎች!

"እነሱንም እንደ ጌታ ፈቃድ አንድ በአንድ እየበታተንን እናያቸዋለን። አንደኛ ለድኅነት ስልሳ ስድስት መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ። ላቲኑ እንዲህ ይላል 'sola scriptura' (መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ) በቃ ትርፍ ነገር አያስፈልግም። የምን ተጨማሪ መጽሐፍ ነው? የምን አዋልድ መጽሐፍ ነው? በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማንኛውም ልምምድ፣ አስተምሕሮና ሥርአት በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻና ብቻ ይዳኛል፤ ይገመገማል ይታረማል።

"እስኪ እንዴት እንዴት ተደርጎ ነው 'ቃየል በየዋሕነት የተከተለውን ወንድሙን በሴት ቀንቶ ገደለው' የሚለውን መቃብያን፤ 'ገንዘብ በቃኝ አትበል' የሚለውን የሲራክን መጽሐፍ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አካል የምንቀበለው? እስኪ ገንዘብ በቃኝ አትበል የሚለውን ቃል ከአንደኛ ጢሞቴዎስ ከምዕራፍ ስድስት ከቁጥር አስር ላይ ካለው 'ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ስር ነው' ከሚለው የወንጌል ቃል በምን እናስታርቀው ወዳጆቼ? ኧረ በኢየሱስ ስም በሉ እስኪ እባካችሁ?" አዳራሹ ውስጥ የታደመው ሴት ወንድ ሁሉ 'በኢየሱስ ስም!' አለ አንድ ላይ። የፌስአልጎስ አባላት ቪዲዮውን እየተመለከቱ በቁጣና በደም ፍላት "እህምም…" የሚሉ አሉ።

ፓስተር ናፍያድ በስብከቱ ደስተኛ ይመስላል። አሁንም አሁንም ከልብ በሆነ ፈገግታ ሳቅ ይላል "እኛ የምናውቀው መጽሐፍ ቅዱስ ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ብቸኛ ቤዛና አዳኝ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ በግልጽ እየተናገረ በአገራችን ግን መጽሐፍ ቅዱስ ከልብ ወለድ ተቀይጦብን ቤዛና አዳኝ ማርያም፣ ሚካኤል ወይም ሌሎች እያለ የሚሰብከንን መጽሐፍ እንዴት እንቀበል?

"መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን ጥሩ ጥሩ አስተማሪዎች ያስፈልጉናል። ሐዋርያት የወንጌል አዋቂዎች እንጂ የአይሁድ ቀሳውስት፤ ወይም ድምጽ እያሳመሩ ለሁለትና ለሦስት ሰዓት የሚቀድሱ አይደሉም። ቀሳውስትም ካስፈለገን የሚያስፈልገን በመጻሕፍ ቅዱስ ትምሕርት የላቁ፤ ወንጌል የበራላቸውን ራሳቸውንም ያበሩ መሆን ይገባቸዋል እንጂ በማናውቀው ቋንቋ 'ትትትትትት….' እያለ ብዙ የማይገባ ነገር የሚያወራብን አይመቸንም።" የፌስአልጎስ አባለት ቪዲዮውን ቀድመው የተመለከቱት ጭምር ካላዩት ጋር እንደ አዲስ መናደድ ጀመሩ። ያላዩት ደግሞ በአግራሞትና በቁጣ ስብከቱን እየተመለከቱ ነው። አንዳንዶች ዓይን ላይ የንዴትና የቁጭት እንባ አቅርሯል።



CamScanner

"ሁለተኛው ብቻ ደግሞ መዳን በጸጋ ብቻ በላቲንኛ ወይም በሉተርኛ 'Sola Gratia' እስኪ የሚጠራጠር አለ? መዳን በጸጋ ብቻ ነው፡፡ እስኪ ድኅነት በጸጋ ብቻ መሆኑን የማይጠራጠር አንድ ሰው በጸጋው ድኛለሁ ይበል፡፡" አዳራሹ 'በጸጋ ድኛለሁ!' በሚል ቃል ተጥለቀለቀ፡፡

"በጸጋ መዳኑን የሚጠራጠር ካለ በዚህ ቃል ይፅና ኤፌሶን ምዕራፍ ሁለት ቁጥር ስምንት ላይ እንዲህ ይላል 'ጸጋው በእምነት አድኗችኋል፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ በስራ አይደለምና' ይላል የእኔና የእናንተ መጽሐፍ ቅዱስ፡፡ ደስ አይልም?" ጭብጨባና 'አሜን! ሐሌሉያ!' የሚል ቃል አዳራሹን አናወጠው፡፡

"ጸጋ ቁሳቁስ ሳይሆን በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ሕያው ፍቅር እና ግንኙነት ነው፡፡ ጸጋ ማለት ገና ኃጢያተኞች ሆነን ጥፋት ሲገባን የተገኛቢጦሽ የዘላለም ድኅነትና ብጽእና በነጻ መቀበላችንን ያመለክታል፡፡ ሮሜ ምዕራፍ አምስት ቁጥር ስምንት ላይ 'ገና ኃጢያተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል' ብሏል፡፡ ይህ ታላቅ ፍቅር የተሰራው የእኛ ጾም፣ ጸሎት፣ መልካም ምግባር ብህትውና ምንም ለጽድቃችን በቂ ስላልነበረ ነው 'ገና ኃጢያተኞች ሳለን' ተብሎ የተጻፈው፡፡ መዳን ለማይገባን ለእኛ ክርስቶስ ሞቶ የድኅነት ጸጋን ሰጠን፡፡

"ምንድነው ሕግና ሥርአት ማብዛት? ወንጌል እንዲህ ይላል 'ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ፡፡' በቃ የሆነው ይህ ነው፡፡ ጸጋ ከጠላነው፣ ከወጣንበት፣ ካመጽንበት፣ ከራቅነው አምላክ የተሰጠን የማይገባን መዳን ነው፡፡

"ከእኔ ጋር ናችሁ?" አለ ፓስተር ናፍያድ ውኃውን ድጋሚ እየጠጣ

ምእመኑ በደቦ "አዎ!" ሲል መለሰ

"እንደዛ ከሆነ ወደ ሦስተኛው ብቻ ልንሔድ ነው፡፡ ሦስተኛው ሶላ ደግሞ መዳን በእምነት ብቻ 'Sola Fide' ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለጸጋው የምንሰጠው ምላሽ እምነት ብቻ ነው፡፡ በቃ ሌላ ጣጣ ሌላ ዝባዝንኬ አያስፈልግም ለመዳን እምነት ብቻ በቂ ነው፡፡ ታውቃላችሁ በዓለማችን ያሉት ሌሎች እምነቶች የመጨረሻ ፍርድ እንዳለ አምነው ነገር ግን ከዚህ ፍርድ መቼና እንዴት እንደሚወጡ እርግጠኛ መሆን አይችሉም፡፡

"እኛ ግን እንዲህ ብለን እናምናለን፡፡ አንድ ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል በተገኘው ጸጋ በማመን ብቻ ይድናል፡፡ ሐሌሉያ!" አዳራሹ ውስጥ ያሉት ሰዎች 'አሜን! ሐሌሉያ!' እያሉ አስተጋቡ፡፡ "ድኅነትን በእምነት እንቀበላለን እንጂ ድኅነታችንን



CamScanner

እንሰራውም። በእምነት መዳን ማለት ስለ እኛ ኃጢያትና መተላለፍ በመስቀል ላይ ክርስቶስ ኢየሱስ የከፈለው ዋጋ በቂ እንደሆነ በእምነት መቀበል ነው።" ሮዳስ በተመስጦ እንደ አዲስ ከሚያየው ቪዲዮ ላይ ያነቃችው ስንፔር በስልኩ ላይ ደውላ ነው። አወጣና ስልኩን አየው 'ሰን' ይላል። ስልኩን ሳይመልስ ድምጽ አልባ አደረገውና ወደ ኪሱ መልሶ ወደ ቪዲዮው ተመለሰ።

"ስለዚህ ድነነት በመልካም ምግባር፣ በሌሎች ሰዎችም በሉ፣ በጻድቃን ጸሎት እደግመዋለሁ በሌሎች አማላጆች" ይህን ሲል በአዳራሹ ሳቅ ተሰማ፤ ሳቁ ጋብ ሲል ፓስተር ናፍያድ ንግግሩን ቀጠለ "...እውነቱን ነው ድነነት በመመጽወት፣ በመመነን፣ በገንዘብም፣ ከልዩ ዘር በመወለድና በሃይማኖት ሳይሆን፣ ድነነት የኢየሱስ ክርስቶስን በመስቀሉ የሰራውን ቤዛነት በእምነት ብቻ በመቀበል እንደሆነ እንመሰክራለን።" በአዳራሹ ያሉት አንዳንዶች በስሜት ቆመውና መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ወደ አየሩ ላይ እንደመሰንዘር እያሉ፣ ብዙዎችም ተቀምጠው እጃቸውን ወደ ሰማይ በመዘርጋት 'አሜን' አሉ።

"አራተኛ ብቻ፣ ደግሞ መዳን በኢየሱስ ብቻ በላቲንኛ 'solus christus በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም' ይላል ሮሜ ምዕራፍ ስምንት ቁጥር አንድ ላይ። ከኃጢያታችን በደሙ ስለዋጀን እርሱ ብቸኛ አዳኝ ነው፣ በደሙም ስለዋጀን በስጋችን እርሱን ማክበር እንዳለብን ቃሉ ይነግረናል።

"መጽሐፍት ሁሉ ስለ ክርስቶስ ክብርና አምላክነት ሊያውጁ ይገባል። ሐዋርያው ጳውሎስም 'ከክርስቶስ በቀር ሌላ እውቀት የለኝም' ብሏል። ክርስቶስን የማይገልጥ ጴጥሮስም ሆነ ጳውሎስ ቢሰብኩት እንኳ ሐዋርያዊ አይደለም። የትኛውም ቤተ ክርስቲያን ድነነት በኢየሱስ ብቻ መሆኑንና ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ሊሰበክ ግድ ነው። ከዚህ ውጪ ያለው ትምህርት እንዳለ ኑፋቄ ነው።"

በፊስአልጎስ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ "እረ እረ ...ድፍረት!" የሚል አንድ ድምጽ ተሰማ ከወደ ጥግ አካባቢ።

"እሺ ወደ አምስኛው ብቻ ከመሔዴ በፊት በዚህ መዝሙር እረፍት እናድርግ" አለና ወደ ኋላ ዞር ብሎ ኪቦርድ ፊት ለፊት የቆመውን ቆንጆው፣ ፍሪዝ አድርጎ ጥቁር ቲሸርት የለበሰውን ኪቦርድ ተጫዋች ዞር ብሎ ተመለከተው። ልጁም መዝሙሩን ለማጫወት የሙዚቃ መሳሪያ ኪቦርዱን መነካካት ጀመረ።

ዘርፌ ከበደ ከተባለችው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዘማሪት መዝሙር ውስጥ 'መንፈስ ቅዱስ' ከሚለው የመዝሙር አልበሟ ላይ መርጦ በኪቦርዱ ማጫወት ጀመረ። ፓስተር ናፍያድ መዝሙሩን አብሮ ማለት ጀመረ። በአዳራሹ ጥግ ጥግ ያሉት ስፒከሮች የዘርፌን ተስረቅራቂ ድምጽ ማውጣት ጀመሩ።



CamScanner

"የዓለም ቤዛ ኢየሱስ ነው

የፈወሰኝ ጌታ ነው

መዳን በሌላ የለም

እኔ አምናለሁ ዘላለም..."

"ደስ አይልም ወገኖች?"

ኪቦርዱን የሚጫወተው ልጅ መዝሙሩን በጣም ቀነሰውና የፓስተር ናፍያድ ድምጽ መድረኩን እንዲቆጣጠር አደረገው። "ይህን መዝሙር ሙሉውን እናንተ ስሙት። ስለ ኢየሱስ ብቻና ብቻ፤ መዳን እንዴት እንደሆነ ጥሩ አድርጎ የሚገልፅ ኦርቶዶክሳዊ ዝማሬ ነው። እኔ ወደ አምስተኛው ብቻ ልግባ" አለና ወደሚቀጥለው ትምህርት ሊገባ ሲል መዝሙሩ ከሚፈልገው አዝማች ላይ ሆኖ ሰማው "እስኪ አንዴ እሱ ጋር ከፍ አድርግልኝ" አለ ወደ ኪቦርድ ተጫዋቹ ዞር ብሎ። ልጁም የዘርፈን መዝሙር ድምጹን ከፍ አደረገው

"...አንዴ ለዘላለም ደሙ ፈሶልኛል

አሁን ያለ ኃጢያት ውዴ ይታይልኛል

ነፍሴን እንዲያነጻት ታርዷል ፋሲካዬ

በር ሁኖኝ ወደ ክብር አስገባኝ ቤዛዬ..."

እየሰማችሁ በእናታችሁ እዚህ መዝሙር ውስጥ አርብ ቁልጭ ብሎ ይታያችኋል? በቃ አርብን ያያችሁ ጊዜ ሌላ ታሪክ፤ ሌላ አማላጅ፤ ሌላ ቤዛ አያስፈልጋችሁም። በቃ የዓለም ቤዛ ኢየሱስ ነው። ምክንያቱም ውዳችን አንድ ጊዜ ግን ደግሞ ለዘላለም ዋጋ ከፍሎልን በር ሁኖ አስገብቶናል፡" በአዳራሹ የብዙ ሰው 'አሜን!' አስተጋባ።

"ለማንኛውም ወደ አምስተኛውና የመጨረሻው ብቻ እንግባ፤ አምስተኛው ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ 'Soli Deo Gloria' ነው። የዳንነው በእግዚአብሔር ኃይል ነው። ስለዚህ ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ ቅድስናና አምልኮ ለእግዚአብሔር ብቻ መሆን ይገባዋል እንጂ ክብር ለቅዱሳን ወይም ለሌሎች የእግዚአብሔርን የክብር ቦታ ማጣበብ ነው።

"በቃ ከዚህ ውጪ ክርስትና የለም። ክርስትና በእነዚህ መሰረታውያን ካልታነፀች ክርስትና አይደለችም። ተቀባይነትም አይኖረውም። ስለዚህ ኦርቶዶክስነት በዚህ ልክ

ስትታረምና በእነዚህ ሶላዎች ብቻ ስትታነጽ የሁላችን ቤት፤ የሁላችን እናት ትሆናለች። ካልሆነ ግን..." አሜን ጭብጨባ በአዳራሹ ውስጥ ድብልቅልቅ አለ።

በፊስአልጎስ ሕቡዕ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ በተቃራኒው ቁጣ፣ መደፈር፣ መናቅ፣ ብስጭት፣ ክብር መነካት፣ በስሜት ሳግ እየተናነቃቸው የሚያለቅሱም... ይታያል። ቁጣ የአዳራሹ የደንብ ልብስ ይመስል በሁሉም ፊት ላይ ይታያል። ኤልሲድ ፕሮጀክተሩ እንደመጥፋት ብሎ ዳግም በራና የተያየዘበትን ኮምፒውተር ዴስክቶፕ አሳየ።

## ምዕራፍ ፲፯

## አዲስ አበባ-ሳሪስ

ፓስተር ናፍያድ ኢትዮጵያ ከመጣ አስራ ሁለት ሰዓት አልፎታል። የጉዞ ድካም ስለነበረበት እንዲሁም የአንቀልፍ ሰዓቱን ማስተካከል ስለ ነበረበት ኢትዮጵያ ከመጣ ጀምሮ ብዙውን ሰዓቱን ተኝቶ ነበር ያሳለፈው። ስልኩንም ያበራው ዘግይቶ ስለ ነበር የተፈጠረውን ነገር አላወቀም ነበር።

በማኅበራዊ ድረገጽ የተሰራጨውን ቪዲዮ የተመለከቱ ሰዎች ቢደውሉለትም አላገኙትም። ማዕረግና ስንፎር ስለጉዳዩ እንደ ማንኛውም ሰው ቢሰሙም ዘግየት ብለው ነበር ቪዲዮውን ያዩት። ቪዲዮውን ስንፎር ስታየው እጅግ በጣም ደንግጣ ነበር። የምትይዝ የምትጨብጠውን አጣች። አባቷን በዚህ መንገድ ስለማታውቀው እንዳች የሆነ ነገር ይኖራል እንጂ እሱ እንዲህ አይልም ብላ አስባ ነበር። ቢሆንም የሚያጠራጥር ነገር ልታገኝ አልቻለችም።

በተቃራኒው ወንድሟ ማዕረግ በደስታ ነበር ቪዲዮውን የተመለከተው። በአባቱ ትልቅ ኩራት ስለተሰማው ደስታና አድናቆቱን ለመግለጽ ቤት እስኪገባ ድረስ አላደርስ ብሎት ቪዲዮውንካየበት የኢንተርኔት አገልግሎት መስጫ ቤት ውስጥ ሆኖ ለአባቱ ስልክ ደወለ። ቢሆንም የአባቱ ስልክ ዝግ ነበር።

ፓስተር ናፍያድ ከተኛበት ተነስቶ ራሱን ካስተካከለ በኋላ ነበር ስልኩን ያበራው። ስልኩ በከፈተው ቅጽበት ነበር እጁ ላይ የጠራው። ከጥሪው ባሻገር የጽሁፍ መልዕክቱ ማቋረጫ የለውም ነበር። በቪዲዮው ይዘት የተደሰቱ ሰዎች በደስታ ተሞልተው ነበር። በተቃራኒው 'ምን ነካህ ፓስተር?' ያሉትና በድንጋጤ ያናገሩት ሰዎችም ነበሩ። ፓስተር መጀመሪያ ላይ ግራ ቢጋባም ቀጥሎ ነገሩ ትንሽ ትንሽ እየገባው መጣና ስልኩን መልሶ ዘግቶ ቪዲዮውን ለማየት ኮምፒውተሩን አብርቶ ሰሪጂ ሲዲኤምኤውን አገል ኮምፒውተሩ ላይ ሰክቶ ዩቱብን ማሰስ ጀመረ። ሰዎች የቪዲዮውን ርዕስ ስለ ነገሩት ፊልጎ ለማግኘት ብዙም አላስቸገረውም፤ ቪዲዮውን ሲመለከተ ኔትወርኩ እየተቆራረጠ ቢያስቸግረውም ጨርሶ ተመለከተው።

ፓስተር ናፍያድ ቪዲዮውን ሲመለከተው ደንግጧል፤ አዎ ቪዲዮው ላይ ያለው ሰው ራሱ ነው። ግን ቃሉ የእሱ አይደለም። ድምጹን አመሳስለው ያላለውን ቃል ግን እንዳለ አስመስለው አቀናብረውታል። ይህን ስብከት ያደረገው መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ነው። እውነት ነው የዘርፊን መዝሙር የዛን ቀን ተጠቅሟል ነገር ግን ለዚህ አላማ አልነበረም።

ከኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚደርስበት ውርጅብኝና ቁጣ እንዴት አድርጎ ይችለዋል። ዩ ቲዩብ ላይ ያለው አስተያየት በጣም አስፈራው። ከዚህ ሁሉ

ያናደደውና ያስቆጣው እንዲህ ተንኮል ያደባበት ሰው አላማ ነው፤ እምኖበትና የራሱ ሀሳብ ቢሆን እንደዚህ ባልሆነ ነበር። ግን አይደለም።

ፓስተር ናፍያድ ከተቀመጠበት ወንበር ላይ ሆዱን እንደተጣላው ሰው አቅለሸለሸው፤ ወባ እንዳለበት ሰው ሰውነቱ ሙቀት በሙቀት ሆኖ እንደማንዘፍዘፍ አደረገው፤ መላ ሰውነቱ በላብ ተጠመቀ፤ በሰራ አካላቱ ንዴትና ድንጋጤ ተሞላ።

ይህን ነገር ማስተባበል አለበት። ለዚያውም በፍጥነት ካልሆነ አደጋው ከባድ ይሆናል። በእርግጥ ብዙ ደጋፊዎች ከፕሮቴስታንት አማኞች ይኖሩዋል። ግን የፓስተር ናፍያድ የደጋፊ ርሀብተኛ አልነበረም። ከዚያ ይልቅ የነገዋ ኢትዮጵያ ትበልጥበታለች። የነገ የኦርቶዶክስና የፕሮቴስታንት አማኝ ወጣቶች በእሱ የተነሳ የጎሪጥ ሲተያዩ፣ ሲገለማመጡና ሲዛዛቱ ማየት አይፈልግም።

እምነትን ከእምነት፤ አመለካከትን ከአመላካከት፤ ቋንቋን ከቋንቋ፤ ሰው ከሰው፤ ጎሳ ከጎሳ፤ ባልና ሚስት... ማጋጨት፣ ማጣላት፣ ማበጣበጥ በቀላሉ ይቻል ይሆናል። ነገር ግን ፍቅርን እንደነበረው እንደቀደመው መመለስ ቀላል አይደለም። የትውልድ ዘመን ይጠይቃል፤ ጊዜ ይወስዳል። አገሪቷ ያሉባት ሌሎች ራስ ምታቶች ይበቋታል እኔ እንደገና የምትፈርስበትን ጡብ እንዴት አቀብላለሁ፤ እንዴት ዓይኔ እያየ ላደኩበት ማኅበረሰብ፤ ለወጣሁበት ቤተሰብ ጥላቻና መገፋፋትን አሳድጋለሁ' እያለ ማሰብ ጀመረ።

---------//-------

ሰባቱ የፊስአልጎስ ሥራ አስፈጻሚዎች በስብሰባና በውይይት ራሳቸውን ወጥረው ውለዋል። ሥርአት ያለውና ይህ ነው የሚባል ወትሮ የለመዱት መደበኛው እህል በአፋቸው ሳይዞር ውሃና ኩኪስ እየቀማመሱ ከረፋዱ አራት ሰዓት ስብሰባውን የጀመሩ አስር ሰዓት ከሩብ ድረስ ዘልቀዋል።

አፍንጫው ደፍጠጥ ብሎ ኮስታራ የፊት ገጽታ ያለው የፊስአልጎስ ሕቡዕ ቡድን ሰብሳቢ ዶክተር ገመዳ ስብሰባውን በባለ ተሽከርካሪው ምቹ ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ ዓይኑን እያሻሸ መናገር ጀመረ። እንደ ደከመው ያስታውቃል።

"የፊስአልጎስ ሕቡዕ ድርጅት በፍጥነት ለፓስተር ናፍያድ የተሐድሶ አስተምህሮ መልስ መስጠት ይኖርብናል። መልሱም አጥጋቢ እንዲሁም በጣም በፍጥነት መሆን አለበት። ምክንያቱም በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ የተሐድሶ ስሜት ከመቼውም በላይ ልቆ ስለታየና መነጋገሪያ አጀንዳ ስለሆነ ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ ለምእመኑ መልስ መስጠቱና በቂ እውቀት ማስያዙ ግድ ነው።"



CamScanner

ቀጥሎ የተናገረው ጠይሙ የፊስአልጎስ ሕቡዕ ድርጅት ጸሐፊ ታንቱ ጠዋት በርዶት እጁን ጃኬቱ ኪስ ውስጥ ደብቆ ብርዱን እንዳልተከላከለ አሁን ደግሞ የክፍሉ ሙቀት አስቸግሮት ጃኬቱን አውልቆ በሸሚዝ ነው ያለው፡፡

"በአፋጣኝ ምላሽ መስጠቱ ብቻ ሳይሆን ለሲኖዶስ አባላትም ያለውን ችግር አስረድተን በጉዳዩ ላይ አጽንኦት እንዲሰጡ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ በተጨማሪም ቋሚ ሲኖዶሱ ጥብቅ ውሳኔ ሊሠጥበት ይገባል፡፡ ስለዚህም ያለውን ችግር ቪዲዮውንና ከዚህ ቀደም የነበረውን ማስረጃ አስደግፈን ለሲኖዶስ አባላት እንበትን፡፡ ሲቀጥል በማኅበራዊ ድረገጽ ልንለቃቸው ይገባል፡፡" አለ መሀል አናቱን አሁንም አሁንም ቆፈር ቆፈር እያደረገ፡፡

አበጋዝ ዛሬም ጥንቅቅ ብሎ እንደዘነጠ ነው፡፡ ሙሉ ጥቁር ሱፍ የለበሰ ሲሆን ነጭ ሸሚዝ ያለ ከረቫት አድርጓል፤ ሁሌም የሚታወቅበት ቀላልና ማሰሪያ ገመድ የሌለው ጫማ በጥቁር ካልሲ ተጫምቷል፡፡ አበጋዝ በተሐድሶ ጉዳይ በቂ እውቀትና ዝግጅት ስላለው ለፓስተር ናፍያድ ትምህርት መልስ እንዲሰጥ ተወስኗል፡፡

ለመልሱ ሁለት የዝግጅት ቀን ተሰጥቶታል፡፡ አበጋዝ በቤተ ክርስቲያኗ ዲያቆን የሚል ማዕረግ ያለው ሲሆን በዓለማዊ ትምህርት ደግሞ የአእምሮ ሐኪም ስለሆነ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሐን እየተጋበዘ ብዙ ቃለ ምልልሶች ስለሰጠ በከተማው ይታወቃል፡፡ መልሱን በእሱ ማስነገሩ ቅቡልነቱና መነጋገሪያ ርዕስ ማድረጉን ከፍ ያደርገዋል ብለው የፊስአልጎስ አመራሮች አምነዋል፡፡

አበጋዝ ሲናገር ሁሌም እንደሚያደርገው ፀጉሩን ወደ ፊት ለፊት ደፋ ያደርገዋል "አሁን እኔን ያስጨነቀኝ አስቀድሞ የታወቀውና ውጪ ያለው ግፊትና ስድብ አይደለም፡፡ ከዚያ ይልቅ ውስጥ ያሉትን እንዴት ነው የምናጠራው ነው ጥያቄው፡፡ እንደ ስደተኛው ሲኖዶስ ሁሉ እዚህም እኛ ጋር ተሐድሶ የራሳቸውን ጳጳስ እንዳያሾሙብን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል፡፡" አበጋዝ ራሰ በራነት ያራቆተውን ጭንቅላቱን ባለችው ጸጉሩ መለስ አድርጎ ወደ ፊቱ አስተኛትና ንግግሩን አቆመ፡፡

አደይ ከአበጋዝ አፍ ነጠቅ አድርጋ መናገር ጀመረች "አሁን ያለው ተሐድሶ አላማ ሁለት ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያናን ሙሉ ለሙሉ መውረስ ካልሆነም የሕንድ ኦርቶዶክስን የተሐድሶ ተሞክሮ ወስደው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ላይ ቤተ ክርስቲያኗን ለሁለት ጥረት እያደረጉ ነው፡፡ ስለዚህም ቤተ ክርስቲያኗን ለመክፈል ደግሞ የራሳቸው ኤጲስ ቆጶሳት ስለሚያስፈልጋቸው እነሱን ለማስሾም የማይፈነቅሉት ድንጋይ አይኖርም፡፡" አደይ የፌዝ ፈገግታ ፈገግ ስትል ጥርሷ ንጣቱ ደስ ይላል፡፡

በፍጥነት ፈገግታዋ ዳመነና ጠቆር ብሎ የነጥብ ምልክት ያለውን የላይኛዋን ከንፈሯን እንደ መንከስ አለችና ንግግሯን በድጋሚ ቀጠለች "ስለዚህ የተሿሚዎችን

ማንነት እያጠራን ለሕዝቡና ለሲኖዶሱ ከበቂ ማስረጃ ጋር ልናቀርብ ይገባል፡፡ የተሐድሶው ተሿሚዎች በገንዘብም ሆነ እራሳቸውን ለማስተዋወቅ በቂ የሆነ ድጋፍ ከተሐድሶው ቡድን ስለሚኖረው ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ይሄ አሁን የተለቀቀው ቪዲዮ የዚሁ አካል ይመስለኛል፡፡ ምልከታችንን ቪዲዮው ላይና ወደ ውጪ ስናደርግ ከውስጥ አደጋ ለመፍጠር ነው፡፡ ስለዚህ ቁጥጥራችንን ሳንዘናጋ አንዱ ላይ ብቻ ሳናተኩር ከውስጥ ከውጪም ልናደርግ ይገባል፡፡"

ሌላኛዋ የአስፈጻሚ ኮሚቴው አባል ሐዊ ጉሮሮዋን እንደመጠራረግ ብላ ንግግር ማድረጓን ቀጠለች "አሁን ከዚህ ቀደም እንዳለው ሁሉ በኦርቶዶክስ እና በፕሮቴስታንት መካከል ያለውን ልዩነት በግልጽ ልናስቀምጥ ይገባል፡፡ በጣም በሰፊው አንድ ስለ መሆናችን ሳይሆን ስለ ልዩነታችን ለኦርቶዶክስ ምእመናን በቂ ገንዛቤ ልንሰጥ ይገባል፡፡"

የፊስአልጎስ ሰብሳቢ ወደ ሐዊ እየተመለከተ "ጨረስሽ?" አለ፡፡ ሐዊ ስርጉድ የሚለውን ጉንጯን በፈገግታ ይበልጥ ሰርጎድ አድርጋ "አዎ" አለች፡፡ አበጋዝ ሐዊ እንደ ጨረሰች ሲያውቅ እድሉን ሳይጠይቅ መናገር ጀመረ፡፡ እንዲህ እንዲናገር ያደረገው በግብጽ አገር ተነስቶ በነበረው የተሐድሶ እንቅስቃሴ በወቅቱ የግብጹ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ የነበሩት አቡነ ሽኖዳ ተሐድሶን ለመቆጣጠር የወሰኑት ውሳኔዎችና የጻፏቸው መጽሐፍት ትዝ ብሎት ነው፡፡ ከምንም በላይ 'ኮምፓራቲቭ ቲዮሎጂ'፣ 'ዩዝ ኮንሰርን ኩዌሽን'፣ 'ፕሪስትሁድ' እና 'ዘ ሰቨን ወርድስ አወር ሎርድ ኦን ዘ ክሮስ'፣ 'ዘ ኤንጅል' የሚሉትን መጽሐፍት ደግሞ ደጋግሞ አንብቧቸዋል፡፡ በተለይ ኦርቶዶክስ እና ፕሮቴስታንት ሃይማኖት ያላቸውን ልዩነቶች በግልጽ ግን በትህትና "our brethren protestant" እያሉ ያስቀመጡትበትን 'ኮምፓራቲቭ ቲዮሎጂ' መጽሐፍ ሲወደው፡፡

"ሐዊ ከጨረሰች እዚህ ላይ የምጨምረው ነገር አለኝ፡፡ በእምነቶች ላይ ቅየጣ ወይም ሲንክሬቲዝም የሚከሰተው ምእመኑ የራሱን የእምነት ድንበር አለማወቁ ነው፡፡ አለማወቁ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች እምነቶች ጋርም በምን በምን እንደሚለያይ ስለማያውቅ ነው፡፡ አለማወቁ ደግሞ 'ምን ችግር አለውና እዚህም ሆነ እዚያ ፈጣሪ ነው የሚመለከው' ወደሚል መደምደሚያ ይገፋዋል፡፡ ይሄ ደግሞ 'ቤተ ክርስቲያኗ የአስተምህሮ ለውጥ ያስፈልጋታል' ለሚለው ቡድን አመቺ መደላድል ይፈጥርለታል፡፡ እንደዚህም ሊገዳደሩን የቻሉት ሰፊ የሚባለው የኦርቶዶክስ አማኝ የነገረ መለኮት እውቀቱ አናሳ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ የህዝቡን መንፈሳዊ እውቀት ከፍ ማድረግ ይኖርብናል፡፡"

--------//------



CamScanner

## አዲስ አበባ ሳሪስ

ዘላለም ጥቁር መነፅር አድርጎ ፓስተር ናፍያድ ከአሁን አሁን ወጣ አልወጣ እያለ እንደ ንዳድ በምታቃጥለው ፀሐይ እየተጠበሰ በመጠባበቅ ላይ ነው። ዘላለም ዛሬ የፓስተር ናፍያድን ጉዳይ እንዲያጠናቅቅ ተነግሮታል።

የደቂቀ እስጢፋኖስ አፋኝና ገዳይ የሆኑት ዘላለም እና ዳንኤል ዱባይ ውስጥ በመዝናናት ላይ የነበሩ ቢሆንም ከትናንት በስቲያ በቶኒ ትእዛዝ ነው አዲስ አበባ የገቡት። ከእነሱ የሚጠበቀው ዝግጁ ሆነው መጠበቅና እንደታዘዙት ቅጠፉ የተባሉትን ምንም እንኳ ገና ያልበሰለ ውብ ጽጌረዳ ቢሆንም፤ ምንም እንኳ ብዙ ያፈራ ግን ያልበሰለ ጣፋጭ ፍሬ ቢሆንም ይቀጥፋሉ።

ሰውሩ የተባሉትን ምንም እንኳ የሚሰወረው የግመል ያህል ቢተልቅ፤ ተልኮው በመርፌ ቀዳዳ የመሽሎክ ያህል አስቸጋሪ ቢሆን እንኳ በድፍረትና በጭካኔ ተልእኳቸውን ተቀብለው ይሰውራሉ። ግደሉ የተባሉትን ልክ ድመት ልጇን ስትበላ ስቅቅ እንደማይላት ሁሉ፤ በተፋፋመ ጦርነት መሀል ጠላት ላይ እንደሚተኩስ ወታደር ሁሉ ያለምንም መሳቀቅ እና መጨነቅ ይገድላሉ። የሞት ውሳኔ የተላለፈባቸውን ሰዎች ምስል፣ አድራሻና የሕይወት ታሪካቸው ከቶኒ ይላክላቸዋል። ዘላለምና ዳንኤል እንደ ተባሉት ይፈፅማሉ።

የዛሬው ተረኛ ፓስተር ናፍያድ ነው። ስለ ቪዲዮው ቀድሞ ካስተባበለ አደጋው ከባድ ነው። ፓስተር ናፍያድ ሳይቀድም ለመቅደም ዘላለም መኪናው ውስጥ ቁንጥንጥ እያለ ፈዛዛ ቢጫ ቀለም የተቀባውን የፓስተር ናፍያድን በር አፍጥጦ እየተመለከተ ነው።

ዘላለም ያፈጠጠበት የናፍያድ ጊቢ ተከፈተና ጥቁር ያሪስ መኪና ወጣ። ዘላለም ሰውነቱ ንቅቅት ብሎ የምትወጣውን መኪና የምትሄድበትን አቅጣጫ ማየት ጀመረ። ፓስተር ናፍያድ ነው። ፈገግ አለና "ወዴት ሊሔድ ነው ይሄ ሰውዬ?" አለ። የፓስተር ናፍያድ መኪና እንቅስቃሴ በጥንቃቄ እየተመለከተው እያለ የዘላለም ስልክ ላይ መልዕክት ገባ። መልዕክቱ የመጣው በቫይበር ሲሆን ላኪው ቶኒ ነው።

## ምዕራፍ ፲፰

## አዲስ አበባ-አዲሱ ገበያ

ከሰሜን ሆቴል ወደ ቶታል በሚወስደው የበላይ ዘለቀ መንገድ ሽቅብ ሲወጡ በስተቀኝ በኩል ዝም ያለ ቤት አለ። ቤቱ ፎቅ አይደለም ከዚያ ይልቅ በነጭ ጠጠር የተለበጠ ቪላ ነው። የቤቱን ሁለመና ላየ ሰው የግለሰብ ሳይሆን የቆንሲላ ጽሕፈት ቤት ወይም የአገሪቱ ትልቅ ባለ ሥልጣን መኖሪያ ነው የሚመስለው።

ከቤቱ ጣራ በታች ባለ ለውበት በተሰራ የእምነበረድ ድንጋይ ላይ ትልቅ፣ በጊዜ ብዛት የወየበ የውጭ አገር የቴሌቪዥን ጣቢያ መሳብያ ስሀን ወደ ግራ ጋደል ብሎ ተሰቅሎ ይታያል። ለሰዎች ብቻ መግቢያ በሆነው በር ሲገቡ የመኖሪያ ቤቱ ዋና በር ከተከፈተ በጀርባ ያለውን አረንጓዴ ቀለም የተቀቡትን ትናንሽ ቤቶች ማየት ይቻላል።

በመኪና መግቢያው በር በኩል ደግሞ አራት መኪኖች ፊትና ኋላ ሆነው በሁለት ረድፍ ቆመዋል። ሁለት ነጭ የቶዮታ ምርት የሆኑ ያሪስ መኪኖች፣ ጥቁር የሆንዳ ምርት የሆነ ዘመናዊ መኪና እና የሀዩንዳይ ምርት የሆነው ኢላንትራ መኪና ነው።

ከግቢው ዋና በር አምስት ያህል እርምጃ ከተራመዱ በኋላ ከፊት ለፊት እምነበረድ የተነጠፈ ባለሶስት ደረጃ ወጥቶ የዋናው ቤት በር ይገኛል። የዋናው በር እንደ ተከፈተ ፊት ለፊት የሚያስኬድ ኮሪደር ሲኖር ከኮሪደሩ በስተግራ በኩል ደግሞ ውቡ እና ቡኒ መልክ ያለው ቁም ሳጥን እንዲሁም በዝግባ እንጨት የተሰራው ከግራና ቀኝ ካለው ከመዳኛ ጋር ተመሳሳይ መልክ ያለው አልጋ የያዘውን መኝታ ቤት አለ። ከአልጋው በስተግርጌ በሚያምር ፍሬም ውስጥ ያለ ትልቅ መስታወት አለ። ይህ ሁሉ ያለው ባለ እንጨት ወለሉ መኝታ ቤት ውስጥ ነው።

ከመኝታ ቤቱ ፊት ለፊት ትልቁ ባለ ሁለት ክፍል ሳሎን አለ። ይህ ሳሎን ሁለት እንዲባል ያደረገው ከላይ ከጣራው ጀምሮ በውቡ ሳሎን መሀል ለመሀል የሚከፍል ከኮርኒሱ በጥቂቱ ወጣ ያለ ግርግዳ ስላለ ነው። ከታችኛው ሳሎን ውስጥ እሳት ማሞቂያ እንዲሁም በቆዳ ከተሰራው ቀዩ ሶፋና ቄንጠኛ ቅርጽ ባለው በፕላስቲክና በመስታወት የተሰራው ጠረጴዛን ይዟል።

የላይኛው ደግሞ ትንሽ ሆኖ ወደ ቀይ ቡኒ ያደላ ብፌ የያዘ ሲሆን የብፌው እቃዎች ጥራትና የአደራደር ሕብረትና ስብጥር አንዳች ደስታን ይሰጣል። ብፌ ካለበት ፊት ለፊት ወደ ኩሽና የሚወስድ ነጭ ቀለም የተቀባ በር አለ።

የደቂቀ እስጢፋኖስ አባላት ሶፋው አካባቢ ክብ ሰርተው ተቀምጠዋል። ከሶፋው ፊት ለፊት ባለው ጠረጴዛ ላይና ታች መጽሐፍ ቅዱሶች አሉ። መጽሐፍ ቅዱሶቹ እብራይስጥኛ፣ ታዋቂው የእንግሊዝኛ ትርጉም ኪንግ ጀምስ መጽሐፍ ቅዱስ



CamScanner

እንዲሁም በተለያየ ዘመን ኢትዮጵያ ውስጥ የታተሙ መጽሐፍ ቅዱሶች ተቀምጠዋል።

ከተሰብሳቢዎቹ ውስጥ አራቱ የኬንያውን ስብሰባ ተከታትለዋል። ሁሉም ወትሮ ከሚታወቁበት መንፈሳዊ ቀሚስ ተላቀው እንደማንኛውም ሰው ዘንጥ ብለው ሰብሰዋል። በቤቱ ግርግዳ ጥግ ጥግ ላይ በተሰቀሉት አነስተኛ ስፒከሮች ውስጥ በዘመናዊ ሙዚቃ መሳሪያ የተቀነባበረ ለስለስ ያለ የመዝሙር ዜማ ይሰማል። በዚህ ሰዓት የሚሰማው የፕሮቴስታንት እምነት ዘማሪ ኤፍሬም አለሙ 'ሕይወት ይናገር እስኪ' የሚለው የመዝሙር ዜማ ነው።

-------//----

## አዲስ አበባ-ሳሪስ

ሰንፔር እንደ ወትሮዋ ዘንጥ ብላ ከመስታወት ፊት ቆማለች። ከስር የተጫማችው ክፍት ጫማ በቂንጣ የተቀባውን ውብ የእግሯን ጣቶች ያሳያል፤ ታይዋን ሰራሽ ጅንስ ሱሪ የታጠቀች ሲሆን ዳሌዋን ሰብስቦ አውጥቶት በውበቷ ላይ ውበት ጨምሮላታል፤ ከላይ ሰማያዊ ቲሸርት ለብሳለች።

ከንፈሯን ቀይ ሊፒስቲክ ተቀብታለች፤ መልካም መዓዛ ያለውን ሽቶዋን ከቦርሳዋ አውጥታ አንገቷ ላይ ያለ በስሱ አርከፈከፈችውና አልጋዋ ላይ የተቀመጠውን አባቷ ከእንግሊዝ አገር ያመጣላትን ቦርሳ ትከሻዋ ላይ እንደዘበት ጣል አደረገችና ከመኝታ ቤቷ ወጣች።

ወንድሟ ሳሎን ቁጭ ብሏል። እህቱ ከመኝታ ቤቷ ወጥታ ወደ ሳሎን ስትገባ ፊቱን ከስክሶ ተቀበላት።

ሰንፔር ፈገግ ብላ "ምነው?" አለችው

"በሰላም ነው ተኳኳትረሀል" አለች

ማዕረግ አሁንም ያኳሳተረውን ፊቱን ሳይፈታ "ለምን አልኳሳተረም? እኳሳተራለሁ! ሰዎችሽ ጉባኤ ዘርግተው ሊሳደቡ ነው።" ሮዳስ ፍቅረኛዋ እንደሆነ ስለሚያውቅ ሰንፔርን ለማናደድ 'ሰዎችሽ' ይላታል።

"አልገባኝም የምን ጉባኤ ነው?"

"እንቺ ደግሞ ሁሌ የሰዎችሽ ነገር አይገባሽም"

"እንደ ለመዱት የከተማውን ግርግዳ በጉባኤ ጥሪ አደማምቀውታል"

"ታዲያ ምን ችግር አለው? መብታቸው መሰሎኝ"

"እሱማ መብታቸው ነው። የዛሬው ጉባኤ ግን በአባታችን ላይ ጦርነት ላይ ሊያውጁ መሆናቸው ነው እንጂ ክፋቱ"

"ስትል?"

"ስልጣ በአባዬ ትምህርት ላይ መልስ ምት ሊሰጡ ነው። ለዚያ ነው ቦሌ መድኃኔዓለም ጉባኤ ጠርተዋል። ብትችይ በወዳጆችሽ በኩል አንድ ነገር ብታደርጊ?"

ስንፒር ደነገጠች፤ የሆነ የሚጨንቅ ነገር ተሰማት "ምን ላደርግ እችላለሁ"

"ማድረግማ ትችያለሽ ሰውየሽ ለመቼ ይሆንሻል? ምንድነው ወደጆቹ አይደሉም? ነገሩን ማረጋጋት ቢቻል ጥሩ ነው ካልሆነ መልስ ምቱ ይከብዳል በይው" አለ እንደመኩራራት እያለ።

ማዕረግ ሀሳቡ ገረማት "ማዕረግ! ነገሩን የሰፈር ጥል አደረከው እኮ። የቤተ ክርስቲያኗን ጉዳይ በአንድ አባወራ የሚመራ አስመሰልከው። አሁን አሁን የራስ ቤትም በአንድ ሰው አይመራም እንኳን ቤተ ክርስቲያን... ለማንኛውም እስኪ አጣራለሁ።"

"ምን ታጣሪያለሽ ወጣ ስትይ ፖስተሮቹ ይነግሩሻል" ማዕረግ እንደ መደንገጥ ብሎ "...ኡኡ... የሰፈሮቹን ፖስተሮች ገንጥያቸዋለሁ፤ ለነገሩ ወጣ ስትይ ሌላ ቦታ ታገኛቸዋለሽ" አለና በሳቅ ፍርስ አለ።

## ምዕራፍ ፲፱

## አዲስ አበባ-አዲሱ ገበያ

የደቂቀ እስጢፋኖስ ሕቡዕ ቡድን አባላት ስብሰባውን በትጋትና በጥንቃቄ እያካሄዱ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የማደስ ስራ ራሱን 'ደቂቀ እስጢፋኖስ' ብሎ በሰየመው ሕቡዕ ቡድን ይመራል። ይህ ሕቡዕ ቡድን ራሱን ደቂቀ እስጢፋኖስ ብሎ የሰየመበት ዋናው ምክንያት 'በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ላይ የመጀመሪያውን የተሐድሶ እንቅስቃሴ ከጀርመናዊው ማርቲን ሉተር ቀድመው በአሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን አባ እስጢፋኖስ የተባሉ ኦርቶዶክሳዊ አባት አስነስተዋል' ብለው ስለሚያምኑ ነው።

አባ እስጢፋኖስ 'ስግደት ለሥላሴ ብቻ፤ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን በሚገባ ማክበር፤ ምንኩስና ሕይወትን አጥብቆ መከተልና ሁለቱን ሰንበቶች ማክብር' የሚሉ ሀሳቦች ነበር ይዘው የተነሱት። እነዚህ ሀሳቦች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነትና አስተሳሰቦች ናቸው።

አባ እስጢፋኖስ በጊዜው ከነበረው ንጉስ አፄ ዘርዐ ያእቆብ ጋር ግጭት ውስጥ የገቡበት ዋና ምክንያት 'ስግደት ለሥላሴ ብቻ' በሚለው አቋማቸው ነው። "ይህ አቋም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አቋም ቢሆንም ስግደትን በሦስት ከፍላ 'አስተብርኮ፤ አድንኖና እና ሰጊድ' ከሚሉት አካሄዶች ጋር ስላጋጩት ነው" ይላሉ የአባ እስጢፋኖስ አካሄድ ላይ ቅሬታ የሚያነሱ ሰዎች።

"'አስተብርኮ' ማለት ጉልበትን ወደ ምድር ሸብረክ አድርጎ መነሳት ሲሆን ይህም በኢትጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቅዳሴ ላይ ካሕኑ 'ንሰግድ' እያለ በአስተብርኮ እየሠገደ እና ማዕጠንቱን እያጠነ ለሕዝቡ ያሳያል፤ ሕዝቡም 'ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዘ ሠለስቱ አሐዱ' እያሉ ሦስት ሲሆኑ አንድ ስለሚሆኑ ለአብ ወወልድ መንፈስ ቅዱስ እንሰግድ እያሉ ያመሰግናሉ።

"'አድንኖ' ደግሞ ከአንገት ጎንበስ ተብሎ የሚደረግ ስግደት ነው። 'ይህም በቅዳሴ ላይ '...አድንኑ አርስቲክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክነ...' እየተባለ በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ በሉ ይባላል። 'ሰጊድ' ደግሞ ከመሬት ወድቆ ግንባርን መሬት አስነክቶ መስገድ ሲሆን ይህም ለሥላሴ ብቻ የሚደረግ፤ ከሰጊድ በስተቀር የተቀረውን ለቅዱሳን ሁሉ ይደረጋል ቢሉም፤ ናቡከደነጾር ለዳንኤል እንደ ሰገደው፤ እስራኤላውያንም በታቦተ ጽዮን ፊት ተደፍተው ሰግደዋል ስለዚህ ሰጊድም ለቅዱሳን ይፈጸማል።" ብለው የሚከራከሩ አሉ። "ነገር ግን ዳንኤልን እንደ አምላክ ተመለከ ወይም ለታቦቱ እንደ ፈጣሪ ታይቶ ተሰገደ ሳይሆን ለዳንኤል አምላክ፤ ታቦቱን



CamScanner

ለሰጠን ፈጣሪ ተሰገደ እንደ ማለት ነው፡፡ ዋናው ልዩነት ልብ ወይም መንፈሱ ነው፡፡" ይላሉ፡፡

ይህ ነባር ብሒል ነበር አባ እስጢፋኖስ አልፈጽምም ያሉት፡፡ ስለዚህም 'ለመስቀል፣ ለመላእክት እና ለማርያም የአክብሮት ስግደት አልሰግድም' ብለው ነበር፡፡ እንዲሁም ለንጉሱ ለዘርዐ ያእቆብ የአክብሮት እጅ መንሳትንም እንደ ስግደት ስላዩት ጎንበስ በማለት ክብር መስጠቱን ነፈጉ፡፡ በዚህ የተነሳ አባ እስጢፋኖስ እስከ ተከታዮቻቸው መሰደድ እንግልት እንዲሁም በድንጋይ ተወግሮ እስከ መሞት አድርሷቸዋል፡፡

ደቂቅ ማለት ልጅ ሲሆን እስጢፋኖስ የእንቅስቃሴው አስጀማሪ አባት ናቸው፡፡ ለዚህም ነው የተሐድሶው እንቀሳቃሽ ራሱን ደቂቀ እስጢፋኖስ ያለው፡፡ ነገር ግን የአባ እስጢፋኖስም ሆነ የደቀ መዝሙሮቻቸው እንቅስቃሴ ቤተ ክርስቲያን ማደስ አይደለም ብለው የሚከራከሩ አያሌ ናቸው፡፡

ምክንያታቸውን ሲያስቀምጡም "ታቦትን ለቅዳሴ ይጠቀሙ ነበር፣ ለመዳን የኢየሱስ ክርስቶስን አማናዊ ስጋና ደም መቀበል፣ በጥምቀት ያምኑ ነበር፡፡ ገዳማቸው ደብረ ጉንዳጉንዲ የማርያም ቤተ ክርስቲያን፣ ሕይወታቸው ምንኩስና፣ ውዳሴ ማርያምንና አንቀጸ ብርሃንን ለጸሎት መጽሐፍትነት ይጠቀማሉ፣ ክህነት የሚቀበሉት ከጳጳሱ ነው፡፡ የአባ እስጢፋኖስ ደቀመዛሙርት ደግሞ ለማርያም ለመስቀል የአክብሮት ስግደት ያደርጉ ነበር" በማለት ይከራከራሉ፡፡

ተከራካሪዎቹ ከማርቲን ሉተር ጋር ለሚያገናኙትም መልስ ሲሰጡ "በአንጻሩ ማርቲን ሉተር የጀመረው ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ ግን እነዚህን ሁሉ አይቀበልም፡፡ ስለሆነም ደቂቀ እስጢፋኖስ ተሐድሶዎች እንደሚሉት ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ አልነበሩም" ብለው ያስረግጣሉ፡፡

----------//--------

## አዲስ አበባ-አዲሱ ገበያ

አራት ማዕዘን ሆኖ ሰማያዊ ቀለም ያለው ባለ ማዕቀፍ መነጽር ያደረገው፣ እግሩ ላይ ጠበብ ያለውን በሰውነት ልክ የተሰፋውን ካኪ ሱሪ የለበሰው ወጣቱ የሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ምሩቁ ግሩም እየተናገረ ነው፡፡

"በአሁኑ ሰዓት ከወረዳ አልፈን ዞኖችን ተቆጣጥረናል፡፡ ነገር ግን ይህ ይዞታችን ላይቆይ ይችላል፡፡ ማቅ ያለው ነገር በደንብ አውቆታል፡፡" ማቅ ማለት ማኅበረ ቅዱሳንን አሳጥሮ ለመጥራት ተሐድሶዎች የሚጠቀሙበት ቃል ሲሆን ትርጉሙም ሐዘንን ጥቁርን ለመግለፅ ነው፡፡ ተሐድሶዎች ይህን ቃል የሚጠቀሙት ሆን ብለው ማኅበረ ቅዱሳንን ለማሳነስና ለመስደብ ነው፡፡



CamScanner

ጥቁርና እንደ ጦር የሾለ ነው። ትርሲት ቡናው እንዳያቃጥላት ሰግታ ስለ ነበር ራቁቷን መሆኗን ያሰበችው እንኳ ገላዋ እንዳልተቃጠለ ካረጋገጠች በኋላ ነበር።

ግሩም 'አይዞሽ' እያለ ጡቷ ላይ የተንጠባጠበውን ቡና ይጠርግላት ጀመር። ከሥንቱ አልፎ ሱሪውን ያጨናነቀው ወንድነቱ ግን ሊታገስ አልቻለም። ግሩም የትርሲትን ከንፈር ሳመው። ትርሲት ፍዝዝ ብላ ግሩምን ታየው ጀመር። ይህኔ ጡቷን በኃይል ጭምቅ አደረገው። ትርሲት ፊቷን ቅጭም ከማድረግ ከፍ ባለ ምንም ማለት አልቻለችም። ግሩም እቅፍ አደረጋትና ከአጠገባቸው ባለው ሶፋ ላይ አስተኛት። ትርሲትም አልተከላከለችም። ከዚያ በኋላ ግን አልተደገመም።

ግሩም ከቅንዝር ስሜቱ የተመለሰው ትርሲት መናገር ስትጀምር ነው "ተሐድሶውን ብቻችንን እያካሔድን አስመስለነው እኮ? ተሐድሶውን ከውስጥም ከውጪም የሚደግፉን ብዙ አካላት አሉ። ስለዚህ በተለይ ከስደተኛው ሲኖዶስ የሚሆነውን ነገር መጠበቅ ይኖርብናል። ከዚያ ይልቅ ዛሬ ብናወራ ደስ የሚለኝ እዚህ ሰላሉን የሰንበት ትምሕርት ቤት አባሉቻችን ላይ ነው። እነዚህ አባሉቻችን ግማሹ የጸና ገሚሱ የሚወላውል ነው። ስለዚህ ወደቡና አይቀሬው ቀን ሲመጣ ሊከዱን ይችላሉ። ስለዚህ አስፈላጊውን ስልጠና እንዲሁም የማፅናት ስራ ልንሰራ ይገባል።"

ትርሲት ጉልላት መንፈሳዊ እውቀቷ ይህን ያህል የሚያወላዳ አይደለም ምክንያቱም እንደ ብዙዎቹ ዘማሪዎች በሰንበት ትምህርት ቤት ወይም ደግሞ በመደበኛው መንፈሳዊ ኮሌጅ አላለፈችም። ስለዚህም መንፈሳዊ እውቀቷ የተሐድሶው ቡድን ባሰጠናት ልክና ስለ ክርስቶስ እንድትዘምር ከተሰጣት ግጥም በላይ የዘለለ አይደለም።

ከፍ ላለ መንፈሳዊ ውይይትም ሆነ ለንግግር የሚበቃ እውቀት የላትም። ይህንን እሷም ጠንቅቃ ታውቃለች። ከዚያ ይልቅ ስትዘምር በጣም የሚያምር ድምጽ ስላላት ይህን ድምጿን ተጠቅማ በአገሪቱ ላይ ተፅእኖ መፍጠር ትፈልጋለች። በግሏ በጣም የኪነጥበብ አድናቂ ነች። እንዴት አድርጋ ድምጿን እንደምትቀልጽ፣ እንዴት አድርጋ ሰዎችን በአግራሞት እጃቸውን በአፋቸው እንደምታስጭን ነው የምታስበው።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለዝማሬ የተለያዩ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች መጠቀምን እንድትፈቅድ ትፈልጋለች። በዚያውም እሷም ይህን ብቃቷን በመሳሪያ ታግዛ ማውጣትና ተፅእኖ የመፍጠር ትልቅ ሕልም አላት። ከዚያ ውጪ ኦርቶዶክስን በተለይ ደግሞ መንፈሳዊ ሰዎችን አምርራ ትንቃለችም ትጠላለችም። ቄስ፣ ዲያቆን፣ መሪጌታ፣ ቆሞስ፣ ጳጳስ... የሚባሉ ማዕረጎች የውሸት ማታለያ፣ የታይታ ነው የሚመስላት። ብዙዎቹን ታዝባቸዋለች። ስለዚህ ኦርቶዶክስ ይህ መዋቅራዊ አሰራሯ እንዲፈርስ ትፈልጋለች። የፈለገ ሁሉ ቄስ፣ ዲያቆን፣ መምህር... ቢሆን ደስ ይላታል። እሷም ወንጌልን በአውደ ምህረት ላይ ቆማ የማስተማር ጽኑ

ፍላጎት አላት፡፡ ለዚህ ነው ደቂቀ እስጢፋኖስን በሙሉ ኃይሏና ጉልበቷ የምትደግፈው፡፡

"ልክ ነሽ ትርሲት ወረዳ ዞን የኛ ነው ማለት ምን ዋጋ አለው፡፡" አለ ሲናገር ጣራና ግርግዳ የሚያንቃንቀው ባለ ነጎድጓድ ድምጹ የቦሌ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሰባኪተ ወንጌል ኃላፊ ሔራሞ፡፡ ሔራሞ አሜሪካን አገር ሄዶ ነገረ መለኮት አጥንቷል፡፡ የተሐድሶ ፍቅር እንዲያድርበትና የምስጢራዊ ቡድን አባል ያደረገው መርሐዊ ነው፡፡ አሁን በከተማው የታወቀ ሰባኪ ነው፡፡ ብዙዎች በጣም ነው የሚያደንቁት፡፡ አድናቂዎቹ ደግሞ ከኦርቶዶክስ ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ የእምነት ተከታዮችም ጭምር ነው፡፡ በተለይ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች በጣም ነው የሚወዱት፡፡ ይህ ደግሞ የሚፈልገውና የሚመኘው ነው፡፡

ችግሩ ሔራሞ አድናቆት አይጠግብም፡፡ ገና የተደነቀ አይመስለውም፡፡ ስለዚህ ብዙ ጊዜ በከተማው ውዥንብር እየለቀቀ ጋዜጣው፣ መጽሔቱና ማኅበራዊ ድረ ገጹ ስለ እሱ ብቻ እንዲያወሩ ያደርጋል፡፡ ይህኔ ልቡ የምታገኘው ሐሴት እሱ ብቻ ነው የሚያውቀው፡፡ ዋና አላማው ግን ኢትዮጵያዊው ማርቲን ሉተር መባል ነው፡፡ ታሪክ መጻፍ ይፈልጋል፡፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ሲነሳ ማርቲን ሉተር እንደሚነሳ ሁሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ጉዳይ ሲነሳ የእሱ ስም እንዲነሳ በብርቱ ይፈልጋል፡፡

"እውነቴን ነው! አለን የምንለው ነገር የኛና የኛ ብቻ ሲሆን ነው፡፡ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎችን አምነን ነው አለን የምንለው? እነዚህ ልጆች የተቀየሩት በትምህርት ነው፡፡ ማቅ ደግሞ ካውንተር አታኩን አቀላጥፎ አስተምሮ ሊመልሳቸው ይችላል፡፡" ድምጹ በክፍሉ ሲናኝ ያስታውቃል፡፡ ሲናገር ሁሉን የመቆጣጠር ችሎታው ያስደንቃል፡፡

ብዙ ወጣትና ጀማሪ ሰባኪዎች ድምጻቸውን እንደሔራሞ ለማድረግ፣ የእሱን የአነጋገር ዘዬ ለመከተል ገሚሱ የሌለውን ድምጽ ሲያጎረንን፣ ገሚሱ ድምጹን ጎተት ሲያደርግ ይታያል፡፡ ሔራሞ ይህን ሲሰማ የሚሰማውን ደስታ ማንም ሊተካለት አይችልም፡፡

"ሌላው ለእኛም ግልፅ ያልሆነ እንቅስቃሴ አለ፡፡ ይህኛው እንቅስቃሴ ከማቅም ለየት ይላል፡፡ ለሚደረገው ነገር ሁሉ በአፋጣኝና በተመጣጣኝ መልኩ ምላሽ የሚሰጥ ቡድን ነው፡፡ ለምናወጣው መዝሙር በመዝሙር ምላሽ ይሰጠናል፤ በመጽሐፍ ስናወጣ በመጽሐፍ፤ በስብከት ስንሞክር በስብከት ይመለስልናል፡፡ በእርግጥ መልስ የሚሰጡት ሰዎች እንደ ማቆች ዓለማዊ ትምህርት የቀሰሙና መንፈሳዊ ኮሌጆችም ገብተው የተማሩ ናቸው፡፡

"ይህ ሲሆን ደግሞ ትግላችንን ከባድ ያደርገዋል፡፡ የታወቀው ማቅ አሁን ብዙ ጠላቶች አሉበት፡፡ ከአገር ውስጥ እስከ ውጪ ካለው ሲኖዶስ ጥርስ ተነክሶበታል፤ ከመንግሥት ባለሥልጣናት እስከ ጣሊያን ቫቲካን ድረስ በጥላቻ ነው የሚታየው ስለዚህ ጠንክረን ብንታገለው ልንጥለው እንችላለን፡፡ ችግር የሆነው ደግሞ አዲሱ ሕቡዕ ቡድን ነው፡፡ የማቅ ሁለተኛ ድርጅት ሊሆን ይችላል፡፡ በግልጽ ካላወቅነው በግልጽ ማጥቃትም ሆነ ማጥፋት አንችልም፡፡" ሔራሞን ሁሉም በጥሞና እያዳመጡት ነው፡፡

## ምዕራፍ ፰

### አዲስ አበባ- ሳሪስ

ሮዳስና ሰንፔር እንደ ተለመደው ሁልጊዜ የሚጨቃጨቁበት ካፌ ቁጭ ብለዋል። እዚህ ቤት እንጨቃጨቅ ብለው ባይገቡም ነገር ግን እዚህ ቤት ገብተው ራሳቸውን የሚያገኙት ኬክ እየበሉ ሲነዛነዙ ነው። እንደ ምክንያት ሊሆን የሚችለው ካፌው ለሰንፔር ቤት ቅርብ መሆኑ ሊሆን ይችላል።

እዚህ ቤት መጥተው በኃይለ ቃል ቢደባደቡም፤ በነገር ቢወጋገም ተጣልተው ግን አይለያዩም፤ ተኮራርፈው አይሰነብቱም። ሮዳስ ሲግል ሰንፔር ተግ እያለች፤ ሰንፔር ስትግም ሮዳስ እየበረደ ነበር ፍቅራቸውን እዚህ ያደረሱት።

ሰንፔር 'ቴራሚሶ' ሮዳስ 'ኋይት ፎረስት' ኬክ አጋምሰው ከፊት ለፊታቸው ባለ የኬክ ማስቀመጫ ሰሃን ላይ በክሬም ከተጨማለቀ ሹካ ጋር ተቀምጧል። 'ቤሉስ' ካፌ ውስጥ ብዙዎች በቤቱ አስደማሚና እጅ አስቆርጥም ኬክ እየተዝናኑ ነው። ሰንፔርና ሮዳስ ግን ከባድ ጭቅጭቅ ውስጥ ናቸው። በልዩነት የተጀመረው ግንኙነታቸው ፍቅርን እንደ ጋቢ እያለባበሱ ሊሸፍኑት ቢሞክሩም የሆነ ቦታ ይገለጣል፤ አንድ ቦታ ተከፍቶ በልዩነት ውስጥ ይገኛሉ።

የሃይማኖት ልዩነታቸው ችግር እየፈጠረ መጣ። ሮዳስ ገብቶታል ልዩነታቸው ውስጥ እነሱ ብቻ ሳይሆኑ ቤተሰቦቻቸውም አሉበት። በተለይ ለሰንፔር ትልቅ ስቃይ ውስጥ ከቷታል። ሮዳስን በጣም ታፈቅረዋለች። ቢሆንም ለቤተሰቦቿም ፍቅርም ሆነ ክብር አላት። ገበር ምጣድ ላይ እንደተጣደ ዳቦ በሃይማኖት ጉዳይ በአንድ በኩል ከቤተሰቦቿ፤ በሌላ ደግሞ ከፍቅረኛዋ በነገር ፍም ትለበለባለች።

ሰንፔር አሁን የገጠማት ነገር ደግሞ በጣም ከባድ ነው። ከቤተሰቧ ትሁን ወይስ ከፍቅረኛዋ እጅግ አስጨናቂ ችግር ውስጥ ገብታለች። ሮዳስን ብትነግረው ሊያምናት አልቻለም።

"... ልታምነኝ ይገባል ያንን ቪዲዮ ያዘጋጀው አባቴ አይደለም ሆን ብለው ሰዎች ተጠቅመውበት ነው።" ሰንፔር ድምጽ አውጥታ እንደመተንፈስ አለችና ቀዩ ባለስቦንጅ መደገፊያ ወንበር ላይ ዘፍ ብላ ተደገፈች።

"እንደነገርኩህ አባቴ እንግሊዝ አገር ለስብሰባ ሄዶ ነበር። ስብሰባው ላይ አባቴ ከሰዎች ጋር አልተስማማም ነበር። በእሱ አለመስማማት የተበሳጩ ብዙ ሰዎች ነበሩ። ስለዚህ የእሱን ሌላ ስብከት በተንኮል እንዳቀናበሩበት ነግሮኛል።" ሮዳስ ይመናት አይመናት ግራ ገብቷታል ግን ሀቁን ነው የነገረችው።

"ስብሰባው በምን ላይ ያተኮረ ነበር?" አላት ሮዳስ ኮስተር እንዳለ። እንዲህ ያለ የግል ጉዳይ ውስጥ ገብቶ ያውም የፍቅረኛውን አባት የትገቡ የት ወጡ እያለ መፈትፈት አይወደውም ነበር። ፍቅረኛውንም እንኳ 'የት ወጣሽ፤ የት ነሽ፤ ከማን ጋር ነሽ' ማለት አይወድም ነበር።

"ሮዳስ እሱን እኔም አላውቅም፤ ብቻ ስብሰባ ለንደን ውስጥ እንዳለው ነግሮን ነበር። ከእንግሊዝ አገር እንደተመለሰ ግን ይህ ቪዲዮ ተለቀቀ" ሰንፔር እያለቀሰች ነው። እምባዋ ልክ ደረቷ ላይ እንዳሉት ቅስር ያሉት ጡቶቿ የዓይኗ ሽፋሽፍት ላይ እንደ መቆም ይሉና ፍሬ እንደበዛበት የወይን ዘለላ መንታ መንታ እየሆኑ እርግፍ እርግፍ ይላሉ።

"እሺ ምን እንዳደርግ ነው የምትፈልጊው ሰን?"

"አባቴ ከኦርቶዶክሶች መልስ እንደሚሰጠው አ…ው…ቃ…ል…" ሰንፔር እምባዋ እየተናነቃት መናገር አቃታት። ሰንፔር የእምባዋን መፍሰስ ለማስታገስ ንግግሯን ቆም አድርጋ ሁለቱን በሚያብረቀርቅ ፀጉር የተሸፈኑትን ሽፋሽፍቶቿን እንደ ስፖንጅ ጭምቅ ስታደርጋቸው እምባዋ በጉንጯ ላይ ኮለለ እያለ ወረደ። ሮዳስ ጨነቀው፤ እምባ አይወድም። ከሚወዳት ሴት ሲወርድ ደግሞ በጣም ይረብሻል።

"ሰን ተረጋጊ በናትሽ?... እስኪ ተረጋጊና እናውራ" ብሎ የገበታ ሶፍቱን ፊቷን እንድትጠርግ አቀበላትና ሰው እያያቸው እንደሆነ ዞር ዞር ብሎ ተመለከተ። ብዙዎች የራሳቸውን ጨዋታ እንጂ እነሱን ልብ አላሏቸውም።

ጥግ ላይ ነጭ ቲሸርት የለበሰ ፍርጥምጥም ያለ ልጅ ብቻ አፍጥጦ ያያቸዋል። 'ይህኔ አገባሻለሁ ብሎ ሲጫወትባት ቆይቶ ከዚያም አላገባም ብሏት ይሆን? ወይም አስረግዞ አላውቅልሽም ብሏት፤ ወይም በቃሽኝ ጠግቤሻለሁ ሂጂልኝ ብሎ ከድቷት፤ ካልሆነም ወጣት አማረኝ አንቺ አረጀሽብኝ ብሏት… ይሆናል እንጂ ይህቺን የመሰለች ቆንጆ በሌላ በምን ምክንያት ታለቅሳለች ብሎ ነው የሚያስበው። ወይኔ ይቺን የመሰለች ቆንጆ ተበላ። አልገባውም በእጁ የያዙት ወርቅ ሆኖበት ነው። ስትወጣ ተከትሎ በማባበል አሳቦ ልግባባት?' እያለ እያሰበ ይሆን? አለ ሮዳስ።

ሰንፔር እንደ መረጋጋት ብላ ማውራት ጀመረች። ከንፈሯ ቅልት ብሎ የበሰለ እንጆሪ መስሏል፤ ዐይኗ ላይ የተቀባችው ኩል በእምባዋ ምክንያት ተጠርጓል።

"ሮዳስ መልስ የሚሰጠውን ሰው ታውቀዋለህ። እሱን እኔም አውቀዋለሁ። ጓደኛህ ነው። አበጋዝ ነው። የጉባኤውን ማስታወቂያ በየመንገዱ አይቼዋለሁ። ስለዚህ በናትህ በተቻለህ አቅም እንዲረዝም ወይም መልስ እንዳይሰጡ አድርግ?"



CamScanner

ሮዳስ ዐይኑን በድንጋጤ ብልጥጥ አደረገ "ሰን የማይሆን ነገር ነው። ከአቅሜ በላይ የሆነ ነገር ነው የጠየቅሽኝ። በምን አቅሜ ነው የአንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ እንዳይደረግ የማከላክለው። እንዴት ይቻለኛል?"

"ትችላለህ! ትችላለህ! የእለቱ አስተማሪ ጓደኛህ ነው። ቢያንስ ጉባኤው ለአባቴ መልስ እንዳይሆን ማድረግ ትችላለህ። ሌላ መደበኛ ትምህርት እንዲሆን አድርግ እባክህ? አባቴ ሊያስተባብል ጥረት እያደረገ ነው። ስለዚህ አባቴ ካስተባበለ በኋላ እንደፈለጋችሁ።"

"ሰን አልገባሽም አባትሽ ተናገሩት ሌላ ሰው ተናገረው ዋናው ቁም ነገር የንግግሩ ጭብጥና መልዕክቱ ነው። ይህ ሀሳብ ደግሞ ለህዝቡ ደርሷል። ስለዚህም መልስ የሚሰጠው ለአባትሽ ሳይሆን ለተነገረው ሀሳብ ነው። ይህን አቁሙት ማለት ቤተ ክርስቲያ እየተተቸች ተቺው እውነት ነው ብሎ እንደ መቀበል ይሆናል። ሰው ይረበሻል። ያለውን ነገር ማወቅ ይፈልጋል። ስለዚህ ጉባኤው መልስ ሊሰጥበት ግድ ነው። ነገሩ ስለ አንቺና ስለኔ ፍቅር ወይም ስለ አባትሽ ክብር አይደለም ስለ ቤተ ክርስቲያን ፍቅር ስለ ቤተ ክርስቲያን ክብር ነው።" ሮዳስ ተነፈሰ። ይህን ቃል ለማውጣት የፍቅር ይሉኝታ አግዶት ነበር። አሁን ግን ቆርጦ ተናገረው። የሚበልጠውንና የሚያስበልጠውን ወሰነ።

"አንተም ሀሳብህ ይህ ነው? አንተ እንኳ አታምነኝም? አንተ እንኳ እንዴት አትረዳኝም?" ሰንፔር ከተቀመጠችበት ለመነሳት ቦርሳዋን ሸካከፈችና ቆም ብላ እንደ እሳት በሚገርፍ ቁጣ ሮዳስን ቁልቁል ተመለከተችው።

"ሰን ይህ የመረዳት ያለመረዳት ጉዳይ አይደለም። ይልቁንስ ከአቅም በላይ የሆነ ነገርና የአግባብነት ጥያቄ ነው።" አለ ሮዳስ ሰንፔርን ሽቅብ እየተመለከታት። ሮዳስ መንፈሱ ተጨነቀበት የፍቅረኛው እንባና ሀዘን ጭንቀት ውስጥ ከቶታል። ግን ምንም ሊያደርግ አይችልም። ብኩርናውን እንደ ኤሳው አይሸጥም። ልሸጥም ቢል በአሁኑ ሰዓት ገበያ ላይ የሚገዛው የለም፤ የሚጠይቀው ገዢም አያገኝ።

ሰንፔር ምንም ሳትናገር እጇን ከንፈሯ ላይ ያዝ አድርጋ እንደ መሮጥ ብላ ካለችበት ካፌ ወጣች። ሮዳስ ሊከተላት አሰበና ኃይለ ቃል እንዳይነጋገሩ ፈርቶ መልሶ ባለበት ተቀመጠ። ቅድም ሰንፔር እና ሮዳስ ሲጨቃጨቁ አፍጥጦ ሲመለከታቸው የነበረው ሰውዬ ሰንፔርን ለመከታተል ብሎ አስተናጋጇ ገንዘቡን እንድታመጣለት እጁን ንፋስ ላይ እንዳለ ባንዲራ አውለበለበው።

## ምዕራፍ ፳፩

## አዲስ አበባ-ቦሌ መድኃኔዓለም

የቦሌ ሰማይ ከጨረቃ፣ ከከዋክብት፣ ከመንገድ፣ ከሕንጻና መኪናዎች የሚወጡ ብርሃኖች ከምሽቱ ጋር ሕብር ፈጥረው የተለየ ደስ የሚል ድባብ ይዟል፡፡ የቦሌ መንገድ እንደ ዱሮዋ ፈጣን መኪኖች እርስ በእርስ ተገፋፍተውና ተሽዋውደው እየሄዱ አይደለም፡፡ መኪኖቹ ከነ ሾፌሮቻቸው ሰብሰብ ብለው ቦሌ መድኃኔዓለም የገቡ ይመስላሉ፡፡

የጉባኤው ቅስቀሳ የተሰራው በሁለት ቀን ውስጥ ነው፡፡ ባልታወቀ ምክንያት የኤድናሞል በእለቱ የሚታየው የፊልም መርሐግብር አልነበረም፡፡ የሚብለጨለጨው የስክሪን ማስታወቂያ ጠፍቶ ጸጥ ብሏል፡፡ በአካባቢው የሚሰማው የአበጋዝ ድምጽ ብቻ ነው፡፡

አበጋዝ ከላይ ሰማያዊ ሸሚዝና ነጣ ያለ ሹራብ ያደረገ ሲሆን ከስር ጨርቅ ሱሪና ማሰሪያ የሌለው ጫማ ተጫምቷል፡፡ ከበላዩም መስቀል ያለበት ነጭ ነጠላ መስቀለኛ አጣፍቶ ለብሷል፡፡ አበጋዝ ከቆመበት በስተጀርባ ባለ መቀመጫ ላይ የዛሬውን ጉባኤ በጸሎት የከፈቱት የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳዳሪ እንዲሁም ሌሎች መምህራንና ዘማርያን ተቀምጠዋል፡፡ አበጋዝ ቡኒ በጽድ እንጨት የተሰራ ሆኖ የሚያብረቀርቅ ቨርኒሽ የተቀባው አትሮንስ ላይ ያስቀመጠውን መጽሐፍ ቅዱስ ገለጠና የይሁዳ መልዕክት ላይ አደረገው፡፡ በቅድሚያ የመግቢያ ንግግሩን ካደረገ በኋላ ለማስተማር መጽሐፍ ቅዱሱን ከገለጠበት የወንጌል ቃል ላይ አተኩሮ ለማንበብ ተዘጋጀ፡፡

አበጋዝ ማይኩን በግራ እጁ ጨብጦ ይሁዳ ሦስት ላይ ያለውን ጥቅስ ማንበብ ጀመረ፡፡ "ወዳጆች ሆይ፤ ስለምንካፈለው ስለ መዳናችን ልጽፍላችሁ እጅግ ተግቼ ሳለሁ፤ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈፅሞ ስለተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኳችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ፡፡' አበጋዝ የወንጌሉን ቃል ካነበበ በኋላ ቀና ብሎ ሰዉን ተመለከተ፡፡

እጅግ በጣም ብዙ ሰው ከአውደ ምሕረት እስከ ውጪው የቤተ ክርስቲያኗ ደጃፍ ድረስ ሴቶች ነጭ ነጠላ እስከ ራስ ፀጉራቸው ተከናንበው በአንድ ወገን፤ ነጠላ የለበሱም ያልለበሱም ወንዶች በሌላ ወገን በአንክሮ ትምህርቱን እየተከታተሉ ነው፡፡ የቻሉና ቦታ ያገኙ ወንበር ላይ ተቀምጠው፤ በተለይ በእድሜ ከፍ ከፍ ያሉት ወንበር ላይ የተቀመጡ ሲሆን፤ ሌሎች ደግሞ ባገኙት ቦታ ተደግፈው ቆመዋል፤ የተቀሩትም መሬት ላይ ቁጭ ብለዋል፡፡ ብዙዎች ወጣቶች በፓስተር ናፍያድ የተላለፈውን ስብከት ከማኅበራዊ ድረገጽ ላይ ተመልክተዋል፡፡



CamScanner

"ዛሬ ይህን ጥቅስ ያመጣሁበት ምክንያት በአገራችን እንደ ሥልጣኔ ሁሉ፣ እንደ ፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም፣ እንደ ለበስነው ጥብቆ፣ በዘመናት ሒደት እንደሚያድግ ሳይንስ ወይም በሰፊ ጥናትና ምርምር እንደሚቀየር ዓለማዊ እውቀት ሃይማኖትን ለማደስ ለሚጥሩ ለሚታትሩ ወገኖች የተነገረ ጥቅስ ስለሆነ ነው።

"ይሁዳ ሦስት ላይ እንዳያችሁት ሃይማኖት ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈፅሞ.... እደግመዋለሁ ፈፅሞ ማለት ላይደገም ላይከለስ እንደገና ላይታይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ጥንቅቅ ተደርጋ ተሰጥታለች ማለት ነው። ከዚያ በኋላ ሃይማኖታችንን እንደ ተሰጠን፣ እንደ ተገለጠልን፣ እንደ ወረስነው ልክ እናምናለን እናመልካለን። በነገራችን ላይ አትሳቀቁ ሃይማኖት የሚወረስ እንጂ የሚፈጠር አይደለም። አንዳንድ ሰዎች ሃይማኖትን 'እንደ ጋሻ መሬት ወይም እንደ ፍሻሌ ሽጉጥ ወርሳችሁ' እያሉ ሊያላግጡ ይሞክራሉ። ተዋቸው ያላገጡት በእኛ ሳይሆን ባወረሰን ፈጣሪ ላይ ነው።

"የትኛውም እምነት ከአያት ከቅድመ አያት የሚወረስ ነው። የሚያወርስ እግዚአብሔር ነው ወራሽም የክርስቶስ የሆነ ነው። ያወረሰንም በስጋዌ ምስጢር ሰው ሆኖ የተገለጠው እሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ለዚህም ነው በዕብራውያን ምዕራፍ አንድ ቁጥር አንድ ላይ 'ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ሁሉንም ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዘመናትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን' ብሎ ሃይማኖት ለአዳም፣ ለኖኅ፣ ለአብርሃም፣ ለሙሴ፣ ለዳዊት፣ ለነቢያት የተሰጠ በመጨረሻም በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋዌ የተገለጠ ነው።

"ከኢየሱስ ወደ ሐዋርያት፣ ከሐዋርያት ወደ ሐዋርያውያን አበው፣ ከሐዋርያውያን አበው ወደ ቤተ ክርስቲያን ጠበቆች ከእነርሱም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት፣ ከሊቃውንት አባቶቻችን ወደ መምህራን እያለ ዛሬ እኛ ላይ ደርሷል። ይህ የሚያሳየን አንደኛ ሃይማኖት በፈጠራ የሚገኝ ግኝት አለመሆኑን ሁለተኛ ሃይማኖት ከአዳም እስከ አሁን አንድ መሆኑን እንጂ ብልየት ወይም እርጅና፣ መፍረስ ወይም ዘመን የሚሽረው ይመስል ሃይማኖት የሚታደስ አለመሆኑን ነው።

"ችግሩ ምን መሰላችሁ? ሰው ዘመኑን መዋጀት ሲያቅተው፣ ሰው ቀድሞ በተሰራለት መንገድ መንዝ ሲያቅተው ዘመኑን በራሱ ልክ መስፋት ይፈልጋል። በነ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ቅዱስ ዮሐንስ፣ ቅዱስ ጴጥሮስ፣ ቅዱስ ጳውሎስ... ጊዜ ክርስትና ዋጋ ያስከፍል ነበር። በመጋዝ መተርተር፣ በእሳት መቃጠል፣ በመስቀል መሰቀል፣ በሰይፍ መሰየፍ... ይጠይቅ ነበር። ስለዚህ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ከፍለው ዘመኑን የሰማዕታት አደረጉት።

"አሁን ደግሞ ለማመን ተለምኖ ነው፣ እግዚአብሔርን ለማምለክ እናንተና እኛ ተፈልገን በስንት ጉባኤ ተጠርተን ተደልለን ነው። ከኢንተርኔት፣ ከሞባይል ጉርጎራ፣

ካፌ፣ ለካፌ፣ ከመንሸራሸር መንገድ ላይ ከመጎተት ከምናጠፋው ትንሽ የጊዜ ዋጋ ከፍሎ መማርን፣ ማምለክን እንደቁም ነገር ቆጥሮ፤ ከእሱም ብሶ ኢየሱስ ደሙን አፍስሶ ስጋውን በጅራፍ አስተልትሎ የሰራትን ቤተ ክርስቲያን እንደገና ለዘመኑ እንዲመች አድርጋችሁ ስሩልን የምንል ትውልድ ሆንን።

"ብቃ ተሐድሶ ማለት ይህ ነው። ዘመኑን የመሰለ ሃይማኖት ለመስራት መፈለግ። በሰውነት ልክ እንደ ተሰፋ ጥብቆ ወይም ቦዲ ነው የምትሉት እንደሱ ሰውነት ላይ ልክክ የሚል ሃይማኖትን እንደ አዲስ ለመስፋት መጣጣር ነው። ምእመናን ተዋሕዶ እኮ የሞባይል አፕሊኬሽን አይደለም በየዘመኑ አፕዴት የምናደርገው" አበጋዝ ቦዲ ሲል ገሚሱ የቦሌ መድኃኔዓለም ምእመናን የሳቁ ሲሆን 'ተዋሕዶ የሞባይል አፕሊኬሽን አይደለም በየዘመኑ አፕዴት የምናደርገው' ሲል አንድ ላይ ሁሉም ሳቁ።

ሳቃቸው ጋብ ሲል አበጋዝ ንግግሩን ቀጠለ "ሁላችሁ የምታውቁት አንድ ትምህርት በማቴዎስ ወንጌል ላይ አለ። ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን 'የሰውን ልጅ ማን ይሉታል?' ብሎ ይጠይቃል። በማስከተልም ደቀ መዛሙርቱን 'እናንተስ እኔን ማን ትሉኛላችሁ?' ሲል ጠየቀ። ጴጥሮስ 'አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ' ብሎ መልሶለት ነበር። ይህኔ ኢየሱስ ክርስቶስም መልሶ እንዲህ አለው 'የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፤ በሰማያት ያለው አባቱ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ' ብሎታል። ብቃ ሃይማኖት ከእግዚአብሔር ተሰጠ፤ በእግዚአብሔር ተገለጠ እኛም ተቀበልን።

"ራሱ ኢየሱስ እንዳለው ሃይማኖት በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚገለጥ የሚሰጥ እንጂ ማንም በየዘመኑ እየተነሳ ነብረር እያደረገው የሚቃኘው አይደለም። በዘመናት ጥናትና ምርምር ወይም በሰዎች የሥልጣኔ ያስተሳሰብ ልቀት ልክም አይወሰንም። ለዚህም ነው አንደኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ ሁለት ከቁጥር ሁለት ጀምሮ 'እምነታችሁ በእግዚአብሔር ኃይል በመገለጥ ነበረ እንጂ በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም' ተብሎ የተጻፈልን።" አበጋዝ የዛሬውን ትምህርት እዚህ ላይ ማቋረጥ ፈለገ። ጉባኤው ለሁለት ቀን የተዘጋጀ ስለሆነ ነገ ቀኑ ቅዳሜ ስለሆነ የተሻለ ሰው ይመጣል ብሎ ስላሰበ የዛሬውን ትምህርት አቋረጠው።

"የዛሬውን ትምህርት እዚህ ላይ ገታ እናድርግና እግዚአብሔር ቢፈቅድ ነገ እንገናኛለን። ነገ ከመምጣታችሁ በፊት በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የተለቀቀውን ቪዲዮ መጀመሪያ እዩት ከዚያም ጥያቄዎች አዘጋጅታችሁ ኑ። በተጨማሪም ነገ ስትመጡ አንድ ከሆናችሁ ሁለት ሁኑ፤ ሁለት ከሆናችሁ አራት እየሆናችሁ እንድትመጡ። ነገ መዳን ምንድነው? መዳን በኦርቶዶክስ አስተምህሮ ምን ይመስላል? ቀድሞ ክርስትና ምን ይመስል ነበር? ለምን ይሄ ሁሉ አይነት ክርስትና ተፈጠረ? የሚሉ መንፈሳዊ ጉዳዮችን እናያለን።" አለ አበጋዝ ከፊት ለፊቱ የዘረጋውን መጽሐፍ ቅዱስ እያጠፈ።

## ምዕራፍ ፳፱

ሮዳስ እየነዳ አበጋዝ ከጎኑ ጋቢና ውስጥ ተቀምጧል፡፡ መኪናዋ ውስጥ ሸገር ኤፍ ኤም ሬዲዮ ተከፍቷል፡፡ አበጋዝ እና ሮዳስ ግን ተጣልቶ እንደተቀያየመ ሰው ዝም ተባብለዋል፡፡ ሮዳስ ፊቱ ላይ የበዛ ድካምና መሰላቸት ይታይበታል፡፡ በመኪናው ውስጥ የሸገር ኤፍ ኤም ሬዲዮ ተከፍቶ ጋዜጠኛው እያወራ ቢሆንም ሮዳስና አበጋዝ የራሳቸውን ጨዋታ ይዘዋል፡፡

"ሮዳስ ሰላም ነው? ትምህርቱ ላይ ቅር ያለህ ነገር አለ እንዴ?"

ሮዳስ ደንገጥ እንደ ማለት ብሎ "ኧረ አይደለም" አበጋዝ፣ እንቅልፍ በደንብ አልተኛሁም ነበር ለዚያ ነው"

"በእንቅልፍ አታሳብ ሐኪም መሆኔንም አትርሳ የተቀየምክበት ነገር አለ"

ሮዳስ ፈገግ አለና "እውነትህን ነው ከሰንፔር ጋር ተጣልተን ነው"

አበጋዝ ፈገግ አለና "ጠርጥሬያለሁ በዚህ ጉዳይ እንደምትጣሉ"

"እንዴት?" አለ

"ይህ ጉባኤ እንዲደረግ እንደማትፈልግ ግልጽ ነው፡፡ አንተ የኔ ጓደኛ ስለሆንክ ጉባኤው እንዳይደረግ ወይም አጀንዳው እንዲቀየር እንደምትፈልግ ግልጽ ነው፡፡ በነገራችን ላይ በአንተ የፍቅር ሕይወትህ ላይ ተጽእኖ ማሳደር ስለማልፈልግ ነው የማልነግርህ እንጂ እኔም እንዳንተ በሃይማኖት ከምለያየው ሰው ጋር ፍቅር ይዞኝ ያውቃል፡፡ ስለዚህ ህመሙን፣ ጭቅጭቁን፣ ስቃዩን... አይቼዋለሁ"

ሮዳስ ተደንቋል፤ መጀመሪያ የነበረው ድብርቱ ለቆት ስሜት ሕዋሱ ሞቅ ሲል ተሰማው፤ እግሩ ነዳጁን ሲጫነው መኪናው ጭር ባለው የቦሌ ጎዳና ላይ ከነፈች "ምን አንተ? በሃይማኖት ከማትገናኝህ ሴት ጋር ፍቅር ይዞህ ነበር?"

አበጋዝ እየሳቀ እንደ ተለመደው ሁሉ የራሱን ፀጉር ወደ ፊት ገፋ ገፋ እያደረገ "ትቶ እልክ ስትገርም፡፡ ለማንኛውም መኪናውን ቀስ አድርገህ ንዳ ቢያንስ ነገ ጉባኤ አለን፡፡"

"አንተ ትቀልዳለህ ለማንኛውም ታሪኩን? ወዲህ በል ይልቁንስ"

"ታሪኩ አሁን ሲወራ ቀላል ይመስላል እንጂ በጊዜው ከባድ ነበር፡፡ የሕክምና ትምህርት እንዳጠና የተመደብኩት ጎንደር ዩንቨርስቲ ነበር፡፡ የሕክምና ትምህርት

በጣም ጭንቀትና መከራ ስላለበት ሌላ ተጨማሪ የፍቅር ጭንቀት መጨመር ይከብዳል፡፡

"ስለዚህ ያለ ምንም ፍቅረኛና የፍቅር ታሪክ የሕክምና ትምህርቴን ከጎንደር ዩንቨርስቲ ጨረስኩና ለስራ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ተመደብኩ፡፡ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ስመደብ አዲስ አበባ እንደ ጎንደር ዩንቨርስቲ አልነበረችም፡፡ በጣም ግር አለችኝ፡፡ እኔ የዲላ ልጅ ነኝ፤ ቤተሰቦቼም ያሉት ዲላ ነው፡፡ ስለዚህ አዲስ አበባ በብቸኝነት መኖር ትንሽ ከባድ ሆኖብኝ ነበር፡፡"

መኪናው ውስጥ የተከፈተው የሸገር ኤፍ ኤም ሬዲዮ ለሚ ባያገኝም የሚካኤል በላይነህን የትዝታ ዘፈን እያጫወተ ነው

"ቅኔ ነው ትዝታ ዜማ ነው ትዝታ

ጥበብ ነው ትዝታ ሕይወት ነው ትዝታ

ዞረው የሚኖሩት የናፈቁት ለታ..."

"አዲስ አበባን እንድለምድ ያደረገችኝ የውስጥ ደዌ ዋርድ እንደኔ በአዲስነት የተመደበችው ናርዶስ ነበረች፡፡ ናርዶስ የአዲስ አበባ ልጅ ነበረች፡፡ መጀመሪያውኑም ነርሲንግ ትምህርቷን እዚያው ጥቁር አንበሳ ስለ ተማረች አዲስ አበባም ሆነ ጥቁር አንበሳ ብርቋ አይደለም፡፡

"ለእኔ ደግሞ በግልባጩ የአዲስ አበባ ኑሮ ከብዶኝ ነበር፡፡ ናርዶስ ግርታዬን አይታ ይሁን ወይም እኔ ባላወኩት ምክንያት መጀመሪያ የተከራየሁበት ቤት አልተስማማኝም ስል ሰምታ ሰፈሯ አካባቢ የሚከራይ ቤት አገኘችልኝና ተከራየሁ፡፡ ስለዚህ ከናርዶስ ጋር መውጣት መግባት አበዛሁ፡፡ እሷም አንዳንዴ ቤቴ እየመጣች ምግብ ማዘጋጀት ቤት በማስተካከል ትረዳኝ ጀመር፡፡"

ሮዳስ በአበጋዝ ንግግር መሀል ገባና "አበጋዝ መቼም እንዲህ እየተቀራረባችሁ ምንም አልጠረጠርኩም ነበር አትለኝም"

አበጋዝ ሳቀ አለና "አልልህም ግን እሷ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ስለነበረች እኔም ኦርቶዶክስ ስለሆንኩ ሁለታችንም ቅርበታችንን ወደ ፍቅር እንቀይረዋለን ብዬ አላሰብኩም፡፡ ያኔ እንዲህ አሁን እንደምታየኝ አይደለሁም በተለይ ምግብ ማብሰል፣ የቤት እቃ ማስተካከል ሰነፍ ስለነበርኩ እርዳታውም በጊዜው ያስፈልገኝ ስለነበር ነገሮቹን ሁሉ እንደ ንጹህ ጓደኝነት ማየት ምርጫዬ አደረኩት፡፡



CamScanner

"አንድ ቀን ማታ ላይ ናርዶስ እቤቴ አምሽታ ስለ ነበር ወደ ቤቷ ስትሄድ ሸኘኋትና ቻዎ ስንባባል ሳላስበው ከንፈሬን ሳመችኝ። ደነገጥኩ። ከዚያ ቀደም የእንስት ከንፈር ስሞኝ ስለማያውቅ ነገሮች ሁሉ ተደበላለቁብኝ። አይገርምም? ለስሙ ሐኪም ነኝ ቢሆንም እንደ አፍላ ጎረምሳ ነበር የተሽኮረመምኩት፣ ሳቅ ሳቅ አለኝ፣ ደስም አለኝ፣ ከፋኝም፣ ብርቅ ሆነብኝ... ምን ልበልህ ብቻ ግራ ተጋብቼ ነበር።" አበጋዝ ሲያወራ ያን ቀን ማታ ናርዶስ ተንጠራርታ ሊፒስቲክ ባወዛው ከንፈሯ ከንፈሩን ስትስመው እያስታወሰ። በድንጋጤ ከንፈሩን ሲያብሰው እጁ ላይ የቀረው ቀዩ ሊፒስቲክ ነበር። ናርዶስ ዞር ብላ ሳታየው ወደ ቤቷ ቀዩን ንፋስ የሚያውለበልበውን ስስ ሱሪ አድርጋ መጠነኛ ታኮ ያለው ጫማ ተጫምታ ሰበር ሰካ እያለች ስትራመድ በሐዘን ሕሊናው ሳለው።

"...ታሪክ እንደ ቀለም ዘመን እንደ ሸራ

ስለው ያስቀመጡት የሕይወት አሻራ

በእድሜ የሸመኑት በጊዜ በቦታ

አልፎ የሚያጌጡበት ጥበብ ነው ትዝታ..." እያለ ነው ሰሚ ያላገኘው የሸገር ኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያ።

"ከዛስ በናትህ? አጓጓኸኝኮ"

"ዛሬ ፓስዋርድህ ተገኘ በጣም ለወሬ ጓጉተሃል። ለማንኛውም ቢጫው መብራት በርቶልሃል መኪናህን ቀስቀስ አድርጋት። እንዲህ እያልን እንንገርህ እንጂ መቼም ዛሬ ሳታጋጨኝ አትቀርም..."

"እሺ አበጋዝ እንዴት ሆናችሁ በናትህ?" አለ አበጋዝ መኪናው አውቶማቲክ ስለሆነ ቀኝ እግሩን ነዳጁ ላይ ጫን እያደረገ

"ከዚያማ ፍቅር ጀመርን"

"በልዩነት?"

"አይ በልዩነት እንኳ አልነበረም። ናርዶስ መጀመሪያም ቢሆን ጥብቅ ፕሮቴስታንት አልነበረችም መሰለኝ ወይም በፍቅር እንድወድቅ ለመሳዋ ይሁን ብቻ አላውቅም ከኔ ጋር ፍቅር ለመጀመር እሷም ኦርቶዶክስ ልትሆን ተስማማች። ከዚያ አብራኝ ቤተ ክርስቲያን ሄዳ መሳለም፣ ጠዋት ሄዳ ማስቀደስ፣ መማር ጀመረች። ቢሆንም እኔ መደበኛውን የኦርቶዶክስ ትምህርት ተምራ እንድትጠመቅ ስጠይቃት እምቢ ባትለኝም እሺ እሺ እያለች ነገሩን አንተተችው። እኔም ይደርሳል ብዬ ተውኩት።

ሲሆነው ቀልጥ ወዲያ ፍቅር ነው ነገር። ስለሆነ ይመሰክራል የተደረገለት ልቦናቸውን ነዳይ ችላ ያለትም።

ጓደኛ ወር በፍቅር ከሆነን በኋላ ፍርዱ ልብ ተደርጎ መሆን እንድንማማር ነገሮች እንደሆነ እኔ እሷ የሆንኳቸውን ከልብ እንድንማማርበት ነገሮች። እኔም ሁሉን ተቀብዬ መልሳቸውን መርጫ ከሆነ ተሳካን።

ትምርህን ከዋን መደመሪያ ምን አለ ነው የሆንኳቸውን እየደረሰው ያለው? ርዕሰ ይህን ነገር ከተናገረ በኋላ መልሶ ራሱ ስለገፈር የሚያየን ቃል መልሶ ማግረሱ ወሰነን ነው። የራሱን ነገር ችላ ብሎ ወደ ሌላ ነገር ተመልሶ መሄዱን ለየ።

ጓደኛ የሆንበኛቸውን እንደተገናኘን ለማኘት ነገር። ሌላ ግን ወደ ፍቅሬ የሆነ ሰላም ልቤ እሰጥ። ስለዚህ ለጓደኛ የምቀርበው ንግግር ነው። ስለዚህ ሁሉም ፍቅር ደግሞ እያሰተረሳው የሆንኳቸውን እየደረሰው ብላ ሌላ ተገናኝ በተራና ሲሆን ይችላል። ወይም ያለተመቸኘት ሌላ ነገር ለኛ ይችላል። ወይም ለተቀበለው የሚሰጠው ሃሳብ እንደ ዘመን ከለሆነ ይሆናል። ስለዚህ ትንሽ ነው ነገሮችን ለመ ስለነገር ይሆን ደብረት ለሆን ይችላል። እኔ ዲያቆን ስለሆነው ድፍረትን ስለማድረስ ምንም እይታ ጽናቴ ዝግጅትን እንዲኖር ከእስራኤል። ደግሞ የሚያደርገው ስለመመልከትም ይሆናል... ልቡ ከእግዚአብሔር እይታ እኔደርሰውም። ሲሆነው ዛሬ እንዲህ እንደ ቀልድ መለየት ብለን የምገልፀው ቃል ያለ ግንም አይደለም ትልቅ የልብ ቁስል ነበረው። ልቡን እግዚአን ማየት አለፈልገውም። ታውቃለህ ፊደ ያሉ ፍቅርን ሳየው መሆኑት ግንም ያሰደረናል።

በመከራው ወቅት የተከፈተው ፊደ ላይ የሚገመውተው የኒትሽት እንደው ግጥም የሆነው የተዘዘታ ዘፈን እሁንም አለበት

"...ትናንትናችንን በፍሬ አስታውሼ

በዘመን ቁልቁለት የጊዜት ፊደሌ

ከፈለቅኩበት ጋራ ስር ደርሼ

ሕይወትን ከምንጯ ጠጥቼ ተመልሼ..." እያለ ተከረቸፈው የሚዘለል ሙዚቃው ድምጽ ይሰማል።

"እኔ ከዚህ ነው ምን እይታ ልጅ ነች ቀንደ ነች? ልብ ርዕሰ ወሬው እንዲደረሰሩበት የራሱን የፍቅር ታሪክ እንዲያስታውሰው ሰማቸው።

"አይ እንደ አንተ ሰንፔር ቆንጆ አይደለችም። ናርዶስ ጠይምና ጎራዳ ሆና የደስ ደስ ያላት ነች። ከሁሉም በላይ ደስ የሚለኝ ነገር ሕይወትን ቀለል የምታደርገው ነገር ነው። እኔ ደግሞ እንዳንተ ቆንጆ አድናቂ አይደለሁም።"

ሮዳስ እየሳቀ "ለምን? ለምን በናትህ?" አለ

"እኔንጃ ቆንጆ ሴቶች ለትዳር የሚሆኑ አይመስለኝም። ቆንጆዎች እቡይ ይመስሉኛል። አጥፍተው ይቅርታ ከመጠየቅ ይልቅ መልሰው ይቆጡሀል። በራስ መተማመን ሳይሆን ውበት ላይ የተመረኮዘ ትምክህት ያጠቃቸዋል። ከአንተ ጋር ችግር ቢኖርባቸው በሥነ ሥርአት ነገሮችን ከመፍታት ይልቅ እነሱ የሚያሸነፉበትን መንገድ ይመርጣሉ ወይም ፈላጊ ብዙ ነን ብለው ስለሚያምኑ መለያየት ዋና ምርጫቸው ነው። ጮክ ብለህ ለማናገር እንኳ አስፈቅጄ መኖር ደግሞ ትንሽ ይጨንቀኛል። በአጠቃላይ ቁንጅናቸውን የረሱ ቆንጆዎች ስለማላውቅም ቁንጅናን ለትዳር አልመርጥም።"

"አበጋዝ እንዲህ አጠቃለህ ስትፈርጅ አይቼህ አላውቅም"

"ኖኖኖ...አጠቃልዬ እየፈረጅኩ ሳይሆን ግን እንደ ሕይወት አጋር ምርጫዬ ያን ያህል ቆንጆ ሴት አስፈላጊ ነች ብዬ አላስብም። ምክንያቴ ይህ ነው ለማለት ነው። ከውበት ይልቅ ለኔ ሕይወት ሰጥታህ ኑሮህን ቆንጆ የምታደርግ ሴት ትበልጥብኛለች።"

"እኔ እምልህ ናርዶስ አሁን የት ነው ያለችው?"

"አሜሪካ ነች አግብታ የሁለት ልጆች እናት ሆናለች። አንዳንዴ በፌስቡክ አወራታለሁ።"

"ግን ለምንድነው ታሪክህን ልትነግረኝ ያልፈለከው?"

"ምክንያቱም በውሳኔህ ላይ የኔ የፍቅር ታሪክ ተጽእኖውን ሊያጠላብህ ይችላል ብዬ ስላሰብኩ ነው። ወይ ልትለያይ ትችላለህ፣ ወይ ደግሞ በልዩነት መኖርን ልትመርጥ ካልሆነ እንዳችሁ እንዳችሁን ለመጠቅለል ልታስቡ ትችላላችሁ። ግን የአንዳንድ ሰዎችን ታሪክ ስትሰማ ውሳኔህ ላይ ሚዛናዊ መሆን ሊሳንህ ይችላል። ለዚያ ነው ታሪኬን ያልነገርኩህ።"



CamScanner

## ምዕራፍ ፳፫

## አዲስ አበባ- ቦሌ መድኃኔዓለም

ኤድና ሞል ማተ፣ መልቲፐሌክስ ዛሬ ስራውን ሞቅ አድርጎ ከፍቷል፡፡ ከመግቢያው በር አናት ላይ በተሰቀለው የቴሌቪዥን ስክሪን የሚወጡት ብርሃኖች ለአካባቢው ደስ የሚል ድባብ ሰጥተውታል፡፡ መኪናዎች ከየአቅጣጫው ይተማሉ፡፡ በአብዛኛው ዘናጭ ታዳጊ ወጣቶች ከኤድናሞል ሲወጡና ሲገቡ ይታያሉ፡፡

የአቢጋዝ ድምጽ በዚያ ሁሉ ሰው መሀል ልቆ በአካባቢው ላይ የነገሰ ይመስላል "ዛሬ እግዚአብሔር እንደፈቀደ የምናነሳቸው ሀሳቦች ብዙ ስለሆነ ሃይማኖት እንደማይታደስ ትናንት ስላየን ወደዚያ አንመለስም፡፡ የዛሬው የእምነታችንን ዋነኛ ማጠንጠኛ ላይ የሆነውን የመዳንን ትምህርት እናነሳለን፡፡

"ከዚያ በፊት ግን አንዳንድ ሃይማኖቶች በተለይም እኛ እንታደስ ዘንድ ሌት ተቀን የሚለፉት አካላት መዳንን እንዴት ያዩታል መነሻ ምክንያታቸውስ ምንድነው? ብለን ሳናበዛ በጥቂቱ እንይ፡፡ እንደምታውቁት ክርስትና ከአንደኛው እስከ አምስተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በአንድነት ያለመከፋፈል ይጓዝ ነበር፡፡ ያለመከፋፈል አንድ ጌታ፣ በአንዲት ጥምቀት በአንዲት ሃይማኖት ጥላ ስር ተጠልለውና ጸንተው በአራት ዋና ዋና መናብርት ስር የነበረው የክርስቲያኖች መንበር እነዚህ ነበሩ፡፡ እነሱም በቅዱስ ጴጥሮስ ወንበር የሮማው ሊቀ ጳጳስ፣ በቅዱስ ማርቆስ ወንበር የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ፣ በድጋሚ በቅዱስ ጴጥሮስ ወንበር የአንጾኪያው ሊቀ ጳጳስና በቅዱስ ዮሐንስ ወንበር የኤፌሶን ሊቀ ጳጳስ ነበሩ፡፡ በኋላ የኤፌሶን መንበር ለቁስጥንጥንያ ሲባል ወደ ቁስጥንጥንያ ተዛወረ፡፡

"እነዚህ ዋና ዋና መናብርት የቤተ ክርስቲያን አንድነት ለማስጠበቅ ሲሉ በየዘመናቱ የተነሱትን መናፍቃንን ለማውገዝና አንዲት ቤተ ክርቲያንና ሐዋርያዊውን አስተምሕሮ ለማስጠበቅ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ጉባኤ አካሂደዋል፡፡ የመጀመሪያውን ኑፋቄ ያስተማረው አርዮስ ነው፡፡ አርዮስ 'ወልድ ፍጡር ነው' የሚለውን ትምህርቱን ለሰሙት ሁሉ ያስተምር ነበር፡፡ ስለዚህም በ325 ዓ.ም. ኒቂያ በተባለች ቦታ ጉባኤ ተጠርቶ አርዮስን ትምህርቱ ስህተት መሆኑን ነግረው ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ እኩል መሆኑንና ሌሎች አእማደ ምስጢራትን ጨምረው ሰባት አንቀጸ ሃይማኖት ሰሩ፡፡"

ቦሌ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ከትናንትናው በላይ በሰው ተሞልቷል፡፡ አቢጋዝ እንደጠበቀውና እንደፈለገው ሰዎቹ በዝተው መጥተዋል፡፡ ግቢው ሙሉ ለሙሉ በረዶ የጣለበት ይመስል ነጭ ነጠላ የደረቡ ብዙ ሰዎች ይታያሉ፡፡

"በ381 ዓ.ም ኑፋቄው ከቁስ አርዮስ ከፍ ብሎ በጳጳሳት ደረጃ መጥቶ የቁስጥንጥንያው ጳጳስ መቅዶንዮስ 'መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ያንሳል' አለ፡፡

ሌላኛው ደግሞ የላኦዶቅያ ኤጲስ ቆጶስ አቡሊናርዮስ 'በምስጢረ ሥጋዌ ቃለ እግዚአብሔር ሰው በሆነ ጊዜ ሥጋን እንጂ ነፍስን አልተዋሐደም' አለ። ስለዚህም በ381 ዓ.ም የቁስጥንጥንያውን ጉባኤ መጥራት ግድ ሆነ። በቁስጥንጥያም የተገኙት ሊቃውንት መቅዶንዮስንና አቡሊናርዮስን አውግዘው በኒቂያው አንቀጸ ሃይማኖት ላይ አምስት አንቀጽ ጨምረው አስራ ሁለት አደረሱት።

"ጠላት መቼም ስለማይተኛ እንደገና ግርግርና ችግር በማምጣት በቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሱ ንስጥሮስ ሌላ የኑፋቄ ትምህርት አስነሳ። እሱም 'ወልድ ከድንግል ማርያም ከመወለዱ በፊት የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ ከአብ ጋር እኩል ነው። ነገር ግን ከማርያም ከተወለደ በኋላ ሁለት ነው። አንዱ የማርያም ልጅ ሲሆን ሌላኛው የእግዚአብሔር ልጅ ነው። አምላክ ከሰው መወለድ ስለማይችል ማርያም የክርስቶስ እናት ናት እንጂ የአምላክ እናት አይደለችም' አለ።

"ይሁን እንጂ በ431 ዓ.ም. የተጠራው የኤፌሶን ጉባኤ 'ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ነች' ብሎ ጉባኤውን አጸናና ንስጥሮስንም አወገዘ።" አበጋዝ ይህን ሲናገር በተለየ ሁኔታ በሌ መድኃኒዓለም ትምህርቱን እየተከታተሉ የነበሩት ምእመናን በእልልታና በጭብጨባ ደስታቸውን ገለጹ። ምክንያቱ ደግሞ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች በተለየ ሁኔታ የማርያም ፍቅር አላቸው። ስለዚህም የሚወዷትን ማርያምን የፈጣሪያቸው እናት አይደለችም ስትባል እንዴት አይበሳጩ? እንዲህ ያለውም ሰው ሲወገዝ እንዴት ደስ አይላቸው?

አበጋዝ ጭብጨባና እልልታው ሲቆም ማስተማሩን ቀጠለ "ከዚያ ቀጥሎ የመጣው የኬልኬዶን ጉባኤ ሲሆን ክርስትናን ወደ መከፋፈል የከተተውም ይህ ጉባኤ ነበር። ይህም የቁስጥንጥያው መነኩሴና የገዳም አበምኔት የነበረው አውጣኬ 'እግዚአብሔር ከድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ አምላክነቱ ሰውነቱን ዋጠው' የሚለው ጉዳይ ነበር ጉባኤ ያስጠራው።

"እንግዲህ ክፍፍሉ የመጣው ይሄኔ ነበር። በእርግጥ የጥሉ መነሻ በአውጣኬ አስተምህሮ ስህተት ነው አይደለም በሚል ሳይሆን ጉባኤውን ማን ይምራው በሚል የስልጣን ሽኩቻ ተቀየረ። ነገሩ እንዲህ ነው። ያለፉትን ሶስት ጉባኤዎች ሲሰበስቡ የነበሩት የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ነበሩ። ነገር ግን በኬልቄዶኑ ጉባኤ የሮማው ሊቀ ጳጳስ ልዮን የሰብሳቢነቱን ሚና መውሰድ ስለፈለገ የእስክንድርያውን ፓትርያርክ ቅዱስ ዲዮስቆሮስን ከጉባኤው እንዲወጣ የልዮን ተላላኪዎች ገና ስብሰባው ሊጀመር ሲል እንደ ቅድመ ሁኔታ ጠየቁ፤ ያም ብቻ ሳይሆን በኤፌሶን ጉባኤ የተወገዘውን 'ሁለት ባህሪ፤ ሁለት አካል' የሚለውን ትምህርት በኬልኬዶን ጉባኤ ላይ 'አንድ አካል ሁለት ባሕርይ' በሚል አዲስ ካባ አልብሶ የንስጥሮስን ክህደት ልዮን አዲስ ካባ አልብሶ አቀረበው።

"በዚህ ጊዜ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ዲዮስቆሮስ የሮማውን ጳጳስ ልዮንን አወገዘው። በልዮን ሐሳብ አልስማማ ያሉት ከግብጽ፣ ከሶርያና ከአርመን የመጡ ሊቀ ጳጳሳት ቢቃወሙም በጉልበት ዝም አሰኙዋቸው። በጊዜው በሥልጣን ላይ የነበሩት ንግሥት በርክልያና ንጉሥ መርቅያን ደግሞ የእስክንድርያውን ጳጳስ ዲዮስቆሮስን ጨምሮ ሌሎችንም በልዮን ሀሳብ አልስማማ ያሉትን ቢለምኑም ቢያስፈራሩም እሺ አልል ስላሉ የዲዮስቆሮስን ጺሙን ነጭተው ጥርሱን አውልቀው በግዞት አሰሩት።" ጥቂት የማይባሉ ሰዎች በተለይ እንስቶች ትምህርቱን በጥሞና የተከታተሉና ማስታወሻ ቶሎ ቶሎ እየያዙ ነው።

"ከዚህ በኋላ ነው ቤተ ክርስቲያን የተከፋፈለችው። የሮሙ ፓፓ ልዮን እና የቁስጥንጥንያው ሊቃነ ጳጳስ ፍላብያኖስ በአንድ ላይ ሆነው እስክንድርያን አገለሉ ከዚያም በላይ 'አንድ አካል ሁለት ባሕርይ' የሚለውን የኑፋቄ ትምህርት አጸኑ።" በሌ መድኃኔዓለም ቅጥር ቤተ ክርስቲያን ዙሪያው አልፎ አልፎ ጣል ባሉ የፌደራል ፖሊሶች ተከቧል።

"እንግዲህ ከላይ እንዳየነው የሃይማኖት ልዩነቱ የመጣው ከዚህ በኋላ ነበር። ለዚህም ነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንደ ግብጽ፣ ሕንድ፣ ሶርያና አርመን ካሉ ኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት ሶስቱን ጉባኤና አስተምህሮዎች ብቻ ነው የምትቀበለው። መልካም ትንሽም ቢሆን ክርስትናው እንዴት ችግር እንደገጠመው ከተረዳን፤ አሁን ደግሞ እንዲህ አይነት የእምነት ህጸጾች ለምን ተነሱ የሚለውን እናያለን። እነዚህ ልዩነቶች የተፈጠሩት ከትምህርት ቤት ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክርስትናን ከመሰረተ በኋላ ሐዋርያት ሦስት አመት ከሦስት ወር ከኢየሱስ ክርስቶስ የተማሩትን ትምህርት ዳግም ለሌሎች ለማስተማር በ60 ዓ.ም. በቅዱስ ማርቆስ አማካኝነት በግብጽ እስክንድርያ ትምህርት ቤት ተመሰረተ። ቀጠለናም በሦስተኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ሉቅያኖስ በተባለ ሰው ሁለተኛው መንፈሳዊ ትምህርት ቤት በአንጾኪያ ተመሰረተ። በአንጾኪያም ሆነ በእስክንድርያ ትምህርት ቤት የአሪስቶትል እና የፕሌቶ ፍልስፍናዎች ቢያጠቃቸውም ሁለቱ ትምህርት ቤቶች መሰረታዊ የአስተምህሮ መንገድ ልዩነት ነበራቸው።

"አንጾኪያዎች ትምህርታቸውን የሚሰጡት ከክርስቶስ የልጅነት ዘመን ወይም ደግሞ ከማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ ወንጌል በሚገልጹበት መንገድ የኢየሱስ ክርስቶስን የሰው ልጅ የመሆንና በዚህ ዓለም የኖረውን ሕይወት በጣም በማጉላት ላይ ትኩረት ያደርጋል። ይህ አካሔድ የአሪስቶትል የፍልስፍና አካሄድ ሲሆን በኋላም ኢምፕሪሲስዝም የተባለው 'እውቀት እንዴት ይገኛል' በሚለው ፍልስፍናዊ ክርክር ውስጥ አንዱ እይታዊ የሆነ መንገድ ነው። ይህ ከትንሹ ወደ ትልቁ አጠቃሎ መሔድ ወይም ኢንዳክቲቭ ሜተድ ይባላል። አንጾኪያዎች ታሪክ እያጣቀሱ የኢየሱስ ክርስቶስን ሰውነት እያጎሉ ወደ አምላክነቱ መሄድ ይፈልጋሉ።



CamScanner

"እስክንድርያዎች ደግሞ ከአንጾኪያዎች በተቃራኒ የክርስቶስን ጉዳይ ከዮሐንስ ወንጌል 'በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ' እያሉ ከኢየሱስ የሰው ልጅ የዘር ሐረግ ይልቅ ሰማያዊውን ምስጢር እያመሰጠሩ አምላክነቱን ያጎሉና ከዚያ ወደ ሰውነቱ ይሄዳሉ። ከእነዚህ ከሁለቱ ትምህርት ቤቶችና አስተምህሮዎቻቸው ድንቅ ድንቅ አባቶች የተገኙ ሲሆን በዚያው ልክም ኑፋቄን የሚዘሩ የስህተት አስተማሪዎች ወጥተዋል። ነገር ግን ከአንጾኪያ የወጡት የስህተት መምህራን ቁጥራቸው ይበዛ ነበር።

"ከላይ እንዳየነው ከአንጾኪያ የወጡት አርዮስ፣ ንስጥሮስ፣ ዲዮድሮስ፣ ቴዎደሬጥ ሲገኙ ከእስክንድርያ ግን አንዱ አቡሊናርዮስ ብቻ የክህደት ትምህርት አመጣ። የአቡሊናርዮስም አስተምህሮ በእስክንድርያዎችም ተወግዞ የተለየ ነው። በአንጾኪያ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ የሁለት ልጆች ጥምረት ማለትም የእግዚአብሔር ልጅና የማርያም ልጅ በማለት ይገልጻሉ። 'የእግዚአብሔር ልጅ ቃልና የድንግል ማርያም ልጅ ኢየሱስ ጥምረታቸው እንደው ለታይታ ውጫዊ ነው እንጂ ውስጣዊ አይደለም። ድንግል ማርያም የወለደችው ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስን ሲሆን የእግዚአብሔር ቃል ኢየሱስ ክርስቶስን አደረበት ይላሉ።'

"ይህን የስህተት ትምህርት በጳውሎስ ሳምሳጢ የተጀመረ ሲሆን የእነርሱ ተማሪ የነበረው ሉቅያን ባቋቋመው የአንጾኪያ ትምህርት ቤት ሥር እየሰደደ ነበር። በኋላም የዚህ ትምህርት ቤት ውጤት የነበረው ንስጥሮስ የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ሲሆን ትምህርቱን ለአደባባይ አውጥቶ ፀሐይ እንዲሞቀው አደረገው። ነገር ግን በኤፌሶን ጉባኤ ንስጥሮስና አስተምህሮው ተወገዙ። ይሁን እንጂ የሮማው ጳጳስ ልዮን 'ሁለት አካል ሁለት ባህሪ' የሚለውን ትምህርት 'አንድ አካል ሁለት ባህሪ' ብሎ በማሽሞንሞን ዳግም አመጣው።

"ታዲያ እኛ ኦርቶዶክሶች ስለ ክርስቶስ የምናምነው እንዴት ነው? ክርስቶስ ከተዋሕዶ በፊት ከሁለት ባሕርይ፤ ከተዋሕዶ በኋላ ያለ መለያየት፣ ያለ መከፋፈል፣ ያለ መጠፋፋትና ያለ መቀላቀል በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ማለት ነው። በተጨማሪም ኬልቄዶናውያን የሆኑ ካቶሊኮችና መሰሎቻቸው የራሳቸውን ንስጥሮስ ዘመም ስህተት ለመደበቅ ሲሉ እኛን ባልሆነው ስም 'አውጣኪያዊ' እያሉ የማይመለከተንን ታርጋ በመለጠፍ የራሳቸውን ጉድ ለመደበቅ የእኛን ስም ለማጥፋት ብዙ ደክመዋል። ሆኖም እኛ ተዋሕዶ ሚያ-ፊዚት እንላለን እንጂ ነጠላ ሞኖ-ፊዚት አንድ አንልም። ከሁለት ባሕርይ በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ የሆነ ሥግው ቃል፣ ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው!" በቦሌ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን የታደሙት ምእመናን ጭብጨባና እልልታውን አንድ ላይ አስተጋቡት።



CamScanner

## ምዕራፍ ፳፬

## እንግሊዝ-ለንደን

የአንድ መቶ ዘጠኝ አመት ልምድና ብቃት ያለውን የስለላ ድርጅት በቮክስ ድልድይ ላይ ሆነው ሲያዩት ምርጥ ሥነ ምሕንድስና የታየበት ውብ ሕንጻ ይታያል፡፡ በተለምዶ ኤም አይሲክስ (MI SECTION 6) ከሚባለው በምህጻረ ቃል ኤስ አይ ኤስ (SIS) ወይም ሲክሬት ኢንተለጀንት ሰርቪስ የሚል መጠሪያ ካለው ዋና የእንግሊዙ የስለላ ቢሮው እየወጣ ነው፡፡ ቶኒ፡፡ ኤስ አይ ኤስን የተቀላቀለው ከአምስት ዓመት በፊት ነበር፡፡

ዐይኑ ላይ ቁንጠኛ ጥቁር የፀሐይ መነጽር ሰክቷል፡፡ ከታች ቀለል ያለ ካኪ ሱሪ ያደረገ ሲሆን ከላይ ደግሞ በራልፍ ሎውረንስ ኮርፖሬሽን የሚመረተውን ፖሎ ቲሸርት አድርጓል፡፡ ከቢሮው ደረጃ እየወረደ ኢትዮጵያ ላለው የገዳይ ወኪሉ ለዘላለም በስልኩ መልዕክት እየላከ ወደ ቻንግር መኪናው ሄደ፡፡

ቶኒ አባቱ የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ቄስ ሲሆን እናቱ ደግሞ የሁለተኛ ደረጃ መምህርት ነበረች፡፡ የቶኒ አባት የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እንደ መሆናቸው መጠን ልጃቸውም መንፈሳዊ ሕይወቱ ጠንካራ እንዲሆን ያልጣሩት ነገር አልነበረም፡፡ ከዚህ ፍላጎታቸው የተነሳ ቢያንስ በቀን አንድ ከብሉይ ኪዳን አንድ ደግሞ ከሐዲስ ኪዳን ምዕራፍ ሳያነቡና ሳይወያዩ አያድሩም ነበር፡፡

እንዲህ በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ተኮትኩቶ ያደገው ቶኒ አሜሪካ ካምብሬጅ የሚገኘው የሀርቫርድ እህት ዩንቨርስቲ ከሆነው በስተን የሥነ መለኮት ኮሌጅ ገባ፡፡ የሥነ መለኮት ትምህርቱን እያጠና ባለበት ጊዜ ነበር ቬሮኒካን የተዋወቀው፡፡

ፈረንሳዊቷ ቬሮኒካ የሐርቫርድ ዩንቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪ ስትሆን፤ ከቶኒ ጋር የተገናኙት ባቡር ውስጥ ነው፡፡ ባቡሩ ውስጥ 'ፖለቲካል ሪሊጅን' የተባለውን የሉዊጅ ስቱርዞን መጽሐፍ በአርምሞ ስታነብ አያት፡፡ ለምን እንደሆነ ባያውቀውም ሲያያት ገና ውስጡን ደስታና መደናገጥ ጀመረው፡፡ እግሩ እርብትብት አለበት፡፡

ቶኒ ከፊት ለፊቱ ያለችውን እንስት አይቶ ድንብርብር ሲል ቬሮኒካ ቀና ብላ አየችውና ከጎኗ እንዲቀመጥ ጠጋ አለችለት፡፡ ቶኒ እንደ መንከርፈፍ ብሎ አጠገቧ ተቀመጠ፡፡ ቬሮኒካ ቀለል ያለች ሰው ነች፡፡ ለመግባባት የማትከብድ እንደውም ማንንም ሰው በግድ የምትግባባ አይነት፡፡

ስለራሳቸው በትንሹ ከተዋወቁ በኋላ ሁለቱም ሐርቫርድ መማራቸውን ሲሳወቁ ቀለል ባለ መንገድ እሱ ሥነ መለኮት ስለሚያጠና ከሚያጠናው ሥነ መለኮት ትምህርት ጋር ፖለቲካ ምን ያህል ቁርኝነት እንዳለው ትተነትንለት ጀመር፡፡

ስለ ሃይማኖትና ስለ ፖለቲካ፣ ሃይማኖት ውስጥ ስላለው የሃይማኖተኞቹ እርስ በእርስ የመጠላለፍና የመጠላላት ፖለቲካ፣ አንዱ ሃይማኖት ለሌላው ሃይማኖት ያለው ምቀኝነትና ቅናት፣ መንግሥታት እንዴት ሃማኖቶችን ወደ ራሳቸው የፖለቲካ አስተሳሰብ እንደሚጠመዝዙ፣ ሃይማኖትን የጋራና የአገር ስለማድረግ ወይም አንድን የፖለቲካ አስተሳሰብ እንዴት የሕዝብ ሃይማኖት ማድረግ እንደሚቻል፣ የውሸት ሃይማኖት በማኅበረሰብ ውስጥ እንዴት ማስረጽ እንደሚቻል ስትደሰኩርለት አፉን አስከፈተችው፡፡

ቶኒ ሥነ መለኮትን እንዲህና በዚህ መንገድ አስቦት አያውቅም፡፡ በእርግጥ ዩንቨርስቲ ከመግባቱ በፊት ያለው መንፈሳዊ አረዳድና አሁን ዩንቨርስቲ ሲማር ያለው መንፈሳዊ አረዳድ አንድ አይደለም፡፡ በዚህ መደናገሩ ላይ የቬሮኒካ ፖለቲካዊ ቅኝት ሲታከልበት ቶኒ ነገሮች ይብስ ተወሳሰቡበት፡፡

ቬሮኒካና ቶኒ በዚህ መንገድ ነበር የተዋወቁት፡፡ ቬሮኒካ በቶኒ ቁመናና የስፖርተኛ ተክለ ሰውነት ብትማረክም አለቅጥ በተጠናወተው መንፈሳዊነቱ ደስተኛ አልነበረችም፡፡ በመንፈሳዊ ነገር እያሳበበ ብዙም የፍቅር ደስታ አይሰጣትም፡፡ ከንፈር ለከንፈር ለመሳሳም እንኳ ራሱንም እሷንም አሳቀቀ ነበር፡፡ ይህ ነገሩን ልትቀርፍለት ብትፍልግም ቶኒ ግን እሺ የሚል አይነት ሰው አልነበረም፡፡ ስለዚህም ልትተወው ወሰነች፡፡

ስትተወው ግን እንዲሁ በቀላሉ እንዲረሳት አልፈለገችም ነበር፡፡ ከዚያ ይልቅ የገዛ የልብ ጓደኛውን ፍቅረኛዋ አደረገችው፡፡ ለዚያውም ሁሌ በየቀኑ በአክብሮትና በፍቅር ስለእሱ እውርቶ እውርቶ ከማይጠግበውና ከቶኒ ጋር በውጤትም ከሚፎካከረው ጓደኛው ጋር ፍቅር ጀመረች፡፡

የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ቄስ ይሆናል ያለው በምግባርም ሆነ በሥነ መለኮት እውቀቱ አንደኛ ያለው ጓደኛው፣ የገዛ ፍቅረኛውን ቀማውና አረፈው፡፡ ቶኒ ታመመ፡፡ ቬሮኒካን መልሶ ሊያናግራትና ሊያግባባት ሞከረ፡፡ ቬሮኒካ ግን "ፖለቲከኛ ብዙ ጊዜ አስቦ አንዴ ነው የሚወስነው፣ በፖለቲካ በብርቱ ታስቦበት አንዴ የተወሰነን ውሳኔ እንደገና መከለስ ከፍተኛ አደጋና ውድቀት ያመጣል" ብላ አሾፈችበት፡፡

ከዚያ በኋላ ቶኒ ሕይወትን የሚያይበት መንገድ ተለወጠ፡፡ ቬሮኒካን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ካጣት በኋላ እንደ ቶኒ ዱርዬ እንደ ቶኒ አሿፊ ነገር ግን በትምህርቱ በጣም ጎበዝ ሰው ጠፋ፡፡ የድሮ ወግ አጥባቂ ጓደኞቹን ተወ፡፡ ይልቁንም ዘና ፈታ ያሉት ጥቁር አሜሪካውያን ሆኑ የቶኒ ጓደኞች፡፡ በእረፍት ቀኑ የሚቀረው መዝናኛ



CamScanner

ክለብ የለም። በዚያ ላይ የሀርቫርድ ዩንቨርስቲ እንስቶችን በአህጉር ያዳርስ ጀመር። ከአፍሪካ፣ ከእስያ፣ ከአውሮፓ፣ ከአሜሪካ... የየአህጉራቱ ተወካዮች ሲያልቁበት ወደ አገራት ሁሉ ገብቶ ነበር።

ለምን እንደሆነ ቀድሞ ከነበረው ሕይወት ይልቅ አዲሱን ሕይወቱን ወደደው። ምቾትም ሰጠው። በዚህ ህይወት ውስጥ እያለ የመጀመሪያ ዲግሪ የሥነ መለኮት ትምህርቱን በጥሩ ውጤት አጠናቀቀ። የማስተርስ ዲግሪውን ፖለቲካል ሪሊጆን (poleitical religion) የሚል ትምህርት መከታተል ጀመረ። የሃይማኖትና የፖለቲካ ግንኙነትን የሚያጠና ትምህርት ነው።

ከሁሉ በላይ የሚመስጠው 'ሰብስቲትዩት ሪሊጅን' (substitute religion) እና 'ሪሊጂየስ ማንፑሌሽን ባይ ማን' (religious manipulation by man) የተባሉትን ኮርሶች በፍቅር የጨረሰው ትምህርት ነበር። በነዚህ ትምህርቶችም ውጤቱ ኤ ፕላስ (A+) ነበር።

## ምዕራፍ ፳፫

## አዲስ አበባ-ቦሌ መድኃኔዓለም

ቦሌ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለኮሰው ጧፍ ከአውደ ምሕረቱ ላይ ሆኖ ላየው ዐይንን ፍዝዞ አድርጎ የሚያስቀር ደስ የሚል ድባብ አለው። አበጋዝ በዚህ የጧፍ ብርሃን የሚደመምበት ሰዓት አይደለም ስብከቱን ቀጥሏል።

"አሁን ደግሞ የመዳን ትምህርታችን ላይ ስለተነሱት የተሐድሶዋውያን ጥያቄ እግዚአብሔር እንደ ፈቃድ መልስ እንሰጣለን። መነሻችንን 'ድኅነት በእምነት ብቻ' የሚለውን ቃል ማጠንጠኛ አድርገን እኛ ኦርቶዶክሳውያን ድኅነት ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ እንይ።

"በኦርቶዶክስ አስተምህሮ መዳን በክርስቶስ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የአብና የመንፈስ ቅዱስም ሥራ ነው። እኛ አንድን ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነው በአብ ፈቃድ፤ በራሱ ፈቃድ፤ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ በአንዲት ቅድስት ሥላሴ ፈቃድ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስን የማዳን ስራ መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ዕርገት በኋላ ይከናወናል። ሌላው መዳን ክርስቶስ በዕለተ አርብ የፈጸመው የመስቀል ስራ ብቻ አይደለም። ከዚያም ሰፋ ያለና ከኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ እስከ እርገቱ ያለው ነገርና የፈጸመው ድርጊት የመዳናችንም አካል ነው እንጂ እለተ አርብ ላይ የተፈፀመው ስቅለት ብቻ አይደለም።

"ድኅነት ስንል የኃጢያት ደመወዝ ከሆነው ከሞትና ከቅጣት መዳን ወይም ከኩነኔ ማምለጥ ብቻ ነው ብለን ለሰው ልጅ ከተሰጡ ጸጋዎች ሁሉ አንዱን ብቻ አንጠልጥለን አናጮህም። ለእኛ መዳን የኢየሱስ ክርስቶስ ስለእኛ ብሎ የሃጢያታችንን እዳ መክፈል ብቻ አይደለም።

"እኛ መዳን ስንል በዋናነት አራት መሰረታዊ ነገሮችን የያዘ ነው። እነሱም አንደኛ ኃጢአት ካመጣብን ፍዳ ሁሉ መዳን፣ ሁለተኛ ፈጣሪያችንን እንድናውቅ መሆን፣ ሶስተኛ ሐዲስ ተፈጥሮ ማግኘት እና አራተኛው እግዚአብሔርን መምሰል ናቸው። እኛ ድኅነት የምንለው እነዚህ ሁሉ ሲሟሉ ነው። ሆኖም የመዳን ጸጋ በዚህ ብቻ የተገደበ ሳይሆን ከዚህም በላይ ሰፊና ጥልቅ ነው።" በትምህርቱ ላይ የታደሙት ምእመናን አብዛኞቹ ደስ ያላቸው ይመስላል። ንቅትቅት ብለው ነው ትምህርቱን የሚከታተሉት።

"የድኅነታችን ጥግ እግዚአብሔርን ከማወቅና ከማመን ተነስቶ እግዚአብሔርን በመምሰል፤ ከአርአያ እግዚአብሔር ወደ አምሳለ እግዚአብሔር የሚደረግ እድገትን የሚይዝ ሰፊና ጥልቅ ነገር ነው። ሱታፌ አምላካዊ ስንል የጸጋ አምላክነትን ገንዘብ የማድረግ ሒደት በግሪኩ ቲዮሲስ (Theosis) ይባላል:: ይህን መቀደሳችንን እኛ የጸጋ



CamScanner

አማልክት ወደ መሆን የምናደርገውን ጉዟችንን የሚመራንና የሚቀድሰን መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

"ይህንንም ስንል ከራሳችን አፍልቀን ወይንም ደግሞ ተረት ተረት ሳይሆን ክርስትና የመገለጥ ሃይማኖት እንደ መሆኑ መጠን በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጦልን እና በቤተ ክርስቲያን የተቀደሰው ተገልጦልን ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ሲል አስተማረን 'ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋ ሰጠን' ሲል በሁለተኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ አንድ ጀምሮ ጽፎልናል፡፡

"ኢየሱስ ክርስቶስም በዮሐንስ ወንጌል ላይ 'እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ስራ እርሱ ራሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል' ብሏል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም 'የዚያንም የመሬታዊውን መልክ እንደ ለበስን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን' ሲል አንደኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ አስራ አምስት ቁጥር ዘጠኝ ላይ ገልጾልናል፡፡" ሮዳስ ከአውደ ምሕረቱ የፊትለፊት ወንበር ላይ አንድ እጁን ክርኑ ላይ አስደግፎና በመዳፉ ደግሞ አገጩን ደግፎ ቁጭ ብሎ የአበጋዝን ትምህርት እያዳመጠ ነው፡፡ የአበጋዝ አተናተንና ረጋ ያለ አስተምህሮ ፍዝዝ አድርጎታል፡፡

"ምሥራቃውያንን ከምዕራባውያን የሚለየን ሌላም አስተምህሮ አለ፡፡ ይህም ምዕራባውያን አውግስጢኖስ የተባለው የካቶሊክ አባት እንደሚለው 'አርአያ እግዚአብሔር አዳም በበደለ ጊዜ ጨርሶ ጠፍቷል' ሲሉ ምሥራቃውያን የኦርቶዶክሶች አባቶች ደግሞ 'አዳም ሲበድል የተሰጠው የእግዚአብሔር መልክ ደከመ፤ ባሕርዩም ጎሰቆለ እንጂ ጨርሶ አልጠፋም' ነው የሚሉት፡፡ ስለዚህም ምዕራባውያን 'ጥንተ አብሶ' ወይም 'Origina sin' ሲሉ ምሥራቃውያን ደግሞ 'የባህርይ መጎስቆል' ወይም 'Fallen nature' ይሉታል፡፡

"የአውግስጢኖስ ትምህርት በአጭሩ 'የሰው ልጅ ሁሉ በጥንተ አብሶ የተበከለ ስለሆነ ማንም ለዘላለማዊ ሕይወት የበቃ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህም ሁሉም ሰው ከኃጢያተኛነቱ የተነሳ ቅጣት ይገባዋል፡፡ ሆኖም እግዚአብሔር በማይመረመር ባህሪው የተወሰኑትን መርጧቸዋል፡፡ ስለዚህ ዘላለም ሕይወት የሚያገኙት እነዚህ አስቀድሞ በእግዚአብሔር የተመረጡ ብቻ ናቸው' የሚል ነበር አስተምህሮው፡፡

"ከአውግስጢኖስ የአስተምህሮ ጫፍ ደግሞ አየርላንዳዊው ፔላግዮን የተባለው የሮማ መነኩሴ 'የሰው ልጅ መልካም ስራ ለመስራት ያለው ነጻነት ለመዳን በቂ ነው፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው ራሱን ማዳን ይችላል፡፡' ብሎ ያስተምር ነበር፡፡ አውግስጢኖስ ከፔላግዮን በተቃራኒ 'ሰው ለመዳን በሰራው በደል የተነሳ ብቁ አይደለም' ይል ነበር፡፡ ይህ የአውግስጢኖስ አስተምህሮ በማርቲን ሉተር አእምሮ ውስጥ ትልቅ ቦታ አገኘና



CamScanner

በታች እንጠበቅ ነበር' ብሏል። ይህም 'ሕግ' የሚለው ቃል ሕገ ኦሪትን ሲሆን 'እምነት' የሚለው ደግሞ ወንጌልን መሆኑ ነው።

"ስለዚህም በኦርቶዶክስ ሕግ ወይም የእግዚአብሔር ትእዛዝ የፍቅሩ መገለጫ፣ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ ጫና ወይም ሸክም አይደለም። ለዚህም ነው ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ምዕራፍ አስራ አራት ቁጥር ሃያ አንድ ላይ 'ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፣ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል፣ እኔም እወደዋለሁ፣ ራሴንም እገልጥለታለሁ' ብሎ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕጉን ትእዛዙን አጽንቷል ሊያጸናም ነበር የመጣው እንጂ ሊሽርም አልነበረም።

"ከክርስቶስ በላይ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደማይበልጥ ግልጽ ነው። ቢሆንም እንኳ ስለመልካም ስራ ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ ሁለት ቁጥር አስራ ሦስት ላይ 'በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉም' ብሏል። ታዲያ ቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዴ 'መዳን በእምነት ብቻ ስራ አያስፈልግም' እያለ ሌላ ላይ ደግሞ 'ያለ ሕግ ስራ አይጸደቅም' ይላል? ታዲያ እኛ ምን እያልን ይሆን? ወይስ የእኛ አረዳድ ስህተት ነው? ወይስ ጳውሎስ ተሳስቷል? ወይስ መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በእርሱ ይጋጫል? ይህን መልስ 'መዳን በእምነት ብቻ' የሚሉን ቢመልሱት?"

ከአውደ ምህረቱ ፊት ለፊት ካለ የሴቶች መቀመጫ አካባቢ አንዲት እንስት ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ ቆመች። ሙሉ ለሙሉ ነጭ ልብስ የለበሰች ሲሆን በነጠላዋ ጸጉሯን የሸፈነች ነች። በቆመችበት ቀና ብላ መፈክር እንደሚል ሰው ቀኝ እጇን ጨብጥ አድርጋ 'ኢየሱስ ጌታ ነው!' አለች። 'አሜን' የሚል በዛ ያለ የወንዶች ድምጽ ከወንዶች መቀመጫ አካባቢ ተሰማ። አንድ የወንድ ድምጽ በድጋሚ 'ኢየሱስ ያድናል!' አለ። ሌላ የደቦ ድምጽ 'አሜን!' አለ። በቦሌ መድኃኔዓለም የታደሙት ምእመናን ግማሹ ግራ ገብቶት አንገቱን ወደ ሰዎቹ ጠምዝዞ ያይ ጀመር፣ ገሚሱም ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ሰዎቹ እየሄደ ነው፣ የተቀረውም ሞባይሉን አውጥቶ ትዕይንቱን በስልኩ ይቀርጻል።

አበጋዝ ግራ ገባው። እሱን ሲከታተሉ የነበሩት ምእመናን ፊታቸውንም ቀልባቸውንም ወደ ሰዎቹ ሲዞር። ልብሰ ተክሕኖ የለበሱት ዲያቆናት ከሩጫ ባልተናነሰ እርምጃ በሰዎች መሀል እየዘለሉ ወደ ሰዎቹ ሔዱ። 'ኢየሱስ ጌታ ነው!' የምትለው አንዲት እንስት ስትኖር ሌሎች ስድስት ወንዶች 'አሜን!' እያሉ ከግቢው ሊወጡ ሲሉ ሰዎች ግር ብለው ያዟቸው። የደንብ ልብስ የለበሱ የፌደራል ፖሊሶች በፍጥነት ወደ ቅጥር ግቢው መግባት ጀመሩ።

## ምዕራፍ ፳፮

## ኢትዮጵያ-አዲስ አበባ

ዘላለም ፓስተር ናፍያድን እንዳይገድለው ከሦስት ቀን በፊት ትእዛዝ ከቶኒ ሲላክለት ተናድዶ ነበር። አሁን ድጋሚ እንዲገድለው መልዕክት ተልኳል። አላማው ግልጽ አድርጎ እንዲህ ሲል ነግሮታል። "ኦርቶዶክሶች ለፓስተር ናፍያድ ትምህርት መልስ ሰጥተዋል። በዚህ መልስ ምክንያት ከተማው ውስጥ ብቻ ሳይሆን በመላ አገሪቱ የፓስተር ናፍያድና የአበጋዝ ምልልስ የሰዉ መነጋገሪያ ሆኗል።

"ስለዚህ በዚህ ሰዓት ፓስተር ናፍያድ ቢሞት ገዳዮቹ የተናደዱ ኦርቶዶክሶች እንደሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ሌላ ነገር ይኖር ይሆን ብሎ የሚያስብ ብዙም ሰው አይኖርም። በዚህ አጋጣሚ አክራሪውን ማኅበረ ቅዱሳንና በቅጡ የማይታወቀውን አዲሱን ሕቡዕ ቡድን ለማስመታት ምቹ መደላድል ይፈጥርልናል።" ዘላለም የቶኒን እሳቤ አደነቀለት። "አይ ፈረንጅ!" አለ። ጭንቅላቱን በቀኝ ጠቋሚ ጣቱ ነካ ነካ እያደረገ።

ዘላለም መንፈሳዊ ሰው በጣም ይጠላል። ጥላቻውን ደብቆ ይዞ ሥነ መለኮት አጥንቷል። ለጥላቻውም ሆነ ሥነ መለኮት ለማጥናቱ ዋና ምክንያት ነበረው። ዘላለም ተወልዶ ያደገው ጎንደር ወልቃይት ከሚባል ቦታ ነው።

የኢሕአዴግ መንግሥት ሥልጣን እንደያዘ ከኢሕአዴግ በፊት በነበሩ ሥርአቶች ውስጥ የበጌ ምድር ይዞታ የነበረውን ወልቃይት የተባለውን ቦታ ከትግራይ ክልል ጋር አንድ ላይ አካለለው። በዚህ ምክንያት "እኛ ትግሬ አይደለንም፤ እኛን ወደ ትግራይ ያካለላችሁን ለመሬታችንና ለሱዳን መውጫ ስለምትፈልጉን ነው እያሉ" ጥያቄ የሚያነሱትንና የሚቃወሙትን ብዙ የወልቃይት ሰዎች ከባባድ ቅጣትና ስቃይ እንደሚደርስባቸው የዘላለም እናት እና አባቱ ማታ ማታ ሲያወሩ ይሰማ ነበር።

የዘላለም አባትና እናት የወልቃይት ቀደምት ኗሪ ቢሆኑም መጀመሪያ አካባቢ ምንም አደጋ አልደረሰባቸውም ነበር። በቀየው በጣም የታወቁ ሰፊ የሰሊጥና የኑግ እርሻ ነበራቸው። ብዙው የወልቃይት የእርሻ መሬት አዲስ ለተካለሉበት የትግራይ ክልል ባለሥልጣናትና ወዳጆቻቸው ሲሰጥ የአቶ ቢሆነኝን ግን ለጊዜውም ቢሆን መሬት የቀማቸው አልነበረም። ነገር ግን አንድ ባለሥልጣን የዘላለምን አባት መሬት ፈለገው። ስለዚህም መሬቱን ሽጡልኝ ብሎ ይጠይቃቸዋል።

አቶ ቢሆነኝ በቁጣ፣ በንዴትና በቁጭት ሆነው እንደማይሸጡለት ይነግሩታል። ሰውየው "በጸባይ እምቢ ካሉማ በጉልበት" ይልና ብረት አንስቶ ማታ ላይ ሲገላቸው ቤታቸው ሄዶ ተኩስ ይጀምራል። አቶ ቢሆነኝም አጸፋውን እየተታኮሱ ሲገላቸው የመጣውን ሰው ያባርሩታል።



CamScanner

በነጋታውም አቶ ቢሆነኝ ሰውየውን ሊገሉት ይፈልጉት ጀመር፡፡ ይሁን እንጂ ሰውየው በሌላ መንገድ ቄስ ይዞ ለሽምግልና ይቀመጣል፡፡ ቄሱም አቶ ቢሆነኝንና ሰውየውንም ገስጸው አስታርቀዋቸው ይሄዳሉ፡፡ ማታ ላይ ግን ሌላ ታሪክ ተቀየረ፡፡ ሰውየው እንዲሁም ሌሎች ሰዎች ሆነው በአቶ ቢሆነኝ ቤት ላይ እሳት ለቀው ጥይት ይተኩሱ ጀመር፡፡

የዘላለም አባት በንዴትና በወኔ ተሞልተው ጠመንጃቸውን ወደ ፊት ወድረው ከቤት ይወጡና ግቢያቸው ውስጥ መታኮስ ይጀምራሉ፡፡ በተኩሱ መሀል ግን በጥይት ተመተው ይወድቃሉ፡፡ ባለጋራቸው አቶ ቢሆነኝ መውደቃቸውን ሲያይ ወደ እሳቸው ይቀርብና ትከሻው ላይ ያንጠለጠለውን ክላሽ ገፋ አድርጎ ትንሿን ሽጉጡን ከታጠቀበት ወገቡ ያወጣል፡፡ የዘላለም እናት ከሰውየው እግር ስር ተደፍታ እንባዋን ገዳቢ እንደሌለው ውሃ እያፈሰሰች ባሏን እንዲምርላት ብትለምንም ሰውየው ግን በአቶ ቢሆነኝ ጭንቅላት ላይ ሁለቴ አከታትሎ ተኩሰና እግሩ ስር ወድቃ የምትለምነውን ሴት በእግሩ ገፈተራት፡፡ የዘላለም እናት በጀርባዋ ተንጋላ ወደቀች፡፡ የለበሰችው ቀሚስ ወደ ላይ ተሰብስቦ ሰውነቷ ተራቆተ፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ዘላለም ሲቃና እንባ እየተናነቀው ተደብቆ ያያል፡፡

ከዚያም አቶ ቢሆነኝን የገደለው ሰውዬ የዘላለም እናትን ከወገብ በታች እርቃኗን ሆና እንደተንጋለለች ተራምዷት ወደ ቤት ውስጥ ሌላ ሰው ፍለጋ ዐይኑን እያቅበዘበዘ ይገባል፡፡ የዘላለም እናት በተኛችበት በሲቃ እያለቀሰች ነው፡፡ ሌላ ሰው ተከትሎ ወደ ቤታቸው ገባ፡፡ ዘላለም ደንግጦ የሚያየው ነገር ማመን አቅቶት ጭፍን ክፍት አደረገው፡፡ እሱ ነው፡፡ ጠዋት ሽምግልና ብሎ የመጣው ነጭ ጠምጣሚው ቄስ ነበር፡፡ ቄሱ በጠመጠመው ነጭ ሻሽ ፋንታ ኮፍያ አድርጓል፡፡

ዘላለም ትኩር ብሎ ሲያየው መንፈሳዊ ቁመናውን ቀይሮ የገዳይ ወታደር ባህሪን ተላበሰበት፡፡ የዘላለም እናት ላይ ሽጉጡን ይደግንና እያስፈራራ በእጁ የዝም በይ ምልክት ያሳያት ጀመር፡፡ የዘላለም እናት እንባ በዐይኖቿ እየዘራች ከሽጉጡ ትሽሻለች፡፡ ቢሆንም የጠዋቱ ቄስ የአሁኑ ባለ ሽጉጥ የዘላለም እናትን ከወደቀችበት አንስቶ ከንፈሯን ሳመው፡፡

መሬቱን እፈልገዋለሁ ያለው ሰው ቤቱን ፈትሾ ሌላ ሰው አለመኖሩን ካረጋገጠ በኋላ ወጣ፡፡ የጠዋቱ ቄስ የአሁኑ ባለ ሽጉጥ የዘላለምን እናት አስገድዶ መድፈር ይጀመራል፡፡ እየተወራጨችና እየጮኸች ብትታገለውም ከመደፈር ልታመልጥ ግን አልቻለችም፡፡ ሰውየው ከደፈራት በኋላ ሽጉጡን አንስቶ በሁለት ጥይት ይገድላታል፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው በአምስት ደቂቃ ውስጥ ነበር፡፡ ዘላለም በድንጋጤ በድን ሆኖ ከተደበቀበት አጮልቆ ያይ ነበር፡፡



CamScanner

አባቱን አስገድሎ እናቱን የደፈረው ቄስ በአሁኑ ሰዓት የፓትርያርኩ ልዩ ጽሕፈት ቤት ውስጥ ሥልጣን ተሰጥቶት ያገለግላል። የአባቱን መሬት የወረሰው ሰው ደግሞ ትልቅ ባለስልጣንና ሀብታም ሆኗል። ስለዚህም እነዚህን ሁሉቱን ሰዎች መበቀል የሚቻልበትን መንገድ ሲቀይስ እድሜ ዘመኑን ፈጅቷል። በአጠቃላይ ለኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ያለው ጥላቻ መቼም የሚሻር አይመስልም። ዘላለም ቢሆንኝ።

ለዚህ ነው ኦርቶዶክስን በዘላቂነት ለማጥፋት የሚሰራው። በዘላለም አመለካከት "ቤተ ክርስቲያኗ ለነገሰው ሁሉ አንጋሽና አወዳሽ፤ ለባለጊዜ ሁሉ አፈንዳጅ አጎንባሽ፤ አቋም የለሽ፤ ላሸነፈና ለበለጠ ሁሉ ተገዢ ብላ የምትሰብክ የመንግሥት ጠብ-መንጃ ነች እንጂ ለሰው ልጅ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚደረግ ጉዞ መንገድ አይደለችም። እንደውም በተቃራኒው የምድራዊ መንግሥታት እድሜ ማራዘሚያ ነች" ብሎ ያምናል።

---------//--------

## አዲስ አበባ-ቦሌ

አበጋዝ በጣም ስለደከመው እዚያው ቦሌ መድኃኔዓለም አካባቢ ባለ ሬስቱራንት ጎራ ብለው ራት እየበሉ ነው። ሮዳስ በአበጋዝ ትምህርት በጣም ደስተኛ ነው። ግን ቪዲዮው ላይ ከተነሱት ሃሳቦች ውስጥ ያልተመለሱ እንዳለ ተሰምቶታል። ስለዚህ የጎረሰውን የአፉን ምግብ አላምጦ ከዋጠ በኋላ ቀና ብሎ ጥያቄውን ሰነዘረ።

"እኔ እምልህ አበጋዝ ዛሬ ያስተማርከን ትምህርት በጣም ወድጄዋለሁ። ለሰዉ ጥሩ ግንዛቤ እንደሚሰጥ ምንም ጥርጥር የለኝም። ግን ደግሞ ቪዲዮው ላይ ከተነሱት ጥያቄዎች ውስጥ ያልመለስከው አለ። መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ እሱም ስልሳ ስድስቱን መጽሐፍ ብቻ የሚለውን።"

አበጋዝ ውኃውን እየጠጣ ሮዳስን ትኩር ብሎ እያየው "እሱን ነገር ሰፋ አድርጌለላ ቀን ልመለስበት ፈልጌ ነው ዝም ያልኩት። ምን መሰለህ ልዩነታችን የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥሩ ሰማንያ አንድ ወይም ስልሳ ስድስት መሆኑ ላይ አይደለም። ይልቁንስ ችግሩ ምንድነው ትርጉም ላይ፤ የማናችን ሐዋርያዊ ነው አይደለም የሚለው ነው።"

ሮዳስ በአግራሞት እያየው "እንዴት ማለት አልገባኝም?" ብሎ ጠየቀ

"ይኸውልህ ከማርቲን ሉተር ሶላዎች መካከል አንዱ 'ሶላ ስክሪፕቱራ' ነው። ግን ደግሞ ይኸው ዶግማ የሚጣሰው በራሳቸው በፕሮቴስታንት የእምነት አስተማሪዎች ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ይሉህና መጽሐፍ ቅዱስን ለማብራራት፤ የመንፈስ ቅዱስን መገለጥ ለማስረዳት፤ የእምነቱን ቀኖና ዶግማ ለማስተንተን ተብሎ ሌሎች መጽሔቶች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ መጽሐፍትና ጋዜጦች ይሰጡሀል።

'እንዲህ ከሆነ 'መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ' የሚለው ዶግማ ተሻረ ማለት ነው። እኛ ደግሞ አባቶቻችን የጻፉት የትርጉምና የማብራሪ መጽሐፍት ስናመጣ ተረት ተረት! ገድል ወይስ ገደል... እያሉ ሊያሸማቅቁን ይሞክራሉ። ሲመስለኝ የእኛ ትንሽ ቆየት ያለና ብሉና ስለሆነ ተረት ተረት! የእነሱ ደግሞ በማተሚያ ቤት ስለታተመ ቅዱስ የሆነ ይመስላቸው ይሆን? እላለሁ እንጻዴ" አለ አበጋዝ እየሳቀ። ሮዳስም በሳቅ አጀበው።

'ሌላው ሰማንያ አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ ኦርቶዶክሶች የጨመሩት ልብ ወለድ ነው የሚሉ አሉ። ተመልከት የማርቲን ሉተር እንቅስቃሴ እስኪመጣ ድረ ከእንቅስቃሴው በኋላ ቢታተመው የኪንግ ጀምስ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን መጽሐፍ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የግል ንብረት ያደርጉታል።

'እሺ እሱም ይሁን ችግሩ ምንድነው? ለምንድነው የማትቀበሉት? ስትል 'እነዚህ ተጨማሪ የሚባሉት መጽሐፍት ከስልሳ ስድስቱ መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይጋጫል ትባላለህ። ለምሳሌ ቪዲዮው ላይ እንዳየኸው ሲራክን የማይቀበሉት ሲራክ ምዕራፍ አምስት ቁጥር አንድ ላይ ያለውን 'ገንዘብ ቢቃኝ አትበል' የሚለውን ቃል አምጥተው ከአንደኛ ጢሞቴዎስ ከምዕራፍ ስድስት ቁጥር አስር ላይ ካለው 'ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ስር ነው' ከሚለው ጋር ይጋጫል ይሉሀል። ስለሚጋጭም ሲራክ ይቅርብን ይሉሀል።

የሚገርመው ግን የእንዛዚው አረዳድ ይጋጭ ይሆናል እንጂ መጽሐፍ ቅዱሱ እርስ በእርሱ በፍጹም አይጋጭም።" አለ አበጋዝ ሶፍት ከተቀመጠበት ላይ አንስቶ እጁን እየጠረገ። ሮዳስ ደግሞ የአበጋዝን ሃሳብ ላለማቋረጥ በጥሞና እያዳመጠ ነው።

'በመጋጨት የተነሳ መጽሐፍትን እቀበላለሁ ወይም አልቀበልም የምትል ከሆነ ስልሳ ስድስቱ መጽሐፍት ውስጥም በእኛ አረዳድ ብዙ የሚጋጭ የሚመስል ነገር አለ። ለምሳሌ የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አምስት ቁጥር ሰላሳ አንድ ላይ 'እኔ ስለራሴ ብመሰክር ምስክሬ እውነት አይደለም' ይላል። እዚያው ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ስምንት ቁጥር አስራ አራት ላይ 'እኔ ስለ ራሴ ምንም እንኳ ብመሰክር ከወዴት እንደመጣሁ ወዴትም እንድሄድ አውቃለሁና ምስክርነቱ እውነት ነው' ይላል።

"ተመልከት እንግዲህ እንደ ቪዲዮው መልዕክት ከሆነ ዮሐንስ ወንጌል ያውም የጌታ ቃል እርስ በእርሱ ይጋጫል ስለሚባል አንቀበልም ልንል ነው ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ላይ በእኛ አረዳድ ብዙ የተጋጩ የሚመስሉን ነገሮች አሉ። ተጋጩ እያልን የምንቀንስ ከሆነ እጃችን ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ሽፋን ብቻ ይቀራል። ስለዚህ የእኛ ልዩነት የመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛ ሐዋርያዊ ትርጉሙ የቱ ነው ወይ አይደለም የሚል ይሆናል እንጂ ቁጥሩ አይደለም።"

## ምዕራፍ ፳፯

## አዲስ አበባ-ሳሪስ

ፓስተር ናፍያድ ከልጆቹ ጋር ሳሎን ውስጥ ተቀምጧል፡፡ በቀይ ምንጣፍ ያጌጠው የሳሎን ወለል የቤቱን ሙቀት ትንሽ ጨመር አድርጎታል፡፡ የቤት ሰራተኛዋ ረከቦቷን ዘርግታ፤ ፊት ለፊቷ ነጫጭ ሲኒ ደርድራለች፤ ቀይ ሆኖ በደንብ የተያያዘው ከሰል ላይ ጥቁሩን ጀበና ጥዳዋለች፡፡ ቡናው እንደመፍላት እያለ ስለሆነ አልፎ አልፎ 'ድው ድው' ሲል ይሰማል፡፡ አንዳንዴ ከሰሉ ደግሞ ፍንድትድት እያለ የእሳት ፍንጥርጣሪ ይበትናል፡፡

የቤት ሰራተኛዋ ጸጉሯን ሹሩባ የተሰራች ሲሆን አሁንም አሁንም እጇን እየላከች ጸጉሯን ለማስተካከል ትጥራለች፡፡ ፊቷ ብስል ቀይ ሲሆን ጉንጯ ላይ ክብ ንቅሳት አለ፡፡ አንገቷ ላይ መጠነኛ እንቅርት አለባት፡፡ በእንቅርቷ የተነሳ የሰውነቷ ቅመም ስለሚዛባ ስራዋን ስትሰራ ቅዥቅዥ፣ ድንግርግር፣ ውዝግብግብ... ትላለች፡፡ በብር የተሰራ የጆሮ ጌጥ አድርጋለች፡፡ በጆሮዋ ውስጥ ደግሞ ነጩን የሁዋዌ ምርት የሆነውን የጆሮ ማዳመጫ ሰክታ የሀጫሉ ሁንዴሳን "ማለን ጅራ" የሚለውን የኦሮምኛ ዘፈን በስሜት ውስጥ ሁና እያዳመጠች ነው፡፡ አንዳንዴም በስሱ ከዘፋኙ ጋር አብራ ታንጎራጉራለች፡፡

ፓስተር ናፍያድ እና ሰንፔር ትልቁ ሶፋ ላይ ጎን ለጎን ተቀምጠዋል፡፡ ሰንፔር በቤት ልብስ ነው ያለችው፡፡ ፊቷ ውጪ እንደሚታየው እጅግ በጣም ውብ አይባልም፡፡ ዓይኗ ኩል ለምዷል ስለዚህ ኩሉ ሲቀር ፊቷ ያለቀሰ ሰው ያስመስላታል፡፡ አባቷ ሰማያዊ ቁታና ነጭ ቲሸርት ደርቧል፡፡ ማዕረግ ገና ከውጪ መግባቱ ስለሆነ በውጪ ልብሱ ነው ያለው፡፡ ሰንፔር እና ናፍያድ ከተቀመጡበት ሶፋ ፊት ለፊት የነ ሰንፔር እናት ፎቶ በትልቁ በመስታወት ፍሬም ውስጥ ይታያል፡፡ የነ ሰንፔር እናት ሠላም አሁን በሕይወት የለችም፡፡

ፓስተር ናፍያድ ባለቤቱን ልቡ እስኪጠፋ ነው የሚወዳት፡፡ ከሠላም ጋር የተዋወቁት ናፍያድ የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርቱን ሊጨርስ የመጨረሻ አመት ተማሪ እያለ፤ እሷ ደግሞ ሁለተኛ አመት ተማሪ እያለች ነበር፡፡

የተገናኙት የዩንቨርስቲው ቤተ መጽሐፍት ውስጥ ነበር፡፡ ባለቤቱ ሠላም በጣም ቀጭን ብላና ለስለስ ባለ ድምጽ ስለምታወራ አንዳንዴ ሲቀልድባት 'ሶል ላይብረሪ ስላገኘሁሽ ነው አሁን ድረስ ቀስ ብለሽ የምታወሪው?' ይላታል፡፡ ናፍያድ ጥናቱ ላይ አተኩሮ ሳለ ነው አጠገቡ መጥታ የተቀመጠችው፡፡



CamScanner

ሒሳብ ነክ ትምህርት እያጠና ስለነበር ረዥም ስሌት በወረቀት ላይ ስለሚሰራ ብዙ ጊዜ ወረቀት ያልቅበታል፡፡ ከዚያም ወረቀት ለመለመን ቀና ሲል እንደ ጠዋት ፀሐይ የምታበራ ቆንጆ ልጅ አጠገቡ ቁጭ ብላ ያገኘው፡፡

ወረቀት ሊጠይቃት ፊልጎ ቢሆንም ውበቷ ግን ፍዝዝ ያደርግ ነበር፡፡ ፊቷ ቀጭን ነው፤ ጸጉሯ ረዥምና ድብን ያለ ጥቁር ከመሆኑ የተነሳ የሚያብረቀርቅ ነው፡፡ አፍንጫ ጎራዳ ብትባልም የደስደሷ ፊቷን ሙሉ ለሙሉ ስለተቆጣጠረው ገና ሲያዩዋት አንዳች ሐሴትን ታላብሳለች፡፡

ወደ ቆንጆ ፊቷ መዳረሻ መሰላል ይመስል ረዥም አንገት አላት፤ ከመቃ አንገቷ ወረድ ሲሉ እንደ ፀሐይ ከሚያበራው ደረቷ ላይ መንታ የመሰሉት ሁለቱ ጡቶቿ ፊት ለፊት ከሸሚዟ ውጪ አፈትልከን ካልወጣን የሚሉ ይመስላሉ፡፡ በዚያ ላይ ስቃ ሳይሆን ገና ፈገግ ስትል የሚሰረጉደው ጉንጯ ተጨማሪ ማራኪነት አላብሷታል፡፡ ናፍያድ እና ሠላም የተጋቡት ሰላም ትምህርቷን ሐምሌ ላይ ጨርሳ ጥር ላይ ነበር፡፡

ለብዙ ጊዜ ረጋና ቀስ ብሎ የሚናገር አንደበቱን ከፍቶ ሲቆጣ ገና በቅርቡ ንግግር እንደለመደ እንቡቀቅላ ስትኮለታተፍ፤ ከአንደበቷ ይልቅ ከወትሮው ይበልጥ የበሰለ ቲማቲም መስሎ የሚቀላው ጉንጯ፤ መከፋቷን የሚያሳይ ትልቅ ምልክት ነበር፡፡ ይህኔ ናፍያድ ልቡ እንደ ድቤ ይመታበታል፤ ሰውነቱ በሀዘንና በፍቅር እንደ ቅቤ ቅልጥ ይልበታል፡፡ አስከፍታውም ይሁን አስከፍቷት ቀድሞ ይቅርታ ይጠይቃል፡፡

ሰላም እንዲህ ነበረች፡፡ ትገርመዋለች ሁሉ ነገሯ እንደ ስሟ ቀላልና ሰላማዊ ነበር፡፡ ሰንፔርንም ማዕረግንም ስትወልድ በብዙ ሕመምና ምጥ አልተሰቃየችም ነበር፡፡ ትገርመዋለች ነገሯ ሁሉ እንደ ባህሪዋ ቀላል ነበር፡፡

ምን ያደርጋል ትልቅ ችግር ገጥሟት የማያውቀው ሚስቱ ለአንዴና ለመጨረሻ በሚመስል መልኩ ታመመች፡፡ ይህ ሰንፔርንና ማዕረግን አጥብቶ ያሳደገ፤ ለባሏ ደግሞ የደስታ ምንጩ የሆነው ጡቷ በክፉ ድውይ ተመታ፡፡ የጡት ካንሰር፡፡ ሠላም ደፈረሰች፡፡ ሳታውቀው ደስታና እርጋታዋ ጎደለ፡፡ ቢሆንም ጊዜ ወሰደባት እንጂ እንደ ዱሮዋ ለመረጋጋትና ለመስተካከል ሞከረች፡፡

ሠላም የራሷን ሠላም አጣች እንጂ የሌሎች ሰላም እንዳይጎል ጥረት የምታደርግ፤ በሕመሟ የተነሳ የተለየ እንክብካቤና ጭንቀት የማትፈልግ፤ ተጨንቆ ማስጨነቀን ለማስወገድ ሕመሟን ዋጥ አድርጋ የምትችል፤ በሁሉ ሰው ፊት ደስተኛ ሆና መታየት ስለምትፈልግ ልዩ እንክብካቤ እንኳ የማትሻ፤ በጣም ከተንከባከቧት ያመማት ስለሚመስላት ለዚህም ስትል ጠንከር ያለ የህመም ማስታገሻዎችን ትጠቀም ነበር፡፡ መኖር የፈለገችው እንደ ወትሮዋ ቀለል ብላ ነበር፡፡ ለዚህም ይመስላል ስቀዩ ብዙም ሳይበዛ፤ ጣርና መከራዋ ሳይበረታ ከአምስት አመት በፊት ያረፈችው፡፡

--------//--------

ፓስተር ናፍያድ ተናድዷል፣ ግራ ገብቶታል፣ ይህ ሁሉ ስራ ከለንደኑ ስብሰባ ጋር የተገናኘ እንደሆነ እየገባው መጥቷል። እነዚህ ሰዎች ለምንም የሚመለሱ አልመሰሉትም። "አደገኛ ነገር በትውልዱ ላይ እየተቃጣ ነው" አለ።

ፓስተር ነገሮች ሁሉ በተጠናና ሆን ተብሎ እየተካሄደ እንደሆነ የተገነዘበው ዋናውን የስብከት ቪዲዮ ከመካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ሊያገኝ ሳይችል ሲቀር ነው። ፓስተር ናፍያድ ከብዙ ሰዎች ከፍተኛ አድናቆት እያገኘ ሲመጣ ንዴቱና ቁጣው ባሰበት።

ማዕረግ በአባቱ ነገር ዛሬም እንደኮራ ነው። "እኔ አይደለሁም ይህን ቪዲዮ ያዘጋጀሁት" ቢለውም ቪዲዮውን ያዘጋጀው አባቱ እንደሆነ በማመን ደስታ እየተሰማው ነው። በቅርቡ የኦርቶዶክስ መዝሙር ምርቃት ላይ በሕቡዕ ድርጅቱ ደቂቀ እስጢፋኖስ አማካኝነት ተጋብዞ ሄዶ ነበር።

በዝግጅቱ ላይ በጣም የታወቁ የኦርቶዶክስ ዘማሪያንና ሰባኪያን የተገኙበት ነበር። በእርግጥ እነዚህ ሰዎች በኦርቶዶክሶች የሃይማኖት ሕፀፅ አለባቸው እየተባሉ በተደጋጋሚ ቢከሰሱም ነገር ግን ከቤተ ክርስቲያኗ አገልግሎት አልታገዱም። ስለዚህም በጥሩ ሁኔታና ምቾት አስፈላጊውን እንቅስቃሴ እያደረጉ ነው። ማዕረግ በዕለቱ ዝግጅት በጣም ተደስቶ ነበር።

ሰባኪዎች 'መዳን በጸጋና በእምነት ብቻ' የሚለውን አስተምህሮ ቀስ ቀስ እያሉ ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ እያስመሰሉ በሰዎች አዕምሮና ልብ ላይ እየጻፉ እንደሆነ ተገንዝቧል። በዝማሬው ውስጥ ወትሮ ኦርቶዶክሶች ከሚታወቁበት ረጋ ያለና ተመስጦ ያለበት ዝማሬ በተቃራኒ ስሜትና እንደ ልብ በሰውነት መንቀሳቀስ የታጀበ፣ ዐይንን ጨፍኖ እጅን ወደ ላይ በመዘርጋት ከወገብ እየተወዛወዙ ዘምረዋል። ማዕረግ በዚህ ዝማሬ በጣም ተደስቷል። 'ኦርቶዶክስ የኛ ልትሆን ትንሽ ነው የቀረን' ብሎ ነበር ከምርቃቱ ሲወጣ። ለዚህም ነው አባቱን የማይረዳው።

ሰንፔር ግን ከወንድሟ ተቃራኒ የአባቷን ጭንቀት ተረድታለታለች። ኦርቶዶክሶች የሰጡትን መልስ አይታዋለች። መልሱን የሰጠው ዶክተር አበጋዝን የሮዳስ ጓደኛ ስለሆነ ታውቀዋለች። በጣም ሥነ ሥርአት ያለው፣ የምታከብረው ሰው ነው። 'ሀሪሲን' የተሰኘውን የውስጥ ደዌ፣ 'ባርባራ' የተባለውን የሰውነት አመራመርና የታካሚ አጠያየቅ ዘዴ እንዲሁም 'ኔልሰን' የተባለውን የህጻናት ሕክምና መጻሕፍት በስጦታ መልክ አበርክቶላታል።

በተጨማሪም ሰንፔር የመጨረሻ አመት የህክምና ተማሪ ስለሆነች አበጋዝ በሚሰራበት 'ሚድራሺ' ሆስፒታል ልምምድ እንድታደርግ ሁኔታዎች

## ምዕራፍ ፳፰

## ካሊፎርኒያ-ሎስአንጀለስ

መርሐዊ አሁን የሚያነበው ጽሁፍ ከፌስቡክ ጓደኛው ገጽ ላይ የተለጠፈ ሲሆን ለየት ባለ ሁኔታ መረጃ ያዘለ ይመስላል። መርሐዊ ከወይኑ ሳብ አደረገና ምላሱ ላይ ለሰከንዶች ያህል አጣጣመውና በእርጋታ ጽሑፉን ማንበብ ጀመረ። የጽሑፉ ርዕ "ፓትርያርክ ይሰደዳል እንጂ ሲኖዶስ አይሰደድም" ይላል።

"በስደት ላይ ያለው ሲኖዶስ በአራተኛው ፓትርያርክ በአቡነ መርቆሬዎስ የሚመራ ነው። እኚህ ጳጳስ ኢሕአዴግ የሚመራው መንግሥት ሥልጣን ሲይዝ፤ ሁሉንም ነገር መቆጣጠርና ሁሉንም እንደ አዲስ መጀመር ስለፈለገ ፓትርያርኩ በመንበረ ጵትርክናው እንዲሰነብቱ አልፈለገም። ስለዚህ ኢሕአዴግ እንደ ደርግ ሁሉ ፓትርያርኩን ከመንበረ ጵትርክናቸው ለማውረድ ወንበር መነቅነቅ የጀመረው አራት ኪሎ በገባ ማግስት ነው።

"ደርግ ሥልጣን ሲይዝ ሁለተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አቡነ ቴዎፍሎስ ነበሩ። ነገር ግን ፓትርያርኩ እና ደርግ የሚስማሙና የሚግባቡ አልሆኑም። ያልተግባቡበትም ዋና ምክንያት 'አቡነ ቴዎፍሎስ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ከደርግ ተጽእኖ አላቀው በነጻነት ለመሄድ ባላቸው ጽኑ ፍላጎት ነው' የሚሉ ሲኖሩ በተቃራኒው 'አቡነ ቴዎፍሎስ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ደጋፊ በመሆናቸው ነው ደርግ የተጋጫቸው' በማለት የሚከራከሩም አሉ።

"በተለይም ደግሞ ከደርግ ፍላጎት ውጪ 'በእኔ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አትደፈርም' ብለው ሦስት መነኮሳትን አጳጰሱ። ይህኔ ደርግ ደፈሩኝ ብሎ የካቲት 9 ቀን 1968 ዓ.ም. አቡነ ቴዎፍሎስን ከመንበረ ጵትርክናቸው አውርዶ እስር ቤት ወረወራቸው። በምትካቸውም ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና ውጪ አዲሱ ተሿሚ ከ909 ድምጽ ሰጪዎች ውስጥ 317 የመራጭ ድምጽ በማግኘት አቡነ ተክለሃይማኖትም መንበረ ጵትርክናውን ፈቅደው ሳይቀበሉ በግዳጅ ነሐሴ 23 1968 ዓ.ም. 'አባ ተክለሃይማኖት ሳልሳዊ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ' ተብለው እንዲሾሙ አደረገ።

"በደርግ የተጀመረው መንግሥት ሲቀየር ፓትርያርክ የመቀየር አካሄድ ዘመናትን ቆጥሮ ኢሕአዴግ ኢትዮጵያን በተቆጣጠረ ማግስት በቤተ ክርስቲያኗ ላይ ለላ የፓትርያርክ ሹም ሽር አቧራ መነሳት ጀመረ። በጊዜው ፓትርያርክ የነበሩት አቡነ መርቆሬዎስ ከተለያዩ አካላት ከመንበረ ጵትርክናቸው እንዲወርዱ ጫናዎች ይመጡባቸው ጀመር።

"በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት አንድ ሊቃነ ጳጳስ ከሥልጣን የሚወርደው አንደኛው 'በሥልጣን ላይ ያለው ፓትርያርክ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ፣ ሁለተኛው ባለው ምክንያት በገዛ ፈቃዱ ሥራውን ሲለቅ ወይም ሲሰናበት፣ ሦስተኛውና የመጨረሻው በሃይማኖት ሕፀፅና በሥነ ሥርአት ወይንም በቤተ ክርስቲያኗ ቀኖና ላይ ጥሰት ሲፈፅም በቅዱስ ሲኖዶሱ ጉዳዩ ተጣርቶ እውነት ከሆነ ከሹመቱ በውግዘት ይለያል' ይላል።

"ይህን ሕግ የተረዳው ፓትርያኩን ከሥልጣን ማውረድ የፈለገው ሥውሩ እጅ አቡነ መርቆሬዎስን 'በህመም ምክንያት ሥራዬን እንደቀድሞው ማከናውን አልችልም' የሚለውን ምክንያት ለቅዱስ ሲኖዶስ አስቀምጠዋል ብሎ ፓትርያርኩን ከሥልጣን አወረዳቸው ብለው ያምናሉ በዚህ ጉዳይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን።

"ከዚያም አቡነ መርቆሬዎስ ከአገር ወጥተው ወደ ኬንያ በስደት ሄዱ። ፓትርያርኩ ቀድመው አሜሪካ በነበሩ ሌሎች ሊቀ ጳጳሳት አማካኝነት አስፈላጊው ቅድመ ሁኔታ ተመቻችላቸውና ከኬንያ ወደ አሜሪካ ገቡ።

"አቡነ መርቆሬዎስ አሜሪካ ከገቡ በኋላ ኒውዮርክ ከተማ ላይ 1985 ዓ.ም. 'አዲሱ የአቡነ ጳውሎስ የፓትርያርክነት ሹመት ሕገወጥና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን የጣሰ ስለሆነ በእሳቸው የሚመራውን ሲኖዶስ አንቀበልም' ብለው መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገውን ሲኖዶስ በይፋ ተቃወሙ።

"ይህን ተከትሎ በአቡነ ጳውሎስ የሚመራው ሲኖዶስ በአሜሪካ አዲስ የተሰየመውን የሲኖዶስ አባላት ላይ ውግዘት አስተላለፈ። በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ 'በስደት ያለው ሲኖዶስ እና የአዲስ አበባው ሲኖዶስ' በሚል ለሁለት ተከፈለ።

"በዚህ ጉዳይ ላይ ጥናት ያደረጉ ሊቃውንት እንደሚስማሙበት ከሆነ 'የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ለሁለት መከፈል መንግሥት የአንበሳውን ድርሻ ቢወስድም አቡነ መርቆሬዎስም ተጠያቂ ናቸው ይላሉ። በመጀመሪያ ምንም ያህል ከባድ ጫና ቢደርግባቸውም እሺ ብለው ከመንበረ ጵትርክናቸው መልቀቅ አልነበረባቸውም' ይላሉ።

"'ጫናው ከባድ ቢሆንም ጵትርክናዬን አለቅም ቢሉ ኖሮ ውጤቱ ሌላ ይሆን ነበር። ሞትም ቢኖር ሞታችውን አብረን እንቀባላለን' የሚሉ አሉ። ሌሎችም ደግሞ 'ሥልጣኑን አልፈልግም ያሉት በገዛ ደብዳቤያቸው ነው። ይህ ደግሞ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁለተኛውን ፓትርያርክ ሥልጣን የሚለቅበትን ምክንያት ተጠቅመው ነው። ሌላው አቡነ ጳውሎስ ሲሾሙ እዚያው አዲስ አበባ ሆነው ምንም ተቃውሞ ሳያሰሙ እንደውም 'ይደልዎ' ብለዋል ሲሉ ይተቹዋቸዋል።



CamScanner

"አቡነ መርቆሬዎስን የሚተቹ ሰዎች የአቡነ ቴዎፍሎስን ተሞክሮ በመውሰ ጨመር አድርገው ይሞግታሉ። 'ደርግ ሥልጣኑን እያደላደለ ባለበት ሰዓት አቡ ቴዎፍሎስ ላይ አደጋ ሊያደርስ እንደሚችል የገመቱ ሰዎች ቀድመው ከአገ እንዲወጡ ሁኔታዎች ቢመቻችላቸውም አቡነ ቴዎፍሎስ ግን አሻፈረኝ እም በማለት ሰማዕትነትን በመፈጸም ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታማኝነታቸው ገልጸዋል። ስለዚህም አቡነ መርቆሬዎስ ይህን የመሰለ ተምሳሌተ ሰማዕትነት ትተ ምእመናን በትነው ነው የሄዱት፤ ኤጲስ ቆጶስ ከሚያስተዳድረው አገረ ስብከት አይለይ የሚል ጥብቅ ቀኖና ባላት ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ ለምንና እንዴት ይሰደዳል? ሲኖዶስ የሚሰደድ ከሆነ ኮሎኔል መንግሥቱም ዚምባብዌ ሆነው ስደተኛ ፓርላማ ማቋቋም ይችላሉ ማለት ነው?' በማለት ይከራከራሉ።

"በተቃራኒው ደግሞ የአቡነ መርቆሬዎስን መሰደድ የሚደግፉ ሰዎች እ.ኤ.አ በ2012 ዓ.ም. ዊክሊክ ያወጣውን ዘገባ ላይ ተንተርሰው ይሞግታሉ። እንደ ዊክሊክ ዘገ ከሆነ የቀድሞው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ታምራት ላይኔ 'አቡ መርቆሬዎስን ከሥልጣነ ጵትርክና ያስነሳሁት እኔ ራሴ በገዛ ፊርማዬ ሲሆን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ መከፈል ተጠያቂ ነኝ' ይላሉ ብለው እ.ኤ.አ ከ2006 እስከ 2009 ዓ.ም. የአሜሪካ አምባሳደር በኢትዮጵያ የነበሩት ዶናልድ ያማማቶን ዋቢ በማድረግ አውጥቷል።

"'ስለዚህም' ይላሉ የአቡነ መርቆሬዎስ ደጋፊዎች '…ስለዚህም አቡነ መርቆሬዎስ ከሥልጣን እንዲህ በግፍና በተንኮል ተገፍተው በመባረራቸው ነፍሳቸውን ለማዳን ሲሉ ሸሽተው እዚህ መጥተዋል። ሸሽተውም ብቻ ሳይሆን ሲኖዶስ አቋቁመው መምራት ጀምረዋል' ይላሉ።

"እንደማጠቃለያ ዋናው መታየት ያለበት ነጥብ የፓትርያርኩ በሥልጣን ተቀመጡ ሄዱ፤ በሕይወት ኖሩ ቀሩ ሳይሆን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አንድነቷ ሳይነጋ፤ ምእመናኗም ሳይበተኑና ሳይከፋፈሉ መቀጠላቸው ነው። አቡነ መርቆሬዎስ የፓትርያርክ ሹመት ሲያገኙም ሆነ ሳያገኙ የምእመናን አንድነት መጠበቅ ግዴታቸው ነው። ታዲያ እሳቸው ወንበሩ ላይ ያልቆዩ እንደሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ መከፋፈል አለባት? ከእሳቸው ክብርና ሕልውና ወይም ከቀናና በላይ የራሷ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሕልውናና አንድነት አይበልጥምን?" መርሐዊ የጸሐፊውን ሙግት አድንቆለታል። ግን እሱ ለቆመለት አላማ እንዲህ ያለ ሀሳብ አደጋ ነው። ስለዚህ ምን ያህል ኮሜንት፣ ላይክና ሼር እንዳለው ከጽሑፉ ግርጌ ላይ ማየት ጀመረ።

## ምዕራፍ ፳፱

ፓስተር ናፍያድን የሚቀርቡት አንዳንድ የኦርቶዶክስ መምህራን የወንጌላውያን አማኞች እና መምህራን የተሐድሶን እንቅስቃሴ እየደገፉ መሆኑ በጣም እንዳስቀየማቸው ሳይሸሽጉ አጫውተውታል፡፡ ስለዚህ ይህን ነገር እንደ አጋጣሚ ተጠቅመው ጠንከር ጠንከር ያለ ምላሽ እንደሚሰጡ ገብቶታል፡፡

ኦርቶዶክሶችም መልስ እንደሰጡት ቢያውቅም ምላሹን ግን ማየት አልፈለገም፡፡ በተሰጠው መልስ ተናድዶ በስሙ የተለቀቀውን ቪዲዮ የራሱም ባይሆን "ደግ አደረግኩ እሰይ!" እንዳይል ሰግቶ ነበር ቪዲዮውን ያላየው፡፡

ፓስተር ናፍያድ ወደ ወንድ ልጁ በትህትና እያየ "ይኸውልህ ማዕረግ ኦርቶዶክሶች ሃይማኖታቸውን እንደ ካቶሊክ ወይም እንደ ፕሮቴስታንት በማስተማርም፣ በተለያዩ መንገዶችም በብዛት ሲያስፋፉ አይታዩም፡፡ ነገር ግን ሃይማኖታቸው በባህሪው ፈጣሪን ማመስገንና በብርቱ በመጠበቅ ግን ኃይለኞች ናቸው፡፡ ለሃይማኖታቸው ዋጋውን እስከ ደም ጠብታ ይከፍላሉ፡፡ ይህንንም በአፄ ሱስንዮስ ጊዜ አስመስክረዋል፡፡ ሌላም የውጪ ወራራ ሲመጣ እንኳ የኢትዮጵያ ነገሥታት ሕዝቡን የሚቀሰቅሱት ሃይማኖትህን የሚያስለውጥህ ወራሪ መጣ እያሉ ነው፡፡" ፓስተር ናፍያድ የሚጠጣው ቡና ደስ ብሎታል፡፡ ከስኒው ውስጥ ቡናውን በከንፈሩ ሳብ ሲያደርግ በአፍንጫው ደግሞ አየሩን ደርቦ ወደ ውስጥ ሳብ አደረገው፡፡

"ስለዚህ በሃይማኖታቸውና በአስተምህሯቸው ከተሳለቅንባቸው አደገኛ ነው፡፡ እናንተ እንደ እኛ ካላሰባችሁ፣ የእናንተን ሃይማኖት ነው ብለን መቀበል ይከብደናል ነው የሚለው የቪዲዮው እንድምታ፡፡ ስለዚህ መልሳቸው ምንም ሊሆን ይችላል?"

"አባቢ ግን እኮ ከኦርቶዶክሶች ግማሹ አማኝ ቤተ ክርስቲያኗ እንድትታደስና ክርስቶስን ማምለክ ይፈልጋሉ፡፡ ስለዚህ ከኦርቶዶክሶች ውስጥም እኛን የሚደግፉ ብዙ አሉ ማለት ነው፡፡"

"ማዕረግ እየገባህ አይመስለኝም፡፡ የኦርቶዶክስ ቀኖና፣ ዶግማ እና ትውፊት ከእኛ ይለያል ማለት በኢየሱስ አያምኑም፣ ኦሪታዊ ናቸው ወይም ኢየሱስ መወለዱን ገና እየተጠባበቁ ነው ማለት ከመሰለህ ተሳስተሀል፡፡ ያንተ 'ኦርቶዶክሶች ማርያምን እንጂ ክርስቶስን አያውቁትም' ብሎ ማመን በእነሱ ላይ የሚያመጣው ቅንጣት ለውጥ የለውም፡፡ በዚህ አስተሳሰብህ ልታናግራቸው ከሞከርክ ደግሞ ፀብን ትጋብዝ ካልሆነ በስተቀር ውጤት አታመጣም፡፡ እውነት በወንጌል አስተምህሮ ካመንክ መጀመሪያ ሰውን ከነሁሉ ነገሩ ተቀበለው፡፡ ከዚያም አቋሙን እወቀው እና አውራው እንጂ ዝም ብለህ እሱ ነኝ ያላለውን ነህ ብለኸው ቀጥሎም ያንኑ ነህ ያልከውን ደግሞ ስህተት ስለሆነ ላርምህ ስትለው እንዴት አድርጎ ይሰማሀል?"



CamScanner

"እኔ የማይገባኝ ነገር በእናንተ በወጣቶች ብቻ ሳይሆን በትላልቅ ሲቃውንት ዘንድም ያለው ነገር ምንድነው? የማያውቁትን ነገር፣ ከእነሱ እውቅና ውጪ ወይም ማወቅ በላይ የሆነን ነገር በአጠቃላይ ተረት ነው፣ ውሸት ነው፣ እንቶ ፈንቶ ነው ብሎ ማጣጣል በዚህች አገር የበዛ ይመስላል፡፡ አንተ ኦርቶዶክስን ቀርበህ ስለማታውቃት ብቻና ያንተ እምነት ስላልሆነ ጥንቆላን የሚደግፉና የሚያበረታቱ፣ የኢየሱስን መወለድ ገና የሚጠብቁ አይሁድ አድርጎ መሳልና ማሳብ ዞሮ ዞሮ ውጤቱ አደጋ ነው፡፡"

"እውነትህን ነው አባቢ ትክክል ብለሀል፡፡ ሁልጊዜ የሚያወራው ነገር ፀብ ፀብ የሚል ነው፡፡ ከምክንያት ይልቅ ስሜትና ራሱ የፈጠረውን ልብ ወለድ ብቻ ነው የሚሰማው" ስኒውን ለሰራተኛዋ እያቀበለች ሰንፔር ነበር ተናገረችው፡፡

ማዕረግ በእህቱ በጣም ተናደደ፡፡ እህቱ መንፈሳዊ ነገር ስታወራ በጣም ይናደድባታል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ እሷ ኦርቶዶክስ ፍቅረኛ ስላላት ለሃይማኖታዊ አስተያየት የበቃች አይደለችም ብሎ ስለሚያስብ ነው፡፡

ስዚህም ማዕረግ "አንቺ ዝም በይ!" አለ ፊቱ በጥላቻና በንቀት አተያየት እኮሳትሮ፡፡

ከዚያም ወደ አባቱ ፊቱን መለሰ አድርጎ "እነሱስ እናንተ ሰይጣንን በሰይጣን ታወጣላችሁ፣ መናፍቅ፣ የእናንተ አምልኮ ማጓራት ብቻ ነው፣ ጸረ ታሪክ፣ ጸረ ባህል፣ ምንም አታውቁም... ምናምን ምናምን እያሉ ይሰድቡን የለ እንዴ?"

"ታዲያ እንደዛ ተባልኩ ብለህ እነሱንም የሌለ ስም ትሰጣቸዋለህ? ሲጀመር እንዲህ ያለ አመለካከትና አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ውስን ናቸው፡፡ ይሁን ሁሉም እንደዛ ያስቡ አንተ ግን እንደዛ ያሉህን ሰዎች ግልባጭ ትሆናለህ? ከምትነቅፈው ነገር በምን ልትሻል ነው? እሻላለሁ ካልክ በእምነትም በምግባርም መሻል አለብህ፡፡" ሁልጊዜ እንዲህ አትበል ሲባል የሚሰጠው ምክንያት ስላናደዳት፣ ሰንፔር ተቆጥታ ነበር ወንድሟን የተናገረችው፡፡

ማዕረግ እህቱን እንዳልሰማ ሆኖ አባቱን እያየ መናገር ጀመረ "እሺ ለማንኛውም ያንተ ቪዲዮ እኮ ክፋት የለውም፣ እውነት ነው የተናገርከው፡፡ ስለዚህ ምንድነው የሚያሳስብህ? ሲቀጥል ኦርቶዶክሶች ራሱ መታደስ እንደሚፈልጉ ይታወቃል፡፡"

'ኦርቶዶክሶች መታደስ ይፈልጋሉ' የሚለውን አባባሉን በድጋሚ ተናገረው፡፡ ማዕረግ እንዲህ እየተናገረ ራሱን ማሳመን ፈልጓል፡፡ ከዚያም ለተሐድሶው ለሚደረገው እንቅስቃሴ ኦርቶዶክሶችን እንደ ደገፈ እንዲሰማው አዕምሮውን ያደርጋል፡፡ ይህን አስተሳሰብ የወረሰው በቅርቡ ከተቀላቀለው ሕቡዕ የተሐድሶ ቡድን ነው፡፡

በእርግጥ ማዕረግ እንዲህ አይነት አስተሳሰብን የተለማመደው ገና አፍላ ጎረምሳ እያለ 'ደኅንነት' ከሚያስተምረው ፓስተር ነበር። ፕሮቴስታንት ያልሆኑቱን በጠቅላላ 'ያልዳኑ፣ ያልበራላቸው፣ አሕዛብ፣ ዳግም ያልተወለዱ...' እያለ ስለሚጠራቸው ማዕረግም ይህን ንቀትና የበላይነት ስሜት ከመምህሩ በልጅነት አዕምሮው ወርሷል። በተቃራኒው ራሱን ደግሞ 'ጻድቅ፣ በጌታ ዳግም የተወለደ፣ የበራለት፣ የጌታ...' አድርጎ ያስባል። ይህም አመለካከቱ አብሮት አድጎ አሁን እራሱን 'ጻድቅና በጌታ የተመረጠ' አድርጎ ፕሮቴስታንት ላልሆነ ሁሉ ከፍተኛ ንቀት እንዲያድርበት አድርጎታል።

ፓስተር ናፍያድ ተበሳጨ "ማዕረግ እያበላሼኸኝ ነው። በመጀመሪያ እነሱ የሚጠቀሙትን ቃል ልጠቀምና 'የማንን ቤት ማን ያድሳል?' ይላሉ። እውነታቸውን ነው። አንተ 'ማደስ' የምትለውን እነሱ 'ማፍረስ' ብለው ነው የሚያስቡት። ሃይማኖት አደገኛ ነገር ነው። ሰዎችን አሳምነህ ወደውህና ፈቅደው ሲቀበሉህ እንጂ በተንኮል ተነሳስተህ እነሱን ተመሳስለህ ለዚያውም በሚሊዮን የሚቆጠር ሰው የሚያምነውን እምነት እንደሌለ ክደህ ወይም ሰው ሁሉ ስህተት ነው ብለህ መናገር ይከብዳል። እውነት ነው፣ እምነት ሌላው ስህተት ነው እኔ ትክክል ነኝ ብሎ ማመን ነው። ይህ አስተሳሰብ ጤነኛ የሚሆነው ግን የሌሎችን የማመን ነጻነት ሳትጋፋ እንዲህ እንደ አሁኑ መሰለህ ተመሳስለህ ልታታልላቸው ካልሞከርክ ብቻ ነው። አለበለዚያ አደገኛ ነው።"

ማዕረግ በአባቱ በጣም ተናደደ። አባቱ ተሐድሶው ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ የገባው አልመሰለውም፣ ከሃይማኖት ተሐድሶው በተጨማሪ ምን ምን ጥያቄ እንዳለው አልገባውም ስለዚህ ብዙ ጊዜ የማይተነፍሰውን ቁጭት ለአባቱ ዘረገፈው።

"አባቢ የገባህ አልመሰለኝም ይህ እኮ የእነሱ አያቶች ብቻ ሳይሆን የእኛም አያቶች አገር ነው። እነሱ ትላልቅ ካቴድራል ቤተ ክርስቲያኖች አሏቸው እኛ ግን ድንኳን ውስጥ ነን፣ እነሱ ለቁጥር የሚያታክቱ የመቃብር ስፍራ አላቸው እኛ ግን መቃብር ቦታችን እነሱ በሰፈሩልን ልክ ነው፣ እነሱ ከቤተ ክርስቲያናቸው ውጪ ብዙ መሬት በየቦታው ወርሰዋል፣ እኛ ግን በገዛ ገንዘባችን መሬት እንኳን ለመግዛት ስንቱን ተለማምጠን ነው። ስለዚህ መታደስ ግድ ይላቸዋል።"

ፓስተር ናፍያድ አንገቱን ነቀነቀ። በእርግጥ ይህ ጥያቄ የእሱም ነው። በፓስተር ናፍያድ አስተሳሰብ ይህ ጥያቄ የሚፈታው ኦርቶዶክስን በማደስ አይደለም "ችግራችሁ ሌላ ነው። ይህን ጥያቄ መጠየቅ ያለባችሁ መንግሥትን እንጂ ኦርቶዶክስን አይደለም።" ፓስተር ናፍያድ በረዥሙ ተነፈሰ። ሰንፔር ወንድሟን ልትከራከረው አልፈለገችም። አሁን የተናገረው ነገር በእርግጥ ትክክል ነው። ለማንኛውም ከመናገሩ ይልቅ ዝም ብሎ ማዳመጡ የተሻለ ነው ብላ ስላሰበች ዝምታን መርጣለች።

"ለዚህ ነው ተሐድሶ የሚባለው ነገር ባንተ ብቻ ሳይሆን በብዙ ወጣት ወንጌላውያን አማኞች ዘንድ እንደ ሐረ ግሬሳ በየቦታው እየተንሰራፋና እያቆጠቆጠ ያለው? ይህ አካሄድ ከዚያኛው ወገን አጸፋ ከተሰጠው ለሁለቱም ሃይማኖት አደገኛ ከመሆን በላይ ጦሱ ለአገር ይተርፋል፡፡

"እስከ አሁን ድረስ ከሁለቱም ፅንፍ ከሚወረወር የቃላት እርግጫ ባለፈ ጥቃት በሚባል ደረጃ በደል በኦርቶዶክሶች ላይ ሲደርስ እያየሁ ነው፡፡ እስከ አሁን መከላከል እያደረጉ ነው፤ ማጥቃት ከጀመሩ ግን አደገኛ ነገር ውስጥ እንደ አገር እንገባለን፡፡ ሁላችንም ኢትዮጵያዊ ነን፡፡ ሁላችንም መናቅ አንፈልግም፡፡ የሰው ቤት ገብተህ አውቅላችኋለሁ ላድላችሁ ስትል ከንቀት ውጪ ምንም አይሆንም፡፡ ቅድም እንዳልኩህ 'ተሐድሶ' ማለት በእነሱ ትርጉም 'ላፍርሳችሁ' ማለት ነው፡፡

"እናንተ ወንጌላውያን ወጣቶች ማድረግ የነበረባችሁ ሃይማኖቱን ለአማኞቹ ትታችሁ ኦርቶዶክስ ውስጥ ያለውን ታሪክና ብዙ እውቀት ብትፈልጉ ለአገርም ለዓለምም ትተርፉ ነበር፡፡ የአውሮፓ እና የአሜሪካ አጀንዳ ይዛችሁ ሰው ቤተ መቅደስ ውስጥ ትርመሰመሳላችሁ፡፡ እናንተ መገኘት የነበረባችሁ የኦርቶዶክስ ቤተ መቅደስ ውስጥ ሳይሆን ኦርቶዶክስ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ነበር፡፡ አሜሪካ እና አውሮፓውያን እናንተን በፊት በር ቤተ መቅደስ ልከው ሁለታችሁን እዚያው ቅድስት ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት እያጣሉና እያጋደሉ እነሱ በጓሮ ቤተ መጻሕፍት ገብተው የቻሉትን ያህል ብራና መጻሕፍት በግዥና በስርቆት ያግዛሉ፡፡

"እህ እናንተ ምን ታደርጋላችሁ ሰው አስርጎ በማስገባት፤ አመሳስላችሁ በማቆየት ኦርቶዶክሶችን ለማታለል ትጥራላችሁ፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ከሰው ጋር ጸብም ሆነ አካላዊ ግጭት ቢኖርብን ችግሩን የምንፈታው በፊት ለፊት ንግግር ወይም በፊት ለፊት ጸብ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን በትላልቅ ጦርነት እንኳ ምሽግ የማይቆፍሩ፤ ወደ ኋላ የማይሸሹ፤ ለጦርነት ሲሄዱ ለጠላት ኢላማ የሚመች ነጭ ሸማ ለብሰው የሚሄዱ ናቸው፡፡ ጀግና ሲሆኑ የእውነት ጀግና ነበሩ እንጂ ቀረጣ፣ ምሽግ፣ ከጀርባ የማይወዱ ናቸው፡፡ እናንተ ግን በጀርባ... ይህ ደግሞ ኢትዮጵያዊነትም ሆነ ወንጌላዊነት አይደለም፡፡ ኢየሱስ እንኳ ሲያድን 'ልትድን ትወዳለህን?' ብሎ ጠይቆ ነው፡፡ እናንተ ግን ሰው ሳይፈልግ በግድ በማታለልና በማጭበርበር ልታድኑ ያምራችኋል፡፡ "አይከብድም ማዕረግ?

"የኦርቶዶክስ ትላልቅ አባቶች በእድሜም በብስለትም እሾህን በእሾህ አይደግፉም፡፡ የእነሱ ልጆችም ይህን እንደማይደግፉ ይሰማኛል፡፡ ግን ቤተ ክርስቲያናቸው ስትፈርስ ዝም የሚሉ አይመስለኝም፡፡ እንደተለመደው ሁሉ ችግር በመጣ ቁጥር መልስ እየሰጡ፤ ሰው እያወዙ ላይቀጥሉ ይችላሉ፡፡ ችግሩን ከምንጩ እናድርቀው ብለው ወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያናት ላይ ልክ አሁን እየተደረገባቸው እንዳለው እነሱም ሰው አስርገው ማስገባት ከጀመሩ፤ እናንተ ቤተ ክርስቲያኗን ለማዋረድና ለመስደብ ሌት



CamScanner

ተቀን እንደምትስሩት እነሱም ስራዬ ብለው ከቀጠሉ፤ 'የወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያናትን ኦርቶዶክሳዊ' ለማድረግ የሚል አዲስ አጀንዳ ጃስ ካሉ ለማየት ያብቃህ ለወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያናት ትልቅ ተግዳሮት ይመጣባታል። አሁን ኦርቶዶክሶች እያመማቸው ያለው ሕመም ምን እንደሆነ ያኔ ይገባሀል። እመነኝ ለማድረግ ከፈለጉ ደግሞ የገንዘብም ሆነ የጉልበት አቅም ከእኛ በተሻለ አላቸው።" ሰራተኛዋ የጆሮ ማዳመጫዋን ጆሮዋ ላይ እንደሰካች በፓስተር ናፍያድ ፊት ለፊት ካለው ጠረጴዛ ላይ ቡናውን አስቀመጠች።

ፓስተር ናፍያድ ቡናውን አንስቶ ፉት እያለ ንግግሩን ቀጠለ "ተመልከት ብዙ ሰዎች ኦርቶዶክስ ሆነው እንደውም አገልጋይ ሆነው ቤተ ክርስቲያኗን መልሰው ሲያጠቁ፤ ከዚያም ባስ ብሎ ከሃይማኖት አስተምህሮ ውጪ ሲያስተምሩ ቤተ ክርስቲያኗ ዝም የምትለው ወይም የማታወግዛቸው መታደስ ስለፈለገች ወይም ሰዎቹን ስላደነቃቸቻቸው እንዳይመስልህ።

"የእምነቱ አንዱ መርሆ ምን መሰለህ? አንድ ሰው በኦርቶዶክስ አስተምህሮ ካልተስማማ በተለይ የሃይማኖቱ የሆነ ደረጃ ያለው ከሆነ ማለትም ዲያቆን፣ መምህር ወይም ቄስ ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ልዩነቱን ፊት ለፊት መጥቶ ለሊቃውንቱ ማስረዳት አለበት። ከዚያም በኦርቶዶክስ አስተምህሮ መሠረት ሀሳቡ ታይቶ ከቤተ ክርስቲያኗ አስተምህሮ ካልተጣጣመ ብቻ ነው የሚወገዘው። ይህን ታውቃለህ?" ፓስተር ናፍያድ የማዕረግን ዐይን ዐይኑን እያየ ጠየቀው። ማዕረግ እንደማያውቅ አንገቱን በአሉታ በመነቅነቅ መለሰ። ሰንፔር አባቷ እንዲህ በስሜትና በቁጣ ሆኖ ስለ ኦርቶዶክሶች መናገሩ አስገርሚታል። ስለ ኦርቶዶክስ እንዲህ የሚያስብ አይመስላትም ነበር።

"እኔም አንተም የምናውቃቸው የተሐድሶ አቀንቃኞች ከቤተ ክርስቲያኗ ያልተባረሩት ሀሳባቸው ተቀባይነት አግኝቶ፤ በኦርቶዶክስ ሊቃውንቶች ተወዶ ሳይሆን እነዚህ ሰዎች ፊት ለፊት ልዩነታቸውን ስለማያምኑ ወይም ስለማያሳምኑ ነው። በቃ እውደ ምህረት ላይ እንደልባቸው ሲያወሩ በእርግጥ ሽፍንፍን እያደረጉ ይናገሩ ይሆናል እንጂ በቀጥታ ከኦርቶዶክስ ውጪ የሆነ አስተምህሮ ሲያስተምሩ ሰምተን አናውቅም እሱም ቢሆን ኦርቶዶክስ ጎሽ በርቱ እያለቻቸው ከመሰለህ ተሳስተሀል። ቅድም ባልኩህ ምክንያትና አንዳንድ ጊዜም ነገ ይሻሻላሉ ይቀየራሉ የሚሉ፤ እያዩ እንዳላዩ የሚያልፉ ሆደ ሰፊ ትላልቅ አባቶች ስላሏቸው ነው ከውግዘትና ከቤተክርስቲያኗ ከመባረር የዳኑት።" ማዕረግ የአባቱ ነገር ግራ ገብቶታል። 'ሰውየው ኦርቶዶክስ ሆነ እንዴ?' አለ በሆዱ።

"ሌላው ይህ ተሐድሶ ቢሳካ ኦርቶዶክሶች ወንጌላዊ የሆኑ መንፈሳዊ ተቋማትን ይቀላቀላሉ ወይም ይሆናሉ ብለህ ካሰብክ ተሳስተሀል። የሚሆኑት ራሱን የቻለ የታደሰች ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ነው። እሱም አንድ ብቻ ከሆኑ። በጣም ሊለያዩ



CamScanner

ይችላሉ። ከውጤት በኋላ የተለያየ ሀሳብ ሲመጣና እርስ በእርስ ሲፈረካከሱ ይችላሉ።

"እንደው ልክ እንደ ህንድ ኦርቶዶክስ ተሐድሶና ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ተብሎ ቢከፈል እንኳ የኢትዮጵያን የወንጌል አስተምህሮ ያዳክመዋል እንጂ አያጠናክረውም። ጥላቻ በሶስቱም ምእመናን ዘንድ ይንሰራፋል። ተሐድሶ፣ ወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያን እና ኦርቶዶክስ ተብሎ ይከፋፈላል ከጥላቻ ጋር። ይህ ደግሞ አለማዊ ትርፍ እንጂ መንፈሳዊ ትርፍ የለውም።

"ይገባኛል ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው እኛ መምህራኖች ነን። በሁለቱም ጎራ ያለን። በወጣቶች መካከል እውነትና ትክክለኛውን የራሳችንን እውነትና የአስተምህሮ ልዩነትን ብቻ መናገር ሲገባን አንዱን በአንዱ እያነሳሳን፤ ሌላው የማያምነውን ያምናል! አስተምህሮው ያልሆነውን አስተምህሮው ነው እያለን ውሸት እየደባለቅን እያወራን የራሳችንን ደግሞ ከፍ ከፍ እያደረግን ስላወራን በትውልድ መካከል መናናቅና መሰዳደብን ዘራን።

"ተሐድሶ የምትለው እንዲህ ቀላል ነገር አይደለም። ኦርቶዶክሶች መታደስ ቢፈልጉ ዛሬ ሳይሆን ድሮ በአጼ ሱስንዮስ አለፍ ብሎም በአጼ ኃይለሥላሴ ጊዜ ደግሞ በዳቪድ ስቶክስ፣ በነ አለቃ መሠረት ስብሐት ለአብ፣ በነቀስ ኮሲን ማንሰል ይታደሱ ነበር። ስለዚህ ጭራሽ አዳዲስ፣ ኃይለኛ ወጣት ጉልበታም በእውቀትም በመዘመንም የረቀቁ ትውልዶች ሲነሱ ለምን ይታደሳሉ?

"የኔ ቪዲዮ ላይ ያለው እኮ ታደሱ ሳይሆን ፕሮቴስታንት ሁኑ ነው የሚለው። የሆነ የተበላሸ ነገር አስተካክሉ ማለት አንድ ነገር ነው። ቪዲዮው ግን አስተካክሉ ወይም እንደቃሉ ታደሱ ሳይሆን ፍረሱና እንስራችሁ ነው የሚለው። እና ይሰሙኛል ብለህ ታምናለህ? እስኪ ልጠይቅህ? ይህን እንቅስቃሴ ላንተና አንተ በምታምነው ቤተ ክርስቲያን ቢቃጣ ምን ትላለህ?" ፓስተር ናፍያድ ልጁ ውስጥ የበቀለውን የንቀትና የጥላቻ አስተሳሰብ ነቅሎ ማውጣት ፈልጓል። 'እንዲህ አይነት አመለካከት በኦርቶዶክስም አለ ስለዚህ እንዴት ነው ይህ ትውልድ የሚታረቀው?' አለ በውስጡ ፓስተር ናፍያድ።



CamScanner

## ምዕራፍ ፴

## ካሊፎርኒያ-ሎስአንጀለስ

'ወርቃማዋ ግዛት' የሚል ቅፅል ስም ያላት ካሊፎርኒያ የከተማዋ አርማ ላይ 'ዮሬካ' የሚል መፈክር የጻፈች ሲሆን 'እወድሻለሁ ካሊፎርኒያ' የሚል የከተማው ተወዳጅ መዝሙር አላት፡፡ እንግሊዘኛ ቋንቋን በመከተል ስፓኒሽና ቻይንኛ በከተማዋ በስፋት ይነገራሉ፡፡

ከአሜሪካ ግዛቶች በስፋት ሦስተኛ፤ በህዝብ ብዛት ደግሞ ከአሜሪካ ከተሞች አንደኛ ስትሆን፤ ከዓለም ከተወዳደረች ደግሞ ሰላሳ አምስተኛ ነች፡፡ ሳክራሜንቶ የካሊፎርኒያ ግዛት ዋና ከተማ ሲሆን ሎስ አንጀለስ ደግሞ ትልቁ ከተማ ነው፡፡

ለዚህም ይመስላል በስደት ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ ዋና መቀመጫውን ካሊፎርኒያ ያደረገው፡፡ እንዲሁም አሜሪካ ውስጥ ካሉት ሃያ ስምንት ደብሮች ውስጥ ሰባቱን ካሊፎርኒያ ውስጥ የደበረው፡፡

መርሐዊ አቡነ ሰላማ ተብሎ የካሊፎርኒያ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ ከተሾመ በኋላ ነገሮች በፍጥነት እየተለዋወጡ ነው፡፡ ሎስ አንጀለስ የሚገኙትን ጽርሐ አርያም ቅድስት ማርያም እና ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን፤ ሳንሆዜ ያለው መካነ ራማ ቅዱስ ገብርኤል፤ ኢልክ ግሮቭ ቅድስት ሥላሴ፤ ሳንዲያጎ ቅዱስ ገብርኤል፤ ኦክላንድ መካነ ሰላም መድኃኔዓለም እና ሳክራሜንት ውስጥ ያለው መካነ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያናትን በስሩ ያስተዳድራል፡፡ ከዚህም በላይ በስደት ላይ የሚገኘውና ራሱን 'ሕጋዊ' ብሎ የሚጠራው ሲኖዶስ የጠቅላይ ቤተ ክህነቱ ዋና ስራ አስኪያጅ ነው፡፡

ስለዚህም ይህን ሥልጣኑን ተጠቅሞ ብዙ ነገሮች እየፈፀመ ይገኛል፡፡ ፓትርያርኩ በእቅምም በጉልበትም በእድሜም እየደከሙ ስለሆነ የፓትርያርክ ያህል በትረ ሥልጣኑን ተቆጣጥሮታል፡፡ የፓትርያርኩን ማሕተም በመጠቀም የፈለገውን ነገር እያደረገ ነው፡፡

መርሐዊ በዓለም አንደኛ ደረጃ ያለውን ውዱንና ጥቁር ቀለም ያለውን ፒኖት ኖይር ወይን እየጠጣ በስልኩ የተለያዩ መረጃዎችን እያየ ነው፡፡ በተለይ በስደት ላይ ያለው ሲኖዶስ ጳጳሳት ከሾመ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደ አዲስ አሜሪካ እና አዲስ አበባ ስላሉት ሲኖዶሶች ጉዳዩ እንደ አዲስ ተነስቶ በማኅበራዊ ድረገጽ ክርክር አስነስቷል፡፡

---------//---------

ሳሪስ አዲሱ ሰፈር እንደ ሌሎች የአዲስ አበባ መንደሮች ከተቆረቆረ ብዙ አስርት አመታትን ያስቆጠረ አይደለም፡፡ በኮብል ድንጋይ ልብጥ ብሎ የተነጠፈው መንገድ



CamScanner

መኪና ለማሽከርከር ምንም የማይባል ቢሆንም ሰፈሩን ማወቅ ግን ግድ ይላል። መኖሪያ ቤቶች በብዛት ያሉበት፤ እንዲሁም መንገዶቹ ጠመዝማዛና ጠባብ ስለሆኑ ለብዙ አመት የነዳ ሹፌር በፍጥነት የማሽከርከር ልምዱን ተጠቅሞ እዚህ ሰፈር መንዳት ያዳግተዋል።

ፓስተር ናፍያድ ከዋናው መንገድ ተገንጥሎ ወደ ቤቱ ለመድረስ አምስት ቅያሶችን መተጣጠፍ ይኖርበታል። ሰዓቱ ለአራት ሃያ አምስት ጉዳይ ሲሆን ረዥሙን መብራቱን አብርቶ በጥንቃቄ ውስጥ ለውስጥ ባሉት መንገዶች አራተኛው ቅያስ ጋር መታጠፍ ጀመረ።

ዳንኤል "ደርሷል" የሚል መልዕክት በዘላለም የእጅ ስልክ ላይ ላከለት። መልእክቱ ሲደርሰው ዘላለም ረዥሙን የመኪናውን መብራት አበራ። ፓስተር ናፍያድ ሌላ መኪና ሊዞር መስሎት መኪናውን ወደ ቀኝ ዞር ሲያደርገው ዘላለም የመኪናዋን ፊት ለፊት ከማዞሪያው ወጣ አድርገና አንተፋትፎ አቆመው።

ፓስተር ናፍያድ መኪናዋ እምቢ ያለው ስለመሰለው ፍሬኑን ይዞ እስኪስተካከል መጠባበቅ ጀመረ። ዘላለም ከመኪናው ወረደና የመኪናውን የፊት ለፊት ኮፈን ከፈተና እንደመጎርጎር ጎንበስ አለ። ፓስተር ናፍያድ ሊያቆም ነው ብሎ የመኪናውን ሞተር አጠፋና ሊወርድ ሲል ዘላለም ወደ ፓስተር ናፍያድ መሄድ ጀመረ።

ፓስተር ናፍያድ ከመኪናው ሳይወርድ ይጠብቀው ጀመረ። ምን ሊጠይቀኝ ነው ብሎ እያሰበ እያለ ሰውየው ከጎኑ የሆነ ነገር የሚያወጣ መሰለው። ዘላለም ጥቁር ረዥም ብረት ነገር መዘዘ። ሽጉጥ ነው።

ዘላለም ግሎክ 19 የተባለውን አውስትራሊያ ሰራሹን ቀላሉ፤ ላያያዝ ምቹና አጠር ያለ ቁመት ያለውን ሽጉጡን ከግራ ጎኑ መዞ በፓስተር ናፍያድ ላይ አነጣጠረ። ፓስተር ፍያድ በድንጋጤ የሚናገረው ጠፍቶት አፉን ከፈተ። ድምጽ ግን ማውጣት አልቻለም።

ዘላለም በፍጥነት የፓስተር ናፍያድ መኪና ጋር ደረሰና በግንባሩ አስተካክሎ የመጀመሪያውን ጥይት ተኮሰ ጭንቅላቱ ከጎን በኩል ያሉት አጥንቶች ጥቁር ድንጋይ ላይ እንደወደቀ እንቁላል ተጠርምሶ ደሙ በመኪናው ተፈነጣጠቀ። ዘላለም 'አንድ ያጣላል' አለና በፊት ለፊት በኩል ደገመው። ደሙ በዛ ብሎ በመስታወቱና መሪው ላይ ተረጨ።

ዘላለም በፍጥነት ሽጉጡን ከኒላው ከተተና ከኮቱ ኪስ ውስጥ ስፕሬይ አወጣ። ስፕሬዩ ቀይ ነው። በስፕሬዩ መኪናው የፊት ለፊት መስታወት ላይ "ተዋሕዶ አትታደስም!" ብሎ ጻፈ።



CamScanner

## ምዕራፍ ፴፩

## አዲስ አበባ-ጀሞ

አዲስ አበባ የተለመደውን የሰዎች ውክቢያ፣ መንቀዥቀዥ፣ መባተል ልታስተናግድ እየነጋላት ነው፡፡ አንዳንዱ ረፍዶበት ወደ ሥራው ለመድረስ ታክሲ ለመያዝ ይጋፋል፤ አውቶቢስ ለማግኘት ይሰለፋል፤ ሰራተኛው ፊርማ በጊዜ ገብቶ ለመፈረም፤ ከአለቆች 'አርፍደሃል' እሱ ግልምጫ ለመገላገል ብዙዎች ይጣደፋሉ፡፡

መኪና ያላቸው ግን ትንሽ ዘና ይላሉ፡፡ ምንም የመኪናው መጨናነቅ ቢኖርም ባለ መኪኖች ከእግረኞች በተሻለ ሁኔታ ረፈድ አድርገው ይተኛሉ፡፡ ተረጋግተው ቁርስ ይበላሉ፤ ተረጋተው ከቤት ይወጣሉ፤ ቢያንስ ለታክሲ አይሰለፉም ለባስ አይጋፉም፡፡ ሮዳስ ከነዚህ ምድብ ነው፡፡ ከእነዚህም በላይ ነው የራሱ አለቃ ራሱ ነው፡፡ አንድ ሰዓት ከአርባ አምስት ሆኗል እሱ ግን ተኝቷል፡፡

ከራስጌው መብራት ብርሃን ይልቅ በመኝታ ቤቱ አሾልቃ የገባቸው የፀሐይ ብርሃን ባደመቀችው መኝታ ቤቱ ውስጥ እየተገላበጠ የህልም ዓለሙን ከሚቀጭበት ዓለም አባኖ የቀሰቀሰው የአቢጋዝ የስልክ ጥሪ ነው፡፡

ሮዳስ ከእንቅልፉ በመቀስቀሱ እየተነጫነጨ ስልኩን ማታ ቻርጀሩን ሰክቶ ካስቀመጠበት ኮመዲኖ ላይ እያነሳ ከተሰካበት ነቀለና እንቅልፍ ባጎረነነው ድምጽ "ሄሎ?" አለ፡፡

"ሄሎ እንዴት አደርክ ሮዳስ? ከእንቅልፍ ቀሰቀስኩህ እንዴ ይቅርታ?"

"አይ ምንም አይደለም አቢጋዝ እንዴት አደረክ?"

"እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ፡፡ ሰላም ነው? እንዴት ነህ አንተ?"

ሮዳስ ከእንቅልፉ ሰመመን እየተነቃቃ ትራሱን ገፋ አድርጎ ወደ ራስጌው ተደላድሎ እየተቀመጠ "ሰላም ነው አቢጋዝ ምነው በጠዋት? በደህና ነው?"

አቢጋዝ ትንሽ እንደ መሳቀቅ ብሎ ማውራት ጀመረ "ትንሽ ችግር አለ የሰንፔር አባት አርፈዋል"

ሮዳስ ደነገጠ፡፡ የጠበቀው አይደለም፡፡ ቅንድቡን ወደ ላይ ሰቅሎ ትንፋሹን ላፍታ ያዘውና ዝም አለ፡፡

አቢጋዝ ዝምታው ግራ ስለገባው "ሔሎ ሮዳስ አለህ?"



CamScanner

"አሰሁ ምን ሆነው ነው የሞቱት?" አሁን ሮዳስ ተረጋግቶ ከተቀመጠበት አልጋ ተነስቶ የአልጋው ጠርዝ ላይ ቁጭ ብሎ በእግሩ ነጠላ ጫማውን እየፈለገ ነው።

"አሁን ቢቢሲ ላይ ብሬኪንግ ኒውስ ሆኖ እየታየ ነው"

"ቢቢሲ! ቢቢሲ! ብሬኪንግ ኒውስ? እንዴት ሆኖ?"

"ነገሩ ትንሽ ለየት ያለና ከባድ ነው። ለማንኛውም ቢቢሲ ላይ አሁን እየታየ ስለሆነ እየውና ነገሩን በኋላ እናወራዋለን።"

-----//-----

## ካሊፎርኒያ-ሎስአንጀለስ

በምዕራብ ሆሊውድ በ8440 ፀሐይ መጥለቂያ ቦውል ቬርዳ አካባቢ የሚገኘው በሞርጋን የሆቴል ባለቤቶች ቡድን የሚመራው ባለ አስራ ሁለት ወለልና ባለ ሁለት መቶ ሰላሳ ሰባት ክፍሉ ሞንደሪያን ሆቴል ውስጥ ነው ስብሰባው የሚካሄደው።

ቶኒ የስብሰባው መግቢያ አዳራሽ ላይ ብቻውን ቆሞ ቡና እየጠጣ ወደ ስብሰባው የሚገቡትን ሰዎች በጥንቃቄ እየታዘበ ነው። መጀመሪያ ወደ ስብሰባው አዳራሽ የገባው መርሐዊ ነው። መርሐዊ የጽጽስና ቆቡንና በትረ ሙሴውንም ብቻ ሳይሆን አቡነ ሰላማ የሚለውን ስሙንም ጥሎት የመጣ ይመስላል። ሙሉ ጥቁር ሱፍ አድርጎ አጭርም ብትሆን አንገቱን ቀና አድርጎ ወደ ስብሰባው አዳራሽ ቀደም ብሎ ነው የገባው። ከመርሐዊ በመቀጠል ከአዲስ አበባ የመጡት ክብሮምና ሰውየው ናቸው።

ቶኒ አዕምሮው ውስጥ በጥንቃቄ ሲያጠናው የነበረው የሰውየውና የክብሮም ግለ ታሪክ በውስጡ መፍሰስ ጀመረ። ክብሮም የፓትርያርኩ ልዩ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ቢሆንም ይህን ስብሰባ የሚታደመው ግን በድብቅ ቋሚ ሲኖዶሱም ሆነ ፓትርያርኩ ሳያውቁ ነው።

የክብሮምን ቅብጥብጥነት የሚያውቀው ቶኒ በመጣበት ሸንጠ ረዥም ሊሞዚን ውስጥ ሆነ ብሎ እርቃናቸውን ያሉ እንስቶች ፎቶግራፍ ከነአድራሻቸው በአልበም ውስጥ አስቀምጦለት ነበር። እንደ ጠበቀውም ክብሮም ለአንደኛዋ ልጅ ደውሎ ለማታ ቀጠሮ እንዳስያዘ አውቆበታል።

ይህ ድብቁ ባህሪው በፓትርያርኩ ዘንድ ቢታወቅ አይደለም የፓትርያርኩ ልዩ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የአንድ ደብር ጠባቂም እንደማያደርጉት ጠንቅቆ የሚያውቀው ቶኒ የክብሮምን ተግባር በድብቅ ቀርጾ ለአስፈላጊ ቀን እንዴት እንደሚጠቀምበት



CamScanner

እያሰላሰለ ነው። እንዲህ ያለ ሽዳዮ 'ሥነ ምግባር የተላበሱ ጸሎተኛ' ናቸው እየተባለ ለሚደነቁት አባት ቤሰጥ የሚፈጠረውን ነገር ቶኒ ጠንቅቆ ያውቃል። ቶኒ የአሁኑን ፓትርያርክ 'ወግና ሥርአት ጠባቂ'፤ ከእሳቸው ቀደም ያሉት 'ለዘብተኛ' ናቸው እንደሚባሉ ያውቃል። ስለዚህ ካለፉት ፓትርያርክ ይልቅ የአሁኑ ፓትርያርክ ክብሮም እንደሚፈራቸው ያውቃል።

ቶኒ በእጁ የያዘው ቡና ስላለቀበት ቡና ለመድገም ፔርሙዙ ጀርባ የተቀመጠውን ልጅ እንዲቀዳለት የቡና ስኒውን አቀበለውና እሱ ስለፓትርያርክ ልዩ ጽሕፈት ቤት ሥልጣንና ማዕረግ ለማወቅ ጥረት ካደረገው አንዳንድ ነገሮችን ለማስታወስ ሞከረ። በተለይ ከማኅበራዊ ድረ ገጽ ያነበበውን ማሰላሰል ጀመረ።

'ቀድሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቤተ ክህነት ሥልጣን፣ ተዋረድና ማዕከላዊ አሰራር ሲዘረጋ የነበረው መዋቅር የቤተ ክርስቲያኗ ትልቁን ሥልጣን የያዘው ቅዱስ ሲኖዶስ ነው። ከቅዱስ ሲኖዶስ በመቀጠል ቋሚ ሲኖዶስ ከዚያም ጠቅላይ ቤተ ክህነት፣ አኅገረ ስብከት ጽህፈት ቤት፣ ወረዳ ቤተ ክህነት እያለ በተዋረድ የሚሄድ እንጂ የፓትርያርክ ልዩ ጽሕፍት ቤት የሚባል መዋቅር አልነበረም።

የፓትርያርክ ልዩ ጽሕፈት ቤት የሚለው መዋቅር የመጣው በአቡነ ጳውሎስ ጊዜ ነው። ይህ መዋቅር ለአንዳንድ የመንግሥት አካላት በቤተ ክርስቲያኗ ላይ እጃቸው እንደ ልብ ለመሰንዘር ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል ይባላል። ብዙዎቹ የልዩ ጽሕፈት ቤቱ ኃላፊዎች የሚመረጡት በቤተ ክርስቲያኗ አንዱን የክህነት ማዕረግ ቢኖራቸውም በይበልጥ ፖለቲካዊ ቁመናቸው የሚያመዝን፤ እንዲሁም ከቤተ ክርስቲያኗ ጥቅምና ፍላጎት ይልቅ የመንግሥት ርዕዮተ ዓለም ግድ ይላቸዋል እየተባለ በምእመኑ ዘንድ በሰፊው ይታማል።" ቶኒ ቡናውን ፉት እያለ ያነበበውን ማስታወስ ቀጠለ።

'ቀላል ቁጥር የሌላቸው የዚህ ጽህፈት ቤት አገልጋዮች የፓትርያርኩን ትእዛዝ ከሲኖዶሱ ቃል ያስበልጣሉ ይባላሉ። እንዲህ አይነት ሥርአት ያለው በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሲሆን 'ፓትርያርኩ የክርስቶስ እንደ ራሴ ስለሆነ እሱ ያለው ሁሉ ልክ ነው፤ ፓትርያርክ አይሳሳትም' የሚል ቀኖና አላቸው። ክብሮምና አንዳንድ ጓደኞቹ እንደ ካቶሊክ ሥርአት ፓትርያርኩ ከሲኖዶስ በላይ የሆነ ሥልጣን ቢኖራቸው ደስ ይላቸዋል እየተባሉ ይታማሉ። ምክንያቱም በተዘዋዋሪ የልዩ ጽህፈት ቤቱን አቅም ከፍ እንደሚያደርገው ስለሚያውቁት ነው። በተጨማሪም ሲኖዶሱ የወሰነውን በፈለጉት መንገድ አድርገው ያስፈጽሙታል። ለፓትርያርኩ አቤቱታን ማድረስም በጣም ከባድና የልዩ ጽሕፈት ቤቱን ይሁንታ ማግኘት ግድ ነው በማለት በደል የደረሰባቸው ሰዎች ቅሬታቸውን በምሬት ያቀርባሉ።" ይላል ቶኒ ያነበበው ጽሑፍ። ቶኒ በሀሳቡ ስለ ክብሮም ሥልጣን እንዲህ አለ 'ይህን ከባድ ሥልጣን ነው ክብሮም በመዳፉ የተቆጣጠረው።' አለና አንገቱን ነቅነቀ።

ቶኒ ሀሳቡን ከክብሮም ወደ ሌላኛው የዚህ ስብሰባ ታዳሚ አዞረ፡፡ ሙሉ ጥቁር ሱፍ ያለከረቫት አድርገዋል፡፡ የፈረንጅ ክልስ መሆናቸው የሰጣቸው ስልክክ ያለ አፍንጫና ቀይ ፊት ብቻ ሳይሆን ለየት ያለ ነገር መውደድ፤ ከባዱን ነገር የመጋፈጥ አቅምና የጀብደኝነት ባህሪን አላብሷቸዋል፡፡ መልከ መልካምነታቸው ትንሽ የእድሜ መግፋትና የሰውነታቸው ውፍረት ቢያደበዝዘው እንጂ አልጠፋም፡፡ ረዥምና ቀጥ ያለ ቁመናቸው፤ ካላቸው የፖለቲካ ብስለትና ከፍታ ጋር ተደማምሮ በሕዝቡ ዘንድ በጣም ይታወቃሉ፡፡ ሰውየው በፖለቲካ ቁመናቸውም ብዙ መጋፋት፤ ብዙ ማድረግ የሚችሉ፤ ትልቅ የመንግሥት ሥልጣን ያላቸው ሰው ናቸው፡፡ ቶኒ ስለ ሰውየው አቅም ሲያስብ ክብሮም ትዝ አለው፡፡

ለክብሮም እዚህ መድረስ ቁልፉን ሚና የተጫወቱት እኚህ ሰው ናቸው፡፡ ብዙዎች የሚወዷቸውና የሚያደንቋቸው 'ሰውየው' ይሏቸዋል፡፡ ይህን ስም እሳቸውም ሳይከፋቸው ተቀብለውታል፡፡ የማይቀበሉት 'ፊውዳሉ' የሚለውን ስማቸውን ነው፡፡ ፊውዳሉ የሚሏቸው ለእሳቸው ማጎብደድ የማይወዱ የሰውየው የማይጠረቃውን አሞግሱኝ፣ ቅዱስ ቅዱስ፣ አክብሩኝ ባይነታቸውን የማይቀበሉ ሰዎች ናቸው፡፡ ያም ሆነ ይህ በቤተ ክርስቲያን ፖለቲካ በጣም የሚመሰጡ ፖለቲካውንም የሚያውቁ ግን ደግሞ በጣም ተንኮለኛና መሰሪ ናቸው፡፡ ሰውየው፡፡

ሰውየው እና ክብሮም በዶላር በሚከፈል የቀን አበል፤ የአውሮፕላን እንዲሁም የሚቆዩበት ዘመናዊ ሆቴል ሙሉ ለሙሉ በተሐድሶው ሕቡዕ ቡድን ተችለው ነው አሜሪካ የተገኙት፡፡ ሌላው የመርሐዊ የፍቅር ጓደኛው ሪቢዮ አለ፡፡ ከእንግሊዝ ደግሞ ቶኒ መጥቷል፡፡ ከዲሲ ለዓለም መጥቷል፡፡ እነዚህ ሰዎች ብቻ አይደሉም ተሐድሶውን የሚያፋጥኑት፤ ነገር ግን በእነዚህ ሰዎች ትላልቅ ውሳኔዎች አማካኝነት ነገሮች ወደ ተግባር መቀየር ይቻላል፡፡



CamScanner

## ምዕራፍ ፴፪

## አዲስ አበባ-ጀሞ

ሮዳስ ከመኝታ ቤቱ ተወርውሮ ወጣና ሳሎን ቤት ገባ። ሮዳስ በፍጥነት የቴሌቭዥኑንና የዲሹን ሶኬት ሰካና ከቴሌቪዥኑ ፊት ለፊት ከሚታይበት ካለ ሶፋ ላይ ተቀመጦ ባለ አርባ ስምንት ኢንች ሶኒ ቴሌቪዥኑ ላይ ሪሞት ኮንትሮሉን ሰንዘር አድርጎ ጣቢያውን ቢቢሲ ላይ አደረገው።

የቢቢሲ የቴሌቪዥን ጣቢያ ላይ የነ ሰንፔር ቤት ይታያል። ሰፊ ጥቁር ድንኳን በቤቱ ውስጥ ተጥሏል፤ በድንኳኑ ውስጥ ምርር ያለ የደቦና የተናጠል የለቅሶ ድምጽ ይሰማል። "ኢትዮጵያዊው ታላቅ ፓስተር በሰው ተገደለ!" ይላል ከቴሌቪዥኑ ስር ያለው ጽሁፍ። ዜናውን የምትዘግበው እንስት ኢትዮጵያዊ ነች። የእንግሊዘኛ ዘዬው ወደ እንግሊዞች የአነጋጋር ቃና ይወስደዋል።

ሪፖርተሯ ቢጫ ቲሸርቷ ላይ ጠበብ ያለ ጥቁር ኮት የለበሰች ሲሆን ጸጉሯን ፔስትራ ተሰርታዋለች፤ አፍንጫ ጎራዳ ስትሆን፤ ቀይ ሊፒስቲክ የተቀባው ከንፈሯ ትንሽ ሰፋና ወፈር ይላል። ከነ ሰንፔር ቤት በር ላይ ሆና እየዘገበች ሲሆን ሴቶች ነጠላ እያዘቀዘቁ እየጮሁ፤ ወንዶች ደግሞ እጃቸውን አጣምረው ፊታቸውን ቅጭም አድርገው እነ ሰንፔር ቤት ሲገቡ ይታያል።

"...ፓስተር ናፍያድ ከቀናት በፊት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ በስብከታቸው አቅርበው ነበር። ሞታቸውም ይህን ጥሪ አስመልክቶ ሊሆን ይችላል የሚሉ አስተያየት ሰጪዎች ይበዛሉ። ምክንያቱም ከጥንታዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የአጸፋ ምላሽ ከአንድ ቀን በፊት የተሰጣቸው ሲሆን ያንን ተከትሎም ፓስተር ናፍያድ ትናንት ከምሽቱ አምስት ሰዓት ላይ በመኪናቸው ውስጥ ተገድለው ተገኝተዋል።"

ካሜራው ዞረና የፓስተር ናፍያድ ልጅ ማዕረግ በቴሌቪዥኑ መታየት ጀመረ። ሮዳስ ደነገጠ። ያውቀዋል። ለኦርቶዶክስ ያለው ጥላቻና ንቀት በጣም ከባድ ነው። አሁን ደግሞ አባቱ ሞቶበታል። 'ስለዚህ በዚህ ስሜትን በሚያስቆጣ፤ ራስን መቆጣጠር በማይቻልበት ሰዓት እንዲህ ያለ ቃለ ምልልስ ማድረግ አልነበረበትም' አለ ሮዳስ ለራሱ እያጉተመተመ። ማዕረግ ፊቱ ላይ ቁጣና ቁጭት ይነበብበታል።

ጋዜጠኛዋ ማይክራፎኑን ወደ ማዕረግ ፊት አስጠግታ "በአባትህ ሞት እግዚአብሔር ያጽናህ እያልኩ። አባትህን ማን ሊገላቸው ይችላል ብለህ ታስባለህ?"

የማዕረግ ፊት በለቅሶ ብዛት ያበጠ ይመስላል፤ ድምጹም ጎርንቷል፤ ከላዩ ላይ ሰማያዊ ጥለት ያለው ጋቢ ደርቧል፤ ጋቢውን ወደ ትከሻው ሳብ ሳብ እያደረገ



CamScanner

ማውራት ጀመረ "አባቴ ማንንም አያስቀይምም፤ ከማንም ጋር ጸብ የለውም፤ ቢኖረው እንኳ ቢበድልም ቢበደልም ይቅርታ ከመጠየቅ ወደ ኋላ የማይል ነው። አባቴ የተገደለው በቅርቡ በለቀቀው ቪዲዮ አማካኝነት ነው። ስለዚህም አክራሪዎች ገድለውታል ብዬ አስባለሁ። ለቪዲዮው መልስ የሰጡት የማኅበረ ቅዱሳን አባላት ናቸው። ስለዚህ..." ሮዳስ የተቀመጠበት ሶፋ አፉን ከፍቶ ቢውጠው ደስ ባለው። ደነገጠ እንዲህ በድፍረት ይናገራል ብሎ አላመነም ነበር። ግን አደረገው።

ሮዳስ ከድንጋጤው ሲነቃ ማዕረግ ንግግሩን ሲጨርስ ሪፖርተሯ መናገር ጀምራለች "ፓስተር ናፍያድ በወንጌላውያን አማኞች ዘንድ በጣም የታወቁና የተወደዱ መንፈሳዊ መምህር ሲሆኑ የአንድ ወንድ ልጅና የአንድ ሴት ልጅ አባት ነበሩ።"

ሮዳስ ብርድ ብርድ አለው። አላማው አሁን ግልጽ እየሆነለት መጥቷል። 'የምር በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስርስቲያን ላይ ሙሉ ለሙሉ ጦርነት ታውጇል' አለ። ሰንፔር ከሳምንት በፊት ለሮዳስ ነግራው ነበር። "አባቴ አይደለም፤ ይህን ያደረገው ትንሽ ታገሰኝ፤ ወዳጆችህንም እንዲታገሱ አድርግ። እኔ አጣራለሁ። ከዚያ በኋላ የፈለጋችሁትን ማድረግ ትችላላችሁ" ብላው ነበር። ሮዳስ በድንጋጤ ተውጦ ስልክ ለመደወል ወደ መኝታ ቤቱ ዘው ብሎ ገባና ስልኩን ብድግ አድርጎ ወደ ሰንፔር መደወል ጀመረ።

------//------

## ኢትዮጵያ አዲስ አበባ

የፌስአልጎስ የስራ አስፈጻሚ አባላት ለስብሰባ ተቀምጠዋል። ሁሉም ፊት ላይ ድንጋጤና ቁርጠኝነት ይነበባል። መሸነፍን የሚፈቅዱ አይመስሉም። ለአላማቸው ምንም ነገር ከመክፈል ወደ ኋላ የሚሉ አይደሉም።

ሐዊ ሳቅ አለችና ስርጉድ ጉንጯን ይበልጥ አሰርጉዳ ቀዳሚውን ንግግር ማድረግ ጀመረች "እየተቀደምን ነው። ይህን ሁሉ ያደረጉት በእቅድ ነው። አሁን አላማቸው ግልጽ ነው። ሊያጠቁት የፈለጉት ማኅበረ ቅዱሳንን ነው። የፓስተሩ ልጅ ቢቢሲ ላይ ባደረገው ቃለ ምልልስ ላይ ጣቱን የቀሰረው ማኅበረ ቅዱሳን ላይ ነው። አበጋዝንም የማኅበረ ቅዱሳን አባል አድርገውታል። ይህም ትንሽ ለአበጋዝ ሕይወትም አስጊ ነው።"

አበጋዝ ስለ እሱ ስለተነሳ የመናገር ተራውን ወሰደ "አሁን አሁን በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለቤተ ክርስቲያኗ መቆርቆር ያሳየ፤ ቤተ ክርስቲያኗ የቀደም ትውፊቷን፣ አስተምህሮዋን ትጠብቅ ያለን ሁሉ ማኅበረ ቅዱሳን ነው ማለት በጣም እየተለመደ ነው። ይህ በአንድ ጎኑ ጥሩ ነገር ቢሆንም በሌላ ጎኑም ጥሩ አይደለም።

ማኅበረ ቅዱሳን የራሱ የሆነ እንዳችም አስተምህሮም ሆነ አቋም የለውም። አስተምህሮውም ሆነ አቋሙ የቤተ ክርስቲያኗ ነው። ስለዚህ አንድ ሰው ለቤተ ክርስቲያኗ ሲወግን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እንጂ ማኅበረ ቅዱሳን መባል የለበትም። ይህን ደግሞ የሚሰሩት ተሐድሶዎች ሆን ብለው የራሳቸውን ጎራ በኦርቶዶክስ ውስጥ ለመፍጠርና ቀድመው ለተነሱለት የምንታዊነት ባህሪ ሲያጋልጡን ነው። ወይ ተሐድሶ ወይ ማኅበረ ቅዱሳን የሚል ሁለት አንጃ በቤተ ክርቲያኗ ውስጥ ለመፍጠርና ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሚለውን አስተምህሮና የአንድነት ማዕከል ለማፍረስ ነው።"

አደይ ከበረች ከአበጋዝ አፍ ነጥቃ ንግግር የጀመረችው "እዚህ ላይ ማኅበረ ቅዱሳንን የምትቀፍበት ነገር አለኝ። በእርግጥ ማኅበረ ቅዱሳን ለቤተ ክርስቲያን የሰራው መልካም ነገር ሁላችንም ስለምናውቅ ከአድናቆቱ ይልቅ ቢስተካከል የምለውን ልናገር። ተሐድሶዎች ሆን ብለው ማኅበረ ቅዱሳን እና እኛ እያሉ ሲከፋፍሉ ዝም ሊል አይገባም ነበር።" ብዙ ጓደኞቿ ማኅበሩን በጣም ሲያሞላት ትሰማለች። አንዳንዶቹ የምታምናቸውና ለቤተ ክርስቲያን መልካም ያስባሉ የምትላቸው ናቸው።

"ነው ሁሉ ፊቱን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲያዞር እንጂ ወደ ማኅበሩ እንዳይሆን ጥረት ማድረግ ይኖርበታል። ይገባኛል የሚሰራው ስለቤተ ክርስቲያን ነው፤ እየተከፈለ ያለውን ዋጋ ሳላውቅ ቀርቼ አይደለም። ቢሆንም ሰዎች አንዳንዴ ቤተ ክርስቲያንን ትተው ማኅበሩ ላይ ያንጣጥራሉ፤ ይህ ማኅበሩን የማምለክ አካሄድ እንዲያስተካክሉ ማድረግ አለብን።

"ተሐድሶዎች እኛን ለማጥፋት ቢሔዱበት ልክ እኛ ደግሞ ቤተ ክርስቲያናችንን ለመጠበቅ ሌሎች ከሔዱበት በላይ መሄድ ግድ ይለናል። አንዳንዶችን ትንሽ እንክዋዕቤ፤ ትኩረትና አስረጂ በማጣት እያጣናቸው ነው። ሩቁ ላይ ስናተኩር የቅርቦቹን ካጣን ውኃ ቅዳ ውኃ መልስ እንዳይሆንብን እፈራለሁ። ሌሎች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመለሱ ተጋድሎ እያደረግንና ትልቅ ዋጋ ስንከፍል በተቃራኒው በትንሽ ዋጋ ልናተርፍ የምንችላቸውን እያጣን ሊሆን አይገባም።" አለች አደይ ፊቷን ኮስተር አድርጋ።አበጋዝ ጭንቅላቱን በመጠኑ በመዳፉ ዳሰስ እያደረገ የአደይን ንግግር እያዳመጠ ነው።

"ሌላው ቤተ ክርስቲያኗ ኢየሱስ አትበሉ፤ ብትሉ ወዮላችሁ የምትል በማስመሰል መዝሙርና ስብከት ይሰቃሉ። ቤተ ክርስቲያኗ ላይ ያልነበረና ከቀኖናዋና ከዶግማዋ ውጪ የአስተምህሮና የዝማሬ ለውጥ አምጥታችኋል ሲባሉም 'ኢየሱስ ስላልን ተሐድሶ ተባልን' የሚለውን ማምለጫ በተደጋጋሚ ይጠቀሙበታል። ውጤትም አስገኝቶላቸዋል።

"ለዚህም ራሳቸው ከፍተው ከሚያስተዳድሩት ድረገጽ አልፎ አንዳንድ የፕሮቴስታንት ድረ ገጾችና ምእመናን ጭምር 'ኦርቶዶክስን ያነቃቁ፤ የገባቸው ክርስቲያኖች፤ የወንጌል አርበኛ፤ በወንጌላውያንና በኦርቶዶክ መካከል ያለውን ድንበር ያጠበቡ፤ ፕሮቴስታንትን ከኦርቶዶክስ ጋር ያገናኙ ድልድዮች፤ ኢየሱስን በጥልቅ የሚያውቁ... እያሉ አስተምህሮቻቸውንና ዝማሬያቸውን በራሳቸው ድረ ገጽ እየለቀቁ ለሕዝብ እንዲደርስ ያደርጋሉ።"

አበጋዝ አደይን ሲያያት ንግግሯን እንደጨረሰች በዐይኗ ምልክት ሰጠችው። አበጋዝ አየር በአፍንጫው ስቦ ወደ ሳንባው አስገባና በድጋሚ ንግግር ጀመረ "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኢየሱስ መባል የተጀመረው ከሺኅ አመታት መቋረጥ በኂላ አሁን ከሚሊኒየሙ ጀምሮ እያስመሰሉት ነው። በዚህ አካሄድ ሁለት ነገር ተጠቃሚ ሆነዋል። አንደኛው ደርሶ የኢየሱስ ዋስ ጠበቃ በመምሰል በኢየሱስ ስም ተደብቆ የጥፋት ስራን መስራት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ስለ ኢየሱስ መዘመርና መስበክ ጥሩ ሆኖ ሳለ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ግን በጻድቃን ቅዱሳን ተራዳኢነትና አማላጅነት ማመኗ እሙን ነው። እነዚህን ጻድቃን ቅዱሳንንም በኢየሱስ ተክታ ሳይሆን ሁሉንም ያወቀችው በኢየሱስ ስለሆነ እነሱንም ጨምራ እንደምትዘክርና እንደምታከብር ግልጽ ነው።

"ተሐድሶዎች የቤተ ክርስቲያኗን የቀድሞ አስተምህሮ ጠብቁ አስጠብቁ ሲባሉ 'ከለከሉኝ ስሙን እንዳልጠራ፤ ኢየሱስ ስላልኩ ተሐድሶ ተባልኩ፤ በኢየሱስ አልደራደርም' ወደ ሚል አላስፈላጊ ንትርክ ውስጥ ይገባሉ። ይህ አካሄድ በጋዜጠኞች ቋንቋ አጀንዳ ሴቲንግ (Agenda setting) እና ፍሬሚንግ (Framing) የሚሉት ነው። ቤተ ክርስቲያኗን ኢየሱስን የማታውቅና የስሙ ተቃዋሚ ነች የሚል ፍሬሚንግ ወይም የሌለን ነገር አስመስሎ ታርጋ የመለጠፍ ስራን ሆን ብለው በመዝሙርና በስበከታቸው ሰሩ። ቀጠሉና አጀንዳውን ኢየሱስ ብቻ አደረጉትና ኢየሱስን ለኦርቶዶክስ በማስተማር ማደስ የሚል ቀና የሚመስል ካባ ለራሳቸው ይለብሳሉ።" ከአበጋዝ ፊት የተቀመጠችው አደይ በቀኝ እጇ ጣቶች ከንፈሯ ላይ ያለውን ጥቁር ነገር እየነካካች አበጋዝን በአትኩሮት እያዳመጠች ነው።

"ቅዱሳን አያስፈልጉም ኢየሱስን ይጋርዳሉ፤ ስለዚህ ስለ ቅዱሳን መዘመር፤ ማርያምን ማመስገን አስፈላጊ አይደለም ብለው በገሀድ ባይናገሩም ነገር ግን አሁን ኢየሱስን ለማታውቀው ኦርቶዶክስ ኢየሱስን ማስተማር ቀዳሚ አጀንዳ ስለሆነ ለሌላው ለትርፉ ጊዜ የለንም በሚመስል አኳኋን ከትውልድ አእምሮ ውስጥ ማርያምን፤ ቅዱሳን ጻድቃንን በዝምታ ተንኮል በማጥፋት ላይ ናቸው።

"ከዚህም በተጨማሪ ሌላ የምንታዌነት አስተሳሰብ በትውልዱ ውስጥ አመጡ። ትክክለኛውን የኦርቶዶክስ አስተምህሮ ይዞ የሚዘምረውንና የሚንቀሳቀሰውን ማርያም ብቻ (only Marry) የሚል ተቀጽላ በመስጠትና በማሸማቀቅ ራሳቸውን ደግሞ

ኢየሱስ ብቻ (only Jesus) በማለት ሁለት ጎራ ፈጠሩ። ያለምንም ምንታዌ አስተሳሰብ ሁሉንም በአግባቡ አውቃ የምታደርገውን ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በሁለት ጎራ ለመክፈል ነው።" አበጋዝ እንደ ለመደበት ጸጉሩን ወደፊት ገፋ አድርጎ ንግግሩን ቀጠለ።

"እንዲህ ያለ የጎራ አመዳደብ በጋዜጠኞች ቋንቋ ስፓይራል ኦፍ ሳይለንስ (Spiral of silence) ለሚሉት ችግር ያጋልጣል። ምን ማለት ነው? ሰዉ አየሩ ላይ ካለው ሀሳብ በተቃራኒ ሌላ ሀሳብ ቢኖረውም ትክክለኛ የሚለውን ሀሳብ ለመግለጽ ይፈራል። ዋና የሚፈራበት ምክንያት እሱጋ ካለው እውነት በተቃራኒ የሆነው ሐሳብ ብዙ ደጋፊ ካለው እኔን ያገሉኛል ብሎ ስለሚሰጋ ዝምታን ይመርጣል።

"ተሐድሶዎች አየሩን በመዝሙር በስብከት በተደጋጋሚና ለረዥም ጊዜ በመሙላት ትክክል እንደሆኑ በማስመሰል በሰዎች ሥነ-ልቦና ውስጥ እነሱ የሚያቀነቅኑት የብዙሀኑን ሀሳብና እውነት በመሆኑ እነሱን መቃወም ብዙውንና እውነትን መቃወም በማስመሰል ብዙ ሰው ዝምታን እንዲመርጥ እየተገደደ ነው። ተሐድሶዎች ዝምታንም እንደ ድጋፍ ነው የሚቆጥሩት።"

## ምዕራፍ ፴፫

## ካሊፎርኒያ-ሎስአንጀለስ

ውይይቱ በእንግሊዝኛ ቢሆንም እንግሊዘኛ ለሚያዳግታቸው ንግግሩን ወደ አማርኛ የሚቀይር የጆሮ ማዳመጫ እንዲሰኩ ተነግሯቸዋል። ይህ ምቹና ውብ ሆቴል እንዲህ መንፈሳዊ ነክ ውይይት ለማድረግ ብዙም ልምዱ የለውም።

የሆቴሉ አዳራሽ በእውቅ ዲዛይነር ተጠቦና ተጨንቆ የተዘጋጀ ስለሆነ ክፍሉ አንዳች ደስታን ይሰጣል። ጠረጴዛው የለበሰው ጨርቅ ከግርግዳው ቀለም ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሐምራዊ ቀለም ነው። ለስለስና አንዳች ጣእም ያለው የቤት ውስጥ ሽቶ የክፍሉን አየር ሞልቶታል። በሽንበቆ እንጨት በቄንጥ በተሰራ የአበባ ማስቀመጫ ውስጥ ተደርጎ በየግርግዳው ጥጋጥግ የተሰቀለው የተፈጥሮ አበባ ፍቅር ፍቅር ይሳል። የመሬቱ ንጣፍ ግራጫ ቀለም ያለው ሲሆን ንጹህ ነው።።

ሰውየው የቤተ ክርስቲያን ፖለቲካ ይውደዱ እንጂ ያን ያህል የሚያወላዳ እውቀት እንደሌላቸው ከዛሬው ውይይት ተሰምቷቸዋል። በተለይ ደግሞ ኦርቶዶክስ ውስጥ ፀጋ፣ ቅባትና ተዋሕዶ ስለሚባሉት እምነቶች ያላቸው እውቀት ውስን በመሆኑ ተናደዱ። ባህሪያቸው ሆኖ በእውቀት መበለጥን የሚቀበሉት አይደለም፤ ቢሆንም ምንም ማድረግ አይችሉም ዛሬ ተበልጠዋል። ቀድመው ይህን ነገር በደንብ አውቀውት ቢሆን ኖሮ ኦርቶዶክስን እንደ መከፋፈያ ይጠቀሙበት ነበር። ሰውየው።

መርሐዊ እንደተለመደው በመጽሐፍት የታጨቀ ኮምፒውተሩን ከፍቶ ስለጸጋ፣ ቅባትና ተዋሕዶ ልዩነት እያብራራ ነው "ብዙ ጥናቶች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ውስጥ ቅባት፣ ጸጋና ካራ የሚል ክፍፍል የመጣው በአጼ ሱስንዮስ ዘመነ መንግስት ካቶሊክ የአገሪቱ ብሔራዊ ሃይማኖት እንዲሆን ከታወጀ በኋላ ነው ይላሉ። ካቶሊክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሃይማኖት ነው' ተብሎ ከታወጀ በኋላ ኢትዮጵያውያን እርስ በእርስ ኦርቶዶክስና ካቶሊክ በሚል የሃይማኖት ልዩነት ጦርነት ውስጥ ገቡ።

"ይሁን እንጂ አጼ ሱሰንዮስ ታመሙና 1625 ዓ.ም. ሕይወታቸው ሲያልፍ ልጃቸው ፋሲል ነገሰ። ፋሲል ሲነግስ ለአባቱ መሞት ዋነኛው ምክንያት፤ አባቱ የራሱንም የአገሪቱንም እምነት ከኦርቶዶክስነት ወደ ካቶሊክነት ስለቀየረ ነው ብሎ ስላመነ ኦርቶዶክስን መልሶ የሀገሪቱ እምነት አደረገ።

"ቀጠለናም ከሮም እንደ ጳጳስ ሆኖ የመጣውን ሜንዴዝ አልፎንሱንና አብረውት የመጡትን አስራ ስምንት ሚሲዮናውያንን ከአገር እንዲወጡ አደረገ። አፄ ፋሲል አልፎንሱን በምጥዋ በኩል ወደ አገሩ ቢልኩትም ጸጋና ቅባት የሚል አስተምህሮ ግን ለኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አስተምሮ ነበር። የቅብዐትን ባህለ ትምህርት

ለኢዮስጣቴዎስ ዘሳንኪ ጊዮርጊስ ሲያስተምር፤ የጸጋን አስተምህሮ ደግሞ ለቆረንጩ ተክለ ሃይማኖት ዘጆር ገብርኤል አስተምሯል።"

--------//--------

## ኢትዮጵያ-አዲስ አበባ

ስብሰባው ተፋፍሟል። ልክ እንደ ሜዳ ቴኒስ ጨዋታ አንዱ ዝም እንደ ማለት ሲል ቀጣይ ተናጋሪ ከአፍ ቀብ አድርጎ ይቀጥላል። ቀጣይዋ ተናጋሪ የፌስአልጎስ ምክትል ሰብሳቢ ጠይሟና ረዥሮምና ዘናጯ ኢንሴኔ ነች።

"አበጋዝ አሁን ያነሳኸው ሃሳብ ማለፊያ ነው። አጀንዳ ሴቲንግ (Agenda setting)፣ ፍሬሚንግ (Framing) እና ስፓይራል ኦፍ ሳይለንስ (Spiral of silence) የሚሉትን የመገናኛ ብዙሀን ዘዴዎች እኛም ልንጠቀምበት ይገባል። አሁን እንዳልከው የጥቂቶቹን ሀሳብ የብዙ በማስመሰል፤ ሰዎች አንድ እንዳይሆኑ መንታ መንታ የሆኑ ሃሳቦች እየወለዱ ለክፍፍል እየዳረጉን ነው። ስለዚህ መልሰን በዚሁ መንገድ ልናጠቃቸው ይገባል።

"ማኅበራዊ ድረገጾን ጨምሮ ቴሌቪዥን እና ሬዲዮን ተጠቅመን ሀሳባችንና አላማችንን በደንብ ማስረዳትና እንገለሳለሁ ብሎ የፈራውን ብዙ ሰው እንደማይገለልና ሀሳቡ ትክክል እንደሆነ ልናሳየው ግድ ነው። ስለዚህ ተሐድሶዎች በሄዱበት ልክ ሳይሆን ከእነሱ በበለጠ ሁኔታ ልንሔድ ግድ ነው።" ሁሉም የፌስአልጎስ አባላት በመስማማት አንገታቸውን ነቀነቁ።

በመቀጠል መናገር የጀመረው በፊሎሎጂ የፒኤች ዲግሪ ያለውና የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ መምህር እንዲሁም የፌስአልጎስ ስራ አስፈጻሚ ገመዳ ደመቀ ነው። አበጋዝ፣ አደይ እና ኢንሴኔ ክፍ አድርገውት የነበረውን የተሰብሳቢውን ስሜት ገመዳ ረጋ ብሎ ንግግሩን ጀመረ።

"አሁን ያላችሁት ሀሳብ ጥሩና በፍጥነት ወደ ትግበራ የምንገባበት ቢሆንም ግን ሌላ መስዋዕትነት የሚጠይቅበት ሰዓት መጥቷል። በፓስተር ናፍያድ ሞት የተነሳ ማኅበረ ቅዱሳንን ሊያግዱት ወይም ሊያፈርሱት ይችላሉ። ስለዚህ ከዚህ ነገር ልንታደገው ይገባል። እስከ አሁን ድረስ የፓስተሩ ገዳይ አልታወቀም። ነገሮች ሁሉ ደግሞ ወደ ማኅበረ ቅዱሳን እያመሩ ነው።

"ከሰው ግድያ ደግሞ ማኅበረ ቅዱሳን ተፈረጀ ማለት ቤተ ክርስቲያንን ለማሸማቀቅና ለመምታት በደንብ ይጠቀሙበታል ማለት ነው። ምክንያቱም ቀድመው ኦርቶዶክስን ሁሉ ከማኅበረ ቅዱሳን ጋር የማገናኘት ስራ ስለሰሩ። ስለዚህ እኔ ነኝ ገዳይ ብዬ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ልሄድ ወስኛለሁ" አለ የፌስአልጎስ ስራ አስፈጻሚ።



CamScanner

ሁሉም ደነገጡ። ያውቁታል የሁለት ልጆች አባት ነው። በስራውም የተከበረ የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ መምህር ነው። ከፈላስፋነት አባት ውጪ ያን ያህል የጎላ ጉዳይ ጠለቅ ተብሎ የማይታወቅ የተረጋጋ ሰው ነው።

-------//-------

## አዲስ አበባ

ዳንኤልና ዘላለም ቦሌ አካባቢ ከነሙሉ እቃው በተከራዩት ቤት ውስጥ ናቸው። በእርግጥ የቤቱ ባለቤት ዘላለም ነው። ቤቱ ባለሁለት ፎቅ ሲሆን ውስጡ ከዱባይ የመጣ ምንጣፍ ተነጥፎበታል። በግድግዳው ላይ የተሰቀለው ውብ ሥዕል በዘዘ ጎደፍ አልወጣ ከተሰራው ግድግዳ ጋር ሕብር ፈጥሮ ለቤቱ ለየት ያለ ድባብ ሰጥቶታል። ነጭ እና ሌላ ቅርጽ ያለው ሶፋ ከወለሉ ምንጣፍ ጋር ሕብረት ፈጥረው ቤቱን እንከን የለሽ አድርገውታል።

ዘላለም በዚህ ቤት ውስጥ ከብዙ ቆንጆዎች ጋር ተመንሸራሽሮበታል። በመንፈሳዊ ኮሌጅም ሆነ ከዚህ ውጪ ዘላለም ብዙ ሰው ያውቃል፤ ብዙ ሰዎችን ደግሞ ዘወር ያደርጋል፤ ተብሎ ስለሚወራ ሊያገኙት የሚፈልጉት ሴትም ሆነ ወንዶች ብዙ ናቸው።

ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ ብዙ ሴትና ወንድ መንፈሳዊ ልጆችን ያተዋውቅና ለደቂቀ እስጢፋኖስ አባትነት ይመለምላል። አንዳንዶች አሁን ታዋቂ ዘማሪያን እና ሰባኪዎች ሆነዋል። ከነዚህ ውስጥ የሚያስገርም ባህሪ ያላቸው ሰዎች ነበሩ። አንዳንዶቹ ከመንፈሳዊ እውቀታቸው ይልቅ ለወሲብ ያላቸው ጥልቅ ስሜት፤ ለገንዘብ ያላቸው ፍቅር፤ በቅጽበት ሕይወታቸውን ለመለወጥ ምንም ነገር ከማድረግ ወደ ኋላ የሚሉ አልነበሩም።

በደቂቀ እስጢፋኖስ ሕቡዕ ቡድን መዋቅር መሰረት መጀመሪያ የተዋወቃቸውን ሰዎች ካሉት ስምንት ማኅበራት ውስጥ የወጣቶች ማኅበር ከሚባለው ውስጥ ያስገባቸዋል። ከዚያም እንደተሰጥዎቻቸው እድሉን ያመቻቻል። እንዲሁም እድገትና ክፍታ የሚያሳዩ ሰዎች ሲኖሩ ወደ ዋናው የደቂቀ እስጢፋኖስ አባትነት እንዲቀላቀሉ ያደርጋል።

ወንዶቹም ሴቶቹም ብዙ ጊዜ ስልጠናውን የሚወስዱት ቤሉራሞና በጎሩም ነው። ከዚያም ጥሩ አቀባበልና ተሰጥኦ ያላቸው ኬንያ ይሄዱና በቶጊ፤ በሩብዩና በመርሐዊ እምነትነት ከፍ ያለ ስልጠና ይሰጣቸዋል። ይህኔ ነው አንዳንዶቹ ግብረ ሰዶማዊነትን የሚከተሉት። መርሐዊና ሩብዩ ግብረ ሰዶማዊ ስለሆኑ ግብረ ሰዶማዊነትን በልጆቹ ውስጥ ያሰርጻሉ።

መርሐዊና ሩቢዮ በቀላሉና በቶሎ ግብረ ሰዶማዊ መሆናቸውን አይገልጹም። ግን ቀስ በቀስ ትምህርቱን ከመንፈሳዊ ይዘት ጋር እየቀላቀሉ እያዋዙ ያስተምሯቸዋል። ሩቢዮና መርሐዊ ግብረ ሰዶማዊነታቸውን ለመግለጥ ለተማሪዎቹ ብዙ የሥነልቦና መደላድል፣ የቃል ትምህርት እንዲሁም በትልቅ የቴሌቪዥን እስክሪን በምስል የታገዘ የተግባር ክህሎት ይሰጣቸዋል።

ከዚያም ተማሪዎቹ ግብረ ሰዶማዊነትን ተቀብለው ከራሳቸው ካዋሐዱት በኋላ ሙሉ ለሙሉ የሥነ ልቦና ዝግጅቱን ሲጨርሱና በቅርብ ያለ ምሳሌ በሚሹበት ሰዓት መርሐዊ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ፓትርያርክ የሚለብሱትን ልብሰ ተክህኖ አድርጎ በእጁ በትረ ሙሴውን ጨብጦ ከፊት ለፊታቸው ይመጣል። ሩቢዮ ደግሞ ጡንቻውን የሚወጥር ቲሸርት ከላዩ ላይ ደርቦ ይመጣና ከመርሐዊ ጋር ከንፈር ለከንፈር መሳሳም ይጀምራሉ።



CamScanner

## ምዕራፍ ፴፩

## አሜሪካ-ካሊፎርኒያ

ሰውየው ጆሯቸው ከምንጊዜውም በላይ ቆሞ ነው የሚያዳምጡት፡፡ ሰውየው የልዩነት አቀንቃኝ ስለሆኑ በተለይም የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችን ቅስም ለመስበር ስለሚፈልጉ ይህን ታሪክ መስማታቸው ራሱ ደስ የሚል ፈንጠዝያ ውስጥ ከቷቸዋል፡፡

"የኦርቶዶክስ ሃይማኖት የአገሪቱ ብሔራዊ ሃይማኖት ሆኖ በአጼ ፋሲል ጊዜ ቢመሰስም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ልዩነቶች ይመጡ ጀመር፡፡ በተለይ ቅብዐትና ካራ ከአጼ ሱስንዮሥ እስከ አጼ ኢዮአስ ድረስ ለትላልቅ ክርክሮች ተቀምጠዋል፡፡ በዚህ የተነሳም አንዳንዴ ካሮች፣ አንዳንዴ ደግሞ ቅባቶች ቤተ ክርስቲያንን እየተፈራረቁ ሲቆጣጠሩ ነበር፡፡ በተለይ ከአጼ ተክለ ሃይማኖትና በሣልሳይ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ማለትም በ1698 ዓ.ም. እስከ 1713 ዓ.ም. የቤተ ክርስቲያኗ ሥልጣን በቁጥጥራቸው ስር ነበር፡፡

መርሐዊ በጽጽስና ስሙ አቡነ ሰላማ ስለ ካራ ገለጻውን እያደረገ ነው "ካራ አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው እምነት ነው፡፡ ካራ ማለት ከቃሉ እንደምንረዳው ቢላዋ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ስለት በአንድ ጎኑ ብቻ ነው፡፡ እንደ ካራ ሁሉ የዚህ እምነት ተከታዮች ስለ ኢየሱስ ሥጋው ሲያስተምሩ በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት፣ በሊቃውንት አባቶች ስለ ሰውነቱ የተነገረውን በመተው አምላክነቱን ያጎድሉታል፡፡ ብዙ ጊዜ ኢየሱስን በአምላክነቱ እንጂ በሰውነቱ አያውቁትም፡፡

"ለዚህም ነው ተቀናቃኞቻቸው ጸጋ እና ቅባት 'ካራ' የሚሏቸው፡፡ በስማቸው ጉዳይ ሌላም ነገር ይባላል ይህም የካራ ወገኖች 'ከዚህ እምነት ውጡ የሚለን ኃይል ቢመጣ እንኳ አንገታችንን ለካራ እንሰጣለን' ስለሚሉ ነው የሚል ነገር ቢኖርም በተቃራኒው ከቅባትና ከጸጋ ጋር መስማማት ሲያቅታቸው ካራ ስለሚያነሱ ነው ካራ የተባሉት የሚሉም አሉ፡፡ ያም ሆነ ይህ ካራ የተባለው አስተምህሮ አሁን ተዋሕዶ የሚባለው እምነት ነው፡፡

ሰውየው 'ካራ' የሚለው ቃል ከአዎንታዊ ይልቅ አሉታዊ ትርጉም ስላለው እንደሚጠቀሙበት ስለተሰማቸው በማስታወሻ ደብተራቸው ከተቧት፡፡ ክብሮምም እንደተለመደው ባህሪው ሰውየው የሚጽፉትን እየተከተለ መጻፍ ጀመረ፡፡ ለዓለም በአንክሮ እያደማጠ ነው፡፡ ሩቢዮና ቶኒ ጎን ለጎን የተቀመጡ ሲሆን፡፡ ሩቢዮ እጁን አጣምሮ መርሐዊን ዓይን ዓይኑን በስስት ያየዋል፡፡ ቶኒ ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ፖለቲካ አሁን ከሚሰማው ታሪክ ጋር እያዳወረ ስለሚሰራው የነገር ሸማ እያደራ ነው፡፡

“የተዋሕዶዎች አስተምህሮ ያው እንደሚታወቀው 'ክርስቶስ በተዋሕዶ የባህርይ አምላክ ነው::' ማለትም አካላዊ ቃል የሰውን ባሕርይ ነሥቶ ስለተዋሐደ ከራሱ አካልና ባሕርይ ጋር አንድ ስላደረገው ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው' የሚል ነው።

“ቀጣዩ አስተምህሮ የቅብዐት ነው። የቅብዐት አስተምህሮ ሦስት አይነት ነው። እነሱም ቤተ ዘኢየሱስ፣ ቤተ አካለ ክርስቶስ እና ቤተ ጎሹ ይባላል። በአፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት የነበሩት ቤተ ዘኢየሱስ ሁለተኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ ስምንት ቁጥር ዘጠኝን ጠቅሰው 'የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቸር ስጦታ አውቃችኋልና፤ ሀብታም ሲሆን፤ እናንተ በእርሱ ድኅነት ባለ ጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሀ ሆነ።' የሚለውን ጥቅስ ጠቅሰው 'ቃል ስጋን በተዋሐደ ጊዜ የባህርይ ክብሩን አጣ፤ መንፈስ ቅዱስን ሲቀበል ወይም ሲቀባ ወደ ጥንት ክብሩ ተመልሶ በሰውነቱም በአምላክነቱም አንድ ወገን የባሕርይ ልጅ' ሆነ ይላሉ።

“ሌላኛው በቀዳማዊ አጼ ዮሐንስ ጊዜ የተነሱት ቤተ አካለ ክርስቶስ 'ቃል ከሥጋ ጋር በተዋሐደ ጊዜ የባህርይ ክብሩን አጣ' የሚለውን የነ ዘኢየሱስን አስተምህሮ ነቅፈው 'መጽሐፍ ተዋሕዶ መንታነትን አጠፋ ስለሚል ሥጋ በተዋሕዶ አንድ አካል ሆነ እንጂ የአምላክነት ክብርን አላገኘም፤ ነገር ግን በማኅፀን በመንፈስ ቅዱስ ሲቀባ ግን ክብር ተሳለፈለት፤ ተፈጥሮም ጠፍቶለት በቅብዐት የባሕርይ ልጅ ሆነ፤ የባሕርይ አምላክ ሆነ' ይላሉ።”

“ሌላኛው በአጼ ቴዎድሮስ ሁለተኛ ጊዜ የተነሱት እነ አራት ዓይና አለቃ ጎሹ የእነ አካለ ክርስቶስን አስተምህሮ ተቃውመው 'መጽሐፍ በተዋሕዶም በቅብዐትም ከበረ ስለሚል ቅብዐት ያለ ተዋሕዶ ብቻውን አያከብርም፤ ተዋሕዶም ያለ ቅብዐት ብቻውን አያከብርም። ስለዚህ በተዋሕዶና በቅብዐት በአንድነት የአምላክነትን ክብርን ክብሮ የባህርይ ልጅ ሆነ' ይላሉ።” ሰውየው ደስታቸውን ሊቆጣጠሩት አልቻሉትም። ይህም ቀድሞ በአደባባይ እንደ ፎከሩት 'የኦርቶዶክስ በኢትዮጵያ ላይ ያላትን ማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና ፖለቲካዊ ተጽእኖ በሌሎች እምነትና አማኞች መተካት' ሊሳካ ስለመሰላቸው ነው።

መርሐዊ ቀና ብሎ ሲመለከት ከተሰብሳቢዎቹ ውስጥ ሰውየው ብቻ በእርካታ እያዳመጡ ሲሆን ክብሮም ግር ያለው ይመስላል፤ ለዓለም ደግሞ 'እና ምን ይጠበስ?' እያለ የሚያዳምጥ ይመስላል። መርሐዊ በመጠኑ ፈገግ አለና ንግግሩን ቀጠለ።

“ሦስተኞቹ ደግሞ ፀጋዎች ናቸው። ፀጋዎች ሦስት ልደት ይባላሉ። 'አንደኛ ቃል እምቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት፤ ሁለተኛ ድኅረ ዓለም ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለ አባት በሥጋ ተወለደ፤ ሦስተኛ በማኅጸነ ማርያም በቅብዐት መንፈስ ቅዱስ የጸጋ ልደት ተወለደ' በማለት ያስተምራሉ።



CamScanner

“ቅባቶች የእነ ቤተ አካለ ክርስቶስ፣ ቤተ ጎሹም ሆነ ቤተ ኢየሱስ የሀሳባቸው ዋና ማጠንጠኛ ‘አብ ቀቢ፤ ወልድ ተቀቢ፤ መንፈስ ቅዱስ ቅባት’ የሚል ቀመር ይወጣዋል። ይህን ቀመር ተዋሕዶዎች ለወልድ በሥላሴ ውስጥ ዝቅተኛ ቦታ ያስጠዋል ብለው አይቀበሉትም። ‘ለልየ ቀባዕኩ ርእስየ’ (ራሴን እኔው ራሴ ቀባሁት) የሚል ጥቅስ ይዘው በቅባቶች ቀመር ምትክ ‘ወልድ ቀባኢ፤ ወልድ ተቀባኢ ወልድ ቅብዕ’ የሚል ቀመር አውጥተው ይከራከራሉ።

“ፀጋና ቅብአት ‘ሥግው ቃል የመንፈስ ቅዱስን ፀጋ ተቀበለ’ በሚለው አስተምህሮ አንድ ናቸው። ነገር ግን ቅብዐቶች ‘ክርስቶስ የመንፈስ ቅዱስ ቅብዐት መቀበሉ የባሕርይ ልጅ ለመሆን ነው ሲሉ’፤ ፀጋዎች ደግሞ ‘አዳም ያስወሰደውን የፀጋ ልጅነት ተቀብሎ ለመመለስ’ ነው በማለት ይለያያሉ።”

---------//--------

## ኢትዮጵያ-አዲስ አበባ

የፌስአልጎስ ሕቡዕ የመሰብሰቢያ አደራሽ በዝምታ አርምሞ ተመቷል። ብዙዎች የገመዳ ውሳኔ ያልጠበቁት የማይታመን ሆኖባቸዋል። ገመዳ ብዙ ስለማያወራ ብዙም ስለማንነቱ እንዳያውቁ ስላደረጋቸው መደነቅን ፈጥሮባቸዋል።

የመሰብሰቢያ ክፍሉን ጸጥታ “አይሆንም!” የሚለው የታንቱ ንግግር አደፈረሰው።

“...ይህማ አይሆንም ምን ማለት ነው? ለምንድነው ለልጆችህ ሰቀቀን የምትሆነው? ስለምንድነው ይህን የሚያክል ኃላፊነት ትተህ ራስህን ለመከራ የምትዳርገው? ባይሆን እኔ ሕይወትን ያልጀመርኩት ኃላፊነቱን እወስዳለሁ እንጂ እንዴት ነው አንተ የምትማገደው?” አለ ታንቱ እምባ እየተናነቀው።

ሐዊ ክው ብላ ደንግጣለች። ስለደነገጠች ነው መሰል ጉንጯ ራሱ መሰርጎዱን ያቆመ ይመስላል። በታንቱ እና በገመዳ ፍቅር፤ ከምንም በላይ ለቤተ ክርስቲያን ሕይወታቸውን ለመስጠት ያላቸውን ቁርጠኝነት ስታይ ደነገጠች። ክርስትና ከዚህም በላይ ዋጋ እንደሚያስከፍል በታሪክ ከቅዱሳን መጽሐፍት ላይ ብታነብም እንዲህ በዓይኗ ግን ‘እኔ ልሰዋ እኔ ልሰዋ’ ሲባል አልሰማችም።

አበጋዝም ይህ ፍቅር አስደንግጦታል። ሌሎችም የስራ አስፈጻሚ አባላትም የሚናገሩትን ቃላት አጡ። አበጋዝ ግን እንደምንም ልውጣ አልውጣ የሚለውን እንባውን አምቆ መናገር ጀመረ “እናንተ ምን በወጣችሁ ነው ዋጋ የምትከፍሉት፤ ያወራሁት እኔ፤ የሰበኩት እኔ፤ የደሰኮርኩት እኔ፤ እንዴት ተደርጎ ነው እኔ እያለሁ እናንተ ኃላፊነት የምትወስዱት?”



CamScanner

"አይሆንም!" አለ ታንቱ በድጋሚ። ሁሌም እንደሚያደርገው መሀል ኮላሩን ቀሬር ቀሬር እያደረገና "አይሆንም ምክንያቱም ብዙ ሰዎች አንተን የማኅበረ ቅዱሳን አባል ነው የሚያደርጉህ፤ ስለዚህ አንተ እኔ ነኝ ብትል ለማኅበሩ ሲሉ መከራ ትጠራለህ እንጂ የምታመጣው ለውጥ የለም። ትርጉም የለሽ መስዋዕትነት ደግሞ አንከፍልም። የምንከፍለው መስዋዕትነት በምድርም በሰማይም በረከት ቢያመጣልን መልካም ነው። ትናንት አውደ ምህረት ላይ ሰብከህ ዛሬ ገዳይ ብትባል አሁንም ለቤተ ክርስቲያናችን ውርደት ነው። እኛ የማንታወቀው ግን ምንም ችግር የለውም።" የመሰባሰቢያ ክፍሉ ለጥቂት ሰከንድ ጸጥ አለ።

ዝምታውን ለመስበር ያህል ገመዳ ንግግሩን ዳግም ጀመረ "ሁላችንም መስዋዕትነት ለመክፈል የሚያስችለን አይመስለኝም። ዘመኑ ዋጋ ያጠይቃል ስለዚህ ብንቀዳደም እንጂ መስዋዕትነቱ እንደሆነ ለእያንዳንዳችሁ አያቀርላችሁም። ስለዚህ እንደ ፊልጶስ ሰብሳቢነትም ቅድሚያ ኃላፊነቱን ልወስድ ግድ ነው። ከሰራዲያን ወዳ የምንግባረው ይህንኑ ነው። በዚያ ላይ ናፍያድን እወቀዋለሁ። ዩንቨርሲቲ በአንድ ወቅት ተምረናል። አንድ ዶርምም ኖረናል ስለዚህ ምን አገናኝቷቸው ገደለው ለሚለው ጥያቄም መልስ ይሰጣል። ስለዚህ ይህን ጉዳይ በዚህ እንዝጋውና ስለ ቀጣዩ ነገር እንወያይ።

"ይልቁንስ እኔ ዛሬ የጀመርኩትን ሰማዕትነት እናንተም ቀጥሉበት። ይህን ሰማዕትነት አስቴፋኖስ ብዬዋለሁ። አስቴፋኖስ ማለት እውነት፤ ከማናቸው በላይ ንፁህ፣ ቅዱስ ማለት ነው። ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን የምንከፍለው ዋጋ ንፁህ፣ ቅዱስና እውነት ብቻ ይሆናል። ስለዚህ ሰማዕቱ አስቴፋኖስን ጀመርኩት እንጂ የምትጨርሱት እናንተ ናችሁ።" ሁሉም ስለ ገመዳ ጽናትና ቁራጥነት ተገረሙ።

አበጋዝ ደግሞ 'ይህቺ ቤተ ክርስቲያን ዛሬም ልጅ አላት፤ ቅዱስ ያሬድን፣ ላሊበላን፣ ይምርሀን ክርስቶስን፣ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫን፣ አባ ቀውስጦስ፣ አባ ፊሊጶስ፣ አቡነ ኤጥሮስን፣ አቡነ ቴዎፍሎስን፣ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬን፣ ... የሚተካ ልጅ ዛሬም ተወልዷል።' እያለ ሰራሱ ሲያሰኩር ነበር ታንቱ ንግግር የጀመረው።

"ቀጣዩ መነጋገር ያለብን ነገር የጳጳሳት ምርጫው ላይ ነው። ምርጫው ላይ ባደረግነው ያላሰለሰ ጥረት ብዙ የሃይማኖት ህጸጽና የምግባር ችግር ያለባቸውን ከውድድሩ እንዲወጡ ማድረጋችን ይታወቃል። ነገር ግን አንድ ሰው ከመጨረሻዎቹ እጩ ውስጥ አለ። እኚህም አባ አወቀ አጥናፉ ናቸው። ሰውየው የሥነ ምግባር ችግር ብቻ ሳይሆን የተሐድሶው ቡድን ደጋፊና አባል ናቸው። እሳቸው ጳጳስ ከሆኑ አደገኛ ነገር ይፈጠራል። አንድ ነገር ብናደርግ መልካም ነው።"

አደይ የተናደደች ይመስላል፤ አንድ ጊዜ የሚያምረውን ሹርባዋን በእጇ ዳበስ አድርጋ ምን ማድረግ እንዳለብን ሁሉ ሊገባኝ አልቻለም። እንግዲህ ያንን ሁሉ ጸያፍ

ስራቸውን በማስረጃ አስደግፌን በሰውየው ላይ አዘጋጅተን ለአስመራጭ ኮሚቴው ሰጥተናል፡፡ አስመራጭ ኮሚቴው ለምን የመጨረሻው እጩ ውስጥ እንዲገኙ እንዳደረገ ሊገባኝ አልቻለም፡፡" አደይ ጠንካራ ጥሩ ጽናት አላት የምትባል የፌስአልጎስ ስራ አስፈጻሚ አባል ነች፡፡ ብዙዎች አበጋዝና አደይን ያመሳስሏቸዋል፡፡

"ከአሁን በኋላ ምንም ማድረግ አንችልም፡፡ ሌላ አማራጭ መጠቀም ይኖርብናል ሰውየው ጻጳስ መሆናቸው አይቀሬ ሆኗል ስለዚህ ቀጣዩ አላማችን መሆን ያለበት የሰውየውንና ያስመረጣቸውን አካል የነገ አላማ አውቀን አፋጣኝ ምላሽ ልንሰጥ ይገባል፡፡"

## ምዕራፍ ፴፰

ዘላለም ለመንፈሳዊ ጉዳይ የሚመጡ እንስቶችን ልቅ ወሲብ በማስተማር ይታወቃል፡፡ በሱ ያለፉት ሴቶች ብዙዎቹ ከእሱ ጋር አንሶላ ተጋፈዋል፡፡ በተለይ አንዷን መቼም አይረሳትም፡፡ አሁን ታዋቂ ዘማሪ ብትሆንም ለመጀመሪያ ጊዜ ግን ወሲብ የፈጸመችው ከዘላለም ጋር ነበር፡፡ ትርሲት ትልላት፡፡

ትርሲት ለዝናና ለመታወቅ ያላት ፍቅር ለጉድ ነው፡፡ ቆንጆ ነች፡፡ ዘላለም መቀመጫዋን ሲመለከት ኤሌክትሪክ እንደጨበጠ ሰው መላ ሰውነቱን ይነዝረዋል፤ ጥምልምል ብሎ ስትንቀሳቀስ የሚነቃነቀው ጭኗ የራሱ ሰውነት ይመስል በሀሳብ አብሯት ይወዛወዛል፡፡ ያለምንም ጡት ማስያዥያና ድጋፍ ቦታ ቦታቸውን ይዘው በተጠንቀቅ የቆሙት ጡቶቿን ጥንቁቅ ያልሆኑ ወንዶችን አይደለም ብዙ ሴት የሚያውቀውን ዘላለምን እንደ አዲስ ይፈታተነዋል፡፡

ዘላለም በተቻለው አቅም ትርሲት ምንም እንዳልሆነች ሊያስመስል ቢሞክርም በጣም ተቸገረ፡፡ ኩራትና ምንም አልመሰለኝም አሉ አይነት ባህሪ ሊያሳይ ቢሞክርም ነገሩ የሚሆን አልነበረም፡፡ ትርሲት ደግሞ የመዝሙር ካሴት ለማውጣት በጣም ጓጉታ ነበር፡፡ በመጀመሪያ ለምን መንፈሳዊ ሰው መሆን እንደመረጠች ለዘላለም በጣም ይገርመው ነበር፡፡ 'ይህቺ ልጅ እኮ ዓለማዊ ብትሆን ይሳካላት ነበር፤ ድምጿም ቆንጆ ነው፡፡ በዚህ የሰውነት ቅርጽ ላይ ዘፋኝ ሆናበት ቢሆን አገር ይተራመስ ነበር' ይላል ለራሱ፡፡

ለነገሩ ለምን ዘማሪ መሆን እንደፈለገች ስትነግረው ነበር የገረመው፡፡ ትርሲት አባቷ በልጅነቷ ስለሞተ ያሳደገቻት እናቷ ነች፡፡ እናቷ በየሰው ቤት ልብስ አጥባ፣ ቤት አጽድታ፣ እንጀራ ጋግራ… በምታገኘው ገቢ ነበር በጭንቅ በመከራ ያሳደገቻት፡፡

ትርሲት ገና ስምንተኛ ክፍል ተማሪ እያለች ሚኒ ሚዲያ ላይ ትሳተፍ ነበር፡፡ በዚያው ውስጥም ድምጿ ቆንጆ ስለነበር ዝፈኝልን እየተባለች የተለያዩ ዘፋኞችን ዘፈን ለሚኒ ሚዲያው አባላት ትዘፍን ጀመር፡፡ ቀጠለናም የትምህርት ቤታቸው ዘፋኝ ሆነች፡፡ በዚህ የብዙ ተማሪና አስተማሪዎችን አድናቆት እያገኘች ስትሔድ በየምሽት ቤቱ እየሔደች ትዘፍን ጀመር፡፡ በዚህ ሙያዋም የእናቷንም የራሷንም ሕይወት ወደ ተሻለ ነገር መቀየር ጀመረች፡፡

እንደውም ካሴት ለማውጣት ዝግጅት ጀመረች፡፡ ቢሆንም እናትም አባትም ሆና ያሳደገቻት እናቷ ታመመች፡፡ ሕመሟ የደም ካንሰር ነበር፡፡ ትርሲት በጣም አዘነች፡፡ ያልጠበቀችው ነገር ስለነበር እናቷ እንድትድን አቅሟ የቻለውን ሁሉ በየሐኪም ቤቱ እየሄደች ሞከረች፡፡ ቢሆንም እናቷ ልትድን አልቻለችም፡፡



CamScanner

ትርሲት የምታደርገው ጠፋት። ወትሮ ከነበራት ባህሪ ተቀይራ ውሎና አዳሯ ቤተ ክርስቲያንና ጸሎት ሆነ። እንደውም 'እግዚአብሔር እናቷን ቢምርላት ዘሬትን እርግፋ አድርጋ ትታ በመዝሙር ፈጣሪዋን እንደምታገለግል' ተሳለችና እናቷን ጸበል ወሰደቻት። እናቷ ለአሥራ አምስት ቀን ከተጠመቀች በኋላ ለምርመራ ወደ ሆስፒታል ሄደች። ውጤቱም ሐኪሞችን እጃቸውን በአፋቸው ያስጫነ፤ ትርሲት እና እናቷን በደስታ እምባ ያራጨ ሆነ። የትርሲት እናት ከደም ካንሰር ተፈወሰች።

ለዚህ ነበር ይህች ቀንጆና የወሲብ ዛር የተሸከመች የምትመስል እንስት መንፈሳዊ ሰው የሆነችው። ትርሲት መንፈሳዊ ሕይወቷን ከጀመረች በኋላ በሰለቷ መሠረት መዝሙር ማውጣት ስለፈለገች እንቅስቃሴ ጀመረች። የዚያኔ ነበር በጥቆማ ከዘላለም ጋር የተቀራረበችው።

ከመቀራረብ አልፈው ቤቱ መዋል ማምሸት ጀመረች። ቢሆንም ግን ዘላለም ለወሲባዊ ግንኙነት ቢገፋፋትም ትርሲት ግን እሺ ልትለው አልቻለችም። ብዙ ጊዜ ሞከረ ግን አልሆነለትም። ትርሲት 'ትንሽ የስኬት መንገዱን ካሳየኝ በኋላ እተወዋለሁ' እያለች የወሲብ ጉትጎታውን ታግሳ ጠበቀችው።

ትርሲት 'ማምለክ' የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማችው ከዘላለም ነበር። 'ማምለክና ማስመለክ' የሚሉ ቃላትን ከኦርቶዶክስ መምህራን ሰምታ ስለማታውቅ ግር ይላት ነበር። ዘላለም ትርሲትን በተደጋጋሚ 'ላስመልክሽ?' እያለ ይጠይቃት ነበር። እሷም መንፈሳዊ ነገር ስለሚመስላት ዝም ብላ 'እሺ' ትለው ነበር። ትርሲት ማስመለክ የሚለው ቃል የገባት ቆይታ የደቂቀ እስጢፋኖስ ስራ አስፈጻሚ ውስጥ ስትገባ ነበር። 'ማስመለክ' የሚለው ቃል በተለይ በጥቂት የደቂቀ እስጢፋኖስ አባላት ዘንድ 'ወሲብ እናድርግ' የሚል ትርጉም አለው።

'ማምለክ' የሚለውን ቃልም ከጥልቅ የወሲብ ግንኙነት ጋር ያይዙታል። በደቂቀ እስጢፋኖስ ዘንድ ወሲብ አንዱ መንፈሳዊ ተግባር ነው ምክንያታቸውንም ሲያቀርቡ "ሔዋን ከአዳም የጎን አጥንት ከመሰረቷ በፊት በአዳም ውስጥ ነበረች። ስለዚህ እግዚአብሔር ይህን የተለያየውን የአዳምንና የሔዋንን አካል በወሲብ ዳግም መልሶ አንድ ማድረግ ነው። ይህ ለእግዚአብሔር ትልቅ ደስታ ይሰጠዋል" ብለው ያምናሉ። ይህ አስተምህሮ ግን ከፍ ላሉት የደቂቀ እስጢፋኖስ አባላት ብቻ ነው። ገና ለጀማሪዎች አይነገርም። ዘላለም በተደጋጋሚ ትርሲትን 'ላስመልክሽ?' እያለ ሲጠይቃት ሳይገባት 'እሺ' ትለው ነበር። በስተመጨረሻ ግን ማስመለክ በሚለው ቃል ባይሆንም በሌላ መንገድ ዘላለም አሸነፈ።

እለቱ በዝናብና በመብረቅ የታጀበ ነበር። ዘላለምና ትርሲት ቤቱ ውስጥ ቁጭ ብለው እየተጫወቱ ቢሆንም ልብስን ሰርስሮ የሚገባው ብርድ የሚቻል አልነበረም። ስለዚህም ዘላለም ፍሙ ጉልጥጥ ያለ እሳት አያያዘና ቤቱን አሞቀው። እሳቱ ብቻውን

ከሚሆን አለና ሉባንጃ እጣንና ሀሽሽ አንድ ላይ ተደባልቆ የተቀመጠበትን ሙዳይ አምጥቶ 'ሺታው ደስ ይላል' እያለ በተንጎለጠጠው እሳት ላይ በተነው። ክፍሉ በሀሽሽና በሉባንጃ እጣን ታጠነ።

ትርሲት በመጀመሪያ ዘላለም በሚያወራው ነገር ሁላ ዝም ብላ መሳቅ ጀመረች፤ ሳቋ ባሰባትና ጭራሽ ዘላለምን ካልጨፈርን ብላ ማስቸገር ጀመረች። ዘላለም ትርሲትን ከተቀመጠችበት አስነሳትና መጨፈር ጀመሩ። ቆመው እየጨፈሩ ባለበት ትርሲት ዓይኗን እያስለመለመች የዘላለምን ከንፈር ሳመችው። መልሶ እሱም እንደ በሰለ እንጆሪ የቀላውንና በወሲብ ጥማትና በሀሽሽ ስካር የሚንቀጠቀጠውን ከንፈሯን ሳመውና ቀና ብሎ አየት አደረጋት፤ ትርሲት ፍዝዝ ብላ ዘላለምን እያየችው። ዘላለም ደገመና አፉን ከፍቶ ከንፈሯን መጠጠው።

ዘላለም ፍጥነቱን ጨምሮ ትርሲት ከላይ የለበሰችውን ልብሷን ማውለቅ ጀመረ። ቀጠለናም መሳ ገላዋን በከንፈሩ እንደ ማር ቀስ ብሎ ይልሰው ጀመር። ትርሲት ራሷን እንደ መሳት ብላ ሶፋው ላይ እርቃኗን ወደቀች። ዘላለም ፓንቷንም ሽርተት አድርጎ አወለቀው። ዐይኑ የሚያየውን ነገር የወሲብ ስሜቱን በጣም ስላነሳሳው ዐይኑ በስሱ እንደመጨፈን አለ። ዘላለም ሱሪውን ለማውለቅ ጊዜው በጣም ረዘመበት።

ዘላለም ከትርሲት ጋር ሲመኘው የነበረውን ወሲብ ለማድረግ ሱሪውን እየተንቀዠቀዠ አወለቀው ብልቱ ፓንቱን አምልጦ ውጥር ብሏል። ፓንቱንም በጀመረው ፍጥነት አውልቆ ወረወረውና ወደ ትርሲት ገላ በጣም ተጠጋ። የትርሲት ትንፋሽ እንደ ፍም እሳት ይጋረፋል፤ የዐይኗ ጥቁሩ ክፍል ወደ ውስጥ ገብቶ ነጩ ብቻ ነው የሚታየው።

ዘላለም ወደ ትርሲት ሰውነት በፍጥነትና በጥልቀት ሲገባ የሚያግድ ነገር ገጠመው። ዘላለም ግራ ገባው፤ ሰውነቱን በኃይል ወደ ትርሲት ገፋው። ትርሲት ድንግል ነበረች። ዘላለም ይህችን የመሰለች ልጅ ቀድሞ የወሲብ ታሪክ አይኖራትም ብሎ ስላላሰበ ክው ብሎ ነው የደነገጠው። ዘላለም ብዙ ተልእኮ ፈጽሞ ያውቃል። ሰው ገድሎም ያውቃል። ነገር ግን እንዲህ ያለ የጥፋተኝነት ስሜት ተሰምቶት አያውቅም።

ከጥፋተኝነት ስሜቱም በላይ አዘነላት፣ ተጨነቀላት አፈቀራት። ልቡ ጥፍት እስኪል ድረስ ወደዳት። ትርሲትም በእሱ ፍቅር ክንፍ አለች። እሱ ባደረገው ነገር ቢሳቀቅም እሷ ግን ሰክራ እንዳደረገችው ቆጠረችው። ከዚያማ ትርሲትና ዘላለም በፍቅር ማዕበል ሲናጡ፤ በወሲብ እርካታ አቅላቸውን ሲስቱ ከረሙ። በዘላለም ቋንቋ 'ሲያመልኩ' ነበር።

ይሁን እንጂ ዘላለም መሳቀቅ ጀመረ። ሕይወቱ ለፍቅር የተደላደለ አልነበረም። በእጁ ላይ የብዙ ሰው ደም አለበት። ዘላለም ከትርሲት ጋር በትዳር መተሳሰር ቢፈልግም

የሥራው ሁኔታ ግን የሚፈቅድለት አልነበረም፡፡ ትርሲትን የወሲብ ጓደኛ ማድረግ እንጂ ፍቅረኛ ማድረግ እንደማይችል ያውቃል፡፡

ስለዚህ ሊለያት ወሰነ፡፡ ምንም ማድረግ አይችልም፡፡ ዘላለም አላማ አለው፡፡ የእናትና አባቱ ደም በገዛ ቤታቸው ደጃፍ ላይ ፈሶ ይጮኽበታል፡፡ አባቱ አውድ ላይ ማንም በሬውን ይነዳበታል፤ ማንም ሞፈሩን ይዘውርበታል፡፡ ውስጡ ዛሬም ድረስ እንደ ትኩስ ደም የበቀል ያለህ እያለ ያምባርቅበታል፡፡ ስለዚህ የሚወዳትን ልጅ መተው በከንቱ የፈሰሰውን የእናትና አባቱን ደም ያህል ሊያመው አይችልም፡፡ ዘላለም ትርሲትን ሲተዋት ግን የወደፊት ሕይወቷ እንዲሳካ የተቻለውን አድርጎ ነበር፡፡ መጀመሪያ የምትፈልገውን መዝሙር እንድታወጣ ረዳት፡፡ በጣም ታዋቂ የሆኑ ገጣሚና ዜማ ደራሲዎችን አገናኛት፡፡

የትርሲት መዝሙር ወጣ፡፡ ዝማሬው የብዙሀኑን ክርስቲያን ጆሮ ለመቆጣጠር ቀናት አልፈጀበትም ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያን፣ መኖሪያ ቤቱ፣ ታክሲው፣ ሻይ ቤቱ፣ ቡና ቤቱ፣ ካፌው፣ ሆቴሉ ሁሉ ሳይቀር የእሷ መዝሙር ሆነ፡፡ ይህ አጋጣሚ ነበር ለደቂቀ እስጢፋኖስ ሕቡዕ ቡድን ቁልፍ ሰው እንድትሆን ያደረጋት፡፡ ደቂቀ እስጢፋኖስ ሕቡዕ ቡድንም መዝሙርን ለተሐድሶው ማስኬጃ ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት ስለተረዳ ለውጥ አደረገ፡፡ ከዚያ በኋላ ነበር በትርሲት አዘማመር ዘዩ አዳዲስ ዘማርያንን በመመልመል ለተሐድሶ አላማ ማስፈፀሚያ ማዋል የተጀመረው፡፡

ትርሲት እና ዘላለም ግን ተለያዩ፡፡ ከመለያየታቸው በፊት ዘላለም ከአገር እንድትወጣ አደረገና አሜሪካ ላካት፡፡ ከዚያም እንደ ተለያዩ ነገራት፡፡ ትርሲት ይህን ሲነግራት እንደማበድ አድርጓት ነበር፡፡ ቢሆንም በሥነ ልቦና ሐኪም እርዳታ ራሷን አረጋጋች፡፡ የቀድሞ መልካም ባህሪዋ ግን ሙሉ ለሙሉ ተቀየረ፡፡ መንፈሳዊ ሕይወቷ በጣም ተጎዳ፡፡ ክርስትና የሚባል ነገር ጠላቻው፡፡ ከዚያ ይልቅ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ማስመሰል፤ የሥልጣን ሽኩቻቸው፣ የፖለቲካው ተፅእኖ፣ በአያሌው የተንሰራፋው ሙስና፣ የወሲብ ርሃቡና ድብቁ ግንኙነት እጅግ በጣም ያስደነግጣት ጀመር፡፡ ሲቆይ ግን ለመደችው፤ ባትወደውም ተዘፈቀችበት፤ ባትፈልገውም ሆነች፡፡

ትርሲት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንንም አምርራ መጥላት ጀመረች፡፡ ደቂቀ እጢፋኖስ ከሚሰጣት ሥልጠና በተጨማሪ አሜሪካ ባለው ሲኖዶስ ውስጥ ያለውን ዘረኝነት፤ የቤተ ክርስቲያኗን የቀደመ አስተምህሮ መጣስ፤ የቀሳውስቱ ራስ ወዳድነት እና ዘረኝነት ተደማምረው ማንነቷን ቀየሩት፡፡ ስማቸውን ለመጥራት ከሚከብዱ የቤተ ክርስቲያን ቆሞሳት ጋር አንሶላ መጋፈፍን እንደ ጀብድ መቁጠር ጀመረች፡፡ ይልቁንም ትልቅ የተከበሩና መንፈሳዊ ሰዎች ጋር ወሲብ እየፈጸመች ዝናዋ ይወራላት ጀመር፡፡ ከቆሞሳት ጋር ያላት የወሲብ ታሪክ ከቤተ ክርስቲያኗ አስተምህሮ ውጪ የሆነ መዝሙር ስትዘምር ማንም እንዳያወግዛት አፍ ማዘጊያ ሆናት፡፡ አሁን የደቂቀ እስጢፋኖስ የስራ አስፈጻሚ አባልና ዝነኛ ዘማሪ ነች፡፡



CamScanner

## ምዕራፍ ፴፮

## አዲስ አበባ ሳሪስ

ሰንፔር አባቷን ከቀበረች ስምንት ቀናት አለፉ። አባቷን በማጣቷ እየተሰማት ያለው ሕመም ልትቋቋመው አልቻለችም። ድምጽ ሳታወጣ ዝም ብላ ማንባት የሰርክ ተግባሯ አድርጋዋለች። የዐይኗ ውስጡ የቀላ ሲሆን ከስር ደግሞ የመንገድ ፋካ ይመስል ጥቁር መስመር ሰርቶ አብጧል።

ከሮዳስ ጋር ተኳርፈዋል። በአሁን ሰዓት ሮዳስን ማናገር አልፈለገችም። አባቷ የሞተ እለት ቢቢሲ ላይ እንደታየ ቢደውልም አላነሳችም። ሀዘን ላይ ነች ብሎ ወደ ቤታቸው ሄደ። ቢሆንም ከሃዘኑ በተጨማሪ በሮዳስም በጣም አዝናለች። ሰው አጠገባቸው ካለ ከአንገት በላይ ብታናግረውም፣ ሰው ከሌለ ግን በዐይኗ ቴጥ እያየች ትገላምጠዋለች። ሮዳስ ግን እየተመላለሰ በየቀኑ ሲያጽናናት ነበር የከረመው።

ሰንፔር ይህን አጋጣሚ ተጠቅማ ከሮዳስ ጋር ተለያይታ ሃዘኗን ጠቅለል አድርጋ መወጣት ትፈልጋለች። ፕሮቴስታንት እሆናለሁ ብሎ ሀሳቡን ስለቀየረ ሁልጊዜም እንደተካደች ይሰማታል። ቢሆንም ከሌላ ሰው ጋር ዝም ብላ ከምታወራ ይልቅ ከሮዳስ ጋር ብትጨቃጨቅ፣ በከረረ ጸብ ውስጥ እንኳ የሚያሳያት መረጋጋትና ነገሮች ለማስረዳት የሚያሳየው ትህትና ይስባታል።

ሮዳስን ማጣት የገዛ አካሏ ተቆርጦ እንደቀረ ይሰማታል። ፍቅራቸውን ባሰበች ቁጥር የመለየት ሕመሙ ጭንቅ ይላታል። በሃይማኖት ልዩነት ውስጥ መኖር አትችልም። የልዩነት ችግሩን በፍቅር ሕይወቷ በየቀኑ ተጋፍጣዋለች ስለዚህ መለያየታቸው ግድ ነው። ነገር ግን ሮዳስን ትተወው ይሆናል እንጂ አትረሳውም፣ ይለያዩ ይሆናል እንጂ ሀሳብ ለሀሳብ፣ ልብ ለልብ አይለያዩም። አንዳንዴ ነሸጥ ሲያደርጋት የሃይማኖት ልዩነታቸው እንዳልተፈጠረ ረስታ ከእሱ ጋር መሆን ያምራታል። መለስ ስትል ደግሞ ልዩነቱን ትፈራዋለች።

ሰንፔርን ከሀሳቧ ያባነናት የእጅ ስልኳ ሲጠራ ነው። የደወለው ወንድሟ ነው። ፊቷን ቀድሞ ከነበረው መከፋት ደሞ ምን ሲል ነው? በሚል ይብስ አጨፈገገችው።

እየደበራት ስልኩን አንስታ "ሄሎ" አለች

ማዕረግ "ሄሎ የት ነሽ?" አለ በመጣደፍ ስሜት ውስጥ ሆኖ ነው የሚያወራው

"ምነው? እቤት ነኝ"

"እሺ እቤት ከሆንሽ ቴሌቪዥን ክፈች?"

"ስምን ለቅሶ እኮ ነው ሰው ምን ይላል? ያምሃል እንዴ አንተ?"

"እሺ የመኝታ ቤቱን ቴሌቪዥን ክፈችው የአባዬ ገዳይ ተገኝቷል፡፡ በቴሌቪዥን እየተነገረ ነው፡፡"

"ምን?!" ሰንፔር ዘላ ከተቀመጠችበት ተነሳች "እውነትህን ነው ማዕረግ?"

"አዎ እውነቴን ነው"

"ምን ቴሌቪዥን ላይ ነው የሚታየው?"

-----//-----

ዘላለምና ዳንኤል ቴሌቪዥኑን በአግራሞት እያዩ ነው፡፡ ዘላለም በገደለው ሌላ ሰው እኔ ነኝ ገዳይ ብሎ መጥቷል፡፡ አስገራሚ መስዋዕትነት ነው የተከፈለው፡፡ ለዘላለም ይሄ ትንግርት ነው የሆነበት፡፡

"አንተ! እነዚህ ሰዎች ሰክረዋል? ምንድነው የሚያደርጉት?" አለ ዳንኤል በአግራሞት

"እእእ... እኔ እራሱ ገርሞኛል፡፡ ኦርቶዶክስነትን እንደ ሀሺሽ ሳይስቡት አይቀሩም፡፡"

"እውነትህን ነው፡፡ ሰምተሀል አይደል ሰውየው እኮ ዶክተር ነው፤ ያውም የልጆች አባት፡፡ በጣም ይገርማል፡፡" አለ ዳንኤል ውስኪው ውስጥ ያለውን በረዶ ለማሟሟት በረዶውን ከብርጭቆው ጥግና ጥግ እያጋጨ፡፡

"ባክህ ተዋቸው እውር ቢሸፍት ከጓሮ አያልፍም፡፡ ለጊዜው መስዋእትነት ምናምን እያሉ እራሳቸውን ያስደስቱ..." ዘላለም ብላክ ሌብሉን ጎንጨት ሲል ፊቱን በስሱ እንደማጨፍገግ አደረገና መናገሩን ቀጠለ፡፡

"እነዚህ ሰዎች እንደዚህ ሰካራም ከሆኑ ስራችንን አድካሚ ማድረጋቸው አይቀርም፡፡ ምን ብናደርግ ይሻላል?"

"ይህን እኮ መጠበቅ አለብህ፡፡ ጠላትህንማ ጠንቅቀህ ማወቅ አለብህ ዳኒ፡፡ እኔ የጠላቴን ምሽግ እየደረመስኩ እንዳለሁ ነው የሚሰማኝ፡፡ ጠላቴ መመሸጊያውን ስመታው ያኔ ራቁቱን ፊት ለፊት አገኘዋለሁ፡፡ ለዚያ ነው መቼም የማልተኛው፡፡ መቼም!" ዘላለም ነበር በስሜትና በቁጣ እየተንተገተገ የተናገረው፡፡

ዳንኤል ዘላለምን ይፈራዋል፡፡ ዳንኤል ወደ እዚህ ስራ የገባው ራሱን ከድህነት አላቆ ሐብታም ለመሆን ብቻ ነው፡፡ የዘላለም አላማ ግን ሌላ ነው፡፡ ዘላለም ለአላማው ሲል መንፈሳዊ ኮሌጅ ገብቶ ተምሯል፤ በሕይወቱ ከመወራረድ ወደ ኋላ ለማይልበት

ፍቅሩን አጥቶበታል፤ ልጅነትንና ወጣትነቱን ዋጋ ከፍሎለታል። ዘላለም ለአላማው መሳካት የማይፈነቅለው ነገር አይኖርም። ስለዚህ ቀጣይ ማድረግ ያለበትን ማሰብ ጀመረ። መጀመሪያ ግን ወደ ቶኒ መደወል ይኖርበታል።

-------//-------

## ካሊፎርኒያ-ሎስአንጀለስ

ውይይቱ ከሚካሄድበት ሞንደሪያን ሆቴል መጠነኛና ውብ አዳራሽ ፊት ለፊት የአትክልት ስፍራና ትልቅ የውሃ ገንዳ አለ። ቶኒ ካለበት ክፍል ውጪ ቢወጣ ደስ ባለው ነበር፤ ግን እያጨሰ ስለሆነ መውጣት አልቻለም። ስለዚህ ካለበት ክፍል ሆኖ በመስኮቱ አሾልኮ ውጪውን መማተር ጀመረ።

በጣም በዙ ቁጥር ያላቸው ሰዎች በደስታ እየዋኙ ነው። ከውሃ ገንዳው ጎን በምታምር ሰማያዊ ኳስ ለአራት ክብ ሰርተው በእጃቸው ኳስ እየተቀባበሉ የሚጫወቱ አሉ። የዋና ፓንትና ጡት ማስያዣ ብቻ ያደረጉት እንስቶች በውሃው ዳር ዞር ዞር ሲሉ ይታያሉ፤ የተቀሩት እንስቶችም በማረፊያው ላይ ገላቸውን ለፀሐይ አጋልጠው፤ ጃሳቸውን በቁንጥ መምጠጫ ቱቦ እየመጠጡ ከጎናቸው ካለ ሰው ጋር ያወጋሉ። ከታች በዋና ፓንት ከላይ በባዶ ያሉ ተባእቶች ደግሞ በእንስቶቹ ዳሌና በጡት ማስያዣ የተወጠረ ጡት እያዩ ምስጥ ይላሉ። ከወላጆቻቸው ጋር ያሉ ሕጻናት ፍንድቅድቅ እያሉ ከውሃ ገንዳው ዳር እየተሯሯጡ ይጫወታሉ።

ከዚህ ሁሉ ዐይንን ከሚስብ ትዕይንት መሀል ሆኖ ቶኒ ነገር ያብሰለስላል። ነገሮች እንደተፈለገው እየሄዱ ነው ሲባል ሌላ ችግር ተፈጠረ። ሳይገድል ገዳይ ነኝ የሚል ሰው መጥቷል። የፓስተር ናፍያድ መሞት ከኦርቶዶክስም ሆነ ከፕሮቴስታንቱ ጎራ ያሉትን ምዕመናን ወደ ከፍተኛ ቁጣና ድንጋጤ ቀይሯቸው ነበር። ይህን የጋለ ውጥረት ሳይጠቀሙበት ገዳይ ነኝ የሚል ሰው መጥቶ ውሃ ቸለሰበት።

ቶኒ ሲጋራውን አሁንም አሁንም በደንብ እስከ ሳንባው ዳርቻ ድረስ ስቦ አስገባውና ጭሱን በአፉም በአፍንጫውም አስወጣው። ሰውየውም ቶኒ አካባቢ ሲጋራቸውን እያጨሱ ስለነበሩ እንደ ምርኩዝ የሚጠቀሚትን ቁንጠኛ ዱላቸውን ወደ ቶኒ አቅጣጫ አዙረው መምጣት ጀመሩ።

“ቶኒ አሁን ምን ብናደርግ ይሻላል?” አሉ እሳቸውም ገዳይ እኔ ነኝ ብሎ የመጣው ሰው ጉዳይ ያሳሰባቸው ይመስላል።

ቶኒ ነገሩን ዳግም መፋፋም እንዳለበት ወስኗል። ደም ወደ አዕምሮው እየተምዘገዘገ ሲፈስ እየተሰማው ነው። በጣም እያሰበ ነው። ሰውነቱ ሳይሆን አዕምሮው እየጋለ

ነው። ዳግም የተንኮል መረቅ ሲቀዳ አዕምሮውን በሃሳብ እንደ ሳም ጡት ያልበው ጀመር።፡

በመጀመሪያ ነገሮችን መስመር መስመር ማስያዝ እንዳለበት ተረዳ። ክብሮምና ሰውየው ከዘላለም ጋር አብረው ቢሰሩ መልካም ነው ብሎ አሰበ። ወትሮ ቶኒ ከእነዚህ ሰዎች ጋር በተናጠል ነበር የሚገናኘው። አሁን ግን ትንሽ ያልተማከለውን መንገድ ተጠቅሞ ዘላለምን፣ ሰውየውንና ክብሮምን አንድ ላይ እንዲሰሩ ማድረግ ነው።

ለእነዚህ ሰዎች ሰው መግደል ማለት የኮምፒውተር መጫወቻ ላይ ያለን ጠላት በዚያው በኮምፒውተሩ ላይ ባለ ተጫዋች እንደ መግደል የቀለለ ስለሆነ የቀድሞውን መዋቅር ትንሽ ማስተካከያ አድርጎ ቴክኒክና ግብአት ድጋፍ እያደረገ በበላይነት እሱ እየተቆጣጠረ ኃላፊነት ለእነሱ ሊሰጥ አስቧል።

"ይህ ነገር እንዲህ በቀላሉ እንዲመክን አልፈልግም። መጀመሪያ ገዳይ ነኝ ያለው ሰው ከየት እንደሆነ በእናንተ በኩል ማጣሪያ ቢደረግበት። ሌላው የእኛ ኤጀንት ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለ ከእርሶና ከክብሮም ጋር ሆኖ በመቀናጀት ቢሰራ ብዬ ነው።" ቶኒ ስሜታዊ ሆኖ ላለመታየት የራሱን አትኩሮት ትንሽ ለመስረቅ ከኪሱ ሌላ ሲጋራውን አወጣና በምታብረቀርቀው ወርቃማ ቀለም ባላት ላይተር መለኮስ ጀመረ።

ሰውየው ሲጋራቸውን ጣሉና "ጥሩ ነው ግን በዚህ ውስጥ እኔ በቀጥታ መግባት አልችልም። ነገር ግን ክብሮም ከአንተ ኤጀንት ጋር ሆኖ ይስራ፣ መረጃዎችን እኔ ከክብሮም እወስዳለሁ" አሉ ሰውየው። ለማንም ቢሆን የማይደራደሩለትን ክብራቸውን ለማስጠበቅ ብለው።

ቶኒ ሀሳባቸው ስለገባው "እሺ" አለ። ቀጠለናም "በቃ ከክብሮም ጋር እንዲገናኝ አደርጋለሁ። በረራችሁ ነገ ስለሆነ ያለውን ነገር ዛሬ ተነጋግረንበት አዲስ አበባ እንደገባችሁ ክብሮምና ዘላለም አብረው እንዲሰሩ እናደርጋለን።"

"የጳጳሳት ሹመቱ መቼ ነው የሚከናወነው?" አለ ቶኒ አዲስ የለኮሳትን ሲጋራ በአውራ ጣቱና በጠቋሚ ጣቱ ይዞ ሳብ ሳብ እያደረገ።

"ከሳምንት በኋላ ይከናወናል"

"ለተሐድሶ የሚፈለገው ሰው ይመረጣል አይደል?"

"እዎ ችግር የለም የሚፈለገው ሰው ሹመት ያገኛል" አሉ ሰውየው ምርኩዛቸውን እየነቀነቁ።



CamScanner

## ምዕራፍ ፴፮

### ካሊፎርኒያ-ሎስአንጀለስ

ሰውየው ነበሩ ከእረፍት በኋላ የውይይቱን የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት፡፡ "አሁን ማድረግ ያለብን ነገር አሜሪካ ላላችሁት ለስደተኛው ሲኖዶስ ተሐድሶውን እንዳታውጁ እንቅፋት የሚሆኑትን ሰዎች ማስወገድ ነው፡፡" ቶኒ ወደሚፈለገው ሀሳብ ስለገቡለት ሰውየውን ወደዳቸው፡፡

ሰውየው ጉሯሯቸውን እንደ መጠራረግ ሲሉ በውፍረት ምክንያት የተንዘላዘለው ጉንጫቸው እንደ ቅጥቅጥ በሬ ሻኛ ወዘወዘ አለ "ስለዚህም የእኔ ሀሳብ ምንድነው እኚህ አሜሪካ ያሉት ጳጳስ አቡነ መርቆሬዎስ ተወግደው አዲስ ጳጳስ ብትሾሙ?" መርሐዊ በድንጋጤ ሰውነቱ ሽምቅቀቀ ሲል ተሰማው፡፡ የደነገጠው ግን ጳጳሱ ይገደሉ ስለተባለ ሳይሆን እሱ ሲያስበው የነበረውን ሀሳብ ሰውየው ስላሉት የልቡን ያወቁበት መስሎት ነው፡፡ ቶኒ የሰውየው ሀሳብ እንደተመቸው ያስታውቃል፡፡

ለዓለም ግን በጣም ደንግጧል፡፡ ጳጳሱ በጣም ደክመዋል ሞታቸው ሰማዕትነት ነው፡፡ ነገር ግን በሰው መገደላቸው ቀጥሎም ሊመጣ ያለው ነገር አስደንግጦታል፡፡ አዲስ አበባ ካለው ሲኖዶስ ጋር የያዘው እልህ እዚህ የሚያደራርስ አይደለም፡፡ በዚያ ላይ በአገልግሎት ዘመኑ ከአገልጋዮች የታዘበው ነገር በጣም ያሳፍራል፡፡

አገልጋዮች መቅደሱን በጣም ይዳፈራሉ፤ መቀደስ ትተው መስቀሉን እንደጦር ዕቃ ተጠቅመው ቅድስት ውስጥ በመጸር የሚደባደቡ፤ ዝሙት አዳሪ ሴቶችን የሚያማግጡ ዲያቆናት፤ ከአስራት በኩራት ገንዘብ እየጨለፉ እንደ ግል ንብረታቸው የሚዝናኑ የሚያጠፉ፤ በዘር የተቧደኑ ካህናትን ብቻ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያኗ ጭምር የአማራ ሚካኤል፣ የትግሬ ገብርኤል... እየተባለ እንደሚከፋፈል ያውቃል፡፡

አዲስ አበባ ያለው ሲኖዶስ ስር ያሉ ዲያቆናትና ቀሳውስትም ቢሆኑ በዘር የተከፋፈሉ፤ ሽጉጥ በጀርባቸው ሸጉጠው የሚቀድሱ፤ ከምእመን ጋር ማታ አንሶላ ሲጋፈፉ አድረው ጠዋት ተነስተው የሚቀድሱ ካህናት፤ ሊያስቀድሱ ከሚመጡ ልጅአገረዶች ጋር በውድም ይሁን በግድ በቤተ ክርስቲያኗ ቅጥር ውስጥ የሚደፍሩ አንዳንድ ዲያቆናት እንዳሉ በደንብ ያውቃል፡፡ ይህ ሁሉ የሞራል ውድቀት እንቅልፍ እየነሳው፤ እራሱንም ተጠያቂ እያደረገ ባለበት ሰዓት ጭራሽ ፓትርያርክ ገድሎ በደም መጨማለቁን ልቡ የሚፈቅድለት አልሆነም፡፡ ቢሆንም ማዳመጡን ቀጠለ፡፡

ቶኒ ነበር ንግግሩን በቀጣይነት የወሰደው "በአሁኑ ሀሳብ በጣም እስማማለሁ፡፡ ሌላው ግን በፓስተር ናፍያድ ግድያ ምክንያት ማኅበረ ቅዱሳንን ተጠያቂ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን እስከ መጨረሻው ታግዶ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ እንዳይነሳ ሆኖ መደምሰስ አለበት፡፡ ለዚህም እርሶን የምጠይቀው..." አለ ቶኒ፡፡

ቶኒ የሰውየውን የፖለቲካ አቅም ስለሚያውቅ በፊቱ ወደ እሳቸው እየጠቆመ ነው የሚናገረው።

"...እርሶን የምጠይቀው በማኅበረ ቅዱሳን ላይ የተቃውሞ ሰልፍ እንዲወጣ ነው። እኔ ደግሞ ሰልፉን በቢቢሲ እና በሲኤንኤን ሽፋን እንዲያገኝ አደርጋለሁ። ከዚያም ማኅበረ ቅዱሳንን በሽብርተኛነት ፈርጀን ለማሳየት ተጨባጭ ማስረጃ ይሆናል። ከዚያም በገሀድ ማኅበሩን መዝጋት ትችላላችሁ።" ሰውየው አንገታቸውን እየነቀነቁ በደስታ ገለጹ። ክብሮምም የሰውየው አንገት ሲነቀነቅ አይቶ እሱም ነቀነቀ።

"አቡነ መርቆሬዎስን ካጸዳን በኋላ አቡነ ሰላማን ማስሾም ደግሞ ግድ ይለናል።" አለ ሩቢዮ ፍቅረኛውን ለማስደሰት ዐይን ዐይኑን እያየ። ክብሮምና ሰውየው የመርሐዊን የጽጽስና ስሙን ስላልያዙት እንደመደናገር አሉ። መርሐዊ ነገሩ ስለገባው እኔ ነኝ አይነት ፈገግታ ፈገግ አለ።

"ስለዚህ የጳጳስ ምርጫው ላይ ብቻ ሳይሆን የምናተኩረው፤ ከአቡነ መርቆሬዎስ በኋላ ምን አይነት ለውጥ ነው በቤተ ክርስቲያን ላይ የምናደርገው፤ እንዲሁም ለህዝቡም እንዴት ነው ቀስ በቀስ ተሐድሶውን የምናለማምደው የሚለውን ልንመክር ይገባል።"

ሰውየው ንግግር ጀመሩ "እስከአሁን ያለው ሀሳብ ተመችቶኛል። እናንተ አቡነ መርቆሬዎስን አስናብታችሁ አቡነ ሰላማን ያስሾማችሁ እንደሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ በስደተኛው ሲኖዶስ የሚመራ ቤተ ክርስቲያን እንድትከፍቱ እንፈቅድላችኋለን። ከዚያ በኋላ አዲስ አበባ ባለው ሲኖዶስ የተቀየመ ሁሉ ወደ እናንተ ይጎርፋል። ከዚያማ ተሐድሶውን ለማወጅ በጣም ቀላል ይሆንላችኋል።" ሰውየው ልክ የጠዋት ፀሐይ ሰውነታችን ላይ ሲያርፍ እንደሚፍታታው ሁሉ አዕምሮአቸው ዘናና ደስ ሲለው ተሰማቸው።

ሰውየው በሆዳቸው 'ሲያምርህ ይቅር' አሉ። በእርግጥ ኢሕአዴግ ኢትዮጵያን እስከገዛ ድረስ ስደተኛውን ሲኖዶስ ኢትዮጵያ ውስጥ የራሱ ቤተ ክርስቲያን እንዲከፍት እንደማይፈቅዱ ያውቃሉ። ነገር ግን ሆን ብለው በውሸት ተስፋ ሲሞሏቸው ነው። ዋናው የሰውየም ሆነ የፓርቲያቸው አላማ ኦርቶዶክስን ባለበት ማድከም፤ ምእመኑን ነገ ምን ይፈጠር ይሆን እያለ ስለ ቤተ ክርስቲያኑ መፍረስና አለመፍረስ እየተጨነቀ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሐብታዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ እርግፍ አድርጎ ትቶ በሰቀቀን እንዲኖር ማድረግ ነው እንጂ አሜሪካ ያለውን ሲኖዶስ ማምጣት አይደለም። አሜሪካ ያለው ሲኖዶስ አውሮፓና አሜሪካ ያለውን ሕዝብ ስለተቆጣጠረባቸው ቂም ይዘውበታል። ስለዚህ ይህንኑ ሲኖዶስ ራሱ መከፋፈል፣ ማፈራረስና ማዳከም ይፈልጋሉ እንጂ ጭራሽ እግር እንዲሰድ እንዲያገነግን አይፈቅዱም። ስለዚህ እለሁ ብለው ሲከዱት ፈልገዋል። ሰዓቱ ሲደርስ።



CamScanner

ሰውየው የተዋሕዶ እምነት ተከታይ ከተረጋጋና ሰላም ከተሰማው ለኢሕአዴግ ሥልጣን አደጋ ነው ብለው ያምናሉ። "ተዋሕዶ ማሰሪያዋ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ነው። ኢትዮጵያን እንደ ቅደስት አገር፣ ባንዲራዋን እንደ ንዋይ ቅድሳት የሚቆጥርን አማኝ 'ና ኢትዮጵያን እናፍርስ?' ቢባል የሚሰማ አይሆንም። ስለዚህ በትንሹም በትልቁም የተዋሕዶ ተከታዮችን በማናደድና በመረበሽ እረፍት የለሽ ማድረግ' የሚሰው አቋማቸው እስከ እለተ ሞት ድረስ የሚቆም አይደለም።

መጀመሪያም ቢሆን አቡነ መርቆሬዎስ አሜሪካ ገብተው 'ሕጋዊውና ትክክለኛው ሲኖዶስ ይህ ነው' ሲሉ ደስታ የተሰማቸው ብቸኛ የመንግሥት ቁልፍ ባለሥልጣን እሳቸው ነበሩ። ምክንያቱም እንዲህ ያለው ሁለት ቤት የሆነ አካሄድ ምን ያህል ለመፍረስ፣ ለመዳከም፣ ለመበላሸት እንዴት እንደሚጠቅም የሚያውቁት በሁለት ቤት አድገው የተበላሹ ልጆች ብቻ ናቸው። ልክ እንደ እሳቸው።

እንደውም ሰውየው ያደጉት ሦስት ቤት ነው። እናትና አባታቸው ተጣልተው ሁለቱም ትዳር ይዘው በየፊናቸው ይኖሩ ነበር። ሰውየው ከእናታቸውና ከእንጀራ አባታቸው ጋር እስከ አስር አመት እድሜያቸው ድረስ ቢኖሩም፣ ቆይተው ግን ከእንጀራ አባታቸው ጋር ተጣሉና ወደ አባታቸው ሄዱ። አጥፍተው እንጀራ እናታቸው ልትመታቸው ስትል አምልጠው በአስራ አራት አመታቸው የእናታቸው እናት ጋር ሄዱ። ከዚያ በኋላ አንዱ ጋር ሲከፋቸው ወደ አንዱ እየሄዱ ለጥፋታቸው ቅጣት እንዳያገኙ አንዱን መደበቂያ በማድረግ ነፃነትን አወጁ።

ሰውየው ንግግራቸውን አልጨረሱም "በተለይ በሰሜን ያለው ተዋሕዶ ማስቸገሩ አይቀርም። አሁን እንኳ ቤተ ክርስቲያኗን ለማደስ ይፈልጋሉ ሲባሉ የምሰማቸው ሰዎች ከደቡብ ናቸው። ደቡብ የራሱን አካባቢ መሰል ኦርቶዶክስ ያስፈለገው ይመስላል። በተቃራኒው ሰሜኑ ደግሞ ራሱን መሰል ኦርቶዶክስ አስቀድሞ ስላበጀ ብዙም አይጎረብጠውም። ስለዚህም የቀደመ ይዞታውና አካሄዱ አይለወጥ ማለቱ አይቀሬ ነው። ስለዚህ ሰሜኑ አካባቢ ፀጋ፣ ቅባትና ካራ የተባለውን ልዩነት ዳግም መቀስቀስ ያለብን ይመስለኛል። እነዚህ ልዩነቶች በሰሜኑ ቢያገረሹ ኦርቶዶክስ ይደክምልናል ስለዚህ አላማችንን ማፋጠን እንችላለን።"

ሰውየው ስለ ኢትዮጵያ ፓለቲካ ሲያወሩ በብዙ ነገር እየከፋፈሉ ነው። በተለይ ሰሜንና ደቡብ የሚለው አከፋፈላቸው በጣም የታወቀ ነው። ሰሜኑን ጨቋኝ ደቡቡን ተጨቋኝ አይነት ምስል ሰጥተው ማውራት የተለመደ ባህሪያቸው ነው። በሰውየው የሰሜንና የደቡብ አሰፋፈር መሰረት ሰሜን ሲሉ አማራ እና ትግራይን ያጠቃለለ ቢሆንም እሳቸው ግን ሰሜን ሲሉ አማራ ብቻ ማለታቸው ነው። ደቡብ ሲሉ ደግሞ ኦሮሚያን ጨምሮ የተቀሩት የኢትዮጵያ ክፍል ማለታቸው ነው። ይህ አስተሳሰባቸው በሃይማኖትም ሲመጡ አይለቃቸውም። ደቡብና ሰሜን እያሉ ለሁለት መክፈል ይቀላቸዋል።



CamScanner

መርሐዊ ለመናገር የፈለገ ይመስላል። ቁንጥንጥ እያለ ነው። ነገር ግን ሰውየው ንግግራቸውን አልጨረሱም። ስለዚህም ንግግራቸውን ቀጠሉ "ሌላው ማኅበረ ቅዱሳን ይበተን በሚባለው አልስማማም፤ እሱንማ እኛም ተበተኑ ብለን በአንድ ቁራጭ ደብዳቤ እንበትነው ነበር። ግን ስለተበተኑ ለቤተ ክርስቲያኗ ይብስኑ የተቆጡና የቆጉ ትንሽ ሳይሆኑ ብዙ ወጣቶች እንፈጥራለን። በጥቂት ሚሊዮን የሚቆጠረው የማኅበረ ቅዱሳን ደጋፊ ሁሉም ኦርቶዶክስ ማኅበረ ቅዱሳን ወደሚል ጠርዝ እንገፋዋለን። ከበተንነውስ በኋላ ይሄ የተበተነ አዕምሮ፣ ጉልበትና አቅም የትም ይቀራል ብላችሁ ታስባላችሁ? ተሳስታችኋል።

"ከዚያ ይልቅ ማኅበረ ቅዱሳን ባለበት ልናዳክመው ይገባል። እየኖረ እንዳይኖር፤ እየታየ እንዳይታይ፤ እየፈለገ እንዲያቅተው ነው ማድረግ ያለብን። ይህም የሚሆነው የራሳችንን አመራሮች በቦታው ስናስቀምጥና አሳሪና ሰባሪ ሕግ በሲኖዶስ በኩል ስናስወጣበት ነው። ያኔ ሽባ እናደርገዋለን። እያየ ይታወራል፤ እየፈለገ ያጣል፤ እየሞከረ አያሳካም፤ አለ ሲሉት ሞቶ ይገኛል። ያኔ ደካማው ማኅበረ ቅዱሳን ደጋፊዎቹ የሚያፍሩበት፤ ከማኅበሩ ጋር እንደ ቀድሞው መቆምና ማበር አይፈልጉም። ስለዚህ ደጋፊዎቹ በራሳቸው ጊዜ እንደ ጢስ በነው፤ እንደ እንፋሎት ተንነው ያልቃሉ።"

መርሐዊ ሰውየው ንግግራቸውን እንደ ጨረሱ መናገር ጀመረ "ፀጋ እና ቅባት የተባሉትን የሃይማኖት አስተምሕሮዎች ዳግም ብንቀሰቅስ ያን ያህል ይጠቅመናል ብዬ አላስብም። በእርግጥ በጎጃም፣ በሸዋና በጎንደር አንዳንድ ገዳሞች ውስጥ ቢኖሩም የበዛ ዝግ ናቸው። አስተሳሰባቸው አሁንም የለም ባይባልም ነገር ግን በጥቂቱ ከኦርቶዶክሶች ተዋሕዶ ጋር ይለያዩ ይሆናል እንጂ ሙሉ ለሙሉ የኦርቶዶክስን ትውፊት ቀኖናና ዶግማ ስለሚቀበሉ እነሱን ለእኛ አላማ ምቹ ማድረግ የምንችል አይመስለኝም።" እስከአሁን ለዓለም ምንም አላወራም። ዝም ብሎ እያዳመጠ ነው።

ሰውየው በድጋሚ ዓይም የለሽ ወፍራም ጉንጫቸውን እንደ መዳበስ ብለው መናገር ጀመሩ "እኔ እኮ ያልኩት ለተሐድሶው በቀጥታ ይረዱናል አይደለም፤ ነገር ግን አማራውን በዚህ የልዩነት ማዕበል ብንመታው ለተሐድሶው እንቅስቃሴ የሚደረገውን መከላከል ስስ ይሆናል ነው። በዚያ ላይ ለጠላትህ ብዙ ጠላት ፍጠርለት የሚባል ነገር እንዳለ ባንረሳ።" ሰውየው ጦርነት ላይ ብዙ ዘመናቸውን ስላሳለፉ አጋጣሚዎችን እንዴት እንደሚጠቀሙበት ያውቁበታል። እንዴት የጠላትን ጠላት ፈልጎ ከጠላት ጋር በማጋጫት ውጤት እንደሚገኝ ልምድና ተሞክሮ አስተምሯቸዋል።

ቶኒም ቢሆን የሰውየው ሀሳብ እምብዛም አልተስማማውም "እኔ በመርሐዊ ሀሳብ እስማማለሁ። የኢትዮጵያውያን ሥነ ልቦና በጣም አስቸጋሪ ነው። በተለይ ሃይማኖታቸው ላይ ያላቸው አቋም ተገማች አይደለም። ውጤቱ እኛ እንዳሰብነው

ላይሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ለዘመናት ያንቀሳቀሱትን አስተሳሰቦች እንደ አዲስ ጠርተን ከዚያም እንጠቀምባቸዋለን ስንል እንደ አዲስ ተዋሕደው ይብስ ጠንካራ ሊሆኑብን ይችላሉ፡፡ ስለዚህም ባሉበት ብንተዋቸው ይሻላል፡፡

"ባይሆን ቅድም የተነሳው ኦሮሚያንና ሌላውን የኢትዮጵያን ክፍል የጨመረ የደቡብ ኦርቶዶክስ የሚለውን ሀሳብ እንደ አዲስ ቢቀነቀንና በራሳቸው የተቃኘ አዲስ የታደሰ ኦርቶዶክስ ቢፈጠር መልካም ነው፡፡ ይህን ማንሳት ደግሞ ብዙም አይቸግረንም አሁን ያለው ሲኖዶስ እናንተን አይወክልም ማለት ብቻ በቂ ይመስለኛል፡፡ ይህኔ ኦርቶዶክስ ያለ ኮሽታ እንድትታደስ ትልቅ በር ይከፍትልናል፡፡ ከቁቤ በስተቀር ምንም የማያውቀውን አዲሱን የኦሮሞ ትውልድ ግዕዝና አማርኛ የሚያቀነቀን የነፍጠኛ ሃይማኖት ማለት ብቻ በቂ ነው፡፡" ሰውየው ድምጽ ሳያወጡ 'እናንተ ምንም ብትሉ ዮሐንስ አራተኛ አንድ አድርጎ ያሰረውን እኔ ድጋሚ ሦስት አድርጌ እፈታዋለሁ' አሉ፡፡

ሪቢዮ ቀጣይ ንግግሩን ወደ ክብሮም አንገቱን ገፋ እያደረገ "አባ አወቀን ጳጳስ እንዲሆኑ ያሳሳለስ ጥረት ማድረጋችሁን ሰምተናል፡፡ በጣም ነው የምናመሰግነው፡፡ የመጨረሻው እጩዎች ውስጥ ነው ያሉት፡፡ ጳጳስ ሆነው መመረጣቸው ይፋ እንደሆነ ተሐድሶውን በኢትዮጵያ፣ በአሜሪካና በአውሮፓ ይፋ እናደርጋለን፡፡" ብሎ ፈገግ አለ፡፡

ክብሮም ምስጋና ስለተቸረው ይመስላል መናገር ጀመረ "የፀረ ተሐድሶ ትግሉን በገሀድ ከሚያደርገው ከማኅበረ ቅዱሳን በተጨማሪ ሌላ ሕቡዕ ድርጅት እንዳለ ከዚህ ቀደም ነግራችሁናል፡፡" አለ ክብሮም ዐይኖቹን ወደ ቶኒና ሩቢዮ እያማተረ፡፡ "...ቢሆንም ስለዚህ ድርጅት ምንም ተጨባጭ ነገር ልትሰጡን አልቻላችሁም፡፡ እነማናቸው?"

ቶኒ ለመመለስ መቀመጫውን አደላደለና ቀጠለ "እውነት ነው ሙሉ መረጃ በበቂ ሁኔታ ልናገኝ አልቻልንም፤ የምናውቀው ነገር አበጋዝ የሚባለው ሰው ለፓስተር ናፍያድ መልስ የሰጠው ሰው የዚያ ሕቡዕ ድርጅት አባል ነው፡፡ ድርጅቱ መቀመጫው አዲስ አበባ ነው፡፡ ግን ቦታው የት እንደሆነ እያጣራን ነው፡፡ በቅርቡ ጥሩ መልስ እናገኛለን ብለን እንገምታለን ምክንያቱም ፓስተር ናፍያድን ገደልኩ ያለው ሰው ከዚያ ሕቡዕ ቡድን የመጣ ይመስለኛል፡፡"



CamScanner

## ምዕራፍ ፴፰

## አዲስ አበባ-ሳሪስ

ሰንፔር የአባቷ ገዳይ ዶክተር ገመዳ ደመቀ ነው ብላ አምና መቀበል አልቻለችም። የአባቷ ሞት ከዚህ ከፍ ያለ ምስጢር እንዳዘለ እየተረዳች ነው። በመጀመሪያ የአባቷን ሞት ቢቢሲ እና ሲ ኤን ኤንን በሚያክል ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሀን መዘገቡ ገርሟት ነበር።

ቀጠለና የአባቷ ገዳይ በሥራቸውና በምግባራቸው ምስጉን የተባሉ የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የፊሎሎጂ ምሁር መሆናቸው ግርምትን ፈጥሮባታል። ዶክተር ገመዳ ደመቀን አንድ ቀን ሰንፔር ከሮዳስ ጋር እየተዝናናች እያለ ሮዳስ አሳይቷታል።

እንደውም ፊሎሎጂ የሚባል የትምህርት አይነት እንዳለም ያወቀችው ያን ቀን ነበር። ስለቀደምት ሥነ ድርሰት የሚያጠና የትምህርት አይነት መሆኑንም የነገራት ሮዳስ ነበር። 'ዶክተር ገመዳ ደመቀ በአገራችን ጥቂት ከሚባሉ የፊሎሎጂ ምሁራን አንዱ ናቸው' ብሏት ነበር።

ስለዚህ 'ምን ፈልገው ነው አባቴን የገደሉት? ለምን ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን ነገሩን ማራገብ ፈለጉ? ለምን አዲስ አበባ እንደመጣ አልገደሉትም? ለምን ኦርቶዶክሶች መልስ ከሰጡ በኋላ ሞተ? ለምን ገዳዩ ራሱ መጥቶ እጅ ሰጠ? ስለምንስ አንድ የተከበረ ዶክተር የእኔን አባት ይገድለዋል? ከሚገድለውስ ማስገደል አይቀለውም ነበር?' እያለች ራሷን መጠየቅ ጀመረች።

ሰንፔር ከተቀመጠችበት ሶፋ ላይ እመር ብላ ተነሳችና አረንጓዴውን ለስላሳ ነጠላ ጫማ ተጫምታ ወደ አባቷ መኝታ ቤት አመራች። አባቷ ከሞተ በኋላ መኝታ ቤቱ ለመግባት ብዙ ጊዜ ብትሳቀቅም ዛሬ ግን ዘው ብላ ነበር የገባችው። ክፍሉ ለቀናት ተዘግቶ ስለሰነበተ ወደ ወስጥ ሲገባ ትንሽ የመታፈን ስሜት ይሰማል። መስኮቱም በሩም ዝግ ስለሆነ ሰንፔር በሩን ከፈተችና በበሩ በስተቀኝ በኩል ቻይና ሰራሹን ማብሪያ ማጥፊያ ተጭና መብራቱን አበራችው።

ውኃ ሰማያዊ ቀለም የተቀባው ግርግዳ ለሰንፔር ጠቀርሻ ሆኖ ነው የታያት። ቤቱ ሰሚኑን እንደለበስችው ባለ ጥቁር ጥለት ነጠላ ተዘቀዘቀባት። እንደ ምንም ራሷን አደፋፍራ ወደ ውስጥ ገባች። ከፍሉን በቅርቡ ያስተካከለው ሰው ስለሌለ አባቷ ከመሞቱ በፊት እንደ ተተወ ነው።

ሰንፔር ወደ አባቷ ራስጌ አመራች። መጽሐፍ ቅዱስ በአይነት በአይነቱ ተሰድሯል። መጽሐፍ ቅዱሱን አነሳችና አልጋው ላይ ካስቀመጠች በኋላ ሌላ ነገር ከስር ይኖር እንደሆን ብላ አየች። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ጮራ፣ ሐመርና ትሪኒቲ የተባሉ

መንፈሳዊ መፅሔቶች ተደራርበ ተቀምጧል። ትንሽ ማስታወሻ እንኳ ተጥሎ ቢሆን ብላ መጽሔቶችንና መጽሐፍቱን ገላልጣ አየች። ግን ምንም ማስታወሻ ልታገኝ አልቻለችም።

መጽሐፍ ቅዱስና መጽሔት ተቀምጠበት የነበረውን ኮመዲኖ ለመክፈት ሞከረች። ግን አልቻለችም። ቁልፍ ነው። የአባቷ የመኪና፣ የቤት፣ የሳጥን ቁልፎች ሞቱን ከተረዱ በኋላ ፖሊሶች አምጥተው ሰጥተዋት ነበር። የት እንዳደረገችው ልታስታውሰው ሞከረች።

የቁም ሳጥኑ ቁልፍ ፊት ለፊት እንደተሰካ ነው። ወደ ቁም ሳጥኑ ዞራ ቁም ሳጥኑን ከፈተችው። ቁም ሳጥኑ እንደተከፈተ የራሷን መስል አሳያት። ጸጉሯ ተንጨባሯል። ፊቷ ኩል ስለለመደ እሷ እንደምትለው 'የተለቀቀ ቤት' መስላለች። ቆንጆው ዐይኗ ሰሞኑን ሲቀባ ሲሽሞነሞን ሳይሆን ስለ አባቷ ፍቅር እምባ ሲያፈስ እንደከረመ ያስታውቃል። ፊቷ ገርጥቷል በዚያ ላይ ከስታለች።

እጇን የአባቷ ሱፍ ኮት ውስጥ ከተተች። ሳንቲሞች አገኘች። እጇን ኪሱ ውስጥ ብታርመሰምስም ከሳንቲም ውጪ ምንም ልታገኝ አልቻለችም። በፊት ለፊት ኪስ ውስጥ ስትከት እንጨት መፋቂያ አገኘች። መፋቂያው ጥርስ በማፋቅ የለፋ በመሆኑ እንክት ብሎ ደርቆ እንኳ ያስታውቃል።

ሰንፔር ሌላኛው የአባቷ ኪስ ውስጥ እጇን ሰደደች ምንም የለም። እንዲሁ እያለች አራተኛው ኮት ውስጥ እጇን ስትከት ብዙ ቁልፎች አገኘች። የመሳቢያዎች፣ የውጪና የግቢ በር ቁልፍ የያዘ ነው። ቁልፍ መያዣው ላይ 'ኢየሱስ ጌታ ነው' ይላል።

-----------//-------

## አዲስ አበባ-ብስራተ ገብርኤል

ይህ ቤት አዲስ አበባ ውስጥ ካሉት ምርጥና ሰፊ ከሚባሉ የከተማው ቤቶች አንዱ ነው። ግቢው እንደ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰፊና ዛፎች የበዙበት ነው። አጠቃላይ የግቢው ስፋት ሁለት ሺህ አምስት መቶ ካሬ ሜትር ሲሆን ከሦስት ሺላ ቤቶች በተጨማሪ ግቢው መሀል ላይ ባለ ሶስት ፎቅ ውብ ሕንጻ አለ። ከቤቱ ፊት ለፊት በስተምሥራቅ አቅጣጫ አምስት ሜትር በሦስት ሜትር የሆነና አንድ ነጥብ አምስት ሜትር ጥልቀት ያለው የውኃ ገንዳ አለ።

የቤቱ እቃዎች አብዛኛው ከጃፓን የመጡ ሲሆን የተገጣጠሙትም ከጃፓን በመጡ ባለሙያዎች ነው። በቤቱ አሳቻ አሳቻ ቦታ ላይ የስውር ካሜራ ተሰቅሏል። ካሜራውን የገጠሙት ደግሞ ቻይናዎች ናቸው። ምርቱም የቻይና ነው።



CamScanner

በሁለት አትክልተኞች ጭንቅ ጥብብ ተብሎ በጥንቃቄ የተዋበው የግቢው አበባ፣ ሳርና ጽድ በሕብር አንድ ላይ ሆነው ለግቢው ትልቅ ድምቀት ፈጥረዋል። በቱርኮች የተሰራው ሙሉ የግቢውም የውጪውም መብራት በርቶ ግቢውን የገና ዛፍ አስመስለውታል።

ውኃው ዳር በዝግባ እንጨት በተሰራው ወደ ኋላ ለጠጥ ብሎ ምቾት ባለው ወንበር ላይ ሰውየው፣ ክብሮምና ዘላለም ሆነው ቁጭ ብለዋል። ፊት ለፊታቸው ውብ ሆኖ የተሰራ ጠረጴዛ ላይ ከአንገቱ ትንሽ ዝቅ ያለ ብሉ ሌብል ውስኪ፣ ቀዝቃዛ ውኃና ወርቃማ የበረዶ ማስቀመጫ አለ። ከሁሉም ፊት ለፊት ጎደል ጎደል ያሉት ብርጭቆዎች የውስኪውን ጠርሙስ ከበውት ተቀምጠዋል።

ሰውየው ቤት ቀድሞ የደረሰው ክብሮም ነበር። ነገር ግን ዘላለም ሲገባ ክብሮም ወደ መጸዳጃ ቤት ሄዶ ነበር። ዘላለም ቁጭ ባለበት ክብሮም ሲመጣ ሁለቱም ተፋጠጡ። ልክ ቀድሞ እንደሚተዋወቁ ሰዎች ለሰከንዶች ተፋጠጡ። ዘላለም ነበር ማፍጠጡን አቁሞ ለሰላምታ አንገቱን ዘንበል ያደረገለት።

ዘላለምና ክብሮም በቅርበት አይተዋወቁም። ክብሮም የፓትርያርኩ የቅርብ ሰው ነው እየተባለ ሲወራለት ሰምቷል። ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ሲመጣ አይቶት ያውቃል። ነገር ግን የፓትርያርኩ ልዩ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ከሆነ በኋላ እንኳ አይቶት አያውቅም። ዛሬ ግን አብረው ሲቀመጡ የሆነ ክብድ የሚል ስሜት ተሰማው።

ሰውየውና ክብሮም ወደ ቀጣይ እቅድ ለመወያየት የተቀመጡት አዲስ አበባ በገቡ ከአሥራ ስድስት ሰዓት በኋላ ነው። ቶኒ እንደነገረው ከሆነ እነዚህ ሰዎች የሚያስፈልጉት ሰውየው የቤተ መንግሥቱን፣ ክብሮም የቤተ ክህነቱን ከለላ እንዲሰጡ ነው።

"ፍንዳታ የሚካሄድበት ቦታ መርጠሀል?" አሉ ሰውየው ጀርባቸውን ወንበሩ ላይ እያደላደሉ።

"አዎ ቦታዎችን መርጠናል፣ ሁሉም ነገር ዝግጁ ነው" አለ ዘላለም በመጠኑ እንደመደናበር እያለ።

ሰውየው ወደ ክብሮም እየተመለከቱ "አንተ ጳጳሱ ከፍንዳታው በኋላ የሚያወጡትን መግለጫና ስለ ማኅበረ ቅዱሳን የሚሉትን አዘጋጅ"

"እሺ!" አለ ክብሮም በበዛ አክብሮት

"ምን አይነት ቦንብ ነው የምትጠቀሙት? ቦንቡንስ ከየት አገኛችሁ?" አሉ ሰውየው በሰርሳሪ ዐይናቸው የዘላለምን ወጠምሻ ትከሻ አፍጥጠው እየተመለከቱ።

"ቦንቡ የተገኘው እንግሊዝ ኢምባሲ ካሉ ሰዎች ነው። ቶኒ ነው እንዲሰጡን ያደረገው። በእርግጥ ቦንቡ ዩኬ ሰራሹ ፒኢ ሰቨን ሳይሆን የጣልያን ምርት የሆነ ቲ ፎር ፕላስቲኮን ነው"

ሰውየው እንደመሳቅ ብለው ፈገግ አሉና "አይ እንግሊዝ እንደው ነገሩ ቢበላሽ ብላ ነው የራሷን ምርት ያልሰጠችን? አባቴ ይሙት ወንዶች ናቸው። ካልተሳካ ነገሩን ከእንግሊካን ወደ ቫቲካን ልትገለብጠው ነው አይደል? ይመቻት!" አሉ ሰውየው የለበጣ ሳቃቸውን ሳያቆሙ በላዩ ላይ ውስኪውን ወደ ውስጣቸው ሳብ እያደረጉ።

"እሺ ክብሮም የጳጳስ ሹመቱስ እንዴት እየሄደ ነው?"

"ጥሩ እየሄደ ነው በሚቀጥለው ሳምንት ይካሄዳል" አለ ክብሮም እየተሽቆጠቆጠ።

"ስንት ጳጳስ አስመረጣችሁ?"

"ሰባት ነው"

በስጨት ብለው "እሱን አላልኩህም የኛ ሰዎች ምን ያህል ናቸው?"

"የኛ ሲሉ ጌታዬ?" ክብሮም ከእኛ ሲሉት ከእነሱ ጎሳ ይሁን ወይም ለተሐድሶው የሚሆን ሰው ግራ ገባው።

ሰውየው እንደ መመናጨቅ እያሉ "አሁን የያዝነው ምንድነው? ለዚህ ለአላማችን ነዋ!"

ክብሮም ስለገባው ደስ አለውና "እእእ.." አለና "አንድ ብቻ ነው ጌታዬ" አለ በጥድፊያ።

"ምነው አቃታችሁ እንዴ?"

"አዎ ብዙዎቹ ቅድመ ሁኔታውን የሚያሟሉ ሆነው አልተገኙም አንዱም በመከራ አሾልከን ነው"

"ጥሩ" አሉ ሰውየው ወደ ዘላለም እየተመለከቱ። ሰውነቱ ሙልት ያለ ወንድ ደስ ይላቸዋል። ዘላለም እጁ ራሱ ሰፊ ነው። ትከሻው ከስፋቱ በላይ በስፖርት የተገራ ቅርፅ አለው። ግን ዘላለም በሆነ ነገር ሀሳብ እንደተጠመደ አውቀዋል።

------//------

ሰንፔር ቁልፉን ተጠቅማ ያገኘችውን መሳቢያና ቁምሳጥን ሁሉ እየከፈተች በርብራለች። ነገር ግን ከአባቷ ሞት ጋር የሚገናኝ ፍንጭ ልታገኝ አልቻለችም። አባቷ ጠንቃቃ ሰው እንደሆነ ታውቃለች ስለዚህ ጠላቶቹ ሲያጠቁት እንደፈለጉ ደግሞ አስቀድሞ አውቆ ነበር። ስለዚህ የሆነ ፍንጭ ይተውልኛል ብላ ነበር መበርበሩን የቀጠለችው።

ሰንፔር ምንም ሲሳካላት ስላልቻለ የአባቷ አልጋ ላይ በቁሟ ዘፍ ብላ በጆርባዋ ተኛችና ዐይኗን ኮርኒሱ ላይ ተክላ ለማሰብ ሞከረች። ቢሆንም በአዕምሮዋ ጓዳ ውስጥ ምንም ጠብ ያለ የሃሳብ ብርሃን አልነበረም። ስለዚህ ከተኛችበት ቀና አለች።

ሰንፔር ቀና ስትል አልጋው ላይ ተዘበራርቆ የነበረው መጽሔትና መጽሐፍ ቅዱስ ወለሉ ላይ ተዘረገፈ። እንደ መደንገጥ ብላ በረኸሙ ተነፈሰችና የተዘረገፉትን መጽሔትና መጽሐፍ ቅዱስ ለማንሳት ወለሉ ላይ በርከክ ብላ መጽሔቶቹን ከተዘረገፉበት ወለል ላይ እያነሳች ለማስቀመጥ ስትል ሐመረ ተዋሕዶ ከሚለው መንፈሳዊ መጽሔት ውስጥ የአማርኛ የፊደል ገበታ ወደቀ።

ሰንፔር በአግራሞት ዝም ብላ ለደቂቃዎች ፊደሉ ላይ አፈጠጠች። ቢሆንም ምንም ነገር ማየት ሲያቅታት ፊደሉን ለብቻው አስቀመጠችና የወዳደቁትን መጽሔቶችና መጽሐፍት አስተካክላ ወደ ቦታቸው መለሰችና ፊደሉን ይዛ ወደ ሳሎን ሄደች።



CamScanner

## ምዕራፍ ፴፬

## አዲስ አበባ-ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል አካባቢ

የጠዋቷ ፀሐይ ደስ ትላለች፡፡ ነገር ግን ግለቷ ቀስ ቀስ እያለ እየገረረ ነው፡፡ ስለዚህም ዘላለም የፀሐይዋን ሙቀትና ጨረር ለመከላከል ዳሽ ቦርዱን ከታጠፈበት አወረደው፡፡ ከዚያም ራሱን መኪናው ላይ አደላድሎ አስቀመጠና በኋላ መመልከቻው ከጀርባ ያለውን አካባቢ ቃኘት አደረገው፡፡

ጥቁሩ ራቭ ፎር መኪና ውበቷ አላፊ አግዳሚውን መሳቧ አልቀረም፡፡ አንዱ ወጣትማ ቆንጆ ሴት እንዳየ ሁለት ሦስቴ እየዞረ መኪናዋን ሲመለከት ዘላለም በአግራሞት በመኪናው የኋላ መመልከቻ መስታወት ውስጥ ይመለከተዋል፡፡ ልጁ ትንሽ ራመድ ይልና አንገቱን እየዞረ መኪናዋን በአድናቆት ያያል፡፡ ዘላለም ገርሞታል 'ሁሉ ብርቱ፤ ሁሉ ምራቅ የሚያስውጠው ትውልድ፤ ለመኪና እንኳ እንዲህ አቅሉን የሚስት ማኅበረሰብ ሲያሳዝን' አለ፡፡

ቀኑ እሁድ ስለሆነ አብዛኛው ክርስቲያን በየሚያመልክበት ቤተ ክርስርስቲያን ሄዶ ለፈጣሪው ምስጋናና ልመናን ያቀርባል፡፡ ለዚህ ነበር ይህን ቀን ዘላለም እና ዳንኤል ለእቅዱ ያመቻቸው፡፡ እቅዱን ያነጣጠረው ከቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም የሕክምና ትምህርት ቤት ፊት ለፊት ሃያ ሜትር ገባ ብሎ ከሚገኘው የጉለሌ አጥቢያ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን እና የሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው፡፡

ዘላለም ከጉለሌ አጥቢያ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አውደ-ምህረት ሥር ሲ ፎር ቦንብ አጥምዷል፡፡ የአምልኮው ስርአት ሲፋፋምና ሰዎች በጥልቅ መንፈሳዊ ስሜት ውስጥ ሲገቡ ሊያፈነዳው ነው ያሰበው፡፡ ስለዚህም እዚያው አቅራቢያ ትንሽ ራቅ ብሎ አገልግሎቱን እያዳመጠ ነው፡፡

--------//------

## አዲስ አበባ- ፊናንስ

ከፊናንስ ወደ ሽጎሌ በሚወስደው የአስፋልት መንገድ ላይ በስተቀኝ በኩል ወደ ውስጥ ገባ ብሎ በሚገኘው የጉለሌ ሙሉ ወንጌል አማኞች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ሌላ የቦንብ ፍንዳታ ተደግሷል፡፡ ይህንን ቦንብ ያጠመደው ዳንኤል ነው፡፡

ዳንኤል ጥቁር የፀሐይ መነጽር አድርጓል፡፡ ከላይ በነጭ መደብ በተለያየ ቀለም መስመር መስመር ያለበትን ሸሚዝ ለብሷል፡፡ ከስር ካኪ ሱሪና ቶማ ጫማ ተጫምቷል፡፡ ዳንኤል ለአራት አመታት ያህል መድኃኒዓለም ሁለተኛ ደረጃ እየተመላለሰ ሲማር ከሚማርበት ትምህርት ቤት አለፍ ብሎ አለመሔዱ በጣም



CamScanner

ገርሞታል። በእርግጥ ፊናንስ ሲባል በተደጋጋሚ የሰማ ቢሆንም የት እንደሆነ በቅጡ አጣርቶም ሆነ ማጣራት ፈልጎም አያውቅም። ሰሞኑን ለዚህ ጉዳይ ከዘላለም ጋር ጥናት ሲያደርጉ ነበር ሰፈሩን ያወቀው።

ብዙ የሰው እልቂት እንዳይፈጸም ሁለቱንም በንቦች የተጠመዱት አዳራሹ ውስጥ ባለው አውደ ምህረት ስር ነው ያለው። የጥቃቱ ዋና አላማም ሰው መግደል አይደለም። አንደኛ ማኅበረ ቅዱሳንን በአሸባሪነት ማስፈረጅ ነው። ሁለተኛ በፕሮቴስታንት እና በኦርቶዶክስ ላይ የመጠላላትና የመጠባበቅ ትኩሳት መጨመር ሦስተኛ የኦሮሞ ተወላጅ ኦርቶዶክሶችን ልብ ማግኘት፤ ቢያንስ የኦሮሞ ተወላጅ ኦርቶዶክሶች ማኅበረ ቅዱሳንን አምርረው እንዲጠሉ ማድረግ።

ለዚህም ሆን ተብሎ እንደ 9/11 የአሜሪካ የመንትዮች ህንጻ በአንድ ቀን ውስጥ በተቀራራቢ ቦታና ሰዓት ላይ ጥቃት መፈጸም የተፈለገው። ዳንኤል አሁን የትምህርት ሰዓት መሆኑን ተረድቷል። ከሩቅ የሚሰማው በሰብከት የጎረነነ ኃይለኛ ድምጽና የሰብከቱን ቃል 'አሜን' እያሉ የሚቀበሉ ምእመናን ድምጽ ይሰማል።

------//-----

ዘላለም በጽሁፍ መልዕክት “አሁን ነው ሰዓቱ” ብሎ ላከለት። መልእክቱን ለዳንኤል ከላከ በኋላ ወንበሩ ላይ ለጠጥ ብሎ ለትንሽ ጊዜ ዐይኑን ጨፈን አድርጎ አሰብ አደረገና ዐይኑን ሳይገልጥ እንዲፈነዳ የሚያዝዘውን ቁልፍ ተጫነው። በቅጽበት አካባቢውን ቀውጢ የሆነ ፍንዳታ አናጋው። ከከባዱ ጩኸት በኋላ ለአፍታ አካባቢው ጸጥ ረጭ አለና መልሶ ፍጥነት በሰዎች ጩኸትና ውክቢያ ተተካ።

ተከትሎም ከሩቅ ሌላ የፍንዳታ ድምጽ ተሰማ። ዳንኤል ነበር ያፈነዳው። ሌላኛውን ፍንዳታ የሰሙ ሰዎች በድጋሚ እየተደናበሩ ወደ ተገኘው ስርቻ መወተፍ ጀመሩ። ጥቁር ጭስ ከመካነ ኢየሱስና ከሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን እየወጣ ወደ ሰማይ ላይ ይትጎለጎላል።

ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ጋወን ያደረጉ የጤና ባለሙያዎች፤ እንዲሁም አስታማሚዎችና መንቀሳቀስ የቻሉ ታማሚዎች ግር ብለው ከየነበሩበት ክፍል ወጥተው ከሆስፒታል ቅጽር ግቢ ሆነው ማየት ጀመሩ። ሰዎች በድንጋጤ መሯሯጣቸውን ትተው ጉዟቸውን ወደ ፍንዳታው አካባቢ ማድረግ ጀመሩ። የጤና ባለሙያዎቹ ለወሬም፤ እርዳታም ለመስጠት ከጳውሎስ ሆስፒታል እየወጡ ወደ ፍንዳታው ቦታ ማምራት ጀመሩ።



CamScanner

## ምዕራፍ ፵

ሰንፔር ከአባቷ መኝታ ቤት ያገኘችውን ፊደል አፍጥጣ እየተመለከተች ነው። ፊደሉ ከስር ላይ በስሱ በእርሳስ 'ዪታጻዪ' የሚል ቃል ተጽፏል። ሰንፔርን ቃሉን ደግማ ደግማ ብታነበውም ምንም ትርጉም ሊሰጣት አልቻለም። ሰንፔር እንገቷን ቀና አድርጋ ወደ በልጅነቷ ማሰብ ጀመረች። ከአባቷ ፊደል ሲያስጠናት ትዝ አላት።

አባቷ ለግዕዝ ቋንቋና ለፊደላቱ ትልቅ ቦታ እንደሚሰጥ ታውቃለች። በህጻንነቷ ትምህርት ቤት ያልተማረችውን የግዕዝ ቁጥሮች አባቷ ነበር ያስተማራት። "ፊደል ይገድላል መንፈስ ግን ያድናል" እያለ ነበር የግዕዝ ፊደላትን ሲያስጠናት የነበረው።

እሷና ወንድሟ ከትምህርት ቤት ከመጡ በኋላ የደንብ ልብሳቸውን ቀይረው መክሰስ ከበሉ በኋላ ልባቸው ሲጫወቱ ያመሻሉ። አባታቸው ከስራ ሲመለስ ወደ አንድ ሰዓት አካባቢ የቤት ስራቸውን ያሰራቸዋል። የቤት ስራቸውን ሲጨርሱ ለጥቂት ሰዓታት ያጠናሉ። በስተመጨረሻ አባታቸው የግዕዝ ፊደል፣ እንግሊዘኛ ቃላትና ትርጉም እንዲሁም ጊዜ ቤት ይጠይቃቸው ነበር።

አንዳንዴም የእጅ ጽሑፋቸውን እያየ ፊደል ገድፈው ሲያይ "ልጆች ፊደል ይገድላል መንፈስ ግን ያድናል" እያለ ያስተካክላቸዋል "ሰንፒ 'ፀኃይ' እኮ እንደዚህ አይጻፍም" ይላል። ብዙሀኑን 'ኀ' እየጻፈ " በዚህ 'ኀ' ቢጻፍም ቃሉን ትርጉም አልባ ያደርገዋል። ይሄ ነው ትክክለኛው ፀሐይ" ይላታል። በሐመሩ "ሐ" እየጻፈ።

"ሌላው 'ጸ'..." ፓስተር ናፍያድ ጸሎቱ ጸን እየጻፈ እያሳያት "...ጸሎቱ ጸ ይባላል። ይኸኛው "ፀ" ደግሞ..." ደብተሯ ላይ እየጻፈ "ፀሐዩ 'ፀ' ይባላል።"

ሰንፔር "እሺ አባቢ" ትለውና መልሳ አባቷን ትጠይቃለች።

"በዚህኛው 'ኀ' ተጻፈ በዛኛው 'ሐ' ምን ለውጥ ያመጣል?" ማዕረግ ዝም ብሎ ያያቸዋል።

"ለውጥማ አለው አባቶቻችን የሰሩልን ቅጥር ይህ ነው ሰንፔር። መጽሐፍ 'ቅጥርን የሚያፈርስ እባብ ይነድፈዋል' ይላል። እሱም ብቻ ሳይሆን ለምሳሌ እንግሊዘኛ ናይፍ (knife) ሲጻፍ ከፊት ለፊቱ 'ኬ' ፊደል አለች አይደል?" የሰንፔርን ዐይን ዐይኗን እያየ ነበር አባቷ የሚያዋራት። ሰንፔርም ግንባሯና ቋጠር ፈታ፤ አንገቷን ጎንበስ ቀና እያደረገች ትመልሳለች።

"...ሲነበብ ግን 'ክናይፍ' አይባልም ይልቁንስ 'ኪ' ሳትነበብ ትገደፍና 'ናይፍ' ይባላል። ስለዚህ ፈረንጆቹን ኬን ስለማታነቡ ለምን አታነሱትም ቢባሉ 'አባቶቻችን የሰሩልን

መንገድ ስለሆነ ነው' ይሉኻል ከዚያ ውጪ ሕግና ሥርአት አውጥተው አነባባቸውን ያስከብራሉ እንጂ ምን ይሰራል ብለው አያፈርሱትም።

"እኛም ከምንተወውና ከምናፈርሰው ይልቅ ሕግና ሥርአት ሰርተን ልንጠብቅና ልንከባከበው ነው የሚገባን። የኛ ፊደል ግን ይህ ብቻ ሳይሆን የራሱ የሆነ የሒሳብ ቀመር አለው። ለምሳሌ በዓል በዓይኑ 'ዐ' ሲጻፍ ትርጉሙ የደስታ ቀን፤ ሰዎች ተሰብስበው የሚያከብሩት እለት ይሆናል። በአል በአልፋው 'አ' ሲጻፍ ደግሞ አንደኛ ነገስት ላይ ያለው ከነዓናውያን የሚያከብሩት የጣኦት ስም ይሆናል። አሁንስ ገባሽ?" ይላል ፓስተር ናፍያድ ልጁን ዐይን ዐይኗን እያየ። ማዕረግ ሳይታወቀው ከእነሱ ርቆ የራሱን ጨዋታ ጀምሯል።

ሰንፔር በመጠኑ እንደገባት ራሷን ትነቀንቅና መልሳ ትጠይቃለች "ቀመር ያልከኝ አሁን ያወራኸውን ነው አባ?"

"አይ አይደለም ሰንፒ ሌላም አለ። እንዳይከብድሽ ብዬ ነው። እነዚህ የግዕዝ ፊደላት የራሳቸው የሆነ ቁጥር አላቸው። በዚህ ቁጥር መሠረት ተደምረው የሚሰጡን ውጤት አለ።" ሰንፔር ፈገግ ስትል አያት። ነገሩን የመስማት ፍላጎት እያሳደረች ነው።

ሰንፔር መማር በመፈለጓ አባቷ በጣም ደስ እያለው ነው የሚያስረዳት። በኤ ፎር ወረቀት ላይ በሰማያዊ ቀለም ታትማ በካርቶን ላይ የተለጠፈችውን ፊደል ከጠረጴዛው ላይ ሳብ አደረገና ማስረዳቱን ቀጠለ። ማዕረግ ሶፋው ስር ተንበርክኮ የተበተኑትን ብሎኮች ይሰበስባል።

"ይኸውልሽ ሰንፔር ግዕዝ ፊደል ከሃሌታው 'ሀ' ጀምሮ ለፊደሉ ከአንድ ጀምሮ ቁጥር ይሰጠዋል። ከዚያም..." ናፍያድ እርሳሱን ይዞ ፊደሉን እየጠቆመ ወረድ ይልና ብዙኃኑ 'ኀ' ጋር ሲደርስ ቆም አለና መናገር ጀመረ። "... ሃያ ይላል ገባሽ አይደል ተን አስር እንልና ቀጥለን ብዙኃኑ 'ኀ'ን ሃያ እንላለን። ነገር ግን ከብዙኃኑ 'ኀ' በኋላ 'ነ' ሲመጣ ሃያ አንድ አንልም ይልቁንስ ሰላሳ እንላለን እንጂ። እንደዚሁ ሁሉ 'ደ'ን መቶ ብለን 'ገ'ን ደግሞ ሁለት መቶ እንላለን።

ሰንፔር በጉጉት የአባቷን ፊት ቀና ብላ እያየች "አባቢ እኔ የማውቀው የፊደል ቁጥር ብዛት እኮ ሃያ ስድስት አይደለም ይልቁንስ ሰላሳ አራት ነው።" አለች አባቷ መሳሳቱን ያሳወቀችው መስሏት በደስታ ፈገግ ብላ።

"ልክ ነሽ ሰንፒ አሁን ያልሽው የፊደል ብዛት ያላው በአማርኛ የፊድ ገበታ ውስጥ ነው እንጂ በግዕዝ አይደለም። ግዕዝ እነዚህን ፊደል አይጠቀምም። አማርኛ ከግዕዝ ሙሉ ፊደሎቹን ወስዶ ከዚያም በተጨማሪ ሌሎች ዲቃላ ፊደሎችን ፈጥሯል። ይህ

ደግሞ የቋንቋ ባህሪ ነው። ማደግ፣ መውረስ መወራረስ ያለ የሚኖር ነው ሰንፒ። አሁንስ ገባሽ?" ሰንፔር አንገቷን በአዎንታ ነቀነቀች።

"ስለዚህም የግዕዝ ቃላት ሲጻፉ የራሳቸው ቁጥርና ትርጉም አላቸው።" ሰንፔር እንዴት ማለት በሚል የጥያቄ አስተያየት አባቷን አየችው።

"ተመልከች ለምሳሌ አዳም የሚለውን ስም በቁጥር እናስላው። በግዕዙ ቁጥር አሰጣጥ መሰረት ፊደል 'አ' አርባ ቁጥር ነው፤ ፊደል 'ደ' ደግሞ መቶ፤ 'መ' ደግሞ አራት ቁጥር ነው። እነዚህ ቁጥሮች ሲደመሩ መቶ አርባ አራት የሚል የድምር ውጤት ይሰጡናል። እንቀጥል ዳግማዊ አዳም ማን እንደሆነ ታውቂያለሽ አይደል?" ሰንፔር በአላውቀውም ስሜት አንገቷን ግራ ቀኝ ወዘወዘች።

"ሰንፒ ዳግማዊ አዳም ማለት ኢየሱስ ነው። ኢየሱስም በዚህ ቁጥር ስሌት ሲሰላ ፊደል 'አ' አርባ ቁጥር ሲሆን፤ ፊደል 'የ' ዘጠና፤ 'ሰ' ሰባት ቁጥር ይሆንና በድጋሚ ፊደል 'ሰ' ሰባት ቁጥር ይወስዳል። የእነዚህ ድምር መቶ አርባ አራት የሚል ውጤት ይሰጠናል።" ሰንፔር በመገረም አፏን ከፍታ ፈገግ አለች።

"ይገርማል አይደል ሰንፒ? የአዳምና የዳግማዊው አዳም በግዕዝ ሲሰሉ እኩል ውጤት መስጠታቸው? ይህ ካስገረመሽ አንድ ሌላ ልጨምርልሽ አብርሃም የመጀመሪያ ስሙ 'አብራም' ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር እባርክሀለሁ ብሎ ስሙን ጭምር ከአብራም ወደ አብርሃም ሲቀይረው የተጨመረለት የእኛዋ አንድ ቁጥር ያላትን ሃሌታው ሀን ነበር። በቅድሙ ስሌት መሠረት የአብራም ድምር ሃምሳ ዘጠኝ ነበር ስሙ ላይ ግን ሃሌታው 'ሀ' ሲጨመርለት ሙሉ ቁጥር ስልሳ ይሆናል። ስልሳ ደግሞ ለአምስት ስናካፍለው የአስራ ሁለት ብዜት ነው። ይህም ማለት አብርሃምን የአስራ ሁለቱ ነገድ መገኛ ሲያደርገው ነው።"

"አባቢ አምስት ቁጥር ከየት አምጥተህ ነው ያካፈልከው?" ናፍያድ በልጁ ማስተዋል ተገርሞ ፍጥጥ ብሎ ተመለከታትና መልሶ ፈገግ አለ "በትክክል አስተዋይ እኮ ነሽ የኔ ጣፋጭ!" ብሎ እቅፍ አድርጎ ሳማት።

"አምስት፣ ስልሳ እና አስራ ሁለት ቁጥር በሰዓት ውስጥ እናገኛቸዋለን። ተመልከች..." ናፍያድ ግርግዳው ላይ የተሰቀለውን ሰዓት እያመለከተ "ዋናው የሰዓት ቆጣሪ አምስት ደቂቃ ስትሄድ፤ ሁለተኛዋ ስልሳ ደቂቃ ታደርሳለች። ስልሳ ደቂቃን ለአምስት ብታካፍይው አስራ ሁለት ጊዜ ይደርሳል። አምስት የመጣው ከዚህ ነው እልሻለሁ። አስራ ሁለትን ለአስራ ሁለት ስታበዥው መቶ አርባ አራት ይመጣል። መቶ አርባ አራት የአንድ ቀን ቁጥር ነው። አዳም የተፈጠረው ደግሞ በየቀኑ ፈጣሪውን ለማመስገን ነው። ስለዚህ የአዳምም ሆነ የኢየሱስ ቁጥር መቶ አርባ አራት ነው።"



CamScanner

## ምዕራፍ ፵፩

## አዲስ አበባ-ጀሞ

የዛሬ የሮዳስ አዳር አዳር አይደለም። ቀድሞም ቢሆን ከሰንፔር ጋር ከተዘጋጉ በኋላ እንቅልፍ እምቢ እያለው ነው። በትንሽ በትልቁ ይንጫንጫል። እንደ ወትሮው ጎኑን አልጋው ላይ እንዳሳረፈ እንቅልፍ አይወስደውም። ቢወስደውም በትንሽ ነገር ተረብሾ ይነሳል። ከተነሳ ደግሞ መልሶ መተኛት ያቅተዋል።

ዛሬ ወደ እንቅልፉ የሔደው ከምሽቱ ስምንት ሰዓት ነው። የቦንብ ፍንዳታው ማን እንዳደረገው ከአበጋዝ ጋር ለማጣራት አደጋው የደረሰበት ቦታ ድረስ ሄደው ነበር። ነገር ግን ሊያገኙት የቻሉት ምንም ፍንጭ የለም። እንዲሁም ከማኅበራዊ ድረገፅ በፍንዳታው ሰዓት የተነሱትን ፎቶዎችን እያወጡ ለማየት ሞክረዋል። ነገር ግን ምንም ፍንጭ አላገኙም ነበር። ሲ ኤን ኤን እና ቢቢሲ በይበልጥ ነገሩን እየተነተኑት ነው።

የፊስአልጎስ አባላት ተሐድሶዎችን መከታተልና መመከት እንጂ ቀድሞ መቆጣጠር ወይም ጥቃቱን ማክሸፍ አልቻሉም። እነሱ የሚሰጧቸውን የቤት ሥራ ከመስራት ውጪ የራሳቸውን አላማ ማስፈጸም አልቻሉም። በዚህም የተነሳ ንዴት ውስጥ የገቡ ይመስላሉ። በቁጭት ውስጥ ሆነው ቦንቡን ማን እንዳፈነዳው ለማጣራት ነበር የሞከሩት፣ ግን አልቻሉም።።

እንደተለመደው ከእንቅልፉ እንደተነሳ ፌስቡክ ገጹን ማየት ጀመረ። በፌስቡክ ላይ የሚታየው ውጥረት የነገሰባት ኢትዮጵያን ነው። በሁለት አብያተ ክርስቲናያት ላይ የደረሰው የቦንብ ፍንዳታ በኦርቶዶክስ እና በፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ዘንድ ኃይለኛ ቁጣን ፈጥሯል። ፕሮቴስታንቶች 'ኦርቶዶክሶች አደረጉት' ሲሉ ኦርቶዶክሶች ደግሞ እንዳላደረጉትና 'ሆን ተብሎ ኦርቶዶክስን ለማጥቃት የተፈጸመ ነገር' እንደሆነ በማኅበራዊ ትስስር ድረገጽ ላይ እየተተነተነ ነው።

በአጠቃላይ በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ለረቡዕ ሠላማዊ ሰልፍ ተጠርቷል። ሮዳስ ጨንቅ ብሎታል። ሰልፉ ማኅበረ ቅዱሳን ላይ ያነጣጠረ ነው። ሰልፉ በመስቀል አደባባይ፣ በውጪ ጉዳይ፣ በቤተ መንግሥት አድርጎ አራት ኪሎ ፓትርያርኩ ጽሕፈት ቤት ድረስ ይሄዳል። ሰልፈኞቹን ፓትርያርኩ እንደሚያነጋግሯቸው ወሬው እየተናፈሰ ነው።

ከረቡዕ ቀጥሎ ባለው እሁድ የጳጳሳት ሹመት አለ። ተሐድሶዎች አንድ ሰው አሾልከው እንዳስገቡ ታውቋል። ጳጳስ አንዴ ከተሾመ በኋላ ሥልጣነ ጵጵስናውን እንደ እራፊ ጨርቅ በቀላሉ መግፈፍ አይቻልም። ይህ በቤተ ክርስቲያኗ ፍትሐ ነገሥት ላይ በማያወላዳ ቋንቋ ሰፍሯል። ተሿሚው ቀድሞ ሕጸጽ ኖሮበት እንደሆነ

አስቀድሞ ማጣራት ግድ ነው። አለዚያ ስህተቱ ከሹመቱ በኋላ የታወቀ እንደሆነ ሊሆን የሚችለው ውግዘት ነው። ውግዘት በጳጳሳት ደረጃ ሲሆን ለቤተ ክርስቲያኗ አንድነት ትልቅ ተግዳሮት ያመጣል ተብሎ ይታመናል። በዚያ ላይ ዛሬ ሾሞ መልሶ ነገ ማውገዝ በራሱ ለትችትና ለፊራጅ እራስን አሳልፎ መስጠት ነው። ስለዚህ "አጣርቶ መሾም ወይስ ሾሞ ማጣራት" የሚሉ ውዝግቦች በማኅበራዊ ትስስር ድረገጾች ላይ ትልቅ የመነጋገሪያ ርዕሶች ሆነዋል።

ሮዳስ ከዚያም በላይ ሌላ የሚያናድደው ነገር አለ። ሰንፔር ነች። ትልቅ የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ እሱ እንዲፈጽምላት በመጠበቋ አዝኖባታል። ከዚያም ብሶ ይቅርታ ትጠይቀኛለች ብሎ ሲያስብ ይቅርታውም እሷም የውሃ ሽታ ሆኑ። ለቅሶውም ላይ ልታናግረው አልፈለገችም። ይለፍላት ብሎ ተዋት። ግን እሷም መልሳ ተወችው እንጂ ሊያልፍላት አልቻለም።

ልዩነታቸው እንደ ፈራው መዘዙን መጎተት ጀምሯል። ያውም የከበደ። በደም የተለወሰ መዘዝ። ሲያስበው ዛሬ ደውሎ ስለ አደጋው ምን እንደምትልና እንዲሁም ስላማዊ ስልፉን እንድታዘገየው ሊጠይቃት ፈልጎ ነበር። ልክ እሷ ለአባቷ የሚሰጠውን መልስ እንዲያዘገየው እንደ ጠየቀችው ሁሉ።

------//------

ሮዳስ ዳር ስላልደረሰው የፍቅር ጅምሩ ማሰብ ጀመረ። በሕይወቱ የተሳሳተው ነገር ቢኖር ፍቅር በዚህ ልዩነት ውስጥ ለመጀመር ማሰቡ ነው። ሁልጊዜም የጥፋተኝነት ስሜት ይሰማዋል። መጀመሪያም ቢሆን ጥፋተኛው እሷ ሳትሆን እሱ እራሱ እንደሆነ በቁጭት ለራሱ ይናገራል።

አንድ ቀን ለልዩነታቸው እልባት ሊሰጡ ተቀምጠው ማውራት ጀመሩ። በእርግጥ "ዛሬ የግንኙነታችንን መጨረሻ እንወስን፤ መስመር እናበጅለት?" ብለው ይቀጣጠሩና በጥልና በጭቅጭቅ ደምድመውት፤ ስለ ወደፊቱ ሕይወታቸው ቁርጥ ያለ ነገር ሳይወስኑ ይለያያሉ።

ተነጋግረው መስማማት ሲያቅታቸው ከሁለቱም ወገን ጥሩ መንፈሳዊ እውቀት ያላቸውን ሰዎች ጠርተው መንፈሳዊ ውይይት አድርገው ያውቃሉ። በእርግጥ ሮዳስ በዚህ ነገር አልተስማማም ነበር።

"እምነትን በሞግዚት ማስተዳደር አይከብድም?" ይላል እየተቆጣ "...አሁን የሞግዚቶቻችም ሀሳብ እንዳቸው አንደኛቸውን ቢረቱ እኛ የረቺውን ሃይማኖት ልንከተል ነው?" ይላል እየተናደደ።



CamScanner

"እኔ ይህን የማደርገው እኔና አንተ በንግግራችን ከመግባባታችን ይልቅ ለሚታዩ እየሆንን መጨቃጨቅና መነታረክ ስላበዛን ነው። ስለዚህ በነዚህ ሰዎች ውይይት ውስጥ አንድ የሚገባን እውነት እናገኝና እንስማማ ይሆን ብዬ ስለማሰብ ነው" ትላለች ሰንፔር እየተብሳጨች።

"ሰን ይሄ ለእኔ የሚያሳየኝ የንግግር ክህሎታችን ደካማ መሆኑን ነው። ነገም ሌላ ነገር ተነጋግረን መግባባትና ችግሮቻችንን መፍታት የማንችል መሆኑን ነው የሚያሳየኝ። ኑሯችንን የምንኖረው እኛ። ስለ እኛ ሕይወት እንደ ተወካይ አለቃ 'ስለ' ብለው የሚወያዩልን ሌሎች..." ይላል እሱም በተራው ብስጭትጭት እያለ።

ሰንፔር እንደዚህ ሲናገራት ይብሱኑ ትናደዳለች "ለዚህ ሁሉ ችግር የዳረከኝ አንተ ነህ። እኔ አይደለሁም። ሃይማኖቴን ሃይማኖትህ አድርገህ ልትቀበል ቃል ገባህ። ቃልህን መልሰህ አፈረስከው። እኔንም ውጥንቅጥ ለበዛበት ፍቅር፣ በትዳር ለማይጠናቀቅ ግንኙነት፣ ላላለምኩት የሕይወት መንገድ መራኸኝ። ሲሆን ሲሆን ይቅርታ ልትጠይቀኝ፣ የማመጣውን የማስታረቂያ ሃሳብ ሁሉ ልትቀበለኝ ይገባል። ካንተ ጋር በሃይማኖት ጉዳይ ሳወራ ሁሌም እናደዳለሁ። እንደተታለልኩ ነው የምቆጥረው። እሱም ብቻ ሳይሆን በልዩነት ለመኖር የሚያስችል ቦታ በውስጤ እንዳይኖር አደረክ። ብዙ ሰው በልዩነት ይኖራል፣ ቢሆንም እኔና አንተ ግን መንገዱን መጀመሪያ ሰብረነዋል።"

"ሰን በግድ ያንቺን ሃይማኖት እንድቀበል ነው የምትፈልጊው?"

"ይኸውልህ እኔ የሰውን ሃይማኖት አከብራለሁ። ማንም ሰው በግድ ሌላ እምነት እንዲቀበል የምፈልግ ሰው አይደለሁም። የእኔና ያንተ ጉዳይ ይለያል። ፍቅር ነው። መጨረሻው በትዳር እንዲቋጭ የምንፈልገው ግንኙነት። ለዚህ ነው የተለያየ ሃሳብ የማቀርበው።"

"አሁን አሁን ሲገባኝ እኔና አንቺ ውይይት ሳይሆን ውሳኔ ነው የሚያስፈልገን። ጥሩ ውሳኔ ማስተላለፍ። በትክክል በየትኛውም ውሳኔ ጉዳት ይደርስብናል። ስለዚህ ከበጣም ጎጂው፣ ገጂውን ብንወስን መልካም ነው።"

"እስኪ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ አንተ ጨክነህ ለምን ፕሮቴስታንት አትሆንም?"

"ለምን እሆናለሁ? ሞክሬው ነበር መሆን ስለማልችል እኮ ነው የተውኩት"

"እስኪ ንገረኝ ምኑ ነው ያገደህ?"

"እየቀለድሽ ነው ሰን?"

"እውነቱን ነው ንገረኝ?"

"ካልሽማ አንደኛው እምነቱ ከኔ እምነት፣ ካለኝ የመጽሐፍ ቅዱስ አረዳድ ጋር በጣም ይጋጫል። ልቀበለው ብልም ምንም ነገር ከራሴ ጋር አልዋሐድ አለኝ።

"ምኑ ነው አልዋሃዳ ያለህ እስኪ?"

"መዳን ምናምኑን ትተነው ለምሳሌ ትውፊትን እንኳ ብንወስድ ትውፊትን አትቀበሉም። ትውፊት ሳትቀበሉ ግን ብዙ ትውፊቶች አሏችሁ። እነዛ የአምልኮ ልምምዳችሁ ደግሞ በጣም ይጎረብጠኛል። ዝማሬያችሁ ከመንፈሳዊነት ይልቅ ስሜትና ስጋዊ ይሆንብኛል፣ ስብከታችሁ ከወንጌል ይልቅ የሰባኪው ጩኸትና፣ 'ተሳክቶልሀል፣ አሁን ድኛለሁ፣ አሁን ሀብታም ሆኛለሁ፣ አጠገብሽ ያለውን እቀፊው፣ ሰላሜ ነህ በይው...' የመሳሰሉት አስተምህሮዎች ደግሞ በጣም ይገፈትሩኛል።"

ሰንፔር በጣም ተናደደች "ሃሃሃ... የእናንተስ ባክህ? ማምለክ የሚገባችሁን አንዱ ኢየሱስ ትታችሁ ዙሪያ ጥምጥም ማርያም፣ ሚካኤል፣ ገብርኤል... ምናምን እያላችሁ ስትሄዱ ነው። ጻድቃን ለምትሏቸው ሰዎች ትዘምራለችሁ። እምነታችሁ ወንድን የበላይ ያደረገ፣ ለሴት ልጅ ክብር የሌለው፣ ሴት ልጅን እንኳን ካህን ሊያደርግ ቀርቶ ቤተ ክርስቲያን ለመግባት እንኳ የወር አበባ አለ የለም እያለ የሚቆጣጠር ኦሪታዊ ሥርአት ይዘህ ነው የፕሮቴስታንቱን የምትነቅፈው?"

"ሰን ለምንድነው ስሜታዊ የምትሆኚው? እኔ ምንድነው የሚጎረብጥህ ስትይኝ ነው መልስ የሰጠሁሽ። ለማንኛውም ያነሳሽው ሃሳብ እንዳንዱን ልመልሰው። በተለይ ስለ ሴት ያነሳሽው። ይህንን ልዩነት ያመጣው ኦርቶዶክስ ሳይሆን ወንጌል ነው። አንድም ቦታ ላይ ሴት ልጅ ኤጲስ ቆጶስ ትሁን አይልም"

ሰንፔር ከአፉ ነጥቃ "አንድም ቦታ ላይ ወንድ ብቻ ኤጲስ ቆጶስ ይሁን አይልም"

"ጥሩ እሱ እውነት ነው። ግን ደግሞ መጽሐፍ 'ዲያቆንም ሆነ ኤጲስ ቆጶስ ስትመርጥ የአንዲት ሴት ባል፣ የወይን ጠጅ የማያበዛ፣ ነውር ነቀፋ የሌለበት፣ ቤተሰቡን የሚያከብር...' ይላል። ይህ የሚያሳየን ዲያቆንም ሆነ ኤጲስ ቆጶስ ወንድ መሆኑን ነው። ኢየሱስም የመረጣቸው ደቀመዛሙርት አሥራ ሁለቱም ወንዶች ናቸው። ወንጌል ላይ በተለያየ ቦታም ሴት ልጅ ሰው በተሰበሰበበት አታውራ፣ የሴት ልጅ ራስ ወንድ... እያለ ይገልጻል።"

"አየህ ያንተ አስተሳሰብ በሃይማኖትህ የተነሳ ኋላ ቀር ነው። ለሴት ልጅ እንኳ ያለህ ቦታ አናሳ ነው። እንዳንተ ያለ ሰው እንዴት ባል ይሆናል? ለዚህ ነው ሃይማኖትህን ሃይማኖቴ አድርጌ መቀበል የሚከብደኝ።"

"ምንም ሊከብድሽ አይገባም። ምክንያቱም የእኔ ሃይማኖት ያመጣው ልምምድ ሳይሆን የፈጣሪ አሰራር ስለሆነ ነው። የእኔ ሃይማኖት ወንድ ሁሉ ይካን አይልም። ከወንዶች ውስጥ ግን የተመረጡት ዲያቆን፣ ካህን፣ ኤጲስ ቆጶስ... ይሁኑ ይላል እንጂ።"

"እኔ እምለው በእናንተ ቤተ ክርስቲያን ሴቶች ነጠላ ለብሰው ቤተ ክርስቲያን ከማሳመር ባለፈ ምንም ተሳትፎ የላቸውም ማለት ነው? ሐዋርያው ጳውሎስ በገላትያ መልዕክቱ ላይ 'አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፤ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፤ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁ' ነው የሚለው። ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመጣ ከለወጠው ነገር አንዱና ዋነኛው ከሰው በታች ከእንስሳ በላይ የሆነችውን ሴት ሊያከብርና ሊያስከብር ነው። ታዲያ እናንተ ከየት አምጥታችሁ ነው ሴት ወንድ የምትሉት?"

"ክህነት ሌላ ሴትና ወንድ እኩል ናቸው ማለት ሌላ። አሁን ያነሳሽው ጥቅስ ለአገልግሎት የተጠቀሰ ሳይሆን ለእምነት የተጻፈ ነው። ገላትያንን ከቁጥር 26 ጀምሮ ስናነበው የእኩልነት ጉዳይ ለአገልግሎት ሳይሆን ለእምነት ነው። ገላትያን ምዕራፍ 3 ቁጥር 26 ላይ እንዲህ ይላል "በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና" ይልና ሴት ወንድ፤ አይሁዳዊ የግሪክ ሰው የለም የሚለውን ቁጥር 28 ላይ ይዘረዝራል። እንደው አንቺ እንዳሰብሽው ገላትያን ላይ ባሪያና ጌታ የሚባል የለም ሁሉም በክርስቶስ አንድና ልዩነት የለም ቢል ኖሮ የዮሐንስ ወንጌልም እንዲያ ባለ ግን የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ቁጥር 16 ላይ ጌታና ባሪያ እንደሚለያይ አስቀምጧል። "እውነት እውነት እላችኋለሁ ባሪያ ከጌታው አይበልጥም። መልእክተኛም ከላከው አይበልጥም" ይላል። ይህ የሚያሳየን ሁላችን ጌታ ኢየሱስን ለማመን እኩል ነን እንጂ እንደየተሰጢችን ግን የተለያየን ነን።

"በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ሴትን ልጅ ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን ሁሉ በላይ ተደርጋ ቅድስት ድንግል ማርያምን ትመሰገናለች ትከበራለች። በዓላትም ሲከበር በዓመት ውስጥ የጌታ ዘጠኝ ጊዜ፤ ለማርያም ግን ሰላሳ ሦስት በዓል ዓላት፤ ከሚጸለየው ጸሎት እና ማሕሌትም ከጌታ ይልቅ የማርያም ይበልጣል።

"በሔዋን ምክንያት ያጣነውን መንግሥት ሰማያት በማርያም በኩል ኢየሱስ መጥቶ ስለመለሰልን፤ ብናጣም በሴት ብናገኝም በሴት ብለን ሴትን ከወንድ እኩል ሳይሆን አብልጠን እናከብራለን። ይኸውልሽ በመንፈሳዊ ሕይወት የሰው ልጅ ሰማያዊ ክብሩ በሕይወት ባለ ጊዜ ባደረገው መንፈሳዊ ተጋድሎ፤ ከሞት በኋላ በሚያሳየው ታምራት ታቦት ሲቀረጽለትና አማልደን ሲባል ነው። እንደ ዓለም አቀፍ ክርስትና ማርያምን እና ሐናን ትተን በኢትዮጵያ እንኳ እንደ ቅድስት አርሴማ፣ ክርስቶስ ሰምራ፣ መስቀል ክብራ፣ እግዚ ኀሪያ... ወዘተ የመሳሰሉት ልክ እንደ ወንዶች ታቦት ተቀርጾላቸው፣ ገድል፣ ታምር ተጽፎላቸው ይነበባል፤ መልክአ ተደርሶላቸው

ይደገማል። ሌላው ሴቶች ሲሞቱ ከወንድ እኩል ፍታት ይፈጸምላቸው፤ የካህን ወይም የዲያቆን ሚስት ከሆኑ ደግሞ ለካህኑ ወይም ለዲያቆኑ የሚደረገው ፍታት፣ ክብር እና ጸሎት ሁሉ ይደረግላቸው።"

ሰንፔር በሮዳስ መልስ አልረካችም እንደውም ተሰላችታለች "ታቦት ምናምን የምትለው ነገር ብዙም አይገባኝም። ተቀረጸላቸው አልተቀረጸላቸው ብዙም ጉዳዩ አይደለም። ዋናው ቁም ነገር፤ የሴትን የመስበክ፤ የመመስከር መብትን ለምን አይከበርም ነው ጥያቄዬ።"

"የምታወሪው ሃሳቤን ለማጣጣል ነው ወይስ ለመግባባት? ላሳይሽ የፈለኩት ቤተ ክርስቲያን ለሴት ልጅ ያላትን ቦታ ነው። ሴቶች እንደ ዕውቀታቸው ርቀት፤ እንደ አዕምሯቸው ስፋት፤ እንደ ተሰጧቸው፤ የቅኔ መምህር፣ ዲያቆናዊት እንዲሁም በትንቢት ሊያገለግሉ ይችላሉ። ከዚያ አልፋ መቅደስ ገብታ አትቀድስም፤ ከዲያቆናዊት ከፍ ብላም አትካንም፤ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ስራዋና አሰራሯ ብዙ እንደመሆኑ መጠን። ብዙ አገልግሎቶችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትፈጽማለች።

"የሴት ልጅ መብት ለምትይው አውሮፓና አሜሪካ የሴት እኩልነት ሳይሉ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሴት ክብርም ሆነ መብት ከወንድ ታስበልጥ ነበር። በመጀመሪያ ሴት ልጅ ከወንድ ግራ ጎን የተፈጠረችበት ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ስትተረጉመው ምን ትላለች መሰለሽ? 'እግዚአብሔር ከእግሩ ሥር ያልወሰደው ሴት የበታች ነች ብሎ ወንዱ እንዳይንቃት፤ ከላይ ከራሱ ያልወሰደው ሴት የበላይ ነኝ ብላ እንዳታስቸግር፤ ከጎኑ ላይ ወስዶ ፈጠራት ይህም እኩልነትን አብሮነት ያሳያል' ይላሉ አባቶች።

"ግሪክና ሮም ያላደረጉትን በኢትዮጵያ ግን ሴት ልጅን ለጋብቻ ለመጠየቅ ሽማግሌ ወደ ቤተሰቦቿ ልኮ ጥሎሽና ውድ ውድ ስጦታን ወንዱ ይሰጣል። በተቃራኒው ግን በምድረ አውሮፓ ለወንድ ልጅ ጥሎሽ ይፈጸም ነበር። ከፍ ሲልም ሴት ልጅ ከባሏ ተጣልታ ከቤቷ ብትወጣ በደለችም ተበደለች ወንድ ልጅ አማላጅ ልኮ፤ ካሳ ክሶ ወደ ቤቱ ይመልሳል። ይሄ ነው እንግዲህ የእምነቱ ትውፊትም እውነትም።"

"የምትሉት ሌላ የሚሆነው ሌላ። እኔ የማውቃት ኢትዮጵያ የወንድ በላይነት የነገሠባት ነች። ወንድ ራስ የሆነበት ቤተሰብ ነው የማውቀው።"

"ለን እሱማ እውነት ነው። '...የወንድ ራስ ክርስቶስ ነው፤ የሴት ራስ ወንድ ነው።' ይህማ የማንሽረው ሃቅ ነው። ይህ ማለት ግን የወንድ የበላይ ነው ማለት አይደለም። አየሽ ልዩነታችን ቃሉ ላይ አይደለም ትርጉም ላይ ስለሆነ ነው።"



CamScanner

## ምዕራፍ ፵፪

## ካሊፎርኒያ-ሎስአንጀለስ

ቶኒ በሎስአንጀለስ መሀል ከተማ ላይ በሚገኘው አሌክሳንድሪያ ሆቴል ውስጥ ነው ያለው። ሚድ ናይት ሮማንስ፣ ድሪም ገርል፣ ዋተር ፎር ኤሌፋንትስ፣ ስፓይደር ማን ሦስትና ዶሚኖ የተባሉ ፊልሞች በዚህ ሆቴል ውስጥ ተቀርጿል።

በአሌክሳንድሪያ ሆቴል ውስጥ ካረፈበት ክፍል ውስጥ ባለው ቢጫ ቀለም ካለው ቅንጡ ሶፋ ላይ እግሩን ዘርግቶ ተቀምጦ ካፒቴን ሞርጋን ውስኪውን እየጠጣ በመስኮቱ አሻግሮ የሎስአንጀለስን እምብርት በዐይኑ እየቃኘ፤ በአዕምሮው ስለ ቀጣይ እቅዱ ያውጠነጥናል።

አሁን ለቶኒ ሁሉ ነገር እንደ ፈለገው እየሔደ ነው። ዘላለም እና ዳንኤል የቶኒን ልብ በሐሴት ሞልተውታል። የኢትዮጵያውያን የተሐድሶ እንቅስቃሴ አጡዘው እዚህ አድርሰውታል። አሜሪካ ያለውን ራሱ ሊፈፅመው ፈልጓል።

ለዚህም ነው ወደ እንግሊዝ ያልተመለሰው። ፓትርያርክ አቡነ መርቆሬዎስን ከዚህ ዓለም ለማሰናበት ወስኗል። ገዳይ መድኃኒት ለመቀመመ በጣም እያሰበ ነው። ሕጋዊ በተባሉ መድኃኒቶች አሳቦ ይግደላቸው ወይም ገዳይ በሚባሉ የእፅ ቅጠል? የሚያደርገው ግራ ግብት ብሎታል።

ቶኒ ውስኪውን ጎንጨት አለና እግሩን እንደ ማፍታታት ብሎ ማሰላሰል ጀመረ። እንደ ናፖሊዮን ቦና ፓርት፣ እንደ እንግሊዙ ጆርጅ ሦስተኛ ሁሉ በአርሴኒክ ሊያሰናብታቸው ፈልጎ ነበር። እንደውም በአርሴኒክ ተመርዘው ክሞቱ በታሪክ በአርሴኒክ ከሞቱ ታላላቅ ሰዎች ውስጥ ስማቸው ይጠቀሳል ግን ያስፈራው አንድ ነገር አለ። አርሴኒክ ሰውነትን ቢጫ ያደርጋል። ስለዚህ ይህ የማይሆን ጥርጣሬ በሌሎች ላይ ሊያስነሳ ይችላል። አቡነ ጳውሎስ ሲሞቱ በባለመስታወቱ ሬሳ ሳጥን መቀበራቸውን ያውቃል እኚህንም እንዲሁም ለትዕይንተ ሕዝብ ክፍት ማድረግ ካሰቡ ጥሩ ላይሆን ይችላል።

"እድሜ ለደራሲ አጋታ ክርስቲ ሲያናይድ ፖታሲየምን በድርሰቷ እያስገባች ዝነኛ አድርጋዋለች። ፓትርያርኩም ለታሪክ ፈጥሯቸው እሳቸውም የፈጣሪ ገጸ ባህሪ ናቸው። ያውም የአንዲት ደሃ ግን አደገኛ አገር የቀድሞ ፓትርያርክ..." ቶኒ አንስቶ በማጨማደድ ብርጭቆው ውስጥ ያለውን ውስኪ ግጥም አድረጎ ጨለጠና ተጨማሪ እየቀዳ "ኦኦኦ እንዳስይሰሙኝ! ለካ በሕይወት ያለ ፓትርያክ የቀድሞ አይባልም። ለማንኛውም እኔ ለእናት አገሬ እንግሊዝ ስል እኩይ ገጸ-ባህሪ፤ እሳቸው ደግሞ ስለ ቤተ ክርስቲያናቸው ሲሉ ምስኪን ሟች ይሆናሉ።" አለና ቶኒ አፉን ከፍቶ

"ሀሀሀሀሀ..." ብሎ ሳቀ "አይ አቡነ መርቆሬዎስ ሸሽተው የመጡት ሞት እዚሁ አሜሪካ ድረስ መጣባቸው" አለ ቶኒ በሹፌት መልክ።

ግን ከሲያናይድ ፖታሲየም ከፍ ያለና በብዙ መቶ ሺጎ እጥፍ በፍጥነት ወደ ሞት ጎዳና የሚልክ የፍልስጤሙን መሪ ያሲር አረፋትን ወደ ሞት ጎዳና የሸኘውን ፖሎኒየምን መጠቀም ፈለገ። ቶኒ ውስጡ አልረካለትም።

በቀማሚ ከተቀመሙ መድኃኒቶች ይልቅ ገዳይ ቅጠሎችን ቢሰጣቸው አሰበ። ወደ ቶኒ አዕምሮ ቶሎ የመጣለት 'ቤላዶና' ነው። ኮሌጅ እያለ የሚያውቃት ጓደኛው ነበረች ስለዚህ ገዳይ ቅጠል ያጫወተችው። የዚህ ተክል ስሙ ራሱ የተወሰደው ከጣልያንኛ ሲሆን 'ቆንጆ እንስት' ማለት ነው። ይህን ተክል በመካከለኛ እድሜ ያሉ እንስቶች የቅጠሉን ጠብታ ዐይናቸው ውስጥ ጠብ ያደርጉና ዐይናቸው ውብና አማላይ ያደርግላቸዋል። ከዚያም በላይ ከዚህ ቅጠል በጉንጮቻቸው ላይ በስሱ ሲያሻሹት መልካም ደም ግባት ይሰጣል። ይሁን እንጂ ይህ አንዲት ቅጠል በአፍ ገብቶ ወደ ሆድ ከደረሰ ግን በአፋጣኝ ይገድላል። ችግሩ ይህን ቅጠል አሁን ማግኘት ያስቸግረዋል።

ስለዚህ ሌላ ቅጠል አሰበ። በምድረ አውሮፓ የነገሠው የዱር ቅጠል 'ሔምሎክ' ይባላል። ይህ ቅጠል ገዳይ ነው። በምርመራም አይታወቅም፤ ችግሩ ግን እንደ 'ቤላዶና' በአንዲት ዘለላ ቅጠል ግዳይን ጠብ አያደርግም። ስምንትና ከዚያ በላይ ቅጠል ይፈልጋል። ይህ ቅጠል ታሪካዊ ነው። የሶቅራጠስን የዚህ ዓለም ቆይታ ፍጻሜ የሰጠው ይኸው ቅጠል ነው።

ግን ለእኚህ መቃብራቸው ለተማሰ ባይገፏቸውም በቅርቡ ወደ ሞት መውረዳቸው አይቀርም ስለዚህ ቶኒ በአዕምሮው ከወጠነው ይልቅ "ሆን ተብሎ መጠነኛ የህክምና ስህተት በመስራት ባሰናብታቸው ይሻላል" አለ። ለዚህ ደግሞ ምቹ የሚሆነው ለስኳር በሽታ የሚወጉትን ኢንሱሊን መጠኑን የሚገላቸው ያክል አድርጎ ቢሰጣቸው የተሻለ ሆኖ አገኘው። ስለዚህ የኢንሱሊኑን መጠን ለሞት የሚያደርሳቸውን ያክል አድርጎ ለሰዓለም ሊሰጠው ወሰነ።

---------//------

ሩቢዮ የወሲብ እርካታ ጥግ ላይ ሲደርስ በከፍተኛ ፍጥነት መተንፈሱን አቁሞ አንድ ጊዜ በረዥሙ ተነፈሰና ከመርሐዊ ጀርባ ላይ ሽርተት ብሎ ወረደና እግሩን ዘረጋግቶ በጀርባው ተኛ። ከዚያም በመጠኑ ፈገግ ብሎ የመርሐዊን ከንፈር በስሱ ሳም አደረገና እራሱን ወደ ሩቢዩ ዘንበል አድርጎ ያወራው ጀመር።

"ተሐድሶው የሚፈልጋቸው ለውጦች ላይ የምትሰራውን ጨረስክ?" አለ ሩቢዮ በወሲብ እርካታ ያላባውን ግንባሩን በቀኝ እጁ እንደ መጥረግ እያደረገ።

"አዎ እየጨረስኩ ነው"

"ባለፈው ካሳየኸኝ ሌላ በተጨማሪ አዳዲስ ነገር ጨምረሀል?" አለ ሩቢዮ ፊቱን አዙሮ በጀርባው እየተኛ

"አዎ ባለፈው በጣም አተኩሬ የነበረው ደኅንነት ላይ ነበር፡፡ መዳን በእምነትና በጸጋ ብቻ፤ አማላጅ ኢየሱስ ብቻ፤ ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ የሚለው ላይ ነበር ያተኮርኩት፡፡ አሁን ግን በዚያ ላይ ሌሎችንም ጨምሬያለሁ፡፡

"ቅዳሴ ላይ ማስተካከያ አድርጌያለሁ ለምሳሌ 'ኢትዝክር ለነ አበሳነ ዘትካት ፍጡነ ይርከበነ ሣህልከ እግዚኦ፡፡'" ግዕዝ እንደማይችል እያወቀ በዜማ ሲቀድስ ሩቢዮ ግራ በመጋባት አፍጥጦ እያየው ነው፡፡ መርሐዊ የሩቢዮ ማፍጠጥ ስለገባው ቃሉን በእንግሊዘኛ ቀይሮ ነገረው፡፡

"ምን መሰለህ ትርጉሙ 'የቀደመ በደላችንን አታስብብን፤ አቤቱ ይቅርታህ ፈጥኖ ይደረግልን' ማለት ነው፡፡ እኔ ይህንን ስቀይረው የቀደመ በደላችንን በደምህ የደመሰስክ አንተ ዛሬም ራራልን ብዬዋለሁ 'ማረን ይቅር በለን' የሚለውን ቃል በአጠቃላይ 'አማልደን እና ራራልን' በሚል ቃል ቀይሬዋለሁ፡፡ ካህኑ 'እኔ' ብሎ ቅዳሴ ላይ የሚናገረውን ቃል 'እኛ' በሚል ቀይሬዋለሁ፡፡

"እኛ ስትል ምን ትርጉም ይሰጣል?" አለ ሩቢዮ ግራ ስለገባው

"ካህኑ እኔ ሲል የካህኑን ማዕረግ እንደተጠበቀ ይሆናል፡፡ እኛ ሲል ግን ካህኑም ምዕመኑም እኩል ሥልጣን ይሰጣቸዋል፡፡" ገባኝ በሚል የአንገት እንቅስቃሴ ሩቢዮ ራሱን ነቀነቀና "ሌላስ?" ብሎ ጠየቀ

"ሌላ ስትል አልገባኝም"

"ማኅበራዊ ኑሮ ላይ? ለምሳሌ መጠጥ ትከለክላለህ?"

"ከዚሁ ጋር ተያይዞ ማኅበራዊ ለውጦች ይኖራሉ፤ ረዥም ጾም አይኖርም ከዚያ ይልቅ ትንሳኤ እና ልደት ሲደርስ የሳምንት ጾምና ጸሎት እንዲኖር ነው ያሰብኩት፡፡ መጠጥ ላልከው ልክ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነው የምሔደው መጠጥ አትጠጡ አልልም፤ እንደውም መጠጥ አስራት ሆኖ ተቀምጧል፤ ስለዚህም ለምን እኔ እቃወማለሁ? አትስከሩ ብትችሉ ምንም አትቅመሱ ብቻ ነው የምለው፡፡ ስካር ግን ኃጢያት እንደሆነ አውጃለሁ፡፡"



CamScanner

ሩቢዮ እንደ መሳቅ ብሎ "አልገባኝም ይሄ ከኦርቶዶክስ የወሰድከውን ትውፊት አትተውም። መጽሐፍ ሙሉ ለሙሉ አትጠጡ ባይልም ግን አለመጠጣትን ነው አበክሮ የሚያጸናው። አስራት ያልከውን ግን አላስታውሰውም ብታሳየኝ?"

"በደንብ አሳይሃለሁ እንደውም ባይገርምህ ጠጣ የሚለው የወይን ጠጅ ብቻ ሳይሆን ብርቱ አስካሪ መጠጥም ጭምር ነው።" ሩቢዮ እስኪ አሳየኝ በሚል ፊት ትክ ብሎ እያየው ነው።

መርሐዊ ስልኩ ላይ ያለውን መጽሐፍ ቅዱስ አወጣና ማንበብ ጀመረ "ዘዳግም ምዕራፍ አስራ አራት ሙሉው የሚያወራው ስለተፈቀዱና ስለተከለከሉ ምግብና መጠጦች ነው። የሚያመሰኳ፣ ሰኮናው የተሰነጠቀ ብሎ ቢልም ከእነሱም ውስጥ የእንስሶችን ስም እየጠራ አትብሉ ይልና ስለመጠጥ ይመጣልሀል። ስለ መጠጥ የሚያወራው ዘዳግም አስራ አራት ቁጥር ሃያ ሦስት ቢጀምርም እኔ ግን ሃያ ስድስት ላይ ያለውን ብቻ ላንብብልህ..." ሩቢዩ በል ቀጥል በሚል አስተያየት እያየው ነው።

"በዚያም በገንዘቡ ሰውነትህ የፈለገውን፣ በሬ ወይም በግ ወይም የወይን ጠጅ...' ስማ እዚህ ጋ ነው ዋናው ነገር ያለው" አለና መርሐዊ ሩቢዮን ቀና ብሎ ተመለከተው። ረቢዮ ምንም ሳይል እየሰማው ነው።

"...ወይም ብርቱ መጠጥ ሰውነትህም የሚሻውን ሁሉ ትገዛለህ፣ በዚያም በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት ትበላዋለህ፣ አንተና ቤተሰብህም ደስ ይላችኋል።' ይኸው ከወይን ጠጅ ከፍ ያለ መጠጥ በእግዚአብሔር ፊት መጠጣት እንደ አስራት እንደሚቆጠር ታያለህ አይደል?"

ሩቢዮ ይህን ቦታ ከዚህ በፊት ቢያነበውም እንዲህ አልተረዳውም ነበርና በአግራሞት ማሰብ ጀመረና አንድ ጥቅስ መጽሐፍ ምሳሌ ላይ ያለው ትዝ ስላለው መርሐዊ ላይ ወረወረው "ምሳሌ ምዕራፍ ሃያ ሦስት ቁጥር ሃያ ላይ 'የወይን ጠጅ ከሚጠጡ ጋር አትቀመጥ ለሥጋም ከሚሳሱ ጋር፣ ሰካርና ሆዳም ይደኸያሉና፣ የእንቅልፍ ብዛት የተቦጫጨቀ ጨርቅ ያስለብሳልና' ይላል ይህንንስ እንዴት ታየዋለህ?"

"ቤብ መልሱ እኮ እዚያው ላይ አለልህ። ጠቢቡ ሰለሞን የከለከለው ሥጋንም ወይንንም ነው። ለምን ወይን ጠጅ ላይ ብቻ እንዳተኮርክ ባይገባኝም ግን ከስር ሲያብራራ ሰካራምና ሆዳም ሲል ገልጾታል። ይህም ከመጠን ማለፍን ነው ለኔ የሚያሳየኝ። ከፈለክ ግን ጥቅስህን በጥቅስ ስመልስ የራሱ የሰለሞን መጽሐፈ መክብብ ምዕራፍ ዘጠኝ ቁጥር ሰባት ላይ 'እግዚአብሔር ሥራህን ተቀብሎታልና ሂድ፤ እንጀራህን በደስታ ብላ፤ የወይን ጠጅህን በተድላ ጠጣ' ይላል።"



CamScanner

ሩቢዮ የመርሐዊ ስመጠጥ እንዲህ ጥብቅና መቆሙ ገረመው "በጣም የተዘጋጀ'ክበት ይመስላል። ምክንያትህ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻና ብቻ ነው ወይስ አንተ መጠጥ ስለምታዘወትር ነው? ለማንኛውም እስኪ ከሐዲስ ኪዳን ማስረጃ ስጠኝ?"

"ተዋ ቤብ እየነገርኩህ ለራሴ ብዬ አይደለም ቃሉ የሚያዘውን ከማድረግ አንጻር ሲሆን፤ ሰውንም በብዙ አታድርግ በሚል ሕግ ውጥር ማድረግ ተገቢ አይመስለኝም። ከሐዲስ ኪዳን ስትለኝ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ አልን እንጂ ሐዲስ ኪዳን ብቻ ያልን አይመስለኝም? አንዳንድ ሰዎች እሱ በገሀድ ስልሳ ሰድስቱን መጽሐፍት ይቀበሉና በግል ግን ሐዲስ ኪዳንን ብቻ ይቀበላሉ። ማስረጃም እንድትሰጣቸው የሚፈልጉት ከሐዲስ ኪዳን እንጂ የብሉይ ኪዳን ማስረጃን እንደ ቅዱስ ቃል መቀበል ይከብዳቸዋል። ለማንኛውም አንደኛ ጢሞቲዎስ ላይ ምዕራፍ አምስት ቁጥር ሃያ ሦስት ላይ 'ስለ ሆድህና ስለ በሽታህ ብዛት ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ እንጂ፤ ወደ ፊት ውኃ ብቻ አትጠጣ' ይላል።"

## ምዕራፍ ፵፫

## አዲስ አበባ-ሳሪስ

የነ ሰንፔር ቤት ሳሎን ነጭ ቀለም የተቀባ ሲሆን ቤቱ እርጋታና ሰላም የሰፈነበት ነው። ቢሆንም በሰንፔር አዕምሮ የሚንጎማለለውን ብዥ ያለ ሀሳብ፣ ያልተጨበጠ እውነት፣ የተደበቀውን የመፈለግ፣ የደፈረሰውን ለማጥራት ከራስ ጋር የምታደርገው ትንቅንቅ አድክሟታል። ከፊት ለፊቷ በፔርሙዝ ውስጥ ቡና አስፈልታ ያስቀመጠች ሲሆን፣ የምትጠጣበት ሲኒ፣ ስኳር ማቅረቢያና ኩኪስ ያለበት ባለ አበባ ሳህን አለ። ሰንፔር ብዙ ቡና ብትጠጣም ራስ ምታቱ ሊለቃት አልቻለም። ስለዚህ የጀርመን ካምፓኒ፣ የ'ዴንክ' ምርት የሆነውን 'ዳይክሎፌናክ' የተባለ የህመም ማስታገሻ ክኒን ዋጠች።

ሰንፔር ቀልቧን ሰብሰብ አድርጋ ፊደሉ ላይ የተጻፈውን ቃል ለመፍታት ጥረት እያደረገች ነው። 'ዱታጻዪ' የሚለውን ቃል ለመተርጎም የተቻላትን ጥረት እያደረገች ነው። ቢሆንም ጠብ የሚልላት ነገር ልታገኝ አልቻለችም። ቃሉን አባቷ ባስተማራት መሠረት ደመረችው የመጣላት ውጤት 509 ይላል። አምስት መቶ ዘጠኝ ቁጥርን ደመረችው አካፈለችው ጠብ ያለ መልእክት አልሰጣት አለ። ሁሉንም ትታ ዐይኗን ጨፍና ማሰብ ጀመረች።

ሰንፔር በአዕምሮዋ ውስጥ አንዳች ነገር ሲመጣ ታያት። በፍጥነት ነቃ እንደ ማለት ብላ ስልኳን እንደ መፈለግ አለች። አዕምሮዋ በተደጋጋሚ 'አናግራም አናግራም' ሲል ይሰማታል። ስልኳን አንስታ ኢንተርኔቱን አበራችውና 'እንዴት አናግራም ይፈታል' የሚል ሐረግ አስቀምጣ ፈልግ የሚለውን ተጫነች።

በተደጋጋሚ አባቷ የውጪ አገር መጽሔትና ጋዜጣ እያመጣ ለእሷም ለወንድሟም "ኑ ልጆች ይህን አናግራም ፍቱና አሳዩኝ? ቀድሞ የፈታ ይሸለማል" እያለ ያዛቸው ነበር። ማዕረግ ብዙም አናግራም መጫወቱን አይፈልገውም። ትንሽ ይሞክርና ጥሎት ይሄዳል። ሰንፔር ለፍታ ለፍታ ትሠራና ለአባቷ ታሳየው ነበር። አባቷም "ጎበዝ የኔ ልጅ! አንቺ በትክክል ትደርሽበታለሽ በትክክል" እያለ አቅፎ ይስማታል።

ሰንፔርም "ምኑን ነው የማገኘው አባዬ ጎበዝ ሠራሽው አልከኝ አይደል እንዴ?" ትላለች።

"ልክ ነው የዛሬውንማ መልሰሻል፣ ነገ ደግሞ ሌላ ከባድ አናግራም ሲመጣብሽም እንደማታሳፍሪኝ ስለማውቅ ነው የኔ ጀግና" ይላታል ጸጉሯን እየዳበሰ።

ሰንፔር አዕምሮዋ ውስጥ ከሚመላለሰው የአባቷ ትዝታ መለስ ብላ ኢንተርኔቱ ያመጣላትን መረጃ ማንበብ ጀመረች።

"እናግራም ማለት ተዘበራርቀው የተቀመጡ ፊደሎችን ወይም ቃላትን ወደ ትክክለኛው አደራደር አምጥቶ ትርጉማቸውን መረዳት ነው። ለምሳሌ ራሱ 'እናግራም' የሚለው ቃል 'ናግ-አ-ራም' በሚል የቃላት አዘበራረቅ ልናስቀምጠው እንችላለን።

"እናግራም ከሙሴ ጊዜ ጀምሮ ታሪክ አለው። በጊዜው የሰዎችን ስም ታሪክና ፍቺ ያለው ማድረግ የተለመደ ነበር። ሰዎች እናግራም የሚጠቀሙት ምስጢራዊ መልእክትን ሰውረው ለተፈለገው ሰው ማስተላለፍ ሲፈልጉ ነው።

"ሌላኛው ስቴጋኖግራፍ ወይም ሥውር ጽሑፍ ይባላል። ይህን ምስጢራዊ የአጻጻፍ ዘዴ የሚጠቀሙት ጽሑፍን ከሌሎች ሰዎች ሰውሮ ለተላከለት ሰዎች ብቻ ለማድረስ ነው። ይህን ዘዴ ሄሮዶተስ የተባለ የታሪክ ጸሐፊ እንደ ዘገበው ከሆነ በስደት ፋርስ የሚኖር አንድ ግሪካዊ የፋርስ መንግሥት የትውልድ አገሩን ሊወርበት መሆኑን ሲያውቅ ለወገኖቹ ለማስጠንቀቅ ብሎ በእንጨት ላይ ፋርስን ግሪክ ሊወር እንደሆነ ጻፈና ጽሑፉን ሰም ቀባው። ግሪኮች ቀድመውም እንዲህ ያለ ዘዴ ይጠቀሙ ኖሮ መልእክቱ በትክክል ስለደረሳቸው ራሳቸውን ከፋርሱ ንጉሥ ጠረክሲስ አስጣሉ።

"በዚህ ዘመን ስቴኖግራፍን ከምንጠቀምባቸው ዘዴዎች መካከል በሰነዶች ላይ የባለቤትነት መብትን ለማመልከት ሥውር ምልክቶችን አሳንሶ ወይም የነጥብ ያህል ማስቀመጥ ነው። ስለዚህም ያን ነጥብ የሚያክለውን ነገር በማሳደግ ማንነትን ማሳየት ይችላል። ይህን ዘዴ በተለየ ሁኔታ የብልግና ሥዕሎችን በጣም አሳንሶ ተራ ነጥብ በማስመሰል ማስተላለፍ ነው።" ሰንፔር ስቴኖግራፍ ከእሷ ጋር የሚያገናኘው ብዙም ነገር እንደሌለ ስለተሰማት ወደ ቀጣዩ ጽሑፍ ቀጠለች።

"ክሪፕቶግራፍ ወይም ሥውር ቃል ይህኛው ዘዴ ደግሞ መልእክቱን ሳይሆን የመልእክቱን ትርጉም በመሰወር የመልእክት ልውውጡን ምስጢራዊ ማድረግ ነው። የጥንቶቹ ስፓርታውያን ስኪታሊ ተብሎ የሚጠራ ተራ የሆነ አጭር ዱላ ላይ ረዥም ቆዳ ይጠመጥሙበትና መልእክቱ ከላይ ወደ ታች ይጽፋሉ። ቆዳው ሲፈታ የሚሰጠው ምንም ትርጉም አይኖረውም፣ ነገር ግን መልእክቱ የተላከለት ሰው ከመጀመሪያው ጋር ተመሳሳይ የሆነ ዱላ ፈልጎ ቆዳውን መልሶ ይጠቀልልና በቀላሉ ማንበብ ይችላል።" ሰንፔር አሁን ያነበበችውም ነገር ምንም እሷ ካገኘችው ጋር የሚገናኝ ስላልሆነ፣ ፍንጭ ሊሰጣት አልቻለም ስለዚህ ንባቧን ቀጠለች።

"ሌላኛው ዘዴ ደግሞ ሳይፈር ተብሎ የሚጠራው ፊደሎችን በሌላ ፊደል መተካት የሚሠራበት ዘዴ ነው።" ሰንፔር የሰውነቷ ሕዋሳት ሲነቃቁ ተሰማት። ልቧ በድንጋጤ እንደ ድቤ መደለቅ ጀመረ። የልቧን ድለቃ እንደ ምንም እምቅ አድርጋ ንባቧ ላይ አተከረች።

"ጁልየስ ቄሳር መልእክቶች ወደ ጦር ሜዳ ሲልክ ሳይፈር የተባለውን ዘዴ በመጠቀም ፊደልን በፊደል እየተካ ይጽፍ ነበር። በዚህ ዘዴ ውስጥ የፊደል ቅደም ተከተል ትልቅ ሚና ይጫወታል። ለምሳሌ 'A' ለመጻፍ ሦስት ፊደል ተዘሎ 'D' ይጻፋል፤ 'B' ለመጻፍ ደግሞ 'E' ይጻፋል። ይህ የአጻጻፍ ዘዴ በአውሮፓ በይበልጥ የተራቀቀው በዘመነ ተሐድሶ ነው።..." ሰንፔር በትክክል እሷን የሚመለከት ጽሑፍ እንደሆነ ገባት። ልቧ መደለቁን አላቆመም ጭራሽ ጽሑፉን ማንበብ ስላቃታት ወደ ራሷ ጽሑፍ ተመለሰች።

ፊት ለፊቷ ላይ ባለ መስመር የደብተር ቅዳጅ ወረቀት ላይ የጻፈችውን 'ዩታጻዪ' የሚለውን ቃል ለመፍታት አሰበች። ከላይ ባነበበችው ጽሑፍ መሠረት ቃሉን ለመፍታት ፊደሏን አቅርባ ማየት ጀመረች።

የመጀመሪያውን 'ዩ' የሚለውን ፊደል ጻፈችና ወደ ፊደል ገበታው ሄዳ መቁጠር ጀመረች። በአማርኛና በግዕዝ ፊደል ገበታ ውስጥ አናባቢ የሚባሉት የፊደል 'አ' ዘሮች ከሌሎች ተናባቢ ፊደሎች ጋር ቃላዊ ውሕደት በመፍጠር ሌሎች ድምጾችን ይፈጥራሉ። ስለዚህ በግዕዝም ሆነ በአማርኛ ፊደልን በፊደል ተክቶ ለመጻፍ ሌሎች ፊደሎችን ከመጠቀም ይልቅ በአንድ ፊደል ውስጥ ያሉ ፊደላትን ቦታ በመቀያየር ሊጠቀም ይችላል ብላ ስላሰበች እዚያው ፊደል 'የ' ቤት ሦስት ቀንሳ መቁጠር ጀመረች።

ሰንፔር ልክ እንደ ሒሳብ ቀመር በመጀመሪያ 'A=D' ብላ ጻፈች። "እንግሊዘኛውን ኤ ለመጻፍ ዲ ከተጠቀመ በዚህ መሰረት አማርኛውም ሀን ለመጻፍ ሌላኛውን ሃ እንደ መጠቀም ማለት ነው" ብላ ቀመር አወጣች። "ስለዚህ..." አለች ሰንፔር ከሌላ ሰው ጋር እንደሚያወራ ድምጿን ከፍ አድርጋ።

"...ስለዚህ ዩ ተብሎ ሲጻፍ ምን ማለት ነው?" ብላ ወደ ፊደል ገበታው ተመለሰችና ከፊደል 'ዩ' ወደ ኋላ ሦስት ፊደል ቆጠረች። ያገኘችው 'ዩ' የሚለውን ፊደል ነበር። ከዚያም ፊደሉ ላይ ያገኘችው ቃል ላይ ከእያንዳንዱ ፊደል ወደ ኋላ ሦስት ሦስት ቆጥራ ያገኘችውን ፊደል ገጣጠመችው። 'ዩተጸዮ' የሚል ቃል ሰጣት። ሰንፔር ግራ ገባት 'ዩተጸዮ' ግራ ገባት "ምንድነው? ሌላ እደናጋሪ ቃል" አለች ሰንፔር ፊቷን አኮሳትራ።

## ምዕራፍ ፵፬

## ካሊፎርኒያ-ሎስአንጀለስ

መልከ መልካም ቀይዳማ ፊቱ እንደ ነሐሴ ሰማይ ዳምኗል፡፡ እንዲህ ያለ የከፋ ነገር ማድረግ ይከብደዋል፡፡ ለስላሳ እጁ ለሰላምታ ከመዘርጋት ውጪ የሰው ሕይወት ለመቅጠፍ ከዚህ ቀደም ተሰንዝሮ አያውቅም፡፡ ቀጠን ብሎ ለግላጋ ቁመናው እንደዚህ አይነት ክፋትን የሚሸከም አልሆነለትም፡፡ የገዛ ሰውነቱ ለራሱ ከብዶታል፡፡

ለዓለም ዛሬ የመጨረሻውንና ትልቁ ተልእኮ ተሰጦታል፡፡ አቡነ መርቆሬዎስን እንዲያሰናብታቸው፤ ኢንሱሊን በመርፌ ውስጥ ተደርጎ እንደሚሰጠው ተነግሮታል፡፡ ሰሞ አቡነ መርቆሬዎስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ልዩነት ሳያጠቡ ለባለ መለያየትና መከፋፈል ዳርገዋት ይቺን ዓለም ይሰናበታሉ፡፡

ለዓለም ጨንቆታል፡፡ በዚህ ልክ መጨከን አልቻለም፡፡ ብቻውን ከራሱ ጋር ማውራት ጀመረ ‘ሥልጣነ ትርክናው ከአቡነ መርቆሬዎስ ከወጣ አውሮፓና አሜሪካ ያለው የስደተኛው ሲኖዶስ ኦርቶዶክስ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በጣም አስቸጋሪና ብልሹ ይሆናል፡፡ በእርግጥ አሁንስ ፓትርያርኩ መች ይመሩታል? ቢሆንም ውስጥ ለውስጥ ያለው ልዩነት በገሀድና ዐይን ባፈጠጠ ሁኔታ ይለይለታል፡፡ ከዚህ የባሰ ከባድ የቀኖናና የዶግማ ልዩነት ይመጣል፡፡ ስለዚህ ፓትርያርኩ ሲሞቱ ሳይሆን ሲሰነብቱ ግድ ነው፡፡’ አለ ለዓለም ሳይታወቀው ከአንደበቱ ድምጽ አውጥቶ፡፡ ይህን ግን የሚረዳው ሰው ያስፈልገዋል፡፡

ለዓለም ሳይፈልግ ከላዩ ላይ የተጣባውን ችግር የሚያዋየው፤ ጭንቀቱን የሚያካፍለው ሰው ሲፈልግ ቶሎ ወደ አዕምሮው የመጣው ዲበኩሉ ነው፡፡ ዲበኩሉ አሜሪካ ውስጥ በውስጥ ደዌ ሕክምና ስፔሻላይዝ የሚያደርግ የሕክምና ተማሪ ነው፡፡ መንፈሳዊ እውቀቱ በጣም ጥሩ የሚባል ነው፡፡ የድቁና ማዕረግም አለው፡፡ የሚያገለግለው አሜሪካ ካለው ስደተኛው ሲኖዶስ ሳይሆን ኢትዮጵያ ባለው ሲኖዶስ በሚመራው ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡

ዲበኩሉ በአቡነ መርቆሬዎስ የሚመራውን ሲኖዶስ ኢትዮጵያ ካለው ሲኖዶስ ጋር የማቀላቀል እቅድ ይዞ የሚንቀሳቀስ ነው፡፡ ጎልሙ የግል እንዲሁም ስሜት ወለድ አይደለም፤ ይልቁንስ በእቅድ የሚከወን እንጂ፡፡ ይህን እንቅስቃሴ ለዓለም በደንብ ታዝቧል፡፡ ይህ ሕቡዕ ቡድን ሦስት አላማ አለው፡፡

አንደኛው በእርቅና በድርድር ስደተኛው ሲኖዶስን ከኢትዮጵያው ሲኖዶስ ማቀላቀል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ወጥና ያልተሸራረፈ ቀናና ዶግማ ተጠብቆ የአባቶች ልዩነት እንጂ የአስተምህሮ ልዩነት እንዳይፈጠር መሥራትና ዘመን ሲፈቅድ እንዲዋሐዱ ምቹ መደላድል መፍጠር፤ ሌላው አደገኛ የሚባለው መንገድ ደግሞ በስደተኛው



CamScanner

ሲኖደስ ሥር ያሉ አብያተ ክርስቲያናትን ወደ ኢትዮጵያው ሲኖዶስ ለማቀላለቀል ጥረት ማድረግ።

እንደውም ይህ ሕቡዕ ቡድን አንድ ቤተ ክርስቲያንም ከስደተኛው ሲኖዶስ ወደ ኢትዮጵያ የሚመራው ሲኖዶስ ቀላቅሏል። ለዓለም የሕቡዕ ቡድን አላማ እያወቀ ዝም ያለበት ዋና ምክንያት ነገ መሸሸጊያ ይሆኑኛል ብሎ ነበር። አሁን ሰዓቱ የደረሰ ይመስላል። ለዓለም ዲበኩሉን ይወቀው እንጂ አሜሪካ ውስጥ ባሉት ከተሞች ሁሉ ይህን ሥራ የሚሠሩ የተማሩና መንፈሳዊ ወጣቶች ብዙ ናቸው። ለዓለም ይህን ጥብቅ ምስጢር ለዲበኩሉ መንገር ስለፈለገ እንዴት ሊያገኘው እንደሚችል በጥንቃቄ ማሰላሰል ጀመረ።

----//-----

## ኢትዮጵያ-አዲስ አበባ

ጭንቅላቷ ላይ የእዝኑን ባለ ጥቁር ቀለም ሻሽ ገርዳሳ አስራለች፤ ከላይ ደግሞ ሰፊና ወፍራም ሹራብ ለብሳለች፤ ከስር ፈዘዝ ያለ አረንጓዴ ቱታ አድርጋ ሁለት ሰው የሚያስቀምጠው ሶፋ ላይ እግሯን ሰቅላ ተቀምጣለች። ሲያዩት ልብን ጥፍት የሚያደርጉት የእግሮቿ ጣቶችን ሳታውቀው እያንቀሳቀሰቻቸው ነው። ሰሞኑን ባተሌ ሆና ስላልተንከባከበቻቸው እንደ ጎበዝ ሠዐሊ ቅርፅ በጥንቃቄ በእግሮቿ ጣቶች ላይ የተሰካኩት ውብ ጥፍሮቿ እንደወትሮው በቀለም አላሸበረቁም ይልቁንስ ቀድሞ የተቀባው የጥፍር ቀለሟ ግምሹ ለቆ ግማሹ ደብዝዞ ያረጀ ቤት ግርግዳ መስሏል።

ሰንፔር አልፈታ ያለ ምስጢር፤ ውሉ ያልለየ ፍቅር፤ አባትን በሞት መነጠቅ አንድ ላይ ተደማምረው ውስጧን ሰቅዝ አድርገው በጭንቀት ይዘውታል። ትርጉሙ አልገባ ያላትን ቃል በጉንጯ ውስጥ እንዳለ አኞ ሥጋ ከአንድ ጉንጭ ወደ ሌላ ጉንጭ ታንከላውሰዋለች። አትውጠው ለጉሮሮ ከባድ ሆኖ ያንቃታል ቢሆንም ማንንለሱን መቀጠል አልፈለገችም።

'ዩተጰዮ' የሚል ቃል ትንሽ ፍንጭ የሚሰጥ ነገር አለ፤ ግን ደግሞ ሙሉ ለሙሉ ቁርጥ ያለ ነገር አላገኘችም። አንድ የሳተችው ነገር ይኖራል። እስከ አሁን ድረስ በሄደችበት ልክ 'ዩተጰዮ' የሚል ቃል ሰጥቷታል። ይህ በመጀመሪያው 'ዬታጳዪ' ከሚለው ቃል የተሻለ የመነበብ እድል ቢኖረውም ምንም ትርጉም ሊሰጣት አልቻለም። ስለዚህ ዐይኗን ጨፍና በጥልቀት ማሰብ ጀመረች። "ምን ማለት ነው? 'ዩተጰዮ' ምን ሊል ፈልጎ ነው? ወይስ ሌላ የአፈታት መንገድ ይኖረው ይሆን?"

አዕምሮዋ ውስጥ አንድ ነገር ሲመጣ ተሰማት እሷም በቃል ተናገረችው "ለምን ሦስት ሦስት ፊደል ብቻ እየተዘለለ ለምን?" አለች ሰንፔር። "ለምን በሦስት ብቻ እስኪ ሦስትን መነሻ አድርጌ ከዚያም በአራት በአምስት ፊደል ልዩነት ልየው" ብላ



CamScanner

እግሯን ከሰቀለችበት የሶፋ ጠርዝ መሬቱ ላይ ካለው እንደ እስፖንጅ ከሚደላው ነጠላ ጫማ ላይ ሰካችና ወደ ጠረጴዛው አጎንብሳ መጻፍ ጀመረች።

በድጋሚ 'ዬታጳዪ' የሚለውን ቃል ጻፈችና የፊደል ገበታዋን አመጣችና መቁጠር ጀመረች። የመጀመሪያው ፊደል 'ዩ' ነው። ቀጠለች በሦስት ፊደል ሳይሆን በአራት ፊደል ልዩነት ከፊደል 'ታ' በፊት አራት ፊደል ቆጠረች አራተኛው ፊደል 'ቶ' ሆነ። ሰንፔር "ምን የሚል ቃል አገኝ ይሆን?" ብላ እያሰበች ነው።

ከፊደል 'ጳ' በፊት አምስት ፊደል ቆጠረችና ፊደል 'ጵ'ን አገኘች። የመጨረሻው ፊደል 'ዪ' ነው። ከ'ዪ' ፊደል ወደ ኋላ ስድስት ፊደል ቆጠረችና ፊደል 'ያ'ን አገኘች። ሰንፔር በጣም ቸኩላለች። እጇ ይንቀጠቀጣል፤ እስኪብርቶውን የጨበጡት ጣቶቿ በላብ ወርዝተዋል።

ሰንፔር ፊደሎቹን ገጣጠመችና 'ዩቶጵያ' የሚለውን ቃል አገኘች። በትክክል ትርጉም ይሰጣል። ዩቶጵያ የሚለውን ቃል አባቷ በተደጋጋሚ ሲያነሳ ሰምታዋለች። "ዩቶጵያ እኮ እኛ ነበርን፤ ዩቶጵያ አሁንም እኛ እንሆናለን" ይላል።

"ያ ስቃይና መከራ የሌለበት፤ ሰዎች በረጋ ማኅበራዊና መንፈሳዊ ሕይወት የሚኖሩበት፤ ማጣትና ስስት ያልተንሰራፋበት ዓለም፤ ይህቺ የእኛ አገር ኢትዮጵያ ነች። እኛ ልጆች የተወሰደብንን የአባቶቻችንን አገር ዩቶጵያን ልንመልስ ይገባል።" ይል ነበር ፓስተር ናፍያድ።



CamScanner

## ምዕራፍ ፺፰

## አዲስ አበባ-መስቀል አደባባይ

ማዕረግ ሙሉ ጥቁር ሱፍ ለብሶ፤ ለዐይኑ መሸፈኛ ጥቁር መነጽር አድርጓል፡፡ ከመኪናው ሲወርድ ልክ እንደ ታዋቂና ተወዳጂ ከያኒ ብዙ ሰዎች ግር ብለው እየሄዱ ያቀፉታል፣ ይጨብጡታል፣ ያጽናኑታል፡፡ ማዕረግ በሰዎች መከበቡ የሰጠው ደስታ ልዩና ሊቆጣጠረው የሚችለው አይደለም፡፡ ለሁሉም ምስጋናና አክብሮቱን እየሰጠ፤ በሰዎች ታጅቦ ወደ ሰልፉ ተቀላቀለ፡፡ ሰንፔር ሰልፉ እንደቀረባት እያንጓ እንደሚነግራት እያሳበ በልቡ ሐሴት አደረገ፡፡

መስቀል አደባባይ በሰዎች መጨናነቁን ቀጥሏል፡፡ መፈክር የያዙ፣ ባዶ እጃቸውን ያሉ፣ የዘነጡ፣ እንደ ነገሩ የለበሱ ሰዎች... በጥድፊያ ከሚኒባስ፣ ከግል መኪና እና ከትላልቅ አውቶቢሶች በጥድፊያ ይወርዳሉ፡፡ አደባባዩ ላይ ነጠላቸውን ያጣፉ ወንድና ሴቶች በብዛት ይታያሉ፤ ብዙም ባይሆን ጥቂት መንፈሳዊ ልብስ የለበሱ የወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያን መምህራን ሰልፉን ለማስተባበር ከወዲያ ወዲህ ተፍ ተፍ ሲሉ ይታያሉ፡፡

በሕብረት ሆነው መንፈሳዊ ትምህርት የሚማሩ እንዲሁም የሚዘምሩ አሉ፡፡ አንድ ቦታ ላይ በተለየ ሁኔታ ወጣቶቹ በሕብረት ሆነው የኦርቶዶክስ ዘማሪ የሆነችውን የምርትነሽን መዝሙር በጋራ እየዘመሩ ነው፡፡ ዘማሪዎቹ በስሜት ጭልጥ ብለው ራሳቸውን ሲስቱ ምንም አልቀራቸውም፡፡ ከበሮ የሚመታው ልጅ ዐይኑን ጨፍኖ በስሜት ነው ከበሮውን የሚመታው፡፡

"ይደንቀኛል ለዘላለም የሰለጠነ ስም ሰምቼ

እኔም ወጣሁ ከእስራት ይህን ስም ጠርቼ ኢየሱስ!

እስኪ ሞት ይደንግጥ ይህንን ስም ልጥራ

ገዳዩን ላድነው ልውጣ ልሰማራ

ተው አታክሩብኝ አትግፏት እውነቱን

በጸናው አለት ላይ ላንጽበት ቤቱን

ላንጽበት ቤቱን ኢየሱስ! ..."

በመዝሙር ተመስጠውና ካለው ችግር ጋር እያገናኙ እያለቀሱ የሚያጨበጭቡ አሉ፡፡ መዝሙሩን በደስታ፣ በፍቅር፣ በተመስጦ፣ እጃቸውን ወደ ሰማይ ከፍ አድርገው፣



CamScanner

ዐይናቸውን ጨፍነው፣ የሚዘምሩት ብዙ ናቸው። ሰላማዊ ሰልፉ ላይ ያሉት የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች መዝሙሩ የኦርቶዶክስ ስለሆነ ከሰልፉ ጋር ተቀላቅለው አብረው ይዘምሩ ጀመር።

"…ማልጄ ልገስግስ ሰልፍ አለብኝ ዛሬ

ወንጭፌና ቀስቴ አንተው ነህ ጠጠሬ

ከሞት የዳንኩበት ማምለጫው አለቴ

ኃይል እስታጣቂዬ ቅደምልኝ ፊቴ

ቅደምልኝ ፊቴ ኢየሱስ! …"

በእልታታና በጭብጨባ፣ በፉጨት ዝማሬው ቀልጥ አለ። ሰልፉ ውስጥ ሌላ ቦታ ደግሞ በስሜትና በቁጣ የሚንቀለቀሉ ወጣቶች በኮምፒውተርና በማርከር የተጻፉ መፈክሮቻቸውን ወደ ላይ ብድግ አድርገው ይታያሉ። ብዙዎቹ መፈክሮች አንድ ዓይነት ሐሳብ ነው ያላቸው። አንዳንዶች የማኅበረ ቅዱሳንን አርማ ከኢሉሚናቲ ጋር አስተካክለው ሰርተው መፈክሮቻቸው ላይ ሰቅለዋል። ሌሎችም የፓስተር ናፍያድን ፎቶ በባነር አሰርተው፣ ከፎቶው በላይ 'የወንጌል አርበኛ' ብለው ጽፈውበት ይዘውታል። መስቀል፣ እንዲሁም ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ የተለያዩ ጥቅሶች ያንጠለጠሉም በብዛት ይታያሉ።

ከመፈክሮቹ ውስጥ የሚበዙ 'ኦርቶዶክስ ወንድም እህቶቻችንን እንወዳለን፣ ኦርቶዶክስ እህት ቤተ ክርስቲያን ነች፣ ኦርቶዶክስ የኢትዮጵያዊነታችን አንዱ ጠባቂም ተሸካሚም ነው፣ ፓስተር ናፍያድ ለእኛም አባት ነው፣ ኦርቶዶክስና ፕሮቴስታንት ሁሌም ወንድማማቾች ነን፣ ማኅበረ ቅዱሳን አሸባሪ ነው፣ ማኅበረ ቅዱሳን በወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያን እና በኦርቶዶክስ መካከል ልዩነትን ያሰፋ ነው፣ ማኅበረ ቅዱሳን የአክራሪዎች መመሸጊያ ነው፣ ማኅበረ ቅዱሳን ደም የጠማቸው መሰብሰቢያ ነው፣ ማኅበረ ቅዱሳን ነፍሰ ገዳይ ነው፣ ማኅበረ ቅዱሳን ሰይጣን፣ ማኅበረ ቅዱሳን የድሮ ሥርአት ናፋቂ፣ ማኅበረ ቅዱሳን የዘመኑ ፈሪሳውያን፣ ማኅበረ ቅዱሳን የወንጌል አርበኞች አሳዳጅ፣ ማኅበረ ቅዱሳን የነፍጠኞች ማኅበር ነው!…' የሚሉ ናቸው።

መፈክር ያንጠለጠሉት ሰዎች ከሰልፉ ፊት ለፊት ቀደም ቀደም እያሉ ሲሔዱ፣ የጋራ ሕብረ ዝማሬ የሚያሰሙ ደግሞ ከኋላ እየተከተሉ ወደ ፓትርያርኩ ጽሕፈት ቤት ማምራት ጀመሩ።

የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ጨምሮ የብሔር ብሔረሰቦች ባንዲራ ከፍ ብሎ ይታያል። የሰልፉ ታዳሚ የሆኑም ያልሆኑም፣ ሞባይሎቻቸውን እያወጡ ይቀርጻሉ። ከተለያዩ



CamScanner

መገናኛ ብዙኃን ሰልፉን ለመዘገብ አሰፍስፍው ወጧ እንዳማረላት ሴት ከወዲያ ወዲህ ጉድ ጉድ የሚሉ ጋዜጠኞችና ካሜራማኖች ይታያሉ፡፡

----//----

## አዲስ አበባ-አራት ኪሎ

የፓትርያርኩ ጽሕፈት ቤት በፌደራል ፖሊሶች ተከቧል፡፡ አድማ በታኝ ፖሊሶች ራቅ ራቅ ብለው ሰልፈኛውን ሕዝብ በጥንቃቄ ይመለከታሉ፡፡ ትላልቅ ኦራል መኪኖች ላይ የተቀመጡ ፌደራል ፖሊሶች ሙሉ ትጥቃቸውን ታጥቀው በተጠንቀቅ ቆመዋል፡፡ አራት ኪሎ የትራንስፖርት አገልግሎት ተቋርጦ በሰልፈኞች ተጥለቅልቋል፡፡ ሰልፈኞቹ ከአራት ኪሎ ዩንቨርስቲ እስከ አምስት ኪሎ ዩንቨርስቲ ያለውን ቦታ ሞልተውታል፡፡

ቅድስተ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ያለው የማኅበረ ቅዱሳን ዋና ቢሮም በፌደራል ፖሊሶች ተከብቧል፡፡ ወደ ማኅበረ ቅዱሳን ሕንጻ ኃዘን ፊታቸውን የዳመነ፤ የእምባ ብዛት ዐይናቸውን ያሳበጠው፤ ቁጭት ግብግብ ያደረጋቸው፤ እልህ የተናነቃቸው በድምጽ ያልወጣ የአካል ቁጣ የሚንጸበረቅባቸው ወጣቶች ሲገቡና ሲወጡ ይታያሉ፡፡

ማዕረግ እና ሌሎች አስር ሰዎች ተመርጠው ለፓትርያርኩ የአቋም መግለጫቸውን ሊያነቡ ወደ ፓትርያርኩ ጽሕፈት ቤት ገብተዋል፡፡ የፓትርያርኩ በር ላይ ብዙ ሰው ክብ ክብ እየሰራ ዝማሬ እያሰማ ነው፡፡ ቅድም የኦርቶዶክስ ዝማሬን ይዘምሩ የነበሩ ወጣቶች በድጋሚ የዘማሪት ምርትነሽን መዝሙር እየዘመሩ ነው፡፡

"እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም አንዋጋም አሜን

መንፈስ ነውና ባላጋራችን

እንደ ዓለመ ጥበብ አንዘምትም አንዘምትም አሜን

ሰይፍ አናነሳም ለክፋታችን

የታለ ስሙ ያ ከፋታችን

የታለ ጸሎቱ መሰወሪያችን

የታለ ቃሉ ደማሚታችን

የታለ ኢየሱስ ፊት አውራሪያችን..."

ዐይኑን ጨፍኖ ከበሮ ሲመታ የነበረው ልጅ ከበሮውን ለሌላ ሰው ሰጥቶ ነጭ ነጠላ አገልድሞ ዝማሬውን እየመራ ነው፡፡ "የታለ ኢየሱስ?" የሚለው አዝማች ላይ ሲደርስ ኢየሱስን እንደሚፈልግ ሰው አንገቱን ዞር ዞር ያደርገው ጀመር፡፡

"…ስሙን ይዘን እንቃትታለን በፊቱ

ወትሮም ጸሎት ነው የአማኝ ጉልበቱ

ጎንበስ ጎንበስ እስኪ ዝቅ ዝቅ ለጌታ…"

መሀል ላይ ሆኖ መዝሙሩን የሚመራው ልጅ መዝሙሩን ያጀቡት ሰዎች ዝቅ እንዲሉ በእጁ ምልክት እያሳየ እሱም ከጉልበቱ ሸብረክ ብሎ እጁን እያሽበሸበ ቁጢጥ አለና መዝሙሩን ቀጠለ፡፡ ጭብጨባው እልልታው 'ዝቅ ዝቅ ለጌታ' የሚለው አዝማች ላይ ሲደርስ አካባቢው በጩኸት፣ በጭብጨባ፣ በእልልታ፣ በሩጫት… ተናወጠ፡፡

"….የእንባ ጠብታ

ሞት እንዲታወክ ቅጽር እንዲፈታ

አቤቱ በአንድ ልጅህ አቤቱ በምትወደው

አቤቱ ባንድ ልጅህ አባት ወይ በምትወደው…"

ጭብጨባና እልልታው አካባቢውን ያናጋው ጀመር፡፡ ክብ ክብ ሰርተው ከሚዘምሩትና ትምህርት ከሚሰጥበት የሰልፉ አካላት ውስጥ ይኸኛው ቡድን ብዙ ቁጥር ያለው ሰው ያለበት ነው፡፡ ብዙ ሰው የአዘቦት ልብስ ያደረገ ቢሆንም ይኸኛው ቡድን ግን ነጭ ነጠላ ያደገደጉ ሰዎችም በብዛት ይገኙበታል፡፡ መዝሙሩ እንደቀጠለ ነው

"…ይቅደምልን እግዚአብሔር ይውጣ በሞገስ

እኛ እንንበርከክ እሱ ቅጥር ያፍርስ…"

ሽበሽባው አሁንም እንደ ቀጠለ ሲሆን መዝሙሩን የሚመራው ልጅ ከመሀል ሆኖ አሁን ዐይኑን ጨፍኖ ሁለት እጆቹን ወደ ሰማይ ዘርግቶ መዘመር ጀመረ፡፡ ይህኔ እሱን ከበው የነበሩት ሰዎች ልክ እንደ መሪቸያው ዐይናቸውን ጨፍነው እጆቻቸውን ወደ ሰማይ ዘርግተው መዘመራቸውን ቀጠሉ፡፡

"…ልባችን ከእጆቻችን ጋር ወደ ላይ



CamScanner

ከፍ ወደ ሰማይ ከአዝማቻችን ጋር እንድንተያይ..."

ዘማሪዎቹ በዚህ የመዝሙር አንጓ ላይ ሲደርሱ ወደ ሰማይ የተዘረጉ እጆች ታጥፈው ማጨብጨብ ጀመሩ፡፡ ሲዘምሩ ብቻ የነበሩ እንደበቶች በእልልታ አካባቢውን ይንጡት ጀመር፡፡ ሁሉም በዝማሬው ተገቢነት በቦታው መዘመሩ የተግባቡና የረኩ ይመስላሉ፡፡

-----//-----

## ካሊፎርኒያ-ሎስአንጀለስ

በአሜሪካ መንግሥት በየከተማው ማዘጋጃ ቤቶች አስተዳደር ሥር ከሚተዳደሩ መዝናኛ ፓርኮች ውስጥ በስፋት አሥራ አንደኛ ሲሆን በካሊፎርኒያ ማዘጋጃ ቤት ከሚተዳደሩ ፓርኮች ውስጥ ደግሞ በስፋት ሳንዲያጎ ካለው ከሚሽን ትሬይልስ ፕሪዘርቭ ቀጥሎ ሁለተኛ የሆነው የሎስአንጀለስ ወንዝን ታኮ የሚገኘው መዝናኛ ፓርክ ነው ግሪፍዝ ፓርክ፡፡

ጌታ ግሪፍዝ ለቁንጠኛ እንስቶች ባርኔጣ መሥሪያ የሚሆን ሳባ ለማግኘት ብሎ የሰጎን ማርቢያ የሚሆን መሬት እ.ኤ.አ በ1882 ከጌታ አንቶኒዮ ፍሊዝ ገዛ፡፡ ይሁን እንጂ ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ ለሎስአንጀለስ ከተማ እንካችሁ እናንተ አስተዳድሩት ብሎ ሰጣቸው፡፡ ለዚያም ነው የከተማ አስተዳደሩ ለጌታ ግሪፍዝ ማስታወሻ ብሎ ፓርኩን በስሙ የሰየመለት፡፡

ለዓለምና ዲበኩሉ በግሪፍዝ ፓርክ ውስጥ ናቸው፡፡ ለጥንቃቄ ማንም ሰው እንዳይለያቸው ራሳቸውን ለመቀየር ሞክረዋል፡፡ ዲበኩሉ ከጭንቅላቱ ላይ በጥጥ የተሰራ ኮፍያ አድርጎ፣ በአንገቱ ላይ ግራጫማ የአንገት ልብስ አድርጎ ሰፊ የዐይን መነጽር አድርጓል፡፡

ለዓለምም እንዲሁ የጥጥ ኮፍያ ያደረገ ሲሆን፣ ከጥጥ የተሠራ እንግሊዝ ስራሽ ሱፍ ኮት በነጭ ሸሚዝ ለብሷል፡፡ እንደ ሽማግሌ ከጀርባው ጎበጥ ብሎ፣ ከጭንቅላቷ ላይ ቆልመም ያለች ምርኩዝ ይዟል፡፡ እንዲህ ሽማግሌ አስመስሎ ያሰናዳው ዲበኩሉ ነው፡፡

ለዓለም እና ዲበኩሉ በስልክ ሳይሆን በአካል ተገናኝተዋል፡፡ በአጋጣሚ ሳይሆን ሆን ተብሎ የተሐድሶውን እንቅስቃሴ ለመከታተል ዲበኩሉ አዲስ አበባ ካለው ፊስአልጎስ ሕቡዕ ቡድን ተልዕኮ ተሰጥቶት ከዋሽንግተን ወደ ካሊፎርኒያ መጥቷል፡፡ ለዚህ ነበር ለዓለም ሲደወልለት በቀላሉ የተገኘው፡፡

ለዓለም ግራ ገብቶታል፡፡ በዚህ በግሪፍዝ መናፈሻ ፓርክ ለሆሊውድ ተራራ ቅርብም ስለሆነ ባክ ቱ ዘ ፊውቸር፣ ዋር ጌም፣ ላ ላ ላንድ፣ ሳልዩት ዩር ሾርትስ... የተባሉ

ፊልሞች እንደ ተቀረጸበት ስለሚያውቅ ዛሬም እየሆነ ያለው ነገር ፊልም እየሠራ ያለ እንጂ እውነት እየመሰለው አይደለም። በዚህን ያክል መፈላለግ፤ በዚህን ያክል ጥንካሬና ትጋት በሁለት ሕቡዕ ቡዱኖች መካከል መተጋተግ ይኖራል ብሎ አላሰበም ነበር። በተለይ ኢትዮጵያ ያለው ሕቡዕ ቡድን ዝም ብሎ ተፍጨርጭሮ የሚተው ነበር የመሰለው። ምክንያቱም ከተሐድሶው ጀርባ ሲአይኤና ኤምአይሲክስ እንዳለበት ስለሚያውቅ።።

ለዓለም እንዲህ የተጠናከረና ለቤተ ክርስቲያናቸው ከገንዘብና ጊዜያቸው በላይ ውድ ሕይወታቸውን አደጋ ውስጥ ከትተው የሚጋፈጡ ሰዎች ያሉ አልመሰለውም ነበር። "ቶኒ ሲጨነቅባቸው የነበሩት ሕቡዕ ቡድኖች እዚሁ አጠገቡ ነበር ያሉስት ለካ።" አለ ለዓለም በአግራሞት። ዲበኩሉንም ዝም ብሎ የማኅበረ ቅዱሳን አባል ይሆናል ብሎ ነበር የጠረጠረው እንጂ የሕቡዕ ቡድኑ አባል ይሆናል ብሎ አላሰበም።

ዲበኩሉ እና ለዓለም ፓርኩን እንደሚጎበኝ ጡረተኛ ሽማግሌ ዝግ ብለው እየተራመዱ ወሬያቸውን የሹክሹክታ ያህል ለስለስ አድርገው ያወራሉ "ፓትርያርኩ እንዲገደሉ የታዘዘው ለኛ ነው።"

ዲበኩሉ ፓትርያርኩ ሞቱ የተባሉ ያህል ስቅጥጥ እያለው "ለምን ለኛ?"

"ምክንያቱ የኢትዮጵያው ሲኖዶስ የጳጳሳት ሹመት ስለሚያደርግ። ሹመቱን ላለመረበሽ ነው።"

"ምን አገባቸው? ያኛው ሲኖዶስ ሾመ አልሾመ እንደውም ቢያስተጓጉሉት ነው እንጂ ደስ የሚላቸው"

"አይ የአዲስ አበባውን ሹመት በጣም ይፈልጉታል፤ በዚያም የራሳቸውን ሰው ያስሾማሉ"

ዲበኩሉ በሀዘኔታ ድምጹ ስልል አለበት። በእርግጥ ከተሐድሶው የሆነ አንድ ሰው እንደሚሾም ዲበኩሉ ያውቃል። የጠየቀው ሌላም ምክንያት ቢኖራቸው ብሎ ነበር።

"እሺ ጥሩ አቅደዋል... ለማንኛውም በምን ሊገድሏቸው እንዳሰቡ ነግረውኃል?"

"ዛሬ ጠዋት ቶኒ መጥቶ ፓትርያርኩን ኢንሱሊን ወግቼ እንድገላቸው አዝዞኛል" ለዓለም ሽማግሌነቱን ይረሳና ቀና ብሎ በስሜት ነበር የተናገረው።

ዲበኩሉ መነጽሩን ደፍጠጥ ወዳለው አፍንጫው ገፋ አደረገና ለዓለም ሽማግሌ መሆኑን እንዲያስታውስ ቅንድቡን ሽቅብ ሰቀለበት። ለዓለም ገባውና መልሶ ጎንበስ ብሎ በለሆሳስ መራመድ ጀመረ።



CamScanner

ለዓለም አኳኋኑን ሲያስተካክል ዲበኩሉ መናገር ጀመረ "ሰውየው በጣም አደገኛ ነው። ፓትርያርኩን በኢንሱሊን ሊገድላቸው የፈለገው ሌላ መግደያ አጥቶ ሳይሆን ሆን ብሎ በራሳ ምርመራ ምንም ፍንጭ ላለመተው ነው። ብዙ ጊዜ ከመጠን በላይ ኢንሱሊን በመውሰድ ራሳቸውን ለማጥፋት የሚሞክሩ ሰዎች የጤና ባለሙያዎች ወይም ኢንሱሊን የሚወስዱ የስኳር በሽተኞች ናቸው። ከመጠን በላይ ኢንሱሊን ወስደው የሞቱ ሰዎች ምርመራ ብታደርግላቸው ይህ ነው የምትለው ውጤት ማግኘት ይከብዳል። የሞተ ሰው ግሉኮስ ከሰውነቱ ስለሚጠፋ፣ የደሙን የግሉኮስ መጠን ብትለካው ይህ ነው የምትለው ውጤት አይሰጥህም።"

ለዓለም እንደ ማስታወስ ብሎ "እእ... ቅድም ያልነገርኩህ ነገር፣ ከራስጌያቸው የተጠጣ ወይን አስቀምጥ ብሎኛል፣ ቤቱ ውስጥም ወይን ድፋ ብሎኛል..." አለ። ለዓለም ይህን ሲያስታውስ ሽማግሌ ሆኖ መተወኑን ረስቶ ድጋሚ ቀና አለ።

ዲበኩሉ ለዓለም እንደ ሽማግሌ እንዲሆን በዐይን ጥቅሻ በድጋሚ ነገረውና "እየህ ሐኪሞች ምርመራውን ሰውነታቸው ግሉኮስ አጥተው ሞቱ ብለው ቢደርሱበት በአልኮል ምክንያት እንደቀነሰ እንዲያስቡ ሊያደርጋቸው ነው። በእርግጠኝነት ይህን ካደረገ ለማንኛውም ብሎ ፓትርያርኩ ለወር ከሆስፒታል የሚወስዱትን መጠን አለጊዜው የጎደለ ሊያስመስለው ይችላል።" ዲበኩሉ የግድያ እቅዱን ሲነገረው ብዙም የሚያደርገው እንደሌለ እየተሰማው ነው። ቶኒ በጥንቃቄና በብልሀት ነው የፓትርያርኩን ግድያ ያሰናዳው።



CamScanner

## ምዕራፍ ፵፮

ኢትዮጵያ ውስጥ ያረበበው ድባብ ያስፈራል። በተለይ አዲስ አበባ አለወትሮዋ ዝም ብላለች። በተለይ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ነገር እየተብሰለሰለ እንደሆነ ከፊታቸው ላይ ያስታውቃል። ሁሉም ወንጌላዊ አማኝ በሰላማዊ ሰልፉ ደስተኛ ነው ማለት አይቻልም።

ማኅበረ ቅዱሳን ላይ ሰልፍ ስለተወጣበት ቀላል የማይባለውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን በጣም አስቆጥቷል። ሲኤን ኤን፣ ቢቢሲ፣ አልጀዚራ እንዲሁም ኢቢሲ ሰልፉን ታትረው ሲዘግቡት ነው የዋሉት። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ መንግሥት ምንም ዓይነት የአቋም መግለጫ አላወጣም።

ነገሩ ከረር ያለ መሆኑን የሚያሳየው ማኅበራዊ ድረ ገጾች የሚሰጡት የተለያዩ አስተያየቶች ናቸው። በተለይም ፌስቡክ ላይ ብዙ የኦርቶዶክስ አማኞች የግል ፌስቡካቸውን የማኅበረ ቅዱሳንን ፎቶ ሲያደርጉ፣ ወንጌላውያን አማኞች የፓስተር ናፍያድን ፎቶ ለጥፈዋል።

ብዙዎች የሰላማዊ ሰልፉን ምስል እንዲሁም ቪዲዮዎች በየፌስቡክ ገጻቸው እያጋሩ ነው። በተቃራኒው በተለጠፈው ምስልና ቪዲዮ የተቀየሙ ሰዎች የሚሰጡት አስተያየት ፌስቡክን ወሮበሎች ነግሰው፣ ያለከልካይ ንብረት የሚቀማሙበት ሕግ የለሽ አገር መስሏል።

በማኅበራዊ ድረ ገጽ ምታ ነጋሪት፣ ክተት ሠራዊት ብሎ አዲስ አበባ ላይ ዳግም ሰልፍ እየተጠራበት ነው። የሰልፉ ደጋፊዎች "የማይቀርበት፣ የሞት ሽረት" ማለት ጀምረዋል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትልቁ ሥልጣን ያለው ሲኖዶስም ወትሮ ከሚሰባሰቡበት ከጥቅምቱና ከግንቦቱ መደበኛ ስብሰባ ውጪ አስቸኳይና ድንገተኛ ስብሰባ ጠርቷል። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ሁሉም ጳጳሳት ለእሁዱ የጳጳሳት ሹመት አዲስ አበባ ላይ ተገኝተው ስለነበር ካሉበት እስኪመጡ ድረስ የሚያስጠብቅ አልነበረም።

ለነገ የሚጎሰመው የሰልፍ ጥሪ ፌስቡክ ጥሩ አራጋቢ ሆኗል። ምሽቱ እስኪነጋ ድረስ አላስችል ያላቸው ብዙዎች ናቸው። ሰልፉ አላደርስ ያላቸው ስድብ ማስፈራሪያውን፣ ቁጣና ትችቱን እንደ ደራሽ ውኃ ያፈስሱታል። እንደ ፌስቡክ ከሆነ የነገዋ ኢትዮጵያ ታስፈራለች።

በዚህ የቁጣና የሰልፍ ጥሩንባ ላይ ማኅበረ ቅዱሳን ነበር ቀዝቃዛ ውኃ የቸለሰበት። ለሰዓታት በአርምሞ ነገሮችን ሲከታተል የነበረው ማኅበረ ቅዱሳን የሰልፍ ጥሪውና የእርስ በርስ ክረቱ ስለጋለ ይሁን ወይም ደግሞ ሲኖዶሱ አስቸኳይና ድንገተኛ ስብሰባ ስለጠራ ይሁን ባልታወቀ ምክንያት መግለጫውን አወጣ።



CamScanner

መግለጫውን በሕጋዊው የማኅበረ ቅዱሳን ድረ ገጽ እንደተለቀቀ በፍጥነት በየግለቦች የፌስቡክ ገጽ ላይ መለጠፍ ተጀመረ። ማኅበረ ቅዱሳን በመግለጫው ላይ በዛሬው ሰልፍ ላይ የተመለከተው ነገር እሱን እንደማይመለከትና፣ መሠረተ ቢስ ሥም ማጥፋት እንደሆነ በአንክሮ ገልጿል። በዚህ ጉዳይም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እንደሚነጋገር የገለጸ ቢሆንም ዋናው ነገር ችግሩም ሆነ ውንጀላው የማኅበረ ቅዱሳን ሳይሆን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአጠቃላይ እንደሆነ አመልክቷል።

የዚህ ሰልፍ አቀናባሪዎችና ደጋፊዎች ሁሉም የፕሮቴስታንት አማኞች እንዳልሆኑ ይገልጽና ቢሆንም ግን ነገሩን በቀላሉ እንደማይመለከተው በአንክሮ አስፍሯል። ነገ የተጠራውም ሰልፍ አስፈላጊ ያልሆነና ስሜት ወለድ መሆኑን ገልጾ የሲኖዶሱን ውሳኔ እንደሚጠብቅ በመግለጽ በጥሩ የክርስትና ጨዋነት ከቤተ ክርስቲያን ትእዛዝ እስኪሰጥ ድረስ በጽናት እንዲጠብቁ ለምእመኑ አሳስቧል።

-----//-----

## አዲስ አበባ-ልደታ

አበጋዝ የጠዋት እንቅልፉን አልጠገበም። ቢሆንም ስብሰባ ስላለበት ለመነቃቃት ብሎ ከመኝታ ቤቱ እየተጨናበሰ ወጣና ሳሎን ቴሌቭዥኑን ከፈተና ከቴሌቪዥኑ ፊት ለፊት ባለ ሶፋ ላይ ቁጭ አለ:: ከላይ የለበሰው ውኃ ሰማያዊ ቲሸርት፣ ከስር ደግሞ ነጭ ቁምጣ ነው። ከራሰ በራነት ያዳኑት ጸጉሮቹ ጭንቅላቱ ላይ ተበታትነው ይታያሉ። ዐይኑ ቀልቷል። ጥሩ እንቅልፍ እንዳልተኛ ፊቱ ያሳብቃል።

ጥቁሩን የዲሽ ሪሞት አንስቶ የተለያዩ የውጪ የዜና ምንጮችን መፈተሽ ጀመረ። ጦርነት፣ የአሸባሪዎች የቦንብ ፍንዳታ፣ የአሜሪካ የምርጫ ቅስቀሳ፣ የእግር ኳስ ውጤት ሆነበት። የዲሹን ሪሞት አነሳና ወደ ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አዞረው።

ዘናጩ ዜና አንባቢ በኩራትና በተለመደው ተዝናኖቱ የጠዋቱን ዜና ጨረሰና ከጸረ ሽብር ግብረ ኃይሉ የወጣ የመንግሥት መግለጫ መኖሩን ገለጸና መግለጫው ማንበብ ጀመረ:: አበጋዝ ዓይኑን ፈጠጥ አድርጎ መግለጫውን ለማዳመጥ መቀመጫው ላይ ተመቻቸ::

የመግለጫው መግቢያ እየተነበበ እያለ ትናንት አዲስ አበባ ላይ የተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ በቪዲዮ መታየት ተጀመረ። ቀጠለና አበጋዝ ከተቀመጠበት እንደ ችግኝ ንቅል ብሎ እንዲነሳ ያደረገውን ነገር ጋዜጠኛው ማንበብ ነበር።

"...መንግሥት የብሔር ብሔረሰቦችን መብት ለመጠበቅና ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ እንዲሁም ልማቱ ያለ ምንም እንከን ሳይደናቀፍ እንዲቀጥል የሥርዓቱ አደጋ የሆኑትን ሙስና፣ አክራሪነት፣ ጠባብነትና ትምክህተኝነትን በትጋት እየተዋጋ



CamScanner

ይገኛል። በተለይ አሁን በሃገራችን የተፈጠረውን የሃይማኖት አክራሪነት ለመከላከልና የዜጎችን በሰላም ወጥቶ መግባት ለመጠበቅ ሲል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤት ማደረጃ ሥር የሚገኘውን ማኅበረ ቅዱሳንን ላልተወሰነ ጊዜ ከምንም አይነት መንፈሳዊ እንቅስቃሴና ተግባር ታግዶ እንዲቆይ የእግድ ደብዳቤ ከፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አውጥቷል።…" ዜና አንባቢው በድምጹ ቃና ውስጥ 'እሰይ ይገባቸዋል' የሚል የንግግር አጽንኦት አለው። አበጋዝ በድንጋጤ ክው ብሎ ነበር ዜናውን የሚያዳምጠው።

## ምዕራፍ ፵፯

## አዲስ አበባ-አራት ኪሎ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ስለ ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ አሠራር እና አካሔድ ላይ ለመምከር ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል። አንደኛው የፋሲካ በዓል ከተከበረ በሃያ አምስተኛው ቀን የሚደረግ 'ርክበ ካህናት' የሚባል ሲሆን ሁለተኛው ጥቅምት አሥራ ሁለት ቀን የሚጀመር ነው። ከዚያ ውጪ የምልአተ ጉባኤ ስብሰባ አይካሄድም። ሌሎች ትናንሽ ችግሮች ሲኖሩ በቋሚ ሲኖዶሱ እና በፓትርያርኩ ይፈታሉ። የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ሕልውና የሚጻረር ከበድ ያለ ጉዳይ ከተፈጠረ ግን ቋሚ ሲኖዶሱ አስቸኳይ ስብሰባ የመጥራት መብት አለው። የዛሬውም ስብሰባ በዚህ መሠረት የተጠራ ነው።

የፓትርያርኩ ጽሕፈት ቤት በተቆጡና በተናደዱ ጳጳሳት ተሞልቷል። ፓትርያርኩ የጳጳሳቱን ስሜት ስለተረዱ ወደ ስብሰባው አዳራሽ መግባት ፈሩ። ቢሆንም ስብሰባውን የሚያስጀምሩት እሳቸው ስለሆኑ ሊቀ ጳጳሳቱ በትናንቱ ነገር፣ በዛሬው የመንግሥት እግድ ያዘኑት ስለሚበቃ ዛሬም በማስጠበቅ ዳግም ሊያስቀጧቸው አልፈለጉም።

ፓትርያርኩ ሲገቡ በስብሰባው አዳራሽ ያሉት ሊቀ ጳጳሳት በአክብሮትና በትህትና ተነስተው ተቀበሏቸው። የመሰብሰቢያው ክፍል ጠረንና ለስለስ ያለው አየር ደስ ይላል። ፓትርያርኩ ግን ጭንቅ ብሏቸው፣ የሚያደርጉት ጠፍቷቸዋል። ዛሬ የነገር አለንጋ መቅመሳቸው አይቀሬ ነው። ከዚያም ከፍ ያለ ተግሣጽ ሊደርስባቸው ይችላል።

ሊቀ ጳጳሳቱ ፓትያርኩን ከበው በወንበራቸው የተቀመጡ ሲሆን፣ ከፓትያርኩ ፊት ለፊት ባለ አንድ ወንበር ላይ ግን ሰው ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ተቀምጦበታል። የዚህ ትርጉሙም "ማንኛውም የምልአተ ሲኖዶሱ ውሳኔ የእኛና የቃሉ፣ የእኛና የመንፈስ ቅዱስ" ለማለት ነው። ውሳኔው ሲኖዶስ ውስጥ የተሰበሰቡ ሰዎች ብቻ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስም መኖሩን ለማረጋገጥ ነው ተብሎ በቤተ ክርስቲያኗ ይታመናል።

የስብሰባው ክፍል ጥርቅም ብሎ ተዘጋና የስብሰባው የመክፈቻ ጸሎት ተጀመረ። ፓትርያርኩ 'የመክፈቻ ጸሎቱ ቀኑን ሙሉ ባይቋረጥ ምናለበት?' ብለው እየተመኙ ነው። ብዙዎቹ ጳጳሳት በትረ ሙሴያቸውን ላይ ሁለት እጆቻቸውን ጭነው አንገታቸውን ወደ መሬት ቀብረው ነበር የሚጸልዩት። ሐዘን ውስጥ ገብተዋል።

ጸሎቱ እንዳለቀ የሚነጋገሩበት አጀንዳ ተያዘ። በሌሎች አጀንዳዎች ላይ እንደሚወያዩ አስቀድመው በአጀንዳ ደረጃ ቢይዙም ቀዳሚውና ቀጣ ያጫረው አጀንዳ ግን በማኅበረ



CamScanner

ቅዱሳን ላይ የተወጣው ሰልፍና ሰልፉን ተከትሎ የተደረገው የመንግሥት እግድ ነው። ፓትርያርኩ እንደ መወያያ ብለው ትናንት ሰልፍ ላይ የወጡትን ሰዎች ጥያቄና ፍላጎት፤ የመንግሥትን የጠዋቱን የእግድ ደብዳቤ ለምልአተ ሲኖዶሱ አቀረቡ።

ከፓትርያርኩ ቀጥሎ የመጀመሪያውን የመናገር ረድፍ የያዙት ልጅ እግሩ መልከ መልካሙ የጎጃም አገር ስብከት ሊቀ ጳጳስ ናቸው "እንደው ቅዱስ አባታችን እንዴት አድርገው ነው የሰልፉን ነገር ያዩት? ሰልፍ የተወጣው እኮ በእኛ ላይ ነው። በእኛ ላይ። እኛው ያቋቋምናቸው ልጆች ሲሰደቡና ባልሰሩት ስራ ሲከሰሱ እንዴት አድርገው ቁጭ ብለው ሰሙ? መንግሥት ሲያግዳቸው እንዴት አስችልዎት ዝም አሉ? ዛሬ በዚህ ዝም ካልነው፤ ነገ ደግሞ ሲኖዶሱንም ያግዳል፤ ምን አለበት?" ፓትርያርኩ የፈሩት ነገር አልቀረም። ዛሬ የነገር አርጩሜ እስኪበቃቸው መቀመሳቸው ነው።

ከፓትርያርኩ በእድሜም ሆነ በሹመት ዘመን የሚበልጡት የጋምቤላው አገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ንግግር ቀጠሉ "ቅዱስ አባታችን ምነው አዋረዱን? በዘመናችን ታሪክ መሥራት ቢያቅተን የአባቶቻችንን መንገድ እንዴት እናስደፍር? ምን በደልንዎ ቅዱስነትዎ? ያለምንም ማስረጃ በሰው ግምት ልጆቻችን እናሳጣለን። እንደው የትኛው የቤተ ክርስቲያን ቀኖና ነው እንዚህን ልጆች በጅምላ ለመፈረጅ አቅሙን የሚሰጠን? አንፈልግም ብለን እንጂ እኛም እኮ ከመንግሥት ያልተናነሰ በልጆቻችንና ለልጆቻችን ሥልጣንም መብትም አለን" የጋምቤላው አገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሲናገሩ እምባቸው በዐይናቸው ይፈስ ጀመር። ጥልቅ ሐዘን የገባቸው ይመስላል። ሳጋቸው መናገር ሲያግዳቸው ለጥቂት ጊዜ ሲኖዶሱ በከባድ አርምሞ ተመታ።።

እምባና ሳጋቸውን የጋምቤላው ሊቀ ጳጳስ ገታ አድርገው ንግግራቸውን በድጋሚ ቀጠሉ "አንታበይ ብለን እንጂ የዚህች አገር ካስማና ማገር የሆነው ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እንደዚህ ዘመን ተንቆና ተደፍሮ አያውቅም። ምን አጠፋን ቅዱስ አባቶቼ? እርስዎ ቅዱስ አባታችን? አገር ባቆየን፤ ነጻነት ባስከበርን፤ ፈሪኃ እግዚአብሔር ባስተማርን፤ ወንጌል በጠበቅን፤ ቁጥር አስልተን ዘመን ባስቆጠርን፤ ፊደል ቀርጸን፣ ቀለም በጥብጠን፣ ቆዳ ፍቀን፣ ማንበብ መጻፍ ባስተማርን፤ ባንዲራን እንደ ወረቀት ከመቀደድ፤ እንደ ጨርቅ ከመቃጠል በታደግን፤ ሞተን ባኖርን ለምን እንገፋ? ምንስ አጎደለን? የተዋሐደ ኢትዮጵያ ስላልን ነው ይህ ሁሉ መከራ?" በጋምቤላው ሊቀ ጳጳስ ሁሉም ሰው ስለተነካ ለደቂቃዎች በስብሰባው አዳራሽ ዝምታ ነገሰ።

ዝምታውን ለመስበር ያህል የትግራይ አገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የመናገር ተራውን ወሰዱ "ቅዱስነትዎ በደል እንቁጠር ከተባለ በተለይ በዚህ ዘመን ከእኛ በላይ በደልና መከራ የቆጠረ አለ? በዮንብ ስላልሆነ ነው እንጂ ስንት ቤተ ክርስቲያን ነው የተቃጠለብን? ስንት ምእመናንና ቀሳውስት በገዛ ቤተ መቅደሳችን የታረዱብን? ስንት

ልጆቻችንን ነው በገዛ ቤታችን ሌሎች እየገቡ በራሳችን አውደ ምሕረት ሌላ ትምህርት እየሰበኩ እንደ ደራሽ ውኃ ያስኮበለሉብን? ሰልፍ መውጣት ያለብንስ እኛ ነን ቅዱስነትዎ። እኛ ነን! የታመምን፣ የተገፋነው፣ የታረድነው፣ ልጆቻችን እንደሚታረድ በግ የተጉተቱብን እኛ! እኛ ነን ቅዱስነትዎ!

ቤተ ክርስቲያናችንን ለአንድ ብሔር ተጠቅልላ እየተሰጠች ስትሰደብ፣ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊነትን ከሌሎች ጋር ሆነን በነጻነትና በክብር ሳቆየን ለእኛ የተሰጠን ስም 'ኢትዮጵያ የዓለም ጭራ ለመሆኗ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ነች' የሚል ስድብ።

"ማንኛውም መሪ እንደ ግል ጠባቂ ጨቋኝ የሆነ እንደሆነ የእሱ መጨቆን ለቤተ ክርስቲያን እየተሰጠ የጨቋኝ መፍለቂያ እየተባልን ስድብ እንደ ውኃ የጠጣን እኛ ምን እንበል? እኛ የት ሰልፍ እንውጣ ቅዱስነትዎ? አገር ባቆየን፣ ባንዲራ ባስከበርን የተሰደብን እኛ! እኛ! ምን እንበል ቅዱስነትዎ?" ረዥምና ነጭ ጺማቸውን እያፍተለተሉ በለሆሳስ ቢናገሩም ቁጣቸው ፊታቸው ላይ ያስታውቃል።

የሰሜን ጎንደር አገር ስብከት ሊቀ ጳጳስ ቀጣዩን ንግግር ጀመሩ "እኛ ልጆቹ ሁሉ ቅዱስ ናቸው አላልንም አንልምም። እንኳን እዚህ በእኛ ጥላ ስር ከተሰበሰቡ ልጆች አይደለም፣ በሰማያዊው ኢየሱስ ክርስቶስ እግር ሥር ቁጭ ብለው ተምረው፣ ታምራቱን አይተው፣ እንጀራ ተባርኮ በልተው፣ ውኃ ላይ ተራምደው፣ ሙት ሲነሳ አይተው፣ እውር ሲበራ፣ ሽባ ሲተረተር ተመልክተው፣ የካዱት፣ በጥቂት ብር የሸጡት አሉ። እኛ የምንለው እንደው በምን ተአምር ነው ማኅበረ ቅዱሳን ሁሉ አሸባሪ የሚሆነው? ቢያጠፉ ቢያጠፉ የሰው ሕይወት የሚቀጥፉት? ቢቀጥፉስ እንዴት ተደርጎ ነው ሁሉም ባንድነት እንደ ገዳሉ ሁሉ የሚወገዙት? በአንድነት ተሰብስበው ቦንብ እንዳፈነዱ የሚቆጠሩትስ? ይህንን የሚያስብልስ ማስረጃ አለ ቅዱስነትዎ?"

ሁሉም ሊቀ ጳጳሳት የተነጋገሩበት በሚመስል ደረጃ አንድ ሃሳብ ወርወር እያደረጉ ዝም ይላሉ። አሁን ደግሞ የሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ቀጣይ ተናጋሪ ሆነዋል። በእድሜም አረጋዊ ስለሆኑ ንግግራቸው ለሰስ ያለና እንደ ጥሩ ውኃ ኮለል እያለ የሚወርድ ነው።

"ቅዱስ አባታችን ሌሎችን በማናገርዎ ቅር አይለንም። ቢቻለንስ ከሁሉ ጋር በሰላምና በፍቅር አብሮ መኖሩ የወንጌልም አላማ፣ የአባትነት ወጉ ነው። ቢሆንም የምናስማራቸው፣ ቀድመን የምንሞትላቸው፣ የምንጠብቃቸው ነፍሶች በተለየ ሁኔታ ተሰጥተውናል።

"ቅሬታችን በመገናኛ ብዙኃን የሰጡት መግለጫ ማኅበሩን በትክክል ነገሩን እንደ ፈጸመ የሚያምንና 'አውግዤ እለየዋለሁ' ያሉት ቃል ነው። ለዚህ ቃልዎ እርሶ

ውግዘት ሊደርስብዎ ይገባ ነበር፤ ችግሩ ቤተ ክርስቲያን ትታወካለች እንጂ፡፡ ቃላችንን እየሰሙ አይደለም፡፡ የቤተ ክርስቲያን ራስ ኢየሱስ ነው፡፡ ከዚያም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ይህ ቅዱስ ሲኖዶስ ነው ያለው፡፡ እንዴት ነው ብቻዎትን እንደዚያ ዓይነት ቃል የሚሰጡት? ልጆቻችንን እየመከርን፤ እየገሠጽን ልናሳድግ እንጂ እያወገዝን ልናሸማቅቅ መቼ ተሾምን ቅዱስነትዎ? ለዚህ ብለን አይደል ስንት አጥፊዎችን የታገስነው? መንግሥትም የእርስዎን ቃል ሰምቶ ልጆቹን አሸባሪ ብሎ ቢፈረጅ ምን ይገርማል? ሰድበው ለሰዳቢ የሰጡን እርስዎ ነዎት! ልጆቹ ለሩብ ምዕት ዓመት የለፉበትን ዓላማ ማጨናገፍ እንዴት ያማል ቅዱስነትዎ? ባይገባዎት እንጂ ልክ እንደ ቀደሙ ደገኛ አባቶቻቸው ዓላማቸው የቤተ ክርስቲያናቸውንም የአገርንም ልእልናና ከፍታ አስጠብቆ ለነገው ትውልድ ማስረከብ ነበር፡፡"

ፓትርያርኩ እየደረሰባቸው ያለው የቃላት ውርጅብኝ የጠበቁት ነው፡፡ ነገር ግን የጳጳሳቱ እንደ ፍም የሚፋጅ ንግግርና የፊት መጥቆር መቋቋሙን ነው ያልቻሉት፡፡ ከወንበራቸው ላይ ሆነው ሲቁነጠነጡ ተንገዳግደው ሊወድቁ ይመስላል፡፡ ቀንጆ ፊታቸው ላይ ደስ የሚል ሞገስ የሚጨምርላቸው ከስር ለስላስና ነጭ ጺም ያለበትን ስልካካ አፍንጫቸውን ዳበስ ዳበስ አደረጉት፡፡ አልቦታል፡፡ የአፍንጫቸውን ላብ እንደ መጥረግ አደረጉና ደረታቸው ላይ የተንጠለጠሉትን አይከናኞች ማስተካከል ጀመሩ፡፡

ፓትርያርኩ አይከናኞቻቸውን ሲያስተካክሉ የሐዋሳ አገር ስብከት ሊቀ ጳጳስ ንግግራቸውን ጀመሩ "ቅዱስ አባታችን 'ቀኝ ግዛት' የሚሉትን ቃልስ ከየት አመጡት? ቀኝ የገዛን ማን ሆኖ ነውና? ቀኝ የተገዛውስ ማነውና? የአብዩን ለእምዩ ሆነ እኮ! እኛ ቀኝ ገዢያችንም እርስዎ ነዎት!" ፓትርያርኩ ደንገጥ ብለው ካቀረቀሩበት ቀና ብለው ተመለከቱ፡፡

የሐዋሳው ሊቀ ጳጳስ ምንም ሳይፈሩ ንግግራቸውን ቀጠሉ "እርስዎ ለማን እየሠሩ ነው? አስተዳድሩ ተብለው የተሾሙበትን ምእመንና ልጆች አሳልፈው ከሰጡ፤ ሰድበው ለሰዳቢ ከዳረጉ፤ አፍረው ካሳፈሩን ቅኝ ግዛት ይሄ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን ላይ እርሶን ሾሙ ቀኝ እየገዛን ያለ ሌላ አካል አለ ማለት ነው፡፡ ከቤተ ክርስቲያናችን ላይ የተጣባውን ሸፍጥና ተንኮል፤ ዘረኝነትና ሙስና፤ መንግስን ካልጣልን ግድ የለዎትም ቀኝ የሚገዙን የገዛ ልጆቻችን ሳይሆኑ የክፋት፣ የሌብነት፣ የዘረኝነት... አስተሳሰቦች ናቸው፡፡" ሊቀ ጳጳሳቱ ጠንከር ባለው የሐዋሳው ሊቀ ጳጳስ ንግግር ደንግጠው ፍጥጥ ብለው ይመለከቷቸው ጀመር፡፡



CamScanner

## ምዕራፍ ፺፰

### ዱባይ

የአውስትራሊያዊው ሐማድ ሐቢብ ንብረት የሆነው፣ እ.ኤ.አ የ2007 የሰሜን አፍሪካና ሩቅ ምሥራቅ ምርጥ የቱሪዝም መዳረሻ ሆቴል ተብሎ ሽልማት ያገኘው፡፡ ዓለም በጥራትና ረጋ ያለ የተዝናኖት ጊዜ ለማሳለፍ ሊሉ ከተባሉት አሥራ አምስት ሆቴሎች አንዱ የሆነው በሼይክ ዛይድ ጎዳና ላይ በዱባይ እንብርት የሚገኝ ባለ አምስት ኮከቡ ኬምፒንስኪ ሆቴል ውስጥ የደቂቀ እስጢፋኖስ አባላት ለወሳኝ ስብሰባ ተቀምጠዋል፡፡

ኬምፒንስኪ ሆቴል ካሉት ዘጠኝ የመሰብሰቢያ አዳራሾች ውስጥ መጠነኛ ሰው ይይዛል በሚባለው ክፍል ውስጥ ነው ስብሰባው የሚካሔደው፡፡ የእንግሊዝ አምባሳደር በዱባይ የስብሰባውንና የተሰብሳቢውን ሙሉ ወጪውን ሲሸፍኑ ለሆቴሉ አስተዳዳሪ ኢትዮጵያውያን መንፈሳዊ ሰዎችን አንድም ሳያጉድል በአግባቡ እንዲያስተናግድ አበክረው ነግረውታል፡፡

የፓስተር ናፍያድ መሞትን ተከትሎ በመካነ ኢየሱስና በሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ላይ የደረሰው የቦንብ ፍንዳታ አዲስ አበባ ላይ ብቻ ሳይሆን በመላ ኢትዮጵያ ላይ ባሉ የኦርቶዶክስ እና የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ዘንድ ከፍተኛ ውጥረት ነግሷል፡፡ ውጥረቱን ተከትሎ ማኅበረ ቅዱሳን ላይ መንግሥት እግድ መጣሉ ደቂቀ እስጢፋኖስን ጮቤ አስረግጦታል፡፡ አሁን ያለ ተቀናቃኝ ተሐድሶው እንደሚያከናውን አውቋል፡፡ ሌላ ሕቡዕ ቡድን እንዳለ ቢያውቅም እሱ ግን ብዙም አያሰጋውም፡፡ ሕቡው ቡድን በገሀድ ሊጋፈጣቸው አይችልም፡፡ ስለዚህ ከማኅበረ ቅዱሳን በላይ የሚከብዳቸው ጠላት አይኖርም፡፡

የዛሬው ስብሰባ ትልቁ አጀንዳ ተሐድሶው የሚታወጅበት ሰዓት ስለ ደረሰ የመጨረሻውን ውሳኔ ለማሳለፍ ነው፡፡ አሥሩም የደቂቀ እስጢፋኖስ አመራሮች ድል ድል እየሸተታቸው ነው፡፡ የተቋመጠለት ተሐድሶ እውን ሲሆን የጥቂት ቀናት ትዕግስትና በዛ ያለ ብልሀት ብቻ ነው የሚጠበቀው፡፡ ከፓስተር ጋቢሶና ከሐዋርያው ሰለሞን በስተቀር የተቀሩት የደቂቀ እስጢፋኖስ አባላት ከአዲስ አበባ አንድ ላይ የመጡ ሲሆን "ለመንፈሳዊ አገልግሎት" በሚል ሽፋን ነው ዱባይ የተገኙት፡፡

ዱባይ በተለይ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚንቀሳቀሱ የተሐድሶ አባላት ጥሩ መናገሻ ከተማ ሆኖላቸዋል፡፡ ዱባይ የነበረውን ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንን ከኢትዮጵያው ሲኖዶስ ገንጥለው ሙሉ ለሙሉ የወረሱ ሲሆን፣ ሌላም ተጨማሪ "የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በዱባይ" የሚል ከፍተዋል፡፡ በተጨማሪም ጽዋ ማኅበር ለመጠጣት በሚል ሥም በየቤቱ እየተሰበሰቡ፣ ዱባይ ያሉ ኢትዮጵያውያንን ስለ ተሐድሶው ግንዛቤ



CamScanner

ይሰጣሉ፡፡ እንዳንዶቹንም "ያመነ የተጠመቀ ነው የሚድነው እንጂ ሳያምኑ ጥምቀት ቀልድ ነው" ብለው ዳግም አጥምቀዋቸዋል፡፡

ሔራሞ ለውጥ ይፈልጋሉ ባላቸው ሀሳቦች ላይ ሰላሳ አንድ አቋሞች ካነበበ በኂላ ቀና ብሎ ተመለከታቸው፡፡ ብዙዎች ፊት ላይ መስማማት ሲታይ ግሩም ግን ደስተኛ አይመስልም፡፡ "የቀረና ይጨመርበት የምትሉት ሐሳብ ካለ እንወያይበትና በቶሎ ለተሐድሶው ዝግጅት እንድናደርግ፡፡ አሜሪካ ያለው ክንፍ ለውጥ ያደረጉባቸውን የቅዳሴ፣ የሥርዓት እና የአምልኮ መንገድም ይህን ይመስላል፡፡" አለ ሔራሞ ካለወትሮው ስሜታዊነቱን ገርቶ ረጋ በማለት፡፡

ግሩም በሔራሞ ንግግር ተቆጣ "ሔራሞ እዚህ ላይ ተቃውሞ አለኝ፡፡ የአሜሪካው ሲኖዶስ ግልባጭ ልንሆን አይገባንም ባይ ነኝ፡፡ እኛ ነን ትልቁን መከራ፣ መገፋት፣ ስቃይና ሕመም የተጋፈጥነው፡፡ ስለዚህ ለውጡን ማድረግ ያለብን እኛ ራሳችን እንጂ መሪያችን አሜሪካ ያለ የመኪና ካማማ አንሆንም፡፡ ለምሳሌ መጠጥ የሚፈቀደው ለምንድነው? ስለ ትዳርስ አንድም ቦታ ላይ ያልተጠቀሰው ለምንድነው? እኛ የትኛውን ትዳር ነው የምንባርከው? ቅዳሴው ላይ ብቻ ምእመኑን ከካህኑ ጋር እኩል ያደርጋል እንጂ አገልጋይነትና የክህነት አካሄዱን ምንም አላሳም፡፡ ነው ወይስ በቀድሞው አካሄድ እንድንሄድ ፈልገዋል?" የግሩም ቀይ ፊት በንዴት የበሰለ ቲማቲም መሰለ፡፡

ሔራሞ ደነገጠ፡፡ ግሩም እንዲህ ይናደዳል ብሎ አላሰበም ነበር፡፡ ሌላም ሳይናገር የቀረው ነገር አለ፡፡ ተሐድሶው ከታወጀ በኂላ እንግሊዝ አገር ኦክስፎርድ ዩንቨርስቲ በተሐድሶው ዙሪያ ማኅበረሰቡን ግንዛቤ ለመስጠትና ደጋፊዎችን ለማብዛት "ተሐድሶ ለማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሐብታዊና ፖለቲካዊ ሕይወት ያለው መልካም ተጽእኖ" በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጽሑፍ እንደሚያቀርብ መርሐዊ በስልክ ነግሮታል፡፡

ከኢትዮጵያም "ተዋሕዶ ለማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሐብታዊና ፖለቲካዊ ሕይወት ያለው መልካም ተጽእኖ" በሚል ርዕስ ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰው እንደሚጋበዝ ተነግሮታል፡፡ እስከ አሁን ግን ለሌሎች አልተነገራቸውም፡፡ ዘግይቶ እንዲነገራቸው ይደረጋል፡፡ ሔራሞ ይህን ምስጢር ለግሩም ሊነግረው ነበር፡፡ ግሩም እኔም ማቅረብ አለብኝ የሚል ስለመሰለው መናገር አልፈለገም፡፡ በዚያ ላይ የመርሐዊን የተሐድሶ ሐሳቦች ወዷቸዋል፡፡ ቢሆንም አሁን በመርሐዊ ሐሳብ ተስማምቻለሁ ማለት ጸብ ሊፈጠር ስለሚችል ዝምታን መረጠ፡፡ መርሐዊ እና ግሩም ልክ እንደ ካልቪን እና ማርቲን ሉተር እየመሰሉት ነው፡፡ የዛሬው ውይይት ትንሽ ጠንከር ያለ ይመስላል፡፡ ትርሲት የኦርቶዶክስ ሥርዓት እና ወግ የሚባለው ነገር እንደ ቀንበር ነው የከበዳት፡፡ ሰውን መሳቀቅ፣ አለባበሷን ኦርቶዶክሳዊ ማስመሰል፣ ንግግሯን መግራት፣ በጣም መንፈሳዊ መምሰል ሰልችቷታል፣ በዝማሬ ብቻ ሳይሆን በማስተማርም መምጣት ፈልጋለች፡፡



CamScanner

"አሁንስ ስለ አንድ አማላጃችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጽሐፍ ቅዱስ ቁልጭ አድርጎ እያተናገረ ዝም የምንልበት፤ መዳን በጸጋ ብቻ መሆኑን በመዝሙራችን ውስጥ ጭንቅ ጥብብ እያልን የምንዘምርበት፤ ከወትሮው ለውጥ ቢኖርም ስለ ኢየሱስ መዘመራችን ሙሉ ለሙሉ ነጻ ፈቃድ አላገኘንም። በየመዝሙራችን መሐል ስለ ማርያም እና ስለ መላእክት ጣል ማድረግ ግድ እየሆነብን ነው። ስለዚህ ከዚህ እስራት ነጻ መውጣት አለብን። ይብቃን የተከፈለው ዋጋ ይበቃል።" ትርሲት ትንሽ ስሜታዊ ሆናለች። ስትናገር ቆጣ ቆጣ ትላለች።

"የቀረን ጥቂት ቀን ቢሆንም ለተሐድሶው ያዘጋጀነውን ዝማሬ በቶሎ ወደ አደባባይ ልንለቀው ግድ ነው። መዝሙሩ ትልቅ ግርግር ማስነሳቱ አይቀሬ ነው። ስለዚህ ግርግሩ ራሱ ሌላ ጥቅም አለው። ምክንያቱም አሁን ጠላቶቻችን የስንግ በየአቅጣጫው ተይዘዋል። ስለዚህ መዝሙሩን ሲመረምሩና መልስ ሲሰጡ አይኖሩም። ቋሳቱም ለማውገዝ ብዙ ቀናት ይወስዳሉ። ከእሱ በፊት እኛ እንለያቸዋለን። አዲሱ የቴሌቪዥን ጣቢያችንም በቅርቡ ሥራ ስለሚጀምር ከሌሎች የወንጌላውያን ጣቢያዎች ጋር ሆነን በዝማሬ የጠላትን ቅጥር እናፈርሳለን።"

ግሩም ስልክክ ያለችውን አፍንጫውን እሽት እሽት አደረገና በረዥሙ ተነፈሰ። ትርሲት ንግግሯን መጨረሷን ሲያውቅ፤ የመናገር ተራውን ወሰደ "ትርሲት ልክ ነች። አንዳንድ ነገሮች ከታሰበው ቀን በታች ቀረብ ብሏል። በጥናት ላይ ያለውን መዝሙር በፍጥነት ለማጠናቀቅ ሞክሩ። አባ አወቀ ጽጽስናውን ከተሾሙ በኋላ ተሐድሶውን ለማወጅ ብዙም አንቆይም።

"መዝሙሩ በትክክል አምስቱ ሶላዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። መዳን በእምነት ብቻ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ፣ መዳን በጸጋ ብቻ፤ ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ እና መዳን በጌታ ኢየሱስ ብቻ መሆኑን የሚያወጁ መዝሙሮችን አሁን በዘወርዋራ ሳይሆን በቀጥታ መዘመር እንዳለብን እምናለሁ።

"እውነት ነው ከመዝሙሩ በኋላ ውግዘት ሊደርስ ይችላል። ስለዚህ የእኛ አባል የሆኑ ሰዎቻችን ቁጥር በተቻለን መጠን ለማወቅ ጥረት አድርገናል። ቀላል የማይባል ተከታይ ነው ያለን። በዚያ ላይ ነገሮች ሲለይላቸው ቆርጠውና እምነው የሚመጡት ቀላል አይሆኑም። እንደ ቀድሞው ሽማግሌዎቹ እኛን ብቻ ሳይሆን ምእመንንም ማውገዝ ይጠበቅባቸዋል። ይህን ያደርጉት እንደሆነ ደግሞ እናያቸዋለን እስኪ። ስለዚህ ተሐድሶው ስኬታማ እንደሚሆን ባለሙሉ ተስፋ ነኝ። በዚያ ላይ የሳተላይት ቴሌቪዥን ጣብያችን የሙከራ ስርጭቱን ጀምሯል። ለተሐድሶው እወጃና ለዝማሬው በደንብ እንጠቀምበታለን።"

የፓስተር ናፍያድ ልጅ ማዕረግ ምንም መናገር አልቻለም። ከዚያ ይልቅ ደስታውና ፈንጠዝያውን ፍንድቅ አድርጎት ሊወጣ ነው። በጣም እምርሮ የሚጠላው ማኅበረ



CamScanner

ቅዱሳን በመታገዱ በጣም እርካታን ተጎናፅፏል። ማፅረግ በስብሰባው ላይ መታደሙ ቢያስደስተውም ከመናገር ይልቅ ማድመጡና ስለ ድሉ ማሰቡ ምቾት ሰጥቶታል።

ቀጣይ ንግግሩን የወሰደው ሔራሞ ነው "እዚህ ጋር አጽንኦት መስጠት የምፈልገው ስሜትና ጉልበት እንዳናበዛ ነው። እስከዛሬ የተንዛዝንበት ጥበብና ትዕግስት እስከ መጨረሻው ድረስ ልናንድል አይገባም። ሌላው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምልጃና ለጻድቃን፣ ለማርያምና ለመላእክት ስግደት ይገባል አይገባም የሚሉ ነገሮች ትንሽ በቤተክርስቲያኗ ዘንድ ሴንሴቲቭ ጉዳይ ነው። ስለዚህ ይህን ሴንሴቲቭ ነገር እያነሳን ልናሸብራቸው ይገባል።"

ግሩም የተነሳው ሀሳብ በጣም ነው ያነቃቃው "ሔር በጣም መልካም ሐሳብ ነው ያነሳኸው። የቤተ ክርስቲያኗ ሊቃውንት ሳይቀሩ በኢየሱስ ክርስቶስ ምልጃ ላይ የተግባቡ አይመስለኝም። በተለይ በዚህ ጉዳይ አንጀቴን የሚያርሱኝ ቀደስ አለማየሁ ሞገስ ናቸው። ጌታ ይባርካቸውና! 'ሁሉም ሁሉን ይወቅ' እና 'ቢጸ ሐሳውያን' በሚለው መጽሐፋቸው ስለ ክርስቶስ ምልጃ ብትንትን አድርገው ነው ያስረዱት።

"ሌላው ስግደት ነው። ቤተ ክርስቲያኗ የአምልኮ ስግደት ሌላ፣ የአክብሮት ስግደት ሌላ እያለች ለማጭበርበር ብትሞክርም አባ እስጢፋኖስን ያስወገረ፤ እኛን ዛሬ እዚህ ያደረሰ ነገር ስለሆነ ዳግም ልናስነሳውና የአባ እስጢፋኖስን ደም በከንቱ ልናስቀር አይገባም። ስለዚህ ሔራሞ እኔ እና አንተ በዚህ ጉዳይ ስብከት እንሠራለን።" አለ ግሩም ፊቱ በደስታ በርቶ።

በመቀጠል ሐዋርያው ሰለሞን ነበር ንግግሩን የጀመረው። በለንደኑ ስብሰባ ላይ የነበረ የፕሮቴስታንት ሐዋርያ ሲሆን ለኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መታደስ በቁርጠኝነት ነው የሚሠራው "አሁን ማሰብ ያለብን መናገሻችን የት ነው የሚሆነው የሚለውን መመለስ ይኖርብናል። የተሐድሶው መቀመጫ የት ከተማ ሊሆን ይገባል? የሚለውን ብንወያይ ደስ ይለኛል።"

"እንደኔ እንደኔ ጥሩ ይዞታ ያለን ሻሸመኔና ሐዋሳ ላይ ነው። ስለዚህ እንደ ከተማና ስልጠን ያለ ቦታ ከታሰበ ግን ይበልጥ ሐዋሳ ተመራጭና አዲስ አበባን መቀናቀን የሚችል ከተማ ነው። አንደኛ በዛ ያለ ቁጥር ያለው የወንጌላውያን አማኞች ስለሚገኙበት፣ ሁለተኛ ሻሸመኔ የተቆጣጠርናቸው አብያተ ክርስቲያናት ስላሉ ከእነሱም ድጋፍ በቀላሉ ስለምናገኝ መናገሻ ከተማችን ሐዋሳ እናድርገው።" አለ ሐዋርያው ሰለሞን።

ትርሲት ውስጧን ፍርሐት ፍርሐት እያላት ነው። ተሐድሶው ሲታወጅ አገር የሚበጠበጥ ስለመሰላት ከአገር እወጣለሁ ብላ እያሰበች ነው። ስለዚህም ተሐድሶው በሚታወጅበት ጊዜ የት መሆን እንዳለባቸው መወሰኑ ጥሩ ነው። ከአገር መውጣት ባትችል እንኳ ሻሸመኔ ካልሆነም ሐዋሳ ልትደበቅ አቅዳለች።



CamScanner

## ምዕራፍ ፶፬

## አምስት ኪሎ-ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን

አበጋዝ እየነዳ ሮዳስ ከጎኑ ሆኖ እያወራ በዓለ ሲመቱን ለመካፈል ከፒያሳ ወደ አራት ኪሎ በሚወስደው መንገድ አሽከርክረው ወደ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ወደሚወስደው መንገድ ሲገቡ ሲሉ መኪናቸውን እንዲያቆሙ በጸጥታ ኃይሎች ተነገራቸው፡፡ አበጋዝ የመኪናውን መስታወት አውርዶ 'ምነው?' ከማለቱ በፊት፤ ቀውላላውና ቀጫጫው የፌደራል ፖሊስ በእጁ ወታደራዊ ሰላምታ ሰጣቸውና "አለቃ ዛሬ መኪና ይዞ መግባት ስለማይቻል መኪናችሁን አንድ ቦታ አስቀምጡና በእግራችሁ መግባት ትችላላችሁ" አለ፡፡

ሮዳስ እና አበጋዝ መኪናቸውን አዙረው ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ፊት ለፊት አቁመው ወደ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በእግራቸው ማምራት ጀመሩ፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን ከቤተክርስቲያን ጉዳይ ስለታገደ በሹመት ላይ አንዳች አደጋ ወይም ሕዝባዊ ተቃውሞ ይነሳል ተብሎ ስለታሰበ ብርቱ ጥንቃቄ እየተደረገ ነው፡፡ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያ ከመግባቱ በፊት አራት ጊዜ ተፈትሾ ነው፡፡ ሮዳስ እና አበጋዝ ይህን ፍተሻ ማለፍ ግድ ነበረባቸው፡፡ አካባቢው በአዲስ አበባ እና በፌደራል ፖሊስ ተወርሯል፡፡ ቤተ ክርስቲያኗ ውስጥም ጠባቂዎች ይታያሉ፡፡ ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ ውጪ ደግሞ በትላልቅ መኪናዎች የተጫኑ ሙሉ ትጥቅ የታጠቁና የደንብ ልብስ የለበሱ የፌደራል ፖሊሶች ይታያሉ፡፡

አበጋዝ ነገሩ ግራ ስለገባው ወደ ሮዳስ ጆሮ ጠጋ ብሎ "ይሄ ሹመት የኤጲስ ቆጶሳት ወይስ የጠቅላይ ሚኒስትር?" አለ፡፡

ሮዳስም ነገሩ በጣም አደናግሮት ስለነበር "ሃ…ሃሃ…" ብሎ ሳቅ አለና "…አስመሰሉት አይደል? በጣም ነው የሚጨንቀት፤ እስከመቼ እንዲህ ተሸብረውና ተጨንቀው ይችሉታል?"

"መቼም የግፉ ጽዋ እስኪሞላ አልልህም፡፡ ጽዋው ሞልቷል፤ ባይሆን ሞልቶ የፈሰሰው ግፍ ይሄን መንግሥት እስኪያንሳፍፈው ይመስለኛል" አለ አበጋዝ በቁጭት ጥርሱን እየነከሰ፡፡

"እውነት ብለሃል፤ የፈሰሰው እስኪያንሳፍፍ ነው፡፡ ያኔ የሚሆነውን የሚያውቀው እሱ ብቻ ነው" አለ ሮዳስ አንገቱን ወደ ሰማይ አቅንቶ፡፡ ሮዳስ እና አበጋዝ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ሰዉ ግጥም ብሎ ሞልቶ መቆሚያ መቀመጫ ሊገኝ አልቻለም፡፡ እንደምንም እየተሹለከለኩ ሔዱና ትዕይንተ ሲመቱ በሚታይበት ቦታ ቆሙ፡፡

አውደ ምሕረቱ ላይ ተሿሚ ኤጲስ ቆጶሳትና ሿሚው ፓትርያርክና ሊቀ ጳጳሳት የተቀመጡ ሲሆን ከዚያም በመቀጠል ሌሎች ሊቀ ጳጳሳት አሉ፡፡ ከጳጳሳቱ ፊት ለፊት ባለ የክብር ወንበር ላይ የመንግሥት ባለስልጣናት እንዲሁም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ካርዲናል ይታያሉ፡፡ ከእሳቸው ጎን የሙሉ ወንጌል፣ የመካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ተወካዮች እንዲሁም የጠለያዩ ሐገራት ዲፕሎማቶች ይታያሉ፡፡

-----//-----

## አዲስ አበባ-ቦሌ

ዳንኤልና ዘላለም ቴሌቭዥኑ ፊት ለፊት ቁጭ ብለዋል፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቴሌቪዥን ጣቢያ በቀጥታ የሚተላለፈው የኤጲስ ቆጶሳት ሹመትን እየተከታተሉ ነው፡፡ ዘላለም የስደተኛውን ሲኖዶስ በዓለ ሲመት ተከታትሏል፡፡ ስለዚህ ለዘላለም አዲስ አይደለም፡፡ ከዚያም በላይ የነገር መለኮት ምሩቅ ስለሆነ ስለሹመቱና ስለ ሥነ ሥርአቱ በቂ እውቀት አለው፡፡ ፓትርያርኩና ሌሎች ሊቀ ጳጳሳት ባሉበት ሆነው የዛሬውን ቅዳሴ በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ከተፈጸመ በኋላ የኤጲስ ቆጶሳት ሹመት ቤተ ክርስቲያኗ በምትተዳደርበት መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያኗ ሥርአትና ሕግ በፍትሐ ነገሥቱ መሠረት ተደርጎ ይከናወናል፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሦስት ዓይነት ሥልጣነ ክህነት አለ፡፡ እሱም ድቁና፣ ቅስናና ኤጲስ ቆጶስነት ነው፡፡ በነዚህ ሥልጣነ ክህነት ውስጥ የተለያዩ ደረጃዎች አሉ፡፡ ዛሬ የሚፈጸመው ሥልጣነ ክህነት የኤጲስ ቆጶስነት ነው፡፡ "ዳኒ በነገራችን ላይ የኤጲስ ቆጶስነት ሹመት የሚከናወነው እሑድ ቀን ብቻ ነው፡፡" አለ ዘላለም፡፡

ዳኒ ግርም ብሎት "ምን ችግር አለው በአዘቦት ቀን ቢሆን?" አለ፡፡

"ቤተ ክርስቲያኗ ከሰኞ እስከ አርብ የሥራ ቀን አድርጋ ወስና ቅዳሜና እሑድን ሰንበት ብላ ብታከብርም፣ ቅዳሜ የመጀመሪያው ሰንበት ስለሆነ ብዙ ሰዎች ሰው በማስታረቅ፣ ሕሙማንና የታሠሩትን በመጠየቅ ዕለቱን ይጠቀሙታል ተብሎ ይታሰባል፡፡ እሁድን ለማስቀደስ፣ ቃለ እግዚአብሔርን ለመስማት፣ ለመቁረብ... ቤተ ክርስቲያን ስለሚመጡ በሕዝቡ መኃል ለመሾም ነው፡፡

"በእርግጥ በቤተ ክርስቲያኗ እሑድ የተመረጠበት ምክንያት ይህም ብቻ ሳይሆን ሌላም ምክንያት አለ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የተጸነሰበት፣ እንዲሁም ከሞት የተነሳበት፣ መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ የወረደበት፣ በደብረ ታቦር ተራራ መለኮቱን የገለጠበት ቀን ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡"

በቴሌቭዥኑ ውስጥ በዓለ ሲመቱን ለመከታተል የመጣው ሕዝብ መታየት ጀመረ፡፡ ሁሉም በሚባል ደረጃ በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ያሉ ሰዎች ነጭ ልብስ ለብሰው



CamScanner

የኤጲስ ቆጶሳቱን ሹመት ለመከታተል በትጋትና በጉጉት እየተጠባበቁ ነው፡፡ ብዙዎቹ በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ውስጥ ያሉት ወጣቶችና በእድሜያቸው ኤጲስ ቆጶሳት ሲሾሙ አይተው ስለማያውቁ በዓለ ሲመቱን ለማየት መጓጓታቸው ፊታቸው ላይ ያሳብቃል፡፡ ጋሚሶቹ የእጅ ስልኮቻቸውን አውጥተው የሹመቱን ሥነ ሥርአት እየቀረጹ ነው፡፡ የተለያዩ መገናኛ ብዙኃንም በካሜራቸው ትዕይንቱን እያስቀሩ ነው፡፡ አዲሱ የደቂቀ እስጢፋኖስ ቴሌቪዥን ጣቢያም ማንነቱን ሳያሳውቅ በዓለ ሲመቱን በምስል እያስቀረ ነው፡፡

ቴሌቭዥኑ ምስሉን ከትዕይንተ ሕዝቡ ወደ አውደ ምህረቱ መለሰ፡፡ በሕዝቡና በካህናቱ ፊት የሚሾሙት ኤጲስ ቆጶሳት ተቀምጠዋል፡፡ ፓትርያርኩና ከፓትርያርኩ ጋር የኤጲስ ቆጶስነት ሹመቱን የሚያከናውኑ ሊቀ ጳጳሳትም አብረው ከጳጳሱ ጎን ተቀምጠዋል፡፡ ሕዝቡና ካሕናቱ ሹመቱን ለመከታተል ፊታቸውን ወደ ተሿሚዎቹና ሿሚዎች አዙረው ቆመዋል፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ፍትሐ ነገሥት ሕግና ሥርዓት መሠረት “ኤጲስ ቆጶስ የሚሾመው በቤተ ክርስቲያኗ ሥርዓት መሠረት ምንም ዓይነት ነቀፋና ነውር የሌለበት፣ ዐይነ ስውርና ደንቆሮ ያልሆነ፣ ዕድሜው ከሃምሳ ዓመት በላይ የሆነ፣ ሐዲስ ኪዳን እና ብሉይ ኪዳንንም ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ ሰነፍ ያልሆነና ፈጥኖ ለመማታት የማይጋብዝ... መሆን ይኖርበታል፡፡” ይላል

ቴሌቭዥኑ ላይ ፓትርያርኩና ከእሳቸው ጋር ሹመቱን የሚያከናውኑት ሊቀ ጳጳሳት እጃቸውን መታጠብ ጀመሩ፡፡ ዳንኤል እጅ መታጠቡ ግራ ስለገባው ዘላለምን ዞሮ አየውና መጠየቅ ጀመረ፡፡ ዳንኤል የሚያየው ነገር ልክ አዲስ ልብስ እንደተገዛለት ሕጻን ብርቅ ሆኖበታል፡፡፡

“ዘሌ ምንድነው? ለምንድነው እጃቸውን የሚታጠቡት?”

ዘላለም ማስረዳቱን ጀመረ “እጃቸውን የሚታጠቡት ምክንያት 'እኛ በምናውቀው በአፍአ ንጹህ ብለን ሾመንሀል፤ አንተ በምታውቀው በውስጡ ዕዳ የለብንም፤ ዕዳው በአንተው ነው' ማለታቸው ነው፡፡” ቴሌቭዥኑ ውስጥ ምስል እንጂ ምንም ዓይነት ድምጽ አይሰማም ሕዝቡ በአጠቃላይ ፀጥ እረጭ ብሎ በዓለ ሲመቱን በአንክሮ እየተከታተለ ነው፡፡ ዳንኤል በአግራሞት ቴሌቭዥኑ ላይ ዐይኑን ሳይነቅል እየተመለከተ ነው፡፡ ፓትርያርኩ ሹመቱን ለማከናወን መስቀል ይዘው ከወንበራቸው ተነሱ፡፡ ሌሎች ሦስቱ ሊቀ ጳጳሳትም ፓትርያርኩን ተከትለው ተነሱ፡፡ አጠገባቸው የነበሩት ቀሳውስት ፓትርያርኩ ከወንበራቸው ሲነሱ በትረ ሙሴያቸውን እንዳይጥሉት አስተካከሉላቸው፡፡ ዲያቆናት በተሿሚው ኤጲስ ቆጶስ ራስ የአራቱን ወንጌላውያን መጻሕፍት ዘርግተው ቆመዋል፡፡



CamScanner

ዳንኤል እንደ ለመደው መጠየቅ ጀመረ "ዲያቆናቱ ለምንድነው መጽሐፍ ቅዱስ የያዙት?"

"ዳኒ ቤተ ክርስቲያን ትሔድ አልነበረ እንዴ? ምንድነው ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አላስተማሩህም?" ዘላለም ሳቁ መጣበት። ዳንኤል እንደመሸማቀቅ አለ።

"ለማንኛውም የዚህ ትርጉም ኤጲስ ቆጶሱን ስለ ወንጌል ታስተምራለህ፤ ስለ ወንጌል መከራን ትቀበላለህ ማለታቸው ነው።" ዳንኤል እንደ መከሳተር አለ።

ዘላለም ዳንኤል የከፋው ስለመሰለው "ዳኒ ይቅርታ አታኩርፍ ስቀልድህ ነው" ትከሻውን በትከሻው ገፋ እያደረገ።

ፓትርያርኩ ጸሎታቸውን እያደረሱ የመጀመሪያው ተሿሚ ኤጲስ ቆጶስ ፊት ለፊት ሄደው "…ንህነ ናነብር እደዊዋ ዲበ ዝንቱ ገብር ኅሩይ ዘ እግዚአብሔር በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ…" እያሉ ቃለ ቡራኬያቸውን እያሰሙ፤ በቀኝ እጃቸው የያዙት መስቀል ለኤጲስ ቆጶሱ አስጨበጡትና እጃቸውን ኤጲስ ቆጶሱ እጅ ላይ ጭነው ጸሎተ ሲመቱን ማድረግ ጀመሩ። ሕዝቡም ሆኑ ካህናቱ የፓትርያርኩን ጸሎት "አሜን!" እያሉ መቀበል ጀመሩ። ዳንኤል መጠየቅ አፍሮ ዝም ያለ ስለመሰለው፤ ዘላለም ሳይጠየቅ ማስረዳቱን ቀጠለ "ፓትርያርኩ ለኤጲስ ቆጶሱ መስቀል ያስጨበጡት ትርጉሙ፤ መከራን ትቀበላለህ ማለታቸው ሲሆን፤ እጃቸውን እጁ ላይ የጫኑበት ምክንያት 'ከእንግዲህ በኋላ እኩል ነን' ማለታቸው ነው።"

ፓትርያርኩ ጸሎታቸውን ከጨረሱ በኋላ ሌሎች ጳጳስ ቆጶሳት ተሿሚውን ኤጲስ ቆጶስ እጅ መንሳት ጀመሩ። ፓትርያርኩ ጎንበስ አሉና የተሿሚውን ኤጲስ ቆጶስ ፊት ለፊት በእስትንፋሳቸው እፍ አሉበት። ዳንኤል የሚያየው ነገር ትንግርት ስለሆነበት ዘላለምን የፓትርያርኩ እፍ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲነግረው ስለፈለገ ዞሮ አየው።

ዘላለምም ምንም የፊት ለውጥ ሳያሳየው በትህትና ያስረዳው ጀመር "ፓትርያርኩ በእስትንፋስ እፍ ያሉበት ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን እፍ ብሎ መንፈስ ቅዱስን እንደ ሰጣቸው ሁሉ ያንን የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት አድርገው ፓትርያርኩ ለተሿሚው ኤጲስ ቆጶሱ መንፈስ ቅዱስን ሲያሳድርበት ነው።" በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ያለ ሁሉም ሰው በአግራሞት እና በአንክሮ ትዕይንተ ሢመቱን እየተከታተለ ነው።

ፓትርያርኩ ሥርአተ ሢመቱን እንደ ጨረሱ ሕዝቡና ካህናቱ በእልልታ በጭብጨባ "ይደልዎ! ይደልዎ! ይደልዎ!" ማለት ጀመሩ። ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ከገባበት ጥልቅ አርምሞ ወደ ጭብጨባና ምስጋና ተቀየረ። ሕዝቡና ካህናቱ ተሿሚውን ኤጲስ ቆጶሱን "ይገባዎታል!" ማለቱን ቀጠሉ።



CamScanner

# ምዕራፍ ፱

## አዲስ አበባ- ሳሪስ

ገና የሳምንቱ የመጀመሪያ ዕለት ነው፡፡ ተማሪዎች ንጹህ የደንብ ልብሳቸውን ለብሰው ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱበት፤ ሠራተኛው የሰንበት እረፍቱን አጣጥሞ ሳይጠግብ፤ ከእረፍት መልስ ወደ ሥራ በመግባቱ፤ ገሚሱ እኩሩፎ፤ ገሚሱ ደስ ብሉትና ሽቅርቅር ብሎ በሚንቀሳቀስበት ዕለት አዲስ አበባ ክፍት ያላት ትመስላለች፡፡

ፀሐይ የለም፤ ዝናብም የለም፤ አየሩ ዳምኗል፡፡ ንፋሱ ከየት መጣ ሳይባል እፅዋቱን ከግራ ቀኝ እየወዘወዘ ያላትማቸዋል፤ ያልጠበቀ ቆርቆሮ ካገኘ ጣራ እንደሚቀይር አናጢ ካልነቀልኩ እያለ ቆርቆሮዎችን ያዙኝ ልቀቁኝ ይላል፤ ቀሚስ ለባሽ እንስት ካገኘ እንደ አግድም አደግ ጎረምሳ በአደባባይ ላይ ካልገለብኩት ብሎ ይፎክራል፤ እቅመ ደካማና ኑሮ የከበዳቸውን አዛውንቶች እንደ ማጅራት መቺ የለበሱትን እራፊ ገፍፌ ካልወሰድኩት ይላል፡፡ የዳመነው አየር ከፍቅረኛው ለተለያየ፤ ኑሮ አልሞላ ብሎ ክፍት ላለው፤ ፍቅር ለያዘው፤ ፈተና ላለበት ጭንቀታም ተማሪ ትንሽ ክብድ የሚል መንፈስ አለው፡፡

ሰንፔር በተቃራኒው ከሰሞኑ ሁኔታ ወጥታ ነቃ ብላ እየዘነጠች ነው፡፡ ቢሆንም ምንም ዓይነት የተለየ የፊት ማስዋቢያ ቅባት አልተቀባችም፡፡ ከሰሞኑ በተለየ ሁኔታ ግን ዐይኗ ኩል ሲያገኝ፤ ከንፈሯ ሊፒስቲክ ሲቀባ የድሮው ደም ግባቷ ተመለሰ፡፡ የጠዋቷ ፀሐይ በእሷ በኩል የወጣች ይመስል ብሩህ ጸዳል ለብሳለች፡፡ ወንድሟ ለስብሰባ ብሎ ዱባይ ስለሔደ ሰንፔር ከሠራተኛዋ ጋር ብቻዋን ነው ያለችው፡፡

አሁን ወደ ዩቶጵያ ልትሄድ አስባለች፡፡ ስለዚህም ከላይ የካሊቪንና ኬሊ' ምርት የሆነውን ሰማያዊ ቲሸርት ላይ ቀይ ሹራብ ደርባለች፤ የታይላንድ ሰማያዊ ጅንስ ሱሪ አድርጋ ከስር 'ኦል ስታር' ሸራ ጫማ ተጫምታለች፡፡ ዩቶጵያ ወደሚባለው አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመሔድ ነው የተነሳችው፡፡ ከትምህርት ቤቱ የሆነ ፍንጭ እንደምታገኝ ተሰምቷታል፡፡ ስለ ዩቶጵያ ለማወቅ ከጣረችው ሁሉ ልትደርስበት የቻለችው አዲስ አበባ ያለው ዮቶጵያ ትምህርት ቤት ብቻ ነው፡፡

ሰንፔር ዩቶጵያ ስለሚለው ቃል ብዙ ተመራምራለች፡፡ ቃሉ በግሪክና በእንግሊዘኛ የተለያየ ትርጉምና አነባበብ አለው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ዩቶጵያ የሚለው ቃል በጥቅም ላይ ያዋለው ቶማስ ሞር ሲሆን የተጠቀመው በግሪክኛ 'እዩ-ቶጵያ' ተብሎ ሲነበብ በ'ou' (ኦዩ) እና በ'topos' (ቶፐስ) ከተባሉ የሁለት ቃላት ውሕደት የተገኘ ሲሆን 'ou' ማለት 'የሌለ' የሚል ትርጉም ሲኖረው topos' ማለት ደግሞ 'ቦታ' ማለት ነው፡፡ ስለዚህ 'ou-topos' 'የትም የሌለ ቦታ' የሚል ትርጉም ያለው ቃል ነው፡፡



CamScanner

በእንግሊዘኛ 'ኢዩ-ቶጵያ' ተብሎ የሚነበብ ሲሆን ትርጉሙም 'Eu' (ኢዩ) የሚለውን ቃል 'ጥሩ' የሚል ትርጉም ሲሰጡት 'topos' (ቶፖስ) ደግሞ 'ቦታ' በማለት ይፈታዋል። በእንግሊዘኛና በግሪክ የትርጉም ልዩነት እንዲኖረው የሆነው በመሠረቱ ቃሉ ተለዋዋጭ ሆኖ ሳይሆን ምሁራኑ በቃሉ ትርጉም ላይ መስማማት ስላቃታቸው ነው።

ዩቶጵያ የሚለው ቃል አሁንም ድረስ በዓለም ላይ የሚታወቀው 'በምድር ላይ የትም የሌላ መልካም የፍቅር፣ የሰላም፣ የፍትሕ፣ የእኩልነት ምኞትን' የሚገልጽ ሲሆን፣ በቶማስ ሞር የተጻፈው መጽሐፍ ሁሉ የተሟላለት ዓይነት አኗኗርን ለመግለጽ ነበር መጽሐፉን ዩቶጵያ ሲል የሰየመው። ቶማስ ሞር መጽሐፉን የጻፈው አሜሪጎ ቬስፑሲ ከተባለ አገር አሳሽ ጋር አብሮ ሲያስስ ከነበረው ራፋኤል የሰማውን ታሪክ ነው።

ይህ መጽሐፍ ከተጻፈ በኋላ በተለይ በእንግሊዝ አገር ውስጥ ብዙ ለውጦች መጥተዋል ብለው የሚስማሙ ምሁራን ብዙ ናቸው። "የእንግሊዝ ነገሥታት ቶማስ ሞር የጻፈውን ዮቶጵያ መሰል አገር በእንግሊዝ ለመፍጠር ጥረት አድርገዋል። በተለይ ንግሥት ኤልሳቤት ዮቶጵያ መጽሐፍ ላይ ያለውን ሥነ መንግሥታዊ፣ ሥነ ማኅበራዊና ሥነ ምጣኔ ሀብት... አኗኗርን በመኮረጅ በእንግሊዝ አገር እውን ለማድረግ ሞክራለች" እያሉ ያደንቋታል። ቶማስ ሞር በዩቶጵያ መጽሐፉ ላይ 'የእግዚአብሔር አገር' እያለ የገለጻትን ቦታ ለማስመሰል ቀላል የማይባል ጥረት ተደርጓል።

"ከዚያ በኋላ አውሮፓና አሜሪካ ዩቶጵያን አገራቸው ውስጥ እውን ለማድረግ የተጓዙበት ርቀት ለተለያዩ ሥነ ምጣኔ ሐብት፣ ሥነ መንግሥስትና ማኅበራዊ ርዕዮተ ዓለሞች መፈልፈል መሰረት የጣለ ነው" ብለው ዩቶጵያ መጽሐፍ ላይ ምርምር ያደረጉ ሰዎች ይሞግታሉ።

አንዳንድ ምሁራን ግን ይህ ቶማስ ሞር በመጽሐፉ ላይ የገለጸው አኗኗር "የድሮ የኢትዮጵያውያን አኗኗር ነው" ብለው ይከራከራሉ። ለዚህም መከራከሪያ የመጀመሪያ ሆኖ የሚቀርበው የመጽሐፉ ርዕስ ዮቶጵያ መሆኑን ነው። ምክንያቱም ዩቶጵያ አንደኛው 'የትም የሌለ ቦታ' የሚል አንድምታ ሲኖረው ሌላኛው ደግሞ 'መልካም ቦታ' የሚለውን ትርጉም ያሳየናል።

"ዮቶጵያ የሚለው ቃል የተወሰደው ከራሱ ከኢትዮጵያ ሲሆን በግዕዙም 'ጦቢያ' የሚል አቻ ቃል አለው።" አሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ቁጥር አራት ላይ ያለውን 'ከመ ጦብ ውእቱ' የሚለውን ሐረግ ወደ አማርኛው በመመለስ 'መልካም እንደሆነ አየ' የሚል ትርጉም መያዙን አስረግጠው ይናገራሉ።



CamScanner

"ይህም መልካም የሚለው ቃል የጦቢያ አቻ ትርጉም ሲሆን በላቲን ደግሞ ዩቶጵያ ነው። ስለዚም የቶማስ ሞር ዩቶጵያ የሚለው የመልካም ቦታ ትርከት ከኢትዮጵያ እንደ ወሰደው ማረጋገጫ ነው" ብለው መከራከሪያቸውን አሀዱ ይሉና "ይሄ 'የትም የሌለ ቦታ' የሚለው ትርጉም ማደናገሪያ እንጂ ትክክለኛው የቃሉ ትርጉም 'መልካም ቦታ' እሱም ከአስራ ሁለተኛ ክፍለ ዘመን እስከ አስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን የነበረችውን ኢትዮጵያን የሚያሳይ ነው" ይላሉ።

ሌላው መከራከሪያቸው "አሳሹ ራፋኤል ሂትሎይድ ጣና ደሴት ላይ ቁጭ ብሎ ካህንም ንጉሥም የሆኑትን ኢትዮጵያውያን የአገር መሪዎችንና ያለ ጭንቀትና ያለ መከራ በሠላም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሕይወትን ካየ በኋላ ለቶማስ ሞር ነግሮት ጻፈው" ይላሉ።

ለዚህም ማረጋገጫ ሲጠቅሱ "ካህንም ንጉሥም የሆኑት እንደ ቅዱስ ላሊበላ፣ ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ፣ ቅዱስ ነአኩቶለአብ እና ቅዱስ ገብረማርያም የተባሉት ነገሥታት ኢትዮጵያውያን የቄሱ ዮሐንስ አገር እንድትባል አድርጓታል" ይላሉ። ከዚህም በላይ መከራከሪያቸውን ከፍ ሲያደርጉ "የኢትዮጵያ ነገሥታት መንፈሳዊ ትምህርት የቀሰሙና መንፈሳዊ እውቀታቸውን አገር ለመምራት ስለሚጠቀሙበትና ኢየሱስ ለሰው ልጅ የሰጠውን የአኗኗር መርህ በአገር ላይ በማምጣት ኢትዮጵያን ለመምራት ጥረት ያደርጉ ነበር። ከዩቶጵያ መጽሐፍ በኋላ ግን ኢትዮጵያ ከውስጥ ችግሯ ይልቅ ከውጪ የሚመጡ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ጥቃቶች እንደ ቀድሞዋ መረጋጋትና ሰላም አግኝታ መቀጠል አልቻለችም" ሲሉ ይሞግታሉ ምሁራኑ። ሰንፔር ይህን ሁሉ ያወቀችው ዩቶጵያ ስለሚለው ቃል ለማወቅ ጥረት ባደረገች ጊዜ ነው።

-----//------

## ኢትዮጵያ-አዲስ አበባ

ዳመናው አሁንም አልገለጠም፣ ሰማዩም ያው እንደከፋው ነው። ይሁን እንጂ ሰንፔር የጉቺ ምልክት ያለበትን ትልቅ የፀሐይ መነጽር አድርጋ ዮቶጵያ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትንሽ ራቅ ብላ ቆማለች። ተማሪዎች እየተንጫጩ ነው። የእረፍት ሰዓታቸው እንደሆነ ግልጽ ነው። የትምህርት ቤቱ ጥበቃ በሩን ገርበብ አድርገው ፊታቸውን ወደ ውጪ አውጥተው ወጪ ወራጁን እየተመለከቱ ነው።

ሰንፔር የትምህርት ቤቱ ጥበቃ እስኪገቡ ድረስ ሰው ቀጥሮ እንደሚጠብቅ ሰው የእጅ ሰዓቷን በተደጋጋሚ ማየት ጀመረች። ጥበቃው ወደ ውስጥ ሊገቡላት ስላልቻሉ በመጣችበት መንገድ ተመልሳ ሔደችና ትንሽ ራቅ ብላ ወደ ኋላዋ ገልመጥ አድርጋ የዘበኛውን ወደ ውስጥ መግባት ተመለከተች።

ዘበኛው ወደ ውስጥ እየገቡ ነው፡፡ ሙሉ ለሙሉ እስኪገቡ ድረስ መሔዷን ሳታቋርጥ ቀስ ብላ በድጋሚ ዞራ አየቻቸው፡፡ አሁን ግቢው ውስጥ ገብተዋል፡፡ ሰንፔር ፊቷን መለሰችና ወደ ዩቶጵያ ትምህርት ቤት መንዝ ጀመረች፡፡

በሩ ላይ ደርሳ ትምህርት ቤቱን መቃኘት ጀመረች፡፡ በትልቁ ትምህርት ቤቱ በር ላይ በግምት ሁለት ሜትር በሦስት በሆነ ብረት ላይ ባነር ተወጥሮ "ዩቶጵያ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት" የሚለው ሐረግ በነጭ ቀለም በፈዛዛ ሰማያዊ በተቀባ መደብ ላይ በትልቁ ተጽፏል፡፡ ከዚያም የተበታተኑ የግዕዝ ቁጥሮችና ሆሔዎች አሉ፡፡ በትልቁ በቀይ ቀለም 'ተ' የሚለው ሆሄ ተጽፏል ከዚያም የሒሳብ ቀመር ምልክት የሆኑት በቀይ ቀለም ብትንትን ብለው '+'፣'-'፣'÷'፣'x' እና ከ 'ተ' ፊደል ትይዩ 'ኧ' ምልክት ይታያል፡፡ ከዚያም በመቀጠል ዩቶጵያ የሚለው ቃል ሆሄዎች ኃደልና በተንተን ብሎ በአነስተኛ መጠን በድጋሚ ተጽፏል፡፡ ከእሱ ቀጥሎ 'ማር 10÷14+6' የሚል ቃል፣ ቁጥርና የሒሳብ ቀመር ተጽፏል፡፡

ከበስተጀርባ ደግሞ ሆሄያትና ቁጥሮች ከላይና ከታች ዝም ብለው እንደ አልባሌ ነገር ተበትነው 'መ[፲] ደ[፬] ረ[፮] ሸ[፫]' የሚል ቁጥርና ሆሄያት የተዋሐዱበት ሐረግ ይታያል፡፡ ሰንፔር የምታየው ሆሔና የግዕዝ ቁጥር ዐይኗ ላይ ተምታታባት፡፡ ስለዚህ ስልኳን አንስታ ፎቶ ማንሳት ጀመረች፡፡



CamScanner

## ምዕራፍ ፶፩

## ካሊፎርኒያ-ሎስአንጀለስ

ቶኒ ራሱ ማድረግ ሲችል ለምን ለዓለም እንዲያደርግ ፈለገ የሚለውን ሃሳብ ሲያወጣ ሲያወርድ ነበር። ቢሆንም ምንም መልስ አላገኘለትም። ዲበኩሉ ግን ፓትርያርኩ መኝታ ቤት ውስጥ ድብቅ ካሜራ እንዳለ ነግሮታል። "ድብቅ ካሜራ ስላለ ነው አንተ ፓትርያርኩን እንድትገድል የሚያደርግህ። ከዚያም ካንተ ሁለት ነገር ያገኛል አንደኛ ማስፈራሪያ ቪዲዮ ሲሆን ሌላው ታማኝነትህን ይለካበታል።" ለዓለም በዲበኩሉ ነገር ተገርሟል። ዲበኩሉን ሲያውቀው ሐኪምና ዲያቆን ሆኖ እንጂ እንዲህ እሳት የላሰ ሰላይ ሆኖ አይደለም። ሰውን አውቀዋለሁ ማለት በጣም እንደሚከብድ በአግራሞት እያሰበ ነው።

ለዓለም ፓትርያርኩ መኝታ ክፍል ገባና ወደ አልጋቸው ማተረ። ድብን ያለ እንቅልፍ ወስዷቸዋል። በስሱ የማንኮራፋት ድምጽ ይመስላል። ለዓለም ከፓትርያርኩ አልጋ ፊት ለፊት ቆመና የእጅ ሰዓቱን ተመለከተ። ልክ ነው ጀንበር እያዘቀዘቀች፤ ምሽቱ የቀኑን ቦታ ሊረከብ ነው። ፓትርያርኩ ኢንሱሊን የሚወጉበት ሰዓት ደርሷል። የዛሬው ኢንሱሊን ሕይወት አድን አይደለም። ሕይወት ቀጣፊ እንጂ። ይህቺን ዛሬ የምትጠልቀውን ጀንበር ዳግም ሳይመለከቱ እስከ ወዲያኛው ያሸልባሉ።

ለዓለም እጁን አጣመረና በተመስጦ ስለ ፓትርያርኩ "ለብዙ ዓመታት እንደለባቸው ሳይሆኑ፤ በሆነው ነገር ሁሉ ሳይደሰቱ፤ በቤተ ክርስቲያን መለያየት እንዳመማቸው፤ ለቤተ ክርስቲያን የሚበጀውን መፍትሔ ሳያመጡ፤ ስማቸው ከመለያየት ጋር ሁሌ እየተነሳ፤ ያልታረመውን የቤተ ክርስቲያንን ስህተት እርምት ሳይሰጡ ለዘላላም ሊያሸልቡ ነው።" አለ ለራሱ።

ከመኝታቸው በላይ የማርያምና የልጇ የኢየሱስ ሥዕል ወይም የተዋሕዶ እምነት ተከታዮች 'ምስለ ፍቁር ወልዳ' የሚሉት ምስል ተሰቅሏል። ሥዕሉ ላይ ቡኒ መቀጠሪያ አለ። ከመኝታ ክፍሉ በስተቀኝ ላይ በትልቅ መስታወት ፍሬም ውስጥ የሚካኤል ሥዕል ይታያል። በስተግራ ባለው ራስጌያቸው አካባቢ ትንሽ ሳጥን ያለች ሲሆን መጻሕፍት ተቀምጠውበታል። በሣጥኑና በአልጋው መሀል ላይ የፓትርያርኩ በትረ ሙሴ ጋደድ ብሎ ተቀምጧል።

በአልጋቸው ፊት ለፊት ባለው ልብስ መስቀያ አናት ላይ የፕትርክና ቆባቸው ተሰቅሏል። ከዚያም ዝቅ ብሎ የክህነት ቀሚሳቸው ተሰቅሏል። ልብሰ ተክህኖው ላይ አይከናቸው ተንጠልጥሏል። የመኝታ ቤቱ መብራት ደብዘዝ ያለ ብርሃን ያለው ሲሆን ክፍሉ ውስጥ የመልካም ሽቶ ጠረን አውዶታል። መኝታ ክፍሉ እንደ ፓትርያርኩ ረጋ ያለ፤ የጸዳና እቃዎቹ ሁሉ በአግባቡ የተሰደሩ ናቸው።



CamScanner

ለዓለም መቁረጥ አለበት ኢንሱሊኑን ሊወጋቸው ወደ ራስጌያቸው ሄደ። ትከሻቸው ላይ ነው የሚወጋቸው። በጣም ሲጠጋቸው ሰውነታቸው በጣም ደክሟል። ቆዳቸው ሥጋ ያለው አይመስልም፤ በእርጅና ተጨረማምቷል። በሃሳብ ድካም የዛሉ ይመስላሉ። በልባቸው የሚያብሰለስሉት ትልቅ ነገር እንዳለ ፊታቸው ላይ ይታያል። ትክት ብሏቸዋል። ለዓለም ኪሱ ውስጥ ካለው ባለ ጥቁር የመነጽር ማስቀመጫ ከመሰለው ጠንካራና ውብ እቃ ውስጥ በኢንሱሊን የተሞላውን መርፌ አወጣ።

ፓትርያርኩ ከተኙበት ተገላበጡ፤ መርፌውን ወደ ትከሻቸው አስጠጋና በቀኝ እጁ ግራ ትከሻቸው ላይ ያዘና መርፌውን ወደ ክንዳቸው ጡንቻ አስጠጋና ከመርፌው እናት ላይ ይገፋው ጀመር። ፓትርያርኩ መርፌው ሰውነታቸው ውስጥ ሲገባ እንደ መንቃት አሉ። ቢሆንም መነሳት ከበዳቸው፤ አቅም አነሳቸው።

------//------

መርሐዊና ሪቢዮ ዜናውን ለመስማት በጥፍራቸው ቆመው እየጠበቁ ነው። አቡነ መርቆሬዎስ መሞታቸውን ቶኒ ደውሎ ነግሯቸዋል። ነገር ግን ሲኤን ኤን ሰበር ዜና ብሎ የፓትርያርኩን ሞት ማርዳት ሲጀምር ፍጥጥ ብለው መመልከት ጀመሩ።

የምዕራብ እንግሊዝ የአነጋገር ለዛ ያላት ዜና አንባቢ ሰበር ዜናውን ለዓለም ሕዝብ ከነገረች በኋላ በስካይፒ የፓትርያርኩን ሞት ያረጋገጡት ጥቁር አሜሪካዊና የኢትዮጵያ የዘር ሐረግ ያላቸውና የካሊፎርኒያ የማኅበረሰብ ሆስፒታል የስኳርና ተያያዥ ጉዳዮች ፕሮፌሰር አቅርባ ማነጋገር ጀመረች።

ጋዜጠኛዋ ጠየቀች "ፓትርያርኩ ካሊፎርኒያ የማኅበረሰብ ሆስፒታል ገብተው ነበር?"

ከነጩ የህክምና ጋዎን ሥር ሰማያዊ ከረቫት በሰማያዊ ሸሚዝ ላይ ያሰሩት ሐኪም ጥያቄው እንዳልተሰማቸው ሁሉ ትንሽ ዘግየት ብለው መልስ መስጠት ጀመሩ

"አይ ፓትርያርኩ እኛ ሆስፒታል መምጣት አልቻሉም ነበር"

"ለምንድነው ያልመጡት?" አለች ጋዜጠኛዋ እንደ መኮሳተር ብላ

"በመጀመሪያ እኛ ሆስፒታል ሲደወል የሕክምና ቡድን አዋቅረን ነበር በአንቡላንስ የላክነው"

ጋዜጠኛዋ አቋረጠቻቸው "እርሶ ቡድን ውስጥ ነበሩ?"

"አዎ የቡድኑ መሪ ሆኜ ነበር የሔድኩት"

"እሺ ዶክተር ፓትርያርኩ መኖሪያ ቤት ሲሄዱ ምን ተፈጠረ ታዲያ?"



CamScanner

“ፓትርያርኩ መኖሪያ ስንደርስ ግን በሕይወት አልነበሩም”

“ምንድነው የሞታቸው መንስኤ?”

“ስኳር ስለ ነበረባቸው ‘ሐይፖ' ግላይሴሚያ ወይም ደግሞ የሰውነታቸው የግሉኮስ መጠን ከሚገባው በታች ወርዶ ነበር”

“ዶክተር ምንድነው ለዚህ ችግር ያጋለጣቸው?”

“ለዚህ ያጋለጣቸው ምክንያት ብዙ ሊሆን ይችላል። አንደኛው ከመጠኑ ያለፈ ኢንሱሊን ሊሆን ይችላል ወይም ደግሞ ምግብ በአግባቡና በሰዓቱ አለመውሰድ ሊሆን ይችላል። በተለይ ይህኛው ምክንያት ውኃ ያነሳል ምክንያቱም መንፈሳዊ ሰው ስለሆኑ ጾምና ጸሎት ያበዛሉ ስለዚህ በከፍተኛ መጠን የስኳር መጠናቸው ሊያወርደው ይችላል።

“የሰውነታቸው የስኳር መጠን በተለያዩ መንፈሳዊ ተግባራት ቀንሶ ተጨማሪ ኢንሱሊን ሲወጉ ለዚህ ችግር ሊዳርጋቸው ይችላል። ሌላኛው ምክንያት ኩላሊት ሥራውን በአግባቡ ማከናወን ሲያቅተው ነው። ይህ እንኳ ሊሆን አይችልም ምክንያቱም በቅርብ ጊዜ ሙሉ የጤና ምርመራ አድርገው ከታወቀው የስኳር ችግራቸው ውጪ ደህና ነበሩ።”



CamScanner

## ምዕራፍ ፶፪

## ሜክሲኮ ሲቲ

ዲበኩሉ በኪራይ ያገኘውን መኪና ለባለቤቱ ቁልፉን አስረከበና ክፍያውን በፖስታ አሽጎ ሰጠው። አቡነ መርቆሬዎስ በትረ ሙሴያቸውን ሳይሆን ተራ መቋሚያ ለሰውነታቸው መደገፊያ ቢይዙም ድካሙን እንዳልቻሉት ፊታቸው ላይ ያስታውቃል። ዲበኩሉ የፓትርያርኩን በድካም የዛለ ፊታቸውን ተመለከተና በፍጥነት የአየር መንገዱን ሠራተኛ ዊል ቼይር እንዲያመጣላቸው በምልክት ነገረው።

ፓትርያርኩን በሜክአፕ እብድ አድርጎ ፓስፖርትና መታወቂያቸው ላይ እንደሚታየው ፎቶ አባ ወልደ ትንሣኤ ታፈሰን አስመስሏቸዋል። ፓትርያርኩም እንደ ጳጳስ ሳይሆን እንደ አንድ ተራ መነኩሴ ነው የለበሱት። ከተፎው የአየር መንገዱ ሠራተኛ የሰው ጋሪ እየገፋ ይዞ መጣና እነ ዲበኩሉ ፊት ውድ መኪና እንደያዘ ኳረምሳ በኩራት ቆመ።

ዲበኩሉ በትህትና ልጁን "እግዚአብሔር ይስጥልን" አለውና ፓትርያርኩን በትህትና እንዲቀመጡ "ቅዱስ አባታችን እባክዎ ይቀመጡ" ብሎ ከወገቡ ጎንበስ ብሎ በእጁ ወደ ዊልቸሩ ጋበዛቸው።

ፓትርያርኩ ከአንገታቸው ጎንበስ ብለው ድምጽ ሳያወጡ ምስጋና አቀረቡና ዊልቸሩ ላይ ቁጭ አሉ። ፊታቸው ላይ የእረፍት ስሜት ተነበበ። ዲበኩሉ የራሱንና የፓትርያርኩን መጠነኛ ሻንጣዎች በሌላ የእቃ ጋሪ ላይ አደረገና የሰው ጋሪ ያመጣለትን ወጣት ልጅ እንዲገፋለት ጠየቀው።

ዲበኩሉ ፓትርያርኩን እየገፋ ወደ ሜክሲኮ ሲቲ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ተርሚናል መግባት ጀመረ። ዲበኩሉና አቡነ መርቆሬዎስ ወደ አዲስ አበባ ሊመጡ ነው። አቡነ መርቆሪዮስ የግድያ ሙከራ እንደተቃጣባቸው ካወቁ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ መሄድ ፈቅደው ከነዲበሉ ጋር መተባበር የጀመሩት። ዲበኩሉ ፓትያርኩን በዊልቼር እየገፋ በሀሳብ እንዴት ፓትርያርኩን እንዳስመለጠ ያስብ ጀመረ።

---------//---------

ዲበኩሉ ፓትርያርኩ ሊገደሉ መሆኑን መረጃ ሲደርሰው አዲስ አበባ ካለው የፊስአልጎስ ሕቡዕ ቡድን ጋር መነጋገር ነበር የጀመረው። ሕቡዕ ቡድኑ አሜሪካ እና አውሮፓ በልዩ ሁኔታ የትምህርት እድል እንዲያገኙ ካደረጋቸው ውስጥ ካሊፎርኒያ በርክሌይ ዩንቨርስቲ በፒኤችዲ መርሐ ግብር የኮምፒውተር ሳይንስ ተማሪው ዋልድባ እንዲያግዘው ተደረገ። ዋልድባ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ውጤቱ በጊዜው አብረውት

ከተፈተኑት ብቻ ሳይሆን ከዚያ በኋላ ከተካሄደው ብሔራዊ ፈተና ሁሉ ትልቁ ውጤት የእሱ ነው።

ዋልድባ እና ዲበኩሉ መጀመሪያ ያደረጉት ስቴት ዲፓርትመንት የሚሠሩ ሰዎችን ፈልገው ከፍተኛ ዶላር ከፍለው አዲስ አበባ ካለው የፊስአልጎስ አባል ከሆኑት ሰው ስምና ፎቶ በማስመሰል ፓስፖርት አወጡላቸው።

ፓስፖርቱ ከተገኘ በኋላ ከአሜሪካ ወደ ሜክሲኮ ለመሄድ ፈቃድ ካለው ድርጅት መኪና መከራየት፣ ሕጋዊ የመንጃ ፈቃድ፣ ሜክሲኮን ለመጎብኘት የሚያስችል የቱሪስት ፈቃድ ለሦስቱም ማውጣት ይጠበቅባቸው ነበር። ዋልድባ መኪናውን በራሱ ስም አወጣና ቤተሰቦቹንም ይዞ እንደሚወጣ አስመዘገበ። ለፓትርያርኩም በአዲሱ ፓስፖርታቸው መሠረት የጉዞ ፈቃድ አወጣላቸው።

ቀጥሎ ያለው ጉዳይ ሬሳ ማግኘት ነበር። ሐኪም ስለሆነ ለዲበኩሉ ሬሳ ማግኘት ቀላል ነበር። ሬሳው ይገኛል ችግሩ ፓትርያርኩን መምሰሉና የሞት ሪፖርቱን የሚፅፍለት ሐኪም ማግኘቱ ነበር። ይኸኛው ፓስፖርት እንደማግኘት የሚከብድ አልነበረም። በየቀኑ ሕይወታቸው ከሚጠፋ ጎዳና ተዳዳሪዎች ውስጥ የአንዱን ሬሳ ማግኘት ቀላል ነበር። በዚያ ላይ ፓትርያርኩ በክፍት ሬሳ ሳጥን መቀበር እንደማይፈልጉ ስለታወቀ እንዴ ሞታቸው ከታወቀ ቶሎ ሬሳ ሳጥን ውስጥ ከትቶ ሳጥኑን ማሸግ ቀላል ባይሆንም ፓስፖርት የማግኘት ያህል አልከበደም።

የሞት ሪፖርቱን ለመጻፍ የካሊፎርኒያ ሆስፒታል ፕሮፌሰር የሆኑት ትውልደ ኢትዮጵያዊው ፕሮፌሰር ፓርክ በላቸው ተገኙ። በእለቱ ተረኛ ባይሆኑም በመላ ተራቸውን አስቀየሩና ፓትርያርኩ የሚገደሉበት ቀን ሆስፒታል ተገኙ። ሉስ አንጀለስ ጎዳና ላይ በድብድባ ጭንቅላቱን ተመትቶ የሞተ ጎልማሳው የሜክሲኮና የናይጀርያ ክልስ ሰው ስላገኙ ሬሳውን ለፓትርያርኩ ምትክ አደረጉት።

ቶኒ ለዓለምን በድብቅ ካሜራ እንደሚያየው ስለታወቀ እንዳይጠረጥረውና እንዲሁም ፓትርያርኩን ከክፍሉ ይዘዋቸው ሲወጡና ነገሩን እስኪያስረዷቸው ድረስ ለጊዜው ጥልቅ ሰመመን ውስጥ የሚከት መድኃኒት ወጓቸውና ፓትርያርኩ ራሳቸውን የመሳት ያህል እንቅልፍ ወሰዳቸው።

ዲበኩሉና ዋልድባ ወደ ሜክሲኮ ድንበር ለመሻገር የሚመች መኪና አዘጋጅተው መጠባበቅ ጀመሩ። ለዓለም ለፓትርያርኩ የሰመመን መድኃኒቱን ከሰጣቸው በኋላ ሞታቸውን ሲያረጋግጥ ለሆስፒታል እንዲደውል በተነገረው መሠረት መጀመሪያ ሆስፒታል ደወለ።

ፕሮፌሰር ፓርክ በላቸው መጣና መሞታቸውን አረጋግጦ የሞት ማረጋገጫውን ምስክር ወረቀት ሰጥቶ ሔደ። ከዚያም ለዓለም ለነዲበኩሉ እስኪደውልላቸው ድረስ

ጭንቅላቱን ተመትቶ የሞተውን ሬሳ መኪናቸው ውስጥ ይዘው ፓትርያርኩ ግቢ አቅራቢያ መጠባበቅ ጀመሩ፡፡

ሬሳ ቅይይር ከማድረጋቸው በፊት የፓትርያርኩን መኝታ ቤት የድብቅ ካሜራ ባለበት ለደቂቃዎች እንዲቆም የኮምፒውተር መሐንዲሱ ዋልድባ የአይቲ ክህሎቱን ተጠቀሞ በቁጥጥሩ ሥር አደረገው፡፡ ለዓለም እና ዲበኩሉ ሬሳውን ለፓትርያርኩ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ከትተው አሸጉት፡፡ ከዚያም ፓትርያርኩን በመኪና ጭነው ወደ ሜክሲኮና አሜሪካ ድንበር እብስ አሉ፡፡

## ምዕራፍ ፵፫

የኢጲስ ቆጶሳት ሲመተ በዓል ለሦስት ቀን የሚከበር ቢሆንም መርዶ ከወደ አሜሪካ በሁለተኛው ቀን ተሰማ። ሁለቱ ሲኖዶሶች ተወጋግዘው የተለያዩ ቢሆኑም አንዳቸው የአንዳቸውን መሞት አይፈልጉም። ከሁለቱም ወገን አንድ ቀን ዳግም የመዋሐድ ተስፋና ፍላጎት ያለው ጳጳስና አገልጋይ ትንሽ አይደለም። ስለዚህም በደስታ በዓለ ሲመቱን ለማክበር የሚሆን አልሆነም።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንም በየቀኑ አዲስና አስደንጋጭ ነገር እየሰሙ ነው የሚያድሩት። ማኅበረ ቅዱሳን ታገደ፤ ሲኖዶሱ እገዳው እንዲነሳ ለመንግሥት ደብዳቤ ቢጽፍም መንግሥት ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ተወው፤ አራተኛው ፓትርያርክ አረፉ።

መንግሥትም ከጠበቀው በላይ የከተሞች ውጥረት አስጨንቀውታል። በተለይ ባህርዳር፣ አዲስ አበባ፣ ጎንደር፣ ትግራይ፣ ደሴ፣ ናዝሬትና ደብረ ብርሃን በየትኛውም ሰዓት ያልተጠበቀ የሕዝብ ቁጣ ሊፈነዳ እንደሚችል በየድረ ገጹ ላይ የፖለቲካ ተንታኞች እየተነተኑት ነው።

የፊስአልጎስ አባላትም ሥራ እና ጫና በዝቶባቸዋል። ማኅበረ ቅዱሳን ስለታገደ ትንቅንቁ ይብስ እየከበደባቸው ነው። ስለዚህም ቀኑን ሙሉ ሲሠሩ የዋሉትን ማታ ተሰብስበው ይገመግሙና ለቀጣይ ቀን አቅደው ይለያያሉ።

አበጋዝ የድሮውን ዝነጣና መሽቀርቀር ትቷል። ጸጉሩን እንኳ እያበጠረ አይደለም። እንኳን ለመዘነጥ፤ ማኅበራዊ ጉዳዮችንም ለመከወን ጊዜ ጠፍቷል። የተቀሩት የፊስአልጎስ ሥራ አስፈጻሚ አባላትም ሆኑ ተራ አባላቶቹ የአቅማቸውን ያህል ትግል እያደረጉ ነው። የሥራ አስፈጻሚዎቹ እቅድና ውሳኔ ለሌሎች አባላት ከሰላሳ ደቂቃ በኋላ በኢሜይል እንዲደርሳቸው ይደረጋል።

ከምሽቱ አራት ሰዓት ሆኗል ሁሉም ፊት ላይ መድከም መዛል ይነበባል። ቢሆንም ውይይቱ መጀመር ስላለበት አበጋዝ የመጀመሪያውን ንግግር ጀመረ "ኀበዝ የማኅበረ ቅዱሳን አመራር አባላት እየታሰሩ ነው። ስለዚህ ተጨባጭ ማስረጃ ይዘን ይህን ክስ ልንገለብጥ ይገባል" አለ አበጋዝ።

አደይ ሲከነክናት የነበረውን ነገር ልትተነፍሰው ከአበጋዝ ቀጥሎ መናገር ጀመረች "በተለይ ደግሞ የጳጳሳት ሹመቱ በኦርቶዶክስ አማኙ ዘንድ ደስታን ቢፈጥርም ቀሞስ አወቀ አጥናፉ አቡነ ጎርጎሪዎስ ሣልሳዊ ተብለው መሾማቸው ለማኅበረ ቅዱሳን ከአገዳው፣ እስርና ከእንግልቱ በላይ ትልቅ ሕመም ፈጥሯል። ምክንያቱም አቡነ ጎርጎሪዎስ ካልአይ ማኅበረ ቅዱሳን እንዲመሠረት ትልቅ አስተዋፅኦና ድርሻ አላቸው የሚባሉ የሸዋ አገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ነበሩ።

ታንቱም ሲያስበው የነበረው ነገር ስለሆነ ለአደይ ቀበል አድርጎ "ልክ ነሽ አደይ ማኅበረ ቅዱሳንን የጠነሰሱት አቡነ ጎርጎሪዮስ ካልዕ ስለሆኑ ማኅበሩ ስማቸው እንዲዘከርና በበጎ እንዲነሳ ብዙ ጥሯል፡፡ በዚህ ቂም ያሳደሩ ሰዎች ለተሐድሶው አቀንቃኝ ለሆኑት ሰው የጵጵስና ስሙን የሰጧቸው፡፡"

"አሁን የቤተ ክርስቲያንን ንውጽውጽታና ሕመም የሚያስታግስልን ነገር መፈለግ ይገባናል፡፡ ተሐድሶዎች ኃይልና ጉልበታቸውን አሳይተውናል፡፡ በተቻለን አቅም ይህን ነገር ልንመክት ይገባል፡፡ ስለዚህም ነገ እንዴት እንቀጥል በሚለው ጉዳይ ላይ እናውራ፡፡" አለ አበጋዝ ፈርጠም ብሎ፡፡

ታንቱ ነጭ ሸሚዝ ያደረገ ሲሆን፣ አንገቱ አካባቢ ያሉትን ሸሚዞች ፈትቷቸው የደረቱ ጸጉሮች ይታያሉ፡፡ ታንቱ የጥቁር መልከ መልካም የሚባል ወንድ ነው፡፡ እንደ በቆሎ እሸት የተደረደደሩት ነጭ ጥርሶቹ ምነው ሁሌ በሳቀ የሚያስብሉ ናቸው፡፡ ታንቱ ፈገግ አለና ንግግሩን ጀመረ፡፡

"አሜሪካ ካለው የተሐድሶ ክንፍ አንድ ሰው አግኝተናል፡፡ ፓትርያርኩ ነገ ማታ አዲስ አበባ ይገባሉ፡፡ ስለዚህም ሰጊዜው እኛ ተቀብለን ልናቆያቸው ይገባናል፡፡ ከዚያ መቼና እንዴት ወደ አደባባይ ልናመጣቸው እንደምንችል ጊዜ ወስደን ልናስብበት ይገባል፡፡" አለ ድጋሚ ቀንጆ ጥርሱን እንደ ጠዋት ፀሐይ ብልጭ አድርጎ፡፡

-------//-----

ሰንፔር ሶፋ ላይ ቁጭ ብላ ዩቶጵያ ትምህርት ቤት መግቢያ ላይ ያገኘችውን ነገር እየመረመረች ነው፡፡ ወረቀት ላይ 'ተ'፣'+'፣'-'፣'÷'፣'x'፣ 'X'፣ 'ማር 10÷14+6' እና 'መ፫ ደ፮ ረ፱ ሸ፲' የሚሉትን ቃላት፣ ሆሄና ምልክቶች ጻፈችና ለመፍታት ማሰላሰል ጀመረች፡፡

በመጀመሪያ መፍታት የፈለገችው የሒሳብ ቀመሮችን ነው፡፡ ወደ አዕምሮዋ የመጣው የፌስቡክ ወዳጇ የሆነው ፊስአልጎስ ነው፡፡ ፊስአልጎስ የሰው ስም አይመስላትም፡፡ ፌስቡክ ላይ የሆነ ሰው ስሙን ቀይሮ የሚጠቀምበት እንደሆነ ታውቃለች፡፡ በዚህ ፌስቡክ ላይ ከጾታው ወንድነት ውጪ የባለቤቱን ምንነት የሚገልጽ ምንም ነገር የለም፡፡

ነገር ግን በገጹ ላይ ጥሩ ጥሩ መንፈሳዊ ጽሑፎችና ትምህርቶች ይወጣሉ፡፡ ስለ ቀደሙ የብራና መጻሕፍት ብዙ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ ጽሑፎቹ በማስረጃና በማጣቀሻ የተደገፈ እንዲሁም ውበት ስላለው ሰርክ ትከታተለዋለች፡፡ ያስጨነቃትን የሒሳብ ቀመሮችና ፊደሎች የሆነ ፍንጭ ቢሰጠኝ ብላ ለመጠየቅ የእጅ ስልኳን አወጥታ ኢንተርኔቱን አበራች፡፡



CamScanner

ሰንፔር ፊቷ ላይ ጥቁርቁር ብሎ ስለኳን ውርውር አደረገችው። አንድ ነገር ፈልጋ እምቢ ሲላት እንደዚህ ያስቆጣታል። ኔት ወርኩ አልከፍት ብሎ አበሳጨት። ስልኳን ከወረወረችበት አነሳችና መልሳ ኢንተርኔቱን አበራችው። ኢንተርኔቱ በርቶ ፌስቡኩ አልከፍትላት አለ።

"ኡፍ!" ብላ ስልኳን አጥፍታ መልሳ አበራችውና ድጋሚ ኔትወርኩን አብርታ መሞከር ጀመረች። ፌስቡክ ተከፈተ። ደስ አላት። በፍጥነት ፊስአልጎስ ብላ መፈለጊያው ላይ ጻፈችና ፈልግ የሚለውን ተጭና መጠበቅ ጀመረች። በፊስአልጎስ የሚጠራ አራት ተመሳሳይ የፌስቡክ ገጽ አየች። የእሷ ጓደኛ የሆነውን መረጠችና ወደ መልእክት መጻፊያው ላይ ገባችና መጻፍ ጀመረች።

"ሰላም ፊስአልጎስ እንዴት ነህ? ማን እንደሆንክ አላውቅም። እኔ ያው እንደምታየው ሰንፔር ናፍያድ እባላለሁ። አንድ ነገር እንድትረዳኝ ፈልጌ ነው። ስለ ሒሳብ ቀመር ማለትም መደመር (+)፣ መቀነስ (-)፣ ማካፈል (÷) እና ማባዛት (×) ትርጉማቸውና የምታውቀው አንዳች የተለየ ነገር ቢኖር ብትረዳኝ እባክህ? ሌላው የምጠይቅህ በመደመር (+) እና በ 'ተ' ሆሄ እና በማባዛት (×) እና በ 'X' የእንግሊዘኛ ፊደል መካከል ያለውን ልዩነት ብታስረዳኝ? አመሰግናለሁ። መልሱን በቻልከው ፍጥነት ብትልክልኝ?" ብላ ጻፈችና ስልኳ ላይ 'ላክ' የሚለውን ቃል ነካች።



CamScanner

## ምዕራፍ ፶፬

## አዲስ አበባ ብስራት ገብርኤል

ከስፋቱ የተነሳ መናፈሻ በሚመስለው ጊቢ ውስጥ ቁጭ ብለዋል፡፡ ሰውየው በቁምጣ ነው ያሉት፡፡ እግራቸው እንደ ሸንበቆ የቀጠነች ስትሆን ከወገባቸው በላይ ደግሞ እንደ ባሉን የተነፋፋ ናቸው፡፡ ከሩቅ ላያቸው ሰው የስላቅ ካርቱኒስት ያበጃቸው ባለ ሦስት ማዕዘን ምስል ይመስላሉ፡፡

ዘላለም ገና እንዳያቸው ነበር ሳቅ እፍን ያደረገው፡፡ ነገር ግን ከአፉ እንዳይወጣ ታገለው፡፡ ክብሮምም በውይይቱ ላይ ተገኝቷል፡፡ ዘላለም ክብሮምን ሲያየው አንዳች የሚከብደው ነገር አለ፡፡ እናቱ ከትዝታው ማኅደር እንደ ጥጥ ፍልቅቅ እያለች፤ ያ የመከራ ምሽት ዐይኑ ላይ ድቅን እያለበት ነው፡፡ እናቱን የደፈረው ጠምጣሚ ሰውዬ በዐይኑ ድቅን ይልበታል፡፡ በእርግጥ የዚያ ሰው ፊት ደብዛ ጠፍቶበታል፡፡ ቢሆንም ሰውየው ልዩ ምልክት አለው፡፡

ያንን ምልክት ዘላለም በጭንቅላቱ ላይ አትሞ ይዞታል፡፡ ንቅሳት ነው፡፡ ንቅሳቱ ግን ኢትዮጵያውያን ብዙ ጊዜ ከሚነቀሱት የንቅሳት አይነት በጣም ይለያል፡፡ ቁስም ስለሆነ ይነቀሳል ብሎ የጠበቀው የመስቀል ንቅሳት ስለሆነ ሰውየው ላይ ያየውን የንቅሳት ዓይነት መቼም አይረሳውም፡፡

ሰሞኑን ስለ ክብሮም ለማጣራት ያስብና በተለያየ ምክንያት ሳይሳካለት ቀርቷል፡፡ ዛሬ ከዚህ እንደወጣ እንደሚያጣራ ለራሱ ቃል ገባ፡፡ ነገሮች እንደፈራው ከሆነ በጣም ከባድ ነው፡፡ ብዙ ዓመት ዋጋ የከፈለላቸው ነገሮች ብልሽትሽታቸው ይወጣሉ፡፡

በውስጡ የመሠረተው የጥላቻ አጥር ላይገነባ ይፈርሳል፤ ለሌላ ጥላቻና ቂጭት ራሱን አሳልፎ መስጠቱ አይቀርም፡፡ ይህ ባይሆን ውስጣዊ ምኞቱ ነው፡፡ ምክንያቱም አሁን ያለበትን ጥላቻና በቀል ይወደዋል፡፡ የኑሮ ምቾትና መደላድል ፈጥሮለታል፡፡ ስለ እናትና አባቱ መበቀሉን እንኳ ረስቶታል፤ ወይም እየተበቀለ እንደሆነ ነው የሚሰማው፡፡ የሰው ሕይወት ሲቀጥፍ፤ የብዙዎችን ሕይወት እንዳልነበረ ሲያፈርስ፤ የሰው አይደለም የቤተ ክርስቲያን ሕልውና ከመሰረቱ ሲንድ ሲውተረተር በቀል የሚባል ማስተባበያ ለራሱ ይሰጠዋል፡፡ ተደፍራ ስለሞተቸው እናቱ፤ ርስቱን ተቀምቶ በእሳት ለተጠበሰው አባቱ ነው፡፡

ከዚህ ሃሳብ ያወጣው የሰውየው ጥያቄ ነው "ነገሮች ጥሩ እየሄዱ ይመስላል፡፡ ቢሆንም ሁልጊዜ እንደተጠበቁት ላይጓዙ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ያልተጠበቀና አስቸጋሪ ነገር እንዳይከሰት ሌሎች ጥንቃቄዎች ማድረግ ይገባናል፡፡"



CamScanner

ክብሮም ሰውየውን ተከትሎ መናገር ጀመረ "እኔም የነገሮች አካሔድ በጣም አስፈርተውኛል። ውጥረቱ በጣም ጨምሯል፤ ሰዉ ከመቼውም በላይ እያጉረመረመ ነው። እንኳን እዚህ መሀል ከተማ አይደለም ትግራይ ራሱ ትኩሳቱ በጣም ጨምሯል። 'ዘንድሮ ይህቺን ቤተ ክርስቲያን አንድ ነገር አድርጓትና ይለዩናል፤ ለሰው አጣላችሁን ዝም አልናችሁ ብላችሁ ብላችሁ ከፈጣሪ ታጋጩን' እያሉ ነው።"

ሰውየው ይህን ማስፈራሪያ ቀድመውም ቢሰሙትም ክብሮም በመንቦቅቦቅ ስላወራው ነው መሰል አስደነገጣቸው። ማጣት የማይፈልጉት ደጀን የትግራይን ሕዝብ ነው። ሌላውን ኦርቶዶክስ አሸማቅቃለሁ ሲሉ ሌላ ያልጠበቁት የፖለቲካ ኪሳራ ሊያደርስባቸው ነው። ያውቁታል የትግራይ ሕዝብ ከዘጠና አምስት ፐርሰንት በላይ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ነው። አዕምሯቸው ሲጨናነቅ ተሰማቸው። ስለዚህ ይህን ሀሳብ ለበኋላ ብለው ከአዕምሯቸው ጓዳ ገፍትረው አባረሩት።

ሁሌም ፈሪ፣ ድንጉጥ፣ ውሽልሽል... መባሉን ስለማይፈልጉ፤ እንዲሁም ከእኔ በላይ መሰኛ የለም ብለው ስለሚያስቡ ሰውነታቸውን አፍታቱና "አይዞህ ክብሮም ለእሱም መላ አይጠፋም። አሁን መነጋገር ያለብን በቀጣይ ምን ማድረግ እንዳለብን ነው።"

ዘላለም ቀጣይ ነገር ሲባል ገርሞታል። ሕዝቡ ነገሩን እንዴት ይቀበለዋል የሚለው ነገር ዋና መከራከሪያ ሊሆን ይገባዋል እያለ ማሰብ ጀመረ። ሰውየው ዘላለም ፊት ላይ የግርታ መንፈስ ስላዩ ለማብራራት በድጋሚ መናገር ጀመሩ።

"ማለቴ የማኅበረ ቅዱሳን እግድ እንዲነሳ ሲኖዶሱ ወስኗል። ስለዚህ እግዱን በቶሎ ልናነሳ ይገባል። የጸረ ሽብር ግብረ ኃይሉ ለነክስ ማስረጃ ይፈልጋል። ስለዚህ ብናወራ ማለቴ ነው" አሉና ወሬ እንደጨረሰ ሰው ለሰከንዶች ዝም አሉና መልሰው መናገር ጀመሩ "እኔ ጋር ሀሳብ አለ። እሱም ምንድነው ትንሽ ማስረጃ ያስፈልገናል። ከዚያም የማኅበረ ቅዱሳንን አመራር አባላት እንዳለ አስረን በሌላ መሰል አመራር እንድንተካ ነው የፈለኩት።"

ዘላለም ማስረጃ ስጠኝ እያሉት እንደሆነ ገብቶታል። ችግሩ ምን አይነት ማስረጃ ሊሰጣቸው ይችላል። እነዚህ ሰዎች ከቆዩ፤ የነገሮች ማጣፊያ ካጡ መስዋዕት ሊያደርጉት ይችላሉ። ስለዚህ ስለቀጣይ ነገር ማሰብ ጀመረ። ከዚያ በፊት ግን ሁሌም ሲከነክነው የነበረው ነገር ጠየቀ።

"ፓስተር ናፍያድን ገደልኩት ያለው ሰው ምንም አልተናገረም?"

ሰውየው በጣም የገረማቸውን ነገር ስለጠየቃቸው ደስ አላቸው "እሱ ሰውዬ በጣም ነው የሚገርመው። እሱ ከፈለገው ነገር ውጪ ምንም ሊተነፍስ አልቻለም። ለማሰቃየት ያልተሞከረው ነገር የለም አሉ። ሰውየው ግን ምንም ሊተነፍስ አልቻለም።"

ዘላለም ንግግሩን ሳይጨርስ ስላቋረጡት ገፅም ያሉ ስለመሰለው ንግግሩን መልሶ ቀጠለ "ስለ ሕቡዕ ቡድኑ ምንም ነገር ሊታወቅ አልተቻለም ማለት ነው?" አለ ዘላለም፡፡ ለምን እንደሆነ ባያውቅም ይህን ሕቡዕ ቡድን ፈራው፡፡ ይሕ ሕቡዕ ቡድን ራሱ ማኅበረ ቅዱሳን ለክፉ ቀን ብሎ እቅድ 'ለ' ብሎ ያዘጋጀው ይመስለዋል፡፡ አፈረስነው ሲባል አለመፍረሱ፤ ገደልነው ሲባል ሕያው መንፈሱ የሚያስጨንቅ እየመሰለው ነው፡፡

ዘላለም ስለ መንፈሳዊ ድርጅቶች ብዙ አንብቧል፡፡ ለበጎ ነገር ሲሠሩ በጣም ስኬታማና ኀበዞች ናቸው፡፡ አለአግባብና አለልክ የተገፉ እንደሆነ ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ቁጣና እልሃቸው፤ ኃይልና ጉልበታቸው እነሱን እያድርገኝ ነው፡፡ ሁሉን የሚያደርጉት ስለፈጣሪ ስለሆነ ምንም ቢያደርጉ ቅንጣት ታክል አይሰማቸውም፡፡

እስራኤሎች ሽብርን የመሠረቱት የአይሁድ እምነታቸውን ወደ ፖለቲካዊ አቋም የቀየሩት ዕለት ነው፡፡ ይህን ቁጣና እልሃቸውን ያጠናከረላቸው ደግሞ የናዚ ጭፍጨፋ ነው፡፡ ከናዚ በኋላ አይሁድ የሚባል እምነት ስሙ እንጂ አምልኮው ለዘላለም አይታየውም፡፡



CamScanner

## ምዕራፍ ፶፫

### አዲስ አበባ-ሳሪስ

ሰንፔር መልስ ይሰጠኛል ብላ ስትቁነጠነጥ ነበር። ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ መልሱን ሳይሆን ፊስአልጎስ መልእክቷንም እንዳላየው ፌስቡክ አሳውቋታል። ስለዚህ ቁጭ ከምል ብላ የቀሩትን ምስጢሮች ለመፍታት መሞከር ጀመረች።

ሰምኑን እንደምታደርገው ያልተጻፈበት ነጭ ወረቀት አምጥታ "'መ፫ ደ፮ ረ፬ ሸ፫ እና 'ማር 10÷14+6'" ብላ ጻፈች። ቅድም የመጣላት ሃሳብ ነበር። ፊደሉን ልክ እንደ ሒሳብ ቀመር ማሰብ ፈልጋለች። 'መ፫' የሚለውን ሆሄ ጻፈችና። ማሰብ ጀመረች። "መቼም 'መ' ኪዩብድ ማለት 'መ' ሲባዛ በ 'መ' ማለት አይደለም። እንዲህ ከሆነ ትርጉም አይሰጥም። ስለዚህ ሊሆን የሚችለው። ሦስተኛው 'መ' ነው።" ብላ አሰበችና ምግብ ጠረጴዛው ላይ ያስቀመጠችውን የፊደል ገበታ ለማምጣት ከተቀመጠችበት ሶፋ ተነሳች።

ሰንፔር የፊደሉን ገበታ ከጠረጴዛው ላይ አንስታ መጣችና የፊደል 'መ'ን ቤት ቆጠረችና ሦስተኛው ላይ ደረሰች። 'ሚ' የሚለውን ሆሄ አገኘች። ቀጠለች 'ደ፮' የሚለውን ፊደል አመጣችና የ'ደ'ን ቤት ስድስት ቆጠረችና 'ድ' የሚል ሆሄ አገኘች። ሰንፔር ልቧ እየመታ ነው። ምን የሚል ትርጉም ይሰጠኛል እያለች እየተጨነቀች ነው። 'ረ፬' ወደሚለው ፊደል ሄደችና የረን አራተኛ አነበበች። 'ራ' የሚል ሆሄ ሰጣት። ሰንፔር ይብስ ደነገጠች። በፍጥነት ዐይኗን ወደ ቀጣዩ ላከችው። ትክክል ነች የገመተችው ነው። ቀጣዩ የምታገኘው ቃል 'ሺ' ነው። "ሚድራሺ!" ብላ ሁለቱንም እጆቿን አፏ ላይ ጫነች።

"አባቴ ከዚህ ሆስፒታል ምን ያገናኘዋል? እኔንስ ኢንተርንሺፕ እዚህ ሆስፒታል እንድገባ ያደረገኝ አበጋዝ ከዚህ ሆስፒታል ጋር ከመሥሪያ ቤትነት ባለፈ ምን አገናኛቸው? ምንድነው እየሆነ ያለው? በኢየሱስ ስም!" አለች ከስተር ብላ

-----------//---------

### አዲስ አበባ-ቦሌ

ዘላለም ቫራይቲ ካፌና ሬስቱራንት ውስጥ ቁጭ ብሏል፤ ከፊት ለፊቱ ካለው ባለመስታወት ጠረጴዛ ላይ የመኪና ቁልፉን እና የፀሐይ መነጽሩን አስቀምጦ አስተናጋጁ ከመምጣቱ በፊት የሚያዘውን ምግብ ስም ማሰብ ጀመረ። እዚህ ቤት አንድ የሚወደው ግን ደግሞ ስሙ የማይያዝለት ምግብ አለ። ስለዚህም ምግቡን ስሙን ጠርቶ ከሚያዝ ይልቅ ከምን ከምን እንደሚሠራ ቢናገር ይቀለዋል። ግልጽ

ነው ቲጣ፣ የተጠበሰ ሥጋ፣ ቲማቲም፣ ቱና… እያለ መዘርዝር ይችላል። ስሙ ግን ምንም አይመጣለትም።

አንድ ቀን የምግቡን ስም ሊሸመድደው ሞክሮ ነበር። ከዚያም ሸምድዶት ወጣና ሌላ ቀን ተመልሶ ሊጠራው ቢፈልግ ከየት ያምጣው፤ ከዚያን ቀን በኋላ ተወው። አስተናጋጆቹ ስለሚያውቁት ዘላለም መጥቶ ሲቀመጥ "ይምጣ?" ይሉታል። እሱም ሳቅ ይልና "አዎ" ይላል።

ዘላለም ያዘዘው እስከሚመጠላት ከቦሌ መድኃኒዓለም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ካለው የሬስቶራንቱ በረንዳ ላይ ቁጭ ብሎ ስልኩን መጎርጎር ጀመረ። በስልኩ የክብሮምን የፌስቡክ ከፍቶ የተለያዩ ፎቶዎችን እያየ ነው። ነገር ግን የሚፈልገውን ዓይነት ምስል ሊያገኝ አልቻለም። ዘላለም የሚፈልገው ክብሮም ራቁቱን ሆኖ ቢሆን ጥሩ ቢሆንም፤ ብዙዎቹ ልብስ ተከህኖውን አድርጎ ሲቀድስ፤ መጸር ላይ የተሰካ ትልቅ መስቀል ይዞ፣ በሱፍ ቂቅ ብሎ፣ ልጁን አቅፎ፣ ቂቅ ብሎ ዘንጦ፣ ከጓደኞቹ ጋር አንድ ላይ ሆኖ… ነው።

ዘላለም የሚፈልገውን ፎቶ ስላላገኘ ኢንስታግራም ላይ ካለ ብሎ ወደ ኢስታግራም አድራሻው ሄዶ መፈለግ ጀመረ። የኢንስታግራም ላይ ያለው ምስል ትንሽ ለየት ለየት ያለ ነው። በቅርቡ አሜሪካ ሔዶ የተነሳቸው ፎቶዎች በብዛት ይታያሉ።

ቀጥሎ ዘላለምን የሳበው ፎቶ አየ። ክብሮም ከላይ ራቁቱን ሆኖ ከስር የዋና ፓንት አድርጎ ግዮን የዋና ገንዳ አካባቢ የተነሳውን ፎቶ አየው። ፎቶው ፊት ለፊት ስለሆነ የሚፈልገውን ነገር ሊያገኝ ስላልቻለ ሌላ ፎቶ አወጣ። በትክክል ግራ ክንዱን አየው። ራሱ ነው። ንቅሳቱ በትክክል ራሱ ነው። ዘላለም ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ቆመ። መልሶ ቁጭ አለ።

ዘላለም የፈራው ነገር ደረሰ። አስደንጋጩን ንቅሳት አየው። ባለአምስት ኮከብ ንቅሳት ግራ ክንዱ ላይ እንደተነቀሰ ነው። በትክክል ራሱ ነው። ክብሮም እናቱን የደፈረበት። አባቱን ሸምግሎ ለሞት ያመቻቸው ቂስ። ክብሮም ነበር።

-----//-----

## አዲስ አበባ-ሳሪስ

ሰንፔር ፊስአልጎስ መልስ ሰጥቶኝ ይሆን ብላ ኢንተርኔቱን አብርታ ፌስቡክ ውስጥ ገባች። በትክክልም መልእክት መምጣቱን የሚያሳየው ምልክት ላይ አምስት መልእክት እንዳለ ያመለክታል። ሰፍ ብላ መልእክቱን ከፈት የሚለውን ተጭና ከፈተችው።

ከአምስቱ ውስጥ አንዱ የፊስአልጎስ ሲሆን የተቀሩት ሁለቱ ግን ዋኔ ቀንጆ፣ እንዴት ነሽ ተገናኝተን እናውራ፣ በአባትሽ ሞት በጣም አዝኛለሁ አግኝቼ ባጽናናሽ ደስ ይለኛ፣ ሀይ፣ ስልክሽን ባገኘው ደስ ይለኛል የማወራሽ ነገር ነበረኝ የኔ ስልክ 0923..."

ሰንፔር የፊስአልጎስን መልስ ስታገኘው አፍጥጣ ማንበብ ጀመረች። "ሰላም ሰንፔር። ጥያቄሽን አይቼዋለሁ። ጥያቄሽ ብዙ እና ሰፊ መልስ ቢኖረውም አንቺ ግን መልሱን በፍጥነት እንድመልስልሽ ስለጠየቅሽኝ፣ በአቅራቢያ ካሉ መጽሐፍትና ድረ ገጽ አገላብጬ ያገኘሁት ይህን ይመስላል።

"መጽሐፍ ቅዱስ ላይ 'ከቀስትህ ፊት ያመልጡ ዘንድ ለሚፈሩህ ምልክት ሰጠሃቸው' ይላል። ስለዚህም ምልክት መስጠት የሰው ብቻ አይደለም። እግዚአብሔር ለሚወዱትና ለሚፈሩት ምልክት ይሰጣቸዋል። ወደ አንቺ ጥያቄ ስመጣ፣ አራቱ የሒሳብ መሰረታውያን የሚባሉት መደመር፣ መቀነስ፣ ማካፈልና ማባዛት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሊቃውንት ዘንድ 'አርባዕቱ ትእምርተ ቀመር' ይባላሉ።

"መደመር (+) የአዳም ምልክት አድርገን እንወስደዋለን። አዳም የተፈጠረ እንጂ ያልተወለደ መሆኑ፣ ነገር ግን ከእሱ ሔዋን መፈጠሯ ሁለት ሆኖ እንደ አንድ መፈጠሩን ያሳየናል። መቀነስ (-) ደግሞ ከአንዱ አዳም ጎን ቀንሶ ሔዋንን ስለፈጠራት በመቀነስ ትመሰላለች። መቀነስ ማለት አንድ ከሆነ ነገር ላይ የተቀነሰ ስለሆነ ነው። ከዚያም አዳምና ሔዋን ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሏት ተብለዋል ይህንንም በማባዛት (×) ምልክት ይገለጻል። ማካፈል (÷) የሞት ምልክት ነው። አዳም መሬት ነህ ወደ መሬት ትገባለህ መባሉ እውነት ነው። ሰው ሲሞት ነፍስና ሥጋ ተለያይተው ሁለት ቦታ የሚካፈሉበት ነው። ሥጋ ወደ መሬት፣ ነፍስ ደግሞ ወደ ሰማይ ትሔዳለች።

"ስለ አርባዕቱ ትእምርተ ቀመር ይህን ካልኩ ስለ 'ተ' ምልክት ትንሽ ልበል። 'ተ' በቤተ ክርስቲያን ብዙ ትርጉም አለው። የዓለም ማዕዘናት ምልክት ነው። ሰሜንን፣ ምሥራቅን ደቡብን እና ምዕራብን ያሳያል። ሌላው የክርስትና ምልክትም ሆኖ ይገኛል። በዓለም ላይ ክርስቲያን ነን የሚሉ ብዙ ሰዎች የመስቀል ምልክት ይጠቀማሉ። ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ግን 'ተ' ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደትም በፊት በግዕዙ ፊደላችን ውስጥ ነበር። እንጠቀመውም ነበር።

"በእንግሊዘኛው ኤክስ (X) የሚባለው ፊደል በእኛ 'ትእምርተ ፊቂው' ይባላል። ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት የሚለው ምልክት ነው። በእርግጥ ይህ ምልክት የብዙ ነገሮች መለያ ነው። ለምሳሌ አውሮፓውያን የኔቶ ጦር የቃልኪዳናቸው ምልክት ነው። የአሜሪካ መንግሥት ምልክትም አድርገውታል። ፒራሚድን ብታይው ሶስት ማዕዘን ይመሰል እንጂ ከስር የትእምርተ ፊቂው ምልክት ነው ያለው።

"በአውሮፓውያን ዕይታ ትእምርተ ፈቲው ብዙ ትርጉም አለው። ከጾታ ግንኙነት ጋር እንዳለው በጣም ያስረግጣሉ። ምክንያቱም የወሲብ ፊልሞች በ 'XXX' ምልክት ይገለጻሉ። በሮማውያንም ዘንድ የአስር ቁጥር ማለት ነው። በአውሮፓውያን ዘንድ ትእምርተ ፈቲው የለውጥ ወይም የትራንስፎርሜሽንም ምልክት ነው። ይህ ምልክት የድብቁ ማኅበረሰብ ወይም የኢሉሚናንቲዎች ምልክት ነው። ሌላም ብዙ ትርጉም አለው። ከድረ ገጽ ልታይው ትችያለሽ። ነገር ግን በአውሮፓውያንም ሆነ በእኛ በተለይ የሁለት ነገሮች መገናኘትን በይበልጥም ወሲብን ያመለክታል።

"ሌላው ግን ትምሕርተ ፈቲው ምሥጢራዊ ቦታዎችን ለማመልከት ይጠቀሙበታል። ዋና ከተማቸውን ሲሠሩ ወይም ድንኳኖቻቸውን ሲተክሉ ወይም ሀብት ንብረት፣ የጦር መሣሪያ ሲያስቀምጡ ይህን ምልክት ይጠቀማሉ። የተቀረውን ከድረ ገፅ ተመልከቺው? አመሰግናለሁ።" ይልና የምታነበውን ድረ ገጽ መገኛ አድራሻ አስቀምጦላታል። ሰንፔር በጣም ደስ ስላላት የምስጋና ምልአክት መጻፍ ጀመረች።

## ምዕራፍ ፶፯

ዘላለም ዐይኑ ቀልቶ ድልህ መስሏል፣ ፊቱ ድካምና መሰላቸት ይነበብበታል፡፡ የቀላው ዐይኑ ላይ እንባ አቅርሯል፡፡ ከፊት ለፊቱ ባለው ጠረጴዛ ላይ ብሉ ሌብል የተጋመሰ ውስኪ፣ የውስኪ መጠጫ ብርጭቆ የበረዶ ማስቀመጫ አለ፡፡ ቀዝቃዛውን አምቦ ውኃ በቀዳው ውስኪ ውስጥ ጨመረና በአንድ ትንፋሽ ጨለጠው፡፡

አድሜ ልኩን የቆመለት ዓላማ ስህተት መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ የእናትና አባቱን ገዳዮች አደግድጎ ሲያገለግላቸው፣ እናትና አባቱን እንጂ ሳይሆን በተደጋጋሚ ሲገላቸው ነበር፡፡ ቁጭት ገላ ላይ እንዳረፈ ሳማ ለበለበው፣ ምዝምዝ አደረገው፡፡ ያደረገው ነገር ሁሉ ልክ አፍንጫ ውስጥ እንደ ገባ የቃሪያ ፍሬ ቆጠቆጠው፡፡

ዘላለም አሁንም አሁንም የሚታየው ነጭ ሽማ ያደረገችው፣ ጨረቃ ጠልሰም ከነድሪ አንገቷ ላይ ያሰረችው፣ በአጭሩ ጸጉሯን የተቆረጠችው፣ አገጯ ላይ የመስቀል ንቅሳት ያላት፣ ጥርሷን የተነቀሰችው፣ የዋኂና ሳቂታዋ እናቱ ስትኮላተርበት ይታየዋል፡፡

"ገደልከኝ፣ ከጠላቶቼ ጋር አብረህ ዳግም ገደልከኝ፡፡ አይ ልጅነት¡ ድንቄም ወንድ ልጅ¡ ድንቄም ደም መላሽ¡" ስትለው ይሰማዋል፡፡ አባቱ ጀርባውን ሰጥቶት ስቅስቅ እያለ ሲያለቅስ ይታየዋል፡፡ ሲያባብለው ሲሄድ "ክላልኝ ወዲያ!" እያለ ሲቆጣው ነው ይታየዋል፡፡

የመሐሪ ደገፋውን "የኛ ነው የኛ" የሚለውን ዘፈን እስከ መጨረሻው ድረስ ከፍቶ እየደጋገመ እየሰማ ነው፡፡ ሲፈልግ ከዘፈኑ ጋር አብሮ ይዘፍናል፡፡ የዘፈኑ አንዳንድ ስንኞች ይበልጥ እየነኩት ሲመጡ ከተቀመጠበት ተነሳና እያለቀሰ ከዘፋኙ ጋር አብሮ እየተኮላተፈና እየተንሰዳደፈ ይዘፍን ጀመረ፡፡

"...ጃኖ በል! ጃኖ በል!

አልበለጥም አልበለጥም የካሳ ዘር ነኝ

ያውም ጎንደሬ እጄን ብሞት አልሰጥም

አልገደድም አልገደድም

ርስቱን ጉልቱን ቅዬን

ትቼ ብሞት የትም አልሄድም

ወልቃይት ዋልድባ አንቺን ቢያስረሳኝ

የምዬን ሥጋ እርም ይሁንብኝ

አንቺን ቢያስረሳኝ

ቀኝ እጄ ትርሳኝ..."

ዘላለም ዘፈኑ ንስሐ የሰጠው ይመስል ደርሶ አገር ወዳድ እንደሆነ እየተሰማው ነው:: ዘፈኑን ስለሰማ ብቻ ለእናቱ የተበቀለላት፤ ለአባቱ ርስቱን ያስመለሰለት መሰለው:: ይሁን እንጂ ዘፈኑ የውስጥ ሕመሙን ከማሻር ይልቅ ቁጭቱ ላይ ቤንዚን ጨመረበት::

ዘላለም በቅጽበት ከዘፈኑ ጋር አብሮ መዝፈኑን ትቶ መኝታው ጋር ወዳለው ሳጥን መሔድ ጀመረ:: ሰውነቱ እየተልፈሰፈሰበት ነው:: እግሩ በጥሩ ሁኔታ መሬት መቆንጠጥ ተስኖት፤ ሰውነቱ እንደ ቀድሞው ራሱን በራሱ መሸከም አቅቶት እየተንገዳገደ ነው:: ቢሆንም ወደ መኝታ ክፍሉ ግራ ቀኝ ካለው ግድግዳ እየተላተመም ቢሆን ገባና ሽጉጡን አወጣው:: የፓስተር ናፍያድን ሕይወት የቀጠፈውን ግሎክ 19 የተባለው አውስትራሊያ ሰራሹን ሽጉጥ አነሳ:: ከዚያም እየተኮላተፈ ሽጉጡን መኝታ ቤቱ ባለው ትልቅ መስታወት ፊት ለፊት አናጣጠረና እየተኮለታተፈ "ለ..ክ..ብ..ሮ..ም" አለ::

--------//-------

ሰንፔር ፊስአልጎስ የላከላትን መልእክት እሷ ከምትፈልገው በተለይም ከሚድራሺ ሆስፒታል ጋር አልገናኝ አላት:: ለማንኛውም አሁን የቀራት 'ማር 10÷14+6' የሚለውን መፍታት ነው:: በማኅሊያ መሳሪያ እንደሚያይ ሰው ዐይኗን አጨንቁራ ማሰላሰል ጀመረች:: አጻጻፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ይመስላል::

አንድ ነገር እንደተገለጠላት ሁላ ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ የ1954 ዓ.ም. የአማርኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም አመጣችና ማርቆስ 10÷14 ላይ አወጣችና ጥቅሱን ማንበብ ጀመረች:: "ኢየሱስ ግን አይቶ ተቆጣና፤ ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተው አትከልክሉአቸው፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናትና::"

አባቷ ምን ሊላት ፈልጎ ነው? ግራ ገባት:: አባቷ የሕፃናትን ጥምቀት ይቀበላል:: ሁለቱም ልጆቹ በመካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በልጅነታቸው ነው ያስጠመቃቸው:: በዚህ አቋሙ እንደውም ከብዙ አገልጋዮች ዘንድ ትችት ይደርስበት ነበር::

"ያመነ የተጠመቀ ይድናል ብሎ እያስተማረ መልሶ ደግሞ የሕፃናትን ጥምቀት ይደግፋል" እያሉ ብዙ ትችት ያቀርቡበታል:: ፓስተር ናፍያድ በሃሜት መልክ ያወሩበትን እሱ ግን በአደባባይ መልስ ይሰጥበት ነበር:: በተለይ ማርቆስ ምዕራፍ

አሥር ቁጥር አሥራ አራት ያለውን ጥቅስ ሁሌ ይጠቅሳል፡፡ "ኢየሱስ ሕፃናቱን አስተምሮ ሳይሆን 'መንግሥተ ሰማያት ለእነሱና ለእነሱ መሳዮች ናት' ብሎ እንዲሁ ነው እጁን ጭኖ የባረካቸው" ይላል፡፡

ፓስተር ናፍያድ በዚያ ብቻ አያቆምም "ሕፃናት አይጠመቁ ማለት፣ በሌላ ቋንቋ እግዚአብሔርን አያውቁትም እንደ ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ግን ከማኅፀን ጀምሬ አውቂሀለሁ ይላል፡፡ ሕፃኑም እኛ በማይገባን ግን እግዚአብሔር እና ሕፃኑ በሚያውቁት ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ እግዚአብሔርን ያውቃል፡፡ እንኳን ሕፃናት እንስሳትም፣ እንኳን እንስሳት ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ አፈር አለት ወይም ሌሎች ግኡዝ አካላት እግዚአብሔርን ያውቃሉ፡፡ ለዚያም ነው ኢየሱስ ሲሰቀል ፀሐይ የጨለመችው፣ ጨረቃ ደም የመሰለችው፡፡ መጽሐፍም 'እናንተ ዝም ብትሉ ድንጋይ እንኳ ይመሰክራል' ይላል፡፡

ስለዚህም ሕፃናት አይጠመቁ ማለት ለእግዚአብሔር መንግሥት አይገቡም እንደ ማለት ነው፡፡ መጽሐፍ ደግሞ 'ሰው ከመንፈስና ከውኃ ካልተወለደ በስተቀር መንግሥተ ሰማያት አይወርስም' ይላል፡፡ እኛ ክርስቲያኖች ሰው ብለን የምንቆጥረው በእናቱ ማኅፀን ውስጥ ያለን ሁሉ ይጨምራል፡፡

"ያመነ የተጠመቀ ይድናል' የሚለው ቃል ሁሌ ላይሳካልን ይችላል፡፡ አንዳንዴ እኛ እምነት የምንለውን የሥነ መለኮት እውቀት በቅጡ ሊረዱ የማይችሉ ልጆች ሊኖረን ይችላል፡፡ ለምሳሌ በአእምሮ ዝግመት፣ በተለያየ የማገናዘብ ችግር ምክንያት እኛ በምናስበው መልኩ ለልጆቻችን እምነትን ልናስተምር የማንችልበት ችግር ሊገጥመን ይችላል፡፡ ያኔስ 'ያመነ የተጠመቀ ይድናልን' እንዴት ልናደርገው ነው? ከማስጠመቅ ውጪ?" እያለ ይሟገታል፡፡

ፓስተር ናፍያድ በሕፃናት ጥምቀት ብቻ ሳይሆን በአዋቂዎችም ዳግም ጥምቀት አያምንም፡፡ ለዚህም 'አንዲት ጥምቀት አንዲት ሃይማኖት' የሚለውን ጥቅስ ይጠቅሳል፡፡ "ከኦርቶዶክስ ወይም ከካቶሊክ ሃይማኖት ወደ ፕሮቴስታንት የሚመጡ ሰዎች መጠመቅ የለባቸውም፡፡ ምክንያቱም ጥምቀት አንዴ ስለሆነ ኦርቶዶክስም ሆነ ካቶሊክ ያጠመቋቸው እኛም በምናጠምቃቸው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ነው፡፡ ስለዚህ ዳግም ጥምቀት አይገባም" እያለ ይሟገታል፡፡

ሰንፔር የአባቷ ነገር ስታስበው ግራ እየገባት ነው፡፡ ድሮ ባይታያትም አሁን ግን መለስ ብላ ስታየው አባቷ በጣም አፈንጋጭ ነው፡፡ ከፕሮቴስታንት አስተምህሮ አንዳንዴ ይወጣል፤ ልጁ ኦርቶዶክስ ፍቅረኛ እንዳላት እያወቀ ዝም ብሏታል፤ ከመሞቱ በፊት "ስለ ኦርቶዶክስ ተሐድሶ አያገባንም" እያለ ከማዕረግ ጋር በጣም ተከራክሮ ነበር፡፡ በብዙ ፓስተሮች ዘንድ "ተሐድሶ ለሁሉም ቤተ ክርስቲያን ያስፈልጋል" የሚለው ነገር የታመነ ቢሆንም፤ ፓስተር ናፍያድ ግን "ስለራሳችን



CamScanner

ተሐድሶ ማውራት መተግበር እንችላለን፤ ስለ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ግን አያገባንም። ተሐድሶ የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ሃይማኖትን አድሱ ሳይሆን፤ ራሳችሁ በእምነት ታደሱ ነው የሚለው" እያለ ይከራከራል።

ሰንፔር ቀጣይ ያልፈታችው ጥቅስ አለ። "ማርቆስ ምዕራፍ አስር ቁጥር አሥራ አራት ላይ ስድስት ሲደመር ይላል። ስለዚህ የድምሩ ውጤት ማርቆስ ምዕራፍ አስር ቁጥር ሃያ ይሰጠናል" አለች ። ወደ መጽሐፍ ቅዱሱ ሄዳ ማርቆስ ምዕራፍ አስር ቁጥር ሃያን ማንበብ ጀመረች። "እርሱም መልሶ። መምህር ሆይ ይህን ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሮ ጠብቄያለሁ አለው" ይላል። ሰንፔር ማሰብ ጀመረች "በዚህስ ምን ሊል ነው? ከሚድራሺ ሆስፒታል ጋር ምን ያገናኘዋል?" ብላ ለራሷ አንሾካሾከች።



CamScanner

## ምዕራፍ ፶፯

### አዲስ አበባ-ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ

ሮዳስ አበጋዝን ለለንደን ጉዞው ወደ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ከሸኘው በኋላ ለደቂቃዎች አካባቢውን መቃኘት ጀመረ፡፡ አየር ማረፊውን ላየ ሰው ሁሉም ሰው ከአገር የሚወጣ ነው የሚመስለው፡፡ ግርግሩ፣ ወከባው፣ ከአገር ለመውጣት የጓጓው፣ ለመቀበል የተንሰፈሰፈው፣ መተቃቀፉ፣ መሳቀሱ፣ መሳሳሙ... ማየት አንዳች ውስጥን የሚረብሽ ነገር አለው፡፡

ሮዳስ ተገርሞ ሸኚ ተቀባዩን፣ መጪና ሂያጁን እየማተረ እያለ አበጋዝ ሻንጣውን እየጎተተ በሁለት ሰዎች ታጅቦ ከተርሚናሉ ወጣ፡፡ አበጋዝ በንዴት ፊቱን አኮሳትሮ ሲራመድ ሰዎቹም ከኋላው ጣደፍ ጣደፍ እያሉ ይከተሉታል፡፡

ሮዳስ በድንጋጤ የግንባሩን ቆዳ ወደ ላይ ሸብቦ አፉን በመጠኑ ከፍቶ ግራ በመጋባት ያየዋል፡፡ አበጋዝ ከንዴቱ የተነሳ ጠይም ፊቱ ከስሏል፡፡ አበጋዝን የሚከተሉት ሰዎች ሮዳስ እና አበጋዝ ሲገናኙ ሮዳስን እንደሚያውቁት ሁሉ ራቅ ብለው ቆሙ፡፡

ሮዳስ የአበጋዝን ዐይን ዐይን እያየ "ምንድነው ምን ተፈጠረ?" አለ

"ባክህ መብረር አትችልም ለጥያቄ እንፈልግሀለን" አሉኝ አለ በቁጣ እጁን እያወናጨፈ

"ሪሊ? ለምን? ምንድነው ችግሩ?"

"ምን አውቄ... ለጥያቄ ትፈለጋለህ ብቻ ነው የተባልኩት፡፡ ያው የፈረደበት ማኅበረ ቅዱሳን ይሆናላ..."

"ታዲያ እስከዛሬ ምን ሆነው ነው ዛሬ ምን አባነናቸው?"

"ታውቃቸው የለ ትንሽ አይደሉ ከእንግልቱ በላይ አንተን ማናደዱ ትፍስህት ይሰጣቸዋል፡፡ ሆን ብለው ኮንፈረንሱን እንዳልሳተፍ ብለው ነው ይህን ያደረጉት"

"ሲገርሙ! ትንሽማ ትንሽ ናቸው፣ በቃ አትናደድ ከተናገርካቸው ደግሞ ይብስ ይጎዱሃል"

"ባክህ ተዋቸው ደናቁርት ብቻ" አለ አበጋዝ እጆቹን በብስጭት እያወጨናፈ

"ለማንኛውም ይሔን ሻንጣ ይዘህልኝ ሂድ" አለ አበጋዝ ሻንጣውን ለሮዳስ እያቀበለ፡፡



CamScanner

-------//----

## አዲስ አበባ-ቦሌ

ቦሌ ሌሊቱን ሙሉ ድምቅ ለማለት ብትጥርም ሰው ግን የድምቀቷን ያህል አያጅባትም። ሰው በየመዝናኛ ምሽቱ መሽጎ በመንገዷ ላይ ብዙም አይታይም። የእጁ ሰዓቱን አየው። ከለሊቱ ሰባት ሰዓት ከሠላሳ አምስት ይላል። ከሚሊኒያም አዳራሽ ጀርባ ያሉት ውብ ቤቶች ያሉበት ሰፈር ጸጥ እረጭ ብሏል።

ዘላለም ጥቁሩን የፊት ጭንብል ድንገት ሰው ቢያየው እንኳ ብሎ ጭንቅላቱ ላይ ሰብስቦ እንደ ኮፍያ አድርጎታል። ዘላለም በተርታና በቁንጥ የተሠሩት ቤቶች ውበታቸው ማራኪ እንደሆነ አየ። ቢሆንም አሁን የመጣው ቀን ቀን ከአዲስ አበባ ጥጋጥግ መጥተው የቤቶቹን ማማር አድንቀውና በኖረኝ ብለው ተመኝተው እንደሚመለሱ አንዳንድ የአዲስ አበባ ኗሪዎች ፎቅ ቤት ቅልውጥ አልመጣም።

ቢሆኑም የቤቶቹ ውበት ዝም ብሎ ታይቶ አይታለፍም። "አሁን ቀንጆና እሸት ብቻ ሳይሆን ቀንጆ ቤትም ከርፈፍ ብለው ማየት ግድ እየሆነ ነው።" ነው አለና ፈገግ አለ። ቤቶቹ እንደ ቀድሞው የአዲስ አበባ መንደሮች ዝም ብለው በነሲብ አልቆሙም። በጥሩ መሐንዲስ ጥንቅቅ ተደርገው በመንገዱ ዳር የተሰደሩ ናቸው። ብዙዎቹ ቤቶች መዋኛ ገንዳ ጭምር አላቸው። አብዛኛው የአዲስ አበባ ኗሪ እንደዚህ ዓይነት ሰፈር መኖር ይመኛል እንጂ አይኖርም። እንደውም ቀደምት ኗሪዎች ለመጤ ኗሪዎች እንዲህ ያለ ቁንጠኛ ቤት እየሰሩ እንዲኖሩ ለቀው መሄድ ግዴታቸው እየሆነ ነው።

የፓትርያርኩ ልዩ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የሚኖረው እዚህ ቁንጠኛ ሰፈር ውስጥ ነው። ዘላለም እንደራሱ ቤት በተመሳሳይ ቁልፍ በጥንቃቄ በቀስታ በሩን ከፈቶ በጥንቃቄ ግራ ቀኝ እየተገላመጠ ወደ ግቢው ገባ። የግቢው ማማር ለጉድ ነው። ስፋቱ፣ የመዋኛ ገንዳው፣ የውጪው መብራት፣ የግርግዳው ቀለም... ተዳምረው ለቤቱ አንዳች መስህ ሰጥተውታል።

"ድሃዋ ከሌላት ላይ መቀነቷን እየፈታች ለፈጣሪዋ አስራት በኩራቷን ትለግሳለች፤ እንደ ክብሮም ያሉት ደግሞ 'እድሜና ጤና ለምእመናን ይስጥልኝ' እያሉ በሙዳየ ምጽዋት በኩል ለፈጣሪ የሚመጣውን ገንዘብ፤ ቪ ኤይት ገዝተው፣ የውኃ ገንዳ ያለው ቤተ መንግሥት መሰል ቤት ሠርተው ይንደላቀቁበታል።" አለ ዘላለም በቁጭት።

ዘላለም የአንድ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ቤት ሳይሆን አንድ ካቴድራል ቤተ ክርስቲያን የገባ ነው የመሰለው። ግቢው ጸጥ ረጭ ያለ ሲሆን የቤቶቹ መብራት



CamScanner

ጠፍተዋል፡፡ ዘላለም ወደ ጥበቃው ቤት ሄዶ በተኛበት አንቆ ራሱን እንዲስት አደረገው፡፡

ጥቁሯ ቪ ኤይት መኪና ለአንድ ወንደ ላጤ በምትሆን ቤት ውስጥ ቆማለች፡፡ ከቤቱ በስተግራ በኩል ነጭ ትልቅ አቡጀዴ ጨርቅ ሸፋን ተደርጎላት ደግሞ ሐዩንዳይ ኢላንትራ መኪና ቆማለች፡፡ ግቢው 'ጢር… ጢርር…' የሚለው ትል ድምጽ ይሰማል፡፡ ዘላለም ወደ ትልቁ ቤት የሚወስደውን መንገድ ይዞ በጥንቃቄ መራመድ ጀመረ፡፡

ዘላለም በሮችን በሚከፍትበት ቁልፍ እና ዘዴ በያዘው ብረት በጥንቃቄ የበሩን እጀታ ይዞ የቤቱን በር ከፈተው፡፡ በሩ ሲከፈት ትንሽ ድምጽ አሰማና ብርግድ አለ፡፡ ሳሎኑ ጨላልሟል የውጪው ብርሃን በበሩ መስታወትና መጋረጃ አልፎ ቤቱ ውስጥ በስሱ ፈንጥቆበታል፡፡

-----//----

## እንግሊዝ-ለንደን

'የነገሮችን ምክንያት ለማወቅ' በሚል መፈክር የሚመራው ዌስት ሚኒስተር በተባለው የለንደን እምብርት ላይ የሚገኘው ለንደን ስኩል ኦፍ ኢኮኖሚክስ እ.ኤ.አ በ1896 በፋቢን ማኅበር የሃያ ሺህ ፓውንድ ድጋፍ ነበር ሥራውን የጀመረው፡፡ የእንግሊዛውያንን ሕይወትና ፖለቲካዊ ምልከታ በትምህርት አስደግፎ ከፍ ወዳለ ዕይታ ለማሳደግ ቢመሰረትም፤ አሁን ግን ከ159 የዓለም አገራት ዜጎችን 'ኑና ተማሩ' የሚል መፈክሩን አንግቦ፤ የነገሮችን ምክንያት ለማግኘት የሚመራመሩበት ዩንቨርስቲ ነው፡፡

በአሁኑ ሰዓት ዓለም ላይ ካሉ ምርጥ አስር ዩንቨርስቲዎች ውስጥ አንዱ የሆነው 'ስኩል ኦፍ ኢኮኖሚክስ' በጁሊያ ብላክ ዳይሬክተርነት እየተመራ ከአስር ሺህ በላይ ተማሪዎችን የሚያስተምር ሲሆን ከአምስት ሺህ በላይ የሚሆኑት ተማሪዎች ሁለተኛ ዲግሪና ከዚያ በላይ ተማሪዎች ናቸው፡፡

በዚህ ዩንቨርስቲ ነው ዛሬ ተሐድሶና ተዋሕዶ የሚፋለሙት፡፡ ተሐድሶ ከሃይማኖታዊ ጠቀሜታውና አስፈላጊነቱ ባሻገር ለማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አንድምታውን ለማሳየት ትልቁና እስከ አንድ ሺህ ሰው የሚያስተናግደውና ተሰብሳቢዎች እንዳይደክማቸው፤ እንዳይሰለቹ፤ ከሰለቹም የፈለጉት ምግብና መጠጥ ጠብ እርግፍ የሚሉ አስተናጋጆችን የያዘ ባለሁለት ሬስቶራንት ባለው አዳራሽ ውስጥ የሚተነተነው፡፡



CamScanner

በዚህ አዳራሽ በቅርቡ አቡነ መርቆሬዎስን ተክተው አምስተኛ ፓትርያርክ ሆኖ የተሾመው አቡነ ሰላማ ነው ትንተናውን የሚሰጠው፡፡ ከመርሐዊ ወይም ከአቡነ ሰላማ በመቀጠል ተዋሕዶ ከመንፈሳዊ አንድምታው ባሻገር ለአገር ሁለንተናዊ እድገት ያለውን ጥቅም የሚተነትነው ደግሞ ዶክተር ሰናይ ነው፡፡

በመጀመሪያ ይህን ትንተና ይሰጣል የተባለው ዶክተር አበጋዝ ቢሆንም፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ከአገር እንዳይወጣ ስለተከለከለ በእሱ ምትክ ቦታው ባዶ እንዳይሆን ዶክተር ሰናይ ተተክቷል፡፡ ይህ እንዲሆን ያደረገው አቡነ ሰላማ ነው፡፡ ምክንያቱም ወዳጁ ስለሆነ እንዲሁም ሰናይ ተሐድሶውን ይደግፋል ስለተባለ ብዙም ሳያተጋትግ ተሐድሶን የሃሳብ የበላይነት እንዲያገኝ ነው፡፡

ከዚያም በመቀጠል እዚያው ፒኮክ አዳራሽ በስደት ላይ ያለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ እንደሚያደርግና ኢትዮጵያ ላለው ሲኖዶስም ጥሪ እንደሚያደርግ መርሐ ግብር ተነድፎለታል፡፡ ይህኛው መርሐ ግብር ግን በጥቂት ሰዎች ዘንድ፣ በቢቢሲ ቴሌቪዥን ታላላቅ ባለ ሥልጣናትና ከዕለቱ ሪፖርተሮች በስተቀር ማንም አያውቅም፡፡

## ምዕራፍ ፶፰

ዘላለም ሠራተኛዋን በመኝታ ክፍሏ ውስጥ በገመድ አሥሯታል፡፡ ሁለቱ ልጆቹ መኝታ ክፍል ገብቶ ሲያያቸው ድብን ያለ እንቅልፍ ወስዷቸዋል፡፡ ባሉበት መኝታ ቤቱን ብቻ ቆለፈውና ወደ ባልና ሚስቱ መኝታ ቤት ሄደ፡፡

በሩን ከፍቶ እስኪገባ ድረስ እንቅልፍ ወስዷቸዋል፡፡ ዘላለም ረጋ ብሎ ግሎክ 19 ሽጉጡን በቀኝ እጁ በጥንቃቄ ይዞ በሩን ከፈተና ወደ ውስጥ ገባ፡፡ ባልና ሚስቱ ራሳቸውን የሳቱ ያህል እንቅልፍ ወስዷቸዋል፡፡

ክብሮም የበሩ መከፈት ድምጽ እና ብርሃን ከወደ ውጪ ሲገባ ነቃ አለና እንደ ምንም ብሎ እየተጨናበሰ የራስጌ መብራቱን አበራው፡፡ ዐይኑ በስሱ ከፈት ብሎለት ማየት ሲጀምር አፈ ክፍት ጥቁር ነገር ፊት ለፊቱ ታየው፡፡ በደንብ ዐይኑን ሲገልጥ የድምጽ ማፈኛ ያለው ሽጉጥ ፊት ለፊቱ ተወድሯል፡፡

ክብሮም በድንጋጤ ከተኛበት ተነሳና "ምንድነው? ማነው?" ብሎ ድምጹን ከፍ አድርጎ ባረቀ፡፡ በድምጹ ጩኸት ባለቤቱ ከእንቅልፏ ተነሳች፡፡

"ምንድነው የኔ ጌታ? ምን ሆንክብኝ?" ብላ ከእንቅልፏ ባንና ባሏን ተመለከተችው፡፡ ባሏ በቁምጣና በቲሸርት ከአልጋው ወርዶ ቆሟል፡፡ የክብሮም ባለቤት ባሏን አየችና ቆሞ የሚያየውን ተመለከተች፡፡ አልገባትም፡፡ እጇን ወደ ራስጌዋ ሰዳ ዋናውን መብራት አበራችው፡፡

--------//--------

## እንግሊዝ-ለንደን

ፒኮክ አዳራሽ ጢም ብሎ በሰዎች ተሞልቷል፡፡ ተጋባዥ እንግዶች፣ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ የፓርላማ አባላት... በአዳራሹ ታድመዋል፡፡ አቡነ ሰላማ ከእጁ ላይ መስቀል ባይኖርም በጣም ወፍራም ስለሆነ በትረ ሙሴውን እንደመቋሚያ እየተመረኮዘ እየተጠቀመበት ነው፡፡

አቡነ ሰላማ እንደ ውኃ የጠጣውን 'ዘ ፕሮቴስታንት ኤቲክስ ኤንድ ካፒታሊዝም' የሚለውን የማክስ ዌብርን መጽሐፍ እና የቤንጃሚን ፍራንክሊንን የሕይወት ታሪክ የሚያትተውን መጽሐፍ እያጣቀሰ ሲተነትን ነበር፡፡ ፕሮቴስታንት መሆን ለምጣኔ ሐብት እድገት ያለውን ጠቀሜታ፤ አሜሪካና መላው አውሮፓ ይህን የማክስ ዌበርን ጽንሰ ሐሳብ ተጠቅመው እንዴት የሐብት ማማ ላይ እንደወጡ ተንትኖላቸዋል፡፡ ቀላል የማይባለው ተሰብሳቢው ሁሉ ነበር ያጨበጨበለት፡፡ በተለይ የኦርቶዶክስ ጳጳስ ሆኖ እንዲህ ዓይነት ትንታኔ መስጠቱ ብቻውን አስገርሟቸዋል፡፡



CamScanner

አቡነ ሰላማ ምንም የረካ አይመስልም፡፡ አሁን ደግሞ የተሐድሶው ትሩፋት በዓለም ላይ ምን እንደሚመስል በጥቂቱ መተንተን ጀመረ "…ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ መጀመሪያ ያደረገው እምነትን ለዓለም አውጆ ቤተ ክርስቲያንን ከቤተ መንግሥት አፋትቷታል፡፡ ቤተ ክርስቲያን የቤተ መንግሥት ተላላኪ ሆና ሰማያዊ ሳይሆን ዓለማዊ ልምምድ ለሕዝቡ እያመጣች፤ ሕዝብን ለመንግሥተ ሰማያት ሳይሆን ለምድር ገዢዎች ባሪያ አድርጋ ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያንን ከዚህ ተላላኪነት ነጻ ያወጣት የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ነው፡፡

"ሃይማኖት ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ለራሳቸው ያዘጋጁት መንገድ ሲሆን ክርስትና ግን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰው የመጣበት መንገድ ነው፡፡ ይህን መንገድ ያወቀና የጠነቀቀ፤ ጠንቅቆም የተጠቀመው የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ነው፡፡"

ፒኮክ አዳራሽ ፊት ለፊት መቀመጫው ላይ የአንግሊካን እንዲሁም የካቶሊክ ቀሳውስት ልብሰ ተክህኗቸውን ለብሰው ተቀምጠዋል፡፡ ሌሎች ሁለት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳትም ይታያሉ፡፡ አንደኛው በአቡነ ሰላማ የተተኩት የካሊፎርኒያ አገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቴዎፍሎስ ሲሆኑ ሌላኛው ደግሞ የዋሽንግተን ዲሲ አገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ አቡነ አትናትዮስ ናቸው፡፡ እነዚህ ጳጳሳት የአቡነ ሰላማ ደጋፊና ተሐድሶን አጥብቀው የሚፈልጉ ናቸው፡፡

አቡነ ሰላማ ላፍታ ያህል በፕሮጀክተሩ ብርሃን አማካኝነት የሚታየውን ጽሑፍ ላመል ያህል አየት አደረገና ንግግሩን ቀጠለ "የተሐድሶ ትሩፋት ከእምነት ባሻገር ሳይንስና ቴክኖሎጂ ላይ ነው ብርሃንና መራቀቅን የፈነጠቀበት፡፡ ተሐድሶ መጀመሪያ ጀርመን ላይ ቢታወጅም በይበልጥ ግን ትሩፋቱን ያጣጣመችው እንግሊዝ ነበረች፡፡ ድንቁን ውሳኔ የወሰነው የእንግሊዙ ንጉሥ ጀምስ በስሙ የተሰየመለትን መጽሐፍ ቅዱስ በእንግሊዘኛ እንዲተረጎም ማድረጉ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ኢየሱስና ፀጋው ለሁሉ ሰው በራ፡፡" አቡነ ሰላማ አሁን የሚያወራው ከሰው ይልቅ ፊት ለፊቱ ተኮልኩለው ለሚቀርጹት ካሜራማኖች ይመስል ወደ ካሜራው አፍጥጦ ነው፡፡

"የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ባይኖር ኖሮ አውሮፓ ከጨለማ ዘመን ተላቃ አትወጣም ነበር፡፡ ከፕሮቴስታንት ተሐድሶ በፊት የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ምንም ዓይነት ሳይንሳዊ ምርምር ወደ ውጤትና ተግባር ከመግባቱ በፊት ውግዘት በሚባል አጨናጋፊ ተግሣጽ የምታዳክምና የምታቀጭጭ ነበረች፡፡" ነጭ ጨርቅ ለብሶ በላዩ ላይ ውብና ብዙ አበባ በቁንጥ ተዘጋጅቶ ከተቀመጠበት ጠረጴዛ ላይ ያለውን ውኃ ለመጠጣት በወፍራም ሰውነቱና ላይ የለበሰው የክህነት ቀሚሱ ተጨምሮ ራሱን እየጎተተ የሚሄድ አስመሰለው፡፡ ለማንኛውም ውኃው በብርጭቆ ተቀድቶ የተቀመጠ ስለነበር አንስቶ ተጎነጨለትና ወደ ንግግሩ ቀጠለ፡፡

ቀድም እንዳነሳሁላችሁ ማክስ ዌበር 'በፕሮቴስታንት ኤቲክስ ኤንድ ዘ ስፒሪት ኦፈ ካፒታሊዝም' ላይ እንዳለው ከፕሮቴስታንት ተሐድሶ በኋላ የንግዱን ክፍል በመሪነትና በሀብት ባለቤትነት የተቆጣጠሩት ፕሮቴስታንቶች ብቻ ናቸው። ይህ የሚያሳየን ፕሮቴስታንት ለሁለንተናዊ ዕድገት ያላት ቀናና መልካም ዕይታን ነው። ፕሮቴስታንት ለሥራ ትልቅ ክብር ያላት፤ በስር ለሚገኝ የሀብትም ሆነ ሌላ ከበሬታን የምታደንቅ ነች።

ከዚያ በፊት ያለች ቤተ ክርስቲያን ግን ሰዎችን በየቀኑ በሚከበር በዓል የምታዳክምና የምታሰንፍ፤ ብዙ የሚሠራውና የሚያመርተውን ጉልበትና አዕምሮ ሁሉን ትተህ ካልመነንክ አትጸድቅም እያለች በየጫካውና በየገደላገደሉ የምትልክ ነበረች። 'ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት፤ ጋብቻ ክቡር ነው መኝታውም ንጹህ ነው' የተባለውን ቃል ሽራ በትዳር አብሮ መኖርን፣ መዋለድን አኮስሳ ምናኔን የምታበረታታ፤ ዓለም እንዳትቀጥል ጥያቄ ውስጥ የከተተች፤ የሚሰራ እጅና የሚያስብ ጭንቅላት ዳግም እንዳይፈጠር የገደገደች ነበረች የቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን።

የሰውን ልጅ አዕምሮ ዓለምን በቀና እንዳያይና ዓለምን በተንሸዋረረና በሰባራ የካህናት ሽንቁር ዕይታ በኩል እየተመጠነ እንዲመለከተ ተደርጎ፤ ከመፍጠር ከመመራመር ይልቅ ቁጭ ብሎ ፈጣሪን ማማጸን፤ ምድራዊ ነገር ሁሉ ክፉ ነው ብሎ በማውገዝ ብቻ መንግሥተ ሰማያት ይገባ ይመስል በተሳሳተ መንገድ ሲጓዝ የነበረውን የዓለም መርከብ ወደ ቀናው ጎደና የመራ ነው ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ!" ፒኮክ አዳራሽ በጭብጨባ ተናጋ። ኢትዮጵያውያኑ ጳጳሳትም በአድናቆት መዳፋቸውን አማቱ።

አቡነ ሰላማ የአደራሹ የአድናቆት ጭብጨባ ጋብ ሲል በትረ ሙሴውን ወደ ላይ ከፍ አድርጎ መናገር ጀመረ "ለዚህም ምላሽ ሲሰጥ ማርቲን እንዲህ ብሎ ነበር 'በዚህ ምድር የምንሠራውን ማንኛውም ሥራ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። ሥራችን በቤተ ክርስቲያን ይሁን በቤት፤ በማዕድ ቤት ይሁን በእርሻ ሁላችንም እግዚአብሔርን እያገለገልን ነው።' በቃ ሁላችሁም ምንም ሥሩ ምን፤ የትም ይሁን የት ዋናው መልካምና ፈጣሪን አያስከፋው እንጂ እግዚአብሔርን እያገለገላችሁ ነው።

"ከመጨረሴ በፊት ሕያው የሆነ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ በደቡብ ኮሪያ ላይ ምን እንዳመጣ በማስረጃ አስደግፌን እንይ።" አለና አቡነ ሰላማ በእጁ በያዘው የርቀት መቆጣጠሪያ በመጠቀም ፕሮጀክተሩ ላይ ያለውን ጽሁፍ አጠፋና የዓለም ካርታ እንዲወጣ አደረገ፤ ከዚያም ደቡብ ኮሪያ ያለችበትን አሀጉር እስያን አወጣ፤ ከዚያም ደቡብ ኮሪያን ለብቻዋ አጎላት። ቀጠለና የጽሑፍ ማስረጃዎች መውረድ ጀመሩ።

"ተመልከቱ እ.ኤ.አ ከ1960-1968 ዓ.ም. ውስጥ ደቡብ ኮሪያ በከባድ ድርቅ ተመትታ ሕዝቡ የሚቀምስ የሚልሰው አጥቶ ነበር። ከዚያም ብሶ ደቡብ ኮሪያ በሰሜን ኮሪያ በተወረረች ጊዜ ሐገሬ ኢትዮጵያ ሳይቀር 600 ወታደሮችን የያዘ 'ቃኘው ሻለቃ'

የተባለ ወታደር ልካ ከባርነት አድናቸዋለች፡፡ እ.ኤ.አ እስከ 1900 ዓ.ም. ድረስ ደቡብ ኮሪያ ውስጥ ወንጌል ሊሰበክ ቀርቶ በልብ ማሰብ ራሱ ከባድ ነበር፡፡ ከዚያ ይልቅ የተለያዩ የምድር ልምምዶች፣ ቡድሒዝም፣ የእርኩስ መንፈስ አምልኮ የበዛባትና የተጠናወታት ነበረች፡፡

"ከመቶ ዓመት በኋላ ግን በዋና ከተማዋ ሴኦል ብቻ ከሰባት ሺህ በላይ ቤተ ክርስቲያን ሲኖር እያንዳንዳቸው ከ10,000 በላይ አባላት ያላቸው ናቸው፡፡ ኢግ ጂን ኪም በደቡብ ኮሪያ ያለውን የወንጌላውያን ዕድገት ሲያስቀምጡ እንዲህ ብለዋል፡፡ 'ባለፉት መቶ ዓመታት የክርስትና ዕድሜ 40% ከአገሩ ሕዝብ የወንጌል አማኝ ሲሆን፣ 170 ወንጌላውያን ቤተ እምነቶች፣ 47,810 አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት፣ 430 አገር በቀል ክርስቲያናዊ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ 210 ባሕር ዘለል ሚስዮናውያንን የሚልኩ መንፈሳዊ ድርጅቶች፣ 180 የነገረ መለኮት ሴሚናሪዎች፣ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች፣ 521 ትልልቅና ብሔራዊ ልዩ የጸሎት ማዕከላት፣ 15,000 ባህር ዘለል ሚስዮናውያን ወደ 170 የዓለም አገራት የተላኩ ሲሆን፣ በዚሁ ተግባሯ ከአሜሪካ ቀጥላ ሁለተኛ ደቡብ ኮሪያ ስትሆን በቅርቡ ከአሜሪካ ቀዳሚነቷን እንደምትረከብ ተስፋ አለን' ብለው ጽፈዋል፡፡

"ከዚሁ ጋር ተያይዞ የደቡብ ኮሪያን ኢኮኖሚና ፖለቲካ ብናይ አስደናቂ እና ተአምራዊ ነው፡፡ እ.ኤ.አ ከ1962 ዓ.ም. ወዲህ የደቡብ ኮሪያ ዕድገት በአማካይ አርባ ሺህ እጅ እንዳደገ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህንን አስደናቂና ተዓምራዊ እድገት ያዩት ሮበርት ባሮ እና ራሔል ማክሊሪ የተባሉ እውቅ የሐርቫርድ ምሁራን 'ክርስትና በደቡብ ኮሪያ የኢኮኖሚ ዕድገት ቀዳሚ ሚና ተጫውቷል' በማለት አድንቀዋል፡፡

"በአሁን ሰዓት ደቡብ ኮሪያ በኢኮኖሚ ደረጃዋ ከእስያ አገራት በአራተኛ ደረጃ ስትገኝ፣ በዓለም ደግሞ አስራ አንደኛ ደረጃን ትይዛለች፡፡ እ.ኤ.አ በ2014 ዓ.ም. ደቡብ ኮሪያ ከዓለም ሰባተኛ አገር ላኪና አስመጪ ነች፡፡ በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ከዓለም አንደኛ እድገት ያሳየች አገር ነች፡፡"

አቡነ ሰላማ ለራሱ ራሱ የደቡብ ኮሪያ ነገር በጣም የመሰጠው ይመስላል "ተመልከቱ እንግዲህ ይሄነው የሚባል የተፈጥሮ ፀጋ ማለትም ነዳጅ ወይም የሚገደብ ውኃ ወይም የከበሩ ማዕድናት የላትም እንደውም በተቃራኒው ትንሽ የቆዳ ስፋትና ብዙ የሕዝብ ቁጥር ነው ያላት፡፡ ይሁን እንጂ በአስገራሚ ሁኔታ ኢኮኖሚዋ እየተወነጨፈ ነው፡፡ ፖለቲካውም ቢሆን የተረጋጋና ዲሞክራሲያዊ ነው፡፡ የምጣኔ ሀብት እድገቱም የመጣው ከተረጋጋው ፖለቲካ፣ ከበሰለና ከነጠረው ፖሊሲዋ ነው፡፡

"እንግዲህ እኛ ኢትዮጵያውያን እጇን ይዘን ነፃ ያወጣናት አገር ከኋላችን ተነስታ በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው እና በመንፈሳዊው ሕይወታቸው ከተተከለች፣ ኢትዮጵያ ይህን የተሐድሶ እንቅስቃሴ ተቀብላ ብትተገብረው ምን ሊፈጠር ይችላል ብላችሁ

ታስባላችሁ? የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ተሐድሶ ብናዘገየው እንጂ ልናስቀረው የማንችለው ነገር ስለሆነ ይልቁንስ ያለ አደጋና ግጭት በሰላም ታድሰን ሕዳሴያችንን ብናፋጥን እላለሁ።

"በእኔ በኩል የስደተኛውና የሕጋዊው ሲኖዶስ ፓትርያርክ እንደ መሆኔ መጠን ቤተ ክርስቲያናችን አስፈላጊ ነው የምትለውን ለውጥ በመጽሐፍ ቅዱስና በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ተንተርሳ ሰዋዊና ምድራዊ አሠራርን አጥርታ ለኅብረተሰባችን ሁሉን አቀፍ ሕዳሴ እንዲመጣ በጸሎት፣ በሥራ እና በእምነት ብቻ እውን እናደርገዋለን።" ይህ ቃል ከአቡነ ሰላማ እንደወጣ የመጀመሪያውን ጭብጨባ ያሰሙት አቡነ ቴዎፍሎስ ናቸው። እሳቸውን ተከትሎ ሌላውም ሰው ማጨብጨብ ጀመረ። አቡነ ሰላማ በኋላ ላይ ጋዜጣዊ መግለጫ መስጠቱ አይቀርም ግን በዚህ ሞቅታ ላይ ሰዉን ትንሽ ለማለማመድና ቢቢሲም ለአሁን የሚሆነውን ዜና እንዲያገኝ ብሎ ነው።

## ምዕራፍ ፺፬

ዘላለም ጥቁሩን የፊት ጭንብል እንደለበሰ ነው፡፡ ክብሮምና ሚስቱን ወንበር ላይ በወፍራም ፕላስተር አስሯቸዋል፡፡ ክብሮም በቁምጣና በነጭ ቲሸርት ሲሆን ሚስቱ አልማዝ ነጭ ቢጃማዋን እንደለበሰች ነው፡፡ ፊቷ ክብ ሆኖ፤ ዐይኗ ጎላ ጎላ ያለ ሲሆን አፍንጫዋ ጎራዳ ነው፡፡ አልማዝ ድንግጣ ፊቷ አመድ እንደተነሰነሰበት ቡን ብሏል፡፡

ዘላለም ፊቱን ሳያየውና ሳያውቀው ክብሮምን ሊገድለው አልፈለገም፡፡ ቀስ ብሎ ጭንብሉን አወለቀና ፊቱን ገለጠ፡፡ ግንባሩ በጣም አኮሳትሮ የመረረ ጥላቻና የገረረ ቁጣው ፊቱ ላይ ይነበባል፡፡ ባለ መደገፊያው የእንጨት ወንበር ላይ የጀርባ መደገፊያውን አዙሮ ለደረቱ መደገፊያ አድርጎ ሽጉጡን እየወዘወዘ እያወራ ነው፡፡ ክብሮም ድንጋጤው ከሚቆጣጠረው በላይ ሆኖበታል፡፡ ዘላለም ይሆን እንዴ እያለ በድምጽ ሲጠራጠረው የነበረው ነገር እውን ሆነ፡፡ ዐይኑን ሁለት ጊዜ ጭፍን ክፍት እያደረገ ተመለከተው፡፡ ዘላለም ነው፡፡

"...እንደነገርኩሽ ባልሽ ሰው ገዳይ ብቻ ሳይሆን አባቴንና ርስቱን የወሰደ፤ እናቴን እፊቴ ደፍሮ ያለ እናት ያስቀረ ነው፡፡ ታውቂያለሽ?" ዘላለም ራሱን መቆጣጠር ያቃተው ይመስላል፡፡ "... ስገድለው ለእሱ ትልቅ ውለታ እንደዋልኩለት ነው የምቆጥረው፡፡ ችግሩ የእሱ ደም ሲፈስ እኔ ደስታዬ ጣራ አይነካልኝም፡፡ አንቺን ዐይኑ እያየ እደፍርሽ ነበር፡፡ ግን ምንም እንደማይመስለው አውቃለሁ፡፡ ባልሽ እንዲህ ያለ ነገር ሲያደርገው ስለከረመ እንደውም ደስ ነው የሚለው፡፡ ስለዚህ አላደርገውም፡፡" አልማዝ ሰውነቷ ሽምቅቅ፣ ኩምትርትር አለ፡፡ ቀይ ፊቷ ይብሱኑ ቀላ፡፡

ዘላለም ከተቀመጠበት ወንበር ተነሳና ሽጉጡን ወደ ፊት ቀስሮ ክብሮም ግንባር ላይ አነጣጠረና "እሺ ከአንተ ጋር የነበረው ሰው ማን ነበር እሱን ንገረኝ እስኪ?" ክብሮም አፉ በፕላስተር ስለ ተሸበበ ፊቱን እና አንገቱን እየነቀነቀ እየተማጸነ ነው፡፡

"ምን ልትነግረኝ ነው ልፍታህ?" አለ ዘላለም እንደ ማሾፍ እያለ፡፡ ክብሮም በእምንታ አንገቱን ነቀነቀ፡፡ ዘላለም ክብሮም አፍ ላይ የለጠፈውን ጥቁር ፕላስተር እንዲያመው አድርጎ በፍጥነት ላጠው፡፡ ፕላስተሩ ሲነሳ የክብሮ ጺም ስለነቀለው ክብሮም ሕመሙ በጣም ተሰማው፡፡

ክብሮም ልክ አፉ እንደ ተፈታለት "እባክህ ማረኝ? የፈለግከውን ልክፈልህ? እባክህ ማረኝ? እባክህ?" እያለ በመላ ሰውነቱ መማጸን ጀመረ፡፡ ዘላለም በንቀት ዐይን ክብሮምን እየው፡፡ መልሶ ፕላስተሩን ከንፈሩ ላይ አደረገና ጉልበቱ ላይ አነጣጠረ፡፡ ክብሮም ሰውነቱ ይንቀጠቀጥ ጀመረ፡፡

ዘላለም ግን ማፈኛ በተገጠመለት ሽጉጡ ጉልበቱ ላይ ተኮሰበት፡፡ ክብሮም ለደቂቃዎች ያህል ራሱን እንደመሳት አደረገ፡፡ አልማዝ እያለቀሰች ነው፡፡ ክብሮም ሲተኮስበት



CamScanner

ዐይኗን ጨፍና ለሰከንዶች ቆየችና መልሳ ገለጠችው። የባለቤቷ ቀኝ እግር ደም በደም ሆነ።

"አንተ ትቀልዳለህ፤ አንተም ልመናን ታውቃለህ? አንተም?" ዘላለም በቁጣ ነድዷል። ዘላለም ወደ ክብሮም ባለቤት ተመለከተ። እምባዋ ዝም ብሎ ይፈስሳል። እንዳትናገር አፏ ተሸብቧል። ፊቷ ላይ ያረበበው ሐዘንና ስቃይን ማየት ይከብዳል።

"በመጀመሪያ ምህረትን ታውቀዋለህ? አታፍርም ስታስጠላ የሚያመኝ ካንተ ጋርና ላንተ ዓላማ መሳካት መሥራቴ ነው። ታውቃለህ በምን እንዳወቅኩህ?" አለና ወደ ክብሮም ግራ ክንድ ሄደና የኮከብ ንቅሳቱን በግሉክ ሽጉጡ እየነካው "በዚህ ነው" አለው። ከዚያም ሽጉጡን ግራ ክንዱ ላይ አድርጎ ተኮሰበት። ክብሮም ራሱን ሳተ። ሰውነቱ በላብ ተጠመቀ። ዘላለም ጨርሶ ክብሮምን ሊገለው ስለፈለገ፤ ጭንቅላቱ ላይ አነጣጠረና ሁለቴ አከታትሎ ተኮሰ። አልማዝ ራሷን ስታ ከነ ወንበሯ ወደ ግራዋ ወደቀች።

-------//------

ሰንፔር ነጭ ጋውን ለብሳ የጋምኗ ደረት ላይ ዶክተር ሰንፔር ናፍያ የሚል ባጅ አድርጋለች። ከስር የናይክ ምርት ስኒከር ጫማ የተጫማች ሲሆን፤ ቱርክ ሠራሽ ካኪ ሱሪ በጥቁር ሸሚዝ አድርጋለች። ጸጉሯን 'ፐብሊስ' የተባለውን ተኩስ ተተኩሳለች።

ሚድራሺ ሆስፒታል ግቢ ውስጥ ሰዎች ከወዲያ ወዲህ ውር ውር ይላሉ። ሰንፔር ከሕፃናት አስተኝቶ ማከሚያ የሐኪሞች ቢሮ ሆና ወደ ውጪ እየተመለከተች ነው። ፀሐይዋ እያዘቀዘቀች ነው። ከተረኛ ሐኪሞችና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በስተቀር ሌሎች ሰራተኞች እየወጡ ነው።ቀኑን ሙሉ የዋለችው የሕፃናት አስተኝቶ ማከሚያ ክፍል ነው። ዛሬ አዳር ተረኛ ባትሆንም 'አድሬ መስራት እፈልጋለሁ' ብላ ከጓደኞቿ አስፈቅዳ ልደር ብላቸዋለች። ሰንፔር ሚድራሺ ሆስፒታል የልምምድ ጊዜ ጨርሳለች። ልትመረቅ የቀራት ሁለት ወር ነው። አሁን እስክትመረቅ ድረስ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ነው እየሠራች ያለችው።

ሚድራሺ ሆስፒታል እንደፈለገች መጥታ ልምምድ እንድታደርግ አበጋዝ ስላመቻቸላት ብዙም ሳትጨናነቅ አድራም ሆነ ውላ መሥራት ትችላለች። በሥራና በእውቀቷም ጎበዝ፣ ተግባቢና ረጋ ያለች ስለሆነች ብዙዎች ሠራተኞች ሁሌም ብታድር ደስተኛ ናቸው እንጂ አይከፋቸውም።

ሰንፔር ሐኪሞች ቢሮ ውስጥ ብቻዋን ከተቀመጠችበት ክፍል ተነሳችና ቦርሳዋን ካስቀመጠችበት መስኮት አካባቢ ሄዳ ጽፋ ያዘጋጀችውን ወረቀት ከቦርሳዋ ስባ እያወጣች 'ነገሩ ያለው ሕፃናት ክፍል ነው' አለች ለራሷ።

## ምዕራፍ ፳

## እንግሊዝ-ለንደን

አቡነ ሰላማ በጣም በሰው ተከብቦ ስለነበር ወደ ፒኮክ አዳራሽ ሲገባ ዶክተር ሰናይ እንዴት ሆኖ እንደመጣ ልብ አላለውም ነበር። እድሉ ተሰጥቶት ወደ መድረክ ሲመጣ ግን ደነገጠ። አለባበሱ ነጭ በነጭ ሲሆን በላዩ ላይ አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለም ያለው ጥለት ትከሻው ላይ ጣል አድርጓል። ሰናይ ቁመናው ረዥም ስለሆነ ልብሱ ከሰውነቱ ጋር ተስማምቷል።

ዶክተር ሰናይ የአይታ መነጽሩን ስልካካ አፍንጫው መሀከል ላይ አድርጎ በመነጽሩ መስታወት ጽሑፉን፣ ከመነጽሩ በስተላይ ዐይኑን ቀና አድርጎ ደግሞ በአዳራሹ የታደመውን ሰው ይግትራል። በአቡጀዲው ላይ የሚታየው ጽሑፍ በነጭ መደብ ላይ በቀይ ቀለም የተጻፈ ነው። 'ለኢትዮጵያ ተዋሕዶ ወይስ ተሐድሶ?' ይላል። ሰናይ ፊቱን ወደ ሕዝቡ መለስ አደረገና ገለጻውን ጀመረ።

"ወደ ተዋሕዶ ከመሄዴ በፊት ስለ ተሐድሶ መነሻና መድረሻ በጥቂቱ ብል ደስ ይለኛል።" አለና ጉሮሮውን እንደ መጠራረግ ብሎ ወደ ንግግሩ ገባ "ተሐድሶ ወደ ኋላ መለስ ብለን ስናየው መሠረቱ አውግስጢኖስ ነው። አውግስጢኖስ ሃያ ሁለት ጥራዞች ያሉት 'የእግዚአብሔር ከተማ' የተባለ መጽሐፍ ጻፈ።

"አውግስጢኖስን ይህን መጽሐፍ እንዲጽፍ ያደረገው ገፊ ምክንያት ሮም እየወደቀች ስለመጣች 'የሮም መውደቅ ዋናው ምክንያት እናንተ ክርስቲያኖች በአዲሱ ሃይማኖታችሁ ምክንያት አማልክትን ስላስቆጣችሁ ነው' እያሉ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ይከስሷቸው ነበር። ለዚያም ክስ መልስ ይሆን ዘንድ በሃያ ሁለት ጥራዞች የተቀነበበ 'የእግዚአብሔር ከተማ' የሚል ርዕስ ያለው መጽሐፍ ጻፈ።

"አውግስጢኖስ በመጽሐፉ ውስጥ 'የዓለም እና የእግዚአብሔር ከተማ' የሚባሉ ሁለት ከተሞች እንዳሉና 'ሰዎች ሁሉ በእነዚህ ሁለት ከተሞች ውስጥ አንዱን መርጦ የመኖር መብት እንዳለው ነገር ግን ሁለቱንም ማግኘት እንደማይቻል' ገልጿል። የሮም መንግሥትም አሁንም በእግዚአብሔር ቦታ እንዳላት አስረግጦ ለከሳሾቹ ተናግሯል።

"በአውግስጢኖስ እምነት ምድራዊቷ ከተማ የሰዎችን ሥጋዊ ወይም ዓለማዊ ሕይወት የሚመሩና የሚያስተዳድሩ ማናቸውንም የምድር መንግሥታት የምትወክል ስትሆን ሰማያዊቷ ደግሞ የማትታይና ከሞት በኋላ ብቻ የምትወረስ የሰማይ መላእክት የሚኖሩባት መንፈሳዊት ከተማ ናት። በአውግስጢኖስ አስተሳሰብ 'የሰው ልጅ አካል በእግዚአብሔር ቢፈጠርም ምድራዊ አካሉ የመለኮት ባሕሪ የለውም' ብሎ ያምን ነበር።

"አውግስጢኖስ 'አርአያ እግዚአብሔር አዳም በበደለ ጊዜ ጨርሶ ጠፍቷል' ብሎም ያምን ነበር። ስለዚህም አውግስጢኖስ ሙሉ በሙሉ በባህሪ ጉስቁልና ስለሚያምን የእግዚአብሔር ከተማ ተወካይ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን እንኳ ከሙስና፣ ከጉስቁልና፣ ከተንኮል ከክፋት… ልትጠራ እንደማትችል አስረግጦ ጽፏል።

"የአውግስጢኖስ ትምህርት ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አማኞችም በአጠቃላይ ምንታዌነትን ወይም ሁለትዮሽን እንዲቀበሉ አደረገ። ይህ ምንታዌ አስተሳሰብ በጥንት ሮማውያን ዘንድ የኖረ እምነት ነበር። 'መለኮታዊው እና ዘለዓለማዊው ኩነት (metaphysical) ከሰብአዊውና ምድራዊው ዓለም (physical) ፈጽሞ የተለየና በባህሪውም አብሮ የማይሄድ ነው' ብለው ያምኑ ነበር። ያንኑ የተለመደውን አስተሳሰብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አድርጎ አውግስጢኖስ አመጣው። ከዚያም በአጭር ጊዜ ተቀባይነቱን ከአውግስጢኖስ የበሰለ እውቀት እንዲሁም ፍልስፍና እና ማራኪ የክርክር ዘዬ ተጠቅሞ በኅብረተሰቡ ሥነ ልቦና ውስጥ ሀሳቡ ትልቅ ቦታ ያዘ።

"ከዚያ በኋላ የምዕራቡ ክርስትና ሁለትዮሽ እየሆነ መጣ። አንዱን መፈለግ ሌላውን መተው፤ አንዱን መውደድ ሌላውን መጥላት ሆነ። ይህም የካቶሊኩን ዓለም ክርስትና በተቃርኖና በጥላቻ የተሞላ አደረገው። ሕይወት የምርጫ ሆነ። ሴትና ወንድ ተደጋጋፊ ሳይሆን ተቃራኒ እንደሆኑ ማመን፤ ምድራዊ ኑሮን እንደ ርኩስ መቁጠር፤ ቀጥታና ቀላል ሀሳብ ከማምጣት ይልቅ ማወሳሰብ ተአምር መሥራት እንደ ትልቅ ነገር መቁጠር፤ ከተማ መኖር ከገጠር ይበልጣል በሎ ማሰብ፤ ሰው በተፈጥሮው መልካም ነው ብሎ ከማሰብ ይልቅ መጥፎ ነው ብሎ ማሰብ፤ የመንግሥት ሥራና የሕዝብ ፍላጎት የተለያዩ ናቸው ብሎ ማመን… የመሳሰሉት ነገሮች ሁለትዮሽ እያደረገ ወደ ምርጫ ሕይወት ገፋቸው። ይህ የምንታዌነት አስተሳሰብ አውሮፓን የጨለማው ዘመን ወደ ተባለው የጦርነት፣ የድንቁርና እና የድኅነት ቀውስ ገፋቸው።

"ስለዚህ አውሮፓ ከዚህ የምንታዌነት አስተሳሰብ ትወጣ ዘንድ ተሐድሶ ግድና አስፈላጊ ነበር። በተለይ የአውግስጢኖስ 'ጥንተ አብሶ' እና 'የቅድመ ምርጫ' አስተምህሮን ለፕሮቴስታንት እምነት መስራቹ ማርቲን ሉተር ትልቅ ተግዳሮትና ጭንቀት ፈጥሮበታል። በጊዜው ማርቲን ሉተር እንደ ካቶሊክ መነኩሴነቱ የአውግስጢኖስን ትምህርት ያነብ ነበር።

"በተለይ 'የሰው ልጅ ሁሉ ከአዳም በወረሰው የኃጢያት ዝንባሌ (ጥንተ አብሶ) ምክንያት ለዘላለማዊ ሕይወት የበቃ ሊሆን አይችልም። ስለዚህም ሁሉም ሰው ከኃጢያተኛነቱ የተነሳ ቅጣት ይገባዋል። ሆኖም እግዚአብሔር በማይመረመር ባህሪው የተወሰኑትን መርጧቸዋል። ስለዚህ የዘላለም ሕይወት የሚያገኙት እነዚህ አስቀድሞ በእግዚአብሔር የተመረጡ ናቸው' የሚለው የአውግስጢኖስ አስተምህሮ ማርቲን ሉተርን በእግዚአብሔር ምርጫ ውስጥ እገኝ ወይስ እቀር ወደሚል ጭንቀት



CamScanner

ገፋው፡፡ ስለዚህም ከዚህ ጭንቀቱ ለመውጣት 'መዳን በጸጋ ብቻ' (Sola Grafia) ብሎ ተነሳ፡፡

"ይሁን እንጂ ተሐድሶውን ደግፈው ነገር ግን የማርቲን ሉተርን የመዳን ጽንሰ ሐሳብ ነቅፈው የሚከራከሩ ሌሎች ብዙ ሰዎች ተነሱ፡፡ በተለይ በወቅቱ የካቶሊክ መነኩሴ የነበረው ዴዚዴሪየስ ኤራስመስ የሚጠቀስ ነው፡፡ ኤራስመስ 'የሰው ልጅ በተፈጥሮው መልካም እንደሆነና ይህ መልካምነት በትምህርትና በግብረ ገብነት ቢታገዝ እንዲሁም ሃይማኖታዊ ትምህርት ራሱ የሰው ልጅን አስኳል አድርጎ ሊያስተምር ይገባል' ሲል ማርቲን ሉተር በተቃራኒው ከአውግስጢኖስ የወሰደውን ትምህርት በማንጸባረቅ 'የሰው ልጅ ከአዳም በተላለፈበት የውርስ ኃጢአት ምክንያት በውስጡ ክፉ እንደሆነና በሥራው ሳይሆን በፀጋ ብቻ የሚድን ሲሆን፤ ሃይማኖታዊው ትምህርትም የሰው ልጅ ላይ ሳይሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ማተኮር' እንዳለበት አወጀ፡፡ ይህም የሁለት ሀሳቦች በተሐድሶ ጊዜም እንዳይቋረጥ በር ከፈተ ብቻ ሳይሆን አባሰው፡፡ ኤራስመስም ሆነ ማርቲን ሉተር 'አውግስጢኖስ ስለ ሰው ልጅ ተፈጥሮ ያለው አስተሳሰብ መጠነኛ ስህተት አለው' ከማለት ውጪ ከአውግስጢኖስ መሰረታዊ ከሚባለው ጽንሰ ሀሳብ ፈቀቅ ማለት አልቻሉም፡፡

"ስለዚህ ተሐድሶ በምንታዌነት የተጠቃ ሃሳብ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ይህም በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው እና በማኅበራዊው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በእምነቱ ውስጥ ራሱ የቅዱሳንን፣ የጻድቃንና የማርያምን በእምነት ውስጥ ቦታ እስከ ማሳጣት ደረሰ፡፡ ተሐድሶ ምንታዌነት ገፍቶ ያነፀው፤ ምንታዌነት የነገሠበት ጽንሰ ሐሳብ ነው፡፡ ስለዚህ ድንግል ማርያም ማለት ኢየሱስን እንደ ማስረሳት መቁጠር፤ መላእክት ቅዱሳንን እንደ ተራዳኢ መቁጠር ኢየሱስ ክርስቶስ አይረዳኝም ብሎ እንደ ማመን ማሰብ፤ ጻድቃን ቅዱሳን ያማልዳሉ ሲባል የኢየሱስ ክርስቶስ የፈሰሰው ደምና እርባ የከፈለውን ቤዛነት እንደማራከስ መቁጠር... ሆነ፡፡

"ስለዚህም ጻድቃን፣ ቅዱሳን፣ መላእክት እና ድንግል ማርያም ከቤተ ክርስቲያን ተገፍትረው እንዲወጡ ተደርጎ በኢየሱስ ብቻ በሚል ተተካ፡፡ መገፋት ብቻ ሳይሆን ምርጫ ውስጥ የገቡት ተሐድሶዎች ኢየሱስን መረጡ ማለት ነው፡፡ ኢየሱስን መምረጣቸው ትክክል ነው፡፡ እንደ እኔ እምንት ግን ሁሉም የሚመራረጡ ወይም የሚወዳደሩ ሳይሆን እንደ ደረጃቸው የሚቀመጡ ነበሩ፡፡" አለና ሰናይ የፒራምድ ቅርጽ ያለው ግራፍ ኮምፒወተሩ ላይ አወጣ፡፡

ግራፉ የፒራምድ ቅርጽ ያለው ሲሆን ሰማያዊ መደብ ላይ በቀይ የተሠራ ግራፍ ነው፡፡ ሰናይ ስለ ግራፉ ማስረዳት ጀመረ "እንደምትመለከቱት ግራፉ ላይ ከስር ብዙ ሰው ይታያል፤ ክርስቲያኑን በአጠቃላይ ለማመልከት ነው፡፡ በመቀጠል ጻድቃንን ያሳያል፤ ቀጥሎ ቤተ ክርስቲያንን በሥራና በእምነታቸው 'ቅዱስ' የተባሉት ናቸው፡፡ ከላይ መላእክት ይታዩዋችኋል፡፡ ከመላእክቱ በላይ እንደምታዩት የኢየሱስ እናት



CamScanner

ማርያም ትታያለች፡፡ ከማርያም በላይ የሥላሴ ምስል ይታያል፡፡ ፒራሚዱ ከስር ሰፊ ይሆንና ከላይ ይጠባል፡፡

"ከምንታዊነት በፊት ክርስትና እንዲህ ነበር፡፡ በተለይ ደግሞ የአውግስጢኖስ ምንታዌ ሳይሆን የነ ማርቲን ሉተር ምንታዌ ከመምጣቱ በፊት በምሥራቁም ሆነ በምዕራቡ ክርስቲያን ውስጥ እንዲህ ያለ ከታች ወደ ላይ (Vertical) ነው፡፡ ይህም ሲባል ከስር ያለው ክርስቲያን የሚባለው ብዙ ማኅበረሰብ በቀጥታ ሥላሴን ማግኘት ይችላል፡፡ መብቱ ነው፡፡ ግን የክብር ተዋረዱ እንዲህ ነው፡፡ የሚዳነው በአንድ ሥላሴ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ክርስትና እርስ በእርስ የሚሳሳቡበት፣ የበረታው የደከመውን የሚስብበት፣ የጸደቀው ሌላው እንዲጸድቅ መንገድ የሚያሳይበት ነው፡፡ ስለዚህ ክርስትና ለሌሎችም እንደ አቅማቸው ቦታ ነበረው፡፡" ሰናይ እጁ ላይ ባለው ሪሞት አሳልፍ የሚለውን ተጫኑና ሌላ ገጽ አወጣ፡፡ አንዱ በጥቁር አንዱ በነጭ ቀለም የተቀባ ሁለት ሁለት ነገሮች በቀይ መደብ ላይ መጡ፡፡

"ከተሐድሶ በኋላ ሁሉንም አቅፎ የነበረው ክርስትና ምርጫ መጣበት፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ወይስ ድንግል ማርያም፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ወይስ ጻድቃን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ወይስ መላእክት ወደሚል ምርጫ መጣ፡፡ ምርጫው የመጣው የማይወዳደሩ ነገሮች ተወዳድረው፣ የማይመጣጠኑ ነገሮች ተመጣጥነው ነው፡፡ ስለዚህም 'ኢየሱስ ብቻ' ወደሚል ጠርዝ ተገፋና ሌሎች ቦታ አጡ፡፡ የኢየሱስ ብቻ ትርክት ሌላም ጫፍ አመጣ እሱም አብና መንፈስ ቅዱስን የሚያስረሳ ሁሉ ሆነ፡፡"

ቶኒ ድጋሚ ተሸወደ፡፡ ትንሽ ለዘብተኛ ይሆናል ያለው ሰው ባልተጠበቀ ሁኔታ ጭልጥ ብሎ ተሐድሶን እያጣጣለ ነው፡፡ 'የአቡነ ሰላማን ሀሳብ ሙሉ ለሙሉ እየመታው ነው፡፡' አለ ቶኒ ለራሱ በሆነ ሹክሹክታ፡፡

----//----

## አዲስ አበባ-ቦሌ

ዘላለም ግራጭ ቲሸርት ለብሷል፡፡ የእጁ ጡንቻዎች ውጥርጥር ብሏል፡፡ ጸጉሩ ተንጨባርሮ እልፎ እልፎ ጥጥ ይዟል፡፡ ፊቱ ንብ እንደነደፈው ገላ በቁጣ፣ በብስጭት እና በማልቀስ እብጥብጥ ብሏል፡፡ ምድር ቤት ካለው ሳሎን ሶፋ ላይ ቁጭ ብሏል፡፡ ከፊት ለፊቱ የአሜሪካ ምርት የሆነው አፕል ኮምፒውተር የተከፈተ ሲሆን የፓስተር ናፍያድን ማስረጃ ጨምሮ ብዙውን የተሐድሶ እንቅስቃሴ የሚያሳይ የቪዲዮና የጽሑፍ ማስረጃዎች ወደ ማኅበረ ቅዱሳን ዌብ ሳይት በምስጢር መላኪያው በኩል እየላከ ነው፡፡ ስልሳ አምስት እጁ እንደተላከ ኮምፒውተሩ ላይ ያሳያል፡፡

ዘላለም መልእክቱ ወደ ማኅበረ ቅዱሳን ዌብ ሳይት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ተልኮ እስከሚያልቅ ድረስ የፎቶ አልበሙን ከጠረጴዛው ስር አውጥቶ መመልከት ጀመረ፡፡ በጆሮው ደግሞ የተሸመ ምትኩ ዘፈን ሰሰስ ብሎ እየተንቆረቆረ ነው፡፡

"...ጥያቄ መጣልሽ መቼም አትረቺ

አባክሽ ኢትዮጵያ እስቲ ይህኔ ፍቺ

ትናንትና ሌሊት አንድ ህልም አይቼ

በጣም ተገረምኩኝ እራሴው ቃዥቼ..."

ዘላለም ኮምፒውተሩ እስከሚልክ ብሎ የእናት እና የአባቱን ፎቶ እያየ ነው፡፡ ፎቶው ከሚሰማው ዘፈን ጋር ሆኖ ሆድ ባሰውና እንባው ዝም ብሎ ይፈስ ጀመር፡፡ እምባው ከዓይኑ እየወረደ ፎቶው ላይ ያርፋል፡፡ ፎቶው ላይ ያረፈውን እንባውን በልብሱ ለመጥረግ ይሞክራል፡፡ ዘላለም ሳጉን መቆጣጠር እያቃተው ሰውነቱ እየተንቀጠቀጠ '...እህ እህ እህ...እህ ....' እያለ ስቅስቅ ብሎ ማልቀስ ጀመረ፡፡

ዘላለም ከልቅሶው እንደመባነን ብሎ ስልኩን አውጥቶ ለዳንኤል መልእክት ለመላክ መጻፍ ጀመረ፡፡ 'እዚህ ነገሮች እየተበላሹ ስለሆነ በፍጥነት ወደ ዱባይ ሂድ፡፡ ብትችልም ሌላ አገር ሂድ' ብሎ ላከለትና መልእክቱን ከስልኩ ላይ መልሶ አጠፋው፡፡

በፍጥነት የዘላለም ስልክ ጮኸ፡፡ ደዋዩ ዳንኤል ነው፡፡ ዳንኤል ሽብርብር ድንብርብር እያለ "ለምን? ምንድነው? ምን ተፈጠረ?" ሲለው ነው፡፡ ዘላለም ስልኩን ዘጋበትና የሶኒ ምርት ያለውን ቴፕ ሪከርደር ጋር ሔዶ ሙዚቃውን ከፍ አደረገው፡፡ ዘላለም እንባውን እየጠረገ ለስላሳውን የተሸመ ምትኩን ዘፈን ጮክ አድርጎ አብሮ መዝፈን ጀመረ፡፡

"...ሕልሜም እንዲህ ነበር እስኪ ልንገርሽ

አገሬ ኢትዮጵያ ታመሽ ተኝተሽ

አሜሪካን ቁሞ መርፌ ሲያስወጋሽ

እንግሊዝ ዳር ቁሞ ሲደባብስሽ

ጣልያን ሐኪም ሆኖ ሲመለከተሽ

ጀርመን ሞትሽን አውቆ አዝኖ ልኮልሽ



CamScanner

አረቦች በድንሽን ሲከፋፈሉሽ

አይሁዳም ሕዝብሽን ለቅሞ ወስዶብሽ

ፈረንሳይ ጠበቃ ሲያነጋግርሽ

ይህንን አለምኩት እስኪ ልንገርሽ

ወይ አገሬ ሆዬ ወይ አገሬ ሆዬ

መዳን ትድኛለሽ እስከዚያው እዬዬ..."

ዞላለም አብሮ መዝፈኑን ያቆመው የውጪው በር በኃይል ሲንኳኳ ነው፡፡ የማንኳኳት ድምጹ የሚረብሽና የሚያናድድ ዓይነት ስለሆነበት ምድር ላይ ካለው ሳሎን ወደ ላይኛው ፎቅ ላይ ወጣና ያንኳኪውን ማንነት ለመለየት በመኝታ ቤቱ መስኮት በኩል ማየት ጀመረ፡፡

ፌደራል ፖሊሶች በኦራል መኪና ተጭነው መጥተዋል፡፡ ሁለት ፖሊሶች በሩ ፊት ለፊት ሲሆኑ፤ አንዱ በሩን ያንኳኳል፡፡ አንደኛው ሩሲያ ሰራሹን ኤኬ-47 ሽጉጡ ወደ በሩ ወድሮ ቆሟል፡፡ መኪናው ላይ ደግሞ አራት ፌደራል ፖሊሶች ዐይናቸው በሩ ላይ እያጉረጠረጡ ተቀምጠዋል፡፡

ዞላለም የጠበቀው ነገር ስለነበረ ምንም አልደነገጠም፡፡ ይልቁንስ በፍጥነት ከመኝታ ቤቱ ወጣና ወደ ሳሎን ወርዶ ኮምፒውተሩን ይዞ ወደ መኝታ ቤቱ ተመለሰና ላፕቶፑን አልጋው ላይ አስቀመጠው፡፡ መረጃው ሰማንያ እጁ ተልኳል፡፡ ወደ ማብሰያ ክፍሉ ሔደና አስር ሊትር የሚይዝ ሰማያዊ ጀሪካን ውስጥ የተሞላ ጋዝ እምጥቶ መኝታ ቤቱ በረንዳ ላይ አደረገው፡፡ የግቢው በር በጣም እየተደበደበ ነው፡፡

ከዚያም መኝታ ቤቱ ወዳለ ቁም ሳጥን ሄደና ከልብስ ማስቀመጫው በስተጥግ ላይ በጥንቃቄ የተሰራች የምስጢር ሳጥኑ ውስጥ ያስቀመጠውን ሔክለርና ኮች ጂ3 ሽጉጡን አወጣው፡፡ ጂ3 የሩሲያውን ኤኬ4 ይተካል ተብሎ በጀርመን የተሰራ ነው፡፡ በደህና ጊዜ ቶኒ አስታጥቆታል፡፡ ቀጠለና መኝታ ቤቱ ኮመዲኖ ላይ ያስቀመጠውን ግሎክ19 አነሳና በጎኑ ሻጥ አደረገ፡፡ የበሩ መንኳኳት ፍጥነትና ኃይል ጨመረ፡፡

ዞላለም ፎቁ ላይ ካለው የመኝታ ቤት በረንዳ ላይ ወጥቶ ጂ3 ክላሹን በሩ አካባቢ ወዳሉት ፖሊሶች አነጣጠረ፡፡ በመጀመሪያ ሊመታው የፈለገው የሚያንኳኳውን ሳይሆን ክላሹን ወድሮ የቆመውን ነው፡፡ በጂ3 ቀለበት ውስጥ አድርጎ አንድ ዐይኑን አጨንቁሮ ማየት ጀመረ፡፡

ዘላለም የመጀመሪያውን ቃታ ሳበ። ሲተኮስ መኪናው ላይ የነበሩት ፌደራል ፖሊሶች ከመኪናቸው ዘልለው ወረዱና ሽጉጣቸውን ወደ በሩ አነጣጠሩ። ጭንቅላቱን የተመታው ፌደራል ፖሊስ በጀርባው ዘፍ አለ። በሩን ሲያንኳኳ የነበረው ወታደር መሬት ላይ ተኝቷል።

ዘላለም የመጀመሪያውን ግዳይ እንደጣለ ሲያውቅ ጂ3 ክላሹን ወደ ፌደራል መኪናው አነጣጠረና መኪናውን መደብደብ ጀመረ። የአጸፋ ተኩስ ተመልሶ ከፌደራል ፖሊሶች ተከተለ። ዘላለም አከታትሎ ፌደራል ፖሊስ መኪናዋ ጎን ላይ ሲተኩስ የመኪናዋን የነዳጅ ጋን ስላገኘው መኪናዋ ባለችበት መንደድ ጀመረች።

አካባቢው በተኩስ መናጥ ጀመረ። ተጨማሪ መኪኖች የአደጋ ጊዜ ጩኸት እያሰሙ መምጣት ጀመሩ። ቦታው በፌደራል ፖሊሶ መወረር ጀመረ። ተኩሱ ዘላለም ቤት ግቢ ላይ በረታ። የቤቱ መስኮት እና መስታወት እየተመታ መረጋገፍ ጀመረ። የውጪው በር በጥይት ንድልድል አለ። ግን አልተከፈተም።

ዘላለም በቀለበቷ በኩል እያነጣጠረ ዕይታው ውስጥ የገቡትን የፌደራል ፖሊሶች ላይ መተኮሱን ቀጥሏል። ነገር ግን እሱ ከቆመበት በስተጀርባ ተኩስ እየሰማ ነው። ቀለበት ውስጥ እያስገቡት ነው።



CamScanner

## ምዕራፍ ፳፩

## እንግሊዝ ለንደን

ውቡና በጥንቃቄ የተዘጋጀው የስኩል ኦፍ ኢኮኖሚክሱ ፒኮክ አዳራሽ ጸጥ ረጭ ብሏል። ሰናይ ደስ ብሎታል። ፊቱ ላይ የሚያበራው የደስታ ጸዳል ጥናታዊ ጽሑፉን ለሚከታተሉት ሰዎች ሁሉ የሚጋባ ዓይነት ነው። ከታሸገው ውኃ በደንብ ስቦ ተጎነጨለት። ውኃው ጉሮሮውን ደቅድቆት ሲያልፍ ገርገጭ የሚል ድምጽ አወጣ። ሰናይ ውስጡ ቅዝቅዝ ብሎ ልቡ በሐሴት ሲሞላ ተሰማው። ወደ ኮምፒውተሩ ጎንበስ ብሎ ጽሑፉን አየት አደረገና ገለጻውን ቀጠለ።

"ተሐድሶን የዚህን ያህል ካየን ተዋሕዶን ደግሞ እንይ እስኪ። አለቃ ኪዳነ ወልደ ክፍሌ 'መጽሐፈ ሰዋሰው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ' በሚለው የመዝገበ ቃላት መጽሐፋቸው 'ተዋሕዶ' የሚለው ቃል 'ተዋሐደ' ወይም 'አንድ ሖነ' ከሚለው ቃል የመጣ ነው ይሉናል። ይህ ቃል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ዘንድ የሃይማኖታቸው መገለጫ ነው። 'ተዋሕዶ' የሚለው ቃል የሰውንና የአምላክን አንድ መሆን የሚያመለክት ነው።

"መጽሐፍ ቅዱስ የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ጀምሮ ሰናነብ ይህን እናገኛለን…" አለና ሰናይ ፕሮጀክተሩ ላይ የኪንግ ጀምስ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉምን አወጣ "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ነበረ። ኹሉ በእርሱ ነበረ ኾነ፤ ከኾነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም። በእርሱ ሕይወት ነበረች፤ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች። ብርሃንም በጨለማ ይበራል፤ ጨለማም አላሸነፈውም።…ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር። በዓለም ነበረ፤ ዓለሙም በእርሱ ሆነ፤ ዓለሙም አላወቀውም። የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፤ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ሁሉ ግን፤ በስሙ ለሚያምኑት፤ ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም፤ ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም። ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ፀጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፤ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን።'

"ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ብዙዎቻችሁ እንደምታውቁት አውቃለሁ። ነገር ግን የተዋሕዶ እምነት ሊቃውንት ይህን የዮሐንስ ወንጌልን ምንባብ በብዙ መልኩ ይተረጉሙታል። ለምሳሌ የዮሐንስ ወንጌል ላይ ያሉትን አንዳንድ ቃላት እያነሳን እንይ። 'ሕይወት፣ ብርሃን እና ሥልጣን' የሚሉትን ቃላት።

"ለሰው ልጆች 'ሕይወትን' ስንል ጤናን፣ ደስታን፣ ቅዱስ መንፈስን፣ ቅንነትን፣ ዘላለማዊነት የመሳሰሉትን፤ 'ብርሃንን' ማለትም ዕውቀትን፣ ጥበብን፣ እምነትን፣ አስተዋይነትን ለስህተትና ለማደናገሪያ አለመሸነፍን እንዲሁም 'ሥልጣን' ስንል በሥራ የሚገለጥ፣ ክፋትን ሁሉ ለማሸነፍ የሚበቃ ኃይልን፣ ጽናትን፣ ብርታትን፣ ንጽሕናን፣ ግርማ ሞገስን ችሎታን... 'ይህ ሁሉ የተገኘው እግዚአብሔር ሰው ሲሆን ነው።'

"እውነተኛ ፍላጎትና አምልኮት ወደ እርሱ ሲቀርቡ ከርሱ የሆነ ነገር ሁሉ በፀጋ ሊከብሩበት መንገዱ ተከፈተላቸው። ስለዚህ የሰው ልጅ ለፍትሕ፣ ለሰላም፣ ለደስታ ለእኩልነት በአጭሩ 'መልካም' ለተባሉት ነገሮች በሙሉ እንዲጓጓ የሆነው እግዚአብሔር ሰው ስለሆነ የተገኘ በረከት ነው።

"የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ሁለት ቁጥር አሥራ አራት ላይ 'ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን፤ ሠላምም በምድር፤ ለሰውም በጎ ፈቃድ' ይላል። ይህ ምን ማለት ነው? 'የሰው በጎ ፈቃድ ማለትም መልካም ነገር የመፈለግ ዝንባሌው በክርስቶስ ሰው መሆን ወይም በተዋሕዶ ምክንያት መልስ ተገኘለት' ብለው የተዋሕዶ ሊቃውንቶች ለእምነቱ ተከታዮች ያስተምራሉ።

"የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ባሕሪ በመዋሐዱ አማካኝነት ሰው ሁልጊዜ ሲፈልገው የነበረው ደስታ ተገኝቷል። ይህ ደስታ ስለመገኘቱ መጽሐፍ ቅዱስ ምስክር ነው። የእግዚአብሔርን ሰው መሆን ያበሰረው መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ድንግል ማርያምን ሄዶ 'ደስ ይበልሽ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፤ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው' ብሎ ነበር የተናገረው። የእግዚአብሔር ሰው መሆን ለሰው ልጅ ደስታን ነው ያመጣው።" ስናይ በመነጽሩ ሳይሆን ከመነጽሩ በላይ በዐይኑ በፕሮጀክተሩ ላይ የሚታየውን ጽሑፍ በእጁ በያዘው የርቀት መቆጣጠሪያ በመጠቀም አሳለፈውና አዲስ ርዕስ መጣ።

"ይበልጥ በተሐድሶ እና በተዋሕዶ መካከል ያለው ልዩነት ስለ ቀደመው ኃጢአት ያለ አተያይ ነው። ምሥራቃውያን ኦርቶዶክሶች 'አዳም ሲበድል የተሰጠው የእግዚአብሔር መልክ ደከመ፣ ባሕርዩም ጎሰቆለ እንጂ ጨርሶ አልጠፋም።' በኦርቶዶክሳውያን አገላለጽ 'የባሕርይ ማጎሳቆል' ወይም 'Fallen nature' ይሉታል 'ስለዚህም እግዚአብሔር ሰው ሲሆን የቀድሞ አዳም ክብሩ ተመልሷል' ባይ ናቸው። በተቃራኒው ደግሞ ምዕራባውያን 'ጥንተ አብሶ' ወይም 'Origina sin' ነው በማለት የሰው ልጅ የቀደመ ክብር እንዳልተመለሰ ያምናሉ። ይህ ጽንሰ ሀሳብ ለማይታረቅ የሰው ልጅ የአኗኗር አተያይ ገፍቷቸዋል።

"በተዋሕዶ ዕይታ የነገሮች ውሕደት እንጂ ምንታዌነት የለም፤ ሁለቱን አንድ ላይ እንጂ አንዱን መምረጥ ግድ አይልም። በተዋሕዶ መነጽር ሌሎች ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ አተያዮችም ከተሐድሶ በተቃራኒ ነው። ወንድ ልጅ ሴትን



CamScanner

በድንግል ማርያም መስሎ የሚያከብርበት፣ ሰው በተፈጥሮው ጥሩ ነው ብሎ ማመን፣ ገጠርና ከተማ ለሰው ልጅ ሀልውና እኩል ነው ብሎ ማመን፣ መንግሥትና ሕዝብ አንድ ነው ብሎ ማመን፣ ቀሳል፣ ቀጥተኛ ነገሮችን ማክበርና መፈለግ… ነገር ይታያል።

"ቅድም ቅዱስ አባታችን አቡነ ሰላማ ለኢትዮጵያ የተሐድሶ ጥያቄ አቅርበዋል። እኔ ግን ለኢትዮጵያ ተሐድሶ ሳይሆን ተዋሕዶ ያስፈልጋታል እላለሁ። ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት ከአቅም በላይ በሆነ የተሐድሶ ሃሳብ በግልብ ተነስቶ አገሪቷን እያመሳት ነው።

"ተሐድሶ ኢትዮጵያን የምርጫ ፖለቲካ ውስጥ እየከተተ ብሔራዊ አንድነቷን አደጋ ውስጥ ከቷል። ኢትዮጵያ ወይም ኦሮሚያ፣ ኢትዮጵያ ወይም ትግራይ፣ ኢትዮጵያ ወይም አማራ፣ ኢትዮጵያ ወይም ጋምቤላ፣ ኢትዮጵያ ወይም ሌሎች ጎሳዎችን እያነሳ ለምርጫ እያቀረበ ነው። የአንድን አገር ባንዲራ ብዙ በማድረግ፣ ባንዲራን የማንነትና የአርማ ምርጫ ውስጥ ከቶ ዋናውን የኢትዮጵያን ባንዲራ ሕልውና እየተፈታተነ ነው።

"የኢትዮጵያውያን አስተሳሰብ በአሁኑ ሰዓት ምንታዌነት የመታውና ቀድሞ ከነበረው የተዋሕዶ አስተሳሰብ ወጥተው አውሮፓ በጨለማው ዘመን ትዳክርበት የነበረው ርዕዮተ ዓለም ማስተጋባት ከጀመሩ ዋል አደር ብለዋል። ይሄ ደግሞ ኢትዮጵያን ለእርስ በእርስ ጦርነት የሚያጋልጥ፣ ኢትዮጵያ እንደ አገር እንዳትቀጥል ትልቅ ተግዳሮት እየሆነባት ነው። ስለዚህ ለኢትዮጵያ ተሐድሶ ሳይሆን ተዋሕዶ ነው የሚያስፈልጋት። የተዋሐደች ኢትዮጵያ እንጂ የተከፋፈለች ኢትዮጵያ ወደ ፊት አትቀጥልም። የተዋሐደች አገር በምጣኔ ሐብት የበለጸገች፣ ኅብረተሰባዊ ቀውስም የማያሰጋት ትሆናለች።

"ታውቃላችሁ ኢትዮጵያውያን አድዋ ድል የተቀዳጁበት ዋናው ምስጢር ተዋሕዶ ነው። ተዋሕዶ ስል ቤተ ክርስቲያንን ማለቴ አይደለም። በእርግጥ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አሌ የማይባለውን አርበኝነት አድዋ ላይ ፈጽማለች። ነገር ግን ዋናው የድሉ እምብርት የሚገኘው ተዋሕዶዋዊ አስተሳሰብ ነው። በዚህ ጦርነት ላይ ሴት ከወንድ፣ ካህኑ ከሼሑ፣ ነገሥታት መኳንንቱ ከሕዝቡ፣ ሕዝቡ ከመልክአ ምድሩ ስለተዋሐዱ ነው ያ ምድር አንቀጥቀጥ እውነት፣ በዓለም መድረክ አዲስ የታሪክ ትርክት የተጻፈው። የተዋሕዶ ምስጢር ይህ ነው።

"ይህን ተዋሕዶ አስቀድመው መስመር ያስያዙት ደግሞ አጼ ዮሐንስ አራተኛ ናቸው። ለዘመናት ቅባት፣ ተዋሕዶ እና ፀጋ እየተባባለ ሲጋጭ እና ሲነታረክ የነበረውን ሕዝብ በተዋሕዶ አንድ እንዲሆን አደረጉት። ይህን የቤተ ክህነት አንድነት ደግሞ አጼ ሚኒልክ ሁለተኛ ወደ ሁሉን አቀፍ ውሕደት አምጥተው ልዕለ ኃያል አገርን አሸመደመዱና አድዋ የሚባል ታሪክ ጻፉ። ተዋሕዶ ማለት ልዩነትን

ሳያበሳልጡ፣ ሳያጠፋፉ እና ሳያገፋፉ አዋሕዶ አንድነትን መመሥረት ማለት ነው።" ከአዳራሹ በስተቀኝ ያለ ሰው ብቻውን አጨበጨበ። ከዚያም ትንሽ ቁጥሩ ጨመር ያለ ሰው ማጨብጨብ ጀመረ።

ሰናይ ጭብጨባው ጋብ ሲል መናገሩን ቀጠለ "ቢያንስ በአንድ ነገር እንኳ የተባበረ እና የተዋሐደ ማኅበረሰብ መፍጠር ለአንድ አገር ቀጣይነት ይበጃል እንጂ ልዩነትን ሁሉ ማግለብለብ ውበት አይሆንም፤ አይደለምም። ተዋሕዶን እንደ አንድ የምጣኔ ሐብት፣ የፖቲካና የኅብረተሳባዊ መንገድ ከወሰደን የተሻለ ለውጥ ይመጣል እላለሁ። ልክ ፕሮቴስታንት ለካፒታሊዝም መፈጠር መሠረት እንደጣለና መነሻ እንደሆነ ሁሉ ለኢትዮጵያ ደግሞ ተዋሕዶን መሰረት ያደረገ ርዕዮተ አለም ብናመጣ መልካም ነው።

"አሁን ደግሞ ቅዱስ አባታችን ያነሱትን አንዳንድ ሀሳቦች እንይ። 'ለኢኮኖሚያው፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ... እድገት ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ ግድ ነው' ብለዋል። እኔ ግን አይደለም እላለሁ።" አቡነ ሰላም ፊቱ በንዴትና በቁጣ ተለዋወጠ። አጠገቡ ያሉትም ሊቀ ጳጳሳትም አከረፉ።

"ቅዱስ አባታችን ደቡብ ኮሪያ ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ ስለ ተቀበለች አደገች ብለዋል። እኔ ግን በፍጹም እላለሁ። ምክንያት ብባል? አንደኛ ደቡብ ኮሪያ ያለምንም የተፈጥሮ ሀብት እንዲህ ሽቅብ የወጣ የምጣኔ ሀብት ማማ ላይ የሰቀላት፤ አሜሪካ በቀጣናው ያላት ልዩ ፍላጎት ነው። ስለዚህም ሰሜን ኮሪያን ለማስቀናት እንዲሁም የተቀሩትን በቀጠናው ከፍተኛ እና ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት እያሳዩ ያሉትን አገራት ለመተካከል አሜሪካ ፈጠር ኢኮኖሚ በአካባቢው ለመመስረት ነው።

"ሲቀጥል ለምን ደቡብ ኮሪያ ብቻ ፕሮቴስታንት ስለሆነች ታድጋለች? ስንትና ስንት የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ የአፍሪካ አገራት አሉ እኮ። ለምሳሌ ሱዳን፣ ኬንያ፣ ናይጄሪያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ጋና፣ ኡጋንዳ፣ ማላዊ... እነዚህ አገራት የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች የሚበዙባቸው ናቸው። ነገር ግን እድገት አይደለም የሚፈለገውን መንፈሳዊ እውቀትም እንኳ በቅጡ አልያዙም። ከዚያ ይልቅ ለእርስ በእርስ ጦርነቶች፣ ለኤች አይቪ ኤድስና ለሌሎች ወረርሽኞች የተጋለጡ፣ አንድ የነበሩት አገራት በሃይማኖታቸው የተነሳ በመናናቅና በመጠላላት ለሁለት መከፈል እጣቸው የሆነ ነው። ታዲያ ምነው ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ አፍሪካ ላይ አቃተው? እንዲያውም ለእነዚህ አገራት ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ በረከት ሳይሆን መቅሰፍት ነው ያመጣባቸው።

"በተቃራኒው ፕሮቴስታንት ሳይሆኑ ምጣኔ ሀብታቸው በዓለም ላይ በሚያስደነግጥ ሁኔታ ያደጉ አገራት ብዙ ናቸው። ሩሲያ ትልቁን የሕዝብ ቁጥር የሚይዘው ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ነው፤ ጃፓን ከ2.3 ፐርሰንቱ ክርስቲያን በስተቀር የተቀረው የሽንቶ እና የቡዲዝም ሃይማኖት ተከታይ ነው፤ ቻይናን የወሰድን



CamScanner

እንደሆነ ከ2.5 ፐርሰንቱ ክርስቲያን በስተቀር የተቀረው ኮንፊሺየኒዝም፣ ታኦይኒዝም እንዲሁም ቡዲዝም አማኝ ነው። እስራኤል የክርስቲያን አገር ሳትሆን የአይሁዳውያን ነች። እነዚህ አገራት ግን የዓለምን ምጣኔ ሐብታዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ጉዳዮች በበላይነት የሚዘውሩ ናቸው።

"ይህ የሚያሳየን ለእድገት የሰው ነገር መኮረጅ ሳይሆን የራስን ባህል፣ ሃይማኖትና ታሪክ ጠንቅቆ አውቆ፣ በዚያ መሠረት የአገር ሁለንተናዊ እድገት ለመቀየስ ጥረት ማድረግ እንጂ ፕሮቴስታንት ካልሆናችሁ አታድጉም ማለት የዓለምን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ የስህተት አስተምህሮ ነው።

"በስተመጨረሻ መስመር ያሰበት አንድ ጉዳይ አለ። ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ ሲጠራ የተጠራው ለኦርቶዶክስ ሳይሆን ለካቶሊክ ነው። ማርቲን ሉተር ያነሳው ጥያቄ ካቶሊክ ተሳስታለች እንጂ ምሥራቁ ክርስቲያን ወይም ኦርቶዶክስ ተሳስቷል የሚል አይደለም።

"በቅንነት ካየነው ማርቲን ሉተር የምሥራቁ ወይም የኦርቶዶክስን አስተምህሮ አያውቀውም። ስለዚህ ከቅዱስ ቃሉ ይልቅ የጳጳሱን ቃል ስታዳምጥ የኖረችውን ካቶሊክን ተቃወመና በቤተ ክርስቲያኗ ላይ ተሐድሶን አመጣ። ነገር ግን ማርቲን ሉተር የምሥራቁን ወይም የኦርቶዶክስን አስተምህሮና ሥርዓት በደንብ ቢያውቀው ኖሮ ኦርቶዶክስ ይሆን ነበር እንጂ ተሐድሶ አያስነሳም እላለሁ። ለዚህ ምሥክር ለመጥቀስ ብዙ ሩቅ መሄድ ሳያሻን ራሷ ኦርቶዶክስ ምስክር ነች። የትኛውም የኦርቶዶክስ አባት ቤተ ክርስቲያኗ ስህተት መሆኗን ሲያሳይ አላየንም። ከዚያም ገፍቶ እንዲህ እንደ ፕሮቴስታንታዊ አይነት ተሐድሶ ያስነሳ አባት የለም። ቢያስነሳም የሚቀበለው ምእመን የለም። ምክንያቱም የጎደለበት አንዳች እንኳ ስለሌለ ነው። አንዳች እንኳ!

"ስለዚህም ኦርቶዶክስ ላይ ተሐድሶ ለማፋፋም ለጓጓችሁ ለእናንተ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ትታደስ ካልታደሰች አናድግም ብላችሁ ለምታምኑ ለእናንተ የምለው አለኝ። ይልቁንስ እናንተ ራሳችሁ ተሐድሶ አድርጉ። ከዚያም ኦርቶዶክስ ተዋሕዷዊ እንቅስቃሴን በኢትዮጵያ ላይ አፋፍሙ። ያኔ ምጣኔ ሐብታዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ እድገት እናሳያለን።" አለ ሰናይ። ለመጀመሪያ ጊዜ ሆን ብሎ አቡነ ሰላማን ተመለከተው። እጁን አጣምሮ በመኮሳተር ሰናይን አፍጥጦ እየተመለከተው ነው። በጣም የተናደደበት ይመስላል።



CamScanner

## ምዕራፍ ፳፪

### አዲስ አበባ-ቦሌ

የዘላለም ግቢ በር ተከፍቷል፡፡ ውጪ ላይ የሞቱት ፌደራል ፖሊሶች አራት ደርሰዋል፡፡ አሁን ሽጉጣቸውን ወደ ፊት የወደሩ ፌደራል ፖሊሶች እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊሶች ወደ ዘላለም ቤት እየገቡ ነው፡፡ ዘላለም ከመኝታ ቤቱ በረንዳ ላይ ሆኖ አሁንም እየተኮሰ ነው፡፡

ከበረንዳው ላይ ላፕቶፑን ጋዝ አርከፍክፎ እያነደደው ነው፡፡ የፌደራል ፖሊሶች ሳሎኑ ውስጥ እንደገቡ አውቋል፡፡ ስለዚህ የመጨረሻውን ውሳኔ መወሰን አለበት፡፡ ከጎኑ የሸጎጠውን ግሎክ 19 ሽጉጥ አወጣና ዐይኑ ፊት ለፊት በእጁ ይዞ እያወዛወዘ "እንደ አባቱ ካሳ" አለ፡፡ ዘላለም በገዛ ጭንቅላቱ ላይ ግሎክ 19 ሽጉጡን ደገነና ለሰከንዶች ዐይኑን ጨፈነ፡፡ እጁ በመጠኑ ይንቀጠቀጣል፡፡ ከዚያም በጠቋሚ ጣቱ የሽጉጡን ምላጭ ሳበው፡፡

-------//----

### ኢትዮጵያ-ሐዋሳ

ሔራሞ እንግሊዝ አገር ለውይይቱ ይሔዳል ተብሎ የታሰበ ቢሆንም ኢትዮጵያ ቀርቶ ከግሩም ጋር ተሐድሶውን እንዲያውጅ ስለተነገረው ቀርቷል፡፡ ጋዜጠኞች ረዥም ሆኖ በእንቁላል ቅርጽ በተሠራው የሴንትራል ሆቴል ውብ አዳራሽ ውስጥ ተቀምጠዋል፡፡ ግሩምና አቡነ ጎርጎሪዮስ ሣልሳዊ ከመሀል የተቀመጡ ሲሆን ከግራ በኩል ሔራሞ፤ ከቀኝ ደግሞ ትርሲት ተቀምጣለች፡፡ ከእነሱ ፊት ለፊት የተለያዩ መገናኛ ብዙኃን መቅረጸ ድምጽ ከፊት ለፊታቸው ተቀምጧል፡፡ ቀድሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥር የነበሩ፣ ጥቂት የማይባሉ አብያተ ክርስቲያናት ከዋናው ቤተ ክርስቲያን ተገንጥለው 'የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተሐድሶ ቤተ ክርስቲያን' መባላቸውን አውጀዋል፡፡ በሥራቸው ቀላል የማይባሉ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዳሉና ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም እንደሚቀላቀሏቸው እንደሚጠብቁ ተናግረዋል፡፡

አብዛኞቹ ጋዜጠኞች በሰሙት ነገር የደነገጡ ይመስላል፡፡ ከፋና ሬዲዮ ጣቢያ የመጣው ጋዜጠኛ ነበር የመጀመሪያውን ጥያቄ የሰነዘረው "በተለያዩ ክልሎች ውስጥ ተሐድሶውን የደገፉ አባላት እንዲሁም አብያተ ክርስቲያናት እንዴት እና የት ሆናችሁ ነው የምታስተዳድሩት?"

ግሩም ነበር ምላሽ የሰጠው "ለጊዜው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተሐድሶ ቤተ ክርስቲያን መቀመጫውን ሐዋሳ ያድርግ እንጂ በተለያዩ ክልሎች ቢሮውን ይከፍታል፡፡ ስለዚህም



CamScanner

ሁሉንም ነገር በየአጥቢያው እየሔድን እንከታተላለን። ሐዋሳ ግን የተሐድሶው ፓትርያርክ መቀመጫ እንዲሆን ለጊዜው ወስነናል። በቀጣይ ለውጥ የምናደርግ ከሆነ እናሳውቃለን።"

ቀጣዩ ጠያቂ ከኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬት የመጣው ሙሉ ጥቁር ሱፍ ያደረገውና ፊገግ እያለ ጥያቄ እያቀረበ ነው "እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የሚቀጥሉ ነገሮች እንዳሉ ቅድም ተናግራችኋል። ይህ ነገር ሥርዓተ አምልኮው በተለይ ቅዳሴው በግዕዝ እንደሆነ ይቀጥላል። ሌሎችም የአምልኮት ሥርዓቶች በግዕዝ ቋንቋ ነው የሚሆነው?"

አቡነ ጎርጎሪዮስ ነበር መልስ የሰጡት "ይህማ አይሆንም! አንዱ ሕዝቡን ለተሐድሶ እንቅስቃሴ የገፋውና ለለውጥ ያነሳሳው ቃለ እግዚአብሔርን በማያውቀው ቋንቋ መሰበኩ ነው። ስለዚህ ማንኛውም ክልል ውስጥ ያለ አብያተ ክርስቲያን በራሱ ቋንቋ የማምለክ፣ የመማር፣ የማስተማር፣ የመቀደስ፣ የማስቀደስ... መብት አለው።"

ቀጣይዋ ጠያቂ እንደነገሩ የለበሰችው ባለ ቆንጆ ድምጿና መልከ መልካሟ የሸገር ኤፍ ኤም ጋዜጠኛ ነበረች ውብ ድምጿን እያስረቀረቀች "በአሁኑ ሰዓት ምን ያህል ቤተ ክርስቲያኖች ተሐድሶውን ደግፈዋል?"

ይህንን ምላሽ የሰጠችው ድመጸ መረዋዋ ዘማሪ ትርሲት ነች። ዛሬ ደግሞ ያለ ነጠላ ነች። ጥቁር አጭር ቀሚስ በቦዲ ቲሸርት ለብሳ እንዲሁም ጸጉሯን 'ሳብ ሳብ' ተሰርታለች። አንገቷና መዳፏ ጀርባ ላይ የተርከፈከፈችው ሽቶ ጠረኑ ልብ ጥፍ ደርጋል። የወርቅ ሐብል አንገቷ ላይ አንጠልጥላለች። ትርሲት ውብ በረዶ የመሰለ ጥርሷን ብልጭ አድርጋ መናገር ጀመረች።

"ሻሸመኔ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ሙሉ ለሙሉ ተሐድሶውን ደግፈዋል። እንዲሁም ሐዋሳ ከጥቂት አብያተ ክርስቲያናት በስተቀር የተሐድሶው ደጋፊ ናቸው ሌሎች ክልሎችም አሁን በቁጥር እንዲህ ነው የማንላቸው ቤተ ክርስቲያኖች ተሐድሶውን ተቀላቅለዋል። በሚቀጥለው ቀን በምንሰጠው መግለጫ ላይ ሁሉንም ይፋ እናደርጋለን። የተቀረውንም በቅርቡ በተከፈተው የቴሌቪዥን ጣቢያችን ላይ ከስር ከስር አፕዴት እናደርጋለን።"

ሲናገር ጥርሱን ነክሶ የሚመስለው፣ ግን ደግሞ ጆሮ ገብ ድምጽ ያለው የቪኦኤው ጋዜጠኛ ለመጠየቅ እጁን አነሳና እድሉ ሲሰጠው መጠየቅ ጀመረ "ቅድም እንደ ነገራችሁን ብዙው አስተምህሯችሁ የፕሮቴስታንት ነው። ምንም ልዩነት የሌለው እስኪመስል ድረስ አንድ አይነት ነው። በተለይ ደግሞ ጳጳሳት ባለትዳር መሆን እንደሚችሉ፣ የሴት ካህናት እና ጳጳሳት ደግሞ አዲስ ነገር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት እንዲህ ያለ አሰራር ይቻላል? ታዲያ ተሐድሶ የራሱ የሆነው ነገር ምንድነው?"



CamScanner

ግሩም በቪኦኤው ጋዜጠኛ ተናድዷል መልሱን እራሱ መመለስ ስለፈለገ ማንም ሳይቀድመው መናገር ጀመረ "ከኦርቶዶክስም ሆነ ከፕሮቴስታንት ጠቃሚ ሐሳቦች ካሉና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እስካልተጋጩ ድረስ እንቀበላለን። መዳን በእምነት፣ በኢየሱስ እና በፀጋ ብቻ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ እና ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ የሚለውን አስተምሕሮ የተሐድሶው መሰረት ነው። የምንቀበለውም መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚልና እውነት ስለሆነ ብቻ ነው። ባለ ትዳር ጳጳስ መሆን ይችላል የሚለው እዎ መጽሐፍ ይደግፈናል። 'የአንዲት ሴት ሚስት የሆነና ምስጉን ሰው ሊቀ ጳጳስ መሆን ይችላል።' ቃሉ ነው የሚለው። ይህ አሰራርም ቀድሞ በቤተ ክርስቲያን ነበር።

"ሌላው ስለ እንስቶች የተነሳው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ቁርጥ ያለ ነገር እንስቶች ካህን ይሁኑ አይሁኑ አይልም። ያም ሆነ ይህ እንስት ካህናት ያስፈልጉናል። ስለዚህ እንስቶችን እስከ ሊቀ ጳጳስ የሚደርሱበትን አሰራር እናመጣለን። ሴቶችን ከቤተ ክህነት ማግለል አንችልም እነሱም ሊያስቀድሱ ብቻ ሳይሆን ሊቀድሱም ይገባል። ካህን ብቻ ሳይሆን ጳጳስ ሊሆኑ ግድ ነው።" ትርሲት በደስታ አንገቷን በአዎንታ እየነቀነቀች ነው። ምክንያቱም የመጀመሪያውን የኤጲስ ቆጶስ ሹመት እንደሚሰጣት ስላወቀች ነው።

ግሩም ስሜቱን ለመቆጣጠር እየሞከረ ንግግሩን ቀጠለ "አንዳንድ አሰራሮች ግን ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እንወስዳለን። የአባቶቻችን ስለሆነ የመውሰድ መብታችን የተጠበቀ ነው። ለምሳሌ አስተዳደርን አስመልክቶ በጣም ማዕከላዊነትን ባናስፍንም መጠነኛ ማዕከላዊነት እንዲኖር እናደርጋለን። ሥርዓተ ቅዳሴም መጠነኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማሻሻያ ተደርጎበት ይቀጥላል። ከስልሳ ስድስት ውጪ ያሉ መጽሐፍን ጨምሮ አዋልድ መጽሐፍትን አንቀበልም። በእርግጥ ሙሉውን የሃይማኖት መግለጫውን በቅርቡ በቴሌቪዥን ጣቢያችን ይፋ እናደርጋለን።"

ቀጣዩን ጥያቄ ያነሳችው ከቢቢሲ የመጣችው ትርሃስ ነች "የንብረት ጉዳዮችን እንዴት ልታደርጉ ነው? ማለቴ አሁን የወሰዳችሁት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነው። ስለዚህ ተገንጠልን ስትሉ ይህ ንብረት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለሆነ መመለስ አለበት። ቅጽር ቤተ ክርስቲያኗ፣ ንዋየ ቅድሳቷ፣ ሐብት ንብረቷ... ማለቴ ነው?" ይህን ጥያቄ ምላሽ የሰጡት አቡነ ጎርጎሪዮስ ሳልሳዊ ናቸው "የኢትጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሚባል ንብረት የለም። ንብረቱን የምእመኑ ነው። ይህ ምእመን ደግሞ ሲፈልግና ሲቀየር ንብረቱን ቅጽር ቤተ ክርስቲያኑን ጭምር መውሰድ ይችላል። መብቱም ስለሆነ። ለማንኛውም ይህ ጉዳይ በአገሪቱ ሕግ ይዳኛል ብለናል።"



CamScanner

# ምዕራፍ ፳፫

ሰንፔር "ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተው አትከልክሏቸው..." የሚለውን ጥቅስ ያገናኘችው ከሚድራሺ ሆስፒታል ነው። "ሚድራሺ ሆስፒታልና ሕፃናትን ሊያገናኝ የሚችለው ብቸኛው መንገድ 'ፔዲያትሪክ ዋርድ' ብቻ ነው" አለች።

ስለዚህ የሕፃናት አስተኝቶ ማከሚያ ክፍል ቁጭ ብላ ዙሪያ ገባውን ማየት ጀመረች። ሰንፔር ኳስ ኳስ የሚያክሉ ዐይኖቿን በግርግዳው ላይ እያንከራተተች ተመለከተች። ምንም ፍንጭ ልታገኝ አልቻለችም።

ድጋሚ ወረቀቷ ላይ የጻፈችውን ምልክትና ጽሑፍ አውጥታ ማንበብ ጀመረች የሚቀራት ጥቅስ አለ። "..ከሕፃንነቴ ጀምሮ ጠብቂያለሁ..." ሰንፔር ዐይኗን ብልጥጥ አድርጋ ማሰብ ጀመረች። በእርግጥ የጥቅሱ ሀሳብና መንገድ በጣም የተለየ ነው። ይህ ጥቅስ ያለው አንድ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን 'መንግሥተ ሰማያትን እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ?' ብሎ ይጠይቀዋል። ኢየሱስም "አስርቱ ትእዛዛትን አክብር" አለው። ሰውየውም "እሱንማ ከሕፃንነቴ ጀምሮ ጠብቂያለሁ" ይላል። ይሕን ጥቅስ በትክክል መጽሐፉ እንደሚለው እንድትተረጉመው እንዳልተቀመጠላት ገብቷታል።

ሰንፔር አስባ የመጣችውን ሁለተኛውን ሀሳቧን ማሰላሰል ጀመረች። 'እስኪ ልሞክረው' አለችና ተነስታ ወደ ጨቅላ ሕፃናት መታከሚ ክፍል መሔድ ጀመረች። የሕክምና ባለሙያዎች ጨቅላ ሕፃናት (Neonate) የሚሉዋቸው ከተወለዱ እስከ ሃያ ስምንት ቀን ድረስ ላሉት ነው። እነዚህ ሕፃናት ከሌሎች ሕፃናት ጋር አንድ ላይ አይታከሙም። ለብቻቸው የጨቅላ ሕፃናት ክፍል አለ። ብዙ ጊዜ እናትና ልጅን እንዲይዝ ተደርጎ የሚዘጋጅ ክፍል ሲሆን በጣም ሙቀትና የክፍሉ ብርሃን በጥንቃቄ የተመጠነ ነው።

ሮዳስ ለልደቷ የሰጣትን ሰማያዊ ቀለም ያላትን ሰዓቷን ተመለከተች። ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ከሩብ ሆኗል። ከዚህ በፊት የጨቅላ ሕፃናት አስተኝቶ ማከሚያ ክፍል ገብታ አታውቅም። ቢሆንም አሁን መሄጃ ግድ ነው።

ነጩን ጋወኗን ቀለፈችና ሁለቱንም እጆቿን በጋወኗ ኪስ ከትታ የጨቅላ ሕፃናት አስተኝቶ ማከሚያ ክፍል ምድር ላይ ስለሚገኝ ከነበረችበት አንደኛ ፎቅ ወደ ምድር አመራች። ስትወጣ ሳቂታዋና ወጣቷ የሕፃናት ክፍል ነርስ አገኘቻት "ዶክተር ወዴት ነሽ? ነይ ቡና ልናፈላ ነው ትጠጫለሽ?" አለቻት እየሳቀች

ሰንፔር እንደመደናበር ብላ "እ ሲስተር ታውቂ የለ? ቡና እኮ ማታ ማታ አልጠጣም! ከጠጣሁ እንቅልፍ አይወስደኝም"



CamScanner

"እውቃለሁ አብረሽን እንድትጫወቺ ብዬ ነው ነይና ትጫወቻለሽ ደሞ ጠፍተሻል። ስንት ወሬ አለ መሰለሽ"

"እሺ ሰርጂካል ዋርድ አንድ የማየው ኬዝ አለኝ ከዚያ በጊዜ ካለቀ እመጣለሁ ሲስተርዬ" ብላ ዋሸቻት

"እሺ እንዳልሽ ከቻልሽ ግን አትቅሪ?"

"እሺ ሲስተርዬ" አለችና በእምነበረድ በተሠራው ደረጃ ቀስ ብላ መውረድ ጀመረች።

-----//-----

አበጋዝ "ለጥያቄ ትፈለጋለህ" ተብሎ ከቦሌ ዓለም አቀፍ አየር መንገድ ከተወሰደ በኋላ ብዙም ሳያቆዩት፤ ይህ ነው የማይባል ጥያቄ ሳይጠይቁት ከሃያ አራት ሰዓት በኋላ ፈቱት። ሆን ተብሎ እንግሊዝ እንዳይሔድ እንደተደረገ ገብቶታል። ግን ደግሞ በጣምም አልቆጨውም።

ምክንያቱም ዶክተር ሰናይ እሱን ተክቶ ጥሩ ትንተና እንደሰጠ ነግሮታል "...እንደውም በጠበቁት ሳይሆን ባልጠበቁት ሰው፤ እንዲህ መደረጋቸው ጥሩ ነገር ነው..." ሲል ነበር አበጋዝ። ዛሬ አበጋዝ ያደረው ሮዳስ ቤት ስለነበረ አበጋዝና ሮዳስ የተሐድሶውን ተገንጥሎ ራሱን የቻለ ቤተ ክርስቲያን መሆኑን ያወቁት አንድ ላይ ሆነው ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን "ተዋሕዶ እና ተሐድሶ ተብሎ ተከፈለ" የሚል ዜና ከታወጀ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ ያገረሸው ዳግም ውጥረት እና ቁጣ ማንም የሚያቆመው አይመስልም። በማኅበራዊ ድረ ገጾች ዛቻና ማስፈራሪያው ደርቷል።

የነገዋ ኢትዮጵያ ታስፈራለች። ዜናው የተለቀቀው ማታ የሆነው ሆን ተብሎ ነበር። ሮዳስም ሆነ አበጋዝ ተደንቀው ስለጨረሱ የሚሆነውን በመጠበቅ ላይ ናቸው። ከመደነቅ ይልቅ ነገ ምን ይፈጠራል የሚለው ነገር ተናፋቂና አጓጊ ሆኗል።

ከሀሳቡ ያናጠበው ስልኩ ሲጮህ ነው። አበጋዝ ስልኩን ከኪሱ አወጣና የደዋዩን ማንነት ተመለከተ። ሐዊ ነች። አነሳው።

"ሔሎ ሰላም እንዴት አመሸሽ"

"እንዴት አመሸሕ አበጋዝ?" አለች።

"ደህና ነኝ ምን አዲስ ነገር አለ?"



CamScanner

"አዲሱን ነገርማ አይተኸዋል"

"አሁን ስብሰባ ዋናው ቢሮ አለን" አለች

"አሁን?" ብሎ ደነገጠ መልሶ "እሺ ከሮዳስ ጋር ነኝ እመጣለሁ" አለ

"ከሮዳስ ጋር አብራችሁ ኑ ስብሰባው ላይ ሁሉም አባላት እንዲገኙ ይደረጋል"

"እሺ" አለ አበጋዝ።

------//----

ሰንፔር የጨቅላ ሕፃናት ክፍል በር ላይ ቆማለች። አስተኝቶ ማከሚያ ክፍሎቹ በአጠቃላይ ቁልፍ ናቸው። በላያቸው ላይ "በእድሳት ላይ ስለሆነ የጨቅላ ሕፃናት ወደ አራተኛ ፎቅ ተዛውሯል" የሚል ጽሑፍ ተለጥፎበታል፤ ከጨቅላ ሕፃናት አስተኝቶ ማከሚያ ክፍል ጎን ያለውን የሐኪሞች ማረፊያ ክፍል ተመለከተችው። ምንም የተጻፈበት ነገር የለም። ዝግ ይመስላል።

ሰንፔር በሩን ለመክፈት እጇን ስትዘረጋና እጀታውን አዞረችው። በሩ አልተቆለፈም ነበር፤ ወለል ብሎ ተከፈተ። ክፍሉ ጨለማ ነው። ስለዚህ እጇን ሰደደችና በበሩ በኩል ማብሪያ ማጥፊያ ካለ ብላ ዳሰሰችው። የሚጎረብጥ አራት ማዕዘን ነገር አገኘች፤ ማብሪያ ማጥፊያ ነበር። አበራችው። ክፍሉ ውስጥ መጠነኛ ብርሃን በራ። ብርሃኑ ሰማያዊ ነው። ግን በጣም ደብዛዛ ነው።

የክፍሉ ብርሃን ነገሮችን ለመለየት በጣም ያስቸግራል። ሰንፔር ወደ ውስጥ ገባችና በሩን በላይዋ ላይ ዘግታው ቆመች። ዐይኗ ክፍሉን መለማመድ ጀመረ። ከፊት ለፊቷ ወንበርና ጠረጴዛ የተቀመጠ ሲሆን ጠረጴዛው ላይ መጽሐፍት ተቀምጧል።

ሰንፔር ክፍሉን እየተዘዋወረች መመልከት ጀመረች። ክፍሉ በስተቀኝ ጥግ ላይ የሐኪሞች ጋዎን ማስቀመጫ ሳጥን ቆሟል። ሳጥኑ በብረት የተሰራ ሲሆን ቡኒ ቀለም ተቀብቷል። ሳጥኑ ባለ ሁለት ተካፋች እንደሆነ መሀል ላይ ያለው ስንጥቅ ያሳያል። ከበስተላዩ 'ትእምርተ ፈቲው' ወይም 'የኤክስ' ምልክት አለ።

ሰንፔር ፊስአልጎስ የጻፈላትን ለማሰብ ሞከረች "ትእምርተ ፈቲው የወሲብ ግንኙነት ምልክት ቢሆንም ለአቅጣጫ መጠቆሚያና ምስጢራዊ ቦታን ለማመልከትም ይጠቀሙበታል" ብሎ ጽፎላታል። ሰንፔር ልቧ ሲመታ ለክፍሉ ሁሉ የሚሰማ ነው። ትንፋሽ አጠራት፤ እጇን አልቧታል። እንደ መንቀጥቀጥም ይላል።



CamScanner

ሳጥኑን ለመክፈት እጀታውን ይዛ ሳበችው፡፡ አይከፈትም፡፡ ወደ ግራ ወደ ቀኝ አዞረችው፤ ዝግ ነው አይከፈትም፡፡ መክፈቻውን ለቀቀችውና ቁም ሳጥኑና ተደግፋ ማሰብ ጀመረች፡፡ ሰንፔር ድክምክም ስላላት በጣም እየተነፈሰች ነው፡፡

ሰንፔር ከሳጥኑ የላይኛው ጠርዝ ጋር ሔዳ ወደ ጎን ገፋችው፡፡ ሳጥኑን መግፋት ከባድ ቢሆንም ሳጥኑን ሲገፋ '…ሲጢ…ጢጢ…' እያለ በመንቀሳቀስ ተቀምጦበት ከነበረው መሬት ፈቀቅ ማለት ጀመረ፡፡

## ምዕራፍ ፳፬

ሁሉም የፊስአልጎስ አባላት ለስብሰባ ተቀምጠዋል፡፡ ብዙ ሰዎች ፊት ላይ ሐዘንና መከፋት ይታያል፤ ቢሆንም ብዙዎቹ የፊስአልጎስ አባላት ተሐድሶው ዛሬ እንደሚታወጅ አስቀድመው ነበር ያወቁት፡፡ ስለዚህ ቅድመ ዝግጅታቸውን እያደረጉ ስለነበር የዛሬው የተሐድሶ አዋጅ እንደሌላው ሰው አልረበሻቸውም፡፡ ብዙዎቹ የማኅበረ ቅዱሳን አባላት ለፊስአልጎስ ተጨማሪ የሰው ኃይል ሆነው በትጋትና በቆራጥነት እያገለገሉ ነው፡፡

የፊስአልጎስ አባላት ሥራቸውን ጨርሰው ነገ ፍሬውን የሚያዩበት ነው፡፡ ሁሉም ነገር በጥንቃቄ እየተከናወነ ነው፡፡ አሁን ከመንግሥት ጋር ለድርድር የሚቀርቡ ሐሳቦችን እያዘጋጁ ነው፡፡ አምስት ነጥብ ያለው መንግሥትን የሚያስገድድ የአቋም መግለጫ ያወጡ ሲሆን በምትኩም እነሱ የሚገቡትን ግዴታም አስቀምጠዋል፡፡

ከብዙዎች አንደበት የሚደመጠው "የነብርን ጅራት አይዙም ከያዙም አይለቁም" የሚለው ተረት ነው፡፡ ሁሉም የነገውን ሰላማዊ ሰልፍ በጉጉት እየጠበቁ ቢሆንም ሰዉ እንደሚፈለገው ባይወጣስ ብለውም እያሰቡ ነው፡፡ የሚፈለገውን ያህል ሰው በየከተማው ከወጣ መንግሥትን ማስገደድና ተፈላጊውን ተጽእኖ ማምጣት እንደሚቻል አምነዋል፡፡

ሌላው የተስማሙበት ነገር ሰልፉን የጠራው ማኅበረ ቅዱሳን ነው እንዲባልና ኃላፊነቱን እንዲወስድ ነው፡፡ ብዙዎቹ የማኅበረ ቅዱሳን ስራ አስፈጻሚ አባላት እስር ቤት ስላሉ አዲስ ኮሚቴ ተዋቅሮ የማኅበረ ቅዱሳን ጊዜያዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚል እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ ዋናው ምክንያት ግን ማኅበረ ቅዱሳን በሲኖዶስም ሆነ በመንግሥት ሕጋዊ እውቅና ስላለው በዚያ መንገድ መሄዱ ይበልጥ ነገሩን ያጎላዋል ብለው ስላመኑ ነው፡፡

---------//----------

ሰንፔር ከፊት ለፊቷ ያለው ግርግዳ ላይ ክብ ጥቁር ነገር አየች፡፡ የሚሽከረከር የምስጢር ቁልፍ መዝጊያ ይመስላል፡፡ እላዩ ላይ ልክ እንደ ግርግዳ ሰዓት ከአንድ እስከ አስር ቁጥር የተጻፈ ሲሆን አስራ ሁለት ቁጥር ላይ የመደመር ምልክት አለበት፤ ቀጥሎ ሦስት ቁጥር ላይ የማካፈል ምልክት አለ፤ ስድስት ቁጥር ላይ የማባዛት ምልክት አለ፤ ከስድስት ቀጥሎ ዘጠኝ ቁጥር ላይ የመቀነስ ምልክት አለ፡፡

ሰንፔር ፊት ለፊቷ የምታየው ነገር አስገርሚታል፡፡ ፊቷ ላይ በጣም መደነቅና ጉጉት ይታያል፡፡ ሰዓት መሰሉን ነገር ዝም ብላ ልክ የሰዓት ደቂቃ ቆጣሪ እንደሚቆጥረው አዞረችውና አፍጥጣ ግርግዳውን ተመለከተችው፤ ምንም የመጣ ነገር የለም፡፡

ዐይኗ ፍጥጥ አለ፡፡ እጇን አልቧታል፤ የልቧ ምት ፍጥነቱም ሆነ ድምጹ በጣም የጨመረ እየመሰላት ነው፡፡ ሰንፔር ማሰላሰሏን ቀጥላለች፡፡ ዩቶጵያ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ አራቱን የሒሳብ ቀመር ምልክቶች አይታዋለች፡፡

በትክክል ፊስአልጎስ ስለ አራቱ የሒሳብ መሰረታውያን አብራርቶላታል፡፡ "መደመር፣ መቀነስ፣ ማካፈልና ማባዛት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሊቃውንት ዘንድ 'አርባዕቱ ትእምርተ ቀመር' ይባላል፡፡" ሰንፔር የፊስአልጎስን ጽሑፍ ማስታወስ ጀመረች፡፡

"መደመር (+) የአዳም ምልክት አድርገን እንወስደዋለን፡፡ አዳም የተፈጠረ እንጂ ያልተወለደ መሆኑ ነገር ግን ከእሱ ሔዋን መፈጠሯ ሁለት ሆኖ እንደ አንድ መፈጠሩን ያሳየናል፡፡ መቀነስ (-) ደግሞ ከአንዱ አዳም ጎን ቀንሶ ሔዋንን ስለፈጠራት በመቀነስ ትመሰላለች፡፡ መቀነስ ማለት አንድ ከሆነ ነገር ላይ የተቀነሰ ስለሆነ ነው፡፡ ከዚያም አዳምና ሔዋን ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሏት ተብለዋል ይህንንም በማባዛት (×) ምልክት ይገለጻል፡፡ ማካፈል (÷) የሞት ምልክት ነው፡፡ አዳም መሬት ነህ ወደ መሬት ትገባለህ መባሉን እውነት ነው፡፡ ሰው ሲሞት ነፍስና ሥጋ ተለያይተው ለሁለትና ሁለት ቦታ የሚካፈሉበት ነው፡፡ ሥጋ ወደ መሬት ነፍስ ደግሞ ወደ ሰማይ ትሄዳለች፡፡" ፊስአልጎስ የጻፈላት ነገር አንድ በአንድ ታወሳት፡፡

ስለዚህ ክቡን ነገር ወዴት ማዞር እንዳለባት ማሰብ ጀመረች፡፡ 'አዳምን መሰረት አድርገው ነው የቀረጹት፡፡' አለች ለራሷ በሆነ ሹክሹክታ፡፡ አባቷም 'ዳግማዊ አዳም ኢየሱስ ነው፤ የአዳምና የኢየሱስ ስም በቁጥር ሲሰላ እኩል ነው' ብሎ አስረድቷታል፡፡ ሰንፔር ፈገግ አለችና እጇን ወደ ክቡ ሰዓት መሰል ነገር ሰደደች፡፡

ሰንፔርን እጇን ሰድዳ ቀስ አድርጋ ክቡን ሰዓት መሰል የምስጢር መቆለፊያ ዝም ብላ በፍጥነት አዙራ ጨረሰችና ከግርግዳው ራቅ ብላ መመልከት ጀመረች፡፡ ምንም የተፈጠረ ነገር የለም፡፡ "አዳም ነው መሠረቱ፤ የአዳም ሕይወት መደመር ወይም ሰው መሆን ነው፡፡ ከዚያም መቀነስ ወይም ከራስ ቀንሶ ሔዋንን መፍጠር፤ ማባዛት ማለት የአዳምና የሔዋን ሲዋሐዱ ይባዛሉ፤ የመጨረሻው ቃሉ እንዲፈጸም 'አፈር ነበርክና አፈር ትሆናለህ' የሚለው ቃል እንዲፈጸም መሞት ነው፤ ይህኔ ይካፈላል፤ አፈር የሆነው ሥጋ ይበሰብሳል፤ እስትንፋስ የሆነው ነፍስ ወደ ፈጣሪው ይሄዳል" አለችና ዳግም ወደ ግርግዳው ቀርባ ማዞር ጀመረች፡፡

ሰንፔር እጇ እየተንቀጠቀጠ ነው፡፡ በጥንቃቄ ቀስ ብላ ከአስራ ሁለት ቁጥር ጀምራ ወደ ዘጠኝ ቁጥር አዞረችውና ዘጠኝ ላይ ስትደርስ ይብሱኑ እጇን ቀስ አደረገችውና ዘጠኝ ላይ ሙሉ ለሙሉ ሳታቆመው ያዝ አደረገችው፤ ግጥም ብሎ ሲገባ ተሰማት፡፡ ከዚያም ማዞሪያውን ሳትለቅ ይዛው መውረድ ጀመረች፤ ስድስት ቁጥር ላይ ስትደርስ ቀስ አደረገችው፤ ማባዛት ላይ ልክ እንደ ቅድሙ ሲገባ ተሰማት፤ እጇን ሳትለቅ



CamScanner

ቀጠለችና ሦስት ቁጥር ላይ ጠንቀቅ ብላ አስገባችው፤ ገባላት ፈገግ ብላ ማዞሪያውን ለቀቅችውና ግርግዳው አንድ ነገር ቢሆን ብላ ጠበቀችው።

ምንም ነገር አልተፈጠረም። ምንም። ሰንፔር ግራ ገባት በትክክል ማዞሪያው በቦታው ሲገባላት ተሰምቷታል። "ምንድነው የሳትኩት?" ብላ ራሷን ጠየቀች። ማሰብ ጀመረች። "ምንድነው የቀረኝ?" ብላ ጭንቅላቷን በቀኝ እጇ አሻሸችው። ዐይኗን እንደመጨፈን ብላ ዳግም ማሰብ ጀመረች፤ አንድ ነገር ወደ አእምሮዋ ብልጭ አለላት። 'በኢየሱስ ሥም!' ብላ ጮኸች።

'በትክክል አዳም ሞቶ አልቀረም ኢየሱስ መጥቶ ከሞት አስነስቶታል። ዳግማዊ አዳም ሲመጣ ነው አዳም ትንሳኤን ያገኘው' አለች። 'ስለዚህ አሥራ ሁለት ላይ ጀምሮ አሥራ ሁለት ላይ ያቆማል፤ በአዳም ጀምሮ በኢየሱስ ይፈጸማል' አለች። ሰንፔር ሳቅ አለች።

ሰንፔር በፈገግታ ታጅባ በልበ ሙሉነት በጥንቃቄ ማዞር ጀመረች። ሦስት ቁጥር ላይ ስትደርስ ትንሽ ረገብ ብሎ የነበረው ልቧ ዳግም መምታት ጀመረ። በጥንቃቄ ማዞሪያውን ይዛ አሥራ ሁለት ቁጥር ላይ አደረገችና ቆም አለች። የቆመችበት መሬት ነቅነቅ ሲል ተሰማት። ሰንፔር ራቅ ብላ ማየት ጀመረች።

ሙሉ ለሙሉ ቁምሳጥኑ ተቀምጦበት የነበረው ግርግዳ ወደ ላይ እንደ መጋረጃ ተገለጠ። ሰንፔር ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ቢሆንም ለመራመድ ሞከረች። እግሯ ግን እስርስር እያለ፤ አንዱ ከአንዱ ይጋጭባት ጀመረ። እንደ ምንም ራሷን ለማረጋጋት እየሞከረች ወደ ተከፈተው ግርግዳ ገባች።

ግርግዳው ወደ ቦታው ከተመለሰ በኋላ እንደ ሊፍት ወደ ታች ይሰርግ ጀመር። ሰንፔር ራሷን ልትስት እየመሰላት ነው። ቀኝ እጇን እንስታ ደረቷ ላይ አደረገችው። ይመታል። ልቧ ከደረቷ ፈንቅሎ ሊወጣ እየመሰላት ነው። ላብ ከመላ ሰውነቷ ይመነጭ ጀመረ። አፍንጫና ግንባሯ አለወትሯቸው ላብ አስምጧቸዋል።

ሊፍቱ መሬቱ ላይ አረፈና ነጭ ቀለም የተቀባው ግርግዳ ከጎንና ከጎን ተከፈተ። ከፊት ለፊቷ ልክ የጨቅላ ሕፃናት ማከሚያ ክፍል እንዳለው ሰማያዊ ደብዛዛ ብርሃን ይታያል። ዐይኗ በትክክል ለማየት ስለተሳነው ለሰከንድ ጭፍን አደረገችው።



CamScanner

## ምዕራፍ ፳፭

## አዲስ አበባ

አዲስ አበባዎች እንደፎከሩት መስቀል አደባባይ መውጣት የጀመሩት ገና ሳይነጋ ነው። መፈክር ያነገቡ፣ የኢትዮጵያን ባንዲራ ያንጠለጠሉ፣ ብዙዎቹ ባንዲራዎች ኮከብ የሌላቸው አረንጓዴ፣ ቢጫ ቀይ ብቻ ናቸው። አብዛኛዎቹ እንስቶቹ ነጠላ ለብሰዋል። በየትኛው ፍጥነት እንደ ተዘጋጀ ባልታወቀ ሁኔታ 'አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንድ ጥምቀት፣ ተዋሕዶ ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ እግዚአብሔር ይተወኝ፣ ተዋሕዶ እናቴ መቼም አትታደሽም፣ ማርያም ፊደል ናት ኑ ተማሩ፣ ኢየሱስ ፈራጅ ማርያም አማላጅ...' የሚሉ ጥቅሶችን ያሉበት ቲሸርት የለበሱ፣ በትላልቅ ባነር ላይ የተጻፉ፣ በወረቀት ተጽፈው በብረትና በእንጨት የተንጠለጠሉ መፈክሮች ይታያሉ።

አብያተ ክርስቲያናት ከየደብሩ ደወል እያሰሙ ነው። ሰዎች ከየአቅጣጫው ወደ መስቀል አደባባይ ይተምማሉ። አዲስ አበባ ታስፈራለች። በቁጣ የሚንተገተጉ ወጣቶች በአደባባዩ ይታያሉ። የጸጥታ አስከባሪዎች ሙሉ ለሙሉ ትጥቅ ለብሰው ከአምስቱ አንዱ አስለቃሽ ጭስ ይዘው ከባድ የጦርነት ቀጠና ውስጥ ያሉ ይመስላል።

መስቀል አደባባይ በፍጥነት ነገሮች እየተቀያየሩ ነው። ሙሉ ለሙሉ ነጭ ልብስ የለበሱ ተባዕትና እንስቶች በገና እየደረደሩ ከእስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን በሰልፍ ወጡ። የበገናው ድምጽ ልብን ትርትር የሚያደርግ አንዳች ነገር አለው። ሰልፉን የሚመሩት ወንዶች ከለበሱት ነጭ በነጭ የአገር ባህል ልብስ ላይ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ የተጠለፈበት ጃኖ ትከሻቸው ላይ ጣል አድርገው መስከት እየነፉ ወደ ሕዝቡ መቀላቀል ጀመሩ። ሰልፉ ላይ የነበረው ሰው በገና ደርዳሪዎቹን ሲያይ በእልልታ፣ በፉጨት፣ በጭብጨባና በጩኸት አካባቢውን ያቀልጠው ጀመር።

በገና ደርዳሪዎች በገናውን መደርደር ሲጀምሩ፣ የአካባቢው ጩኸት ተግ አለና በአርምሞ አንዳች የሚነዝር ስሜት ያለውን በገና ድርደራ ማዳመጥ ጀመሩ። በገና ደርዳሪዎች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታዋቂ በገና ደርዳሪ የሆኑትን የአለሙ አጋን በገና መደርደር ጀመሩ። የሰልፉ ታዳሚዎች በአርምሞ በገናውን ማዳመጥ ጀመሩ።

"...ጎጃም ተሸምቶን ይቀናል በኔ ምድር

እየከዳ እምቢ አለ ወዳጅና ምድር

ያንተን ሥራ ያንተን ክብር

ማን ይመራመር

አለሀም እንዳልል እንዲህ ይደረጋል

የለሀም እንዳልል ይመሻል ይነጋል

ያንተን ሥራ ያንተን ክብር

ማን ይመራመር

እባክህ አምላኬ ስጠኝ መስታወት

የሰው ሥራ ጥዬ የኔን አይበት..."

-----//-----

## ትግራይ

መቀሌ ብቻ ሳይሆን አድዋ፣ አዲግራት እና አክሱም በሰላማዊ ሰልፍ እየተናጡ ነው:: "ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ያህል የድጋፍ እንጂ የተቃውሞ ሰልፍ ስታስተናግድ እምብዛም አልታየችም" እየተባለ በሌላው ኢትዮጵያዊ ስትተች የነበረችው ትግራይ ዛሬ የሃያ አምስት ዓመት ብሶቷን የምታሰማ ነው የሚመስለው::

ከአራቱ የትግራይ ዋና ዋና ከተሞች በአይነቱ ለየት ባለ ሁኔታ መቀሌ ብሶትና ቁጣ የሞላው ሕዝብ በአደባባዩ ፈስሷል:: በሰማዕታት አደባባይ በአልባሶ ሹሩባቸው ላይ ወርቃቸው አድርገው፣ የሐበሻ ቀሚሳቸውን ለብሰው እጅና እግራቸውን እንሾሽላ ተቀብተው ብዙ እንስቶች ይታያሉ:: ወንዶቹ ጉራማይሌ የለበሱ ሲሆን ብዙዎች ሽመል የያዙ ናቸው::

ጥቅስና መፈክር ያለበት ቲሸርት የለበሱ፣ መፈክር የተጻፈበት እንጨት ወይም ብረት ያንጠለጠሉ ሰዎች በብዛት ይታያሉ:: የመቀሌው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ እንደ አዲስ አበባው ሙሉ ለሙሉ በታጠቀ፣ ለመተኮስ ትንሽ ኮሽታ የሚጠብቁ ወታደሮች አይጠበቅም:: መቀሌ ፊታቸው እንደ እሳት የሚጋረፍ ወታደር ቢፈለግ ማግኘት ከባድ ነው:: በተቃራኒው ሰልፉ ሲስተጓጎል ፈገግ ብለው በትህትና "እባካችሁ መስመራችሁን በአግባቡ ትይዙ?" እያሉ በትህትና መልክ የሚያስይዙ ፖሊሶች ናቸው:: ሰላማዊ ሰልፉ ላይ ይበልጥ ጎልቶ የሚሰማው "ተዋሕዶ" የሚለው መዝሙር ነው::

"ተዋሕዶ ሃይማኖቴ

የጥንት ነሽ የእናትና አባቴ

ማሕተቤን አልበጥስም

ትኖራለች ለዘላለም…"

-------//----

## ጎንደር

ይኸኛው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ጎልቶ የሚታየው የኢትዮጵያ ባንዲራ ነው። አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለም ያለው ደማቁ ባንዲራ እንደ ችቦ እጅብ ብሎ ከሰማዩ ላይ ሲቀዝፍ ይታያል። ባንዲራው በእንጨት ላይ ብቻ ሳይሆን በረዥሙ ተሰፍቶ ሰላማዊ ሰልፍ ከወጡ ሰዎች አናት ላይ ለብሰውት የሚሄዱ ሁልቆ መሳፍርት ሰዎች ይታያሉ።

ከባንዲራ እና ከመፈክር ሌላ በአቡጀዴ ጨርቅ የተሠራ የኢትዮጵያ ካርታ ይታያል። ካርታው ኤርትራን የጨመረ ሲሆን አማራ የሚባለው ክልል የፌደራል መንግሥቱ ከሚለው በተለየ ሁኔታ በኢትዮጵያ ላይ ሰፋ ብሎ ይታያል። ከዚያም በላይ ሽጉጥ የታጠቁ ብዙ ወንዶች እየፎከሩና እየሸለሉ ነው። በመሀል በመሀል ወደ ሰማይ ደግነው ለረዥም ሰዓት የሚተኩሱም አሉ።

ይኸኛው ሰላማዊ ሰልፍ መልኩን የቀየረ ይመስላል። በብዛት የሚዘመረው 'አንመካም በጉልበታችን እግዚአብሔር ነው የኛ ኃይላችን ነው' የሚለው መዝሙር ነው። ሌላው ሰልፉ ላይ ጎልቶ የሚሰማው የኦርቶዶክስ ዘማሪ የሆነው የሊቀ መዘምራን ይልማ ኃይሉ ነው። መዝሙሩ 'ትንሳኤሽን ያሳየን!' የሚለው ነው።

"ትንሳኤሽን ያሳየን ትንሳኤሽን ያሳየን

ውዲቷ ኢትዮጵያ አገረ እግዚአብሔር

ትንሳኤሽን ያሳየን ትንሳኤሽን ያሳየን

የአባቶች ዘመን ተመልሶ እንድናይ

አለን ኢትዮጵያ ሆይ የፍቅር ራዕይ

ትቢያሽን አራግፈሽ ሀዘንሽን ሽረሽ

ዳግም ትነሻለሽ አገሬ እንደ ድሮሽ…"

---------//------

## አዳማ

የአዳማው ሰላማዊ ሰልፍ የአዲስ አበባውን ይመስላል። ብዙ ወጣቶች በኦሮምኛና በአማርኛ መፈክር የተጻፈበት ቲሸርት ለብሰዋል። የቤተ ክርስቲያን ደውሎች ከየአካባቢው ይሰማሉ። ነጭ ለብሰው በገና የሚደረደሩ ወንድና ሴቶች ከፊት ለፊት በሰዎች ታጅበው ይታያሉ።

የአዳማው ሰልፍ ላይ በተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ በጉልህ የሚታወቀው "ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ ማነው?" የሚለውን መዝሙር ሴት ወንድ፤ ወጣት አዛውንት ሳይሉ በሕብረት እየዘመሩት ነው።

----//---

## ደብረ ብርሃን

ከደብረ ብርሃን ሥላሴ እስከ ጠባሴ ያለው መንገድ በሰዎች ተጣብቧል። ሽመላቸውን ከፍ ዝቅ እያደረጉ የሚጨፍሩ፤ ጠመንጃ ትከሻቸው ላይ ያነገቱ ቁምጣ እንዲሁም ቦላሌ ሱሪ የለበሱ ወጣትና ጎልማሳዎች በብዛት ይታያሉ። ነጭ ነጠላ የለበሱ የደብረ ብርሃን ዩንቨርስቲ የግቢ ጉባኤ ተማሪዎች ከአካባቢው ሰው ጋር ሆነው መዝሙር በሕብረት እየዘመሩ ከጠባሴ ተነስተው በሬሳ ድልድይ ላይ ደርሰዋል። የአብዛኛውን ሰው ቀልብ የያዘው ግን በደቦ ሆነው፤ ሽመላቸውን ከፍ ዝቅ እያደረጉ፤ በእግራቸውን መሬቱን እየደቀደቁ የሚዘፍኑ ወጣቶችን ናቸው።

"እያሃ የተዋሕዶ ነን በለው!

እያሃ የሥላሴ ነን በለው!

እያሃ የዘርዐ ያእቆብ ነን በለው!

እያሃ ቤተ ክርስቲያንን አልሰጥም በለው..."

---------//------

የኢትዮጵያ ጠዋት ክብድ ብሏል። በእርግጥ የጠዋቱ ፀሐይ ለሰስ ያለ ነው። ሰማዩም ጥርት ያለ ሰማያዊ። በዚህ ሰልፍና በሰልፈኞቹ ቁጣ ውስጥ ሆኖ ለታዘበ ሰው ግን የሚያስፈራ ነገር አለው። ዛሬ የያዘው ጭንቀት ሲታይ ቀኑ ሃያ አራት ሰዓት አይመስልም። እያንዳንዷ ደቂቃ ምን ልትወልድ እንደምትችል ማንም አያውቅም። ለሰልፍ የወጡት ተመልሰው ወደ ቤት የሚገቡ አይመስሉም። ሌሎች ከተሞችም የሰልፍ ጥሪውና የሕዝቡ ቁጣ ከፍ እያለ ነው።



CamScanner

አርባ ምንጭ፣ ባህርዳር፣ ወሎ፣ ደብረ ማርቆስ፣ ዝዋይ፣ ደብረዘይት… ለቀጣዩ ቀን ሰልፍ እየተጠራ ነው፡፡ ሰበታ፣ ሐዋሳ እና ሻሸመኔ ግጭት ተነስቷል፡፡ "ቤተ ክርስቲያናችንን ለማንም አሳልፈን አንሰጥም" ባሉና "እንታደሳለን ቤተ ክርስቲያኗን የእኛም ነች" ባሉ ሰዎች መካከል ትልቅ ግጭት ተነስቷል፡፡ አራት ሰዎች የሞቱ ሲሆኑ፣ ከሟቾቹ ሦስቱ ሻሸመኔ አንዱ ደግሞ ሰበታ ነው፡፡ ከሐዋሳ አካባቢ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ሐዋሳ ሪፈራል ሆስፒታል ገብተዋል፡፡

## ምዕራፍ ፳፮

## አዲስ አበባ-ሕቡዕ የፊስአልጎስ ድርጅት

ሰንፔር ከመሬት በታች በተገነባው ሕቡዕ የፊስአልጎስ ድርጅት ውስጥ ለመላው ኢትዮጵያውያን ክፍት የሆነው የዩቶጵያ ክፍል ውስጥ ነች። ትልቁ የዩቶጵያ አዳራሽ ላይ በትልቁ "ኢትዮጵያውያንን ኢትዮጵያ ውስጥ መውሰድ ሳይሆን፤ ኢትዮጵያን ኢትዮጵያውያን ውስጥ እንውሰድ" ይላል።

ትላልቅ የምርምር ክፍሎች ተዘዋውራ የጎበኘች ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ያሏትን መጽሐፍትና ቅርሶች ለመጠበቅ ተብሎ የተገነባው ትልቅ አዳራሽ ውስጥ ያየቻቸው ቅርሶች፤ ብዛትና ውበት ዐይኗን እንዳትነቅል አድርጋት ነበር። በተለያዩ ዘመናት የተጻፉ ብራና መጽሐፍት፣ የተለያዩ ዓይነት መስቀሎች፣ ዋንጫዎች፣ የክህነት ልብሶች፣ የነገሥታት አልባሳት፣ መቋሚያዎች፣ ብራና መጽሐፍት... በመልክ በመልክ ተደራጅተው ይታያሉ።

ሌላው በጣም አስገራሚ የሆነባት ነገር፤ ሞተዋል የተባሉት ሰዎችን ማየቷ ነው። ሰንፔር የምታደርገውን አጥታለች። በተለይ አባቷ ሁሌ የሚያደንቃቸው፤ ከአፉ ነጥሏቸው የማያውቀው ቄስ ጉዲና ቱምሳን ማየቷ አስገርሟታል። ቄስ ጉዲና ቱምሳ በዝግባ እንጨት በተሰራ መቀመጫ ላይ ቁጭ ብለዋል። ከጎናቸው የመስቀል ቅርጽ ያለው መቋሚያ እንጨት አለ። ፊታቸው ትንሽ የከሳ ሲሆን፤ ጥንካሬ ይነበብታል። ሰርሳሪና ፊጣን ዐይኖቻቸው ሰንፔር ላይ ከወዲያ ወዲህ ከብለል ከብለል እያሉ የሚመረምሯት ይመስላል።

ቄስ ጉዲና ቱምሳ የመካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ነበሩ። ሰንፔር ስለ ቄስ ጉዲና በጣም በብዛት ታውቃለች። አባቷም ሆነ ሌሎች የወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያን መምህራን ሲጠቅሷቸው በደንብ ታስታውሳለች። ቄስ ጉዲና ቱምሳ የኦርቶዶክስ፣ የካቶሊክ እና የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በሚያግባቧቸው ጉዳዮች እንዲሠሩ ብለው በ1969 ዓ.ም. 'የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መተባበር ጉባኤ' የሚል ተቋም መስርተው ነበር።

ቢሆንም በጊዜው የነበረው የደርግ መንግሥት በቄስ ጉዲና ቱምሳ እንቅስቃሴና በየአብያተ ክርስቲያናት በመገኘት፤ በመንግሥት ላይ በሚያደርጉት የሰላ ትችት መንግሥት ጥርስ ውስጥ ገቡ "...በተለይ ቤተ ክርስቲያን በምታምነው እውነትና በቄስ አካልነት መካከል አንዳች ማመቻመች ሆነ እርቅ ሊኖር እንደማይገባ ግልጽ መሆን አለበት። ከዚህም የተነሳ ቤተ ክርስቲያንና የማርክሲዝም ፍልስፍና ከቶም አብረው መጓዝ የሚችሉበት ፈለግ የላቸውም። የማቴሪያሊዝም አስተሳሰብ እና የኑሮ ዘይቤ ከሚጨብጥ አሳብ ጋር ብቻ የተጎዳኘ እና የፈለቀ ሲሆን የቤተ ክርስቲያን

ሕልውና ግን ከላይ ከመጣው ከእግዚአብሔር መንፈስ ነው..." የሚለው ንግግራቸው ሃይማኖትን 'ጸረ ሳይንስ ሕዝብን የምታደነዝዝ' እያለ ለሚከስሰው ደርግ የሚጎረብጥ ነበር።

ቄስ ጉዲና ቱምሳ ለአገልግሎት ሐምሌ 21 ቀን 1971 ዓ.ም. ኡራኤል አካባቢ የሚገኘው መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት ባለ ስልጣኖች ከተወሰዱ በኋላ በድጋሚ ሊታዩ አልቻሉም። ኢሕአዴግ ደርግን ጥሎ ኢትዮጵያን ከተቆጣጠረ በኋላ ሰኔ 21 ቀን 1984 ዓ.ም. ሞታቸው በይፋ ታውጇል። ሰንፔር የምታውቀው ይህን ታሪክ ብቻ ነው። ስለዚህ እሳቸውን ማየት ለእሷ ትንግርት ነበር።

ሰንፔር በዚህ ተገርማ ሳታበቃ በደርግ የተገደሉትን ሌላኛው ጳጳስ ደግሞ አየች። እኚህ ጳጳስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሁለተኛው ርዕሳነ ሊቃነ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ቴዎፍሎስ ናቸው። በአግራሞት እየተመለከተቻቸው ነው። በጣም ረዥምና መልከ መልካም ናቸው። ፊታቸው ላይ ያለው ጺም ሙሉ ለሙሉ ነጭ ነው። የፊት ቆዳቸው ተሸብሽቦ እርጅና ይታይበታል። ተቀምጠው እንኳ ትከሻቸው ላይ ጎበጥ ማለታቸው ያስታውቃል።

ሰንፔር በሁሉ ነገር እየተገረመች ነው። እጇን አፏ ላይ ጭና በተደጋጋሚ "በኢየሱስ ስም! በኢየሱስ ስም!" ትላለች። ከአባቷ አፍ የማይጠፉትን ቄስ ጉዲና ቱምሳን አየች ከሮዳስ አፍ የማይጠፉትን አቡነ ቴዎፍሎስን ማየት ደግሞ ሌላ ትንግርት ሆኖባታል። አቡነ ቴዎፍሎስንም እንደ ቄስ ጉዲና ሁሉ ደርግ ገድሏቸዋል ነበር የተባለው።

አቡነ ቴዎፍሎስም ደርግ እንዲቆጣ እና ኃይሉን እንዲጠቀም ያደረገው ግንቦት 17 1967 ዓ.ም. "...ምእመናን ሆይ!... ኅብረተሰቡ ውስጥ በደል የሚደርሰው የኅብረተሰቡ ሥነ ሥርአት የቤተሰብን ሥነ ሥርዓት አልመስል ሲል ነው። ለኢትዮጵያ ከሌላ የመጣ ሳይሆን በመጠኗ በፍላጎቷ የተሠራ ሥርዓት ለማውጣት ሁላችንም እንትጋ። ጥረቱም በበለጠ ፍሬ እንዲያፈራ በያለንበት ድምጻችንን ከፍ አድርገን እንጸልይ። እያንዳንዱ ለአቅመ ውክልና የደረሰ ኢትዮጵያዊ የሚፈልገውን ሥርዓት እስካልተገነባ ድረስ፤ የሚቋቋመው የአስተዳደር ሥርዓት በምንም ዓይነት ኢትዮጵያዊ ስለማባይል፤ ዘላቂ አስተዳደርን ለማቋቋም ያለው ዘመቻ መላ ኢትዮጵያን እንጂ እንደ ሌሎች ዘመቻዎች ለወታደሮች ብቻ የሚተው አይደለም..." የሚለው ንግግራቸው ነው።

"ከዚህ ቀን በኋላ ደርግ ወደ ሞት ቀጠና የሚወስድበት ነገር ከጎነጎነባቸው በኋላ የካቲት 9 1969 ዓ.ም. በቁጥጥር ስር ዋሉ። ከዚያ በኋላ ከእስር ቤት ጠፉ ተባለ፤ መልሰው ደግሞ ተያዙ ከተባለ በኋላ አቡነ ቴዎፍሎስን እዚህ ነበሩ ብሎ በትክክል የተናገረ አልተገኘም።"

ለሰንፔር ይህን ታሪክ የነገራት ሮዳስ ነበር። ከሮዳስ አፍ የማይጠፉት አቡነ ቴዎፍሎስ ሁሌ እንዳደነቃቸው ነው "...ታውቂያለሽ አቡነ ቴዎፍሎስን ብዙ ሰዎች 'እናሽሽዎት?' ብለዋቸው ነበር እሳቸው ግን 'አባቶቼ ሐዋርያትና ሰማዕታት ስለ እውነትና ስለቀናች ሃይማኖታቸው ሲሉ በሰይፍ ተቆርጠው፣ በገመድ ታንቀውና በእሳት ተቃጥለው በሰማዕትነት ተሰውተዋል። እኔም ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ክብር ሲባል እስከ ሞትም ድረስ ቢሆን መከራና ስቃይ ከመቀበል በቀር ወደ ኋላ የምልበት ምክንያት የለም...' ብለዋል አይደንቁሽም ሰን? በጣም ነው የሚደንቁት" ይላል የውስጡ አድናቆትና ክብር በቃላት ለመግለጽ እየከበደው።

------//------

ምቹ በሆነው ሶፋ ላይ አቡነ ቴዎፍሎስ እና አቡነ መርቆሬዎስ በጥሞና እያወሩ ነው። ከአቡነ ቴዎፍሎስ ይልቅ አቡነ መርቆሬዎስ በጣም ያረጁና የደከሙ ይመስላሉ። አቡነ ቴዎፍሎስ ፊት ላይ አይበገሬነት ይታያል። እርጅና ቢጫጫናቸውም ሰውነታቸው ግን አልደካከመም።

አቡነ ቴዎፍሎስ በትረ ሙሴያቸውን በተቀመጡበት ጫን ብለው ተደገፉትና "...ቅዱስነትዎ እርስዎ በሕይወት መትረፍዎ መልካም ነው፤ አሁን የሚያስፈልገው የቤተ ክርስቲያኗን አንድነት መመለስ ነው። ዋናው በእርስዎ ምክንያት የተከፈለችውን ቤተ ክርስቲያን ዳግም ለመመለስ መሞከርዎ ነው። የተቀረውን እግዚአብሔር ይረዳናል።"

አቡነ መርቆሬዎስ ጀርባቸውን መቀመጫቸው ላይ አደላዱና፤ ስልል ባለ ድምጽ መናገር ጀመሩ "እውነት ነው ቅዱስነትዎ ስህተት ተሰርቷል። ሰማዕትነት ከአባቶቼ ከነ አቡነ ጴጥሮስ ከእርስዎ መማር ነበረብኝ..." አቡነ ቴዎፍሎስ ስልል ያለው የአቡነ መርቆሬዎስ ንግግር አልተሰማቸውም ስለዚህ ጆሯቸውን ወደ አቡነ መርቆሬዎስ አስጠግተው ማዳመጥ ጀመሩ።

አቡነ መርቆሬዎስ ሲናገሩ ድክም ይላቸዋል። ስለዚህ ለሰከንዶች ዝም ይሉና ንግግራቸውን ይቀጥላሉ "ግፉን ቻል አድርጌ፤ መስዋዕትነቱን ይሁነኝ ብዬ ተቀብዬ የቤተክርስቲያንን ደህንነት መጠበቅ ነበረብኝ። ተሳሳትኩ።"

"ቅዱስነትዎ እንደሱ አይበሉ። እንኳን እኛ ጴጥሮስም ፈጣሪውን ክዷል። የሰው ልጅ ይፈራል፣ ይደክማል፣ ይዝላል... ስለዚህ ለምን ተሳሳተ ሳይሆን መቼና እንዴት ንስሐ ይግባ የሚለው ነው። ስለዚህ ንስሐ መግባቱ ነው ዋናው ነገር። ይኸው በቤተ ክርስቲያን ላይ የተወረወረውን ሰይፈ ሊመክቱ አይደል? እግዚአብሔር እርሶን የፈለገው ለዚህ ቀን እንደሆነ ማን ያውቃል? ስለዚህ አይቆጩ። እሱ በፈቀደ ጊዜ ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ጋሻ አድርጎ ሊያቆምዎ ነው።" አሉና አቡነ ቴዎፍሎስ ቀና ብለው አቡነ መርቆሬዎስን ተመልክተው እንደገና ለሰስ ባለ ድምጽ

"ቅዱስነትዎ ዛሬ አሜሪካ ላለው ሲኖዶስ የአንድነት ጥሪ ያቅርቡ እንጂ ውግዘት አያስተላልፉ።"

"አይ አላስተላልፍም። ቢቻለንማ ይቅር ብንባባል ነው የሚሻለን፤ ኢትዮጵያ ያለው ሲኖዶስ እንዴት እንደሚቀበለኝ ራሱ እኔም አላውቅም። መንግሥትስ ይተወኛል ብለው ነው? ግን ይሕን ፈርቼ ሃያ አራት አመት ባከንኩ አሁንስ የምፈራውም ነገር የለኝም። እግዚአብሔር ጸሎቴን ቢሰማኝ አላማዬ የቤተ ክርስቲያኗን አንድነት መመለስ ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ ብሞትም አይቆጨኝ።" አሉ አቡነ መርቆሬዎስ ትክዝ ብለው መሬት መሬቱን እያዩ።

-------//----

ቄስ ጉዲና ቱምሳ በራሳቸው የመኖሪያ ክፍል ውስጥ ነው ያሉት። ዐይናቸው ላይ የንባብ መነጽር ሰክተዋል። ሰማያዊና ነጭ ሸንተረር ያለው ሸሚዝ አድርገው ጥቁር ካፖርት ደርበዋል። ሳሎን ቤታቸው በመጻሕፍት ስለ ተሞላ መኖሪያ ቤት ሳይሆን ቤተ መጻሕፍት ነው የሚመስለው።

ሰንፔር በቄስ ጉዲና ፊት እያለቀሰች ነው። እሳቸው ፊት ላይም ከባድ ሐዘን ይነበባል። እንባቸው ሳያስቡት ከዐይናቸው ይፈስ ጀመር። ሰንፔር ስለ አባቷ አንስታ እያወራች ነበር ሳግ ተናንቆ ያስቆማት።

"አይዞሽ ልጄ አባትሽ የተቀበለው ሰማዕትነት ነው። እሱ ጻድቅ ነው። ፓስተር ናፍያድ ስለ ቸርች ስለ ምእመናን አንድነት፤ አብሮ ስለ መኖር የተከፈለ መስዋእትነት ሳይሆን ራሱ መስዋዕት ነው። ስለዚህ የዚህ ሰው ልጅ ስለ መሆንሽ መኩራት ነው እንጂ ማዘን የለብሽም።" ቄስ ጉዲና ከተቀመጡበት ሁለት ጊዜ ቁጭ ብድግ ብለው እንደምንም ተነሱና ጎተት ብለው ሄደው ሰንፔርን እቅፍ አድርገው እንባዋን ይጠርጉላት ጀመር። ሰንፔር አባቷን ያገኘች ይመስል፤ ቄስ ጉዲና እቅፍ ውስጥ ሽጉጥ አለች።

"አባትሽ እንደ ማንም ሰው ኮርቶ መኖር ይችል ነበር። ስለ እውነት፣ ከሌሎች ጋር አብሮ ለመኖር ሲል ነው ራሱን የሰዋው። ይሄ ደግሞ ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር ተከባብሮና በሰላም ለመኖር ያለንን ፍላጎትና ፍቅር የሚያሳይልን ምልክት ነው። ዛሬ ቸርች እንደ ፓስተር ናፍያድ ዓይነት ሰው ባታገኝ ኖሮ ነገ የነ ማንን ታሪክ እንጽፍ ነበር? ነገ የነማንን ገድልና መስዋዕትነት ይተረክ ነበር።

"እግዚአብሔር ሕዝብን ያለ መሪ እንደማያስቀር ያወኩት የፓስተር ናፍያድን አቋምና ብርታት ሳይ ነበር። ወንጌላዊ አብያተ ክርስቲያናት ጀግና፣ ድንቅ፣ ቆራጥ፣ ኢየሱስንና መስቀሉን ትምክህቱ ያደረገ ትውልድ ሊነሳ ግድ ነው። እስዚያ በተንኮልና



CamScanner

በመሸመቅ አገርም ትውልድም አይባረክም።" ቄስ ጉዲና በጣም ወደ እቅፋቸው ሳብ አድርገው ሰንፔርን አቀፏት።

"ሐዘኑ እንዲህ ግብ ግብ ያደረገሽ አባትሽ ስለሆነ ነው። እንደ ቸርች ግን ሰማዕትነቱ ክብርና ደስታ ነው። ምክንያቱም ሌሎች ብዙ ጀግና የወንጌል አርበኞችን እንዲያፈራ ይረዳናል። ስለዚህ መስዋዕትነት ከባድና የሚያም ቢሆንም ከዚያ በኋላ ግን ትልቅ በረከት አለው። ልጄ ይህን የምልሽ በአባትሽ እንድትኮሪ እንጂ እንድታዝኚ አይደለም።" ሰንፔር በአባቷ ሞት ብታዝንም የቄስ ጉዲና ማጽናናት ደስታን ሰጣት።

ሰንፔር ጠልቃ ከሰመጠችበት የሐዘን ባህር የወጣችው ሮዳስ የቄስ ጉዲንና ቤት በስሱ አንኳኩቶ "ሰላም ሰንፔር" ሲላት ነው። ሰንፔር ሮዳስን እዚህ ማየቷ ግርምትን ፈጠረባት። ፍጥጥ ብላ ለሰከንዶች ያህል ታየው ጀመር። ሮዳስም ከአንደበቱ ተጨማሪ ቃላት ማውጣት ተስኖት ፍጥጥ ብሎ ይመለከታት ጀመር።

## ምዕራፍ ፳፯

በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉት ከተሞች አደባባይ ላይ የወጡት ሰዎች ወደ ቤታቸው ሳይመለሱ አደባባዩ ላይ ቀሩ። ጠዋት ከአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ የተነሱት ሰላማዊ ሰልፈኞች ፓትርያርኩን ሲያናግሩ ወደ አራት ኪሎ ሔደው ነበር። ቢሆንም ፓትርያርኩ ሊያነጋግሯቸው ስላልፈለጉ ተወካይ ልከውላቸው ነበር።

ሰልፈኞቹ ግን "ፓትርያርኩ ካልመጡ ማንንም አናናግርም" በማለት ወደ መስቀል አዳባባይ ተመልሰው ቆሙ። ጭራሽ ወደ ቤት አንገባም አሉ። ሰልፉን ላይ ያልነበሩ ሌሎች ሰዎችም ከቤታቸው እየመጡ ሰልፉን እየተቀላቀሉ ነው። ከመንግሥት ባለ ሥልጣናት ሰልፉ በኃይል እንዲበተን ቢታዘዝም ትእዛዙ በትእዛዝ ተሻረ።

ምክንያቱም ሰላማዊ ሰልፉ ሃይማኖታዊ ስለሆነ ወደ ከበደ ግጭት እንዳይቀየር ስለ ተፈራ ውሳኔው በውሳኔ ተቀለበሰ። የኢሕአዴግ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት እርስ በእርሳቸው እየተስማሙ አይደለም። ለሃይማኖታቸው ያደሉ ባለ ሥልጣናት በብዛት ቁጣቸውን እየገለጹ ነው። በሌላ ጽንፍ የተሐድሶው ደጋፊዎች ተሐድሶውን ደግፈው ስብሰባውን አክርረውታል።

ሰላማዊ ሰልፉም አዝማሚያውን እየተቀየረ አንዳንድ ቦታ ግጭት እየወለደ፣ አንዳንድ ቦታ ደግሞ ፖለቲካዊ መልክ እየያዘ ነው። በኢሕአዴግ ሥልጣን ውስጥ ትልቁን የወሳኝነት አቅምና ጉልበት አለው የሚባለው ሕወሐት "እንዴት ተሞክሮ?" በሚሉና "ይህ ክፍፍል ለነገ ይጠቅመናል" በሚሉ ሁለት አንጃዎች ተከፍሏል። ይህ ክፍፍል ሰላማዊ ሰልፉ ተፋፍሞ እንዲቀጥል ጥሩ እድልን ፈጠረ።

የኢሕአዴግ ማዕከላዊ ኮሚቴ ለስብሰባ የተቀመጠው ለድርድር ጥያቄ ቀርቦለት ቢሆንም ከድርድሩ በፊት ግን እርስ በእርሳቸው በጉዳዩ ላይ መስማማት አልቻሉም። የድርድር ጥያቄ የቀረበው በማኅበረ ቅዱሳን ዌብ ሳይት ሲሆን በምስጢር መልእክት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት የተላከው ጥያቄ ይህን ይመስላል።

"አንደኛ መንግሥት ማኅበረ ቅዱሳን ላይ የጣለውን እግድ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲያነሳ፣ ሁለተኛ ፓስተር ናፍያድን ማን እንደ ገደለው እኛ ማስረጃ አለን ስለዚህ የትኛውም የቤተ ክርስቲያን ተቋም በውሸት ክስ ተጠያቂ እንዳይሆን፣ ሦስተኛ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አንድነት እንዳይመለስ የሚደረገውን ጣልቃ ገብነት እንዲቆም፣ አራተኛ አቡነ መርቆሬዎስ ኢትዮጵያ ውስጥ ስላሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ጳጳሳት ጋር አንድነት እንዲመሰረት በሚያደርጉት ጥረት መንግሥት እንቅፋት እንዳይሆን፣ አምስተኛ ተሐድሶ በሚል ክፍፍል ያስነሳችሁትን ቤተ ክርስቲያንን የማዳከም ሴራ እንዲቆም አድርጋችሁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ



CamScanner

ክርስቲያንን ሕጋዊ መብቷን፣ የቀደም ክብሯን፣ ስሟን እና ሙሉ ነጻነቷ ይመለስ" የሚል ነው።

በምትኩም ተደራዳሪው አካል ሊያሟላ ቃል የገባው ነገር አለ። "አንደኛ ሰላማዊ ሰልፉ ምንም ዓይነት ሕገ ወጥነት እንዳይደርስ ጥንቃቄ እናደርጋለን፣ ሁለተኛ መንግሥት እጁን ተጠምዝዞ ሳይሆን በመልካም ፈቃዱ ሰላም እንዲሰፍንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሕልውናን እንዲጠበቅ እንዳደረገ ሰዉ እንዲያምን እናደርጋለን፣ ሦስተኛ የፓስተር ናፍያድን የሞት ምስጢር ማስረጃ እናንተ በምትፈልጉት መንገድ ይገለጻል፣ አራተኛ ከአቡነ መርቆሬዎስ ጋር ሰላም እንዲፈጠር ካደረጋችሁ የአቡነ መርቆሬዎስን ኢትዮጵያ መምጣት የእናንተ መልካም ፈቃድ እንዳለበት እናሳውቃለን፣ አምስተኛ ሁሉ በሰላም ከተጠናቀቀ ሰላማዊ ሰልፍ የወጡት ሰዎች ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን። መልሱን በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ እንጠብቃለን። ጊዚያዊው የሰልፍ አስተባባሪ ኮሚቴ።"

--------//-----

ሮዳስ እና ሰንፔር ቄስ ጉዲና ቁምሳ ፊት ለፊት ጥፋት አጥፍቶ እንደሚመከር ሕፃን ልጅ ጭንቅንቅ ብለው የቄስ ጉዲንና ዝም ያለ ፊት ላይ ዐይናቸውን እያቁለጨለጩ ተቀምጠዋል። ሮዳስን እዚህ አየዋለሁ ብላ ስላልገመተች ሰንፔር በጣም ተገርማለች።

ሮዳስ ደግሞ ሰንፔር እንዴት ልትመጣ እንደቻለች ቀድሞ ተነግሮት ስለነበረ ብዙም አልተገረመም። ይልቁንስ ቄስ ጉዲና የፍቅር ግንኙነታቸውን ሲሰሙ ደስተኛ የሆኑ አልመሰለውም። ፊታቸው ላይ መደሰትም መከፋትም አይታይም። እንዲሁ ለደቂቃዎች ያህል ዝም አሉ። ከዚያም ጉሮሯቸውን እንደመጠራረግ አሉና ንግግራቸውን ቀጠሉ።

"ይኸውላችሁ ልጆች ፍቅር ትልቅ ነገር ነው..." ሮዳስ ድምጻቸውን ሲሰማ ደስ አለው። ከዝምታቸው ይልቅ ድምጻቸው ውስጥ የተሻለ ነገር ሰማ።

"እግዚአብሔር እናንተን በልዩነት አያውቃችሁም፣ እናንተ ሁሌም ልጆቹ ናችሁ። የሞተው ለካቶሊክ ወይም ለኦርቶዶክስ ወይም ለፕሮቴስታንት አይደለም። ጌታ የሞተው ለእኛ ለሁላችን ፍቅርና ድኅነት ሲል ነው። የዚህኛው ሃይማኖት ተከታይ መሆናችሁ በእግዚአብሔር ፊት የተለየ ሞገስ አያሰጣችሁም፣ ማነስም አያመጣም... ነገር ግን እምነትን የሚሰጣችሁ ሃይማኖታችሁ ስለሆነ በዚህ የተነሳ ትለያያላችሁ። ልዩነታችሁ የሃይማኖት ሳይሆን የልብ ይሆናል።

"ትዳር ትዳር የሚሆነው ወንድና ሴት ከራስ ጸጉር እስከ እግር ጥፍር ግጥም ሲሉ፣ ልብና ስሜታቸው ተዋሕዶ እንደ አንድ አካል ሲሆኑ፣ ሁለት የተለያዩ ነገሮች ተዋሕደው አንድነትን ሲሰጡ ነው። ይህን ደግሞ የምናገኘው የመንፈስ አንድነት



CamScanner

ሲኖር ነው። የዚህ አንድነት መሠረት ደግሞ እምነታችሁ ነው። ስለዚህ የሃይማኖታችሁ መለያየት ለነገ ትልቅ ተግዳሮት ያመጣባችኋል።" ሰንፔር ይህን ምክር ስትሰማ መለያየቱ ትክክለኛ ውሳኔ እንደሆነ ተሰማት። በልዩነት መቀጠል የሚባለውን እንደ አማራጭ ብትይዘውም በሮዳስ እና በእሷ ግትር ባህሪ ነገሩ የሚሆን ስላልመሰላት ውሳኔዋን አጸናች። ሮዳስ ደግሞ ጊዜ ሰጥቶ ለመወያየት በውስጡ እያሰበ ነው።

"ልጆች እኔ ይህን እምነት ያዙ፤ ያንን አትያዙ አልልም። ነገር ግን አንድ ሁኑ፤ ተዋሐዱ እላችኋለሁ። ስለዚህ ወደ ትዳር ከመሄዳችሁ በፊት አንድ ሁኑ። ባለማወቅና በግትርነት ፍቅርን አትጡት ይልቁንስ ፍቅር እና እውነት ልባችሁን ይሙላ እንጂ። ይገባኛል የእምነት ነገር በተለይ በፍቅር መሀል፤ በተለይ ለእንደኛ ላለ አገር እና ቤተሰብ ውስጥ ላደገ ከስሜታዊነት ፀድተን፤ ከወገንተኝነት ወጥተን፤ እውነትና እውነትን ይዘን መነጋገር ያዳግታል።

"ነገር ግን ፍቅር የሚያስችላሁ ይህን ነው። መጽሐፍ እንዲህ ይል የለ? 'ድሆችን ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፤ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም። ፍቅር ይታገሳል፣ ቸርነትም ያደርጋል፤ ፍቅር አይመካም፤ አይታበይም፤ የማይገባውን አያደርግም፤ አይበሳጭም፤ በደልን አይቆጥርም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ አመጻ ደስ አይለውም፤ ሁሉን ይታገሳል፤ ሁሉን ያምናል፤ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፤ በሁሉ ይጸናል። ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፤ ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፤ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ፤ እውቀትም ቢሆን ይሻራል።' ይህን ቃል አንደኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ አስራ ሦስት ከቁጥር ሦስት ጀምሮ ታገኙታላችሁ።" ሰንፔር ልቧ መልሶ ሲሰበር ተሰማት። ቆርጣ የነበረው። አልቀጥልም ከእሱ ጋር እያለች ከራሷ ጋር ስትሟገት እንዳልነበረ አሁን ደግሞ በተቃራኒው ጊዜና ልቧን ዳግም ልትሰጥ ፈለገች።

"ልጆች ፍቅራችሁ ከልብ ከሆነ እግዚአብሔር ዝም አይላችሁም። 'ምንም ነገር ይሻራል ፍቅር ግን አይሻራም' የሚለው ቃሉ ነው። ለቃሉ ታማኝ የሆነው ጌታ እናንተን ያያል። ብቻ እናንተ ፍቅራችሁ እውነተኛ እንደሆነ መርምሩ። በሰበብ በአስባቡ ለመለያየት የምታቀብቁቡ ከሆነ መጨረሻችሁ መልካም አይሆንም። መለያየት ብዙ አይነት ነው። ቁርጡ መለያየት ከመምጣቱ በፊት ቀድማችሁ በሃሳብ፣ መንፈስ፣ በአካል፣ በልብ... አትለያዩ። ቀድሞ በሃሳብና በልቡ የተለያየ ሰው የሃይማኖት ልዩነት አይደለም የድምጻችሁ መወፈር ወይም መቅጠን ሊያፋታችሁ ይችላል።

"ስለዚህ ልጆች በመጀመሪያ ፍቅራችሁን ቆሮንቶስ ላይ ባለው ቃል መሠረት አንጹት፤ አንጸነዋል ካላችሁም ግዴለም ደግማችሁ ከልሱት። ከዚያም 'ፍቅር እውነት ነው' ይል የለ? እውነት ደግሞ ነጻ ያወጣችኋል። እውነት ደግሞ ራሱ ጌታችን ነው።



CamScanner

ስለዚህ ፍቅርን ይዛችሁ እውነትን ፈልጉ። እውነትና ፍቅር ደግሞ አንድ ላይ ናቸው። አይነጣጠሉም። ከተነጣጠለባችሁ፤ ከተለያየባችሁ ችግሩ እውነቱ ሳይሆን የእናንተ ፍቅር ነው። ፍቅራችሁ እውነተኛ ነውን? እሱን ሳትዋሹ ለራሳችሁ ጠይቁ? እውነት በሆነው ጌታ ፊት እውነቱን ተናገሩ የእውነት አምላክ በእውነት እንድ ያደርጋችኋል ልጆች!" ሰንፔር ከተቀመጠችበት ተነስታ እያለቀሰች ቁስ ጉዲና አንገት ላይ ተጠመጠመች። ሮዳስ የሚያርገው አጥቶ አይኑ እምባ አቅርሮ ከተቀመጠበት ተነሳ።

--------//------

ጠቅላይ ሚኒስትሩና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከአዳራሹ በስተፊት ለፊት ባለው ወንበራቸው ላይ ተሰይመዋል። አሁን እየተናገሩ ያሉት ከአማራ ክልል ተወክለው የመጡት ሰው ናቸው። ትልቅ መነጽራቸውን ወደ ላይ ገፋ ገፋ እያደረጉ ነው የሚናገሩት "እኔ እምለው እኛ ከምናውቀው ውጪ ሌላ መንግሥት አለ? ይህ ሁሉ በቤተ ክርስቲያኗ ላይ ሲደረግ የት ሔደን ነው? ምንድነው እየሆነ ያለው ነገር?"

ቀጣዩ ቀጭኑና ምሁሩ ሰውዬ መናገር ጀመረ። የዶክትሬት ዲግሪ ያለው ሲሆን በጣም መንፈሳዊና ጭምትነት ስለሚያበዛ ደብተራው እያሉ ያሾፉበታል፤ የሕወሐት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ነው "ትንሽ ሰክዩላሪዝም ለሚለው ጽንስ ሃሳብ ያለንን አተያይ መለስ ብለን ብናየው ደስ ይለኛል። መንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ አይገባም ማለት እንዴት እንደሆነ ብንረዳ። በመጀመሪያ እውነቱን እንነጋገር ከተባለ በሃይማኖቱ ውስጥ አላስፈለጊ ጣልቃ ገብነት እናደርጋለን፤ በዚያው ልክም ለአስፈላጊና ለወሳኝ ነገሮች ቸልተኝነትን ሆን ብለን እናሳያለን። ችግሩን ዐይናችን እያየ ይኸው ልንነካጨው ነው።"

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍንጭት ጥርሳቸውን ብልጭ አድርገው ከደቡብ ክልል ለመጣው ተወካይ እድሉን ሰጡት፤ የደቡብ ክልሉ ሰውዬ በምኞት የደለበ ስንጋ ያስመሰለውን ጫንቃውን አሸት አሸት አደረገና "እኔ ያለኝ ሐሳብ መወቃቀሱን ትተን ወደ መፍትሔው ብንገባ። የድርድር ሐሳብ ቀርቦልናል። እንደኔ ይህን ሐሳብ ሳንቀበል ይልቁንም ችግሩን ባለበት እናስተናግደው። ኦርቶዶክስን ለሁለት ተከፍላለች ስለዚህ ለተከፈሉት ሰዎች ሁሉን ነገር አንድ ሁለት እያልን እናካፍላቸው። ይህን በፌዴሬሽን ጉዳዮች አማካኝነት እንፍታው እላለሁ።" ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፈገግ ብለው አንገታቸውን በአዎንታ ወዘወዙ።

ብዙ እጆች በፍጥነት ከመድረኩ ተነሱ። እስከ አሁን ለኦህዴድ ተወካዮች እድሉ ስላልተሰጠ እድሉ ለኦህዴድ ተሰጠ "አሁን ከመድረኩ የተነሳው ሐሳብ ወደ ለየለት ብጥብጥና መቆሚያ ወደ ሌለው ከንቱ ደም መፋሰስ የሚመራን ነው። ምን ማለት ነው? ለአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመት ራሷን ችላ የኖረች ቤተ ክርስቲያንን ዛሬ ላይ



CamScanner

ደርሰን እንደ አቡጀዴ እናካፍል ስንል አይከብድም? ሕዝቡ እንዲሁም አይወደንም ይብሱን ወደ ከፋ ጥላቻ ውስጥ ገብተን ሳንታረቅ እንለያያለን። ይሔ ደግሞ የሌላ እምነት ተከታዩን ጥልቅ አሳቢ ኢትዮጵያዊ የሚያስከፋና ነግ በእኔ ብሎ ከኦርቶዶክሶች ጋር አንድ ላይ መነሳታቸው አይቀርም።"

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኢሕአዴግ ውስጥ ሀሳብ አመንጪ ለሚባሉት ሰው እድል ሰጡ። እኚህ ሰው ሕዝቡ አብዝቶ ነው የሚጠላቸው። እሳቸውም እንደሚጠላቸው አንጥረው ያውቃሉ። ቢሆንም የቆሙት ለሕዝቡ ሳይሆን ለፓርቲያቸው ስለሆነ ደንታ የላቸውም። ጥቁር ሱፍ በሸሚዝ የለበሱ ሲሆን አፍንጫቸው ላይ የንባብ መነጽራቸውን ሰክተው አንዴ ወረቀቱን፣ አንዴ መድረኩ ላይ የተቀመጡትን ጠቅላይ ሚኒስትሩን እና ምክትላቸውን፣ አንዳንዴ ተሰብሳቢውን ገልመጥ እያደረጉ ማውራት ጀመሩ።

"እኔ እንኳ ያለኝ ሃሳብ ምንድነው? ይህን ችግር ለእኛም ለሌላውም እንዲጠቅም አድርገን እንፍታው ባይ ነኝ። ለተሐድሶዎች 'የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተሐድሶ' ብለው ቤተ ክርስቲያን እንዲከፍቱ እንፍቀድላቸው። ግን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ንብረት ማካፈል አይገባንም። ነገር ግን ትልቅ የኦርቶዶክስ ካቴድራል ቤተ ክርስትያንን የመሰሉ ሕንጻ እንዲገነቡ ከጀርባ እንርዳቸው። ኦርቶዶክስ ተዋሕዶም ሆነ ተሐድሶው ይቀጥል። እመኑኝ የኦርቶዶክሶችን ትምክህት እና እብሪት ቀስ ቀስ እያልን እናበርድላቸዋለን። ተዋሕዶ አክራሪነትና እርጅና ስለሚታይበት ተሐድሶው ወጣቱን ትውልድ ይቆጣጠርልናል። በዚህ አጋጣሚ ተሐድሶውን እኛ እዚህ ስላደረስነው እኛ በፈለግነው መንገድ ውስታ እንዲውልልን እናስገድደዋለን።"

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አሁንም ፈገግ አሉ። ሐሳቡ የተመቻቸው ይመስላል። ከዚህ በላይ ሌላ ሃሳብ ባይቀበሉ ሁሳ ይመኙ ነበሩ።። ግን አይደለም ሌላም ሐሳብ መቀበል ግዴታቸው ነው። ስለዚህ ድጋሚ ከአማራ ክልል ተወካዮች ለተነሳ እጅ እድል ሰጡ "እኔ በአሁኑ ሃሳብ ላይ ቅሬታ አለኝ። ሰዉ ሞኝ አይደለም። በተለይ ወጣቶቹ ማኅበረ ቅዱሳን የሚባለው ማኅበር ዳግም ችግር ይፈጠራል ብሎ ስለሚያስብ ነገሮችን በእንክሮ እንደሚያየው እሙን ነው። ስለዚህ እኛ ሌሎችን በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቁመና የመሰለ ሌላ ቤተ ክርስቲያን እንዲያንጹ ድጋፍ ከሰጠን ዳግም ሕዝቡን ያሳምጽብናል። ከዚያ በኋላ ሰላም የሚባል አናገኝም።"

መሳጣውና ኮስታራው የሕወሐት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባሉ ቀጣዩን ንግግር መናገር ጀመሩ። እኚህ ሰው በሕዝቡ ዘንድ የሚታወቁት በውሸታምነታቸው ነው። ምንም ነገር ቢናገሩ ሕዝቡ አያምናቸውም።

CamScanner

"አንዳንድ ሰዎች ስናወራ የመንግሥትን ሕልውና እየረሳን ይመስለኛል፡፡ ከፈለግን የአሁኑንም ቁጣ በኃይል ጸጥ እናሰኘዋለን፡፡ ይሄ ማነው ማኀበረ ቅዱሳን ምናምን የሚባለው ማን የሆነ ይመስለዋል? እኔማ እሱና ሙስሊም ብራዘርሑድ አንድ ነው የሚመስሉኝ፡፡ ደግሞም ናቸው፡፡ ቀሳውስቱ ራሱ ሲፈሩዋቸው፡፡ በዚያ ላይ 'ነጋሽም ቀዳሽም ከኛው ነው' እያሉ ይዝታሉ አሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ዝም ከተባሉ እንደ ፎከሩት 'ቀዳሽም ነጋሽም ከኛው ነው' የሚለው መፈክራቸውን እውን ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡ ስለዚህ በአጭሩ እንቅጣቸው፡፡ የምን እሹሩሩ ነው፡፡ ለአሁን ይቺን ነገር እስክናልፍ እንደራደር ነገ ግን ከአሸባሪ ጋር አንደራደርም፡፡" የመላጣው ሰውዬ ንግግር ዲፕሎማቲክ ስላልሆነ ጠቅላይ ሚኒትሩ ፊታቸውን ቅጭም በማድረግ ቅሬታቸውን ገለጹ፡፡

## ምዕራፍ ፳፰

### አዲስ አበባ-መስቀል አደባባይ

የከተማው ሰው ንቅል ብሎ የወጣ ነው የሚመስለው፤ መስቀል አደባባይ በአጠቃላይ በሰዎች ተሞልቷል። ብዙዎቹ መሬት ላይ ምንጣፍ አንጥፈው ተኝተዋል። በጧፍና በመንገድ ላይ መብራት ቦታው ድምቅ ብሎ ደመራ መስሏል። ወትሮ የተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ለደመራ የሚሰበሰቡበት መስቀል አደባባይ ዛሬ ማደሪያቸው አድርገውታል።

በቴሌቪዥን እስክሪኑ ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አራተኛ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ መርቆሬዎስ መግለጫ እየሰጡ ነው። ሞተዋል የተባሉት ጳጳስ በዐይን በማየቱ ሰዉ ሁሉ ውስጥ አግራሞትና ድንጋጤ ፈጥሯል። ገሚሱ እያለቀሰ ነው። ገሚሱ እጁን በአፉ ጭኖ በአድናቆት የፓትርያርኩን ንግግር እያዳመጠ ነው፤ አንዳንድ ሰው ግራ ተጋብቷል።

"ሎቱ ስብሐት!" እያለ እጁን ያማትባል። ነጭ ነጠላ መስቀለኛ አጣፍቶ ባዶ እግሩን ያለው ወጣት።

"ዘንድሮ በእኛ የመጣው እግዚአብሔር ይመልሰው" የመዘምራን ልብስ የለበሰችውና እንዳለቀሰች ፊቷ ላይ የሚያሳብቅባት ወጣት ልጅ።

ከሁለት ልጆቻቸው ጋር ሆነው ሰማያዊ የላስቲክ ምንጣፍ ላይ የቆሙት እናት "ወላዲተ አምላክ በአማላጅነቷ ከልጇ ከወዳጇ ታስታርቀን እንጂ እንጃ! እንጃ! ዘንድሮ የእኛን ነገር" ነጭ ሻሻቸውን በአንድ እጃቸው እያስተካከሉ፤ በአንድ እጃቸው ደግሞ መቋሚያቸውን ይዘው።

"በእግዚአብሔር ስም!" ከሥራ መልስ በዚያው ሰልፉን የተቀላቀለችው ልጅ እግር እንስት።

"ጌታ ሆይ አንድ ነገር አድርግ?" እያለች የምታማትበው ዘናጯ ልጅ።

-------//----

### ካሊፎርኒያ-ሎስአንጀለስ

አቡነ ሰላማ በጣም ተቆጥቷል። ውጤቱ እንደ ጠበቀው አልሆነም። በስደተኛው ሲኖዶስ ሥር የነበሩት ምእመናን ኢትዮጵያ ወዳለው ሲኖዶስ መመለስ ጀምረዋል። ይሠራሉ ተብለው የተጠበቁ መምህራን የሚፈለገውን ውጤት አላመጡም።



CamScanner

ክፍሉ ውስጥ አቡነ ሰላማ እና ሩቢዮ ቁጭ ብለዋል፡፡ አቡነ ሰላማ እየተንጎራደደ ነው የሚያወራው፡፡ "ሰዓለም አታሉናል በጣም ነው የተጫወተብን፡፡ የሚገርመው ምንም ሳንጠረጥረው ወደ ኢትዮጵያ መሄዱ ነው፡፡" እጁን እያወናጨፈ ነው የሚያወራው፡፡

"አሁን ይሄ ሳይሆን የሚያሳስበው በስደተኛው ሲኖዶስ ስር የሚተዳደረው ቤተ ክርስቲያን ምእመን ወደ ኢትዮጵያው እየተቀላለቀ ነው፡፡ ዲሲ ያለው ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል፣ እዚሁ ካሊፎርኒያ ያለው ቅድስት ሥላሴ እና ዕርሐ አርያም ዳግማዊት ግሸን ማርያም ቤተ ክርስቲያን በይፋ ወደ ኢትዮጵያው ሲኖዶስ ተቀላቅለዋል፡፡ አሁን የፓትርያርኩን ድምጽ ከሰሙ በኋላ ሙሉ ለሙሉ ይተውናል" አለ ሩቢዮ በመበሳጨት፡፡

"ታውቃለህ ተሸውደናል፡፡ ዝም ሲሉን ያሸነፍናቸው መስሎን ነበር፡፡ ግን ዝምታቸው ውስጥ ተንኮል ነበረው፡፡" አለ አቡነ ሰላማ፡፡

የሩቢዮ ስልክ መጮኽ ጀመረ፡፡ ሩቢዮ ስልኩን አውጥቶ ማየት ጀመረ፡፡ ሩቢዮ የደዋዩን ቁጥር አላወቀውም፡፡ አነሳና "ሔሎ" አለ

ከዚያኛው ጫፍ ቀጠን ያለ የወንድ ድምጽ ተሰማ "ኢንተርኔት ላይ አንተና ኢትዮጵያዊው ጳጳስ ወሲብ ስትፈጽሙ በምስልና ድምጽ ተለቅቋል፤ ብትችል አጥፋው?"

ሩቢዮ ደንግጦና ተናዶ "ሔሎ አንተ ማነህ ምንድነው?" አለ እየተቆጣ፡፡ ቢሆንም ስልኩ ተዘግቷል፡፡

-------//----

### እንግሊዝ-ለንደን

ቶኒ ቢሮው ባለው ኮምፒውተር ላይ አፍጥጦ ማኅበራዊ ድረ ገጽ ላይ የጫነውን የሩቢዮን እና የስደተኛው ሲኖዶስ አምስተኛ ፓትርያርክ የአቡነ ሰላማን የግብረ ሰዶም ቪዲዮ እያየው ነው፡፡ በግማሽ ሰዓት ውስጥ ሁለት መቶ ሺህ ሰዎች ቪዲዮውን ተመልክተውታል፡፡

ስድብና እርግማኑን ከስር የሚጽፈው ሰውም በብዙ ሺዎች እየተቆጠረ ነው፡፡ ይህ በራሱ የተመልካቹን ቁጥር እንዲበዛ አድርጎታል፡፡ ቶኒ ትንሽ ልቡ ቂቤ የጠጣው በዚህ ነው፡፡ ዓላማው ካቶሊክን በሕፃናት ደፈራ እንዳጋለጡት ሁሉ፤ ኦርቶዶክስን ደግሞ ከግብረ ሰዶም ጋር ስሟ እንዲነሳ ማድረግ ነው፡፡

'የኢትዮጵያው ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት የምክክር መድረክ ላይ ሽንጣቸውን ይዘው የተቃወሙትን ግብረ ሰዶም የራሳቸው ፓትርያርክ አድርጎት እንደማየት ምን የሚያስደስት ነገር አለ...' አለና ድምጹን ከፍ አድርጎ ሳቀ፡፡

"አሁን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስን ሳይሆን የዓለም ኦርቶዶክሶችን አንገት የሚያስደፋ ነገር ተደርጓል" አለ ቶኒ ኮራ ብሎ፡፡ "ከዚህ በኋላ በግብረ ሰዶማዊነት አውሮፓ ብቻ ስሟ አይነሳም፤ ካቶሊክና ፕሮቴስታንት ብቻ አይታሙም፤ ኦርቶዶክስም ከመድረኩ ተቀላቅላለች፡፡ እንኳን ደህና መጣሽ ኦርቶዶክስ..." አለ፡፡

------//------

## አሜሪካ ካሊፎርኒያ

መርሐዊ የፓትርያርክ ልብሱን አንድም ሳያስቀር ለብሷል፡፡ አንገቱ ላይ ሦስት አይከን አንጠልጥሏል፡፡ ቆቡን ከጭንቅላቱ በላይ ጭኗል፡፡ ውስጡ የመንፈስ መሰበር ይታይበታል፡፡ ቢሆንም አምርሮ የሚጠላትን ቤተ ክርስቲያን በሞቱም ሊበቀላት ፈልጓል፡፡ አንድ እግሩን ከፍ አድርጎ ከገመዱ ትይዩ ባስቀመጠው ወንበር ላይ አወጣው፡፡

መርሐዊ ግብረ ሰዶማዊነቱን ሙሉ ለሙሉ እንዳልተቀበለው ያወቀው ምስሉን በየድረ ገጹ ተሰራጭቶ በሕዝብ ከታየ በኋላ በተሰማው የኃፍረት ስሜት ነበር፡፡ ከሚኖርበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መውጣት አፈረ፤ ሰው ቀና ብሎ ማየት እንኳ በጣም ተሳቀቀ፡፡

ከዚያም በላይ በመላው አሜሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በሰላማዊ ሰልፍ ውግዘትና ስድብ፤ ንቀትና ጥላቻቸውን ሲያሳዩት... ውስጡ ይህንን መገፋት መቋቋም አልቻለም፡፡ ጉዳዩ በእቅዱ መሰረት ስላልሄደ የሃፍረት ካባ ቢለብስም፤ በሞቱ ዳግም ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን እንደሚያሸማቅቃት ተሰማው፡፡ 'ስለ ቤተክርስቲያናቸው ብለው ለገዳዮች አንገታቸውን ለገመድ የሰጡ ፓትርያርክ እንዳሏት ሁሉ፤ ለክብሩ ለዓላማው ሲልም ራሱን በገመድ ሲል ያደረገ ፓትርያርክ እንዳላት ሊነገር ይገባል' ብሎ ደምድሟል፡፡

መርሐዊ በትረ ሙሴውን ተደገፈና ካንጠለጠለው ገመድ ትይዩ የተቀመጠው ወንበር ላይ በሁለት እግሩ ቆመ፡፡ ወንበሯ ከበድከኝ የሚለውን ሮሮ ማሰማት ጀመረች፡፡ አቡነ ሰላማ የለበሰው ልብሰ ተክህኖ እየተንኮሻኮሸ ድምጽ አሰማ፡፡ "...እኔ አቡነ ሰላም የኢትዮጵያ አምስተኛ ፓትርያርክ..." እያለ አንገቱን ወደ ገመዱ ከተተው፡፡



CamScanner

የገመዱ መቋጠሪያ ዝቅ ዝቅ… እያለ አንገቱን መከርከር ጀመረ። አቡነ ሰላማ ጨከነና የቆመበትን ወንበር ገፈተረው። ዐይኑ ፈጠጠ፣ እግሩ መንፈራገጥ ጀመረ፣ ከዐይኑ እንባው ጠብ ጠብ ማለት ጀመረ፤ በእጁ የያዘውን በትረ ሙሴ ከመዳፉ ወጣና ወለሉ ላይ ወደቀ፤ በትሩ መሬቱ ላይ ሲወድቅ ከመሬቱ ጋር ተጋጭቶ ጩኸት አሰማ። አቡነ ሰላማ ስልል ብሎ የበትሩና የወለሉ መጋጨት ተሰማው። ክፍሉ ከበትሩ ጩኸት ቀጥሎ ከመርሐዊ በሚወጣው አይነ ምድር ሽታ ተበከለ።

## ከሁሉ በኋላ

የደቂቀ እስጢፋኖስ አባላት እንዳሰቡት ስላልተሳካላቸው ተስፋ አልቆረጡም። ከሚደግፏቸው የመንግሥት ባለ ሥልጣናት ጋር መክረው ሌላ መርሐ ግብር ነድፈው እየተንቀሳቀሱ ነው። "ተሐድሶ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን" የሚል ከፍተዋል።

ግሩም ቦሌ መድኃኔዓለም አካባቢ ካለ ውድ ሕንጻ ተከራይቶ "የቦሌ አጥቢያ ተሐድሶ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን" የሚል ከፍቷል። ሔራም ደግሞ "የመካኒሳ አጥቢያ ተሐድሶ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን" የሚል ከፍቷል። ትርሲት ደግሞ ብስራት ገብርኤል አካባቢ የብስራተ ገብርኤል አጥቢያ "ተሐድሶ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ብስራተ ገብርኤል አጥቢያ" በሚል ከፍታለች።

በክርስቶስ ተሐድሶ ስም በየአካባቢው ሌሎች ቤተ ክርስቲያኖች ለመክፈት እቅድ ላይ ናቸው። 'የክርስቶስ ተሐድሶ ቤተ ክርስቲያን' አስተምህሮ ከኦርቶዶክስ እና ከፕሮቴስታንት አስተምህሮ የተቀላቀለ ነው። ስለዚህ የተቀላቀለውን አስተምህሮ የሚደግፉ ምእመናን ከኦርቶዶክስም ከሌሎች ወንጌላዊ አብያተ ቤተ ክርስቲያናት እየለቀቁ እነሱን የሚቀላቀሉ ናቸው።

-------//-------

የተሐድሶው እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ነገር ነው ይዞላት የመጣው። አንደኛው ከአገር ውጪና አገር ውስጥ ያለ ሲኖዶስ የሚለው ክፍፍል ቀርቶ ቤተ ክርስቲያኗ ማዕከላዊ አሠራሯ ተመልሶላታል። ብዙ ወጣቶች ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን በፍቅር ለማገልገል ከቀድሞ ይልቅ ወደ ቤተ ክርስቲያኗ መጉረፍ ጀምረዋል።

ያመጣበት አሉታዊ ተፅእኖ ደግሞ ግብረ ሰዶማዊና ራሱን ያጠፋ ፓትርያርክ ነበራት ተብሏል። ይህ ታሪክ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ ላሉ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የታሪክ እድፍ ሆኖ ይቆጠራል። ሌላው የደቂቀ እስጢፋኖስ አባላትን ተከትለው የወጡ ሰዎች ቁጥር ቀላል አይደለም። በምእመኑ ዘንድም መሳቀቅና ነገ ምን ይመጣብን ብሎ ፍርሃትና መሸማቀቅ ውስጥ ገብቷል።

-------//----

የፊስአልጎስ ሕቡዕ ድርጅት የተሐድሶ እንቅስቃሴ ዳግም እንዳይነሳ በማለት ለአራት ቀን ሰፊ ውይይት አድርጓል። በዚህ ውይይት ውስጥ የተነሱ ነጥቦች በጥብቅ ምስጢር በሰባ አራት ሉክ ታትመውና ተጠርዘው ተፈጻሚነቱ ለሚመለከታቸው



CamScanner

ሰዎች ሁሉ ተልኳል፡፡ ጥራዙ "ዘመቻ አላቲኖስ" ይላል፡፡ ትርጉሙ "የእውነትና ንጹህ ዘመቻ" እንደ ማለት ነው፡፡

ከጥራዙ ውስጥ አንኳር ነጥቦቹ የሚመለከቱት ሲሆኑ የተቀሩት ግን ዝርዝር ተግባራት ናቸው፡፡

1ኛ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮችን የቤተ ክርስቲያኗን ዶግማ እና ቀኖና በትክክል ለሕዝቡ ለማሳወቅ ያለሳለሰ ጥረት ማድረግ፡፡

2ኛ. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተንሰራፋውን ዘረኝነት እና ሙስና ዳግም እንዳይመለስ አድርጎ ለማጥፋት በቁርጠኝነት መታገል፡፡

3ኛ. በተለያዩ መገናኛ ብዙኃንና በተለያዩ ቋንቋዎች የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከወንጌላዊ አብያተ ክርስቲያናት ጋር በምን በምን እንደምትለያይ በግልጽና በአጭር ቋንቋ መግለጽ፡፡

4ኛ. ወንጌላዊ አብያተ ክርስቲያናት በአጠቃላይ ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን ወደ ራሳቸው እንዲመለከቱ 'ተሐድሶ ለወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት' የሚል አጀንዳ ማንሳት፡፡ እነዚህንም አጀንዳዎች የተለያዩ መገናኛ ብዙኃን በመጠቀም በኅብረተሰቡ ውስጥ ማስረጽ፡፡

5ኛ. ወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ በአጠቃላይ ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት እንዲቀጣጠል ማድረግ፡፡

6ኛ. ወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ አሠራርና አንድ ወጥ አመራር እንዲኖራቸው ማድረግ፡፡

7ኛ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ ቀደመ ጊዜ ከወንጌላዊ አብያተ ክርስቲያናት የሚነሱትን መንፈሳዊ ጥያቄዎችን መመለስ ሳይሆን ሥርዓት፣ ምግባር እንዲሁም አግባብነት ያላቸውን ጥያቄዎች በአፋጣኝ እና ያለማቋረጥ ለወንጌላዊ አብያተ ክርስቲያናት ማንሳት፡፡

8ኛ. ምንም አይነት ከኢትዮጵያ ውጪ ያሉ የፋይናንስም ሆነ የቁሳቁስ ድጎማዎችና ተፅእኖዎችን በወንጌላዊ አብያተ ክርስቲያናት ላይ እንዳይኖር መከላከል፡፡

9ኛ. በምእመናን መካከል መናናቅ ሳይሆን መከባበርን እንዲኖር የማንኛውንም እምነት ተከታይ በፍቅር እና በአክብሮት መመልከት፤ እምነቱን እንዲያውቅ መርዳት እንጂ ማጥላላት፣ መሰለል፣ ማደራጀት፣ ማሳደም... እንዳይኖር ተግቶ መሥራት፡፡



CamScanner



ቃልኪዳን ኃይሉ አዲስ አበባ ከተማ ተወልዶ ያደገ ሲሆን፣ በማኅበረሰብ ሳይንስ (Public Health) ከደብረ ብርሃን ዩንቨርስቲ የመጀመሪያ ዲግሪውን አግኝቷል:: ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በጋዜጠኝነት (Journalism and Comunication) የማስተርስ ዲግሪውን ይዟል:: በ2006 ዓ.ም "የነገድጓድ ልጆች" የተባለ የበኩር ሥራውን ያስነበበን ሲሆን፣ በ2007 ዓ.ም "ለምን አትቆጣም- (ያ ትውልድ Vs ይህ ትውልድ)" የሚለውን የአጫጭር ልብ ወለዶችና የወግ ስብስቦችን አስነብቦናል:: በ2010 ዓ.ም አላቲኖስ የተባለ ረዥም ልብ ወለዱን አሳትሟል:: በ2013 ዓ.ም ክብር የተሰኘ ልብወለድም አሳትሟል። በተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማም "ዳና" በተሰኘ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ ላይ ምዕራፍ አራት ላይ አምስት ክፍሎችን በመጻፈ አሀዱ ያለውን የተከታታይ ድራማ ጽሁፍ "ወላፈን" በተባለ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ ላይ ከምዕራፍ አራት ጀምሮ እስከ ፍጻሜው ድረስ ሃምሳ አራት ክፍሎችን በመጻፍ ገፍቶበታል::


ደራሲዎች፡ ሙዚቀኞችና፡ ሌሎች፡ የኪነ፡ ጥበብ፡ ባለሙያዎች፡ እነዚህን፡ ርእስ፡ ጉዳዮች፡ ለመድፈር፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ ሲቸገሩ፡ እናያለን። በ"ሃይማኖት"፡ ስም፡ አገርን፡ የሚጎዱና፡ አንድነትን፡ የሚያናጉ፡ አመለካከቶች፡ እየተበራከቱ፡ ሲመጡ፡ ጉዳዩን፡ በቀጥታ፡ አንስተው፡ ትውልድን፡ የመታደግ፡ ሥራ አንዳይሠሩ፤ የሰዎችን "የሃይማኖት ነጻነት" የሚነኩ እየመሰላቸው፡ ዳር፡ ዳሩን፡ ብቻ፡ ሲዞሩ፤ የምናስተውለው ነገር ነው:: ምናልባት፡ በጉዳዩ፡ ላይ፡ ከማናችንም፡ የተሻለ፡ ግንዛቤ፡ ቢኖራቸው፡ እንኳ፡ የአገሪቱን፡ የፖለቲካና፡ የሃይማኖት፡ ግጭት፡ እሳት፡ የበለጠ፡ እንዳያጋግሉት፡ በመፍራት፡ ከርእሱ ወደኋላ ያፈገፍጋሉ። ፍርሗታቸው፡ አንዳንድ፡ ጊዜ፡ ትክክል፡ ቢኾንም፡ አንዳንድ፡ ጊዜ፡ ግን፡ አይደለም። ስለአገር፡ ጉዳይ፡ በይፋ መልእክት፡ የሚያስተላልፉ፡ የኪነ፡ ጥበብ፡ ባለሙያዎች፡ የመኖራቸውን፡ ያኽል፡ ከርሱ፡ ተነጥሎ፡ ሊታይ፡ ስለማይችለው፡ ስለሃይማኖት፡ ግን፡ በቀጥታ፡ የሚያነሱ፡ ብዙ፡ አይደሉም።

ደራሲ፡ ቃልኪዳን፡ ኃይሉ፡ የኢትዮጵያዊነትና፡ የተዋሕዶ፡ ሃይማኖትን፡ ዕጣ፡ ፈንታ፡ በዚህ፡ ልብወለድ፡ ውስጥ፡ ፍርጥርጥ፡ አድርጎ፡ ጽፎታል ! ይህ፡ "አላቲኖስ"፡ የተሰኘ፡ ልብወለድ፡ የወቅቱን፡ የአገራችንን፡ መንፈሳዊና፡ ፖለቲካዊ፡ ቀውስ፡ በዋናነት፡ በክርስትና፡ ሃይማኖት፡ ውስጥ፡ ያለውን፡ መከፋፈል፡ በሚመረምር፡ መነጽር፡ የተጻፈ፡ ድርሰት ነው። ልብወለዱን፡ "ልብወለድ"፡ እንበለው፡ እንጂ፡ የሚወከለው፡ የገሃዱን፡ ዓለም፡ ግለሰቦች፡ ማኅበራትና፡ ተቋማት፡ ነው። አንዳንዶቹ፡ በቀጥታ፡ የተጠቀሱ፡ ሲኾኑ፡ የሌሎቹን፡ ማንነት፡ ደግሞ፡ ከገጸ፡ ባሕርያቱ፡ መገመት፡ አይከብድም። በድርሰቱ፡ ውስጥ፡ የደራሲው፡ አቋም፡ ከገጸ፡ ባሕርያቱ፡ ግልጽ፡ ቢኾንም፡ ጥሩ፡ የኾነ፡ ሚዛናዊነትና፡ መልካም፡ የስምምነት፡ ተስፋም፡ ይታይበታል። ቃልኪዳን፡ የኢትዮጵያ፡ ቤተክርስቲያን፡ ከሌሎች፡ አብያተ፡ አምነቶች፡ ጋር፡ የገባችበትን፡ የወቅቱን፡ ፍትጊያ፡ በተለይ፡ "ተሃድሶ"፡ ስለሚባለው፡ የእምነት፡ አቋሟንና፡ የኢትዮጵያዊነት፡ መሠረት፡ ያደረጓትን፡ እውነታዎች፡ የመሸርሸር፡ እንቅስቃሴ፡ በሚገባና፡ በቀላል፡ አተራረክ፡ ለአንባቢው፡ ያሳየበት፡ የተዋጣለት፡ ሥራ፡ ነው።


አላቲኖስ ይቀጥላል !

ዶክተር መስከረም ለቺሳ (ደራሲ)

በባህር ዳር ዩንቨርስቲ የትምህርትና የሥነ ባህሪ ኮሌጅ ረዳት ፕሮፌሰር









ዋጋ 253.00 ብር
$20

CamScanner